እንቅልፍ፡ለምን።

ሦስተኛ ፡ እትም ፤

ከብላቴን ፡ ጌታ ፡ ማኅተመ ፡ ሥላሴ ፡ ወ ፡ መ ፡
ተዘጋጀ ።

ተንትመ ፡ ገዝቱ ፡ መጽሐፍ ፡ በቫወፂ ፡ ዘመን ፡ መንግሥቱ ፡


ስቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

አዲስ ፡ አበባ ፡ ሐምሌ ፡ ፲፯ ፍቀን ፡ ፲፱፻፷፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ም ፡

በአርቲስቲክ ፡ ማ ተ ሚ ያ ፡ በ[illegible] ተ መ ።

398
ማ
1ኛ፡ቅ.





ያለደራሲው ፣ ፈቃድ ፣ መልሶ ፣ ማተም ፣
ክልክል ፣ ነው ።
All Right reserved



ግርማዊ ፣ ቀዳማዊ ፣ ኃይለ ፣ ሥላሴ ፣
ንጉሠ ፣ ነገሥት ፣ ዘኢትዮጵያ ።

መግቢያ ።

ያንድ ፡ አገር ፡ ታሪክ ፡ የሚታወቀው ፡ በሕንጻዎቹና ፡ በሐውልቶቹ ፡ በጽሑፎቹና ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ የኪነ ፡ ጥበብ ፡ ሥራዎቹ ፡ ሌላም ፡ እንዲሁም ፡ እነዚህን ፡ በመሳሰሉት ፡ ሁሉ ፡ መሆኑ ፡ ግልጥ ፡ ነው ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ በጽሑፍም ፡ ባይሆን ፡ ከባት ፡ ለልጅ ፡ ሲወራረሱ ፡ የመጡት ፡ በምሳሌ ፡ እንደ ፡ ወግ ፡ ልማድ ፡ እድር ፡ በህል ፡ እንደነዚህም ፡ ያሉት ፡ ሁሉ ፡ ሲመረመሩ ፡ ያንድን ፡ አገር ፡ ታሪክና ፡ ሥልጣኔ ፡ ለመግለጥ ፡ ምክንያት ፡ ከሚሆኑት ፡ ከሐውልቶችና ፡ ከእጅ ፡ ብልኅት ፡ ሥራዎች ፡ ጋራ ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ ሆነው ፡ የሚገመቱ ፡ አስረጂዎች ፡ ሆነው ፡ ይገኛሉ ።

ታሪክ ፡ እንደሚነግረን ፡ አገራችን ፡ ኢትዮጵያ ፡ በቀደምትነት ፡ ከሚታወቁት ፡ አገሮች ፡ አንዷ ፡ ናት ። በመንግሥትነትም ፡ መታወቅ ፡ የገዦመረችበት ፡ ዘመን ፡ ሲቈጠር ፡ ከጌታ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ፲፭፻ ፡ ዓመት ፡ ታመጣለች ። የነገሥታቱም ፡ ቍጥር ፡ ከቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ እስከ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ፻፶፰ ፡ ሆኗል ። ይኸውም ፡ ከቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ በፊት ፡ ያለው ፡ ቀርቶ ፡ ነው ።

ኢትዮጵያም ፡ ገና ፡ ስትወጠን ፡ ገዦምራ ፡ ትውልዱንና ፡ ግዛቷን ፡ ለማስፋፋት ፡ የአእምሮና ፡ የዕውቀት ፡ መንፈሷን ፡ ለማደርጀት ፡ የበዘነችበት ፡ ጊዜ ፡ እንዳልነበረ ፡ በየመጻሕፍቱ ፡ ተነግሯል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ በየዘመኑ ፡ ከውስጥም ፡ ሆነ ፡ ከውጭ ፡ በሚደርስባት ፡ ሁከት ፡ (ጦርነት) ፡ ምክንያት ፡ እንዳሰበችውና ፡ እንደ ፡ ተመኘችው ፡ ሥልጣኔና ፡ ኀይል ፡ ልታገኝ ፡ አልቻለችም ፡ ነበር ።

እንዲህም ፡ ስለ ፡ ተባለ ፡ የሽግግሯቷና ፡ ያዋቆቿ ፡ የመንፈስ ፡ ብርታት ፡ ጋሻና ፡ መከታ ፡ ሆኗት ፡ ሥልጣኔዋ ፡ ፈጽሞ ፡ ሳይደመሰስ ፡ ከባት ፡ ለልጅ ፡ እየተላለፈ ፡ እስካለንበት ፡ ጊዜ ፡ ሊደርስ ፡ ችሏል ።

ምንም ፡ እንኳ ፡ እንደ ፡ ዘመኑ ፡ ክዛትና ፡ እንዳገሪቱም ፡ ጥንታዊትነት ፡ መጠን ፡ ለሥልጣኔዋ ፡ ማስረጃ ፡ የሚሆኑት ፡ ሐውልቶችና ፡ ሕንጻዎች ፡ በብዛት ፡ ባይገኙ ፡ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ እስከ ፡ ዛሬው ፡ ትውልድ ፡ የደረሰው ፡ የአእምሮ ፡ እድገት ፡ ሲመረመር ፡ ምን ፡ ያኽል ፡ የበሰለ ፡ አስተያየት ፡ ያላቸው ፡ ሽግግሎችና ፡ ዐዋቆች ፡ እንደ ፡ ነበሩት ፡ አውንም ፡ እንዳሏት ፡ ያስ

ረዳል። ሕዝቡም ፣ አስተዋይነትና ፣ አመዛዘኝነት ፣ ከተፈጥሮው ፣ የታደለ ፣ ስለ ሆነ ፣ የተማረው ፣ ቀርቶ ፣ ንባብና ፣ ጽሕፈት ፣ እንኳ ፣ የማያውቀው ፣ ባስተ ዳደርና ፣ በዳኝነትም ፣ ላይ ፣ የሚያደርጋቸው ፣ ትችቶችና ፣ አስተያየቶች ፣ እን ዲሁም ፣ ደስታውንም ፣ ሆነ ፣ ሐዘኑን ፣ የሚገልጥባቸው ፣ ያማርኛዎቹ ፣ መር ቀቅና ፣ ጥልቅ ፣ መሆን ፣ በእውነቱ ፣ ከፍ ፣ ያለ ፣ ያዋቂነት ፣ ግምት ፣ የሚያ ሰጠው ፣ ነው ። ።

ይህ ፣ ሁሉ ፣ ለተመለከተውና ፣ አርቆም ፣ ላስተዋለው ፣ አላፊውን ፣ ጊዜ ፣ እንደ ፣ ፎቶግራፍ ፣ ወይም ፣ መስተዋት ፣ ገልጦና ፣ አጣርቶ ፣ ያበቶቻ ችንን ፣ ችሎታና ፣ ዝና ፣ የሚያሳይ ፣ ነው ። ።

ብዙ ፣ የውጭ ፣ አገር ፣ ሰዎች ፣ ኢትዮጵያን ፣ እየተዘዋወሩ ፣ በመጐብ ኘት ፣ በየጊዜው ፣ የመሰላቸውን ፣ ጽፈዋል ፤ ይኸውም ፣ በወይን ፣ የሚታየ ውን ፣ ይህም ፣ በይሆን ፣ በቋንቋ ፣ ችግር ፣ ምክንያት ፣ ሁኔታውን ፣ ጠንቅቆ ፣ ለመረዳት ፣ በማያስችል ፣ ባስተርጓሚ ፣ እርዳታ ፣ ስለ ፣ ሆነ ፤ አንዳንድ ፣ ጊዜ ፣ ትክክለኛውንና ፣ እውነተኛውን ፣ ጽፈዋል ፣ ለማለት ፣ ሕምብዛም ፣ አያስ ደፍርም ። ።

በእውነትም ፣ ቅኔዎቻችንን ፣ አማርኛ ፣ አነጋገራችንን ፣ ምሳሌዎቻች ንን ፣ (ተረቶችን) ፣ ለመረዳትና ፣ ለማስረዳት ፣ ግእዝንም ፣ ሆነ ፣ አማርኛን ፣ አጣርቶ ፣ ማወቅ ፣ ያስፈልጋል ። ያለዚያ ፣ ከነወዙ ፤ ከነለዛው ፤ ከነጣዕሙ ፣ ለመተርጐም ፣ ይቅርና ፣ ለመረዳት ፣ እንኳ ፣ አስቸጋሪ ፣ እንደሚሆን ፣ ግልጥ ፣ ነው ። ።

ስለዚህም ፣ እኛ ፣ ኢትዮጵያውያን ፣ አገራችን ፣ ጥንታዊት ፣ መሆኗን ፣ ሥልጣኔንም ፣ በመሸተ ፣ ዐዋቆችና ፣ አስተዋዮች ፣ አባቶቻችን ፣ በብዙ ፣ የደከሙ ፣ መሆናቸውን ፣ በመገንዘብ ፣ ላገራችን ፣ ወጣቶችም ፣ ሆነ ፣ ወይም ፣ ለውጭ ፣ አገር ፣ ሰዎች ፣ እውነተኛውንና ፣ ምስክርም ፣ ሊሆን ፣ የሚ ገባውን ፣ ሁሉ ፣ አየሰበሰብን ፣ ማዘጋጀት ፤ ለመጭውም ፣ ትውልድ ፣ እን ዲተላለፍ ፣ ማድረግ ፣ አለብን ። ።

ከዚህ ፣ በፊት ፣ ይህንኑ ፣ መሠረት ፣ በማድረግ ፣ እኔ ፣ በበኩሌ ፣ የኢ ትዮጵያን ፣ የሥልጣኔ ፣ ሥራዎች ፣ ለመግለጥ ፣ ስል ፣ «ዝክረ ፣ ነገር» ፣ «ያባ ቶች ፣ ቅርስ» ፣ «አማርኛ ፣ ቅኔ» ፣ የተባሉ ፣ መጻሕፍት ፣ አዘጋጅቼ ፣ ስለ ፣ ታተሙ ፣ ይኸው ፣ ዛሬ ፣ በትምህርት ፣ ገበታ ፣ ላይ ፣ የሚገኙትና ፣ ሌሎችም ፣ ያገራችንን ፣ ታሪክ ፣ ለመረዳት ፣ የሚሹ ፣ ሁሉ ፣ ሲያነቧቸውና ፣ ሲጠቀሙ በቸው ፣ ይታያል ። ።

አሁን ፣ ደግሞ ፣ በዚህ ፣ «እንቅልፍ ፣ ለምኔ» ፣ ተብሎ ፣ ቤተሰየመው ፣ መጽሐፍ ፣ አባቶቻችን ፣ በጠለቀ ፣ አስተያየታቸው ፣ ሕፃናቱ ፣ ሳይሰለቹ ፣ በመ ደሰት ፣ የግብረ ፣ ገብነትና ፣ የመመራመር ፣ (ፈሎዞፊ) ፣ ትምህርት ፣ ገና ፣ ከልጅነታቸው ፣ ዝምሮ ፣ እንዲዋሐዳቸው ፣ ለማድረግ ፣ ከፍ ፣ ባለ ፣ ፊሊጥ ፣ ያደራጁዋቸውን ፣ ተረቶች ፣ ወይም ፣ ምሳሌዎች ፣ ሰብስቤ ፣ አቅርቢያለሁ ። ።

ይህ ፣ መጽሐፍ ፣ ምንም ፣ እንደ ፣ ቢልት ፣ አነጋገር ፣ ቢጻፍ ፣ መነሻና ፣ መድረሻ ፣ ያለው ፣ አንዳንድ ፣ መ-ሉ ፣ ታሪክ ፣ የያዘ ፣ ነው ። ሕፃናቱም ፣ ሳይሰለቹ ፣ ማንበብ ፣ እንዲደፍሩ ፣ ከግቡም ፣ ሳይደርሱ ፣ እንዳያርፉ ፣ በማ ሰብ ፣ የተቻለኝን ፣ ያክል ፣ ባቀራረቡ ፣ ላይ ፣ ደክሜበታለሁ ። ።

ያገራችን ፣ ሽማግሌችና ፣ ባልቴቶች ፣ ለሕፃናት ፣ ማታ ፣ ማታ ፣ አስደ ሳች ፣ የሆነ ፣ እንደ ፣ እንቆቅልሽ ፣ ተረት ፣ ያሉትን ፣ ማውጋት ፣ ልማዳ ቸው ፣ ነው ፤ ስለዚህም ፣ የያንዳንዱን ፣ ታሪክ ፣ ከሥር ፣ ዝምረው ፣ በፈገ ግታና ፣ ደስ ፣ በሚያሰኝ ፣ አነጋገር ፣ ሲተርኩ ፣ ይታያሉ ። ።

ሕፃናቱም ፣ ከዚህ ፣ የተነሣ ፣ መንፈሳቸውን ፣ የሚያስደስትና ፣ እአ ምሯቸውን ፣ የሚቀሰቅስ ፣ ነገር ፣ ስለሚያገኙበት ፣ ከሌላው ፣ ጨዋታ ፣ ይልቅ ፣ ሽማግሌቹን ፣ ከበው ፣ እንደ ፣ ማርና ፣ ወተት ፣ የጣፈጠ ፣ ምክራ ቸውን ፣ ለመቀበልና ፣ ለመስማት ፣ የተዘጋጁ ፣ ሆነው ፣ ይገኛሉ ። የሰሙት ንም ፣ በሙሉ ፣ ልባቸው ፣ ስለሚቀበሉት ፣ በጠየቋቸው ፣ ጊዜ ፣ ያላንድ ፣ ችግር ፣ ያዳመጡትን ፣ ከዳር ፣ እዳር ፣ ይወጡታል ። ።

እኔም ፣ ምንም ፣ ከዛሬ ፣ ፵፭ ፣ ዓመት ፣ በፊት ፣ የሰማሁት ፣ ቢሆን ፣ ይኸው ፣ ዛሬ ፣ አንዳንዱን ፣ ከሞላ ፣ ጐደሉን ፣ ለማስታወስና ፣ ለመጻፍ ፣ ችያለሁ ። ይህንንም ፣ መጽሐፍ ፣ እንቅልፍ ፣ ለምኔ ፣ ብዬ ፣ ሰይሜዋለሁ ። እንዲህም ፣ ለማለት ፣ ያሰበኝ ፣ ሕፃናቱ ፣ ወይም ፣ ወጣቶቹ ፣ ከጨዋታ ፣ መርጠው ፣ ከእኽልና ፣ ከውሃም ፣ አብልጠው ፣ እንቅልፍ ፣ ሳያምራቸው ፣ ለመኝታም ፣ ሳይጓጉ ፣ ተረት ፣ ለመስማት ፣ ያላቸውን ፣ ፍላጎት ፣ በመመል ከት ፣ ነው ። ።

መጽሐፉንም ፣ ሳዘጋጅ ፣ የተቻለኝን ፣ ያክል ፣ ሐሳቡ ፣ የተያያዘ ፣ ማሰ ሪያም ፣ ያለው ፣ እንዲሆን ፣ ተጣቅሪያለሁ ። ።

ከዚህም ፣ ሌላ ፣ የሕፃናቱን ፣ መንፈስ ፣ ለመሰብና ፣ ለመሰብሰብ ፣ መጽ ሐፉ ፣ የሚያሰለች ፣ እንዳይሆን ፣ አስፈላጊ ፣ መስሎ ፣ በታየኝ ፣ ቦታ ፣ ላይ ፣ ለታሪኩ ፣ ተስማሚ ፣ የሆኑትን ፣ ሥዕሎች ፣ አልፎ ፣ አልፎ ፣ አግብቻለሁ ። ።

በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ወጣቶቹ ፡ ጽሑፉ ፡ በእጃቸው ፡ ሲገባ ፡ የያንዳ
ንዱን ፡ ሥዕል ፡ ታሪክ ፡ ለመረዳት ፡ በከፊል ፡ ወይም ፡ በሙሉ ፡ ከላነበቡ
ትና ፡ ከልተገነዘቡት ፡ መንፈሳቸው ፡ እንደማያርፍ ፡ አምናለሁ ።

ይህም ፡ ሲሆን ፡ መጽሐፉን ፡ ለማንበብ ፡ ስለማይበገሱ ፡ ንባብ ፡ ከመ
ማራቸውም ፡ በላይ ፡ ፍሬ ፡ ነገሩን ፡ በማስተዋል ፡ ለመረዳት ፡ ቻሉ ፡ ማለት ፡
ነው ።

በመጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ ተረቶች ፡ ቁጥራቸው አነስተኛ ፡
ቢሆንም ፡ ባገራችን ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ታሪክና ፡ ምሳሌ ፡ በብዛት ፡
ስለሚገኝ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ የሚያዘጋጁት ፡ ሰዎች ፡ የኮይለውን ፡ በመሰብሰብ ፡
የተሻላ ፡ እንደሚያደርጉት ፡ አምናለሁ ።

በዚህ ፡ ዐይነት ፡ መንፈስ ፡ ተመርተው ፡ ካሁን ፡ በፊት ፡ ያበቶቻች
ንን ፡ ዝና ፡ የሚያስነሣ ፡ አንዳንድ ፡ መጽሐፍ ፡ ለጻፉ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ምስ
ጋና ፡ ሳላደርግላቸው ፡ አላልፍም ። ምንም ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ቀጥረቸው ፡
የበዛ ፡ ዐይነታቸው ፡ የተለያየ ፡ ምስጢራቸው ፡ የዘለቀና ፡ የጠለቀ ፡ ተረ
ቶች ፡ ከታላላቅ ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ ሊቆችና ፡ ዐዋቆች ፡ የተደረሱ ፡ መኖራቸ
ውን ፡ በውቅ ፡ ይህንን ፡ መጽሐፍ ፡ በማዘጋጀቴ ፡ የሚሰማኝን ፡ ደስታ ፡
ከፍ ፡ አድርጌ ፡ የምመለከተው ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ የሆነውን ፡ ያበቶች ፡ ተረት ፡
ሰብስቤ ፡ ለዛሬዎቹ ፡ ሕፃናት ፡ ለነገዎቹ ፡ ወጣቶች ፡ ማስታወሻ ፡ እንዲሆና
ቸው ፡ በማበርከቴ ፡ ነው ።

ከቦር ፡ የትምህርትና ፡ ሥነ ፡ ጥበብ ፡ ሚኒስቴርም ፡ ጠቃሚነቱን ፡ በመ
ረዳት ፡ መጽሐፉ ፡ በቶሎ ፡ ታትሞ ፡ እሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ በማድረጉ ፡
ከፍ ፡ ያለ ፡ ምስጋና ፡ አቀርብለታለሁ ።

በላምባራስ ፡ ማኅተመ ፡ ሥላሴ ፡ ወልደ ፡ መስቀል ።

ስንገሮ ።

አንዲት ፡ ድኻ ፡ ሰት ፡ ስድስት ፡ ወንድ ፡ ልጆች ፡ ወልዳ ፡ በብዙ ፡
ድክም ፡ እየለመነችና ፡ የሞያተኛ ፡ እየሠራች ፡ በምታገኘው ፡ ገንዘብ ፡
አሳደገቻቸው ። እነሱ ፡ ግን ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ የሌላቸውና ፡ ሀኬት ፡ የበዛባ
ቸው ፡ ሆኑ ። አድገውም ፡ ለሥራ ፡ ስለ ፡ ደረሱ ፡ አርሰውና ፡ ቄፍረው ፡
ከችግር ፡ ያድኑኛል ፡ በማለት ፡ በእርሻ ፡ ሰዓት ፡ ሰው ፡ ሲዘራ ፡ አይታ ፡
አሷም ፡ ስንዴ ፡ ባቄላ ፡ ዐተርና ፡ ልዮ ፡ ልዩ ፡ የአኽል ፡ ዐይነት ፡ ከባለጸጋ ፡
ተበድራ ፡ አምጥታ ፡ «በሉ ፡ እናንተም ፡ እንደ ፡ ሰዎቹ ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡
እረሱና ፡ ዝሩ» ብላ ፡ ዘሩን ፡ ሰጠቻቸው ። እነሱ ፡ ግን ፡ የተቀበሉትን ፡
እኽል ፡ እየቄሉ ፡ ይበሉና ፡ የማታ ፡ ማታ ፡ እግራቸውን ፡ ጭቃ ፡ ቀብተው ፡
አምዬ ፡ ቀፋፎው ፡ ገደለን ፡ አገር ፡ ምድሩን ፡ ዘርተነው ፡ ዋልን ፡ እያሉ ፡
ለናታቸው ፡ ሐሰት ፡ ወሬ ፡ ይነግሯታል ።

እሷም ፡ ሳትጠራጠር ፡ እውነት ፡ በሥራ ፡ የዋሉ ፡ እየመሰላት ፡ ልጆቼ ፡
ተገዳብኝ ፡ በማለት ፡ ማታ ፡ ማታ ፡ ለእግራቸው ፡ ውሃ ፡ በኑስኑስት ፡
አመቃ ፡ እንዲታጠቡ ፡ ትሰጣቸዋለች ። የሚተኙበትንም ፡ ቄጥ ፡ እሷው ፡
ራሷ ፡ ታነጥፍላቸዋለች ።

በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ሲያታልሏት ፡ ከቄዩ ፡ በኋላ ፡ የዘሩ ፡ ወቅት ፡ አልፎ ፡
የሸት ፡ ወራት ፡ ሲደርስ ፡ የየሰዎቹ ፡ ልጆች ፡ ለወላጆቻቸው ፡ እሸት ፡ ሲያ
መጡላቸው ፡ አይታ ፡ እኔም ፡ አምሮኛል ፡ ምነው ፡ ከእርሻችሁ ፡ ብታመ
ጡልኝ ፡ ስትል ፡ ጠየቀቻቸው ። ተንኰለኞቹ ፡ ልጆቿም ፡ እቤት ፡ ድረስ ፡
ያላመጣንልሽ ፡ ዐይንሽ ፡ ያየውን ፡ መርጠሽ ፡ እንድትበይ ፡ በማለት ፡ ነው ።
እርሻችንም ፡ ያው ፡ልሽ ፡ እዚያ ፡ ማዶ ፡ ከላይ ፡ ዝምሮ ፡ እስከ ፡ ታች ፡ የሚ
ታዮው ፡ በሙሉ ፡ የኛው ፡ ነው ። ማንም ፡ ከልከይ ፡ የለብሽም ፡ ሄደሽ ፡ እንደ ፡
ልብሽ ፡ የፈለግሽውን ፡ ዐይነት ፡ እሸት ፡ ቀጥፈሽ ፡ መብላት ፡ ትቸያለሽ ፡ ሲሉ ፡
ያንዱን ፡ ሀብታም ፡ ገበረ ፡ ሰብል ፡ አሰዩዋት ። እናታቸውም ፡ የልጆቿን ፡
ጉልበት ፡ እያመሰገነች ፡ ወደ ፡ አመለከቷት ፡ ዝሪት ፡ ሄደችና ፡ ከባለጸጋው ፡
ሰብል ፡ መከከል ፡ እንፈራጣ ፡ ተቀምጣ ፡ እየቀጠፈችና ፡ እየዘነበጠች ፡ ትበላ ፡
ዝመር ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የእኽሉ ፡ ባለቤት ፡ ሽመሉን ፡ መዘ ፡ ሲሮጥ ፡ መጥቶ ፡
ማን ፡ ፈቀደልሽና ፡ ነው ፡ ከዚህ ፡ የገባሽው ፡ በይ ፡ አሁን ፡ አትወጭም ፡ ሲል ፡
ጠየቃት ። እሷም ፡ የት ፡ ነው ፡ የምወጣው ፡ በልጆቼ ፡ አዝመራ ፡ ዐይንህ ፡
ይውጣና ፡ አትሄድም ፡ ስትል ፡ በልበ ፡ ሙሉነት ፡ ተሰድባ ፡ መለሰችለት ።

እሱም ፡ ያለርኅራኄ ፡ በያዘው ፡ ሽመል ፡ እየጨረገደ ፡ ከእኅሉ ፡ ውስጥ ፡ እስወጥቶ ፡ አባረራት ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ከልጆቿ ፡ ቀጣፊነት ፡ የተነሣ ፡ በመደ ብደቧ ፡ እጅግ ፡ አዝና ፡ ወደ ፡ ፈጣሪዋ ፡ አንጋጣ ፡ ጌታዬ ፡ መልክ ፡ ወይም ፡ ቁመት ፡ አልልህም ፤ በቁም ፡ ነገር ፡ ከነዚህ ፡ የተሻለ ፡ አውራ ፡ ጣት ፡ የሚያኽል ፡ ብልኅ ፡ ልጅ ፡ ስጠኝ ፡ ስትል ፡ በቁመቷ ፡ ሙሉ ፡ እንባዋን ፡ እያወረደች ፡ ብፅዐት ፡ አደረገች ።

ና

እግዚአብሔርም ፡ የለመኑትን ፡ የማይነሣ ፡ የነገሩትን ፡ የማይረሳ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እንደ ፡ ምኞቷ ፡ አውራ ፡ ጣት ፡ የሚያኽል ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ሰጣት ። ለልጁም ፡ በቁመቱ ፡ ማጠር ፡ ምክንያት «ስንዝሮ» የሚበል ፡ ስም ፡ ወጥቶለት ፡ በዚሁ ፡ እየተጠራ ፡ አድጎ ፡ እናቱን ፡ በሥራ ፡ ለማገልገል ፡ ደረሰ ። ቅን ፡ አገልጋይ ፡ በመሆኑና ፡ ወላጅቱን ፡ በማስደሰቱ ፡ እየተወደደ ፡ ስለ ፡ ሄደ ፡ ወንድሞቹ ፡ ቀንተው ፡ ለመግደል ፡ ይመክሩበት ዠመር ።

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እነዚሁ ፡ ስድስቱ ፡ አጉራማ ፡ ወንድሞቹ ፡ ከብት ፡ እንስረቅ ፡ እንስረቅ ፡ ተባብለው ፡ ወደ አንዱ ፡ አገር ፡ ሄዱ ። ስንዝሮም ፡ እየተሸሸገ ፡ ሳያዩት ፡ እሥር ፡ እሥራቸው ፡ እያለ ፡ ተከተሳቸው ። ለመስረቅ ፡ ከሰቡበትም ፡ ቦታ ፡ ቢደርሱ ፡ አጥሩ ፡ የጠበቀ ፡ መዝጊያው ፡ በተዋጋ ፡ የጠነከረ ፡ ኖሮ ፡ ለመግባት ፡ ባለመቻላቸው ፡ ዋይ ፡ ነዶ ፡ ዛሬ ፡ ስንዝሮ ፡ መጥቶ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ይህን ፡ ጊዜ ፡ ይጠቅመን ፡ ነበር ፡ ሲባባሉ ፡ ሰማ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እለሁ ፡ እኔ ፡ ወንድማችሁ ፡ ሲል ፡ ከሥራቸው ፡ ብቅ ፡ አለ ። እነሱም ፡ በመኖሩ ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ በል ፡ ግባና ፡ ከብቶቹን ፡ አስወጥተህ ፡ እምጣ ፡ ሲሉ ፡ እዘዙት ። ትንሹም ፡ ሰው ፡ በወንዳ ፡ ወንዱ ፡ ሥር ፡ ሾልከ ፡ ገባና ፡ እበረት ፡ ሲደርስ ፡ ወንድሞቹ ፡ ዳለቻውን ፡ ነው ፡ ስመግማውን ፡ ወይስ ፡ ደግማውን ፡ ማናቸውን ፡ በሬ ፡ ነው ፡ የማመጣው ፡ እያለ ፡ ይለፈልፍ ፡ ዠመር ። ባለቤቱ ፡ ድምፅ ፡ ሰምቶ ፡ የራስጌውን ፡ ዱላ ፡ መዞ ፡ ለዜውን ፡ አገንድሮ ፡ ቢወጣ ፡ ከበሬ ፡ ጥፍር ፡ ሥር ፡ ተሸሸገ ። እየተዘዋወረ ፡ ቢፈልግም ፡ ሰው ፡ ስላጣ ፡ ሰይጣን ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ተመልሶ ፡ ገብቶ ፡ ከቄጡ ፡ ተኛ ። እሁንም ፡ ጥቂት ፡ ቈይቶ ፡ እንደ ፡ በፊቱ ፡ ወንድሞቹ ፡ የማስወጣው ፡ ጥቍሩን ፡ ነውን ፡ ነጩን ፡ ወይስ ፡ ወይንማውን ፡ ወይስ ፡ ደግሞ ፡ በለጫማውን ፡ እያለ ፡ በጉሳ ፡ ድምፅ ፡ ሲጠይቅ ፡ ተሰማ ። ባለቤቱም ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ወጥቶ ፡ በሩን ፡ ቢመረምር ፡ እንደዚያው ፡ በተዋጋ ፡ ተጠርቅሞ ፡ እንደ ፡ ተዘጋ ፡ አገኘው ። ከበረትም ፡ ከብቶቹን ፡ ቢቈጥራቸው ፡ ሁሉም ፡ መኖራቸውን ፡ አረጋገጠ ።

ስለዚህም ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ሰይጣን ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ከቤቱ ፡ ገብቶ ፡ ተመልሶ ፡ ተኛ ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ስንዝሮ ፡ ከበሬው ፡ እግር ፡ ሥር ፡ ወጥቶ ፡ እጉራውን ፡ ከፍቶ ፡ የሠባ ፡ የሠባውን ፡ በሬ ፡ መርጦ ፡ ነድቶ ፡ ለወንድሞቹ ፡ አስረከበ ። እነሱም ፡ አፍአዊ ምስጋና ፡ አደረጉለትና ፡ ቶሎ ፡ ብለው ፡ አንዱን ፡ በሬ ፡ አረዱት ። ብልትም ፡ ማውጣት ፡ እንደ ፡ ዠመሩ ፡ በምን ፡ አዋዜና ፡ አፍርንጅ ፡ ሥጋውን ፡ እንብላው ፡ ይሆን ፡ እያሉ ፡ ሲጠያየቁ ፡ ሰምቶ ፡ አቶ ፡ ስንዝሮ ፡ አታስቡ ፡ እኔ ፡ አመጣላችኋለሁ ፡ ብሎ ፡ ተመልሶ ፡ ከዚያው ፡ ከባለከብቱ ፡ ቤት ፡ በፋካ ፡ ሾልከ ፡ ገባ ። ወዲያው ፡ እማልደያ ፡ ሳይ ፡ ቆሞ ፡ ወንድሞቹ ፡ የቅቤውን ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ የድልኹን ፡ ቅል ፡ የማመጣው ፡ እያለ ፡ በመጣራት ፡ ሲለፈልፍ ፡ ተሰማ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ባለቤቱ ፡ እረ ፡ ዛሬ ፡ ምን ፡ ጉድ ፡ መጣብን ፡ በማለት ፡ ሚስቱን ፡ ተነሽ ፡ እሳት ፡ አንድጂ ፡ ሲል ፡ አዘዘት ። እሷም ፡ የግዷን ፡ ስትጨነቅ ፡ ከቄጥ ፡ ወርዳ ፡ ማዘንቱ ፡ ላይ ፡ ተቀምጣ ፡ የተዳፈነውን ፡ እሳት ፡ ለማንደድ ፤ እፍ ፡ ስትል ፡ የስእለቱ ፡ ልጅ ፡ ረመጡን ፡ አፍሶ ፡ ባይኗ ፡ ድር ግም ፡ አደረገባት ። ወዲያው ፡ ደንግጣ ፡ እረ ፡ በእሳት ፡ እቃጠለኝ ፡ እያለች ፡ እዘያው ፡ እማዘንቱ ፡ ላይ ፡ ወድቃ ፡ ትንፈራፈር ፡ ዠመር ። ባልዮውም ፡ የማትረቢ ፡ እሳት ፡ እንኳ ፡ ማንደድ ፡ የማይሆንልሽ ፡ ፈዛዛ ፡ በማለት ፡ በቀጣጭ ፡ ከቄጡ ፡ ወርዶ ፡ ለማንደድ ፡ አጉንብሶ ፡ እፍ ፡ ሲል ፡ ሳለ ፡ ስንዝሮ ፡ አውንም ፡ ተንጠራርቶ ፡ ረመጡን ፡ አፍሶ ፡ በዐይኑ ፡ ሞጀረበት ። እሱም ፡ ሰማይና ፡ ምድሩ ፡ ዞሮበት ፤ የሚይዘውንና ፤ የሚጨብጠውንም ፡ አጥቶ ፡ ሲደናበር ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ እማጀቱ ፡ ገብቶ ፡ እየተንጐራደደ ፡ የሚፈልገውን ፡ ካገኘ ፡ በኋላ ፡ የቅቤና ፡ የድልኽ ፡ ቅሉን ፡ ተሸክሞ ፡ ወጣና ፡ ለወንድሞቹ ፡ ይኸው ፡ ይገር ፡ መጣሁ ፡ ብሎ ፡ ሰጣቸው ። እነሱ ፡ ግን ፡ ስለ ፡ አገልግሎቱ ፡ አንዳች ፡ እንኳ ፡ ምስጋና ፡ ሳያደርጉለት ፡ ሥጋውን ፡ ለመብሳት ፡ ቸኮለው ፡ ቅቤውንና ፡ ድልኹን ፡ ተቀብለው ፡ ና ፡ ሂድ ፡ ከፊታችን ፡ ብለው ፡ እንደ ፡ ውሻ ፡ አባረሩት ።

ስንዝሮም ፡ እያዘነና ፡ እየተከዘ ፡ አባካችሁ ፡ ወንድሞቹ ፡ ቄሽትና ፡ ወተት ፡ እንዣቡን ፡ እንኳ ፡ ስጡኝ ፡ ብሎ ፡ አጥብቆ ፡ ለመናቸው ። ምኞቱ ፡ ይህ ፡ ከሆነ ፡ ይውሰድ ፡ በማለት ፡ ሁሉም ፡ ተስማሙ ። እሱ ፡ ግን ፡ እናቱን ፡ በጣም ፡ ይወዳት ፡ ነበርና ፡ ያገኘውን ፡ ምናምን ፡ ሳይቀንስለት ፡ ለርሷ ፡ አስቀመጠ ። ወንድሞቹም ፡ የሚበቃቸውን ፡ ያኽል ፡ ከተመገቡ ፡ በኋላ ፡ የተረፈ

ውን ፡ ሥጋና ፡ ከብቶቹን ፡ መካፈል ፡ ያዙ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ስንዝሮ ፡ እንዲት ፡ የከሳች ፡ ላም ፡ ነበረችና ፡ ይህችን ፡ እንኳ ፡ ስጡኝ ፡ ሲል ፡ ጠየቃቸው ። እነሱም ፡ ስለ ፡ ፈቀዱለት ፡ ወሰዳትና ፡ በሚገባ ፡ ይዘ ፡ ከሚጸላው ፡ እያበላ ፡ በጣም ፡ አወፈራት ፤ መልኳም ፡ እጅግ ፡ አማረ ።

ስንዝሮ ፡ ይህቺ ፡ ላምህ ፡ በምን ፡ መፈረችልህ ፡ ሲሉ ፡ ወንድሞቹ ፡ ጠየቁት ። እሱም ፡ በተንኰል ፡ አንድ ፡ በመሆኗ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ መለሰላቸው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እነዚያ ፡ ቂሎች ፡ ለካ ፡ የሯም ፡ አንዳንድ ፡ ቢሆኑ ፡ ይወፍሩ ፡ ኖሯልና ፡ ብለው ፡ አንዳንድ ፡ ከብት ፡ እያስቀሩ ፡ ሌሎቹን ፡ በሙሉ ፡ ፈጇዋቸው ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ ቍጥራቸውን ፡ ቢቀንሱ ፡ ሳይወፍሩላቸው ፡ ቀሩ ። ስለዚህም ፡ በቀሩት ፡ መገደል ፡ ተጸጽተውና ፡ ተናደው ፡ የስንዝሮን ፡ ላም ፡ ቀምተው ፡ አርደው ፡ በሉበት ። ትንሹም ፡ ሰው ፡ በላሙ ፡ መቃረድ ፡ እጅግ ፡ አለመጠን ፡ አዘነ ፤ ተከዘም ። በኋላም ፡ ሄደና ፡ እባክችሁ ፡ ወንድሞቼ ፡ ሌላው ፡ እንኳ ፡ ቢቀር ፡ ቈዳዋን ፡ ስጡኝ ፡ ብሎ ፡ ለመናቸው ። እነሱም ፡ እንዲወስድ ፡ ፈቀዱለት ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቈዳውን ፡ አድርቆ ፡ ተሸከሞ ፡ በማለዳ ፡ እገበያ ፡ ሄደ ። ሕዝቡ ፡ ከሚገበያይበትም ፡ ቦታ ፡ ትልቅ ፡ ዛፍ ፡ ነበረና ፡ ከዚያ ፡ ላይ ፡ ወጥቶ ፡ ድምጡን ፡ አጥፍቶ ፡ ተቀመጠ ። ገበያውም ፡ በደራ ፡ ጊዜ ፡ ያንን ፡ ቈዳ ፡ በጎይል፡እየመታ፡ የተሰበሰበውን፡ሰው ፡ አሸበረው ። እንዲያውም ፡ በመንጠራራት ፡ እየደጋገመ ፡ በመደብደቡ ፡ ዲና ፡ መጣብን ፡ እያለ ፡ ነጋዴውና ፡ ገበያተኛው ፡ ሸቀጡንና ፡ ዕቃውን ፡ እየጣለ ፡ በያለበት ፡ ተበታትነ ። ጥቂት ፡ ቈይቶ ፡ ቀበሌው ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ሲሆን ፡ አይቶ ፡ ስንዝሮ ፡ ሆዬ ፡ ከዛፉ ፡ ላይ ፡ ወረደና ፡ ሰዉ ፡ ጥሎ ፡ የሸሸውን ፡ እኽል ፡ ወርቅ ፡ ብርና ፡ ማናቸውንም ፡ ሸቀጥ ፡ ሁሉ ፡ በገበያተኛው ፡ እህያና ፡ እጋሰስ ፡ ጭኖ ፡ እየነዳ ፡ ሄዶ ፡ ማታ ፡ ከቤቱ ፡ ገብቶ ፡ ለናቱ ፡ እስረከበት ።

ወንድሞቹ ፡ ፈረሶችና ፡ በቅሎዎች ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ ማናቸውንም ፡ ለኑሮ ፡ ጠቃሚ ፡ የሚሆን ፡ ብዙ ፡ ሀብት ፡ ማግኘቱን ፡ አይተው ፡ ይህንን ፡ ሁሉ ፡ ከወዴት ፡ አመጣኸው ፡ ሲሉ ፡ ጠየቁት ። እሱም ፡ ወንድሞቹ ፡ ሆይ ፡

የዚያችን ፡ የላሜን ፡ ቈዳ ፡ በቀጭኑ ፡ እየተለተልኩ ፡ አድርቄ ፡ እገበያ ፡ በወጣው ፡ ቈዳ ፡ ተወዶ ፡ ኖሮ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ስላገኘሁበት ፡ ይህንን ፡ ሁሉ ፡ ሲሳይና ፡ ዕቃ ፡ ለመግዛት ፡ ቻልኩ ፡ ሲል ፡ መለሰላቸው ።



ነጋዴውና ፡ ገበያተኛው ፡ ሸቀጡንና ፡ ዕቃውን ፡ እየጣለ፡ በያለበት ፡ ተበታተነ ።

እነሱም ፡ ይህንን ፡ በመስማታቸው ፡ የተረፈቸውን ፡ ከብቶች ፡ አርደው ፡ ቈዳቸውን ፡ ሠንጥቀው ፡ ወደ ፡ ገበያ ፡ ይዘው ፡ ወጥተው ፡ እየተዘዋወሩ ፡ ቈዳ ፡ ግዙ ፡ ይሉ ፡ ዠመር ። በገበያ ፡ ያለውም ፡ ሕዝብ ፡ የምን፡ ቂሎች ፡ ናቸው ፡ የቈዳ ፡ ቋንጣ ፡ ይዘው ፡ የሚዘሩ ፡ እያለ ፡ መሣቂያ ፡ አድርጓቸው ፡ ዋለ ። ማታም ፡ ምንም ፡ ሳይሸጡለት ፡ እንደ ፡ ተሸከሙ ፡ ወጀየሰፈራቸው ፡ ተመልሰው ፡ ገቡ ። በማግስቱም ፡ ጪት ፡ ከየቤታቸው ፡ ተጠራርተው ፡ ከንድ ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ተሰብስበው ፡ እየዶለቱ ፡ ሲማከሩ፡ ከስድስቱ ፡ አንዱ ፡ ወንድማቸው ፡ እረ ፡ ይህ ፡ ስንዝሮ ፡ ምንኛ ፡ ጠገበ፤ ሲያሞኘን ፡ ያንድ ፡ ላም ፡ ቈዳ ፡ ይህንን ፡ ሁሉ ፡ ገንዘብ ፡ አወጣልኝ ፡ ብሎ ፡ ከብቶቻችንን ፡ አሳርዶ ፡ የገበያ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ መሣቂያ ፡ እድርጎን ፡ ዋለ ። እንግዲህ ፡ ምን ፡ ይበጀናል ፡ ሲል ፡ ጥያቄ ፡ አቀረበ ። አንዱ ፡ ደግሞ ፡ እሱን ፡ ከነቤቱ ፡ እናቱን ፡ ጭምር ፡ አቃጥለን ፡ ካላጠፋነው ፡ ምንም፡ ጤና ፡ አናገኝም ፡ ሲል ፡ ሐሳቡን ፡ በመግለጡ ፡ ሁሉም ፡ በምክሩም ፡ ተስማሙ ።

ስንዝሮም ፡ ወንድሞቹ ፡ ሊገድሉት ፡ ማሰባቸውን ፡ ስላወቀ ፡ ሙቀ ጫውን ፡ ልብስ ፡ አልብሶ ፡ ከቄጥ ፡ ላይ ፡ አስተኝቶ ፡ እናቱን ፡ ይዘ ፡ ተሸ ሽገ ። ወንድሞቹም ፡ እንደ ፡ ተማከሩት ፡ በጭላንጭል ፡ ሰው ፡ መኖሩን፡ ከረጋገጡ ፡ በኋላ ፡ በቤቱ ፡ እሳት ፡ ለቀቁበት ። ቆመውም ፡ ቃጠሎውን፡ ሲመለከቱ ፡ አንዳንድ ፡ ነገር ፡ በፈነዳ ፡ ቊጥር ፡ እሰይ ፡ የዚያች ፡ የፈር ሳም ፡ ልቧ ፡ ፈነዳ ፡ ወይኗ ፡ ፈነዳ ፡ እያሉ ፡ በመደሰት ፡ ቄይተው ፡ እሳቱ፡ ሲበርድ ፡ ወደየቤታቸው ፡ ተመለሱ ። በማግስቱ ፡ ስንዝሮ ፡ ከወንድሞቹ፡ ዘንድ ፡ ሄዶ ፡ እባካችሁ ፡ የቤቴን ፡ አመዱን ፤ እንኳ ፡ ፍቀዱልኝና ፡ ልው ሰድ ፡ አላቸው ። እነሱም ፡ ከመቃጠል ፤ በመዳኑ ፡ እየተደነቁ ፡ ውሰ ደው ፡ እኛ ፡ ምን ፡ ቸገረን ፡ አመድ ፡ ምን ፡ ያደርግልናል ፡ ሲሉ ፡ መለ ሱለት ።

ከዚህ በኋላ ፡ ስንዝሮ ፡ ከገበያ ፡ ባመጣቸው ፡ ከብቶች ፡ በስልቻ ፡ አመዱን ፡ ጭኖ ፡ ወደ ፡ ማይታወቅበት ፡ አገር ፡ ሲጓዝ ፡ ውሎ ፡ ከንድ ፡ ሀብታም ፡ ግቢ ፡ ሲደርስ ፡ የመንግሥት ፡ እኽል ፡ ጭኖለሁና ፡ አሳድሩኝ፡ ሲል ፡ ለመነ ። የመንግሥት ፡ እኽል ፡ የጫነ ፡ ክብር ፡ አለውና ፡ ያ ፡ ከበርቴ፡ ቶሎ ፡ ተቀብሎ ፡ አሰፈረው ። ለከብቱም ፡ አስፈላጊውን ፡ ገፈራ ፡ ሰጥቶ፡ ስንዝሮን ፡ በሚገባ ፡ አስተናግዶ ፡ ከድንክ ፡ አልጋ ፡ ላይ ፡ እስተኛው ። እኩለ ፡ ሌሊት ፡ ሲሆን ፡ በለቤቱን ፡ እንቅልፍ ፡ ድብን ፡ አድርጎ ፡ ሲወ ስደው ፡ አያቶ ፡ ስንዝሮ ፡ ሆዬ ፡ ከተኛበት ፡ ተነሥቶ ፡ ጉተራ ፡ ቀዶ ፡ ነጩን ፡ ጤፍ ፡ አውጥቶ ፡ እሱ ፡ ስልቻ ፡ ድረስ ፡ ነስንሶ ፡ ተመልሶ ፡ ተኛ። ጧት ፡ ከመችታው ፡ ተነሥቶ ፡ ወንድሞቹ ፡ አጫጭኑኝ ፡ መንገድ ፡ በማ ስዳ ፡ ነው ፡ አላቸውና ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ጭነቱ ፡ ሄደ ። ወዲያው ፡ አረ ፡ ይህ ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ የፈሰሰው ፡ እያለ ፡ እንደ ፡ ተሰረቀ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ይቅበጠበጥ ፡ ዠመር ። የቤቱም ፡ ጌታ ፡ ድምፁን ፡ ሰምቶ ፡ ምን ድነው ፡ ወንድሜ ፡ ምን ፡ አገኘህ ፡ አለው ። በጭነቴ ፡ ዙሪያ ፡ ነጭ ፡ ጤፍ ፡ ፈሷል ፤ ይህም ፡ እኔ ፡ የያዝኩትን ፡ ይመስላል ፤ እረ ፡ ለመሆኑ ፡ እስቲ ፡ ሽልቻዬን ፡ ልየው ፡ ና ፡ ርዳኝ ፡ አለና ፡ ቢፈታው ፡ አመድ ፡ ሆኖ ፡ አገኙት።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አቶ ፡ ስንዝሮ ፡ የጨዋ ፡ ግቢ ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ ከቤታችሁ ፡ ባድ ር ፡ የመንግሥቱን ፡ ጤፍ ፡ እንዲራችሁ ፡ ስትገለብጡ ፡ ታድሩ ፡ ትዘርፉኝ ፡ እንግዲህ ፡ እኔ ፡ ምን ፡ አደርጋለሁ ፤ ወደ ፡ መንግሥት ፡ አደባባይ ፡ ሄጀ ፡ እጮ ሃለሁ ፡ እያለ ፡ ይጋበዝ ፡ ዠመር ። ወዲያው ፡ ከበርቴው ፡ እጫማው ፡ ላይ ፡ ወድቆ ፡ እባክህ ፡ ወደ ፡ ዳኛ ፡ አትሂድ ፤ ሀብቴን ፡ አታስወርሰኝ ፡ የመንግሥቱን፡

ነጭ ፡ ጤፍ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እኔ ፡ እከፍላለሁ ፡ ብሎ ፡ ከስታገሠው ፡ በኋላ ፡ አመዱን ፡ እየገለበጠ ፡ ጤፉን ፡ በስልቻው ፡ ሞልቶ ፡ አጫጭኖ ፡ ወደ ፡ ሀገሩ ፡ ሰደደው ።

ስንዝሮም ፡ ከብቶቹን ፡ እየነዳ ፡ እኽሉን ፡ ይዘ ፡ ሄዶ ፡ ለናቱ ፡ አስረከባት ። ወንድሞቹ ፡ ግን ፡ እንደልማዳቸው ፡ መጥተው ፡ ደግሞ ፡ ይህንን ፡ ሁሉ ፡ ጤፍ ፡ ከየት ፡ አመጣኸው ፡ ሲሉ ፡ ጠየቁት። እሱም ፡ እናንተ ፡ ቤቴን ፡ ብታ ቃጥሉት ፡ አመዱን ፡ ውድ ፡ ከሆነበት ፡ አገር ፡ ወስጄ ፡ በጤፍ ፡ ለወጥኩታ ፡ አለና ፡ መለሰላቸው ።

እነሱም ፡ እንግዲያው ፡ ማ ፡ አመድ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ጤፍ ፡ ከለወጠ ፡ እኛስ ፡ ቤታችንን ፡ እናቃጥለምን ፡ ብለው ፡ ስድስቱም ፡ ያላቸውን ፡ ቤት ፡ አጋይተው ፡ አመዱን ፡ ከያምባው ፡ በለሙት ፡ በአጋሰስ ፡ ጭነው ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ አገር ፡ ሄደው ፡ አመድ ፡ በጤፍ ፡ ለውጡን ፡ እያሉ ፡ መንደር ፡ ለመንደር ፡ ይዘሩ ፡ ዠመር ። ያገሩም ፡ ሰዎች ፡ ይህ ፡ አነጋገር ፡ እንግዳ ፡ ስለ ፡ ሆነባቸው ፡ ከወዴት ፡ የመጣችሁ ፡ ቂሎች ፡ ናችሁ ፡ ለመሆኑ ፡ አመድ ፡ ያድርጋችሁና ፡ በማን ፡ አገር ፡ ነው ፡ አመድ ፡ በነጭ ፡ ጤፍ ፡ ይለወጣል ፡ ሲባል ፡ የሰማችሁት ፡ እያሉ ፡ መሣቂያና ፡ መሣለቂያ ፡ አደረጓቸው ።

እነሱም ፡ በመታለላቸው ፡ በጣም ፡ ተናደውና ፡ ተበሳጭተው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ ተመልሰው ፡ እንደ ፡ ገቡ ፡ ስንዝሮን ፡ ገደል ፡ ለመጣል ፡ ምክር ፡ አደረጉ ። ወዲያውኑ ፡ ቀፎ ፡ ሠርተው ፡ ከዚያ ፡ ውስጥ ፡ ለማባበት ፡ ይዘውት ፡ ሰለ ፡ እባካችሁ ፡ ወንድሞቼ ፡ እንዳያቃዠኝ ፡ ከራስጌዬ ፡ የማስቀምጠው ፡ ማጭድ ፡ ስጡኝ ፡ አላቸው ። እነሱም ፡ ይሁን ፡ እሺ ፡ ብለው ፡ ሰጡት ። ቀፎውን ፡ ዘግተው ፡ ከጨረሱ ፡ በኋላ ፡ ተሸክመው ፡ ሲጓዙ ፡ በመንገዳቸው ፡ አጠገብ ፡ ዳስ ፡ አዩ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ መቼም ፡ ስሆ ዳቸው ፡ የሞቱ ፡ ነበሩና ፡ ጥቂት ፡ በልተንና ፡ ጠጥተን ፡ እንመለስ ፡ ብለው ፡ የተሸከሙትን ፡ ከንድ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ አኑረው ፡ ወደ ፡ ድግሱ ፡ ቤት ፡ ሄዱ ። ገና ፡ እግራቸው ፡ እልፍ ፡ ሲል ፡ ስንዝሮ ፡ ሆዬ ፡ በሰጡት ፡ ማጭድ ፡ ቀፎውን ፡ ቀዶ ፡ ወጥቶ ፡ በራሱ ፡ ምትክ ፡ ድንጋይ ፡ ጨምሮ ፡ ቀዳዳውንም ፡ በደንብ ፡ ደፍኖ ፡ ተሸሽገባቸው ። ወንድሞቹም ፡ ሲጠጡ ፡ ውለው ፡ ስካር ፡ ስለ ፡ ተጫ ጫናቸው ፡ እንደ ፡ መጡ ፡ ቀፎውን ፡ ካኖሩበት ፡ አንሥተው ፡ ወደ ፡ ገደል ፤ ሰደው ፡ ገደልነው ፡ ብለው ፡ ወደየቤታቸው ፡ ተመለሱ ።

ስንዝሮ፡ ግን ፡ ከሞላ ፡ ወንዝ ፡ ዳር ፡ ተቀምጦ ፡ ይጠባበቅ ፡ ነበርና ፡ በማ ኽል ፡ አንድ ፡ ሴት ፡ ጃኖ፡ ለብሳ ፡ አገልግል ፡ ተሸክማ ፡ ከሩቅ ፡ ስትመጣ ፡ ተመ ለከተ ። እንደ ፡ ደረሰችም ፡ ከወንዙ ፡ ዳር ፡ ሲንጐራደድ ፡ አይታ ፡ በመጣራት፡ ጌታ ፤ እባክዎ ፡ ያሻግሩኝ ፡ ስትል ፡ ለመነችው።ስንዝሮም ፡ እሺ ፡ ደኅና ፡ ነው ፡ በሴት ፡ ልጅ ፡ ላይ ፡ አይጨክንምና ፡ ያላንድ ፡ ኪሳራ ፡ አንችንም ፡ ዕቃሽንም ፡ በደኅና ፡ አድርጌ ፡ አሻግራለሁ ፡ ብሎ ፡ ቃል ፡ ሰጣት ። ወዲያው ፡ ጃኖውንና ፡ አገልግሉን ፡ ብቻ ፡ ተሸክሞ ፡ በቁም ፡ ዋናኺ ካሻገረ ፡ በኋላ ፡ ተመልሶ ፡ መጥቶ፡ ሴቲቱን ፡ ይዞ ፡ ገባ ። ነገር ፡ ግን ፡ በልቡ ፡ ተንኰል ፡ አስቦ ፡ ኖሮ ፡ ከማኽል ፡ ሲደርስ ፡ ስለ ፡ ለቀቃት ፡ ፈረሰኛው ፡ እያዶፋ ፡ ይዟት ፡ ወረደ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ስንዝሮ ፡ የሚችቱን ፡ ልብስ ፡ ተከናንቦ ፡ ከንድ ፡ ዛፍ ፡ ሥር ፡ ተቀምጦ ፡ አገልግሉን ፡ ከፍቶ ፡ ፍትፍቱን ፡ ይበላ ፡ ዠመር ። ሊጠግብ ፡ ሲል ፡ አንድ ፡ ፈረሰኛ ፡ በመንገድ ፡ ሲያልፍ ፡ አየና ፡ ጠርቶ ፡ ወንድም ፡ እንደኔ ፡ እርቦህ ፡ አንደ ፡ ሆነ ፡ እንካ ፡ ብላ ፡ ብሎ ፡ አገልግሉን፡ አቀረበለት ። ሰውዬውም ፡ መመገብ ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ ይህ ፡ ፈረስህ ፡ ጮሌ ፡ ነውን ፡ አስቲ ፡ ጥቂት ፡ ልሞክረው ፡ አለው ። ስለ ፡ ፈቀደለትም ፡ ተቀምጦ ፡ እስቲሞቀው ፡ ድረስ ፡ በደንገላሳ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ይል ፡ ዠመረ ። ወዲያ ፡ ስሄድ ፡ መጣ ፡ ወደዚህ ፡ ስመጣ ፡ ሄደ ፡ እያልክ ፡ ሳትቸኵል ፡ ቀስ ፡ እያልክ ፡ ብላ ፡ ብሎ ፡ አስጠንቅቆት ፡ ነበርና ፡ ወዲያ ፡ ሲሄድ ፡ መጣ ፡ ወዲህ ፡ ሲመጣ ፡ ሄደ ፡ በማለት ፡ ጥቂት ፡ ከላመደ ፡ በኋላ ፡ ልበ ፡ ሙሉው ፡ ስንዝሮ ፡ ኰርኵሮ ፡ ጋልቦ ፡ ጠፋ ።

ባለፈረሱ ፡ ግን ፡ በልማድ ፡ መጣ—መጣ ፡ ሲል ፡ ቂይቶ ፡ በመጨረሻው፡ ዘወር ፡ ቢል ፡ ላይኑ ፡ እንኳ ፡ የሚያየው ፡ አጣ ።

ስንዝሮ ፡ ግን ፡ ጃኖውን ፡ ደርቦ ፡ በፈረስ ፡ ተቀምጦ ፡ እየተቄነነ፡ከቤት ፡ ገባ ። ወንድሞቹም ፡ እንደ ፡ ልማዳቸው ፡ ይህንን ፡ መሰይ ፡ ፈረስና ፡ ልብስ ፡ ከወዴት ፡ አመጣህ ፡ ብለው ፡ አጥብቀው ፡ ጠየቁት ።

እሱም ፡ ገደል ፡ ከገቡ ፤ ባዝራው ፡ ድንጕላው ፡ ጃኖው ፡ እንዲህ ፡ አይ ደለም ፡ ሞልቷል ፡ አላቸው ። እንግዲያውስ ፡ እባክህ ፡ እኛንም ፡ ስደደን ፡ ሲሉ ፡ ለመኑት ። እሱም ፡ ምን ፡ ከፋኝ ፡ እሽ ፡ እኔ ፡ እንደናንተ ፡ ምቀኛ ፡ አይደለሁም ፡ ሌላ ፡ ከሚጠቀምበት ፡ ወንድሞቼ ፡ ብትወስዱት ፡ ደስ ፡ ይለ ኛል ፡ አለና ፡ ስድስቱንም ፡ ወስዶ ፡ በተርታ ፡ ከገደሉ ፡ አፋፍ ፡ ላይ ፡ አቁሞ ፡

አንዱን ፡ ያውልህ ፡ ይታይሃል ፡ ብሎ ፡ ሲያጕነብስ ፡ በስውር ፡ ከቂጡ ፡ ገፋ ፡ በማድረጉ ፡ ከድንጋይ ፡ ላይ ፡ ተከስክሶ ፡ ደሙ ፡ ስለ ፡ ቀላ ፡ ወጥንቱ ፡ ስለ ፡ ነጣ ፡ ለቀሩት ፡ ይኸው ላችሁ ፡ ጃኖውን ፡ መዘዘው ፡ አላቸው ።

አንኮላ—ቂል ፡ ወንድሞቹም ፡ በመመቀኛኘት ፡ ሳይጨርስና ፡ ሁሉ ንም ፡ ሳይወስደው ፡ ቆሎ ፡ እኔን ፡ ስደደኝ ፡ እኔን ፡ ስደደኝ ፡ በማለታቸው ፡ ሁሉንም ፡ እያከታተለ ፡ ገደል ፡ አገባቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እናቱን ፡ በመል ክም ፡ አድርጎ ፡ አገልግሉና ፡ ጦሮ ፡ ስትሞትም ፡ በወግ ፡ በማዕርግ ፡ ቀበራት ።



ሳይጨርስና ፡ ሁሉንም ፡ ሳይ ወስድ ፡ ቆሎ ፡ እኔን፡ስደደኝ።

አሱም ፡ በደኅና ፡ ሲኖር ፡ ቂይቶ ፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ የረጋ ፡ ወተት፡ በጣባ ፡ ቅድዶ ፡ እያማገ ፡ እስቲጠግብ ፡ ምሳውን ፡ ከበላ ፡ በኋላ ፡ ትንሽ ፡ የርጎ ፡ ፍንጣቂ ፡ አሆዱ ፡ ላይ ፡ ጠብ ፡ ብላ ፡ በማየቱ ፡ አሷን ፡ ጐንበስ ፡ ብዬ ፡ እልሳለሁ ፡ ሲል ፡ አተቀመጠበት ፡ ፈንድቶ ፡ ሞተ ፡ ይበላል ።

※ ሰው ፡ አጠረ ፡ ቀጠነ ፡ ተብሎ ፡ አይናቅም ። ስደግም ፡ ሆነ ፡ ለክፉ ፡ ሥራ ፡እንደ ፡አእምሮው ፡ስፋት ፡ችሎታ ፡ይኖረዋል ፤ይሁን ፡እንጂ ፡የጎደ ለኛውም ፡ የደከማውም ፡ የብልጉም ፡ የየዋሁም ፡ አሸናፊ ፡ ሞት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ይኸን ፡ዐውቆ ፡ከተንኰል ፡ርቆ ፡ውለታ ፡ቢስ ፡ሳይሆኑ ፡በጎ ፡ሥራ ፡ አየሠሩ ፡ መኖር ፡ የተመረጠ ፡ መሆኑን ፡ ማወቅ ፡ ይገባናል ።

ስለ ፡ አንዲት ፡ የቆቅ ፡ ልጅ ፡ በወጥመድ ፡ መያዝ ።

አንዲት ፡ የቆቅ ፡ ልጅ ፡ የስንዴ ፡ እሸት ፡ ትርክክ ፡ ብሎ ፡ በስሎ ፡ በሚ ገኝበት ፡ እርሻ ፡ አጠገብ ፡ ወጥመድ ፡ ተጠምዶ ፡ አይታ ፡ እናቷን ፡ እናቴ ፡ ሆይ ፡ እሸት ፡ አምሮኝ ፡ ነበር ፤ ከዚህ ፡ ማሳ ፡ ገብቼ ፡ እንዳልበላ ፡ ወጥመድ ፡ ተጠምዷል ፡ ምን ፡ ይሻለኛል ፡ አለቻት ።

እናቷም ፡ ተዪ ፡ ልጄ ፡ ይቅርብሽ ፡ ትያዣለሽ ፡ አይሆንም ፡ ብላ ፡ መከረቻት ።

ልጅቷ ፡ ግን ፡ ግድ ፡ የለሽም ፡ አይዘኝም ፡ ትንሽ ፡ ተክ ፡ ተክ ፡ አድርጌ ፡ ልውጣ ፡ አለችና ፡ ገብታ ፡ ስትበላ ፡ ያ ፡ ወጥመድ ፡ እናቷ ፡ እንደ ፡ ፈራችው ፡ እግሯን ፡ ጥርቅም ፡ አድርጎ ፡ ያዛት ።

መቼም ፡ መከራ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ መዠመሪያ ፡ የሚታሰቡት ፡ ወላጆች ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ ያች ፡ የናቷን ፡ ምክር ፡ አልሰማ ፡ ያለች ፡ ልጅ ፡ እናቴ ፡ አረ ፡ ተያዝኩልሽ ፡ አለቻት ። እሷም ፡ ምነው ፡ ልጄ ፡ አስቀድሜ ፡ ነግሬሽ ፡ አልነበረምን ፡ አሁን ፡ ታዲያ ፡ ምን ፡ ላደርግልሽ ፡ እችላለሁ ፡ ስትል ፡ መለሰችላት ።

—እማምዬ ፡ እበክሽን ፡ ፍቺልኝ ፤

—በምን ፡ እጄ ?

—ታዲያ ፡ እንዴት ፡ ልሁን ፤ ምን ፡ ይብጀኝ ? የኔ ፡ እናት ፤

በዚህ ፡ ጊዜ ፤ እናት ፡ ለልጅዋ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ምክር ፡ ዐዋቂ ፡ ናትና ፡ ዝም ፡ ብለሽ ፡ የሞትሽ ፡ መስለሽ ፡ ተኚ ፤ ባለወጥመዱ ፡ ሲመጣ ፡ ሞታለች ፡ ብሎ ፡ ፈትቶ ፡ ይለቅሻል ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ታመልጫለሽ ፡ አለቻት ።

ያ ፡ ባለወጥመድ ፡ ሰው ፡ ሰብሉን ፡ ጎብኝቶ ፡ መጣና ፡ ቢመለከት ፡ ዝልፍልፍ ፡ ብላ ፡ ተኝታ ፡ ዐይኗን ፡ አጨልማ ፡ አገኛት ።

እሱም ፡ የሞተች ፡ መሰለውና ፡ እዴ ፡ ጉድ ፡ ወጥመዴ ፡ ቆቅ ፡ ይዘልኝ ፡ ነበረ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በክታለች ፡ እያለ ፡ እዘነ ።

ጓደኛው ፡ ከበላዩ ፡ ሰብል ፡ ይጠቅ ፡ ነበርና ፡ ወንድም ፡ ብሎ ፡ ተጣርቶ ፡ ወጥመዴ ፡ ቆቅ ፡ ይዘልኝ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በክታ ፡ አገኘኋት ፡ አለና ፡ ነገረው ። ባልንጀራውም ፡ እስቲ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ አጕናት ፡ አለው ። እሱም ፡ እያት ፡ አለና ፡

ወደ ፡ ሰማይ ፡ ወርወር ፡ ቢያደርጋት ፡ ቱር ፡ ብላ ፡ ከጫካዋ ፡ ጥልቅ ፡ አለች ፡ ይባላል ።



እያት ፡ አለና ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ወርወር ፡ ቢያደርጋት ፡ ቱር ፡ ብላ ፡ ከጫካዋ ፡ ጥልቅ ፡ አለች ።

። ልጆች ፡ ሆይ ፤ ያበትና ፡ የናት ፡ ምክር ፡ ጠቃሚ ፡ መሆኑን ፡ ተገንዝባችሁ ፡ ከምክር ፡ ከትእዛዝና ፡ ከፈቃድ ፡ አትውጡ ።

ስለ ፡ አንድ ፡ አባት ፡ ኑዛዜ ።

ኾስት ፡ ወንድ ፡ ልጆች ፡ ያሉት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፡ ይባላል ። እሱም ፡ አርጅቶ ፡ ጊዜ ፡ ሞቱ ፡ ስለ ፡ ተቃረበ ፡ ሽማግሎችንና ፡ የንስሓ ፡ አባቱን ፡ አስጠርቶ ፡ ኑዛዜ ፡ አደረገ። ይኸውም ፡ እንዲያው ፡ በደፈናው ፡ አንዱን ፡ ልጄን ፡ መርቄዋለሁና ፡ ርስቴንም ፡ ቤቴንም ፡ ከብቴንም ፡ ያለ ፡ ሀብቴንም ፡ ሁሉ ፡ በሙሉ ፡ ይውሰድ ፤ ምንም ፡ አይነካበት ፤ አለቃ ፡ አድርጌዋለሁ ፡ አንድም ፡ ከብት ፡ ያሰፈቃዱ ፡ አይነካበት ። ሁለተኛው ፡ ልጄ ፡ ምንዝር ፡ ሆኖ ፡ ይብላ ፤ የወንድሙን ፡ ቃልና ፡ ትእዛዝ ፡ ሰምቶ ፡ ይደር ። ዳግም ፡ ሦስተኛውን ፡ ልጄን ፡ ረግሜዋለሁና ፡ ከርስቴም ፡ እንዳይበላ ፡ ከቤቴም ፡ እንዳይቀመጥ ፡ ከብትም ፡ እንዳይካፈል ፡ የሚል ፡ ነው ።

ነገር ፡ ግን ፡ የመረቀውንም ፡ ምንዝር ፡ ሆኖ ፡ ይብላ ፡ ያለውንም ፡ የረገመውንም ፡ ለይቶ ፡ ሳይናገር ፡ ቀረ ። ሽማግሎቹና ፡ የንስሓ ፡ አባቱም ፡ ይህንኑ ፡ ሳያጣሩ ፡ ኑዛዜውን ፡ ብቻ ፡ ሰምተው ፡ ተነሥተው ፡ መጀየቤታቸው ፡ ሄዱ ።

ይህም ፡ ሽማግሌ ፡ ሰው ፡ ምንም ፡ ያኽል ፡ ሳይቈይ ፡ ጥቂት ፡ ሰንብቶ ፡ ጠዲያው ፡ ሞተ ። እነዚያም ፡ ሦስቱ ፡ ልጆች ፡ በገመድ ፡ ታጥቀው ፡ ሲያለቅሱ ፡ ውለው ፡ አባታቸውን ፡ ቀብረው ፡ ማታ ፡ ሕዝቡን ፡ ወጀየቤቱ ፡ አሰናበቱ ። አባታቸው ፡ ጥሩ ፡ ክርስቲያን ፡ ነበረና ፡ ልጆቹ ፡ ከሞተበት ፡ ቀን ፡ ዠምረው ፡ ጣልስቱን ፡ ሰበቱን ፡ ዐሥራ ፡ ሁለቱን ፡ ኻያውንና ፡ ሠላሳውን ፡ አስቈርዘው ፡ አርባውን ፡ ደግሞ ፡ በመልካም ፡ ደግሰው ፡ አወጡ ። በማግስቱ ፡ ዚያት ፡ ሦስቱ ፡ ወንድማማቾች ፡ ዳሱ ፡ ሳይፈርስ ፡ ዋንጫው ፡ ሳይመለስ ፡ ያባታችንን ፡ ኑዛዜ ፡ ንገሩን ፡ ብለው ፡ የንስሓ ፡ አባትየውንና ፡ ያናዘዙትን ፡ ሽማግሎች ፡ ጠየቋቸው ።



ያባታችንን ፡ ኑዛዜ ፡ ንገሩን ፡ ብለው ፡ የንስሓ ፡ አባትየውንና ፡ ያናዘዙትን ፡ ሽማግሎች ፡ ጠየቋቸው ።

እነሱም ፡ ብዙ ፡ ምስክሮች ፡ ባሉበት ፡ አባታችሁ ፡ አንደኛችሁን ፡ መርቆ ፡ ያለውን ፡ ሀብት ፡ ሁሉ ፡ ሰጥቶ ፡ አለቃ ፡ አድርጎታል ፤ ሁለተኛውን ፡ ምንዝር ፡ ሆኖ ፡ ለወንድሙ ፡ ታዛ ፡ ቃሉን ፡ ሰምቶ ፡ እንደ ፡ አባት ፡ አክብሮ ፡ እንዲያድር ፡ ሲያደርግ ፤ ሦስተኛውን ፡ ግን ፡ ረግሞ ፡ ከርስቱም ፡ አይብላ ፡ ከወንድሞቹም ፡ አይቀላቀል ፡ ከቤቱም ፡ አይቀመጥ ፡ ብሏል ፡ ሲሉ ፡ ኑዛዜውን ፡ አፈሰሱ ። ልጆቹም ፡ ተራቸውን ፡ የተመረቀውን ፡ ምንዝር ፡ ሆኖ ፡ ይብላ ፡ የተበለውን ፡ የተረገመውን ፡ በስም ፡ በስሙ ፡ ለይታችሁ ፡ ንገሩን ፡ ብለው ፡ ጠየቋቸው ። አናዛዦቹ ፡ ግን ፡ ይህንኑ ፡ ነገረን ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ የገለጸልን ፡ ነገር ፡ የለም ፤ ስለዚህ ፡ ወደ ፡ ተማረ ፡ ዐዋቂ ፡ ሄዳችሁ ፡


ይለይላችሁ ፡ እንጂ ፡ እኛ ፡ ፍቺውን ፡ አላወቅነውም ፡ አሏቸው ።

ወንድማማቾቹም ፡ ስለ ፡ ተቸገሩ ፡ ተነሥተው ፡ ከንድ ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ ፊላስፋ ፡ ዘንድ ፡ ሄዱ ። እሱንም ፡ ምንም ፡ አርጅቶ ፡ ከተቀመጠበት ፡ መነሣት ፡ አቅቶት ፡ ከቤት ፡ ውሎ ፡ መናገር ፡ አውከት ፡ ቢያገኙት ፡ ጌታችን ፡ ሆይ ፡ አባታችን ፡ ሲሞት ፡ አንደኛችንን ፡ መርቄዋለሁና ፡ ርስቴንም ፡ ከብቴንም ፡ በሙሉ ፡ ይውሰድ ፤ አንደኛችንን ፡ ምንዝር ፡ ሆኖ ፡ ይብላ ፡ ለወንድሙ ፡ ታዛ ፡ ቃሉን ፡ ሰምቶ ፡ አንደ ፡ አባት ፡ አድርጎ ፡ አክብሮ ፡ ይደር ፤ አንደኛችንን ፡ ደግሞ ፡ ረግሜዋለሁ ፤ ከርስቴም ፡ አይብላ ፡ ከቤቴም ፡ አይቀመጥ ፡ ከብቴንም ፡ አይንካ ፡ ከልጆቼም ፡ ዘንድ ፡ አይድረስ ፡ ብሎ ፡ ተናግሮ ፡ ሞተ ። ነገር ፡ ግን ፡ የተመረቀውን ፡ ምንዝር ፡ የሚሆነውን ፡ የተረገመውን ፡ በመለየት ፡ አልገለጸልንም ። አንተ ፡ ምስጢርን ፡ የምትመረምር ፡ ሀዋቂ ፡ መሆንክን ፡ ስለ ፡ ሰማን ፡ ይህንን ፡ ነገር ፡ ፈተህ ፡ ትነግረን ፡ ዘንድ ፡ ይኸው ፡ ወዳንተ ፡ መጥተናል ፡ አሉት ። ፊላስፋውም ፡ ዝርዝር ፡ ጕዳዩን ፡ ከዳመጠ ፡ በኋላ ፡ የዚህ ፡ ፍቺው ፡ በውነት ፡ ለኔ ፡ አልተገለጸልኝም ፤ ስለዚህ ፡ በጣም ፡ የተማረ ፡ ሰውነቱም ፡ ከኔ ፡ ልጅ ፡ የሆነ ፡ ታላቅ ፡ ወንድም ፡ አለኝና ፡ ከሱ ፡ ዘንድ ፡ ብትሄዱ ፡ ትርጕሙን ፡ ሊነግራችሁ ፡ ይችላል ፡ አላቸው ።

ወንድማማቾቹም ፡ ይኸ ፡ ትንሹ ፡ እንደዚህ ፡ ያረጀና ፡ የወደቀ ፡ ሲሆን ፡ ትልቁማ ፡ ምን ፡ መናገር ፡ ይችላል ፤ እንዲያው ፡ መንገድ ፡ መቶን ፡ እንመጣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ብለው ፡ ሄዱ ። በደረሱም ፡ ጊዜ ፡ ያ ፡ ታላቅ ፡ የተባለውን ፡ ወንድም ፡ ገና ፡ ያልቀና ፡ ወይፈን ፡ ሲገርፍ ፡ አገኙት ። እነሱም ፡ እንደ ፡ ተለመደው ፡ የመጡበትን ፡ ጕዳይ ፡ ዘርዝረው ፡ ካስረዱ ፡ በኋላ ፡ ችግራቸውን ፡ የሚያስወግዱበትን ፡ ብልኀት ፡ እንዲነግራቸው ፡ ለመኑት ። ነገሩን ፡ ሰምቶ ፡ በልቦናው ፡ ገምቶ ፡ አውጥቶና ፡ አውርዶ ፡ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፤ ይህ ፡ ነገር ፡ በጣም ፡ ምስጢሩ ፡ የረቀቀ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ለታላቅ ፡ ወንድሜ ፡ እንጂ ፡ ለኔ ፡ የሚገለጽልኝ ፡ አልሆነም ። ስለዚህ ፡ ፈልጋችሁ ፡ ንገሩት ፡ ስላላቸው ፤ ትንሹ ፡ በማርጀቱ ፡ ትልቁ ፡ ወይፈን ፡ እየገረፈ ፡ በማቅናቱ ፡ እየተደነቁና ፡ እየተገረመ ፡ አንጋፋ ፡ ወደ ፡ ሆነው ፡ ዘንድ ፡ ሄዱ ።

ይኸም ፡ ግልገል ፡ በቅሎ ፡ በልጓም ፡ ይዘ ፡ ሲገራ ፡ አገኙት ። ለዚህ ፡ ለሦስተኛው ፡ ሊቅ ፤ ስለ ፡ ወንድማማቾቹ ፡ የተገላቢጦሽ ፡ እርጅና ፡ መደነቃቸውን ፡ ጭምር ፡ ያመጣጣቸውን ፡ ሁኔታና ፡ ችግራቸውን ፡ ዘርዝረው ፡

ገለጹለት ። ጕዳዩን ፣ በሙሉ ፣ ካዳመጠ ፣ በኋላ ፣ አባታችሁ ፣ በጣም ፣ ብልኅ ፣ ሰው ፣ ኖሯል ፣ የተናዘዘው ፣ መልካም ፣ ነው ፣ በማለት ፣ ንግግሩን ፣ ቀጠለ ። ያ ፣ አርጅቶ ፣ ከመሬት ፣ መነሣት ፣ እቅቶት ፣ ያያችሁት ፣ ትንሹ ፣ ወንድሜ ፣



ግልገል፣በቅሎ፣በልጓም ፣ ይዞ ፣ ሲገራ ፣ አገኙት ።

ነው ። ለቤት ፣ ለንብረት ፣ ከደረሰም ፣ ወዲህ ፣ ቢሠራ ፣ ጠብ ፣ እይልለትም፣ በሕፃንነቱ ፣ እናቱና ፣ አባቱ ፣ ሞተው፡በት ፣ በሰው ፣ ቤት ፣ ሲንገላታ ፣ የሰው፣ ፊት ፣ እንደሳት ፣ ሲጠብሰው ፣ ካንዱ ፣ ወደ ፣ አንዱ ፣ ቤት ፣ ሲል ፣ ያደገ ፣ ነው ። ደግሞ ፣ በዚህም ፣ ላይ ፣ ልጆች ፣ ራስ ፣ በራስ ፣ ወልዷል ። እነዚህም ፣ የሚበሉት ፣ ምግብና ፣ የሚለብሱት ፣ ልብስ ፣ እየተቸገሩ ፣ ባለቀሱበት ፣ ቍጥር ፣ በዕድሉ ፣ ስለሚያዝንና ፣ ከልጆቹ ፣ ጋራ ፣ ስለሚሠቃይ ፣ እንባው ፣ ፊቱን ፣ ጣፊያ ፣ አስመስሎታል ። ጧትም ፣ ነጋ ፣ አልነጋም ፣ ብሎ ፣ ነጠላውን ፣ ለል ጆቹ ፣ አልብሶ ፣ እሱ ፣ ትንሽ ፣ የበግ ፣ ሌጦ ፣ እትከሻው ፣ ላይ ፣ ጣል ፣ አድርጎ ፣ ማጭዱን ፣ ይዞ ፣ ብርድ ፣ እየፈደፈደው ፣ ላንድ ፣ ባለጸጋ ፣ የሞያተኛ ፣ ለማጨድ ፣ ይሄዳል ። እርሻውም ፣ ከደጋ ፣ ላይ ፣ በመሆኑ ፣ ያ ፣ የጥቅምት ፣ ውርጭ ፣ ከዒት ፣ እስከ ፣ ማታ ፣ ሲወርድበት ፣ ይውልና ፣ ቄፈን ፣ እንደ ፣ ያዘው ፣ እንድ ፣ እምስ ትና ፣ ስድስት ፣ ነዶዎች ፣ ተሰጥቶት ፣ ይመጣል ። ማታም ፣ ይህንኑ ፣ ለልጆቹ ፣ ያቀምስና ፣ በዚሁ ፣ አድሮ ፣ ይውላል ። ስለዚህ ፣ በችግር ፣ ተቈራምዶ ፣ በመኖሩ ፣ ይኸው ፣ እንዳያችሁት ፣ ከመሬት ፣ መነሣት ፣ አቅቶታል ። ወይፈን ፣ የሚያቀናው ፣ የሱ ፣ ታላቅ ፣ ደግሞ ፣ ምንም ፣ እንኳ ፣ ለሰው ፣ የሚተርፍ ፣ ሀብት ፣ ባይኖረው ፣ ራሱን ፣ ችሎ ፣ ልጆቹን ፣ እንደ ፣ ልባቸው ፣ አብልቶና ፣ አልብሶ ፣ ያድራል ። ነገር ፣ ግን ፣ ግልፍተኛና ፣ ብስጩ ፣ በመሆኑ ፣ ሸብቶ ፣ ይታያል ። እኔ ፣ ግን ፣ ክብርና ፣ ምስጋና ፣ ለፈጣሪዬ ፣ ይግባውና ፣ የናትና ፣ ያባቴ ፣ ትዳራቸው ፣

በናይለበት ፣ ጊዜ ፣ በመወለዴ ፣ ችግር ፣ ምን ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ ሳላውቅ ፣ ወተ ትና ፣ ጮማ ፣ ሳይለየኝ ፣ በመንቀባረር ፣ ትምህርቱንም ፣ እየተማርኩ ፣ ያደ ግሁ ፣ ነኝ ። በቁማቸውም ፣ ደኅና ፣ የጨዋ ፣ ልጅ ፣ ድረው ፣ ሀብታቸውን ፣ ከፍለው ፣ ሰጥተውኝ ፣ እንደ ፣ ልቤ ፣ በጌትነት ፣ ስለምኖር እንደምታዩኝ ፣ የሁለቱም ፣ ታናሽ ፣ እንጂ ፣ ታላቅ ፣ መስዬ ፣ አልታይም ። ሰውን ፣ ያለጊዜው ፣ የሚያስረጀውና ፣ የሚያገሳቍለው ፣ ሣጣት ፣ የሰው ፣ ፊት ፣ ማየት ፣ መበሳጨት ፣ መቈጨትና ፣ እነዚህን ፣ የመሳሰሉ ፣ ተቃዋሚዎች ፣ በገጠመኝ ፣ ጊዜ ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ የዕድሜ ፣ ብዛት ፣ ብቻ ፣ አይደለም ። አሁንም ፣ ስለ ፣ መጣችሁበት ፣ ጕዳይ ፣ እንዳስረዳችሁ ፣ ዘመዶቻችሁን ፣ ጎረቤቶቻችሁን ፣ ያባታችሁን ፣ የንስሓ ፣ አባትና ፣ ያናዘዙትንም ፣ ሽማግሌች ፣ ሁሉ ፣ ሰብስባችሁ ፣ ከወላጃችሁ ፣ መቃብር ፣ ዶማ ፣ ይዛችሁ ፣ ቁዩኝ ፣ አላቸው ። እነሱም ፣ ምስጋና ፣ እቅርበው ፣ ተሰናብተውት ፣ ሄዱ ።

እንደ ፣ ታዘዙትም ፣ ሁሉ ፣ ፈጽመው ፣ ሲጠባበቁ ፣ ፈላስፋው ፣ መጣና ፣ በሉ ፣ እንግዲህ ፣ ይህንን ፣ መቃብር ፣ ቈፍሩ ። አሁን ፣ አባታችሁ ፣ የኑዛዜውን ፣ ትርጕም ፣ ይገልጽላችኋል ፣ አላቸው ።

በዚህ ፣ ጊዜ ፣ እንደኛው ፣ ልጅ ፣ ርስቱም ፣ ቤቱም ፣ ከብቱም ፣ ማናቸውም ፣ አዲኛው ፣ ይቅርብኝ ፣ እንጂ ፣ ያባቴን ፣ መቃብር ፣ አልቈፍርም ፣ የትም ፣ አገር ፣ ተሰድጄ ፣ እየለመንኩ ፣ እኖራለሁ ፣ አለና ፣ እንቢ ፣ አለው ።

ሁለተኛው ፣ ደግሞ ፣ ዶማውን ፣ እኅና ፣ ጥቂት ፣ እንደ ፣ ቈፈረ ፣ እኔ ፣ ሆዴ ፣ ቡጭ ፣ ቡጭ ፣ እለብኝ ፣ አለና ፣ ተመ ። ሦስተኛው ፣ ግን ፣ እኔ ፣ ቈፍሬ፣ አስመሰክራለሁ ፣ እንጂ ፣ እንደዚሁ ፣ በከንቱ ፣ የተመረቀውን ፣ ምንዝር ፣



እኔ ፣ ቈፍሬ ፣ አስመሰክራለሁ፡ እንጂ ፣ እንደዚሁ ፣ በከንቱ ፣ የተመረቀውን ፣ ምንዝር ፣ ሆኖ ፣ ይብላ ፣ የተባለውንና ፣ የተረገመውን ፣ ሳላውቅ ፣ እል ተውም ፣ . . . . . .

ሆኖ ፡ ይብላ ፡ የተባለውንና ፡ የተረገመውን ፡ ሳላውቅ ፡ አልተውም ፡ ብሎ፡ ሰናፈሉን ፡ ባጭር ፡ ታጥቆ ፡ ሲቄፍር ፡ ድራሩን ፡ ነክው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የተማረው ፡ ምስጢር ፡ ዐዋቂው ፡ ፈላስፋ ፡ ዶማውን ፡ ተቀብሎ ፡ በሰው ፡ ሁሉ ፡ መካከል ፡ ቆሞ ፡ ንግግሩን ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ዠመረ ። ሰማችሁ ፡ ወንድሞቼ ፤ ይህ ፡ የሞተ ፡ ሰው ፡ በጣም ፡ ዕውቀት ፡ የተመላው ፡ ኖሯል ። አንዱን ፡ ልጁን ፡ መርቄዋለሁ ፡ ያለው ፡ ይህ ፡ አሁን ፡ ያባቴ ፡ ርስቱ ፡ ቤቱና ፡ ከብቱም ፡ ማናቸውም ፡ አዲኛው ፡ ይቅርብኝ ፡ ተሰድጄ ፡ እኖራለሁ ፡ እንጂ ፡ መቃብሩን ፡ አልቄፍርም ፡ ያለው ፡ ነው ። ምን ዝር ፡ የተባለው ፡ ልጁም ፤ ይህ ፡ ጥቂት ፡ ሞክሮ ፡ ሆዴ ፡ ተንበጫበጨብኝ፡ ብሎ ፡ መቄፈሩን ፡ የተወው ፡ ነው ። ቄፍሬ ፡ አስመሰክራለሁ ፡ እንጂ ፡ የተመረቀውንና ፡ ምንዝር ፡ ሆኖ ፡ ይብላ ፡ የተባለውን ፡ የተረገመውንም ፡ ሳላውቅ ፡ አልተውም ፡ ብሎ ፡ እስከ ፡ ድራሩ ፡ ድረስ ፡ የቄፈረው ፡ ግን ፡ የተረገመው ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የኑዛዜውን ፡ ትርጉም ፡ በመዘርዘር ፡ አስረዳ ። የተሰበሰቡትም ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ በሆነው ፡ ነገር ፡ ተገርመውና ፡ ተደንቀው ፡ ፈላስፋውን ፡ ከመሰገኑ ፡ በኋላ ፡ ተበታትነው ፡ ተለያዩ ፡ ይባላል ።



ሰማችሁ ፡ ወንድሞቼ ፡ ሆይ፡ ይህ ፡ የሞተ ፡ ሰው ፡ በጣም ፡ ዕውቀት ፡ የተመላው ፡ ኖሯል።

፡፡ ልጆች ፡ ሆይ ፤ በስውር ፡ ክፋ ፡ አድርጋችሁ ፡ በደባባይ ፡ ተፈርዶባችሁ፡ ውርደት ፡ ቅሌት ፡ ኀፍረት ፡ እንዳያገኛችሁ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ደግ ፡ ሠርታችሁ ፡ እንዳፈረድላችሁ ፡ መሆን ፡ ይገባችኋል ። ደግሞ ፡ መማርና ፡ ዕውቀት ፡ ማግኘት ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ለሰው ፡ የተሰወረውን ፡ ምስጢር ፡ መርምሮ ፡

ለመረዳት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በትምህርታችሁ ፡ ለመትጋትና ፡ ለመጣጣር ፡ ከመሸቀዳደም ፡ አትበዝኑ ። ከዚህም ፡ ሌላ ፡ መልከም ፡ ጉሮ ፡ ጤና ፡ አስገኝቶ ፡ የሰውን ፡ ዕድሜ ፡ የሚቀጥል ፡ መሆኑንም ፡ በለመዘንጋት ፡ ትዳርን ፡ ለማሻሻል ፡ መታገል ፡ እንደሚገባችሁ ፡ አስተውሉ ።

አንድ መነኩሴና ነብር ።

አንድ ፡ ደክማ ፡ የሆኑ ፡ መነኩሴ ፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ከዳገት ፡ ላይ ፡ ሲቄፍሩ ፡ አዳኞች ፡ የሚያባርሩት ፡ ነብር ፡ መጥቶ ፡ አባ ፡ አባክዎ ፡ አድኑኝ ፡ አላቸው ።

መነኩሲውም ፡ ከስልቻቸው ፡ ውስጥ ፡ አግብተው ፡ አጥፋቸውን ፡ አልብሰው ፡ እንደ ፡ ደበቁት ፡ አዳኞቹ ፡ መጥተው ፡ አባታችን ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ዋሉ ፡ አንድ ፡ ነብር ፡ በዚህ ፡ ሲያልፍ ፡ አላዩምን ፡ አሏቸው ።



አዳኞች ፡ የሚያባርሩት ፡ ነብር ፡ መጥቶ ፡ አባ ፡ አባክዎ ፡ አድኑኝ ፡ አላቸው ።

መነኩሴውም ፡ ልጆቹ ፡ ከቀኑፋሮዬ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ ቀና ፡ ስላላልኩ ፡ እረ ፡ አላየሁትም ፡ ሲሉ ፡ መለሱላቸው ። አዳኞቹ ፡ ከሄዱ ፡ በኋላ ፡ የማታ ፡ ማታ ፡ መነኩሴው ፡ ነብሩን ፡ እንግዲህ ፡ የሚፈልጉህ ፡ የሉም ፤ ርቀ ዋልና ፡ ተነሥተህ ፡ ጥፋ ፡ አሉም ፡ መሸቶብኛልና ፡ ወዴ ፡ ቤቴ ፡ እገባለሁ ፡

ብለው ፡ ከስልኮቹ ፡ ሲያወጡት ፡ አስረው ፡ መሜን ፡ አውለው ፡ እንዲሁ ፡ ልሄድ ፡ ነውን ፡ እርስዎን ፡ እበላለሁ ፡ እንጂ ፡ አላቸው ። ።

ከሞት ፡ በዳንኩህ ፡ ፈንታ ፡ ልትበላኝ ፡ ቢሉት ፡ አዎን ፡ አላቸው ። እንግዲያውስ ፡ አራዊት ፡ በሽንጎ ፡ ተሰብስበው ፡ ይፍረዱ ። ደግ ፡ መልካም ፡ ይፍረዱ ፡ ይፍረዱ ፡ ተባብለው ፡ አራዊት ፡ ከተሰበሰቡበት ፡ ሽንጎ ፡ ቀርበው ፡ ነገራቸውን ፡ አመለከቱ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዝንጅሮ ፡ ተነሣና ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ከስልኮ ፡ ውስጥ ፡ አሸንብተው ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ብሎ ፡ የሚመገበውን ፡ እንዳያፈልግ ፡ አስረው ፡ አውለው ፡ አሁን ፡ ምን ፡ ይሁን ፡ ብለው ፡ ነው ፡ ሊበላዎ ፡ ይገባል ፡ በማለት ፡ ፈረደባቸው ።

ፍየል ፡ ደግሞ ፡ ጠመን ፡ አውለው ፡ ምን ፡ ይብላ ፡ ብለው ፡ ነው ፡ ሊበላዎ ፡ ይገባል ፡ ብላ ፡ ፈረዱች ።

ውሻ ፡ ዥብ ፡ የቀሩትም ፡ ሁሉ ፡ በየተራቸው ፡ እየተነሡ ፡ ሊበላዎ ፡ ይገባዋል ፡ እያሉ ፡ ተቀመጡ ።

ጠጣ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ቀርታ ፡ ነበርና ፡ እንደ ፡ መጣች ፡ አየና ፡ ነብሩ ፡ ይዝሙልሽ ፡ እንኩዬ ፡ ጠጢት ፡ ጠሜን ፡ አውለው ፡ ማታ ፡ ሂድ ፡ አሉኝ ፡ ይሸንን ፡ ፍርድ ፡ እስቲ ፡ አንቺ ፡ እዩልኝ ፡ አላት ። ወንድሜ ፡ አያ ፡ ነብሮ ፡ እኔ ፡ ከነፍ ፡ ላይ ፡ እንጂ ፡ ከምድር ፡ ተቀምፌ ፡ መፍረድ ፡ አላሙቅም ፡ አለችው ። አሱም ፡ እንደ ፡ ፈቀድሽ ፡ የትም ፡ ሁኚ ፡ ግድ ፡ የለም ፡ ከነፋም ፡ ከሆነ ፡ ነገሩ ፡ በዪ ፡ ውሬና ፡ ፍረጂ ፡ አላት ።

ከነፋ ፡ ላይ ፡ ወጣችና ፡ አባ ፡ አያ ፡ ነብሮን ፡ ከዳኞች ፡ እኔ ፡ አዳንኩት ፡ እያሉ ፡ የሚፎክሩት ፡ እንዲት ፡ አድርገው ፡ ነው ፡ እርስዎ ፡ ደህማ ፡ ነዎት ፡ እርሱ ፡ ግን ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ሁሉን ፡ የሚያንቀጠቅጥና ፡ የሚያሸንፍ ፡ ጐበዝ ፡ ነው ፡ እረ ፡ ለነገሩ ፡ በእንዲት ፡ ያለ ፡ አኳኋን ፡ ነው ፡ ያዳኑት ፡ እንጂ ፡ እውነት ፡ አይመስለኝም ፡ እስቲ ፡ ለመሆኑ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ አድርገው ፡ እንደ ፡ ሸሸጉት ፡ ያሰዩኝ ፡ አለኮቹ ።

መነሱሴውም ፡ ይዝሙልሽ ፡ እንኩዬ ፡ ጠጢት ፡ እንደዚህ ፡ አድርጌ ፡ ነው ፡ ያዳንኩት ፡ አሉና ፡ ከስልኮቹው ፡ ውስጥ ፡ አግቡተው ፡ አጥፋቸውን ፡ አልብሰው ፡ ቢያሳዩዋት ፡ አባ ፡ እንግዲህ ፡ አባ ፡ እንግዲህ ፡ አለኮቹው ።

ቀና ፡ ብለው ፡ አየት ፡ ቢያደርጓት ፡ የስልኮውን ፡ አፍ ፡ አስረው ፡ ይደብድቡት ፡ በማለት ፡ አመለከቱኮቹው ። እሳቸውም ፡ እንዳሰየኮቹው ፡ አቁማዳውን ፡ አስረው ፡ ጎይለኛውን ፡ በለጋሬ ፡ በቂመጥ ፡ ነርተው ፡ ገደሉት ፡ ይባላል ።



እስቲ ፡ ለመሆኑ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ አድርገው ፡ እንደ ፡ ሸሸጉት ፡ ያሳዩኝ ።

፠ በፍርድ ፡ ላይ ፡ መፍራትና ፡ ማድላት ፡ አይገባም ። ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ለተንኰለኛ ፡ ሰው ፡ ደግ ፡ ቢሠሩለት ፡ ሸሩን ፡ አይተውም ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ፍርድ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነውና ፡ ተንኰሉ ፡ ያጠፋዋል ።

ሰለ ፡ አንዲት ፡ ገበያተኛ ፡ ሴት ።

አንዲት ፡ ሴትኛ ፡ አዳሪ ፡ ገበያ ፡ ወጥታ ፡ ወደ ፡ ቤቷ ፡ ስትመለስ ፡ ከመንገድ ፡ ዳር ፡ አንድ ፡ ማሽላ ፡ ጠባቂ ፡ አገኘችና ፡ ሰላምታ ፡ ሰጠችው ። አሱም ፡ አኳቴ ፡ ሆይ ፡ ዛሬ ፡ አንቺ ፡ ዘንድ ፡ መጥቼ ፡ ነውና ፡ እራቴን ፡ የምበላው ፡ ተዘጋጅተሽ ፡ እንድትቄዪኝ ፡ አላት ። እሷም ፡ እሺ ፡ ወንድሜ ፡ እንዳልክ ፡ ፈቃድህን ፡ እፈጽማለሁ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የማሽላ ፡ እሸት ፡ አምሮኛልና ፡ አንድ ፡ ሸክም ፡ ይዘህልኝ ፡ ና ፡ አለችውና ፡ መንገዷን ፡ ቀጠለች ። ሁለተኛ ፡ ደግሞ ፡

አንድ ፣ የፍየል ፣ እረኛ ፣ አገኘችና ፣ እሱም ፣ እንደዚያው ፣ እንደ ፣ ፈተኛው ፣ ሰውዬ ፣ ዛሬ ፣ አዳሬ ፣ ካንቺ ፣ ዘንድ ፣ ነውና ፣ እንድትጠብቂኝ ፣ አላት ። አሁንም ፣ እሺ ፣ ወንድሜ ፣ እንደ ፣ ፈቃድህ ፣ ነገር ፣ ግን ፣ ሥጋ ፣ አምሮኛልና ፣ ከነዚህ ፣ ከፍየሎችህ ፣ አንድ ፣ ደኅና ፣ ጠቦት ፣ ይዘህልኝ ፣ እንድትመጣ ፣ አለችው ።

ከሱም ፣ አጠገብ ፣ ገና ፣ ምንም ፣ ያክል ፣ ያትርቅ ፣ አንድ ፣ የላሞች ፣ እረኛ ፣ አገኘች ። ለዚህም ፣ ሰላምታ ፣ ሰጥታው ፣ አለና ፣ ስትል ፣ አንቺ ፣ ሴት ፣ እስቲ ፣ እባክሽ ፣ ቄዩኝ ፣ አንድ ፣ የምንግርሽ ፣ ጉዳይ ፣ አለኝ ፣ አላት ።እሷም ፣ ወደርሱ ፣ መለስ ፣ ብላ ፣ ወንድሜ ፣ ምነው ፣ በደኅና ፣ ነውን ፣ ቄዩኝ ፣ የምትለኝ ፣ ስትል ፣ ጠየቀችው ፣ ጉዳዩስ ፣ ቀላል ፣ ነው ፣ እኅቴ ፣ ሆይ ፣ ዛሬ ፣ እራቴን ፣ ካንቺ ፣ ቤት ፣ ለመብላት ፣ አስቢያለሁና ፣ ፈቃድ ፣ ታደርጊልኝ ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ ብዬ ፣ ነው ፣ ብሎ ፣ መለሰላት ። ምን ፣ ቸገረኝ ፣ ነገር ፣ ግን ፣ ወተት ፣ ስላማረኝ ፣ እንተ ፣ ይኸው ፣ እንዳየሁህ ፣ ባለጠጡ ፣ ላሞች ፣ ነህና ፣ አንድ ፣ ቅል ፣ ርጎ ፣ ይዘህልኝ ፣ እንድትመጣ ፣ እኔም ፣ ተደራጅቼ ፣ እጠብቅ ሃለሁ ፣ በማለት ፣ ሸንግላው ፣ ሄደች ።

አራተኛ ፣ ደግሞ ፣ አንድ ፣ ዱግ ፣ ሠጋር ፣ ዘሆነች ፣ በቅሎ ፣ ተቀምጦ ፣ እሸከሩን ፣ ነፍጥ ፣ አሲዞ ፣ ሲያሠግር ፣ ደረሰባት ። ከወዴት ፣ ትመጫለሽ ፣ ብሎ ፣ ጠየቃት ። እሷም ፣ ከገበያ ፣ ነው ፣ ጌታዬ ፣ ብላ ፣ መልሳለት ፣ እየተጨዋወዙ ፣ ጥቂት ፣ መንገድ ፣ እንደ ፣ ተጓዙ ፣ ሰሌውን ፣ ከበቅሎ ፣ ላይ ፣ አውጣት ፣ እለውና ፣ አፈናጠጧት ፣ እስከ ፣ ቤቷ ፣ ድረስ ፣ ይዟት ፣ ሄደ ። እንግዲህ ፣ ግን ፣ መጥቼ ፣ ከዚሁ ፣ ቤት ፣ እራት ፣ እበላለሁና ፣ ከሌላ ፣ ሰው ፣ እንዳትጋገሪ ፣ አሁን ፣ ግን ፣ ወደ ፣ ቤቴ ፣ ደርሻ ፣ ልምጣ ፣ አላት ። ጥቂት ፣ ቂይቶም ፣ ጊዜው ፣ መምሸት ፣ ስለ ፣ ገፆረ ፣ ያ ፣ ከገበያ ፣ ስትመጣ ፣ የቀጠረችው ፣ እኽል ፣ ጠበቂ ፣ እንዳዘዘችው ፣ አንድ ፣ ሸክም ፣ የማሽላ ፣ እሸት ፣ ተሸክሞ ፣ መጣ ። እሷም ፣ የያዘውን ፣ ከተቀበለች ፣ በኋላ ፣ ሰውዩውን ፣ ከማጀት ፣ ገብቶ ፣ እንዲቀመጥ ፣ አደረገችው ። ከሱ ፣ በኋላ ፣ ደግሞ ፣ ያ ፣ የፍየል ፣ እረኛ ፣ መልክም ፣ ሰናፊል ፣ አጥልቆ ፣ ረዥም ፣ ጥብቆ ፣ ለብሶ ፣ ድጉን ፣ ታጥቆ ፣ ኩታውን ፣ አጣፍቶ ፣ ፍየል ፣ እየሳበ ፣ መጣ ። እሱንም ፣ ከብቱን ፣ ተረከበችና ፣ ከድብኝት ፣ ውስጥ ፣ ደበቀችው ። ሦስተኛው ፣ በለላሙ ፣ ርጎውን ፣ ይዘላት ፣ ደረሰ ፣ የወተቱንም ፣ ቅል ፣ ተቀብላ ፣ ከማዘንቱ ፣ በላይ ፣ ከውሲያኑ ፣ ላይ ፣ ከሰቀለች ፣ በኋላ ፣ ሰውየውን ፣ ከልጋ ፣ ሥር ፣ አስገብታ ፣ ሸሸገችው ።

በመጨረሻው ፣ በበቅሎ ፣ ይዟት ፣ የመጣው ፣ መኰንን ፣ እሸከሩን ፣ አስከትሎ ፣ ነፍጡን ፣ አሲዞ ፣ ከተፍ ፣ አለ ። እሷም ፣ ቤቷን ፣ አንጥፋ ፣ ተዘጋጅታ ፣ ትጠብቀው ፣ ስለ ፣ ነበረ ፣ ርጎ ፣ የያዘው ፣ ጨርሶ ፣ ከተሰቀለበት ፣ በታች ፣ ማዘንቱ ፣ ላይ ፣ አስቀመጠችው ።

ጥቂት ፣ ጨዋወት ፣ እንደ ፣ ያዙም ፣ ያ ፣ ማሽላ ፣ ጠዛቂ ፣ አረኝ ፣ ላረኝ ፣ ከጠጣና ፣ ከዝንጅሮ ፣ ጋራ ፣ ወዲያና ፣ ወዲህ ፣ ሲሮጥ ፣ በመዋሉ ፣ ደክሞት ፣ እንቅልፍ ፣ ይዞት ፣ ኖሮ ፣ ከማጅት ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ ሲቃኝ ፣ ተው ፣ በር ፣ በሩን ፣ ቅደመው ፣ አለ ። በዚህ ፣ ጊዜ ፣ ዱባ ፣ ተነሥቶ ፣ እሸሽለሁ ፣ ሲል ፣ የተሰቀ



ርጎው ፣ በጭንቅላቱ ፣ ላይ ፣ ተከለበሰበት ።

ለውን ፣ የወተት ፣ ቅል ፣ በራሱ ፣ ስለ ፣ መታው ፣ ርጎው ፣ በጭንቅላቱ ፣ ላይ ፣ ተከለበሰበት ። ተደናግሞም ፣ ነፍጡን ፣ እንኳ ፣ ሳይገ ፣ ከነሎሌው ፣ ፈረጠጠ። ባለፍየሉም ፣ ድብኝቱን ፣ በታትኖ ፣ ኩታውን ፣ ጥሎ ፣ አውጫኝ ፣ እግሬ ፣ አለ ። በለወተቱም ፣ ከተሸሸገበት ፣ ብድግ ፣ እላለሁ ፣ ሲል ፣ አልጋውን ፣ እንሥቶ ፣ ዘውሃ ፣ እንስራውና ፣ በቡሖ ፣ ሰቃው ፣ ላይ ፣ ስለ ፣ ጣለው ፣ ሸክላው ፣ እንክትክት ፣ ስብርባር ፣ ብሎ ፣ ገል ፣ ዐፈር ፣ ሆነ ። መውጫውም ፣ ጠፍ ፣ ቶበት ፣ ሲደናበር ፣ መዝጊያውን ፣ ከሥር ፣ ሰቅስቆ ፣ ወንዱውን ፣ ነቅሎ ፣ እልም ፣ ብሎ ፣ ጠፋ ።

ያ ፣ ወተት ፣ የተደፋበት ፣ ሹም ፣ ነፍጡን ፣ ጥሎ ፣ ነፍሱን ፣ አጥቶ ፣ እየተክነፈፈ ፣ ከሮጠ ፣ በኋላ ፣ ከመንገድ ፣ አሸከሩን ፣ አንተ ፣ ራሴን ፣ ተመት ፮ለሁና ፣ እስቲ ፣ እባክህ ፣ ጉድጉኝ ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ ቆም ፣ ብለህ ፣ አይተህ ፣ ንገረኝ ፣ አለው ። ሎሌውም ፣ ጭንቅላቱ ፣ ነጭ ፣ ነገር ፣ ለብሶ ፣ አየና ፣ እረ ፣

ጌታዬ ፡ ምንም ፡ አልተረፉ ፡ ደምዎ ፡ አልቆ ፡ አንጐልዎ ፡ ወጥቷል ፤ እንዲ ያውም ፡ የሚያድኑ ፡ አይመስልም ፤ አሁን ፡ ግን ፡ በጠላት ፡ እጅ ፡ ከምንገባ፡ እናምልጥ ፡ ብሎ ፡ ሽሽታቸውን ፡ ቀጠሉ ።

በለፍየሉም ፤ በለወተቱም ፡ እንዲሁ ፡ እየተከታተሉ ፡ ሄዱና ፡ ያው ፡ በፊት ፡ ያገኛት ፡ ባለማሽላው ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ቀረ ። አሱም ፡ ይህንን ፡ ፍጅትና ፡ ሽብር ፡ ሳይሰማ ፡ ቄይቶ ፡ በመጨረሻው ፡ ከአንቅልፉ ፡ ከነታ ፡ በኋላ ፡ ከዚ

ኖ



ባለፍየሉም ፡ ባለወተቱም ፡ እንዲሁ ፡ እየተከታተሉ ፡ ሄዱና ፡ ያው ፡ በፊት ፡ ያገኛት ፡ ባለማሽላው ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ቀረ ።

ያች ፡ ሴት ፡ ቤት ፡ አድሮ ፡ በማግስቱ ፡ ጧት ፡ አፉን ፡ አሟሽቶ ፡ ወደ ፡ ማሽላ ፡ ጥበቃው ፡ ተነሥቶ ፡ ሄደ ፡ ይባላል ፡

※ ማናቸውም ፡ ቢሆን ፡ ለሮጠም ፡ ለተሸቀዳደመም ፡ ለቸኰለም ፡ ሳይ ሆን ፡ ዕድሉ ፡ ለፈቀደለት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የሚሆነው ።

የሰው ፡ ገንዘብ ፡ የወሰዱና ፡ ሰው ፡ በግፍ ፡ የገደሉ ፡ ወንበዴዎች ።

በየጊዜው ፡ የግፍ ፡ ሥራ ፡ በመሥራት ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚያስቀ ይሙ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ። ከነዚህም ፡ አንደኛው ፡ ደግና ፡ የሆነውን ፡ ንጹሕ ፡ ሰው ፡ በልሠራው ፡ ሥራ ፡ በግፍ ፡ ገድሎ ፡ ደሙም ፡ በክንቱ ፡ በጉማ ፡

ተረሳስቶ ፡ እንዲቀር ፡ ያደረገ ፡ ሲሆን ፡ ሁለተኛው ፡ ደግሞ ፡ የሰው ፡ ገን ዘብ ፡ አጭበርብሮ ፡ ሰውሮ ፡ የበላ ፡ ነበር ።

ሁለቱም ፡ ግፈኞች ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ በሞት ፡ ተለዩ ። ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀንም ፡ የዚያ ፡ የሰውን ፡ ገንዘብ ፡ ሰውሮ ፡ የበላ ፡ ሰው ፡ ልጅ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ በስልቻ ፡ ቋጥሮ ፡ ተሸክሞ ፡ ወደ ፡ ንግድ ፡ ሄደ ። ብዙ ፡ ቀንም ፡ ሲጓዝ ፡ ከቄየ ፡ በኋላ ፡ በመጨረሻው ፡ ካንዲት ፡ ምንሴ ፡ አጠገብ ፡ ምሳውን ፡ በላና ፡ ሲነሣ ፡ ያንን ፡ ብር ፡ ረስቶት ፡ ሄደ ። ገንዘቡንም ፡ ተላላፊ ፡ መንገደኛ ፡ አን ሥቶ ፡ ወሰደው ። ጥቂት ፡ እንደ ፡ ቄየም ፡ ባለገንዘቡ ፡ ዕቃ ፡ መርሳቱ ፡ ትዝ ፡ ብሎት ፡ እየሮጠ ፡ ቢመለስ ፡ የዚያ ፡ በግፍ ፡ ነፍስ ፡ ገድሎ ፡ የነበረው ፡ ሰው ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ሥራ ፡ ሲሄድ ፡ ከዚያው ፡ ከምንሴ ፡ አጠገብ ፡ ዐርፎ ፡ ምሳውን ፡ ሲበላ ፡ አገኘው ። እንደ ፡ ደረሰም ፡ አንተ ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ ቦታ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ረስቼ ፡ ሄጀ ፡ ነበረ ፡ እኔ ፡ ታለፍኩ ፡ ወዲህ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ በዚህ ፡ መንገድ ፡ ከቶ ፡ አልተከተለኝም ፡ ወይም ፡ አልፎኝ ፡ አልሄደም ፡ ያነ ሣኸው ፡ አንተ ፡ ሳትሆን ፡ አትቀርምና ፡ መልስልኝ ፡ አለው ። እሱም ፡ ደን ግጦ ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጠርቶ ፡ አልወሰድኩም ፡ አለው ። ባለገን ዘቡ ፡ ግን ፡ ሰውቀቱ ፡ የጸጋ ፡ በመሆኑ ፡ መለሳውን ፡ ሳይቀበለው ፡ ቀርቶ ፡ በጦር ፡ ወግቶ ፡ አሠቃይቶ ፡ ገደለው ።



መሐሳውን ፡ ሳይቀበለው ፡ ቀርቶ ፡ በጦር ፡ ወግቶ ፡ አሠቃይቶ ፡ ገደለው ።

ይህም ፡ ስፍራ ፡ ጫካነት ፡ ያለው ፡ የግሑሣን ፡ በታ ፡ ኖሮ ፡ ሐሩረ ፡ መዓልትን ፡ ቍረ ፡ ሌሊትን ፡ ግርማ ፡ ጽልመትን ፡ ዩምፀ ፡ አራዊትን ፡ ታግሦ ፡ ለርዕየት ፡ ሀያንም ፡ ተሰውሮ ፡ የሚኖር ፡ አንድ ፡ ቢሕታዊ ፡ የተደረገውን ፡

ተመለከተ ። መናኒውም ፡ ይህንን ፡ ሁሉ ፡ የግፍ ፡ ሥራ ፡ አየና ፡ እኔ ፡ ለሁሉም ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ ዋጋውን ፡ የምትከፍል ፡ አምላክ ፡ ነህ ፡ ብዬ ፡ ከወገኖቹ ፡ ተለይቼ ፡ እንደዚህ ፡ ስደክምና ፡ ስንገላታ ፡ ለካስ ፡ ሰው ፡ በልሠራው ፡ ሥራ ፡ እንዲሞት ፡ ታደርጋለህ ፡ በላየው ፡ በላደረገው ፡ የምታጠፋ ፡ ከሆንክ ፡ አንተን ፡ ለማገልገል ፡ ምን ፡ ያታክተኛል ፡ ብሎ ፡ በአቡነ ፡ ለቆ ፡ ለመሄድ ፡ ሲሞክር ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጠርቶ ፡ አንተ ፡ ደካማ ፡ ፍጡር ፡



አንተ ፡ ደካማ ፡ ፍጡር ፡ እግዚአብሔር ፡ በባሕርይ ፡ ዕውቀቱ ፡ የፈጸመውን ፡ ፍርድ ፡ ትቃወማለህን ፤

እግዚአብሔር ፡ በባሕርይ ፡ ዕውቀቱ ፡ የፈጸመውን ፡ ፍርድ ፡ ትቃወማለህን ፤ ፍጡር ፡ ሆይ ፡ አስተውል ፡ የዚህ ፡ የሚች ፡ ሰው ፡ አበት ፡ ሰው ፡ በግፍ ፡ አስፈጨንቆና ፡ አሠቃይቶ ፡ ገድሎ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ የፍርዱ ፡ በለቤት ፡ እግዚአብሔር ፡ ፍጻውን ፡ በልጁ ፡ መክፈሉ ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ የዚህ ፡ ገንዘብ ፡ የጠፋበት ፡ ሰው ፡ አባት ፡ የሰው ፡ ገንዘብ ፡ ሰውሮ ፡ በልቶ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ የሱን ፡ ብድር ፡ በልጁ ፡ መፈጸሙ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ አንተ ፡ በማታውቀው ፡ ምስጢር ፡ የአምላክን ፡ ፍርድ ፡ መቃወም ፡ የለብህምና ፡ ወደ ፡ ቀድሞ ፡ አገልግሎትህ ፡ ተመለስ ፡ ብሎ ፡ ምስጢሩን ፡ አስረድቶ ፡ ወደ ፡ በአቡ ፡ መለሰው ፡ ይበላል ።

* ብድር ፡ አይቀር ፡ በምድር ፡ የተበለው ፡ እውነተኛ ፡ መሆኑን ፡ ከተገነዘብን ፡ በኋላ ፡ በንጹሓን ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ለሚደረገው ፡ ግፍ ፡ ተቢቃዩ ፡ እግዚአብሔር ፡ መሆኑን ፡ ማመን ፡ ይገባናል ።

ያንድ ፡ ሽማግሌ ፡ ምርቃት ።

በንድ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ግብረ ፡ ገብ ፡ የሆኑ ፡ ብዙ ፡ ልጆች ፡ ያሏቸው ፡ አንድ ፡ ሽማግሌ ፡ ነበሩ ።

ሰው ፡ ሆኖ ፡ ዙሮ ፡ ዙሮ ፡ ከቤት ፡ ኑሮ ፡ ኑሮ ፡ ከመሬት ፡ የማይቀር ፡ ስለሆነ ፡ በእርጅናቸው ፡ ምክንያት ፡ ጊዜ ፡ ሞታቸው ፡ መቃረቡን ፡ ስለ ፡ ተረዱት ፡ ልጆቻቸውን ፡ ጠርተው ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ የመሰናበቻ ፡ ንግግር ፡ አደረጉ ።

ቃሉም ፡ ልጆቼ ፡ ሆይ ፡ ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ ኑሮ ፡ በምፈጽምበት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ትዳሬ ፡ ሳይጐድል ፡ እናንተን ፡ በማግኘቴና ፡ ለቁም ፡ ነገርም ፡ በማብቃቴ ፡ የሚሰማኝ ፡ ደስታ ፡ ወሰን ፡ የለውም ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ እናንተም ፡ ከደረሳችሁልኝ ፡ ጊዜ ፡ ዝምሮ ፡ በግብረ ፡ ገብነት ፡ ያደረጋችሁልኝ ፡ ርዳታ ፡ ቀላል ፡ በለመሆኑ ፡ አስተዳደራችንን ፡ በጣም ፡ ደግፎታል ። ስለዚህም ፡ ሞት ፡ ሌባ ፡ ነውና ፡ የሚመጣበት ፡ ሰዓት ፡ ስለማይታወቅ ፡ አስቀድሜ ፡ ተሰናብቻችሁ ፡ እንድቂይ ፡ በማለት ፡ ነው ፡ የጠራኋችሁ ፡ የሚል ፡ ነበር ። ሁሉም ፡ በተርታ ፡ ከፊታቸው ፡ እንደ ፡ ቆመ ፡ ንግግራቸውን ፡ በመቀጠል ፡ ልጆቼን ፡ በሙሉ ፡ ስለምወዳችሁ ፡ በረከቱ ፡ በሁላችሁም ፡ ላይ ፡ ይደር ፡ ፍቅር ፡ ለናንተ ፡ ይሁን ፤ ያለኝንም ፡ ሀብቴንና ፡ ንብረቴን ፡ ሁሉ ፡ እኩል ፡ አድርጋችሁ ፡ ተካፈሉ ። ይሁን ፡ አንጂ ፡ አንዲ ፡ ጣት ፡ ከንዲት ፡ እንደምትበልጥ ፡ ለዚህ ፡ ለታላቁ ፡ ወንድማችሁ ፡ በተለይ ፡ አገልግሎት ፡ ስላለው ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ምርቃት ፡ አሰጠዋለሁ ። ልጄ ፡ ሆይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለቀደሙ ፡ አባታችንና ፡ እናታችን ፡ ለአዳምና ፡ ሔዋን ፡ ብዝኑ ፡ ወተባዝኑ ፡ ወምልአዋ ፡ ለምድር ፡ ብሎ ፡ የሰጠውን ፡ ትእዛዝ ፡ ስፈጽም ፡ መገሥፈሪያ ፡ አንተን ፡ በማግኘቴ ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ የተሰማኝ ፡ ደስታ ፡ እስከ ፡ ዕለት ፡ መቃብር ፡ አይዘነጋኝም ። ከልጆቼ ፡ ቀደም ፡ ብለህ ፡ ለአእምሮ ፡ ከደረስክበት ፡ ጊዜ ፡ ዝምሮ ፡ ያደረግኸልኝ ፡ አገልግሎት ፤ ፍጹም ፡ ቅንነት ፡ የተመላበትና ፡ እጅግ ፡ አስደሳች ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ አንደኛ ፡ ብልኀትና ፡ ምክንያት ፡ የሴትን ፡ ሁለተኛ ፡ ጉልበት ፡ የጉንዳንን ፡ ሦስተኛ ፡ መብል ፡ የአንበጣን ፡ ይስጥህ ። ከገንዘቤም ፡ የእልቅናህን ፡ የምቀመጥበትን ፡ ግርንቡድ ፡ ውስድ ፡ ብለው ፡ መረቁት ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ንግግራቸውን ፡ አቁመው ፡ ሁሉንም ፡ አሰናበቷቸው ።

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ያ ፡ የበኽር ፡ ልጅ ፤ አባቴ ፡ ጕልበት ፡ የጕን
ዳንን ፡ ብልኀትና ፡ ምክንያት ፡ የሴትን ፡ መብል ፡ የአንበጣን ፡ ይስጥህ ፡ ከገ
ንዘቤም ፡ የአልቅናህን ፡ የምቀመጥበትን ፡ ግርንቡድ ፡ ውሰድ ፡ ሰጥቼሃለሁ ፡
ያለኝ ፡ ከጕንዳንስ ፡ ያነሰ ፡ ምን ፡ ዐቅም ፡ ኖሮ ፡ ነው ፡ ከሴት ፡ አእምሮ ፡



ብልኀትና ፡ ምክንያት ፡ የሴትን ፡ ጕልበት ፡ የጕ
ንዳንን ፡ መብል ፡ የአንበጣን ፡ ከገንዘቤም ፡ የል
ቅናህን ፡ የምቀመጥበትን ፡ ግርንቡድ ፡ ውሰድ ፡

የደከመስ ፡ ምን ፡ ተገኝቶ ፡ ነው ፡ መብልስ ፡ የአንበጣን ፡ ያለኝ ፡ ከአንበጣ ፡ ያነሰ ፡
ሆድ ፡ ምን ፡ አለና ፡ ነው ፡ ስለ ፡ አልቅናውስ ፡ ግርንቡድ ፡ ሰጠሁህ ፡ ያለኝ ፡
ደግሞ ፡ ከሰ ፡ ያነሰ ፡ ምን ፡ ዕቃ ፡ ኖሮ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ አዝኖና ፡ ተክዘ
በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ ብቻ ፡ ወደ ፡ ስደት ፡ ሲሄድ ፡ ሰለ ፡ አንድ ፡ የ-ተማሩ ፡
አረጋዊ ፡ ቄስ ፡ በመንገድ ፡ አገኘ ። እኒህም ፡ ሽማግሌ ፡ አንዴት ፡ አደርክ ፡
ወንድሜ ፡ ወዴትስ ፡ ትሄዳለህ ፡ ብለው ፡ ጠየቁት ። እሱም ፡ አባቴን ፡ በቅን
ነት ፡ ሰገለግል ፡ ኖሬ ፡ በመጨረሻው ፡ ጕልበት ፡ የጕንዳንን ፡ ብልኀትና ፡
ምክንያት ፡ የሴትን ፡ መብል ፡ የአንበጣን ፡ ይስጥህ ፡ ብሎ ፡ ስለ ፡ ረገመኝ ፡
ደግሞ ፡ ከገንዘቤ ፡ ስለ ፡ አልቅናህ ፡ የምቀመጥበትን ፡ ግርንቡድ ፡ ሰጥቼሃለሁ ፡
ስላለኝ ፡ ከሀገር ፡ ተሰድጄ ፡ መሄዴ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መለሰላቸው ። ቄሱም ፡
ይህን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ አባትህ ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ አደርገው ፡ መረቁህ ፡ እንጂ ፡
አልረገሙህም ፡ ስለዚህም ፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ አሰጥሃለሁና ፡ ተመለስ ፡ ብለው ፡

ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ይዘውት ፡ ሲጓዙ ፡ ጕንዳን ፡ በለበት ፡ ቀበሌ ፡ ደረሱ ። በዚህ ፡
ጊዜ ፡ አንዱ ፡ ያንዱን ፡ ጕንዳን ፡ ሬሳ ፡ ብቻ ፡ ለብቻ ፡ ተሸክሞ ፡ ሲሮጥ ፡
አዩተው ፡ ይኸውልህ ፡ ይህች ፡ ጕንዳን ፡ የጓደኛዋን ፡ ሬሳ ፡ ይዛ ፡ ስትሮጥ ፡
ትመለከታለህን ፡ እስቲ ፡ ተችል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እኔን ፡ ከመሬት ፡ አንሥተህ ፡
ከትከሻህ ፡ ላይ ፡ አድርገኝ ፡ ብለው ፡ እንደ ፡ ሬሳ ፡ ዝርግት ፡ ብለው ፡ ተኙ ።
ለመሸከም ፡ ቢሞክር ፡ ማንሣት ፡ ተሣነው ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቄሱ ፡ ያባትህን
ምርቃት ፡ ብትቀበለውና ፡ ቢደርስህ ፡ ኖሮ ፡ አንሥተኸኝ ፡ ትሮጥ ፡ ነበር ፤
ደግሞ ፡ ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ማስረጃ ፡ ልሰጥህ ፡ እችላለሁ ፡ ብለው ፡ ይዘውት ፡
ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ሄዱና ፡ ለሚስታቸው ፡ ይኸውልሽ ፡ የአግዚአብሔርን ፡ እን
ግዳ ፡ ይዤልሽ ፡ መጣሁ ፡ አሏት ። እሷም ፡ ይህንን ፡ ከመስማቷ ፡ ወዲያው ፡
ምግብ ፡ አሰናድታ ፡ አቀረበችላቸው ። ቀጥሎም ፡ ባዶሬ ፡ መጠጥ ፡ ብታ
መጣላቸው ፡ ከነገቹ ፡ ካልቀረበ ፡ አይዘልቅንም ፡ ስላሏት ፡ ወደ ፡ ማጀት ፡
ገባች ። እንግዳውን ፡ ሰውዬ ፡ በል ፡ ተከትለህ ፡ ወደ ፡ ጓዳ ፡ ግቢና ፡ ጋን ፡
ስታነሣ ፡ ርዳት ፡ ደግሞ ፡ ጕንበስ ፡ ስትል ፡ አይተህ ፡ ድብን ፡ አድርገህ ፡
ቄንጥጣት ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የምታመጣውን ፡ ምክንያት ፡ ታያለህ ፡ ብለው ፡
ካህኑ ፡ በምስጢር ፡ መከሩት ።

እሱም ፡ ተከትሎ ፡ ገባና ፡ የጠላውን ፡ ዕቃ ፡ ለማንሣት ፡ ስታጕነብስ ፡
ድብን ፡ አድርጎ ፡ ቄንጠጣት ፡ ሲቲቱም ፡ ደንግጣ ፡ ቃሏን ፡ አሰምታ ፡ ውይ ፡
ብላ ፡ ጮኸች ። ቄሱ ፡ ምን ፡ ሆንሽ ፡ ብለው ፡ ቢጠይቋት ፡ የማርያምን ፡ ገች ፡
አነሣለሁ ፡ ብሎ ፡ ያበን ፡ ጋን ፡ አነሣዋ ፡ ብላ ፡ መለሰችላቸው ። የተፈለገ
ውና ፡ የተጠየቀው ፡ ሁሉ ፡ ቀርቦ ፡ ግብገባው ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ እንግዳ
ውን ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ሲሸኙት ፡ አየኻት ፡ ወንድሜ ፡ ይህቺ ፡ ሴት ፡ ድንገት ፡
የመለሰችውን ፡ መልስ ፡ አንተም ፡ ያባትህ ፡ ምርቃት ፡ ቢደርስህ ፡ እንደ
ዚሁ ፡ ድንገት ፡ ስትጠየቅ ፡ በቂ ፡ መልስ ፡ ለማግኘት ፡ በቻልክ ። መብል ፡
የአንበጣን ፡ ይስጥህ ፡ ያሉህ ፡ አንበጣ ፡ አፈቱ ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ በልቶ ፡
ጨና ፡ ይሆነዋል ፡ አይቄርጠውም ፡ አይፈልጠውም ፡ አንተም ፡ ያባትህ ፡
ምርቃት ፡ ቢደርስህ ፡ የተገኘውን ፡ ጥሬውንም ፡ ብስሉንም ፡ በልተህ ፡ ሙሉ ፡
ጤና ፡ ታገኝ ፡ ነበር ። ስለ ፡ አልቅናህም ፡ መቀመጫዬን ፡ ግርንቡድ ፡ ውሰድ ፡
ሰጥቼሃለሁ ፡ ያሉህ ፡ በውስጡ ፡ ጠቃሚ ፡ ነገር ፡ አኑረውበት ፡ ይሆናል ። ስለ
ዚህ ፡ አባትህ ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፡ አልቀው ፡ መርቀውሃልና ፡ ወደ ፡ ቤትህ ፡ ግባ ፡
ብለው ፡ አስረድተውት ፡ በደስታ ፡ ጨዳገሩ ፡ ተመለሰ ። ሄዶም ፡ ያንን ፡ ያባቱን ፡


ግርንቡድ ፡ ቢፈልጠው ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ወቄት ፡ ወርቅ ፡ ስላገኘበት ፡ ቄሱ ን ፡ አመስግኖ ፡ ያባቱን ፡ ዕዕም ፡ እየመረቀ ፡ በደኅና ፡ ቤቱንና ፡ ንብረ ቱን ፡ አዘጋጅቶ ፡ ኖረ ፡ ይባላል ።

። ልጆች ፡ ሆይ ፡ በውል ፡ መርምሮ ፡ ሳያውቁ ፡ ያባትን ፡ ስጦታና ፡ ምር ቃት ፡ ማቃለልና ፡ መንቀፍ ፡ ታላቅ ፡ ኀጢአት ፡ ነው ፡ ደግሞ ፡ ባልተረዱ ትና ፡ ባልተገነዘቡት ፡ ነገር ፡ በከንቱ ፡ ሚሚረር ፡ ከሳ ፡ ያለ ፡ ስሕተት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ከእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ሁሉ ፡ መጠንቀቅ ፡ ይገባል ።

ያንድ ፡ ሽኮብ ፡ ሞት ።

አንድ ፡ አሮጌ ፡ ሽኮብና ፡ ልጅቱ ፡ ማንሾለላና ፡ መዝሩጥ ፡ አብረው ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ሲሄዱ ፡ አንድ ፡ ወይል፡ አህያ ፡ አግኝተው፡ ተረዳድተው፡ ዘርጥጠው ፡ ጣሉት ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አባትየው ፡ ልጆቹን ፡ አባሮ ፡ ለብቻው ፡ ይበላ ፡ ዠመር ። በልቶም ፡ ጠገብ ፡ ሲል ፡ ለማንሾለላ ፡ አንድ ፡ ዠሮ ፡ ሰጠው ። ለመዝሩጥ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ሳይሰጠው ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ሲበላ ፡ አባታችን ፡ እረ ፡ ኒ ፡ አሉት ።



አባትየው ፡ ልጆቹን ፡ አባሮ ፡ ለብቻው ፡ ይበላ ፡ ዠመር ።

ተዉ ፡ ቄዩ ፡ ግድ ፡ የለም ፡ የፌረቃን ፡ ንጋትና ፡ ያህያን ፡ ሥባት ፡ የማ ውቅ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ እናንተ ፡ አታውቁም ፡ እያለ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ሲዘላ ፡ ኒጋ ። ከኒጋም ፡ በኋላ ፡ ያህያው ፡ ባለቤት ፡ መጣና ፡ ሲያሳድዳቸው ፡ ልጆቹ ፡ አባታ ቸውን ፡ ጥለውት ፡ ቀድመው ፡ ሸሹ ።



አባትየው ፡ ግን ፡ መሮጥ ፡ አቅቶት ፡ ሲንቀረደድ ፡ ያህያው ፡ ባለቤት ፡ ደርሶ ፡ በጦር ፡ ወግቶ ፡ ገደለው።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ያ ፡ ሽኮብ ፡ ሆዱ ፡ ሞልቶ ፡ መሮጥ ፡ አቅቶት ፡ ዘርገፍ ፡ ዘርገፍ ፡ እያለ ፡ አድነኝ ፡ ልጇ ፡ ማንሾለላ ፡ ቢለው ፡ ምን ፡ ሰጥተኸኝ ፡ ኖሯል ፡ ካንድ ፡ ዠሮ ፡ ሌላ ፡ ብሎት ፡ ሸሽቱን ፡ ቀጠለ ። ሁለተኛውን ፡ ደግሞ ፡ አድነኝ ፡ ልጇ ፡ መዝሩጥ ፡ ቢለው ፡ ምን ፡ ሰጥተኸኛል ፡ አባቱ ፡ እንደ ፡ በላሀ ፡ ሩጥ ፡ አለውና ፡ ሁለቱም ፡ ልጆቹ ፡ በቦዱ ፡ አንዠታቸው ፡ ቀልጥፈው ፡ አመለጡ ። አባትየው ፡ ግን ፡ መሮጥ ፡ አቅቶት ፡ ሲንቀረደድ ፡ ያህያው ፡ ባለቤት ፡ ደርሶ ፡ በጦር ፡ ወግቶ ፡ ገደለው ፡ ይባላል ።

* ብዙውን ፡ የበላ ፡ ብዙውን ፡ ይሞታል ፡ የተባለው ፡ እንዳይደርስባችሁ፡ ያገኛችሁት [illegible] ከወገ[illegible]ና ፡ ከዘመዳችሁ ፡ ጋራ ፡ ተካፈሉት ፡ አሉ[illegible] ፡ ለናንተ ፡ ሕይ[illegible] ፡ ኑ[illegible] ፡ ይሰጣል ።

ወታደርና ፡ ተማሪ ።

አንድ ፡ ወታደር ፡ ሠንጋ ፡ ፈረስ ፡ ጭኖ ፡ ጠመንዣውን ፡ አንግቶ ፡ በገሃዳና ፡ ሲገሰግስ ፡ አንድ ፡ ተማሪ ፡ ደበሎውን ፡ ለብሶ ፡ ልብሱን ፡ በኩፋዳው ፡ ቋጥሮ ፡ ሲሄድ ፡ ደረሰበት ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ወታደሩ ፡ ተማሪውን ፡ ተሜ ፡ ምን ፡ ይዘሃል ፡ ወዴትስ ፡ ትሄዳለህ ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቀው ፡ ጥጥ ፡ መሳይ ፡ መዝሄ ፡ ለናቱ ፡ መውሰዴ ፡ ነው ፡ አለው ። ወታደሩ ፡ በሠንጋ ፡ ፈረሱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሲፈስ ፡ ተማሪው ፡ ብቻውን ፡ ቁንዳይሆን ፡ እየተከታተለው ፡ ሲሄድ ፡ ውሎ ፡ መሸባቸውና ፡ ወታደሩ ፡ እዘህም ፡ አባካችሁ ፡ አሳድሩኝ ፡ እዘያም ፡ እባካችሁ ፡ አሳድሩኝ ፡ እያለ ፡ በየቤቱ ፡ ሲለምን ፡ እሺ ፡ የሚለው ፡ አጣ ። ተማሪው ፡ ግን ፡ የክት ፡ ልብሱን ፡ ከአኩፋዳው ፡ አውጥቶ ፡ ለብሶ ፡ ጥምጥሙን ፡ ጠመጠመና ፡ በእንተ ፡ ስሚ ፡ ለማርያም ፡ ስለ ፡ ቸሩ ፡ እግዚአብሔር ፡ የመሸብኝ ፡ መንገደኛ ፡ አሳድሩኝ ፡ ብሎ ፡ ለመናቸው ። እነዚያም ፡ ሰዎች ፡ ወዲያው ፡ አባቱ ፡ ይምጡ ፡ ብለው ፡ አስገቡና ፡ ጐዝጕዘው ፡ የሠንጋ ፡ ቊርበት ፡ ባልጋው ፡ ላይ ፡ አንጥፈው ፡ ጠላውን ፡ ከማጀት ፡ ቀድተው ፡ እንጀራውን ፡ ከሌማት ፡ በገበታ ፡ አድርገው ፡ ግብር ፡ ሠሩና ፡ ማዕድ ፡ ይባርኩልን ፡ ብሰው ፡ አስባርከው ፡ አፈታቸውን ፡ በመልካም ፡ አድርገው ፡ ተጋበዙ ። ያ ፡ ወታደር ፡ ግን ፡ ፈረሱን ፡ ይዘ ፡ ከደጅ ፡ ተቀምጠ ፡ ነበርና ፡ ተማሪው ፡ በሰቤቶቹን ፡ አሽከሬ ፡ እደጅ ፡ ከብት ፡ ይዘ ፡ ተቀምጧልና ፡ አስገቡልኝ ፡ አላቸው ። ባለቤቱም ፡ ተነሥቶ ፡ ወጥቶ ፡ ፈረሱን ፡ ተቀብሎ ፡ አስገብቶ ፡ ለሰውየው ፡ የተማሪውን ፡ ትርፍራፊ ፡ እንዳበላ ፡ ሰጠው ። ከራትም ፡ በኋላ ፡ ተማሪውን ፡ በመልክም ፡



የዚያን ፡ የተማሪ ፡ ልብስ ፡ በእሳት ፡ እዘያም ፡ እዘያም ፡ እየለኰሰ ፡ ብስትስት ፡ አድርጎ ፡ ተመልሶ ፡ ተኛ ፡

ከተነጠፈ ፡ አልጋ ፡ ላይ ፡ አስተኙት ። ወታደሩ ፡ ግን ፡ በአሽከር ፡ ደንብ ፡ ተማሪው ፡ ከተኛበት ፡ ቤት ፡ ከማደያው ፡ ላይ ፡ ትንሽ ፡ ደላጎ ፡ ተሰጠውና ፡ ያችን ፡ አንጥፎ ፡ ከዚያ ፡ ከደረቀ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ተኛ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንቅልፍ ፡ ሲወስደው ፡ ወታደሩ ፡ ሌሊት ፡ ከተኛበት ፡ ተነሣና ፡ እሱ ፡ እንደዚህ ፡ የተከበረው ፡ በዚህ ፡ በልብሱ ፡ አይደ ለምን ፡ ብሎ ፡ ከምድጃ ፡ የግራር ፡ ጕልጥምት ፡ ተዳፍኖ ፡ ነበርና ፡ የዚያን ፡



ለካ ፡ ያንተ ፡ ፈረስ ፡ የሚበቀው ፡ የኔን ፡ ልብስ ፡ መቃጠል ፡ እያየ ፡ ናፍቆል ፡

የተማሪ ፡ ልብስ ፡ በዚያ ፡ በእሳት ፡ እዘያም ፡ እዘያም ፡ እየለኰሰ ፡ ብስትስት ፡ አድርጎ ፡ ተመልሶ ፡ ተኛ ። ተማሪው ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ሲሠራ ፡ ተከናንቦ ፡ ያይ ፡ ነበርና ፡ ወታደሩ ፡ እንቅልፍ ፡ ሲወስደው ፡ ጠብቆ ፡ የሠንጋ ፡ ፈረሱን ፡ ለንጨጭ ፡ በጩቤ ፡ መልጭ ፡ አድርጎ ፡ ቈረጠና ፡ ተመልሶ ፡ ተኛ ። ማለዳ ፡ ሲነጋጋም ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ተነሥቶ ፡ ያንን ፡ በእሳት ፡ የተቃጠለ ፡ ልብሱን ፡ ለብሶ ፡ በዚያ ፡ በወታደር ፡ ፈረስ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ቆሞ ፡ ዳዊት ፡ ይደግም ፡ ገሥመር ። ያም ፡ ወታደር ፡ ከንቅልፉ ፡ እንደ ፡ ተነሣ ፡ መጣና ፡ የፈረሱን ፡ ለንጨጭ ፡ መቀልፈፍ ፡ ሳያይ ፡ ደብተራ ፡ ልብስህን ፡ ምን ፡ እንደዚህ ፡ አቃጠለብህ ፡ አለው ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ተማሪው ፡ እንዳላየ ፡ ሰው ፡ ውይ ፡ ውይ ፡ ለካ ፡ ያንተ ፡ ፈረስ ፡ የሚሥቀው ፡ የኔን ፡ ልብስ ፡ መቃጠል ፡ እያየ ፡ ኖሯልን ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ፡ ወታደሩም ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ ቢያይ ፡ ፈረሱን ፡ ጥርሱን ፡ አግጦ ፡ ስላገኘው ፡ ራሱን ፡ ይዘ ፡ ጮኸ ፡ ይበላል ።

... እግዚአብሔር ፡ በሰጠው ፡ ዕድል ፡ ምቀኛ ፡ መሆን ፡ አይገባም ፡ ቅንነት ፡ እንጂ ፡ ተንኰለኛነት ፡ አይጠቅምም ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ሠሪውን ፡ ከመጕዳት ፡ አይመለስም ።

ባልና ፡ ሚስትን ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እንዳታለላቸው ።

ባልና ፡ ሚስት ፡ ሆነው ፡ ይኖሩ ፡ የነበሩ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ በንድ ፡ ጊዜ ፡ ሞቱ ፡ ይባላል ። የወለዱትም ፡ ልጅ ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ብቻ ፡ ስት ሆን ፡ እሷውም ፡ በጣም ፡ ቂልነትን ፡ ያምታበዛ ፡ ነበረች ። ትዳር ፡ መያ ዝም ፡ ስለማይቀር ፡ ባል ፡ አግብታ ፡ ስትኖር ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እናትና ፡ አባቷ ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ቄይጳ ፡ ባሷ ፡ ወደ ፡ መንገድ ፡ ሲሄድ፡ አንድ ፡ አታላይ ፡ ሰው ፡ ተጠባበቆ ፡ መጣና ፡ ቤቶች ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ዋላ ችሁ ፡ አለ ። ሴቲቱም ፡ ብቅ ፡ አለችና ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ ብላ ፡ ሰላምታ ፡ ከሰጠችው ፡ በኋላ ፡ ወንድሜ ፡ ከወዴት ፡ መጥተሃል ፡ አለችው። ሰውዮውም ፡ እናትሽና ፡ አባትሽ ፡ ልከውኝ ፡ ነው ፡ አላት ። ምን ፡ ብለው ፡ ላኩህ ፡ ለጤናቸውስ ፡ ደኅና ፡ ናቸውን ፡ ብላ ፡ ብትጠይቀው ፡ ደኅንነቱንስ፡ ደኅና ፡ ናቸው ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ሁሬቆቱ ፡ ክልጃችን ፡ ዘንድ ፡ ልብስ ፡ አምጣ ልን ፡ ብለው ፡ ነው ፡ የላኩኝ ፡ አላት ።

ይህንንም ፡ እንደ ፡ ነገራት ፡ አዬ ፡ ጉድ ፡ ተራቀ·ተው·ብኖላ ፡ በል ፡ ና ፡ ብላ ፡ ከቤት ፡ አስገብታ ፡ ምሳውን ፡ አብልታ ፡ መጠጥ ፡ አጠጥታ ፡ የባሷን ፡ ስናፊል ፡ እጀ ፡ ጠባብ ፡ በሰንበት ፡ ቀን ፡ የሚለብሰውን ፡ ኩታውን ፡ ጃኖውንና፡



አዬ ፡ ጉድ ፡ ተራቀ·ተው·ብ ኖላ ፡ በል ፡ ና ፡ ብላ ፡ ከቤት ፡ አስገብታ ፡ በስልቻ ፡ ከታ ፡ ስጠችው ።

ድጉን ፡ ከተቀመጠበት ፡ ማጀት ፡ ከጋን ፡ ውስጥ ፡ አውጥታ ፡ ይኸንን ፡ ላባቱ ፡ ስጥልኝ ፡ ደግሞ ፡ የርሷን ፡ ቀሚስና ፡ ኩታ ፡ መቀነትና ፡ የራስ ፡ ማሰሪያ ፡

ለናቴ ፡ ስጥልኝ ፡ ሰላምታም ፡ እናንተ ፡ እንደምንድናችሁ ፡ እኔ ፡ ጤናዬን ፡ ደኅና ፡ ነኝ ፡ ብለህ ፡ ንገርልኝ ፡ ልብሱንም ፡ አሁን ፡ ቶሎ ፡ ብለህ ፡ አድርስ



አረ ፡ ስንገሩ ፡ ማነው ፡ ስምህ ፡ ስትል ፡ ጠየቀችው ።

ላቸው ፡ ብላ ፡ በስልቻ ፡ ከታ ፡ ሰጠችው ። ወዲያው ፡ እረ ፡ ለንገሩ ፡ ማነው ፡ ስምህ ፡ ስትል ፡ ጠየቀችው ። እሱም ፡ ስሜ ፡ አታለለኝ ፡ ነው ፡ ብሏት ፡ ሰቃ ውን ፡ ይዞ ፡ ሄደ ። ጥቂት ፡ ቄይጶ ፡ እንዲጋጣሚ ፡ ባሷ ፡ ከሄደበት ፡ መንገድ ፡ መጣ ፡ ወዲያው ፡ ገና ፡ ሰያርፍ ፡ እንቱዬ ፡ ዛሬ ፡ እናቲና ፡ አባቲ ፡ ልብስ ፡ አል ቆብናል ፡ ላዚልን ፡ ብለው ፡ መልክተኛ ፡ ስለ ፡ ላኩ ፡ የርስዎን ፡ የክት ፡ ልብስ ፡ ሰናፊልዎንና ፡ ድግዎን ፡ እጀ ፡ ጠባብዎንና ፡ ኩታዎን ፡ እንዲሁም ፡ ጃኖዎን ፡ ላባቲ ፡ የኔን ፡ ቀሚስና ፡ ኩታ ፡ መቀነትና ፡ የራስ ፡ ማሰሪያ ፡ ለናቲ ፡ ሰደድኩ ላቸው ። ሰላምታዎ ፡ እናንተ ፡ እንዴት ፡ ናችሁ ፡ እኛ ፡ ደኅና ፡ ነን ፡ ብለው ፡ ልከው ፡ ነበር ፡ አለችው ።

እሱም ፡ ተናደደና ፡ አዬ ፡ ጉድ ፡ ከመቼ ፡ ወዲህ ፡ ነው ፡ የሞተ ፡ ሰው ፡ ልብስ ፡ የሚፈልገው ፡ እንዲያው ፡ ሲያታልልሽ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለመሆኑ ፡ በየት ፡ በኩል ፡ ነው ፡ የሄደው ፡ አሳዩኝ ፡ አላት ። እርስዋም ፡ ያውልዎ ፡ በዚያ ፡ በኩል ፡ ነው ፡ አለችው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሠንጋ ፡ ፈረሱን ፡ ጭኖ ፡ ሲጋልብ ፡ አታላዩ ፡ ሰው ፡ እንደሚከተለው ፡ ጠርጥሮ ፡ ኖሮ ፡ ያንን ፡ ልብስ ፡ ከነስልቻው ፡ እቀጥቂጦ ፡ ሥር ፡ ደብቆ ፡ ከዛፍ ፡ ሥር ፡ ቀሩቢ ፡ ብሎ ፡ ቄየው ።

ፈረሰኛውም ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ ወንድሜ ፡ በዚህ ፡ መንገድ ፡ የተቃጠረ ፡ ስልቻ ፡ የያዘ ፡ ሰው ፡ ሲሄድ ፡ አላየህምን ፡ አለው ። እሱም ፡ በዚህ ፡ ሸለቆ ፡ ወደ፡

ታች ፡ ወረደልህ ፡ መንገዱ ፡ ግን ፡ ለከብት ፡ አይመችም ፡ ሲል ፡ መለሰለት ። የተና ደደውም ፡ ሰው ፡ እውነት ፡ መስሎት ፡ እንግዲያውስ ፡ በድፍረት ፡ ይቅርታ ፡ አድርግልኝና ፡ ደርሼ ፡ እስክመለስ ፡ ይህንን ፡ ፊረስ ፡ ያዝና ፡ ቂየኝ ፡ ብሎ ፡ ለመነው ። እሱም ፡ ብጅ ፡ ቶሎ ፡ ናልኝ ፡ እንጂ ፡ ለመያዙ ፡ ግድ ፡ የለም ፡ እሺ ፡ ስጠኝ ፡ አለና ፡ ፊረሱን ፡ ተቀበለው ። ከመለያየታቸውም ፡ በፊት ፡ ወንድም ፡ ምናልባት ፡ አገኘውና ፡ ስንጨቃጨቅ ፡ ትንሽ ፡ ያቂየሁህ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማን ፡ ብዬ ፡ ልጥራህ ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ። አታላዩም ፡ ስሜ ፡ "ያሁኑ ፡ ይባስ" ፡ ነው ፡ ያሁኑ ፡ ይባስ ፡ ያሁኑ ፡ ይባስ ፡ ብለህ ፡ ጥራኝ ፡ አለው ።



እሱም ፡ በዚህ ፡ ሽሰቆ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ወረደልህ ፡ ሲል ፡ መለ ሰለት ።

ከዚያ ፡ በኋላ ፡ በዚያ ፡ ሥርጥ ፡ ሲወርድለት ፡ ያንን ፡ ልብስ ፡ ከደበቀ በት ፡ ቀጥቂጠ ፡ ውስጥ ፡ አውጥቶ ፡ ከፊረሱ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ እየከረከረ ፡ ሸምጠ ፡ ሄደ ። የልብሱም ፡ ባለቤት ፡ በሥርጡ ፡ ሲወርድ ፡ የተባለውን ፡ ሰው ፡ ሳያገኘው ፡ ቀረ ። ተመልሶ ፡ ሲመጣም ፡ ባላደራው ፡ ፊረሱን ፡ ይዘበት ፡ ጠፋ ። እረ ፡ ያሁኑ ፡ ይባስ ፡ እረ ፡ ያሁኑ ፡ ይባስ ፡ እያለ ፡ ሲጣራም ፡ ከወዴት ፡ ያግኘው ! ከልብሱ ፡ ጥፋት ፡ ይልቅ ፡ ፊረሱንም ፡ አስወስዶ ፡ አተረፍ ፡ ባይ ፡ እጉዳይ ፡ ሆኖ ፡ ሁሉንም ፡ አጥቶ ፡ ባዶ ፡ እጁን ፡ ተመልሶ ፡ እቤቱ ፡ ገባ ፡ ይባላል ።

ምንም ፡ ሴትዮዋ ፡ እጅግ ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ የሞሀ ፡ ብትሆን ፡ ወንድዮ ውም ፡ ተሞኝቷል ። አያድርስ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከቶ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ መታለል ፡ አይቀርም ።

የዝሆብ ፡ ልጅ ፡ ሞት ።

ዝሆብ ፡ ልጁ ፡ ሞተበትና ፡ ለነእንከሴ ፡ አሀዮት ፡ ልጅ ፡ ሞቷልና ፡ አላ ቅሱኝ ፡ ሲል ፡ መርዶ ፡ ነጋሪ ፡ ላከ ።

ተረጅምቹም ፡ እንግዲህ ፡ ሰምተን ፡ ብንቀር ፡ ይጣላናል ፡ ብንሄድም ፡ ይበላናል ፡ እንዴት ፡ ብናደርግ ፡ ይሻላል ፡ በማለት ፡ ምክር ፡ ገፖሩ ። ነገር ፡ ግን ፡ ቀርተን ፡ ከሚጣላን ፡ ሄደን ፡ ቢበላን ፡ ይሻላል ፡ ብለው ፡ ተነሥተው ፡ ልብሳቸውን ፡ አሸራርጠው ፡ ሄዱ ።

ከለቅሶውም ፡ ቦታ ፡ እንደ ፡ ደረሱ ፡ አንደኛዋ ፡ ብድግ ፡ አለችና ፡
ምን ፡ ሀጥንት ፡ ቢሆን ፡ ይሰብራል ፡ ጥርስም ፡
ምን ፡ ፈኤለማ ፡ ቢሆን ፡ እሾኽ ፡ አይወጋም ፡
ምን ፡ ጥቅር ፡ ቢበሉ ፡ ነጭ ፡ ነው ፡ ዅስም ፡
ያንን ፡ ጐፈ ፡ ዘሮ ፡ ይሰማል ፡ ድምጥም ፡
አሁን ፡ የርስሞን ፡ ልጅ ፡ ምን ፡ አገኘብዎ ፡
እያለች ፡ መ·ሸ ፡ ታወርድ ፡ ዝመር ።

እሱ ፡ ደግሞ ፡ ቀበል ፡ አለና ፡ እንችስ ፡ ደግ ፡ ብለሻል ፡
መልካም ፡ አልቅሰሻል ፡
ይህ ፡ ሁሉ ፡ አዘንተኛ ፡ ምን ፡ ይብላ ፡ ብለሻል ፡
ሲል ፡ መለሰ ።

እንዳልማራቸው ፡ በወቂ ፡ ጊዚ ፡ እንግዲህ ፡ አለቀቀንም ፡ ምን ፡ ማድ ረግ ፡ ይሻለናል ፡ ብልው ፡ እነእንከሴ ፡ አሀዮት ፡ ምክር ፡ ገፖሩ ። እንዲት ፡ አናቷ ፡ የሞተችባት ፡ ወርንጭላ ፡ ከነርሱ ፡ ጋር ፡ ነበረችና ፡ ይህችን ፡ እን ስጥና ፡ እንገላገል ፡ ብለው ፡ ሲነጋገሩ ፡ ግልገሏ ፡ አሀያ ፡ ሰምታ ፡ ምነው ፡ እኔ ፡ ወርንጭላ ፡ ማ—ይዘኝ ፡ በሩጫ ፡ ብላ ፡ ተነሥታ ፡ እልም ፡ አለች ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጭንቅ ፡ ያዛቸውና ፡ መቼስ ፡ ምን ፡ ይደረግ ፡ ለንበጫች ንን ፡ ሰጥተነው ፡ እንሂድ ፡ ብለው ፡ ተማከሩ ። ወዲያው ፡ በል ፡ እንግዲህ ፡ የላይ ፡ የይላ ፡ ለንበጫችንን ፡ ውሰድ ፡ አሉት ። እሱም ፡ እንዳመለከቱት ፡ ለንፌሌጭ ፡ ለንጫጮውንፌ ፡ ገሃጣጠለና ፡ ለቀቃቸው ።

በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ደግሞ ፡ እስቲ ፡ ዛሬ ፡ ግልስቲ ፡ ነውና ፡ እመቃብሩ ፡ ላይ ፡ ደርሰን ፡ አያ ፡ ዝቦን ፡ ጠያቂን ፡ እንምጣ ፡ ብለው ፡ ዘሄዱ ፡ አያ ፡ ዝቦ ፡ ቀድሞ ፡ ከመቃብሩ ፡ ላይ ፡ ሲያለቅስ ፡ ደረሱ ።

አያ ፣ ኾቦም ፣ ድዳቸውን ፣ ገልፍጠው ፣ በየ ፣ ጊዜ ፣ ለካ ፣ የኔ ፣ ሐዘን ፣ ለናንተ ፣ ሰርግና ፣ ምላሽ ፣ ሆኖላችኋልና ፣ የኔ ፣ ልጅ ፣ ትላንትና ፣ ሞቶ ፣



በል ፣ እንግዲህ ፣ የላይ ፣ የላይ ፣ ለንቦጫችንን ፣ ውሰድ ፣ አሉት ።

ዛሬ ፣ እናንተ ፣ እየተሰላቻችሁ ፣ የመጣችሁት ፣ በምን ፣ ምክንያት ፣ ነው ፣ ብሎ ፣ ተቈጣና ፣ ለወገኖቹ ፣ እረ ፣ በሉ ፣ አንድ ፣ አንድዋን ፣ እየዘረጠጣችሁ ፣ ጣሉ ልኝ ፣ አላቸው ። ከዚህ ፣ በኋላ ፣ የኾቦ ፣ ወገን ፣ ያህያን ፣ ልጅ ፣ እየገነጣጠለ ፣ ጣለ ፣ ይበላል ።



የኔ ፣ ልጅ ፣ ትላንትና ፣ ሞቶ ፣ ዛሬ ፣ እናንተ ፣ እየተሳላቃችሁ ፣ የመጣችሁት ፣ በምን ፣ ምክንያት ፣ ነው ፣

። በላጋራን ፣ ቆቅ ፣ ሆኖ ፣ ዘልቂዩት ፣ ምንም ፣ ቢለማመጡት ፣ ማጥቃቱን ፣ አይተውም ። አያ ፣ ኾቦ ፣ ለታመኻኝ ፣ ብላኝ ፣ የተባለውም ፣ ይህ ፣ ነው ።

ሚስቱ ፣ የጕሽ ፣ ወተት ፣ አምጣ ፣ ስላለችው ፣ ሰው ።

ሥራው ፣ ግብርና ፣ የሆነ ፣ አንድ ፣ ደግ ፣ ሰው ፣ ነበር ። ከዕለታት ፣ አንድ ፣ ቀን ፣ ሚስቱ ፣ ከወዳጅዋ ፣ ጋራ ፣ ቀጠሮ ፣ አድርጋ ፣ ኖሮ ፣ በሷን ፣ ዐይኔን ፣ በብርቱ ፣ አሞኛልና ፣ መድኀኒቱ ፣ የጕሽ ፣ ወተት ፣ ነው ፣ ብለው ፣ ስለ ፣ ነገሩኝ ፣ ይህንኑ ፣ ፈልገህ ፣ አምጣልኝ ፣ ብላ ፣ አስፈቀደቻ ፣ ያዘችው ።


የዋሁ ፣ ገበሬም ፣ የታመመች ፣ መስሎት ፣ ተነሥቶ ፣ ሊፈልግ ፣ ሲሄድ ፣ አንድ ፣ መነኰሴ ፣ እመንገድ ፣ አገኙትና ፣ ወዴት ፣ ትሄዳለህ ፣ ልጇ ፣ ብለው ፣ ጠየቁት ። እሱም ፣ ሚስቱ ፣ በድንገት ፣ ዐይኔን ፣ በጠና ፣ ታምማያለሁና ፣ የጕሽ ፣ ወተት ፣ መድኀኒት ፣ ነው ፣ ስላሉኝ ፣ ከምትገባበት ፣ ገብተህ ፣ አምጣልኝ ፣ ብላኝ ፣ ልፈልግ ፣ እሄዳለሁ ፣ ሲል ፣ መለሰላቸው ። መነኰሴው ፣ ነገሩ ፣ የተንኰል ፣ መሆኑን ፣ በመንፈስ ፣ ስለ ፣ ተረዳት ፣ ይህ ፣ ከሆነማ ፣ ዕዳው ፣ ቀላል ፣ ነው ፣ ወደ ፣ ቤትህ ፣ እንመለስ ፣ መድኀኒቱንም ፣ እኔ ፣ አላይሃለሁ ፣ አሉት ። እሺ ፣ ብሎ ፣ ከሰፈሩ ፣ ሲደርስ ፣ በሩቅ ፣ ቤቱ ፣ ያ ፣ ነው ፣ ብሎ ፣ ነገራቸው ። እንግዲያውስ ፣ ቈይ ፣ ብለው ፣ እሱን ፣ በስልጅ ፣ ከተው ፣ በትከሻቸው ፣ ተሸክመው ፣ ከቤት ፣ ደረሱና ፣ እባካችሁ ፣ አሳድሩኝ ፣ ብለው ፣ ለመኑ ። በዚህ ፣ ጊዜ ፣ የተሸከሙት ፣ ሰው ፣ ሚስት ፣ ብቅ ፣ አለችና ፣ አባቴ ፣ ደኅና ፣ ውለዋል ፣ ምን ፣ ተሸከመዋል ፣ አሏቸው ። መነኰሴውም ፣ የታቦት ፣ ሰቀ ፣ ዳውላ ፣ ነው ፣ ብለው ፣ መለሱላት ። ከቤት ፣ አገባቷቸውና ፣ መብራት ፣ ላብራልም ፣ ብትላቸው ፣ አይሆንም ፣ የታቦት ፣ ዕቃዬ ፣ ይታይብኝና ፣ ሕዝ ፣ መጥቶ ፣ ይሰርቀኛል ፣ ከጨለማ ፣ ውስጥ ፣ ነው ፣ ይዤ ፣ የምቀመጠው ፣ አሏት ። እንግዲያውስ ፣ ያውልም ፣ ብላ ፣ ከጓዳ ፣ ቦታ ፣ ሰጠቻቸው ።

ከዚህ ፣ በኋላ ፣ ለወዳጅዋ ፣ የታረደ ፣ መኽኒና ፣ የተጠመቀ ፣ ጠላ ፣ ስለ ፣ ነበረ ፣ ከጠላውም ፣ ከሥጋውም ፣ አድርጋ ፣ እዚያው ፣ እተቀመጡበት ፣ ጨለማ ፣ ውስጥ ፣ እራታቸውን ፣ ሰጠቻቸው ። መነኰሴውም ፣ ስልጅውን ፣ ፈተው ፣ ያንን ፣ ሥጋና ፣ ጠላ ፣ ከጓደኞቹው ፣ ጋራ ፣ ከዘሉና ፣ ከጠጡ ፣ በኋላ ፣ አባቱ ፣ እስቲ ፣ ዘፈን ፣ ያምጡ ፣ እንጫወት ፣ አሏቸው ።

እሳቸውም ፣ ልጇ ፣ እስቲ ፣ ካንቺ ፣ ይገሥመር ፣ ሲሉ ፣ መለሱላት ። በዚህ ፣ ጊዜ ፣ እጕሽ ፣ የሄደው ፣ ወዲያው ፣ በቀረው ፣ እጕሽ ፣ የሄደው ፣ ወዲያው ፣ በቀረው ፣ እያለች ፣ ትዘፍን ፣ ገሥመር ።

መነኩሲውም ፡ ቀበል ፡ አሉና ፡ ይኸንን ፡ ጉባኤ ፡ ስማ ፡ ዳውላዬ ፡ ይኸንን ፡ ጉባኤ ፡ ስማ ፡ ዳውላዬ ፡ እያሉ ፡ እያወረዱ ፡ ሰጫወቱ፡ አመሹ ።

በመኝታ ፡ ሰዓት ፡ እርሷ ፡ ወዳጅዋን ፡ ይዛ ፡ ካልጋዋ ፡ ላይ ፡ ተኛች ። ሌሊት ፡ እንቅልፍ ፡ ይዟቸው ፡ ሳለ ፡ ያ ፡ ባሳ ፡ ተነሥቶ ፡ የሚስቱን ፡ ወዳጅ ፡ አንገቱን ፡ በካራ ፡ ቁርጠ ፡ ጭንቅላቱን ፡ እድፍድፍ ፡ ውስጥ ፡ ጨምሮ ፡ ሄደ ።



አባቱ ፡ አስቲ ፡ ዘፈን ፡ ያምጡ፡ እንጫወት ፡ አሰኙት ።

ሴቲቱ ፡ ከአንቅልፏ ፡ ስትነቃ ፡ ወዳጅዋን ፡ ብትዳብሰው ፡ ራሱን ፡ አጣችው ። እኛን ፡ መነኩሴ ፡ አባ፡ አባ ፡ ብላ ፡ ጠርታ ፡ ወይ ፡ ቢሏት ፡ እረ ፡ ይኸ ፡ ማታ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ የተኛው ፡ ሰው ፡ አንገት ፡ የለውም ፡ ኖሯል ፡ ወይ ፡ ብላ ፡ ጠየቀቻቸው ። እርሳቸውም ፡ ልጄ ፡ ካንገትም ፡ አንገት ፡ መቃ ፡ የመሰለ ፡ አሏት ። እንግዲያውስ ፡ ሰው ፡ ሳያይ ፡ ሳይሰማ ፡ ከዚህ ፡ ላጥፋ ፡ ብላ ፡ ያንን ፡ ሬሳ ፡ ጉትታ ፡ መስዳ ፡ እጉድጓ፡ ቀበረችው። መነኩሴውም ፡ ጧት ፡ ተነሥተው ፡ ዳውላቸውን ፡ ቢያዩ ፡ ባዶ ፡ ሆነባቸው ፡ እንደ ፡ ፊራሁት ፡ የታቦት ፡ ሰኮዬን ፡ አሰረቅሽብኝ ፡ አ ፡ አ ፡ ማለቱ ፡ ነው ፡ ቢሏት ፡ እባክዎ ፡ አይጨክኑ ፡ እኔ ፡ እከሳላለሁ ፡ ብላ ፡ ከቤቷ ፡ በድብኝት ፡ ያላትን ፡ ሸማ ፡ ሁሉ ፡ በስልቻቸው ፡ ከታላቸው ፡ ይዘው ፡ ሄዱ ።

ባሳም ፡ በማግስቱ ፡ መጣና ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ውለሽ ፡ አደርሽ ፡ በጎ ፡ ሆንሽን ፡ ብሎ ፡ ጠየቃት ። እሷም ፡ ያላወቀባት ፡ መስሏት ፡ ደግ ፡ ነኝ ፡ ዛሬ ፡ ቀለል ፡ ብሎኛል ፡ አለችው ።

ጥቂት ፡ ቈይቶ ፡ ሴቲቱ ፡ ከምድጃ ፡ ምንቸት ፡ ጥዳ ፡ ነበርና ፡ ያ ፡ ምንቸት ፡ ሲር ፡ ሲር ፡ ሲል ፡ ሰምቶ ፡ እንቺ ፡ እረ ፡ ይኸ ፡ የጣድሽው ፡ ማሰሮ ፡ ምነው ፡ አንገት ፡ እድፍድፍ ፡ ሬሳ ፡ እጉድጓ ፡ ይላልሳ ፡ እስቲ ፡ የድፍድፉን ፡ ጋን ፡ እዪው ፡ አላት ። ቶሎ ፡ ተነሣችና ፡ ያንን ፡ የድፍ ድፍ ፡ ጋን ፡ ከፍታ ፡ እይዋን ፡ ብታገባ ፡ ጭንቅላት ፡ ከውስጡ ፡ አገኝችና ፡ ገርሮዋን ፡ ይዛ ፡ ብቅ ፡ አደረገችው ። ደግሞ ፡ ሬሳ ፡ እጉድጓ ፡ ይላል ፡ እስቲ ፡ እደጅ ፡ ወጥተሽ ፡ ከጥራጊ ፡ ማፋሰሻ ፡ ያለውን ፡ ጉድጓ ፡ ተመልከቺ ፡ ቢላት ፡ በስቀመጠችበት ፡ ሄዳ ፡ የቀበረችውን ፡ ሬሳ ፡ አወጣች ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አሱ ፡ ይህንን ፡ ነገር ፡ ሰው ፡ የሰማብን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እን ዳንወረስ ፡ መጫኛ ፡ አምፈኛ ፡ ገደል ፡ ጥለነው ፡ እንምጣ ፡ ብሎ ፡ ያንን ፡ ሬሳና ፡ ጭንቅላት ፡ ባቀረበችለት ፡ መጫኛ ፡ ጥፍር ፡ አድርጎ ፡ አስሮ ፡ እዝ ርባዋ ፡ ላይ ፡ አሳዘለው ፡ ሄደው ፡ ከገደል ፡ አፋፍ ፡ ሲደርሱ ፡ የወደድሽው ፡ ነው፡ አትለዪው ፡ ብሎ ፡ ባንድነት ፡ ገደል ፡ ሰዷቸው ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ተመለሰ ፡ ይባላል ።



ከገደል ፡ አፋፍ ፡ ሲደርሱ ፡ የወደድሽው ፡ ነው፡ አትለዪው ፡ ብሎ ፡ ባንድነት ፡ ገደል ፡ ሰዷቸው ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ተመለሰ ።

፠ ሚስት ፡ ለባሳ ፡ ባልም ፡ ለሚስቱ ፡ ታማኝ ፡ ሆነው ፡ መገኘት ፡ ይገባቸዋል ። በየዋሁ ፡ ባልደረባችሁ ፡ ተንኩል ፡ ብታስቡ ፡ ትጠፋላች ሁና ፡ ክፋትን ፡ ከላያችሁ ፡ አርቃችሁ ፡ አስወግዱት ።

ሁለት ፡ ሌቦች ።

ጓደኛ ፡ ሆነው ፡ አብረው ፡ ሲሰርቁ ፡ የሚኖሩ ፡ ሁለት ፡ ሌቦች ፡ ከሰ ለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ከመንገድ ፡ ዳር ፡ ተቀምጠው ፡ ሲጨዋወቱ ፡ አንድ ፡ ባላገር ፡ ለግብር ፡ ታዞ ፡ ማር ፡ ይገንቦ ፡ ተሸክሞ ፡ ሙክት ፡ እየ ሳበ ፡ ሲመጣ ፡ አዩት ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ለመንጠቅ ፡ ተማከሩ ፡ አንዱ ፡ ሌባ ፡ ተነሥቶ ፡ እጫካ ፡ ገባ ። ሁለተኛው ፤ ሞን ፡ እዚያው ፡ እመንገድ ፡ ዳር ፡ ሀይነ ፡ ስውር ፡ መስሎ ፡ ጥቅልል ፡ አለና ፡ ተኛ ።

ያ ፡ ባላገር ፡ ሙክቱን ፡ እየሳበ ፡ ማሩን ፡ በዕቃ ፡ ተሸክሞ ፡ አጠገቡ ፡ ሲደርስ ፡ ሌባው ፡ አየና ፡ ስለ ፡ ቸሩ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብለህ ፡ አትለፈኝ ፡ የቀን ፡ ጨለማ ፡ የወረሰኝ ፡ ነኝና ፡ እየመራኸኝ ፡ ሂድ ፡ ብሎ ፡ ለመነው ። እሱም ፡ እኔ ፡ ለግብር ፡ ቶሎ ፡ አድርስ ፡ ተብዬ ፡ ታዝዤ ፡ መክት ፡ እስባለሁ ፡ ማር ፡ ተሸክሚያለሁ ፡



አጠገቡ ፡ ሲደርስ ፡ ስለ ፡ ቸሩ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብለህ ፡ አትለፈኝ ፡ የቀን ፡ ጨለማ ፡ የወረሰኝ ፡ ነኝና ፡ እየመራኸኝ ፡ ሂድ ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ።

አንተን ፡ እንዴት ፡ አድርጌ ፡ ነው ፡ የምይዝህ ፡ ቢለው ፡ አንተ፡ እኔን ፡ ከያ ዝከኝ ፡ የሙክቱን ፡ መሳቢያ ፡ ገመድ ፡ ሰጥተኸኝ ፡ እኔ ፡ እስበዋለሁ ፡ አለ።

ሰውዬውም ፡ የዋህ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ነበርና ፡ እሺ ፡ ብሎ ፡ የመሳቢያውን ፡ ገመድ ፡ ለወይነ ፡ ስወሩ ፡ አስጨብጦ ፡ እርሱ ፡ ደግሞ ፡ የሌ ባውን ፡ እጅ ፡ ይዞ ፡ ጉዞ ፡ ገሥመሩ ። ጥቂት ፡ እንደ ፡ ሄዱና ፡ ከጫካ ፡ እንደ ፡ ደረሱ ፡ ጓደኛው ፡ በኋላ ፡ ደርሶ ፡ መሳቢያውን ፡ ገመድ ፡ ፈትቶ ፡ ሙክቱን ፡ መሰደው ። ሲሄዱ ፡ ሲሄዱ ፡ ቄይተው ፡ ሳለ ፡ ዓይነ ፡ ስውሩ ፡ ወንድሜ ፡ ም ነው ፡ ገመዱ ፡ ቀለል ፡ ብኝ ፡ እስቲ ፡ ሙክቱን ፡ እይልኝ ፡ እለው ።



ጥቂት ፡ እንደ ፡ ሄዱና ፡ ከጫ ካ ፡ እንደ ፡ ደረሱ ፡ ጓደኛው ፡ በኋላ ፡ ደርሶ ፡ መሳቢያውን ፡ ገመድ ፡ ፈትቶ ፡ ሙክቱን ፡ መሰደው ፡

ይኸም ፡ የዋህ ፡ ሰው ፡ መደ ፡ ኋላው ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ ቢያይ ፡ ሙክቱ ፡ የለም ። ማሩን ፡ ከትከሻው ፡ አውርዶ ፡ እንክ ፡ ቢጅህ ፡ ይዘህ ፡ ጠብቅልኝ ፡ እኔ ፡ ተመልሼ ፡ ሙክቱን ፡ ልፈልግ ፡ አለውና ፡ ሄደ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ያ ፡ ሌባ ፡ ደግሞ ፡ ማሩን ፡ ተሸክሞ ፡ እልም ፡ አለ ። ያንን ፡ የዋህ ፡ የእግዚአብ ሔር ፡ ሰው ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ተንኰል ፡ እነዚህ፡ ሁለት ፡ አታላዮች ፡ ሁሉ ንም ፡ ቀምተው ፡ ሰደዱት ።

። ወንጠን ፡ ሳትመረምርና ፡ ጠባዩን ፡ ሳታውቅ ፡ እምነትህን ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ አትጣል ።

አንድ ፡ በሬ ፡ ስለ ፡ ነበራቸው ፡ ቂሎች ፡ በልና ፡ ሚስት ።

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ኑሯቸውን ፡ ሲወያዩ ፡ ሴት ዮዋ ፡ ለባሏ ፡ ችግርና ፡ ረኃብ ፡ ጸናብን ፡ ፈይሽንን ፡ በሬያችንን ፡ እርደን ፡ እንብላው ፡ ብላ ፡ አሳሰበችው ። ባሏም ፡ እውነትሽ ፡ ነው ፡ እንረደው ፡ አላት። ሁለቱም ፡ በሐሳቡ ፡ ስለ ፡ ተስማሙ ፡ በሬውን ፡ ከዛፍ ፡ ሥር ፡ አርደው ፡ ብልት ፡ ሲያወጡ ፡ አሞራ ፡ እየመጣ ፡ አንዳንዱን ፡ ሙዳ ፡ እየያዘው ፡ ይሄድ ፡ ገሞረ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እሱ ፡ የወሰዱከው ፡ ሥጋ ፡ የብር ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ያዙ ። ደግሞ ፡ ጭልፊቶች ፡ ሥጋው ፡ ስለ ፡ ጣማቸው ፡ እየተመላለሱ ፡ በጥፊ ፡ እያነጐዱ ፡ ቅንጥብጣቢ ፡ ሲነጥቁ ፡ እኛ ፡ ነግረናል ፡ አሁን ፡ የወሰዳችሁት ፡ የብር ፡ ነው ፡ ወውቃችሁ ፡ ግበብት ፡ ይምሩናል ፡ ብላችሁ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አታስቡ ፡ በማለት ፡ ሲወተውቱ ፡ ከቁዩ ፡ በኋላ ፡ ቁዳውን ፡ ገፈው ፡ ሲያበቁ ፡ የተረፈውን ፡ ሥጋ ፡ በጋን ፡ ቀቅለው ፡ በመግላሊት ፡ ከድነው ፡ እንግዲህ ፡ ስንበላ ፡ እጥርሳችን ፡ የሚገባውን ፡ ለመጐርጐሪያ ፡ ስንደዶ ፡ አጭደን ፡ እናምጣ ፡ ብለው ፡ የቤታቸውን ፡ ጭራሮ ፡ መዝጊያ ፡ መለስ ፡ አድር ገው ፡ ማጭዳና ፡ መጫኛ ፡ ይዘው ፡ ሁለቱም ፡ ተያይዘው ፡ ከቤት ፡ ወጡ ። ወዲያው ፡ በዚያው ፡ መንገድ ፡ ባጠገባቸው ፡ ብዙ ፡ ወታደሮች ፡ ተፍ ፡ ተፍ ፡ እያሉ ፡ መጡ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እናንተ ፡ ጐበዞች ፡ ሰማችሁ ፡ በዚህ ፡ በምትሄዱበት ፡ መንገድ ፡ አጠገብ ፡ በጭራሮ ፡ መዝጊያ ፡ የተዘጋ ፡ ቤት ፡ አለና ፡ እኛ ፡ በሬያችንን ፡ እርደን ፡ ሥጋውን ፡ በጋን ፡ ቀቅለን ፡ በመግላሊት ፡ ከድነን ፡ ከወፍጮም ፡ ላይ ፡ ዳቦ ፡ በሌማት ፡ አስቀምጠን ፡ ለጥርሳችን ፡ መጐርጐሪያ ፡ ስንደዶ ፡ ለማጨድ ፡ መጥተናል ፤ በዚያ ፡ ስታልፉ ፡ እንዳትነኩብን ፡ ብለው ፡ ነገሯቸው ። መንገደኞቹም ፡ ይህንን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ገሥግሠው ፡ ሄደው ፡ ያንን ፡ የጭራሮ ፡ መዝጊያ ፡ ከፍተው ፡ ሥጋውን ፡ እደቅ ፡ ላይ ፡ እያወጡ ፡ በልተው ፡ ከጠገቡ ፡ በኋላ ፡ ብጥንቱን ፡ መልሰው ፡ እጋኑ ፡ ውስጥ ፡ ጨምረው ፡ መግላሊቱን ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ከደኑት ። በሌማት ፡ የነበረውንም ፡ ዳቦ ፡ እየተከፋፈሉ ፡ በጭብጦ ፡ መያዣቸው ፡ ከቋጠሩ ፡ በኋላ ፡ ጭራሮ ፡ መዝ

ጊያውን ፡ መለስ ፡ አድርገው ፡ ተነሥተው ፡ መንገዳቸውን ፡ ቀጠሉ ።

ወታደሮቹም ፡ በዝብዘው ፡ ከሄዱ ፡ በኋላ ፡ ባልና ፡ ሚስቱ ፡ ስንደ ዷቸውን ፡ ተሸክመው ፡ መጡና ፡ ቤታቸውን ፡ ከፍተው ፡ ቢገቡ ፡ መግ ላሊቱ ፡ ተንከርፍፎ ፡ ዝንቡ ፡ እቤት ፡ ባለው ፡ ዕቃ ፡ ላይ ፡ በጋኑም ፡ በዋ ዲያቱም ፡ በአፍላሉም ፡ በበገፈጁም ፡ ዳቦ ፡ በነበረበት ፡ ሌማትም ፡ እቤት ፡ ባለው ፡ ደጃፍ ፡ በመለሰውና ፡ ማጀት ፡ ዘንረሠው ፡ ዘማናቸውም ፡ ላይ ፡ ሰፍሮበት ፡ አዩ ። መግላሊቱን ፡ ከጋኑ ፡ ቢያነሡት ፡ ዝንቡ ፡ እው ፡ እያለ ፡ ከውስጡ ፡ ይወጣ ፡ ዝመር ። እጃቸውንም ፡ አግብተው ፡ ቢዳብሱት ፡ አጥ ንቱ ፡ ብቻ ፡ ታጉሮ ፡ ሥጋው ፡ ተበልቶ ፡ አገኙት ። ሥጋችንን ፡ የበላ ብን ፡ ይሽ ፡ ዝንብ ፡ አያደለምን ፡ እንክሰሰው ፡ ብለው ፡ ተነሥተው ፡ ወደ ፡ ዳኛ ፡ ሄደው ፡ አቤት ፡ አቤት ፡ እያሉ ፡ ጮኹ ። ዳኛውም ፡ ምነው ፡ ምን ፡ ሆናችሁ ፡ ምንስ ፡ ተበድሳችሁ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ጠየቃቸው ። እነሱም ፡ ጌታችን ፡ ሆይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያሳይዎ ፡ መልአኩ ፡ ይንገርዎ ፡ በሬያችንን ፡ አርደን ፡ ሥጋውን ፡ በጋን ፡ ቀቅለን ፡ በመግላሊት ፡ ከድነን ፡ ዳቢችንንም ፡ በሌማት ፡ አኑረን ፡ ቤታችንን ፡ ዘግተን ፡ ለጥርሳችን ፡ መጐርጐሪያ ፡ ስንደዶ ፡ ለማጨድ ፡ ሄደን ፡ ተመልሰን ፡ ብንመጣ ፡ ዝንብ ፡ ወጥንቱ ፡ ብቻ ፡ እስኪቀር ፡ ሥጋውን ፡ በልቶ ፡ ዳቢችንን ፡ ጨርሶ ፡ አገኘነው ። የንቀቱ ፡ ንቀት ፡ የድፍረቱ ፡ ድፍረት ፡ ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ ጥፋት ፡ በኋላ ፡ ከቤታችን ፡ ዕቃ ፡ ላይ ፡ ሰፍሮ ፡ ቁየን ። እኛንም ፡ አይቶ ፡ ትንሽ ፡ እንኳ ፡ ደንገጥ ፡ አላለም ። ዝም ፡ ብሎ ፡ የተረፈውን ፡ ይበላል ፡ አሉት ። ዳኛውም ፡ የዚህ ፡ ፍርድ ፡ አስቸጋሪ ፡ አይደለም ፡ ሄዳችሁ ፡ ያለውን ፡ ዝንብ ፡ ሁሉ ፡ ናጁት ፡ በገዛ ፡ ቤታችሁና ፡ በገዛ ፡ ሥጋችሁ ፡ ዝም ፡ በሉ ፡ አልልም ፡ አላቸው ። እነሱም ፡ ይህንን ፡ ፍርድ ፡ ተቀብለው ፡ እጅ ፡ ነሥ ተው ፡ ተመለሱ ።

ከቤታቸውም ፡ እንደ ፡ ደረሱ ፡ ባለቤቱ ፡ ፊጥኖ ፡ ቁመጡን ፡ አንሥቶ ፡ ዝንብ ፡ ለመግደል ፡ ሲሰነዝር ፡ ጋኑን ፡ ከመግላሊቱ ፡ ብትንትን ፡ አደረ ገው ። ደግሞ ፡ ከዋዲያቱ ፡ ላይ ፡ ያረፈውን ፡ ሊገድል ፡ ሽመሉን ፡ ቢያው ዘገዝገው ፡ ዋዲያቱን ፡ ጣባውን ፡ ጉልቻውንም ፡ በንድ ፡ ጊዘ ፡ እንኵት ኩት ፡ አደረገው ።

እማጀትም ፣ ገብቶ ፣ መኽረጁንም ፣ አፍላሉንም ፣ ዶጮውንም ፣ ጅቹ
ንም ፣ አደቀቀው ፣ ዳግመኛ ፣ ወደ ፣ ኋላው ፣ መለስ ፣ ቢል ፣ ከበገፈጁ ፣ ላይ ፣
አንድ ፣ ዝንብ ፣ አርፋ ፣ አየ ። ዝግ ፣ ብሎና ፣ አድብቶ ፣ ቂመጡን ፣ ቢያው
ዘገዝገው ፣ ይኸነንም ፣ እንኩትኩት ፣ አድርጎ ፣ ጣለው ። ዝንቡ ፣ ግን ፣ እም
ልጦ ፣ እሞግዴ ፣ ላይ ፣ አርፎ ፣ ነበር ፤ ተከታትሎ ፣ ወዲያው ፣ ሞግዴንም ፣
ከነምጣዱ ፣ ሰባበረው ። ከዚህም ፣ በላይ ፣ የተሰቀሉትን ፣ ያደስ ፣ የድልሀና ፣
የሽሮ ፣ ቅሎችን ፣ ኩስኩስቱን ፣ ደቁንጮ ፣ በቤት ፣ ያለውን ፣ ማናቸውንም ፣
ዕቃ ፣ ሁሉ ፣ ሰብሮ ፣ ከጨረሰ ፣ በኋላ ፣ አንድ ፣ ዝንብ ፣ ከሚስቱ ፣ ግንባር ፣
ላይ ፣ አረፈች ። እሷም ፣ ጭራሮ ፣ አንሥታ ፣ አመታለሁ ፣ ስትል ፣ ብር ፣ ብላ ፣
አመለጠቻት ። በዚህም ፣ ተናዳ ፣ ሳለች ፣ ሌላዋ ፣ ዝንብ ፣ መጥታ ፣ አፍን
ጫዋ ፣ ላይ ፣ አረፈች ። በዚህ ፣ ጊዜ ፣ አፍን ፣ አሞጥሙጣ ፣ በቆጨት ፣ ባሷን ፣
ጠርታ ፣ በጣቷ ፣ አመለከተችው ። ወዲያው ፣ ቂዩ ፣ እባክሽ ፣ ዝም ፣ በዪ ፣
እኔስ ፣ እንዳንቺ ፣ አላዋዛትም ፣ ብሎ ፣ የመ·ቀጫ ፣ ግልገል ፣ አንሥቶ ፣ ባለው ፣
ጎይል ፣ ሁሉ ፣ ሠርኒን ፣ አደቀቀው ። ነፍሷም ፣ በመጣ ፣ ጊዜ ፣ ጥርሷ ፣ ገጠ ፣
በማየቱ ፣ እረ ፣ ተነሽ ፣ ታጠቂ ፣ ያለዛሬም ፣ ስቀሽ ፣ አታውቂ ፣ አላት ፣ ይባላል ።



ቂዩ ፣ እባክሽ ፣ ዝም ፣ በዪ ፣ እኔስ ፣ እንዳንቺ ፣ አላዋዛትም ፣ ብሎ ፣ የመ·ቀጫ ፣ ግልገል ፣ አንሥቶ ፣ ባለው ፣ ጎይል ሁሉ ፣ ሠርኒን ፣ አደቀቀው ።

ከመጠን ፣ ያለፈ ፣ ቂልነት ፣ ያደርሳል ፣ ከሞት ።

አንድ ፣ ሚስቱ ፣ የተፈጠረችበት ፣ ሰው ።

አንድ ፣ ሰው ፣ ሚስት ፣ አግብቶ ፣ ይኖር ፣ ነበር ። ነገር ፣ ግን ፣ እሷ ፣ ዘወትር ፣ ሰያማት ፣ አሞኛል እያለች ፣ ዝም ፣ ብላ ፣ በመተኛት ፣ ጊዜ
ዋን ፣ ስለምታሳልፍ ፣ እርሱ ፣ ውሃውን ፣ ቀድቶ ፣ ወፍጮውን ፣ ፈጭቶ ፣
ከበረት ፣ የከብት ፣ እበት ፣ አውጥቶ ፣ ጠፍጥፎ ፣ በወንዶቹም ፣ ሞያ ፣
ረገደ ፣ እርሻውን ፣ እርሶና ፣ ቄጥሮ ፣ አጭዶ ፣ ከሥራውም ፣ ሲመለስ ፣
ምጣድ ፣ ጥዶ ፣ እየጋገረ ፣ ወጥም ፣ እየሠራ ፣ ይኖር ፣ ነበር ።

ከቶ ፣ በሰድሚው ፣ ልክ ፣ ምሳ ፣ የሚባል ፣ ነገር ፣ አያውቅም ፣ ማታ ፣
ከሥራውም ፣ ሲገባ ፣ መክሰሱንም ፣ ሆነ ፣ ራቱን ፣ እሱው ፣ ራሱ ፣ አሰና
ዶ ፣ ይበላል ። ሚስቱ ፣ ግን ፣ ክሰው ፣ ቂጥሯ ፣ ደክሟታል ፣ ብላ ፣ ማና
ቸውንም ፣ ነገር ፣ ቢሆን ፣ አሰናዳታለት ፣ አታውቅም ።

እንደዚሁ ፣ ስትፈጠርበት ፣ ኖረ ፣ ሞት ፣ አይቀርምና ፣ ብትሞት ፣
ያለመጠን ፣ አድርጎ ፣ ፈቱን ፣ በገብቶት ፣ ነጭቶ ፣ በገመድ ፣ ታጥቆ ፣ ደረ
ቱን ፣ በድንጋይ ፣ እየደበደበ ፣ ከማ ፣ እለምዳለሁ ፣ እንግዲህ ፣ በባሕሪዬ ፣
ማን ፣ ያውቅልኛል ፣ እንዳንቺ ፣ ማነው ፣ የሚያሸነፈኝ ፣ እንግዲህ ፣
በማነው ፣ የምንቀባጠረው ፣ ከራቱ ፣ በማነው ፣ እንግዲህ ፣ ንብረቱ ፣
ተፈታ ፣ እያለ ፣ ያለቅስ ፣ ዠመር ።

በዚህ ፣ ጊዜ ፣ አንዱ ፣ ባልንጀራው ፣ ምነው ፣ ወንድሜ ፣ ጓደ ፣
ከሞት ፣ የሚቀር ፣ የለም ፣ ሁሉም ፣ እንደምታየው ፣ ሟች ፣ ነው ። እኛስ ፣
ብንሆን ፣ ነገ ፣ ይሁን ፣ ተነገ ፣ ወዲያ ፣ መሞታችንን ፣ መቼ ፣ እናውቀዋ
ለን ፣ ለምን ፣ እንደዚህ ፣ አድርገህ ፣ አጥብቀህ ፣ ታገናለህ ፣ ሐዘኑን ፣
ተወት ፣ አድርገው ፣ እንጂ ፣ በሐዘን ፣ መቼ ፣ ይገፋል ፣ ብለህ ፣ ነው ፣ ትርፉ ፣
ሀያንን ፣ ማጥፋት ፣ ብቻ ፣ ነው ፣ ብሎ ፣ ቢመክረው ፣ እንደርሷ ፣ ያለ ፣
አይገኝም ፣ እንጂ ፣ ሲትማ ፣ ሞልቶ ፣ የለምን ፣ እንደ ፣ እሷ ፣ ያለ ፣ ማንን ፣
አገኛለሁ ፣ አላገኝም ፣ አላገኝም ፣ ሲል ፣ መለሰለት ።

ከዚህ ፡ ወዲያ ፡ መዋዕለ ፡ ሐዘኑን ፡ ሲጨርስ ፡ ያ ፡ ጓደኛው ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ያለሴት ፡ እንዴት ፡ አድርጎ ፡ ለመቀመጥ ፡ ይችላል ፡ በማለት ፡ አስቦ፡ የጨዋ ፡ ልጅ ፡ ትዳር ፡ የምታውቅ ፡ ፈልጎ ፡ አመጣለት ። በጧት ፡ ገና ፡ ሴት የውሃ ፡ አልጋ ፡ ላይ ፡ ሆና ፡ ሳለች ፡ እንደ ፡ ልማዱ ፡ እንስራውን ፡ አንሥቶ ፡ ውሃ ፡ ለመቅዳት ፡ ወደ ፡ ወንዝ ፡ ለመውረድ ፡ ተነሣ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ያች ፡ ሴት ፡ ጌታዬ ፡ ወዴት ፡ ሊሄዱ ፡ ነው ፡ ገና ፡ ሳይነጋ ፡ ጉድጉድ ፡ የሚሉት ፡ ብትለው ፡ የትም ፡ አልሄድ ፡ ከወንዝ ፡ ውሃ ፡ ለመቅዳት ፡ ነው ፡ አሁን ፡ እመጣለሁ ፡ ዝም ፡ ብለሽ ፡ ተኚ ፡ አላት ። እንዴት ፡ እርስዎ ፡ ውሃ ፡ ከቀዱማ ፡ ታዲያ ፡ እኔ ፡ ምን ፡ ላደርግልዎ ፡ መጣሁ ፡ እረ ፡ በሉ ፡ አምጡ ፡ ብላ ፡ ሽርጧን ፡ ታጥቃ ፡ በንገት ፡ ልብሷ ፡ አንገቷን ፡ ጠምጥማ ፡ እንስራውን ፡ ከባሏ ፡ ተቀብላ ፡ ስትንደረደር ፡ እወንዝ ፡ ወርዳ ፡ ውሃዋን ፡ ቀድታ፡




እንዴት ፡ እርስዎ ፡ ውሃ ፡ ከቀዱማ ፡ ታዲያ ፡ እኔ ፡ ምን ፡ ላደርግልዎ ፡ መጣሁ፡ እረ ፡ በሉ ፡ አምጡ ፣

ተመለሰች ። ወዲያው ፡ ቶሎ ፡ ብላ ፡ ድስት ፡ ጥዳ ፡ ለጅ ፡ መታጠቢያ ፡ ውሃ፡ በኮስኮስት ፡ ወዝታ ፡ ማታ ፡ ከባት ፡ ከናቷ ፡ ቤት ፡ ይዛው ፡ የመጣች፡ ውን ፡ የቅቤውን ፡ የድልኩን ፡ የሽሮውንም ፡ ቅል ፡ አቅርባ ፡ ማማሰያዋን ፡ አበጅታ ፡ ወጪን ፡ አሰምራ ፡ ከሠራች ፡ በኋላ ፡ እጁን ፡ በሙቅ ፡ ውሃ ፡ አስታጥባ ፡ ምሳውን ፡ በደንብ ፡ አብልታ ፡ በሉ ፡ እንግዲህ ፡ ወደ ፡ እርሻዎ ፡ ይሂዱ ፡ አለችው ። እሱም ፡ የማያውቀውን ፡ ምሳ ፡ በማግኘቱ ፡ ሰውነቱ ፡ በደስታ ፡ ተመልቶ ፡ ከብቶቹን ፡ ነድቶ ፡ ወደ ፡ ግብርና ፡ ሥራው ፡ ሄደ ።

እርሻውም ፡ ወደ ፡ ደጋ ፡ ነበርና ፡ አፋፉን ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ ቢያስታውስ፡ ምራኑን ፡ ትቶታል ። ስለዚህ ፡ ከፋፋ ፡ ላይ ፡ ብቅ ፡ አለና ፡ ሚስቱ ፡ እንግዳ ፡ በመሆኗ ፡ በስሟ ፡ ለመጥራት ፡ ስለ ፡ ፈራ ፡ እረ ፡ አንቺ ፡ ሴትዮ ፡ ብሎ ፡ ተጣራ ። እሷም ፡ ወዲህ ፡ ነው ፡ ወይ ፡ የምትጣሩት ፡ አለችው ። አዎን ፡ ቢላት ፡ ምነው ፡ ምን ፡ ሆነዋል ፡ ስትል ፡ ጠየቀችው ፤ እረ ፡ ምራኑን ፡ ረስቼዋለሁና ፡ አቀብዪኝ ፡ አላት ።

ያንን ፡ ምራን ፡ እውሻው ፡ አንገት ፡ ላይ ፡ አሰረችና ፡ እንግዲህ ፡ ውሻውን ፡ ይጥሩት ፡ አለችው ።

እሱም ፡ እረ ፡ እኔ ፡ ውሻው ፡ ምን ፡ ያደርግልኛል ፡ አንቺ ፡ ምራኑን ፡ ይዘሽልኝ ፡ ነዪ ፡ አላት ። ይጥሩት ፡ አልኩዎ ፡ አለችና ፡ በቀጣ ፡ ቃል ፡ ተናገረችው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ና ፡ ቡቺ ፡ ና ፡ ና ፡ ና ፡ ብሎ ፡ ቢጣራ ፡ ውሻው ፡ ያንን ፡ ምራን ፡ በንገቱ ፡ ይዘለት ፡ ከተፍ ፡ አለ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ልቡ ፡ በደስታ ፡ ተነካና ፡ እዚያው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተጣርቶ ፡ ከቶ ፡ ለመሆኑ ፡ አንቺም ፡ ትሞቺ ፡ ይሆን ፡ ብሎ ፡ ተናግሮ ፡ ወደ ፡ ሥራው ፡ ሄደ ፡ ይባላል ።



ያንን ፡ ምራን ፡ እውሻው ፡ አንገት ፡ ላይ ፡ አሰረችና ፡ እንግዲህ ፡ ውሻውን ፡ ይጥሩት ፡ አለችው ።

※ በቅን ፡ ልቡ ፡ ለትዳሩ ፡ የደከመ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ሳያልፍለት ፡ ሳይደሰት ፡ እንደዚሁ ፡ እንደማይቀር ፡ ልናምን ፡ ይገባል ።

መልካም ፡ ሚስት ፡ ለባሏ ፡ ዘውድ ፡ ናት ፡ የተባለውም ፡ ስለዚህ ፡ ነው ።

የባልና ፡ ሚስት ፡ በ-ተስቦ ፡ መታመም ።

ባልና ፡ ሚስት ፡ የነበሩ ፡ ሁለት ፡ ጓዶች ፡ አያሌ ፡ ዘመን ፡ አብረው ፡ ሲኖሩ ፡ ቈይተው ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ሁለቱንም ፡ በንደ ፡ ጊዜ ፡ ተስቦ ፡ ያዛቸው ፡ የወሰዱት ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ስለ ፡ ነበሩባቸውም ፡ እሷ ፡ ጠንክራ ፡ ሳት ሰለች ፡ ታስታምማቸው ፡ ገ/መር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ሀብት ፡ ወይም ፡ ቅርስ ፡ የሌ ላቸው ፡ በመሆኑ ፡ ድኽነት ፡ እየተጫናቸው ፡ ሄደና ፡ የሚበሉት ፡ አንኳን ፡ እኽል ፡ አጡ ። በመጨረሻውም ፡ በቤታቸው ፡ ውስጥ ፡ ላዋያ ፡ ያስቀመ ጡት ፡ አንድ ፡ አሞሌ ፡ ነበራቸውና ፡ ልጅቲን ፡ እንቲ ፡ በዚህ ፡ አሞሌ ፡ እኽል ፡ ሽምተሽ ፡ አምጪልን ፡ ብለው ፡ ሰደዷት ።

ያችም ፡ ልጅ ፡ እገበያ ፡ ወጥታ ፡ በዚያች ፡ ጨው ፡ ለገሮሮዋ ፡ ጉትቻ ፡ ገዝታ ፡ አጊጣ ፡ መጣች ። እቤትም ፡ በገባች ፡ ጊዜ ፡ እነዚያ ፡ የታመሙ ፡ ሰዎች ፡ እኽል ፡ በጣም ፡ ናፍቋቸው ፡ ነበርና ፡ ግና ፡ ከመመለሷ ፡ የሸመተችው ፡ እኽል ፡ የታለ ፡ ብለው ፡ ጠየቋት ።

እርሷም ፡ እሱ ፡ ለበሳው ፡ ጉሮሮ ፡ እሱው ፡ ያስብለት ፡ ብዬ ፡ አኔ ፡ ለበሳሁት ፡ ገሮሮዬ ፡ ጉትቻ ፡ ገዝቼበት ፡ መጣሁ ፡ በማለት ፡ ሳታፍርና ፡ ሳት ፈራ ፡ በቀጥታ ፡ ነገረቻቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በሽተኞቹ ፡ በንዴት ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ ሳለ ፡ ማታውን ፡ ንጋዬዎች ፡ ብዙ ፡ እኽል ፡ በወቀሬና ፡ በእጋሰስ ፡ ጭነው ፡ መጥተው ፡ በሽተኞቹ ፡ ካሉበት ፡ ቤት ፡ አሳድሩን ፡ ብለው ፡ ለመኑ ።

ልጅቲም ፡ ርኅርኅት ፡ በመሆኗ ፡ ተቀብላ ፡ አሠፈረቻቸው ። ዐሲት ፡ በማ ለዳ ፡ ወፍ ፡ ያልቀመሰው ፡ ውሃ ፡ ቀድታ ፡ ወላጆቿን ፡ ስታጠምቃቸው ፡ መሸዳሪዎቹ ፡ አይተው ፡ ምን ፡ ሆነዋል ፡ ብለው ፡ ጠየቋት ። እርሷም ፡ በተ ስቦ ፡ ታመዋል ፡ ስትል ፡ መለሰችላቸው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እነዚያ ፡ ንጋዬዎች ፡ ደንግጠው ፡ ከተስቦ ፡ ቤት ፡ ያራገፉትን ፡ እኽል ፡ ጭነን ፡ ሄደን ፡ ልጅቱ





እሱ ፡ ለበሳው ፡ ጉሮሮ ፡ እሱው ፡ ያስብለት ፡ ብዬ ፡ እኔ ፡ ለበሳሁት ፡ ገሮዬ ፡ ጉትቻ ፡ ገዝቼበት ፡ መጣሁ ፡

ወላጆቿን ፡ ስትመለከቻቸው ፡ መሸዳሪዎቹ ፡ አይተው ፡ ምን ፡ ሆነዋል ፡ ብለው ፡ ጠየቋት ።

ትንንና ፡ ዘመዶቻችንን ፡ በበሽታ ፡ ልናስፈጅ ፡ ነውን ፡ አያሆንም ፡ ይቅ ርብን ፡ ብለው ፡ እኽላቸውን ፡ ከነጭልጊው ፡ ጥለውላት ፡ ሄዱ ።

ልጅቲም ፡ ስለ ፡ ሰጣቸው ፡ ሲሳይ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመስግና ፡ በንጋዬዎቹ ፡ እኽል ፡ እናትና ፡ አባቷን ፡ አስታማ ፡ አዳንች ፡ ይባላል ።

እርሷ ፡ እንዳለችውም ፡ ሁሉ ፡ ለበሳቸው ፡ ጉሮዋ ፡ ጉትቻ ፡ ገዝታ ፡ ብታጌጥ ፡ እሱም ፡ (እግዚአብሔር) ፡ ደግሞ ፡ ስከፈተው ፡ ጉረሮ ፡ አስበ ፡ እኽል ፡ አዘጋጀለት ።

* ስለዚህም ፡ በእውነት ፡ በፈጣሪው ፡ ያመነ ፡ ሁሉ ፡ የፈለገውን ፡ ለማግኘት ፡ እንደሚችል ፡ እንወቅ ። የናትና ፡ ያባትን ፡ ትእዛዝ ፡ መጣስ ፡ የማይገባ ፡ መሆኑንም ፡ እንርሳ ።

ያንድ ፡ ድኻ ፡ ሰው ፡ ኑዛዜ ።

ሁለት ፡ ወንድ ፡ ልጆች ፡ የወለደ ፡ አንድ ፡ ድኻ ፡ ሰው ፡ ነበር ። ጊዜ ፡ ሞቱ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ያለው ፡ ሀብት ፡ አንድ ፡ ወደል ፡ አህያ ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ ይህንኑ ፡ ልጆቹ ፡ እንዲካፈሉት ፡ ተናዘዘ ፡ ወዲያው ፡ እሱም ፡ እጅግ ፡ ሳይሰነብት ፡ ለሞት ፡ በቃ ።

አንደኛው ፡ ልጅ ፡ በጣም ፡ በለጸጋ ፡ ሲሆን ፡ ሁለተኛው ፡ ግን ፡ የሰለች ፡ ራት ፡ የሌለው ፡ ችግረኛ ፡ ነበር ። ከድኽነቱም ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ገና ፡ አባቱ ፡ ከመሞቱ ፡ የሚበላው ፡ ቸገረው ። ስለዚህም ፡ ከበርቱ ፡ ወንድሙን ፡ እባክህ ፡ ወንድሜ ፡ ይኽንን ፡ አህያችንን ፡ ሸጠን ፡ እንካፈል ፡ አለና ፡ ለመነው ። ያም ፡ በለጸጋ ፡ በሀብቱና ፡ በገንዘቡ ፡ ብዛት ፡ ተመክቶ ፡ ለችግረኛው ፡ ወንድሙ ፡ እኔ ፡ አርጀ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሸጬ ፡ አልካፈልም ፡ ሲል ፡ በመቃወም ፡ መለሰለት ።

በዚሁ ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ተጣሉ ፡ በሀገሩ ፡ ከሚገኘው ፡ ዳኛ ፡ ዘንድ ፡ ሄዱ ። በለጉዳዮቹም ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የመጡበትን ፡ በየተራቸው ፡ ዘርዝረው ፡ አመለከቱት ። ዳኛውም ፡ በሁለቱም ፡ በኩል ፡ የቀረበለትን ፡ መግለጫ ፡ ከሰማ ፡ በኋላ ፡ አርዳችሁ ፡ ተካፈሉት ፡ ብሎ ፡ ፈረደ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሀብታሙ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ አለው ፡ ችግረኛው ፡ ግን ፡ አገሮ ፡ አምሮ ፡ አለቀሰ ። ሆኖም ፡ ከዳኛ ፡ የተሰጠ ፡ ትእዛዝ ፡ መከበርና ፡ መፈጸም ፡ ስላለበት ፡ ወደል ፡ አህያው ፡ ታረደና ፡ ሥጋው ፡ እሁለት ፡ ላይ ፡ ተመደበ ። በለጸጋው ፡ ድርሻውን ፡ ለውሾቹ ፡ ሰጣቸው ። ድኻው ፡ ግን ፡ እንኳን ፡ ውሻ ፡ ዶሮ ፡ የሌለው ፡ ነበርና ፡ ፈንታውን ፡ ከታረደበት ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ጥሎት ፡ ሄደ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እያዘነና ፡ እየተከዘ ፡ ተቀምጦ ፡ ሳለ ፡ በድንገት ፡ ቤቱን ፡ በእሳት ፡ አቃጥዬ ፡ እሄዳለሁ ፡ ብሎ ፡ ተነሣ ፡ የሚኖርበት ፡ ጎጆና ፡ የበለጸጋውም ፡ ትልልቅ ፡ አዳራሾች ፡ በንድ ፡ አጥር ፡ ግቢ ፡ ውስጥ ፡ ይገኙ ፡ ነበር ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በለጸጋው ፡ ከብቱና ፡ ገንዘቡ ፡ አሳዝኖት ፡ ግሙቱን ፡ ልስጥህ ፡ እንጂ ፡ ለምን ፡ ታቃጥላለህ ፡ ያለዚያ ፡ የኔም ፡ ቤት ፡ አብሮ ፡ ሊነድ ፡ አይደለምን ፡ አለው ። እሱም ፡ እንቢ ፡ እኔ ፡ ገንዘብ ፡ አያሻኝም ፡ ቤቴን ፡ አቃጥዬ ፡ ነው ፡ የምሄደው ፡ ሲል ፡ አጥብቆ ፡ መለሰለት ።

እንግዲያውስ ፡ ዳኛ ፡ ሳይፈርድ ፡ እንዲሁ ፡ ተነሥተህ ፡ አታቃጥልም ፡ በማለት ፡ ጠብ ፡ አብቅለው ፡ ሳለ ፡ ገላጋይ ፡ ስለ ፡ ገባቸው ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለማመልከት ፡ ተያይዘው ፡ ሄዱ ። ዳኛውም ፡ የሚያውቁት ፡ ያው ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ የፈረደው ፡ ነበር ። እሱም ፡ ሁለቱም ፡ ባለጋራዎች ፡ ያመለከቱትን ፡ ከሰማ ፡ በኋላ ፡ ቤቱን ፡ አቃጥሎ ፡ ይሂድ ፡ እንጂ ፡ ለማን ፡ ብሎ ፡ የደከመበትን ፡ ጥሎ ፡ ይሄዳል ፡ ሲል ፡ ፍርድ ፡ ሰጠ ።



ወደል ፡ አህያው ፡ ታረደና ፡ ሥጋው ፡ ከሁለት ፡ ላይ ፡ ተመደበ ።

በለጉዳዮውም ፡ ዳኛው ፡ እንደ ፡ ፈረደለት ፡ ቤቱን ፡ በእሳት ፡ ለኩሰው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የዘያንም ፡ የባለጸጋ ፡ ወንድሙን ፡ አዳራሽ ፡ ነፋስ ፡ ተነሥቶ ፡ ነበርና ፡ እሳቱ ፡ ተመዘግዝጎና ፡ ተወርውሮ ፡ ተያያዘው ። ምንም ፡ ቢጨኬኽና ፡ ቢደክምም ፡ ለማዳን ፡ ስላልቻለ ፡ እልፍኙ ፡ ማድ ፡ ቤቱ ፡ ጎተራውም ፡ ሳይቀሩ ፡ በሙሉ ፡ ተቃጠሉበት ።

አደጋው ፡ ከሰፈ ፡ በኋላ ፡ ባለጸጋው ፡ ቤቶቹ ፡ በተቃጠሉበት ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ የመኖሪያ ፡ ቤቱን ፡ ቀልሶ ፡ ሲቀመጥ ፡ ድኻው ፡ ደግሞ ፡ ጎጆው ፡ የነበረበትን ፡ ድርሻ ፡ ቦታውን ፡ ቈፍሮ ፡ ባቄላ ፡ ዘራው ። በሸ



እሰቱ ተምዘግዝን ፡ የባለጸጋውን ፡ አዳራሽ ፡ ተያያዘው ።

ቱም ፡ መራት ፡ የባለጸጋው ፡ ሲት ፡ ልጅ ፡ ከባቄላው ፡ ውስጥ ፡ ገብታ ፡ እሸት ፡ ስትበላ ፡ ያዝትና ፡ መዲያው ፡ ገላጋይም ፡ ዚገባ ፡ አሸንፎ ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይዟት ፡ ሄደ ። ጌታዪ ፡ ሆይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያሳይዎ ፡ የድኻ ፡ ባቄላዬን ፡ ስትበላ ፡ ያዝኳት ፡ ሆዷን ፡ ሰንጥቄ ፡ ባቄላዬን ፡ እን ድወስድ ፡ ፍርድ ፡ ይስጡኝ ፡ ሲል ፡ አቤቱታውን ፡ ለዳኛው ፡ አቀረበ ።


የልጅቲ ፡ አባትም ፡ በበኩሉ ፡ ባቄላ ፡ ባቄላ ፡ ነው ፡ ይልቁንም ፡ ድልቦን ፡ በገራ ፡ ያለውን ፡ በሙሉ ፡ ይውሰድ ፡ እንጂ ፡ እንዴት ፡ ልጄን ፡



በሸቱም ፡ መራት ፡ የባለጸጋው ፡ ሲት ፡ ልጅ ፡ ከባቄላ ፡ ውስጥ ፡ ገብታ ፡ እሸት ፡ ስት በላ ፡ ያዛት ።

ሆዷን ፡ ይሰነጥቃል ፡ ሲል ፡ ለዳኛው ፡ ቢያመለክት ፡ ድኻው ፡ እሆዷ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ የራሴን ፡ ባቄላ ፡ እንጂ ፡ ያንተን ፡ የገራ ፡ እኽል ፡ አልፈልግም ፡ ብሎ ፡ መለሰ ።

ዳኛውም ፡ መቼም ፡ ፍርደ ፡ ገምድል ፡ ነውና ፡ ልጅቲን ፡ ሆዷን ፡ ሠንጥቆ ፡ የራሱን ፡ ባቄላ ፡ እውጥቶ ፡ ይውሰድ ፡ ሲል ፡ ፈረደ ። ለዚህ ፡ ጊዜ ፡ ያ ፡ ድኻ ፡ ተደስቶ ፡ ስፈነጥዝ ፡ ባለጸጋው ፡ ያሰኝን ፡ ሀብት ፡ ውሰድ ፡ እንጂ ፡ እንዴት ፡ አድርገህ ፡ ልጄን ፡ ታርዳለህ ፡ ሲል ፡ ጠየቀው ። እሱም ፡ አንተ ፡ በማን ፡ ሀገር ፡ ኖረል ፡ አህያ ፡ ሲታረድ ፡ ያየኸው ፡ አለው ።



ዳኛውም ፡ ልጅቲን ፡ ሆዷን ፡ ሠንጥቆ ፡ የራሱን ፡ ባቄላ ፡ አውጥቶ ፡ ይውሰድ ፡ ሲል ፡ ፈረደ ።

በዚህም ፡ መካከል ፡ የሀገር ፡ ሽማግሌች ፡ በግልግል ፡ ገብተዋቸው ፡ እንዲታረቁ ፡ ቢለምኑት ፡ አህያ ፡ አርዶብኝ ! አላቸው ። ይቅር ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ነውና ፡ እባክህ ፡ ብለው ፡ እንደ ፡ ባለጸጋው ፡ ፍላጎት ፡ ሀብቱን ፡ እኩል ፡ ለኩል ፡ አካፍለው ፡ እርቅ ፡ እንዲሆን ፡ ስላደረጉ ፡ ልጅቲ ፡ ከመቀደድ ፡ ድና ፡ ያኸውም ፡ ከችግሩ ፡ መጥቶ ፡ ኑሮውን ፡ በደስታ ፡ ስማሰናፍ ፡ ቻለ ይባላል ።

፠ ልቦናቸው ፡ የዋህ ፡ ለሆነ ፡ ሰዎች ፡ እግዚአብሔር ፡ ቅርባቸው ፡ ነው ። ምንም ፡ ቢውል ፡ ቢያድር ፡ በሰፈሩት ፡ ቀሩና ፡ መሰረር ፡ የማይቀር ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፡ ከእንደዚህ ፡ ያለው ፡ የተንኰልና ፡ የጭካኔ ፡ መንፈስ ፡ መራቅ ፡ ይገባል ።

ሦስት ፡ ቂል ፡ ወንድማማቾች ።

ሦስት ፡ ቂል ፡ ወንድማማቾች ፡ በንድነት ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። ከሰለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አብረው ፡ ሲሄዱ ፡ አልም ፡ ከለ ፡ ገደል ፡ አፋፍ ፡ ላይ ፡ ለሞ ፊር ፡ የሚሆን ፡ ዛፍ ፡ አገኙና ፡ መቀረጥ ፡ ገመሩ ። ነገር ፡ ግን ፡ መሣሪ ያው ፡ ያልሰላ ፡ ሆኖ ፡ ቢሉት ፡ ቢሠሩት ፡ የማይወድቅላቸው ፡ ዘ.ሆን ፡ በዘ.ህ ፡ ተበሳጩና ፡ አንደኛው ፡ ሁለቱን ፡ ወንድሞቹን ፡ እጫኖ ፡ ላይ ፡ ወጥታችሁ ፡ ክዘዱት ፡ እኔ ፡ ከሥር ፡ ልቀረጥ ፡ አላቸው ። እነሱም ፡ እሺ ፡ መልካም ፡ ሐሳብ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ፈጥነውና ፡ አናቱ ፡ ላይ ፡ ፈጥ ፡ ፈጥ ፡ አሉና ፡ እንዲወድቅ ፡ ያወዛወዙት ፡ ገመር ። ያም ፡ ዛፍ ፡ ክርክሩ ፡ ጉድቶት ፡ ኖሮ ፡ ወዲያው ፡ ይዟቸው ፡ ወደ ፡ ገደሉ ፡ ገባ ። ቄራፌ ፡ ተናደ ፡ አረ ፡ ጉድ ፡ ሞፈሩን ፡ ይዘውት ፡ ጠፉ ፡ ብሎ ፡ በዚያው ፡ በገቡበት ፡ ተከታትሎ ፡ ቁልቁል ፡ ዘሎ ፡ ወረደ ።



ቄራፌ ፡ ተናደ ፡ አረ ፡ ጉድ ! ሞፈሩን ፡ ይዘጠት ፡ ጠፉ ፡ ብሎ ፡ በዚያው ፡ በገቡበት ፡ ተከታትሎ ፡ ቁልቁል ፡ ዘሎ ፡ ወረደ ።

፨ እምብዛም ፡ ቂልነት ፡ ያደርሳል ፡ ከሞት ። በሬ ፡ ሆይ ፡ ሣሩን ፡ አየ ህና ፡ ገደሉን ፡ ሳታይ ፡ እየተበለ ፡ የሚተረተው ፡ ይህንን ፡ የመሰለ ፡ ነገር ፡ እንዳይደርስ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ መሆኑን ፡ እንገንዘብ ።

የእሳትና ፡ ውሃ ፡ በሬ ፡ መግዛት ።

እሳትና ፡ ውሃ ፡ አብረው ፡ እንድ ፡ በሬ ፡ ገዝተው ፡ ነበር ፡ ይባላል ፡ ያንንም ፡ በሬያቸውን ፡ ሌባ ፡ ሠርቆ ፡ አረደባቸው ።

በዘ.ህ ፡ ጊዜ ፡ አቶ ፡ እሳት ፡ ጌታዬ ፡ አቶ ፡ ውሃ ፡ ካንተ ፡ በቀር ፡ እኔ ፡ ሁሉን ፡ አሸንፋለሁ ፡ የሚችለኝ ፡ የለም ፤ ገንዘቡ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሁ ለታችንም ፡ ነው ። ስለዘ.ህ ፡ ተነሥቼ ፡ ድኑንም ፡ ሣሩንም ፡ ቤቱንም ፡ አቃ ጥዬ ፡ የበሬያችንን ፡ ሌባ ፡ ልፈልገው ፡ አለው ። ውሃውም ፡ ወንድሜ ፡ አቶ ፡ እሳት ፡ ምነው ፡ እንደዘ.ህ ፡ ማለትህ ፡ የሠረቀውንም ፡ ደኅናውንም ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ አድርጎ ፡ ማቃጠል ፡ የሚገባ ፡ ነውን ፡ ሌባችንን ፡ ለመያዝ ፡ አንድ ፡ ሆነ ፡ የሚቸግረን ፡ ነገር ፡ የለም ፤ አሁን ፡ እናገኘዋለን ።

እጠብስ ፡ ያለ ፡ ካንተ ፡ አጥብ ፡ ያለ ፡ ከኔ ፡ የሚቀር ፡ አለን ፡ በዘ.ያ ፡ ጊዜ ፡ ልንይዘው ፡ ይቻላል ፡ ሲል ፡ መለሰለት ። ወዲያው ፡ ይኸንን ፡ ተነ ጋግረው ፡ ጥቂት ፡ ሰይቈዩ ፡ አንዱ ፡ ቅልጥም ፡ ይዘ ፡ ወደ ፡ እሳት ፡ መጣ ፡ አንደኛው ፡ ደግሞ ፡ ጨንፈ ፡ ሊያጥብ ፡ ከውሃ ፡ ዘንድ ፡ ሄደ ። በዘ.ህ ጊዜም ፡ ሌቦቹ ፡ ስለ ፡ ታወቀ ፡ ተያዙና ፡ ታሰሩ ፡ ይባላል ።

፨ መተባበርን ፡ ገንዘብ ፡ ያደረገ ፡ ጠላቱን ፡ ያሸንፋል ።

የዝንጅሮ ፡ ገደል ፡ መግባት ።

ዝንጅሮ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ በእንቅልፍ ፡ ምክንያት ፡ ገደል ፡ ገብቶ ፡ ጮኩ ፡ ደቀቀ ፡ እጁ ፡ ተሰበረ ፡ እግሩ ፡ ተቈላመመ ፡ ሕመሙም ፡ እየጠናበት ፡ ሄደ ፡ እንዲያውም ፡ ሞት ፡ የሚያሠጋው ፡ ሆነ ። ስለዚህ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ለሚስ ቱና ፡ ለልጆቹ ፡ ለዘመዶቹም ፡ እንግዲህ ፡ እኔ ፡ እንደምታዩኝ ፡ ሕመሜ ፡ እየጠና ፡ ከመሔዱ ፡ በስተቀር ፡ ምንም ፡ የመዳን ፡ ተስፋ ፡ የለኝም ። አሁን ፡ በቁሜ ፡ ሕያዉቱ ፡ ሳለ ፡ ዐይኔ ፡ እያየ ፡ ልጆቹ ፡ ሚስቱ ፡ ዘመዶቹም ፡ ሁና ችሁ ፡ ልቅሶዬን ፡ በቁሜ ፡ አልቅሱልኝ ፡ አላቸው ፡



እንግዲህ ፡ እኔ ፡ እንደምታዩኝ ፡ ሕመሜ ፡ እየጠና ፡ ከመሔዱ ፡ በስተቀር ፡ ምንም ፡ የመዳን ፡ ተስፋ ፡ የለኝም ፡ አሁን ፡ በቁሜ ፡ ሕያዉቱ ፡ ሳለ ፡ ዐይኔ ፡ እያየ ፡ ልጆቹ ፡ ሚስቱ ፡ ዘመዶቹም ፡ ሁናችሁ ፡ ልቅሶዬን ፡ በቁሜ ፡ አልቅሱልኝ ፡ አላቸው ።

ይህንንም ፡ ቃሉን ፡ ስለ ፡ ነገራቸው ፡ ሚስቱና ፡ ልጆቹ ፡ ዘመድ ፡ አገ ማዱቻቸውን ፡ ጠርተው ፡ በሰፊ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ተሰብስበው ፡ ለቅሷቸውን ፡ ዠመሩ ። ።

ለቅሶውም ፡ በተፋፋመ ፡ ሰዓት ፡ «ወንገረዝ» ፡ የሚባለው ፡ ወንድ ፡ ልጁ ፡ ተነሥቶ ፡ አባቱ ፡ አሚዴ ፡ አባቱ ፡ አሚዴ ፡ አሚዴ ፡ አሚዴ ፡ ዘገር ፡ ነቅናቂው ፡ ጋሻ ፡ መከቹ ፡ ገዳዩ ፡ ፈረሰኛው ፡ አሚዴ ፡ አባ ፡ መንትፍ ፡ ያለው ፡ ባሕር ፡ ቀጋ ፡ ከቀኑልጭ ፡ ተነሥቶ ፡ እምቡስ ፡ የሚዋጋ ፡ እያለ ፡ ሲያለቅስ ፡ ተው ፡ ተው ፡ ያለሥራዬ ፡ ልጄ ፡ ያህ ፡ መቼ ፡ የኔ ፡ ሞያ ፡ ነው ፡ እለና ፡ በቀጣ ፡ ቃል ፡ ተናገረው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሴት ፡ ልጁን ፡ «ትውረስን» ፡ እስቲ ፡ አንቺ ፡ ተነሽ ፡ ልጄ ፡ አላት ። እሷም ፡ ተነሣችና ፡ አባቱ ፡ አሚዴ ፡ አባቱ ፡ አሚዴ ፡ ወደል ፡ ውሻ ፡ ገልማጭ ፡ በገደል ፡ ላይ ፡ ሯጭ ፡ የሰው ፡ ነዶ ፡ ዘርጣጭ ፡ አሚዴን ፡ ገደሉት ፡ አግኝተው ፡ በግላጭ ፡ ብላ ፡ በገጠመች ፡ ጊዜ ፡ እሱ ፡ ነዋ ፡ ልጄ ፡ እሱ ፡ ነዋ ፡ አለ ። ደግሞ ፡ የእንጀራ ፡ ልጁ ፡ ተነሣችና ፡

አንኳን ፡ መሞትና ፡ ይፍላበት ፡ በረዶ ፡
ሳያቀምሰኝ ፡ ቀርቷል ፡ ከሰረቀው ፡ ነዶ ፤ ባለች ፡ ጊዜ ፡ ልጁ ፡ ደግሞ ፡ መለስ ፡ አድርጋ ፡

ምነው ፡ የናቱ ፡ ልጅ ፡ ምነው ፡ የምዬ ፡ ልጅ ፡ ይሙት ፡ ትያለሽ ፡ ያድነን ፡ ነበረ ፡ ከምሳ ፡ ወደል ፡ ውሻ ፡ ብላ ፡ ገጠመች ። በዚህም ፡ ልብ ፡ በሚነካ ፡ ግጥሚ ፡ ከዚያ ፡ የተሰበሰበውን ፡ ዘመድ ፡ አዝማድ ፡ ትንሽ ፡ ትልቁን ፡ በአንባ ፡ አራጨችው ፡ ይባላል ።

፨ እንኳን ፡ ያሳደገን ፡ አባትና ፡ ማንንም ፡ በዕድሜ ፡ የሸመገለውን ፡ ሁሉ ፡ ማክበር ፡ ይገባል ።

ያለማያው ፡ የሚደረገው ፡ ምስጋና ፡ ሁሉ ፡ በስተዋዮች ፡ ዘንድ ፡ አንደ ፡ ስድብ ፡ ይቈጠራል ፤ ስለዚህ ፡ ልጆቼ ፡ ይኸን ፡ የመሳሰለውን ፡ አርአያ ፡ ከመከተል ፡ ጥንቃቄ ፡ አድርጉ ።

ድኻ፡ ጥጃ።

እናቱ ፣ የሞተችበት ፣ ድኻ ፣ ጥጃ ፣ ነበረ ፣ ይባላል ። ከዕለታት ፣ አንድ ፣ ቀን ፣ ሣር ፣ ወደ ፣ ለመለመበት ፣ ውሃ ፣ ወደ ፣ ፈለቀበት ፣ ተሰዶ ፣ ሲሄድ ፣ ፍየል ፣ አገኝችውና ፣ አያ ፣ ድኻ ፣ ጥጃ ፣ ወዴት ፣ ትሄዳለህ ፣ በማለት ፣ ጠየቀችው ። እሱም ፣ ሣር ፣ ኔለመለመበትና ፣ ውሃ ፣ እፈለቀበት ፣ አላት ። እንግዲያውስ ፣ እባክህ ፣ እኔንም ፣ አስከትለኝ ፣ አለችው ።

—አንቺ ፣ አፍሽ ፣ አያርፍ ፣ ስትለፈልፊ ፣ ታስበለኛለሽ ፣

—እረ ፣ እኔ ፣ አላስበላህም ።

—እንግዲያውስ ፣ ነዪ ፣ ተነሽ ፣ እንሂድ ፣ ብሎ ፣ አስከትሏት ፣ ሄደ ።

ደግሞ ፣ ሦስተኛ ፣ አቶ ፣ ዶሮ ፣ አገኛቸው ። አያ ፣ ድኻ ፣ ጥጃ ፣ ወዴት ፣ ትሄዳለህ ፣ ሲል ፣ ጠየቀው ። ሣር ፣ እለመለመበት ፣ ውሃ ፣ እፈለቀበት ፣ በማለት ፣ መለሰለት ። እባክህ ፣ እኔንም ፣ አስከትለኝ ፣ ቢለው ፣ ኳክ ፣ ኳክ ፣ ስትል ፣ ታስበላኛለሃ ፣ አላደርገውም ፣ አለው ፤ ስለዚህ ፣ ጥጃው ፣ ፈቀደለትና ፣ ጉዟቸውን ፣ ቀጠሉ ።

ወይዘሮ ፣ ጦጢትም ፣ እንደዚሁ ፣ አያ ፣ ድኻ ፣ ጥጃ ፣ ወዴት ፣ ትሄዳለህ ፣ አለችው ፤ እሱም ፣ ሣር ፣ እለመለመበት ፣ ውሃ ፣ እፈለቀበት ፣ ነዋ ፣ አላት ። እባክህ ፣ እኔንም ፣ አስከትለኝ ፣ ስላለችው ፣ ታስበለኛለሽ ፣ አላት ። እረ ፣ እንዴት ፣ አድርጌ ፣ አላስበላህም ፣ እንደ ፣ ምንም ፣ ብለህ ፣ አስከትለኝ ፣ አለችው ።



ምን ፣ ቸገረኝ ፣ ከሆነልሽ ፣ በዪ ፣ እንሂድ ፣

ምን ፣ ቸገረኝ ፣ ከሆነልሽ ፣ በዪ ፣ እንሂድ ፣ ብሏት ፣ አብረው ፣ ሲሄዱ ፣ ውሃው ፣ እፈለቀበት ፣ ሣሩ ፣ እለመለመበት ፣ ቦታ ፣ ደርሰው ፣ ከዚያ ፣ ሆነው ፣ ሲበሉና ፣ ሲጠጡ ፣ ስለ ፣ ሰነበቱ ፣ ጥጋብና ፣ እብሪት ፣ ተሰማቸው ።

ፍየል ፤ አያ ፣ ድኻ ፣ ጥጃ ፣ ነፋኝ ፣ ቀበተተኝ ፣ አንድ ፣ ጊዜ ፣ እባክህ ፣ ሚያ ፣ ልበልና ፣ ይውጣልኝ ፣ አለችው ። ድኻ ፣ ጥጃም ፣ ተዪ ፣ አይሆንም ፣ ነብር ፣ ይሰማና ፣ መጥቶ ፣ ይበላሽል ፣ አላት ። ግድ ፣ የለህም ፣ አይበላኝም ፣ በማለት ፣ መልስ ፣ ሰጠችው ። እሱም ፣ በዪ ፣ እንግዲያው ፣ ይውጣልሽ ፣ ሚያ ፣ በዪ ፣ አላት ። ሚያ ፣ ስትል ፣ እንደ ፣ ተናገረው ፣ ነብር ፣ መጥቶ ፣ ወደ ፣ ጫካ ፣ ይዟት ፣ ገባ ።

ዶሮ ፣ ደግሞ ፣ አያ ፣ ድኻ ፣ ጥጃ ፣ እንድ ፣ ጊዜ ፣ ኳክ ፣ ልበልና ፣ ይውጣልኝ ፣ እባክህ ፣ አለው ። ተው ፣ አይሆንም ፣ መጠማጥ ፣ ይበላሃል ፣ ይቅርብህ ፣ አለው ። እሱም ፣ ግድ ፣ የለህም ፣ አይበላኝም ፣ ቢለው ፣ በል ፣ እንዳሰኘህ ፣ ነገር ፣ ግን ፣ በኋላ ፣ እንዳትጸጸት ፣ ብሎ ፣ መከረው ። አቶ ፣ ዶሮም ፣ ኳክ ፣ ሲል ፣ መጠማጥ ፣ መጥቶ ፣ ይዘት ፣ ሄደ ።

ጦጢትም ፣ እንደዚሁ ፣ አያ ፣ ድኻ ፣ ጥጃ ፣ እረ ፣ እባክህ ፣ እኔንም ፣ ነፋኝ ፣ ፈቃድ ፣ አድርግልኝና ፣ አንድ ፣ ጊዜ ፣ ጮኬ ፣ ተንፈስ ፣ ልበል ፣ አለችና ፣ ለመነችው ። እረ ፣ ተዪ ፣ እባክሽ ፣ አንቺ ፣ እንኳ ፣ ቻል ፣ አድርጊው ፤ ነብር ፣ መጥቶ ፣ ይበላሻል ፣ አላት ። ምን ፣ ላድርግ ፣ አልችል ፣ አልኩ ፣ እኮ ፣ እንደ ፣ በላ ፣ ይብላኝ ፣ ብትለው ፣ በዪ ፣ አንቺው ፣ ነበርሽ ፣ የቀረሽው ፣ ሞት ሽን ፣ ከፈለግሽ ፣ ፍጪኺ ፣ አለና ፣ ፈቀደላት ። ስትጮኽ ፣ ያ ፣ ነብር ፣ ሰምቶ ፣ መጣና ፣ ለመብላት ፣ ቢያበርራት ፣ ካንዱ ፣ ዛፍ ፣ አንዱ ፣ ላይ ፣ እያለች ፣ በማወክ ፣ እቃተችው ። እሱም ፣ ሰለቸውና ፣ ጥሏት ፣ ሄደ ።

አያ ፣ ድኻ ፣ ጥጃ ፣ እንግዲህ ፣ ሁለታችን ፣ ብቻ ፣ ቀረን ፣ ተነሥተን ፣ ወደ ፣ ሀገራችን ፣ እንሄድምን ፣ አለችው ። እሺ ፣ ከሆነማ ፣ ሁላችንም ፣ በሰው ፣ አገር ፣ እንደ ፣ ወጣን ፣ ከምንቀር ፣ ብንመለስ ፣ መቼ ፣ እጠላለሁ ፣ ብሎ ፣ ተነሥተው ፣ ሲሄዱ ፣ አያ ፣ ድኻ ፣ ጥጃ ፣ ወፍሮ ፣ መሄድ ፣ አቅቶት ፣ በፋፍ ፣ ላይ ፣ ሲሄዱ ፣ አዳለጠውና ፣ ወርዶ ፣ ከፈፋ ፣ ውስጥ ፣ ተወተፈ ።

ጠጪትም ፡ እንደምታወጣው ፡ ተቸግራ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ስትንቄራ ጠጥ ፡ ብዙ ፡ ነጋዴዎች ፡ ማር ፡ በጭልጊ ፡ ጭነው ፡ መጡ ። ጌቶቼ ፡ አቶ ፡ ድኻ ፡ ጥጃ ፡ ገደል ፡ ገብቶብኛልና ፡ እባክችሁ ፡ አውጡልኝ ፡ አለቻቸው ። እኛ ፡ መን ገደኞች ፡ ነን ፡ ጊዜውም ፡ መሽቶብናል ፡ ማራችንንስ ፡ ማን ፡ ይጠብቅልናል ፡ አሏት ። ለዚህማ ፡ እኔ ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ ሥራ ፡ ይዤ ፡ ነው ፡ የምታስዙት ፡ እኔ ፡ እጠብቃለሁ ፡ አለቻቸው ። እንግዲያውስ ፡ እናወጣዋለን ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ገደሉ ፡ ወረዱ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እርሷ ፡ ያንን ፡ ማራቸውን ፡ ከፍታ ፡ ሆዷ ፡ የቻለውን ፡ ያኽል ፡ በላችና ፡ ጭልጊውንና ፡ ገንቦውን ፡ ዐፈሩንም ፡ ዐዛባውንም ፡ ድንጋዩንም ፡ ሞልታ ፡ እንዳይታወቅባት ፡ ከሷሪ ፡ ማር ፡ እድርጋ ፡ መርጋ ፡ ቄየቻቸው ። ነጋዴዎቹም ፡ እንደ ፡ ሰጡት ፡ ቃል ፡ ጓደኛዋን ፡ አወጡላትና ፡ አቶ ፡ ድኻ ፡ ጥጃን ፡ ይዛ ፡ መንገዷን ፡ ቀጠለች ። ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ከሄዱ ፡ በኋላ ፡ ከነጋዴዎቹ ፡ አንደኛው ፡ እረ ፡ ይህ ፡ ማር ፡ ምነው ፡ ከበደኝ ፡ አለ ። እንዱ ፡



ማራቸውን ፡ ከፍታ ፡ ሆዷ ፡ የቻለውን ፡ ያህል ፡ በላችና ፡ ዐፈሩንም ፡ ዐዛባውንም ፡ ሞልታ ፡ መርጋ ፡ ቄየቻቸው ።

ደግሞ ፡ እረ ፡ ታልከስ ፡ እኔንም ፡ ገማኝ ፡ አለና ፡ ወዲያው ፡ ከፍተው ፡ ቢያዩ ፡ ዐዛባ ፡ ድንጋይና ፡ ዐፈር ፡ ሆነባቸው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አንደኛው ፡ ይህንን ፡ ያደረገች ፡ ያቺ ፡ ጦጣ ፡ መሆኗ ፡ የተረጋገጠ ፡ ነውና ፡ ሄደን ፡ እንያዛት ፡ አለ ። ሌላው ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ እናውቃታለን ፡ ሲል ፡ መለሰ ። እሷማ ፡ ዥራተ ፡ ቄራጣ ፡ ብለምልክት ፡ ናት ፡ እታመልጠንም ፡ ሲባባሉ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሰምቶ ፡ ኖሮ ፡ ሮጦ ፡ ሄደና ፡ ለሚት ፡ ጦጢት ፡ በዥራትሽ ፡ ምልክት ፡ ሊይዙሽ ፡ ነውና ፡ ተጠንቀቂ ፡ ብሎ ፡ ነገራት ። እሷም ፡ ወዲያው ፡ ቶሎ ፡ ብላ ፡ ወደ ፡ ጓደኞቿ ፡ ሄደች ።

ዘመዶቿም ፡ ወይዘሮ ፡ ጦጢት ፡ ዥራትሽን ፡ ምን ፡ ጐረደው ፡ አሏት ። አጤ ፡ ቢወዱኝ ፡ ቄረጡልኝ ፡ አለቻቸው ። ከመከከላቸው ፡ አንዱ ፡ እንግዲያውማ ፡ እባክሽ ፡ የኔንም ፡ ቀሩልኛል ፡ አለቻት ። ሌሎቹም ፡ እንዲሁ ፡ እየተከታተሉ ፡ ቀሩልኛል ፡ ሲሉ ፡ አጥብቀው ፡ ለመኗት ። እሷም ፡ ከስቸገራችሁኝ ፡ ፈቃዳችሁን ፡ አፈጽማለሁ ፡ ብላ ፡ የሁሉንም ፡ ጦጣ ፡ ዥራታቸውን ፡ ቄረጠች ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እነዚያ ፡ ነጋዴዎች ፡ መጣሪያቸውን ፡ ይዘው ፡ ቢሄዱ ፡ ጦጣዎቹ ፡ ሁሉ ፡ ዥራተ ፡ ቄራጣ ፡ ሆነው ፡ አገኟቸው ። ስለዚህም ፡ ማንኛው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለይተው ፡ ለማወቅ ፡ ስለ ፡ ተቸገሩ ፡ የሀገሩ ፡ ጦጣ ፡ ሁሉ ፡ እንዲሰበሰብ ፡ ላገረ ፡ ገዥው ፡ ልመና ፡ አቀረቡ ። እሱም ፡ እንዳመለከቱት ፡ ሁሉ ፡ በቀበሌው ፡ የሚገኘው ፡ ጦጣ ፡ በሙሉ ፡ እንዲከት ፡ አዘዘ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ነጋዴዎቹ ፡ ከወንዝ ፡ ዳር ፡ ወሰዷቸውና ፡ ይኸንን ፡ የዘለለ ፡ ማራችንን ፡ አልበላብንም ፡ ያቃተው ፡ ግን ፡ የዘረፈን ፡ መሆኑ ፡ ነውና ፡ እንቄራኝዋለን ፡ ሲሉ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ሰጡ ። ወዲያው ፡ ዝላይ ፡ ተዠምሮ ፡ ያልበላ ፡ ያልበላው ፡ ሁሉ ፡ ቸረር ፡ እያለ ፡ ሲሻገር ፡ ሌባዋ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ቀርታ ፡ ነበርና ፡ እዘላለሁ ፡ ስትል ፡ ወረደችና ፡ ከውሃው ፡ ውጥስ ፡ ወደቀች ። እሷም ፡ የናቱ ፡ ቀሚስ ፡ አወላከፈኝ ፡ አለችና ፡ ሁለተኛ ፡ ለመገለል ፡ ሞከረች ። አሁንም ፡ መገለል ፡ አቅቷት ፡ ከውስጡ ፡ ረብ ፡ አለች ። ውይ ፡ እቴ ፡ ይኸ ፡ ያባቴ ፡ ጋቢ ፡ አወላከፈኝ ፡ ብላ ፡ ብታመካኝም ፡ አጥፊዋ ፡ እሷ ፡ መሆኗ ፡ ታወቀና ፡ ተይዛ ፡ የፌጥኝ ፡ ታሰረች ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ወስደው ፡ በቀላድ ፡ ከግንድ ፡ ጋራ ፡ ጠፈሩና ፡ ለመደብደቢያ ፡ የደረ ፡ ፍልጥ ፡ ሊያመጡ ፡ ሄዱ ። እዘያው ፡ እንደ ፡ ሆነች ፡ አህያ ፡ መጣና ፡ ወይዘሮ ፡ ጦጢት ፡ ምን ፡ ሆነሽ ፡ ታስረሽል ፡ ሰል ፡ ጠየቃት ። ብዬ ፡ ጠፈ ፡ ቢሉኝ ፡ አልበላ ፡ አልጠጣ ፡ ብዬ ፡ ነዋ ! አባክህ ፡ አንተ ፡ ብላልኝ ፡ ጠጣልኝና ፡ አስፈታኝ ፡ አለችው ። እባክሽን ፡ እንኳን ፡ አንቺን ፡ ላስፈታ ፡ እኔ ለራሴ ፡ የሰው ፡ ነዶ ፡ ዘር ጥፌ ፡ ዕዳ ፡ ገብቻለሁ ፡ አለና ፡ ጥሏት ፡ ሄደ ።

አያ ፡ ዥቦ ፡ ደግሞ ፡ እንኩዬ ፡ ጦጢት ፡ ምን ፡ ሆነሽ ፡ ታስረሽል ፡ በማለት ፡ ጠየቃት ። አያ ፡ ዥቦ ፡ ምኑ ፡ ቅጡ ፡ የኔ ፡ ነገር ፡ ብዬ ፡ ጠፈ ፡ ቢሉኝ ፡ አልበላም ፡ አ ልጠጣም ፡ ብዬ ፡ ነዋ ! አንተ ፡ እባክህ ፡ ብላልኝ ፡ ጠጣልኝ ፡ እለችው ። እኔ ፡ ለራሴ ፡ የሰው ፡ ወደል ፡ አህያ ፡ በልቼ ፡ ለማ ምለጥ ፡ በመሸሽ ፡ ላይ ፡ ነኝና ፡ አንቺን ፡ የማስፈታበት ፡ ጊዜም ፡ አላገኝ ፡ ብሏት ፡ አለፈ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አያ ፡ ዝንጅሮ ፡ ጐንበስ ፡ ጐንበስ ፡ ሲል ፡ መጣና ፡ ወይዘሮ ፡ ጦጢት ፡ ምን ፡ ሆነሽ ፡ ታሰርሽ ፡ ምነው ፡ ምን ፡ አገኘሽ ፡ አላት ። እባክህን ፡ ወንድሜ ፡ የናትና ፡ ያባቴን ፡ ተዝካር ፡ ብዬ ፡ ጠጪ ፡ ቢሉኝ ፡



እጀም ፡ የእናቴ ፡ ቀሚስ ፡ አወላክፈኝ ፡ አለችና ፡ ሁለተኛ ፡ ለመዝለል ፡ ሞክረች።

አልበላም ፡ አልጠጣም ፡ ብዬ ፡ ነዋ ! አለችው ። ታዲያ ፡ ምን ፡ ቸገረሽ ፡ አትበዪም ፡ አትጠጪም ፡ ነበር ! ፡ ቢላት ፡ እኔ ፡ ብታዬን ፡ አላልቅ ፡ አለኝ ፡ አለችው ። እንግዲያው ፡ እኔ ፡ እበላልሻለሁ ፡ እጠጣልሻለሁ ፡ እሰሪኝ ፡ አላት ። ደግ ፡ መልካም ፡ በል ፡ እኔን ፡ ፍታኝና ፡ ልሰርህ ፡ ስትል ፡ መለሰ ችለት ። ፈታትና ፡ እሱን ፡ ከዚያ ፡ ግንድ ፡ ጋራ ፡ የፈጥኝ ፡ ጠፍራ ፡ እንግዲህ ፡ መጥተው ፡ ሲጠይቁህ ፡ እበላለሁ ፡ እጠጣለሁ ፡ በል ፡ ብላ ፡ አስጠነቀቀችው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከዛፉ ፡ ላይ ፡ ወጥታ ፡ ቀጭ ፡ አለች ።

እነዚያም ፡ ሰዎች ፡ ፍልጣቸውን ፡ አዘጋጅተው ፡ ተሸክመው ፡ ቢመጡ ፡ በጦጣዋ ፡ ቦታ ፡ ዝንጅሮ ፡ ተተክቶ ፡ አገኙት ። እንተ ፡ ምን ፡ ታደርጋለህ ፡ ቢሉት ፡ እንኩዬ ፡ ጦጢት ፡ አልበላም ፡ አልጠጣም ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ የታሰርኩት ፡ ብትለኝ ፡ እኔ ፡ እበላልሻለሁ ፡ እጠጣልሻለሁ ፡ ስላልኳት ፡ አስራኝ ፡ ሄደች ፡ አላቸው ። እረ ፡ የታባክንስ ፡ ብለው ፡ በዚያ ፡ በደሬ ፡ ፍልጥ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ቢያቀምሱት ፡ እበላለሁ ፡ እጠጣለሁ ፡ እያለ ፡ ይለፈልፍ ፡ ዝመር ። እሷም ፡ ከንዱ ፡ ቅርንጫፍ ፡ ወዳንዱ ፡ ቅርንጫፍ ፡ እየዘለለች ፡ የጦጣ ፡ ብልጣብልጥ ፡ የዝንጅሮ ፡ ቅልጣቅልጥ ፡ ተው ፡ በለው ፡ በደሬ ፡ ፍልጥ ፡ እያለች ፡ ሥጋው ፡ አልቆ ፡ ዐጥንቱ ፡ እስኪታይ ፡ ድረስ ፡ አስደበደቧቸው ።



እንኩዬ ፡ ጦጢት ፡ አልበላም ፡ አልጠጣም ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ የታሰርኩት ፡ ብትሰኝ ፡ እኔ ፡ እበላልሻለሁ ፡ እጠጣልሻለሁ ፡ ስላልኳት ፡ አስራኝ ፡ ሄደች ።

በመጨረሻው ፡ ሞት ፡ ብለው ፡ ገመዳቸውን ፡ ፈተው ፡ ጥለውት ፡ ሄዱ ። እሱም ፡ ነፍስ ፡ ሲዘራ ፡ የተደበደበው ፡ ተሰማውና ፡ እንኩዬ ፡ ጦጢት ፡ እረ ፡ አመመኝ ፡ ምን ፡ ይሻለኛል ፡ አላት ። ሂድ ፡ እዚያ ፡ ከዛሩ ፡ ላይ ፡ ተንከባለል ፡ አለችው ። እያዘገመ ፡ ተጉዞ ፡ ቢንከባለልበት ፡ ሰማ ፡ ኖሮ ፡ ለበለበው ፡ ደግሞ ፡ እንኩዬ ፡ ጦጢት ፡ እረ ፡ ባሰብኝ ፡ አለና ፡ ነገራት ። እንግዲያው ፡ ሄደህ ፡ እዚያ ፡ እመንደሩ ፡ እጠንብ ፡ ሁነህ ፡ ና ፡ ቡች ፡ ና ፡ ና ፡ ና ፡ እያልክ ፡ ተጣራ ፡ ውሾቹ ፡ መጥተው ፡ ቀስልህን ፡ ይልሱልሃልና ፡ ትድናለህ ፡ አለችው ።

እሱም ፡ እንደ ፡ መከረችው ፡ ሄዶ ፡ ና ፡ ቡች ፡ ና ፡ ቡች ፡ እያለ ፡ በተጣራ ፡ ጊዜ ፡ የመንደር ፡ ውሾች ፡ ሁሉ ፡ ተሰብስበው ፡ መጥተው ፡ ሽረ ከክተውና ፡ ገነጣጥለው ፡ ጨጓራውን ፡ ዘርግፈው ፡ ጣሉት ፡ ይበላል ።

፨ እንኳን ፡ ደግ ፡ ለሠራ ፡ ለክፉ ፡ አድራጊም ፡ ቢሆን ፡ ቀና ፡ መሆን ፡ የተገባ ፡ ነው ። ደፋርና ፡ ጢስ ፡ መውጫ ፡ አያጣም ፤ ሆዱን ፡ ያለ ፡ ሆዱን ፡ ተወጋ ፡ እየተባለ ፡ ካባቶቻችን ፡ የሚነገረው ፡ በጠጣዋና ፡ በዝንጅሮው ፡ የተፈጸመውን ፡ ድርጊት ፡ ሊያሳስበን ፡ ይችላል ።

አንበሳና፡የሰው፡ልጅ።

ሁለት፡ሰዎች፡ልጅ፡ይዘው፡ባንድ፡ውድማ፡ውስጥ፡ሲጓዙ፡ወን በደዎች፡ለገንዘባቸው፡መዝረፍ፡ሲሉ፡ገደሏቸው። ልጁን፡ግን፡ባባ ትና፡እናቱ፡ሬሳ፡አጠገብ፡ወድቆ፡ከነሕይወቱ፡እንበሳ፡ስላገኘው፡ወደ፡ ማረፊያው፡ወስዶ፡አስቀምጦ፡ማናቸውንም፡ስምግብ፡የሚሆነውን፡ ሁሉ፡እያደነ፡አብልቶ፡አጠጥቶ፡አሳደገው።



ልጁን፡ግን፡አንበሳ፡ባባትና፡ እናቱ፡ሬሳ፡አጠገብ፡ወድቆ፡ ከነሕይወቱ፡ስላገኘው፡ወደ፡ ማረፊያው፡ወስዶ፡አብልቶ፡ አጠጥቶ፡አሳደገው።

ልጁ፡ነፍስ፡ካወቀ፡በኋላ፡ወደ፡መንደር፡ሄዶ፡ከሰዎች፡መገና ኘት፡ጀመረ። ከዕለታት፡አንድ፡ቀንም፡መንደረተኞቹ፡ካንበሳው፡ ጋራ፡እንደ፡ምን፡ተስማምተው፡እንደ፡ኖሩ፡ስለ፡ጠየቁት፡ደግነቱን፡ በመልክም፡እኳኋን፡እንዳሳደገውና፡የሚያፈቅረው፡መሆኑንም፡ ጭምር፡ገልጾ፡አስረዳቸው። ከቶ፡ምንም፡ነውር፡አላገኘህበትምን፡ ብለው፡እንደ፡ገና፡ቢመረምሩት፡ልጁ፡አንድ፡ነውር፡ብቻ፡አግኝቼበ ታለሁ፡ይኸውም፡አቅፎኝ፡ሲተኛ፡የሚሸተኝ፡የብብቱ፡ክርፋት፡ነው፡ ብሎ፡ነገራቸው። በዚህም፡ጊዜ፡ሰዎቱ፡ምሽት፡ስለ፡ነበር፡እንበሳው፡ በቤቱ፡ጓሮ፡ሆኖ፡አዳምጠ፡ሰምቷቸው፡ኖሮ፡በልጁ፡ንግግር፡ቅርታ፡ ገባው፡እንዲያውም፡ቂም፡ያዘበት፡ልጁ፡ግን፡ካሳደገኝ፡አባቴ፡ዘንድ፡

ልመለስ፡ብሎ፡ያነጋገራትን፡ሰዎች፡ተሰናብቶ፡በቶሎ፡ሄደ።ከ እቤቱ፡እንደ፡ደረሰም፡አንበሳው፡ልጁ፡ከወዴት፡መጣህ፡ምነው፡ መሸብህሳ፡ብሎ፡ጠየቀው፡አባቴ፡አደን፡ሰማሪን፡ጥቂት፡ርቄ፡ሄጄ፡ ስለ፡ነበር፡ነው። ከዚያም፡ጥቂት፡እንደ፡ቈዩ፡አንበሳው፡ጦር፡ አንሥቶ፡እንካ፡ውጋኝ፡አለው።



ግድ፡ነልወጋኸኝ፡ብሎ፡ ቢያስፈራኑትው፡ጦር፡አን ሥቶ፡ወጋው።

ልጁ፡ከወደቅሁበት፡አንሥተህ፡አብልተህ፡አጠጥተህ፡ሰዚህ፡ እስክበቃ፡ድረስ፡አሳድገኸኝ፡እንዴት፡እንተን፡አባቴን፡አወጋለሁ፡ አለው። ግድ፡ካልወጋኸኝ፡ብሎ፡ቢያስፈራኑትውና፡ዚያስገድደው፡ ጦሩን፡አንሥቶ፡ወጋው።

እንግዲህ፡እኔ፡እንተን፡በዱር፡እየተዘዋወርኩ፡እያደንኩ፡እነ ዳሳደግሁ፡ይኸ፡ቀስሌ፡እስቲድን፡ድረስ፡እያደንክ፡አስታመኝ፡ አለው። ልጁም፡በትጋት፡እያደነ፡አስታሞ፡አዳነው። አንበሳውም፡ ቀስሉ፡መዳኑን፡ካየ፡በኋላ፡ሰማህ፡ልጄ፡በጦር፡የወጋኸኝ፡ቀስ ል፡ዳነ፡ነገር፡ግን፡ከዘመድህ፡ከሰው፡ጋራ፡በተገናኘህ፡ጊዜ፡የተ ናገርከው፡የስድብህ፡ቀስል፡ክልቤ፡እልጠፋም። ስለዚህ፡ከእንግዲ ዘ፡ወዲያ፡አብረን፡ልንኖር፡አይቻልምና፡እኔም፡በጫከዬ፡አንተ ም፡ወደ፡ዘመዶችህ፡ሂድ፡ቤብሎ፡አሰናበተው፡ይባላል።

※ በጦር፡ከተወጋ፡በነገር፡የተወጋ፡ይብሰል።

የዶሮ ፡ ዘመቻ ።

አቶ ፡ ዶሮ ፡ ሥንቁን ፡ አሠንቆ ፡ ወደ ፡ ዘመቻ ፡ ሲሄድ ፡ አይጥ ፡ አገኘችውና ፡ ወንድሜ ፡ ወዴት ፡ ትጓዛለህ ፡ ብላ ፡ ጠየቀችው ። ዘመቻ፡ አላት ። በምን ፡ አቅምህ ፡ ልትዋጋ ፡ ብትለው ፡ አዳር ፡ በመላ ፡ ሲል ፡ መለሰላት ። እኔም ፡ ሥንቅ ፡ የለኝም ፡ እንጂ ፡ አብረን ፡ እንሂድ ፡ ነበር ፡ አለች ። አቶ ፡ ዶሮ ፡ ላንድ ፡ ያሉት ፡ ለሁለት ፡ ይበቃልና ፡ ከፈቀድሽ ፡ እንሂድ ፡ አላት ።

ተስማምተው ፡ ሁለቱ ፡ መንገደኞች ፡ ተያይዘው ፡ ሲገሠግሡ ፡ እባብ ፡ አገኟቸውና ፡ አቶ ፡ ዶሮ ፡ ወዴት ፡ ትሄዳላችሁ ፡ ሲል ፡ ጠየቃቸው ። ዘመቻ ፡ ቢሉት ፡ በየትኛው ፡ ወቅማችሁ ፡ አላቸው ። ዶሮ ፡ አዳር ፡ በመላ ፡ ሲል ፡ መልስ ፡ ሰጠው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ወይ ፡ ነዶ ፡ እኔም ፡ ሥንቅ ፡ የለኝም ፡ እንጂ ፡ አብሬያችሁ ፡ እሄድ ፡ ነበር ፡ ሲል ፡ ተናገረ ። ለሁለት ፡ ያሉት ፡ ለሦስት ፡ ይበቃል ፡ እንሂድ ፡ ብለው ፡ ሦስቱም ፡ አብረው ፡ ሲጓዙ ፡ አቶ ፡ እርኩም ፡ ከመንገድ ፡ አገኟቸው ። እሱም ፡ ወዴት ፡ ትሄዳላችሁ ፡ አቶ ፡ ዶሮ ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቅ ፡ ዘመቻ ፡ አለው ። ወይ ፡ ጥጋብ ፡ ወይ ፡ ድፍረት ፡ ከናንተው ፡ ወቅም ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ጦርነት ፡ ትሄዳላችሁ ፡ ቢለው ፡ አዳር ፡ በመላ ፡ ሲል ፡ መለሰለት ። እንግዲያውስ ፡ ሥንቅ ፡ የለኝም ፡ እንጂ ፡ እኔም ፡ ከናንተ ፡ ጋራ ፡ ብሄድ ፡ እወድ ፡ ነበር ፡ አላቸው ። አቶ ፡ እርኩም ፡ ሆይ ፡ ሰሦስት ፡ ያሉት ፡ ላራት ፡ ይበቃል ፡ እንሂድ ፡ አሉት ። አራቱ ፡ ደግሞ ፡ አብረው ፡ ሲሄዱ ፡ አንበሳ ፡ ከመንገድ ፡ አገኟቸውና ፡ አቶ ፡ ዶሮ ፡ ወዴት ፡ ትሄዳላችሁ ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ። ዶሮም ፡ ዘመቻ ፡ አለው ። በምን ፡ ወቅማችሁ ፡ ቢላቸው ፡ አቶ ፡ ዶሮ ፡ አንበሳ ፡ ሆይ ፡ አዳር ፡ በመላ ፡ በማለት ፡ መለሰለት ። አንበሳም ፡ ሥንቅ ፡ የለኝም ፡ እንጂ ፡ አብሬያችሁ ፡ እሄድ ፡ ነበረ ፡ አላቸው ። እነሱም ፡ ላራት ፡ ያሉት ፡ ላምስት ፡ ይበቃልና ፡ አቶ ፡ አንበሳ ፡ እንሂድ ፡ ብለውት ፡ አብረው ፡ ተጓዙ ።

ሲሄዱ ፡ ውለው ፡ የማታ ፡ ማታ ፡ ከላሞች ፡ በረት ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ርቦናልና ፡ ለራታችን ፡ እንዲሆነን ፡ ከዚህ ፡ ገብተን ፡ እንስረቅ ፡ እንስረቅ ፡ ተባብለው ፡ መከሩ ። አራቱ ፡ እንዴት ፡ ይመቸናል ፡ ቢሉ ፡ አቶ ፡ ዶሮ ፡ አይጥ ፡ ሄደሽ ፡ የከብቶቹን ፡ ማሰሪያቸውን ፡ በጥርስሽ ፡ በጥሽው ፤ እባብ ፡ ሄደህ ፡ ሰምቹን ፡ በመርዝህ ፡ ንደፋቸው ፤ አንበሳና ፡ እርኩም ፡ ደግሞ ፡ በውጪ ፡ ሁናችሁ ፡ አግሡ ፡ አላቸው ። ሁሉም ፡ በታ

ዘዙበት ፡ ሥራቸውን ፡ ጊሞሩ ፡ ከብቶቹም ፡ ማሰሪያቸው ፡ ስለ ፡ ተበጠሰ ፡ ደንብረው ፡ ጠደ ፡ ውጪ ፡ ሄዱ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ይኸ ፡ የኔ ፡ ነው ፡ ይኸ ፡ የኔ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ እምስቱም ፡ ጥል ፡ አበቀሉ ።



ላራት ፡ ያሉት ፡ ላምስት ፡ ይበቃልና ፡ አቶ ፡ አንበሳ ፡ እንሂድ ፡ ብለው ፡ አብረው ፡ ተጓዙ ።

አቶ ፡ ዶሮ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ጠቡ ፡ የሚቆምበትን ፡ መገላገያ ፡ መንገድ ፡ አሰበና ፡ ጓዴ ፡ እባብ ፡ እንበሳን ፡ በመርዝህ ፡ ግደለው ፡ አለው ። እንበሳው ፡ ሲሞት ፡ ደግሞ ፡ እርኩምን ፡ እባብን ፡ ዋጠው ፡ አለው ። እባ



እርኩምን ፡ እንትልፍ ፡ ሲይዘው ፡ ክንፍ ፡ ክንፉን ፡ በጥሽው ፡ አላት ።

ብም ፡ ሲሞጥ ፡ አይጥን ፡ እንግዲህ ፡ እንትልፍ ፡ ሲይዘው ፡ አይተሽ ፡ የእርኩምን ፡ ክንፍ ፡ ክንፉን ፡ በጥሽው ፡ አላት ። በዚህ ፡ ዘዴ ፡ ሁሉንም ፡ ከስፈጀ ፡ በኋላ ፡ አይጥን ፡ አንድ ፡ ከብት ፡ ጥለን ፡ ሥጋ ፡ እንብላ ፡ አላት ፡ ይሁን ፡ ተባብለው ፡ ተስማምተው ፡ አርደው ፡ ከፊሬሱ ፡

በኋላ ፣ አቶ ፣ ዶሮ ፣ ቄሽትና ፣ ኮላሊት ፣ አቀረበና ፣ ምረጭ ፣ አላት ።
እሷም ፣ ኮላሊት ፣ ይሻለኛል ፣ አለችው ። ደግ ፣ መልካም ፣ አለና ፣ እሱኑ ፣
ሰጥቷት ፣ ብትውጠው ፣ ጉረሮዋን ፣ አንቋት ፣ ሞተች ፣ ይባላል ።

። የዶሮን ፣ ብልጎት ፣ መመልከት ፣ ትልቅ ፣ ቁም ፣ ነገር ፣ ይሰጣል ።
በስተዋይነቱ ፣ አንበሳን ፣ የሚያክል ፣ ባላጋራና ፣ ሌሎቹንም ፣ አጥፍቶ ፣
ከብቱን ፣ ሁሉ ፣ ለራሱ ፣ አስቀረ ። ስለዚህ፡ አጠረ ፣ ቀጠነ ፣ ብሎ ፣ ትን
ሽን ፣ መናቅ ፣ አይገባም ።

ያውሬ ፣ ሁሉ ፣ ገበያ ።

የምድር ፣ አውሬ ፣ ሁሉ ፣ መሰብሰቢያና ፣ መነጋገጃ ፣ አንድ ፣ ገበያ ፣
ነበር ፣ ይባላል ። ከዕለታት ፣ አንድ ፣ ቀን ፣ አውሬ ፣ ሁሉ ፣ እገበያ ፣ ሲውል ፣
አያ ፣ ጅቦ ፣ ግን ፣ ሳይሄድ ፣ ቀረ ። የማታ ፣ ማታ ፣ ገበያተኛ ፣ ሲመለስ ፣ ከጕ
ሬው ፣ ወጣና ፣ ከመንገድ ፣ ዳር ፣ ተቀመጠ ። ገበያ ፣ ምላሽ ፣ ሲሆን ፣ ኰተቷን ፣
በገርበባዋ ፣ አዝላ ፣ እንኰዬ ፣ ዝንጀሮ ፣ መጣች ። አያ ፣ ጅቦም ፣ እንኰዬ ፣ ዝን
ጀሮ ፣ እንደምን ፣ ዋልሽ ፣ ገበያውስ ፣ እንዴት ፣ ዋለ ፣ ምን ፣ ረክሏል ፣ ምንስ ፣
ተወዷል ፣ ብሎ ፣ ጠየቃት ። ወንድሜ ፣ እኔ ፣ መሽቶብኛል ፣ እቤት ፣ ገብቼ ፣
ገና ፣ ራቴን ፣ እጋግራለሁ ፣ እንኰዬ ፣ ጦጢት ፣ እኳላ ፣ አለችልህ ፣ እሷን ፣
ጠይቃት ፣ ብላው ፣ ሄደች ።

እንኰዬ ፣ ጦጢትም ፣ ወዲያው ፣ ስለ ፣ መጣች ፣ ገበያው ፣ እንደ ፣ ምን ፣
ዋለ ፣ አላት ። እባክህ ፣ አያ ፣ ጅቦ ፣ እኔ ፣ መሽቶብኛል ፣ ገና ፣ እቤቴ ፣ ገብቼ ፣
ወደ ፣ ውሃ ፣ እወርዳለሁ ፣ እንኰዬ ፣ ሚዳቋ ፣ ከኳላ ፣ አለችልህ ፣ እሷን ፣
ጠይቃት ፣ ብላው ፣ አለፈች ።

ሦስተኛ ፣ ሚዳቋ ፣ ቅራቅንቦዋን ፣ አዝላ ፣ በዚሁ ፣ አያ ፣ ጅቦ ፣ በለበት፡
መንገድ ፣ መጣች ። አያ ፣ ጅቦም ፣ ሚዳቋ ፣ እባክሽ ፣ ገበያው ፣ እንደ ፣ ምን ፣

ዋለ ፣ አላት ። እንኰዬ ፣ አህዮት ፣ እኳላ ፣ አለችልህ ፣ እሷን ፣ ጠይቅ ፣
እኔ ፣ እነእንኰዬ ፣ ዝንጀሮ ፣ ስላመለጡኝ ፣ እቸኰላለሁ ፣ ብላው ፣ ሄደች ።

ከዚህ ፣ በኋላ ፣ አህዮት ፣ ከኋላ ፣ ስትንቀረደድ ፣ መጣች ። አህዮት ፣
ዛሬ ፣ ገበያ ፣ እንዴት ፣ ዋለ ፣ ምንስ ፣ ርካሽ ፣ ነው ፣ ምንስ ፣ ውድ ፣ ሆነ ፣
አላት ። እባክህ ፣ አያ ፣ ጅቦ ፣ ደክሞኛል ፣ እስቲ ፣ አረፍ ፣ ብዬ ፣ ላውራልህ ።
ይህ ፣ በዚህ ፣ ያክል ፣ ይህ ፣ በዚህ ፣ ያክል ፣ ሲገዛ ፣ ዋለ ፣ እያለች ፣
ስታወራለት ፣ አህዮት ፣ አረ ፣ ከሆነስ ፣ ሆነና ፣ እኔ ፣ የምዘለውን ፣ ለመዝ
ለል ፣ ትችያለሽን ፣ አላት ። እረ ፣ ንሺ ፣ ሰዎች ! አሳምሬ ! አለችው ።
እሱም ፣ የሞት ፣ ሞቱን ፣ እንጣጥ ፣ ብሎ ፣ ተሸግሮ ፣ እሷን ፣ ደግሞ ፣ በዪ ፣
እስቲ ፣ ዝለዪ ፣ አላት ። እንጣጥ ፣ ስትል ፣ ወረዶችና ፣ እፈፋ ፣ ውስጥ ፣
ውትፍ ፣ ብላ ፣ ቀረች ። በዚህ ፣ ጊዜ ፣ አያ ፣ ጅቦ ፣ ሆዬ ፣ ወርዶ ፣ ሆዷን ፣
ዘርግፎ ፣ ሲበላ ፣ እንኰዬ ፣ ውሺት ፣ እኳላ ፣ ነበረችና ፣ ደም ፣ ደም ፣ ሲሸ
ታት ፣ ጊዜ ፣ አፋፍ ፣ ብቅ ፣ ብላ ፣ ብትመለከት ፣ አህዮትን ፣ ጥሎ ፣ ሲበላ ፣
አየችው ። አበላሉም ፣ ስለ ፣ አስጮመጥት ፣ ለሐፍ ፣ ወርዶ ፣ ከራሱ ፣
ላይ ፣ ጠብ ፣ አለበት ። ቀና ፣ ብሎ ፣ ቢያይ ፣ ውሺት ፣ ከበላዩ ፣ ቆማለች ።
በዪ ፣ እኮ ፣ ነዪ ፣ ውረጂና ፣ እየመተርሽ ፣ አብለኝ ! አላት ፣ እሷም ፣ እሺ ፣
ጌታዬ ፣ ብላ ፣ ወረዶችና ፣ እየመተረች ፣ ስታበላ ፣ ቄይታ ፣ በመኻሉ ፣
ወደ ፣ ኋላው ፣ ዘወር ፣ በለላት ፣ ሰዓት ፣ የአህዮትን ፣ ልብ ፣ ስልቅጥ ፣ አደ
ረገችው ። መለስ ፣ አለና ፣ ቢያይ ፣ ልቧን ፣ አጣው ፣ ውሺት ፣ ልቧ ፣ ወዴት ፣



በዪ ፣ እኮ ፣ ነዪ ፣ ውረጂና ፣
እየመተርሽ ፣ አብሊኝ!

ሄደ ፡ ብሎ ፡ ጠየቃት ። ልብ ፡ ባይኖራት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ልብማ ፡ ካላት ፡ አንተ ፡ ዘንድ ፡ መጥታ ፡ መቼ ፡ ትቀመጥ ፡ ነበር ፡ አለችው ። እሱም ፡ በፊት ፡ አይቶታልና ፡ ታመጪ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አምጪ ፡ አለዚያ ፡ አንቺን ም ፡ እበላሻለሁ ፡ አላት ። ምነው ፡ አያ ፡ ዥቦ ፡ እኔን ፡ በቅቤና ፡ በድልኽ ፡ አጣፍጠህ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ አህዮት ፡ ደረቁን ፡ ትበላኛለህን ፡ አለ ችው ። ሆዳሚ ፡ እውነት ፡ መሰለውና ፡ ቅቤውና ፡ ድልኹ ፡ ከየት ፡ ይመ ጣል ፡ አላት ። ከመቤቴና ፡ ከጌታዬ ፡ ቤት ፡ እኔ ፡ ሄጄ ፡ አመጣዋለኋ ፡ ስትል ፡ መለሰችለት ።

—ሄደሽ ፡ የጠፋሽ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማ ፡ ብዬ ፡ እጠራሻለሁ ፤

—እንኩዬ ፡ ልብ ፡ አጥቼ ፡

—በዪ ፡ እንግዲያውስ ፡ ሄደሽ ፡ አምጪ ፡ አላትና ፡ እሺ ፡ ብላ ፡ ሄዳ ፡ ቅርት ፡ ብትል ፡ እረ ፡ እንኩዬ ፡ ልብ ፡ አጥቼ ፡ እያለ ፡ ተጣራ ። ከመቤቴና ። ከጌታዬ ፡ ቤት ፡ ስምን ፡ ወጥቼ ፡ በግለት ፡ የስድብ ፡ ጮርፍ ፡ ታወርድበት ። ዥመር ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ተናደደና ፡ እንቺም ፡ እጮድፍ ፡ እኔም ፡ እጮ ድፍ ፡ እንገናኝ ፡ የለምን ፡ ብሎ ፡ ዝቶ ፡ ተመለሰ ።

ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ከለፈ ፡ በኋላ ፡ የውሻ ፡ ነገር ፡ መለቃቀም ፡ ትወዳ ለችና ፡ ስትልከሰከስ ፡ ሳይገባ ፡ የቀረ ፡ ከብት ፡ ወይም ፡ ምናምን ፡ ነገር ፡ ቢያጋጥመኝ ፡ ብሎ ፡ ሲሄድ ፡ አያ ፡ ዥቦ ፡ እጮድፍ ፡ አገኛት ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ደነገጠችና ፡ ወደኋ ፡ ፈጠጠ ። እሱም ፡ ውሺት ፡ እረ ፡ ወይንሽ ፡ በምን ፡ እንደ



እሰቲ ፡ እባክሽ ፡ እንደዚህ ፡ ካማረ ፡ እኔንም ፡ ንቀሺኝ ፡ አላት ።

ዚህ ፡ አማረልሽ ፡ አላት ። ጌታዬ ፡ በአሥር ፡ የአጋም ፡ እሾክ ፡ ተነቅሻ ፡ ነዋ ፡ አለችው ። እስቲ ፡ እባክሽን ፡ እንደዚህ ፡ ካማረ ፡ እኔንም ፡ ንቀሽኝ ፡ ብሎ ፡ ጠየቃት ። እሺም ፡ ሄደችና ፡ ከጌታዋ ፡ አጥር ፡ ላይ ፡ ሀሥሩን ፡ የአጋም ፡ እሾክ ፡ ሰብራ ፡ እንድ ፡ ላይ ፡ አሥራ ፡ አመጣችና ፡ ሁለቱ ንም ፡ ዐይኑን ፡ ትቸክችከው ፡ ገመር ። እንኩዬ ፡ ውሺት ፡ እረ ፡ እባክሽ ፡ አመመኝ ፡ አላት ። ተው ፡ ዝም ፡ በል ፡ ሲያጌጡ ፡ ይመላለጡ ፡ ነው ፡ ማማር ፡ እንዲያው ፡ ይገኝ ፡ ይመስልሃል ፡ ብላ ፡ ሁለቱንም ፡ ሀይኖቹን ፡ አጠፋቸው ። በመጨረሻውም ፡ እንግዲህ ፡ ዝም ፡ ብለህ ፡ ከዚህ ፡ ቄየኝ ፡ አለችው ። እሱም ፡ እሺ ፡ ብሎ ፡ ካላየችው ፡ ቦታ ፡ ተቀምጦ ፡ ሳለ ፡ ጤፍ ፡ ወቂዎች ፡ ሆ ፡ ሆ ፡ ሲሉ ፡ ሰማ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እንኩዬ ፡ ውሺትን ፡ እረ ፡ ይኸ ፡ የምሰማው ፡ ሆታ ፡ ምንድነው ፡ እባክሽ ፡ አለና ፡ ጠየቃት ። ወንድሜ ፡ ዘመዶችህ ፡ ሠንጋ ፡ ጥለው ፡ በጮድን ፡ ከዳቢት ፡ ይማታሳ ! አለችው ። እንግዲያው ፡ እባክሽ ፡ እኔንም ፡ አድርሺኝ ፡ አላትና ፡ እየመ ራች ፡ ወስዳ ፡ ከጤፍ ፡ ወቂዎች ፡ መካከል ፡ አገባችው ። ወዲያው ፡ ጤፍ ፡



ይህ ፡ ዥጉ ፡ ከወዲት ፡ መጣ ፡ እያሉ ፡ . . . ለመግደል ፡ ሲሯሯጡ ፡ እሷ ፡ የገበሬዎቹን ፡ ዳቦ ፡ ይዛ ፡ ወደ ፡ ቤታ ፡ ሄደች ።

ወቂዎቹ ፡ ሁሉ ፡ ይኸ ፡ ዥጉ ፡ ከወዴት ፡ መጣ ፡ እያሉ ፡ መውቂያ ፡ መፈ ጭውን ፡ እየመዘዙ ፡ ዥጉን ፡ ለመግደል ፡ ሲሯሯጡ ፡ እሷ ፡ የገበሬዎቹን ፡ ዳቦ ፡ ይዛ ፡ ወደ ፡ ቤታ ፡ ተመለሰች ፡ ይባላል ።

፨ አህያና ፡ ዥጉ ፡ በተላላኑታቸው ፡ ከጉዳት ላይ ፡ ወደቁ ፡ ውሻ ፡ ግን ፡ በብልኀኑቱና ፡ በትዕግሥቱ ፡ ከፈተና ፡ አልፎ ፡ ለመጠቀም ፡ በቃ ። ስለ ዚህ ፡ ትዕግሥት ፡ ትልቅ ፡ ገንዘብ ፡ መሆኑን ፡ መረዳት ፡ ነው ።

የሽፖብና ፡ የነብር ፡ ንስሓ ፡ አባት ፡ መያዝ ።

ነብርና ፡ ሽፖ ፡ ጕሬዛን ፡ የንስሓ ፡ አባት ፡ ያዙ ፡ ይባላል ። ነብርና ፡ ሽፖ ፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ በንድነት ፡ ንስሓቸውን ፡ ሊና ዘዙ ፡ ከጕሬዛ ፡ ዘንድ ፡ ሄዱና ፡ አንድ ፡ በአንድ ፡ ዘርዝረው ፡ የሠሩ ትን ፡ በደል ፡ ሁሉ ፡ ተናገሩ ። ጕሬዛም ፡ እኔ ፡ ለራሴ ፡ ደካማ ፡ የእግዚ አብሔር ፡ ሰው ፡ እንደናንተ ፡ ያለ ፡ ዉንበዴ ፡ ሽፍታ ፡ አልችልም ፤ ሌላ ፡ የንስሐ ፡ አባት ፡ ያዙ ፡ አስናብቻችኋለሁ ፡ አላቸው ። አያ ፡ ሽፖም ፡ አቶ ፡ ነብሮም ፡ ምነው ፡ ምነው ፡ እኛ ፡ አክብረን ፡ ሽማግሌ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ የንስሓ ፡ አባት ፡ ብናደርገው ፡ ወንበዴዎች ፡ ሽፍቶች ፡ ይበለን ! የት ፡ አባቱ ፡ በል ፡ አትጥለውም ፡ ተባባሉና ፡ ነብሮ ፡ ጕሮሮውን ፡ እንቅ ፡ ሲያደርግ ፡ አያ ፡ ሽፖ ፡ ደግሞ ፡ እብሽሽቱ ፡ ገብቶ ፡ ግንጥልጥል ፡ አደረገው ። በዚህ ፡ አካኋን ፡ ጕሬዛን ፡ ከገዳሉ ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ተመካከሩና ፡ የዝንጀሮ ፡ ንስሓ ፡ አባት ፡ ለመያዝ ፡ ተነሥተው ፡ ሄዱ ።

እንደ ፡ ተገናኙም ፡ በሉ ፡ ንስሐችሁን ፡ ንገሩኝ ፡ አለና ፡ ጠየቃ ቸው ። አያ ፡ ሽፖም ፡ ማታ ፡ ማታ ፡ ከጕሬዴ ፡ ወጥቼ ፡ ስሰማራ ፡ ድን ገት ፡ የሰው ፡ አህያ ፡ እያጋጠመኝ ፡ በልቻለሁ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ግፍ ፡ አል ሠራሁም ፡ አለው ። አቶ ፡ ነብሮም ፡ እንደዚሁ ፡ እኔም ፡ ጫካ ፡ ለጫካ ፡ ስዞር ፡ ድንገት ፡ የሰው ፡ ፍዬል ፡ እያገኘሁ ፡ በልቻለሁ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ በደል ፡ የለኝም ፡ ብሎ ፡ ነገረው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዝንጀሮ ፡ ሥራችሁ ፡ ይኸ ፡ ከሆነማ ፡ እናንተ ፡ መቼ ፡ ትቻላላችሁ ፤ እኔ ፡ የብዙ ፡ ልጆች ፡ አባት ፡ ነኝ ፡ ኃጢአታችሁ ፡ ከብዶ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የናንተን ፡ ንስሓ ፡ ማስተስረያ ፡ ጊዜ ፡ አላገኝምና ፡ ሌላ ፡ አባት ፡ ፈልጉ ፡ አላቸው ። አሁንም ፡ አያ ፡ ሽፖና ፡ አቶ ፡ ነብሮ ፡ ምክር ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፡ ዝንጀሮን ፡ ይህ ፡ አታላይ ፡ ሲያላግጥብን ፡ ዝም ፡ ትለዋለህ ፡ በመባባል ፡ ለቀም ፡ አድር ገው ፡ ያዙት ። ምነው ፡ ጌቶቼ ፡ ምን ፡ አጠፋሁ ፡ እያለ ፡ ቢለፈልፍም ፡ ጥርቅም ፡ አድርገው ፡ በጥብቅ ፡ አሠሩት ። እሱም ፡ እንዳለቀቁት ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፡ ግደሉኝ ፡ እንጂ ፡ መደብደብና ፡ መታሰር ፡ አልወድም ፡ አላቸው ። አንተን ፡ ማን ፡ ይገድላል ፡ ማሰር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሲሉ ፡ መለሱለት ፡ ዝንጀሮም ፡ መታሰርማ ፡ ደህና ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ገደል ፡ እንዳትሰ ዱኝ ፡ ብቻ ፡ አማጥኖችኋለሁ ፡ ብሎ ፡ ለመናቸው ። አያ ፡ ሽፖና ፡ አቶ ፡ ነብ ሮም ፡ ደግሞ ፡ አንተ ፡ እንዳልክ ፡ ሆነና ፡ እረ ፡ በል ፡ ያዘው ፡ ይህንን ፡ አሸፈ፡ የኛን ፡ ንስሓ ፡ ያበረከተበትን ፡ ምክንያት ፡ ይንገረን ፡ አሉና ፡ በትራቸው ፡ አስ

ኪሰባበር ፡ ይዠልጡት ፡ ዠመር ። እሱም ፡ ጌቶቼ ፡ እባካችሁ ፡ በከንቱ ፡ አትድከሙ ፡ ክንዳችሁንም ፡ አይመማችሁ ፡ እኔ ፡ እንደ ፡ ሆንኩ ፡ በትር ፡ ልማዴ ፡ ነው ፡ ይልቅስ ፡ ከገዳል ፡ ሳይሆን ፡ ከፉላላ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ወስዳችሁ ፡ ጣሉኝ ፡ አለና ፡ ለመናቸው ። ደግሞ ፡ አንተ ፡ እንደ ፡ ፈለግህና ፡ እንደ ፡ መረ ጥክ ፡ ሆነና ፡ ብለው ፡ አንጠልጥለው ፡ ወስደው ፡ ከገዳሉ ፡ አፋፍ ፡ ላይ ፡ አደረሱትና ፡ ገደል ፡ ልንጥልህ ፡ ነው ፡ እንግዲህ ፡ ንስሓችንን ፡ አስወርድል ን ፡ አሉት ። አዩ ፡ እኔማ ፡ ያልኳችሁን ፡ እንቢ ፡ ብላችሁ ፡ አስራችሁ ፡ አምጥ ታችሁኝ ፡ የለምን ፡ ስለዚህ ፡ አሁን ፡ ገደል ፡ መጣሉ ፡ ላይቀርልኝ ፡ ምንም ፡



አቶ ፡ ነብሮና ፡ አያ ፡ ሽፖም ፡ አንተ ፡ ስመዳን ፡ ባትፈልግ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ የታሰረበትን ፡ ፈተው ፡ ገደል ፡ ጣሉት ።

ቢሆን ፡ ሞቴ ፡ ናትና ፡ አልነግራችሁም ፡ ሲል ፡ መለሰላቸው ። ተው ፡ ለቀቅ ንህ ፡ ቢሉትም ፡ ላትምሩኝ ፡ ምን ፡ ያደርግልኛል ፡ እንቢ ፡ አለና ፡ እቅ ጩን ፡ አስረዳቸው ። አቶ ፡ ነብሮና ፡ አያ ፡ ሽፖም ፡ አንተ ፡ ለመዳን ፡ በትፈልግ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ የታሰረበትን ፡ ፈተው ፡ ገደል ፡ ጣሉት ። ዝን ጀሮም ፡ ከገዳሉ ፡ ተንከባሎ ፡ መርዶ ፡ እሥስተኛው ፡ ዕርከን ፡ ላይ ፡ ሲደርስ ፡ ከቋጥኝ ፡ ላይ ፡ ቊሜ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ እያየ ፡ ድዱን ፡ ገልብጦ ፡ ስቆባ ቸውና ፡ አልምጠባቸው ፡ ከዘመዶቹ ፡ ተቀላቀለ ።

ደግሞ ፡ ሦስተኛ ፡ አቶ ፡ ነብር ፡ አያ ፡ ሽፖን ፡ እንግዲህ ፡ ምን ፡ ይሻለ ናል ፡ ትላለህ ፡ ሲል ፡ ምክር ፡ ጠየቀው ። እሱም ፡ እኔ ፡ ምን ፡ ዐውቄ ፡ ከኔ ፡

በታ ፡ እንዳሉ ፡ ድንገት ፡ አንድ ፡ ወደል ፡ አህያ ፡ አገኛቸው ። አያ ፡ ዥቦና ፡ አቶ ፡ ነብሮም ፡ ከተቀመጡበት ፡ ብድግ ፡ ብለው ፡ እንዴት ፡ ዋልክ ፡ ሰሉ ፡ ሰላምታ ፡ አቀረቡለት ። እሱም ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ ከለ ፡ በኋላ ፡ እረ ፡ ለመሆኑ ፡ ከወዴት ፡ ትመጣላችሁ ፡ አላቸው ። ዝንጀሮ ፡ ገድለን ፡ አሉት ። ምክንያቱን ፡ ለማወቅ ፡ ፈልጎ ፡ እባካችሁ ፡ ምን ፡ ቢያደርጋችሁ ፡ ነው ፡ አስረዱኝ ፡ ሲል ፡ ጠየቃቸው ። የነፍስ ፡ አባት ፡ ይዘነው ፡ የሠራንውን ፡ በደል ፡ ብንናዘዝለት ፡ ንስሓችንን ፡ ስላበረከታብን ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ነገሩት ።

አህያም ፡ ለመሆኑ ፡ ምንድን ፡ ኖሯል ፡ ንስሓችሁ ፡ አለና ፡ ጠየቃቸው ። አያ ፡ ዥቦ ፡ ያንተኑ ፡ ጓደኛ ፡ በልቼ ፡ ነዋ ! ፡ ሌላማ ፡ የሠራሁት ፡ ምን ፡ ኖሮ ፡ ነው ፡ አለ ። እረ ፡ ለመሆኑ ፡ ስንት ፡ አህያ ፡ ነው ፡ የበላኸው ፡ ቢለው ፡ ዐሥር ፡ ሲል ፡ መለሰለት ። ታዲያ ፡ ዐሥራ ፡ አንድ ፡ ከልሞላህ ፡ ምን ፡ ንስሓ ፡ አለብህ ፡ አለው ። አያ ፡ ዥቦም ፡ እንግዲያው ፡ አንተኑ ፡ ደግሜ ፡ ንስሓ ፡ አገባለኋ ፡ አለው ። አህያውም ፡ ያለፈውን ፡ ንስሓህን ፡ ተወጥተህ ፡ እኔን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ አንድ ፡ አትልምን ፡ የማለት ፡ ምክር ፡ ቢያቀርብለት ፡ ሐሳቡ ፡ መልካም ፡ ነው ፡ ያለፈውን ፡ ጎጠአቱን ፡ ለማስተስረይ ፡ ከማን ፡ ዘንድ ፡ መሄድ ፡ ይሻለኛል ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ። ቁመታቸው ፡ አጠር ፡ መል ከቸው ፡ ጠየም ፡ አፍንጫቸው ፡ ጐመድ ፡ ከረሳቸው ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ጥም ጥማቸው ፡ ከበድ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ታገኛላችሁ ። እኔም ፡ አሁን ፡ ከዚያው ፡ መምጣቴ ፡ ነው ፤ በዚህ ፡ በኩል ፡ አድርጋችሁ ፡ ሂዱ ፤ መንገዱም ፡ ቢጠፋ ፡ በችሁ ፡ እኔ ፡ ከዚሁ ፡ ሆኜ ፡ አመለክታችኋለሁ ፡ አላቸው ።

እነሱም ፡ እንደ ፡ ተነገራቸው ፡ ተነሥተው ፡ ቢሄዱ ፡ ለምድር ፡ ለሰማይ ፡ የከበዱ ፡ አዛውንት ፡ ጥምጥማቸው ፡ ያማረ ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ጠጣ ፡ ከሸላ ፡ ላይ ፡ ተቀምጠው ፡ አገኙዋቸው ። አቶ ፡ ነብሮና ፡ አያ ፡ ዥቦም ፡ መሬት ፡ በመሰም ፡ እጅ ፡ ነሥተው ፡ አባታችን ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ዋሉ ፤ አሏቸው ።

ጠጣም ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ እንዴት ፡ ዋላችሁ ፡ ልጆቼ ፡ ከወዴት ፡ መጥታችኋል ፡ ብሎ ፡ ጠየቃቸው ። ከሩቅ ፡ አገር ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ መለሱለት ። ምነው ፡ በደኅናችሁ ፡ ነውን ፡ ቢላቸው ፡ የንስሓ ፡ ልጆች ፡ እንድንሆንም ፡ አርስዎም ፡ አባት ፡ እንዲሆኑን ፡ ብለን ፡ ነበር ። መልካም ፡ ምን ፡ ከፋኝ ፡ በሉ ፡ ትንሽ ፡ ዐረፍ ፡ በሉ ፡ አላቸው ። አቶ ፡ ነብሮና ፡ አያ ፡ ዥቦም ፡ ንስሓችንን ፡ ሰንናገር ፡ አንቀመጥም ፡ ብለው ፡ አስቸገሩት ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እንግዲያውስ ፡ ደግ ፡ ነው ፡ የሠራችሁትን ፡ ጎጠአት ፡ ዘርዝራችሁ ፡

ንገሩኝ ፡ አላቸው ። ሁለቱም ፡ ለየብቻቸው ፡ ንስሓቸውን ፡ ተናዘዙ ። እሱም ፡ ለዚህ ፡ ነው ፡ እንደዚህ ፡ የተጨነቃችሁት ፡ በሉ ፡ እንኳን ፡ መጣችሁልኝ ፡ አንድ ፡ ዕቃ ፡ እዋሽ ፡ ውስጥ ፡ አስቀምጨው ፡ የሚያወጣልኝ ፡ አጥቼ ፡ በጣም ፡ ተቸግሬ ፡ ነበረ ፡ ብሎ ፡ መጫኛውን ፡ ይዘ ፡ አቶ ፡ ነብሮንና ፡ አያ ፡ ዥቦን ፡ አስከትሎ ፡ ወደ ፡ ዋሻው ፡ ሄደ ። ከገደሉም ፡ አፋፍ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ አድርገን ፡ ነው ፡ የምንወርደው ፡ ብለው ፡ ጠጣን ፡ ጠየቁት ። እሱም ፡ አያ ፡ ዥቦን ፡ አንተ ፡ ጐበዝም ፡ ደፋርም ፡ ነህ ፡ ስለዚህ ፡ እኔና ፡ አቶ ፡ ነብሮ ፡ ወገብህን ፡ በመጫኛ ፡ አስረን ፡ እንሰድሃለን ፡ አንተም ፡ በእግርህ ፡ እየቄነጠጥህ ፡ ትረዳናለህና ፡ ቅር ፡ አይበልህ ። እኔ ፡ እንዳልወርድ ፡ ዐቅም ፡ የለኝ ፡ ደግሞም ፡ ሽማግሌ ፡ ነኝ ፡ አንተ ፡ ግን ፡ ጠንካራ ፡ ነህ ፡ ዕቃውም ፡ ከበድ ፡ ያለ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ትችለዋለህ ፡ ብሎ ፡ በስረዳው ፡ ጊዜ ፡ እሺ ፡ በማ ለት ፡ ትእዛዙን ፡ ተቀበለ ። ከዚህ ፡ ዘኋላ ፡ አያ ፡ ዥቦን ፡ ወገቡን ፡ ጥርቅም ፡ አድርገው ፡ በመጫኛ ፡ አስረው ፡ ለቀቂት ። እሱም ፡ ከተባለው ፡ በታ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ እረ ፡ ዕቃም ፡ የለ ፡ ሠልሳችሁ ፡ አውጡኝ ፡ አላቸው ። እነሱም ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ጠጋ ፡ ብለህ ፡ ባታይ ፡ ነው ፡ በቅጡ ፡ መርምር ፡ ብለው ፡ ተቈጡት ።

አንገቱን ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ገባ ፡ አድርጎ ፡ በሚመለከትበት ፡ ሰዓት ፡ ጠጣ ፡ እኛ ፡ ብቻችንን ፡ መጫኛውን ፡ ለመሰብና ፡ እሱን ፡ ማውጣት ፡ አንችልም ፡ ስለዚህ ፡ የንስሓ ፡ ልጆቼን ፡ ሰብስቤ ፡ እመጣና ፡ እናወጣዋለን ፤ አሁን ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ እንሂድ ፡ አለው ። አቶ ፡ ነብሮም ፡ እውነትም ፡ ነው ፡ አቡቱ ፡ ይኸንን ፡ ጥንበ ፡ በላ ፡ ማን ፡ ይችላል ፡ ብለው ፡ ነው ፡ አለውና ፡ መጫኛውን ፡ ለቀው ፡ ወደ ፡ ጠጣው ፡ ቤት ፡ ተነሥተው ፡ ሄዱ ።

ከቤትም ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ላቶ ፡ ነብሮ ፡ ግብግ ፡ አደረገና ፡ ለመግ ደል ፡ ስላሰበው ፡ አሎሎ ፡ አግሎ ፡ ሞራ ፡ አልብሶ ፡ እስቲ ፡ እንድትበረታ ፡ ይኸንን ፡ የተጠበሰ ፡ ሥጋ ፡ ትንሽ ፡ ብላ ፡ በኋላ ፡ ሄደን ፡ አያ ፡ ዥቦን ፡ እና ወጣዋለን ፡ አለው ። አቶ ፡ ነብሮም ፡ የሥጋው ፡ ወዝ ፡ በጣም ፡ የሚያስጐ መኝ ፡ ሆኖ ፡ ስላየው ፡ አነሣና ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ዋጥ ፡ አደረገው ። ወዲያው ፡ ከባሕር ፡ ሆዱ ፡ ገብቶ ፡ አንዣቡን ፡ አከሚትሮ ፡ እዚያው ፡ ድብን ፡ አድርጎ ፡ ገደለው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ጦጣ ፡ ያቶ ፡ ነብሮን ፡ ሬሳ ፡ ይላኝ ፡ ሸፈነና ፡ አያ ፡ ዥቦ ፡ ዘንድ ፡ ሄደ ።

ከአፋፉ ፡ ብቅ ፡ ብሎ ፡ እንደምን ፡ ዋልህ ፡ በማለት ፡ ቢጠይቀው ፡ የሠራችሁኝን ፡ ሥራ ፡ አልረሳውም ፡ ቂይ ፡ ግድ ፡ የለም ፡ ሲል ፡ ዛተበት ።



አባታችን ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ጥሎ ፡



እረ ፡ ዕታም ፡ የለ ፡ መልሳችሁ ፡ አውጡኝ ።

ጠጣም ፡ የኔን ፡ ጭንቅ ፡ አንተ ፡ አላየህልኝም ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ። ምነው ፡ ምን ፡ አገኘም ፡ ቢለው ፡ እረ ፡ ተወኝ ፡ ወንድሜ ፡ የገዛ ፡ ጓደኛህ ፡ ከዚህ ፡ እልፍ ፡ ባልን ፡ ጊዜ ፡ ሊገድለኝ ፡ አምላክ ፡ አላወጣኝም ፡ አለው ። ምክንያቱም ፡ በንተው ፡ ነገር ፡ ነው ፡ እኔ ፡ እናውጣው ፡ ስል ፡ እሱ ፡ ደግሞ ፡ አይ ሆንም ፡ ብሎ ፡ ብርቱ ፡ ክርክር ፡ እድርገን ፡ ከጥል ፡ በመድረሳችን ፡ ነው ።

አይ ፡ አይ ፡ እሱ ፡ ዱሮውንም ፡ ጨካኝ ፡ ነው ፡ እኔ ፡ መቼ ፡ ባሕሬውን ፡ አጣሁት ፤ ወውቀዋለሁ ። አሁን ፡ ለመሆኑ ፡ ምን ፡ ይሻለኛል ፡ ይላሉ ፡ አባቴ ፡ አለ ። ጠጣም ፡ ሆዴ ፡ አልጨክን ፡ ስላለኝ ፡ ተደብቄ ፡ ላወጣህ ፡ መጣሁ ፤ አሁን ፡ ዋናው ፡ ነገር ፡ እሱ ፡ ወደማያገኝህ ፡ ሀገር ፡ ትሄድ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ላውጣህና ፡ ጥፋ ፡ አለው ። አያ ፡ ኹቦም ፡ ከዚህ ፡ ብኮ ፡ ልውጣ ፡ እንጂ ፡ ተነሥቼ ፡ እልም ፡ ብዬ ፡ እጠፋለሁ ፡ ሲል ፡ መለሰለት ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ጠጣው ፡ ከገደሉ ፡ ውስጥ ፡ አወጣውና ፡ አያ ፡ ኹቦ ፡ እንግዲህ ፡ አደራህን ፡ አጥብቀህ ፡ ተሸሸግ ፡ ያየህ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እኔንም ፡ ጭምር ፡ ታስገድለኛለህ ፡ አለው ። እሱም ፡ እረ ፡ አባቴ ፡ እንኳን ፡ ከዚህ ፡ የወጣሁ ፡ እንጂ ፡ ሁለተኛ ፡ በዚህ ፡ ቀበሌ ፡ ይገኛል ፡ ብለው ፡ እያጠርጥሩኝ ፡ አለ ። ጠጣም ፡

መለስ ፡ እድርጎ ፡ አሁን ፡ ግን ፡ ለጊዜው ፡ ሩቅ ፡ ሰይሆን ፡ እይቀርምና ፡ ከቤት ፡ ሄደን ፡ ምሳህን ፡ በልተህ ፡ ትሄዳለህ ፡ አለው ። አያ ፡ ኹቦም ፡ የሆዱ ፡ ነገር ፡ ስለሚብስበት ፡ እሺ ፡ ብሎ ፡ ተከተለው ።

እቤትም ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ወጥንት ፡ ሰጠውና ፡ አንተ ፡ ይኸንን ፡ ብላ ፡ እኔ ፡ ኹራትህን ፡ ልቅመልህ ፡ ግን ፡ ገልመጥ ፡ እንዳትል ፡ አለው ። እሱም ፡ ያሉኝን ፡ እፈጽማለሁ ፡ ብሎ ፡ ወጥንቱን ፡ ይዞ ፡ ሲጋግጥ ፡ ጠጣ ፡ ኹማት ፡ አቅርቦ ፡ ያያ ፡ ኹቦን ፡ ኹራት ፡ ከነብሮ ፡ የፊት ፡ እግር ፡ ጋራ ፡ ግጥም ፡ አድርጎ ፡ ይሰፋ ፡ ዠመር ። ወዲያው ፡ እረ ፡ አመመኝ ፡ ብሎ ፡ ጮኸ ። እንግዲያው ፡ ወጥንቱን ፡ መልሳ ፡ አለው ። ሆዱ ፡ እያማ ፡ ው ፡ ሕመሙን ፡ ታግሦ ፡ ገዛ ፡ ሲል ፡ ጥርቅም ፡ አድርጎ ፡ ሰፍቶ ፡ ከ ጨረሰ ፡ በኋላ ፡ ነዎር ፡ ጌታዬ ፡ አቶ ፡ ነብሮ ፡ ከወዲት ፡ መጣህልኝ ፡ ብሎ ፡ አቶ ፡ ጠጣ ፡ ብድግ ፡ አለ ። ኋ ፡ ጊዜ ፡ ኹቦ ፡ መለስ ፡ ብሎ ፡ ቢያይ ፡ እውነትም ፡ አቶ ፡ ነብሮን ፡ አጠገቡ ፡ ሆኖ ፡ አገኘው ። ዘሎ ፡ የነከሰው ፡ መሰለውና ፡ ያያ ፡ ነብሮን ፡ ሬሳ ፡ ከማጀት ፡ እየጐተተ ፡ መንጥቆ ፡ አውጥቶ ፡ ነፍሱን ፡ አጥቶ ፡ ሲክነፈንፍ ፡ ገደል ፡ ገብቶ ፡ ሞተ ፡ ይበላል ።



ዘሎ ፡ የነከሰው ፡ መሰለውና ፡ ያንን ፡ ያያ ፡ ነብሮን ፡ ሬሳ ፡ ከማጀት ፡ እየጐተተ ፡ መንጥቆ ፡ አውጥቶ ፡ ነፍሱን ፡ አጥቶ ፡ ሲክነፈንፍ ፡ ገደል ፡ ገባ ።

※ እጸድቅ ፡ ያለ ፡ ሙንኩሶ ፡ እካስ ፡ ያለ ፡ ታግሦ ፡ እንደሚበለው ፡ ሁሉ ፡ የንስሓ ፡ አባትን ፡ ትእዛዝ ፡ በዛ ፡ ከበደ ፡ ሰይሉ ፡ ነጠአት ፡ እን ዲሰረይ ፡ መፈጸም ፡ ይገባል ። ከብዙ ፡ ጕልበት ፡ ትንሽ ፡ ብልጎት ፡ ይበ ልጣል ።

አንዲት ፡ ባሏን ፡ የናቀች ፡ ሴት ።

አንዲት ፡ ሴት ፡ አንድ ፡ ባለሟያ ፡ አራሽና ፡ በሰፈው ፡ አምራች ፡ ገበሬ ፡ አግብታ ፡ ሌማቷን ፡ በእንጀራ ፡ ሞልታ ፡ በመብላት ፡ ጠላውን ፡ ጮዞ ፡ በሚያኽል ፡ ጋን ፡ ጠምቃ ፡ ባበሬ ፡ እየደነበቀች ፡ በመጠጣት ፡ ተንቀባራ ፡ አብሬት ፡ ስላደረባት ፡ ያለመዉን ፡ ጠገበች ። የስንዴው ፡ አነባበሮ ፡ ልቧን ፡ ደፈነው ፤ የማይሆን ፡ የማይሆንም ፡ ነገር ፡ ያሳሰባት ፡ ዝመር ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከመጀነኗና ፡ ከኩራቷ ፡ የተነሣ ፡ በዘያ ፡ ገበሬ ፡ ባሏ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ወንደ ፡ ላጤ ፡ ማንዘራሽ ፡ መንደር ፡ አውሌ ፡ የሆነ ፡ ጐረምሳ ፡ ለመደችና ፡ ልቧ ፡ ፈቀርሰ ፡ ወደሱ ፡ ሆነ ። ባሏን ፡ ፈጽማ ፡ ናቀችው ፤ እንዲያውም ፡ ከእብሪቷ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ አላድርም ፡ እያለች ፡ የምትተኛው ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ለብቻዋ ፡ ሆነ ።

ባለቤቷም ፡ እየተናደደና ፡ እየፈራሰ ፡ ታግሦ ፡ ሲኖር ፡ ሳለ ፡ በመ ጨረሻው ፡ ባሏን ፡ ጥላ ፡ ለመሄድ ፡ ከወንደ ፡ ላጤው ፡ ጋራ ፡ ምክር ፡ አደረገች ።

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀንም ፡ ሌሊት ፡ በውድቅት ፡ ይህንኑ ፡ የጠላችውን ፡ ባሏን ፡ ከእንቅልፉ ፡ ቀስቅሳ ፡ አንተ ፡ እኔ ፡ ዛሬ ፡ ሕልም ፡ አየሁ ፡ አለችው ። ምን ፡ ሕልም ፡ አየሽ ፡ ምንስ ፡ አለሽ ፡ አለና ፡ ዚጠይቃት ፡ ፈረሰኛው ፡ ቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ተገልጦ ፡ በፈረሱ ፡ ተቀምጦ ፡ ጦርና ፡ ጦራዬውን ፡ ይዞ ፡ ከፊቱ ፡ ቆሞ ፡ አንቺ ፡ ልጅ ፡ በመልክ ፡ አንዲህ ፡ ስታምሪ ፡ ከዚህ ፡ ከንፋጣም ፡ እንዴት ፡ ትኖሪ ፡ አለና ፡ ነገረኝ ፡ ስትል ፡ የልቦናዋን ፡ እብሪት ፡ አስረዳችው ። እሱም ፡ እባክሽን ፡ እኅቴ ፡ ቅዠት ፡ ነው ፡ አርፈሽ ፡ ተኚ ፡ አላት ። እረ ፡ የለም ፡ ወንድሜ ፡ ቅዠትም ፡ አይደለ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ፈረሰኛው ፡ በግሃድ ፡ ተገልጦ ፡ ነው ፡ የነገረኝ ፡ ከለት ፡ በኋላ ፡ ሁለቱም ፡ ተመልሰው ፡ ተኙ ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ወንድዮው ፡ በጣም ፡ ተናዶ ፡ ነበርና ፡ እንቅልፍ ፡ አልወስድ ፡ ብሎት ፡ ሰውነቱ ፡ በንዴት ፡ መጨስ ፡ መቃጠል ፡ መብገን ፡ ማረር ፡ ዝመረ ። ጥቂት ፡ ቈይቶም ፡ እሷን ፡ እንቅልፍ ፡ ድብን ፡ አድርጎ ፡ ሲይዛት ፡ አየና ፡ እንቺ ፡ እንቺ ፡ ብሎ ፡ ቀሰቀሰና ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ ከተኛን ፡ ወዲህ ፡ ምን ፡ ሕልም ፡ አየሽ ፡ አላት ። ከቅድመ ፡ ወዲህ ፡ ምንም ፡

አላየሁ ፡ ያው ፡ ነው ፡ በማለት ፡ መለሰችለት ። እንግዲያውስ ፡ እኔ ፡ ግሩም ፡ የሆነ ፡ ሕልም ፡ አይቻለሁ ፡ ተነሥተሽ ፡ እሳት ፡ እንጂና ፡ ልንገርሽ ፡ ትፈች ልኛለሽ ፡ አላት ። እሺ ፡ አለችና ፡ ተነሥታ ፡ ያንን ፡ እሳት ፡ እንድዳ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ አድርጎ ፡ ነው ፡ ያሳየህ ፡ ስትል ፡ ጠየቀችው ። እሱም ፡ ብርሃን ፡ ለብሶ ፡ ብርሃን ፡ ተጐናጽፎ ፡ ፊቱ ፡ እንደ ፡ ፀሐይ ፡ የሚያበራ ፡ ጕልማሳ ፡ መጥቶ ፡ ከፊቴ ፡ ቆሞ ፡



ካንተ ፡ ተኝታ ፡ ሌላ ፡ ታማራት ፡ ተው ፡ ተነሣና ፡ በዱላ ፡ በላት ፡ አለና ፡ ነገረኝ ፡ አላት ። አይ ፡ እባክህ ፡ ቅዠት ፡ ነው ፡ ተኛ ፡ አለችው ። የኔስ ፡ ቅዠትም ፡ አይደለ ፡ ቅዠቱስ ፡ ያንቺ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የጠወለገ ፡ የወይራ ፡ አርፌሜ ፡ አንሥቶ ፡ በደረቅ ፡ ዱላ ፡ ሌሊት ፡ እንደ ፡ ራቅ ፡ እያገላበጠ ፡ ወቃት ። ገላጋይም ፡ እንዳይመጣ ፡ እኩለ ፡ ሌሊት ፡ ሆነ ፡ ደግሞም ፡ በሩን ፡ አጥብቆ ፡ በመ ወርወሪያ ፡ ቀርቅሮት ፡ ነበርና ፡ ብትፈነጥቅም ፡ የሚደርስላትና ፡ የሚያድናት ፡ ሰው ፡ አጥታ ፡ ተቸገረች ። ስለዚህ ፡ እንደማይሆንላት ፡ በተረዳችው ፡ ጊዜ ፡ እረ ፡ ተው ፡ እባክህ ፡ በተሰቀለው ፡ የዛሬን ፡ ብቻ ፡ አለችው ። እሱም ፡ ቀና ፡ አለና ፡ ወደ ፡ ጣሪያው ፡ ቢመለከት ፡ የበሬ ፡ ጅራፉን ፡ ከግድግዳው ፡ ላይ ፡ ተሰቅሎ ፡ አየ ። ያንን ፡ አውርዶ ፡ ተሰቀቀባት ፡ ልቧም ፡ ጥፍት ፡ አስክሏ ፡ ድረስ ፡ ዝርፎ ፡ ለቀቃት ፡ ይባላል ።

፨ በተረቱበት ፡ ይረቱበት ፡ እንደሚባለው ፡ ተረት ፡ እሷው ፡ ባመጣችው ፡ ቅዠት ፡ እሱ ፡ አንዠቱን ፡ አራሰበት ። ባልን ፡ ማክበርና ፡ መውደድ ፡ ይገባል ፤ ሴሰኝነትም ፡ በመጽሐፍ ፡ የተከለከለና ፡ ብርቱ ፡ ኀጢአት ፡ መሆኑን ፡ አለመርሳት ፡ ነው ።


የኔስ ፡ ቅዠት ፡ አይደለም ፡ ቅዠትስ ፡ ያንቺ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ራቅ ፡ እያገላበጠ ፡ ወቃት ።

አንበሳና፡አንዲት፡ሴት ።

አንዲት ፡ ጌኔሆይ ፡ ድንቅነሽ ፡ የምትባል ፡ ሴት ፡ በሷ ፡ የጎረ ፡ ቤት ፡ ሴት ፡ ወዳጅ ፡ አበጅቶ ፡ በመብልና ፡ በመጠጥ ፡ ጭምር ፡ እየተዳለለ ፡ ል ቡ ፡ ስለ ፡ ተማረከ ፡ ጨቅጫቃ ፡ ሆኖባት ፡ ተቸግራ ፡ ትኖር ፡ ነበር ። ከዕለ ታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ከመጨነቋ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ምክር ፡ ወዋቂ ፡ ሰው ፡ ዘንድ ፡ ሄዳ ፡ ብትጠይቅ ፡ የአንበሳ ፡ ቅንድብ ፡ ካመጣሽ ፡ እኔ ፡ መድኅ ኒት ፡ አደርግልሻለሁ ፡ አላት ። ጌኔሆይ ፡ ድንቅነሽም ፡ ይኸንንማ ፡ ከወ ዴት ፡ አባቴ ፡ አግኝቼ ፡ አለችው ። ዐዋቂዉም ፡ እንግዲያውማ ፡ ምን ፡ ላደርግ ፡ እችላለሁ ፡ ያለሱ ፡ አይሆንም ፡ አላት ። ጌኔሆይ ፡ ድንቅነሽ ፡ ይ ኸንን ፡ በመስማቷ ፡ እየተከዘች ፡ ወደ ፡ ቤቷ ፡ ስትመለስ ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ወዳጅዋ ፡ የሆነችውን ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ አገኘችና ፡ ከወዴት ፡ ትመ ጪለሽ ፡ አለቻት ። እሷም ፡ የባሌ ፡ ቤሕርይ ፡ ስለ ፡ ተለዋወጠብኝ ፡ ዐ ዋቂ ፡ ዘንድ ፡ ብሄድ ፡ ያንበሳ ፡ ቅንድብ ፡ ካላመጣሽ ፡ አይሆንም ፡ አለኝ ፡ ስለዚህ ፡ በጣም ፡ ተቸግሪያለሁና ፡ ከምን ፡ ቦታ ፡ እንደሚገኝ ፡ እባክሽ ፡ ምክር ፡ አካፍለኝ ፡ ስትል ፡ ጠየቀቻት ። ሴቲቱም ፡ በረ ፡ አርደሽ ፡ አን ድ ፡ አንዱን ፡ ብልት ፡ እየያዝሽ ፡ ከጫካ ፡ ከሄድሽ ፡ አታጪውም ፡ የፈለ ግሽውንም ፡ ታገኛለሽ ፡ አለቻት ።

በለጮዳይዋም ፡ ይህንን ፡ ምክር ፡ ተቀብላ ፡ ከግል ፡ ከብቷ ፡ ውስጥ ፡ ደኅናውን ፡ በሬ ፡ መርጣ ፡ አሰርዳ ፡ ታናሹን ፡ በመዳ ፡ በመዳ ፡ ከፋፍላ ፡ ተሸክማ ፡ አጫካ ፡ ሄዳ ፡ ስትዘር ፡ ስትዘር ፡ ውላ ፡ አንድ ፡ አንዘላ ፡ አገኘች። ገና ፡ በሩቅ ፡ ሳለ ፡ በተቄጣ ፡ አስተያየቱ ፡ ባይኑ ፡ መቅላት ፡ በግርማው ፡ ማስፈራት ፡ ደንግጣ ፡ በመንቀጥቀጥ ፡ ቁማ ፡ ቀረች ።

እሱም ፡ ጋማውን ፡ ነስንሶ ፡ ተቄጥቶ ፡ ወደሷ ፡ መንገድ ፡ ገሥመረ ። ድንቅነሽም ፡ አጠገቧ ፡ ሊደርስ ፡ ትንሽ ፡ ሲቀረው ፡ ሥጋውን ፡ ጣል ፡ እደረገችለትና ፡ ራቅ ፡ ብላ ፡ ትመለከተው ፡ ገሥመር ። የአራዊት ፡ ንጉሥም ፡



ድንቅነሽም ፡ አጠገቧ ፡ ሊደ ርስ ፡ ትንሽ ፡ ሲቀረው ፡ ሥጋ ውን ፡ ጣል ፡ እደረገችለትና ፡ ራቅ ፡ ብላ ፡ ትመለከተው ፡ ገሥመር ።

ዝም ፡ ብሎ ፡ ሥጋውን ፡ መብላት ፡ ያዘ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ጌኔሆይ ፡ ድንቅ ነሽ ፡ ቶሎ ፡ ብላ ፡ ሥጋውን ፡ በልቶ ፡ ሳይጨርስ ፡ ወደ ፡ ቤቷ ፡ ተመለሰች።

ብሥስትኛው ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ልማዷ ፡ ከዚያው ፡ ሥጋ ፡ ይዛለት ፡ ሄደች ። አንበሳውም ፡ ስትመጣ ፡ አያትና ፡ ጠጋ ፡ ጠጋ ፡ ሲላት ፡ የያዘች ውን ፡ ሥጋ ፡ ወረወረችለት ። እንደ ፡ ልማድ ፡ አድርጎ ፡ እሷን ፡ እሷን ፡ እያየ ፡ ሥጋውን ፡ መብላት ፡ ገሥመረ ። እስኪጨርስም ፡ ድረስ ፡ አጠገቡ ፡ ቆማ ፡ ነበርና ፡ በጠገበ ፡ ጊዜ ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ አያት ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ቤቷ ፡ ተመለሰች ።

ዳግም ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ልማዷ ፡ ከዚያው ፡ ሥጋ ፡ ይዛለት ፡ ሄደች ። አንበሳውም ፡ ልምድ ፡ አድርጎ ፡ ይጠባበቃት ፡ ነበርና ፡ የርሷን ፡ መምጣት ፡ በየ ፡ ጊዜ ፡ ወውቋት ፡ ጭራውን ፡ ነሰነሰ ። ጌኔሆይ ፡ ድንቅነሽም ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ሁኔታ ፡ እየተመላለሰች ፡ ሥጋው ፡ እስ ኪያልቅ ፡ ድረስ ፡ ከመገበችው ፡ በኋላ ፡ መፍራቷ ፡ ቀረና ፡ ምግቡን ፡ በእ ጅዋ ፡ ይዛ ፡ ልታበላውና ፡ ልታጐርሠው ፡ ደፊረች ። በልቶ ፡ ከጨረሰ ፡ በኋ ላም ፡ ታከክ ፡ ታከክ ፡ እያለ ፡ በጠጕሩ ፡ ስለሚያሻሻት ፡ ሁለቱም ፡ ተላመዱ ፡ ወዝም ፡ ተጣገቡ ። ስለዚህ ፡ አብረው ፡ ውላ ፡ ማታ ፡ አቤቷ ፡ ሄዳ ፡ አደ ረችና ፡ በረቱኛው ፡ ቀን ፡ እንደዚያው ፡ እንደ ፡ መሰንበቻዋ ፡ ያለውን ፡ ሥጋ ፡ ሁሉ ፡ ልቅም ፡ አድርጋ ፡ ይዛለት ፡ እጫካው ፡ ገባች ። ገና ፡ በሩቅ ፡ ስትመጣ ፡ ባያት ፡ ጊዜም ፡ ከደስታው ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ እየፈነደቀ ፡ እየቦ ረቀ ፡ ካጠገቧ ፡ ደረሰ ። ጌኔሆይ ፡ ድንቅነሽም ፡ በለመፍራት ፡ ዝም ፡ ብላ ፡ እያስተዋለች ፡ ሥጋውን ፡ ሳትሰጥ ፡ አቄየችው ። ቢሆንም ፡ በማዘግየት ፡ ሳይቄጣ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ይለማመጣት ፡ ገሥመረ ። እሷም ፡ እጅግ ፡ ደጅ ፡ ሳታስጠና ፡ ምግቡን ፡ አቀበለችው ። በልቶ ፡ እንደ ፡ ጠገበ ፡ ከላይዋ ፡ ላይ ፡



ጌኔሆይ ፡ ድንቅነሽም ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ መፍራት ፡ ቀረና ፡ ምግቡን ፡ በእጅዋ ፡ ይዛ ፡ ታበላውና ፡ ታጕርሠው ፡ ገሥመረች ።

ተደግሮ ፣ ሽልብ ፣ አደረገው ፣ እንቅልፍም ፣ ድብን ፣ አድርጎ ፣ ያዘው ፣ በዚህ ፣ ጊዜ ፣ ቅንድቡን ፣ ንጭት ፣ አደረገችው ። አሱም ፣ ደንግጦ ፣ ምን ፣ ነካኝ ፣ አለና ፣ ተነሥቶ ፣ ቢያይ ፣ ቀላቢው ፣ ሆነችበት ። ጥቂት ፣ ቈይታም ፣ የመ ጣችበትን ፣ ጉዳይ ፣ ስለ ፣ ጨረሰች ፣ አንበሳውን ፣ አሻሽታ ፣ አባብላ ፣ አገ ርማ ፣ ወደ ፣ ቤቷ ፣ ተመለሰች ።



በልቶ ፣ እንደ ፣ ጠገበ ፣ ከላ ይዋ ፣ላይ ፣ተደግሮ ፣ እንቅል ፍ ፣ድብን ፣ አድርጎ ፣ ያዘው ።

ሳታርፍ ፣ ወዲያው ፣ እዚያ ፣ ዐዋቂ ፣ ሰው ፣ ዘንድ ፣ ሄደችና ፣ ያል ኸኝን ፣ ያንበሳውን ፣ ቅንድብ ፣ አመጣሁ ፣ አለችው ። እሱም ፣ ተገርሞ ፣ እንደ ፣ ምን ፣ አድርገሽ ፣ አገኘሽው ፣ እባክሽ ፣ እስቲ ፣ ንገሪኝ ፣ አላት ። ከዚህ ፣ በኋላ ፣ ከሥር ፣ ገምራ ፣ ምንም ፣ ሳይቀራት ፣ ሁሉንም ፣ ዘርዝራ ፣ አስረዳችው ። ሰውየውም ፣ በጣም ፣ አድርጎ ፣ ተደነቀ ፣ ተገረመም ።

እሱ ፣ ግን ፣ አስቀድሞ ፣ ይህንን ፣ አምፌ ፣ ያላት ፣ አታገኝም ፣ በማ ለት ፣ ነበርና ፣ መሸነፉን ፣ ባወቀ ፣ ጊዜ ፣ አንቺ ፣ የአራዊትን ፣ ንጉሥ ፣ ያገረምሽ ፣ ለባልሽ ፣ ምን ፣ ያቅተኛል ፣ ብለሽ ፣ ነው ፣ እኔ ፣ ዘንድ ፣ የመ ጣሽው ፣ አሁንም ፣ አንበሳውን ፣ እንደ ፣ አለሰለሽው ፣ ባልሽንም ፣ አባብ ለሽ ፣ ተለማምጠሽ ፣ ማሸነፍ ፣ ትችያለሽ ፤ ምግብ ፣ እንኳን ፣ ሰው ፣ አውሬ ፣ ያለምዳል ፣ ወንድም ፣ ጉሉን ፣ ቢጠብቁለት ፣ ምግቡንም ፣ ባያንደላቡበት ፣ ይወዳል ፤ ከዚህም ፣ በቀር ፣ ሌላ ፣ መድኀኒት ፣ የለውም ፣ ብሎ ፣ መከራ ት ። ጌኔሆይ ፣ ድንቅነሽም ፣ ተመልሳ ፣ ቃሉን ፣ ተቀብላ ፣ መልካም ፣ ምግ ብና ፣ መጠጥ ፣ እያዘጋጀች ፣ በመስጠት ፣ እየተለማመጠች ፣ ሲቈጣትም ፣ እየታለች ፣ ተስማምታ ፣ ቤቷን ፣ ንብረቷን ፣ አደርጅታ ፣ በሰላምና ፣ በጤና ፣ ከባሏ ፣ ጋራ ፣ ኖረች ፣ ይባላል ።

※ ልጆቼ ፣ ሆይ ፣ ሞኝን ፣ እንዳይጠላህ ፣ አትምከረው ፣ ብልኅ ፣ ግን ፣ በጥበብ ፣ ላይ ፣ ጥበብ ፣ መጨመር ፣ ስለሚሻ ፣ ምክርህንና ፣ ተግሣጽህን ፣ በደስታ ፣ ይቀበልሃል ፣ ተብሎ ፣ በተነገረው ፣ ለመጠቀም ፣ አትበዝኑ ።

የሦስት ፡ ሌቦች ፡ ምክር ።

ሦስት ፡ ሌቦች ፡ ለስርቆት ፡ ተመካክረው ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ሀገር ፡ ሄዱ ። ከሚሰርቁበትም ፡ ቤት ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ ይሻለናል ፡ ተባብ ለው ፡ ዘዴ ፡ ፈጠሩ ። ከዚህም ፡ ለመስረቅ ፡ ከሰሙበት ፡ ቤት ፡ ድግስ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ከሦስቱ ፡ አንዱ ፡ እዝማሪ ፡ ሆኖ ፡ ሊገባና ፡ የተሰበሰበውን ፡ ሰው ፡ ሊያጫውት ፡ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ሁለቱ ፡ ከበቶቹን ፡ ይዘው ፡ ሊሄዱ ፡ ምክር ፡ አደረጉ ።

እነሱም ፡ ስም ፡ ለስም ፡ እየተዋዠቁ ፡ ኖሮ ፡ ያ ፡ አዝማሪ ፡ የሆ ነው ፡ በኋላ ፡ ማ ፡ ብዬ ፡ ልጥራችሁ ፡ አላቸው ፡ ከሁለቱ ፡ አንደኛው ፡ ተገኙ ፡ በለኝ ፡ አለው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አዝማሪው ፡ ጉበኖ ፡ ጨዋታውን ፡ ገምመረ ። ባለቤቶቹም ፡ የእውነት ፡ መስሏቸው ፡ አፋቸውን ፡ ከፍተው ፡ ሲያዳምጡ ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡ ዘፈነ ።

ወንዱ ፡ ሽማግሌ ፡
ሴቲቱም ፡ እሮጊት ፡
አጥሩም ፡ ኰሸሸላ ፡
ውሻዋም ፡ ቦችላ ፡
ነዪ ፡ ኮቲ ፡ ነዪ ፡ ኮቲ ፡
ነዪ ፡ እኒ ፡ ኒ ፡



ያቺ ፡ ውሻ ፡ በደን ፡ ዐይኑን ፡ እያየች ፡ ትጠብቀው ፡ ገመር።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ያች ፡ ውሻ ፡ የጠራት ፡ መስሏት ፡ ጭራዋን ፡ እየቈላች ፡ ዐይ ን ፡ ዐይኑን ፡ እያየች ፡ ትጠብቀው ፡ ገመር ። በፈት ፡ ግን ፡ ቡና ፡ ቡና ፡ እያለች ፡ አስቸገራው ፡ ነበር ። በጨዋታው ፡ ሰዓት ፡ እነዚያ ፡ ሁለቱ ፡ ሌቦች ፡ ከብቶቹን ፡ ይዘው ፡ ሄደው ፡ ኖሮ ፡ እረኛው ፡ እዲጅ ፡ ጠዋቶ ፡ ከበረቱ ፡ ውስጥ ፡ አንድም ፡ ከብት ፡ ስላጣ ፡ ተመልሶ ፡ ሲሮጥ ፡ ገብቶ ፡ እረ ፡ በበረቱ ፡ አንድም ፡ ከብት ፡ የለ ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ፡ ባለቤቶቹም ፡ ደነገጡ ፡ ጨኸትም ፡ ሆነ ፡ እገሩ ፡ ሁሉ ፡ ተሸበረ ። ይህን ፡ ጊዜ ፡ ያ ፡ ሴ ባ ፡ አዝማሪ ፡ አትጨኹ ፡ እያንዳንዳችን ፡ በያለበት ፡ ተበታትነን ፡ እንሂ

ድና ፡ እንፈልግ ፡ እናንተም ፡ ያገኛችሁ ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ ተገኙ ፡ በሉና ፡ ንገሩኝ ፡ እኔም ፡ ባገኛቸው ፡ ተገኙ ፡ እላችኋለሁ ፡ ብሎ ፡ ከጠገባቸው ፡ ሄደ ። እልፍ ፡ አለናም ፡ ከተራራ ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ አረ ፡ ተገኙ ፡ እያለ ፡ ይጣራ ፡ ገሥመር ። እነዚያም ፡ ከብቶቻቸው ፡ የጠፉባቸው ፡ ሰዎች ፡ ደስታ ፡ ይዟቸው ፡ በሩጫ ፡ አጠገቡ ፡ ደረሱ ። እሱ ፡ ግን ፡ የጠራው ፡ ባልደረባውን ፡ ነበርና ፡ ባለቤቶቹም ፡ የታሉ ፡ ብለው ፡ ጠየቁት ፡ እኔ ፡ የት ፡ እየኋቸው ፡ አላየሁም ፡ አለና ፡ መለሰላቸው ። ታዲያ ፡ ለምን ፡ ተገኙ ፡ አልከና ፡ እታለልከን ፡ ብለው ፡ ያዙት ። ለጊዜው ፡ በውስጡ ፡ ተንኰል ፡ ነገር ፡ በመኖሩ ፡ ደነገጠ ፤ ይዘውትም ፡ እመልከኝ ፡ ዘንድ ፡ ሄደው ፡ ጌታችን ፡ ሆይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያሳይም ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ዘመዝመሪያው ፡ ከቤታችን ፡ ሲመጣ ፡ ከመሸ ፡ ስዓት ፡ ከተላለፈ ፡ በላይ ፡ ነው ፤ ደግሞ ፡ ከብቶቻችን ፡ ስለ ፡ ጠፉብን ፡ እኔም ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ እፈልጋለሁ ፤ በተገኙም ፡ ጊዜ ፡ እጠራችኋለሁ ፡ እናንተም ፡ ስታገኙ ፡ ተገኙ ፡ በሉኝ ፡ ብሎን ፡ ተነሥተን ፡ ስንፈልግ ፡ ተገኙ ፡ ብሎ ፡ ጮኸ ። አጠገበ ፡ ብንደርስ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ከብት ፡ አልነበረም ፤ ስለዚህ ፡ ከብቶቻችንን ፡ የወሰደ ፡ እሱ ፡ ነውና ፡ ይክፈለን ፡ ብለን ፡ ነው ፡ ያመጣነው ፡ በማለት ፡ አመለከቱ ። ዳኛውም ፡ የነሱን ፡ ነገር ፡ አቁሞ ፡ በተራው ፡ ሰውየውን ፡ እህ ፡ ወንድሜ ፡ ይህ ፡ የሚሉት ፡ ነገር ፡ እውነት ፡ መሆኑን ፡ ታምናለህ ፡ ወይስ ፡ ትክዳለህ ፡ መልሱን ፡ ስጠን ፡ አለና ፡ ጠየቀው ።

ሰውየውም ፡ እኔ ፡ ለራሴ ፡ ከብት ፡ የሚባል ፡ አላየሁም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ቤቴ ፡ ልጄን ፡ መጣራቱ ፡ ነበረ ፡ የልጄ ፡ ስም ፡ ተገኙ ፡ ነው ። ተገኙ ፡ ያልኩበት ፡ ምክንያቱም ፡ ልጆቼ ፡ ሁሉ ፡ አልቀው ፡ ብኝ ፡ በመጨረሻ ፡ ስለ ፡ ወለድኩት ፡ ነው ፤ ስለዚህም ፡ ተገኙ ፡ ብዬ ፡ ልጄን ፡ ብጠራ ፡ ደብድበው ፡ አስረው ፡ ይኸው ፡ እንደሚያዩት ፡ ከርስም ፡ ዘንድ ፡ አምጥተው ፡ እንደ ፡ ወንጀለኛ ፡ አቁመውኛል ፡ ሲል ፡ መለሰለት ።

መልከኛውም ፡ ነገሩን ፡ አዳምጦ ፡ ሰምቶ ፡ ተገኙ ፡ ብሎ ፡ ልጁን ፡ በጠራ ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ደብድባችሁ ፡ አስራችሁ ፡ ያመጣችሁት ፡ ይኸ ፡ በደልና ፡ ጥፋት ፡ የናንተው ፡ ነው ፡ ለሱም ፡ ትክሰላችሁ ፡ እናንተም ፡ ትቀጣላችሁ ፡ በማለት ፡ ፈረደባቸው ። የከብቶቹ ፡ ባለቤቶችም ፡ መቀጫቸውን ፡ ተቀጥተው ፡ ለሰውየውም ፡ ክሰው ፡ የበለጠ ፡ ከሰራ ፡ አግኝቷቸው ፡ በንዴት ፡ ላይ ፡ ንዴት ፡ ጨምረው ፡ እያዘኑና ፡ እያለቀሱ ፡ ወደየቤታቸው ፡ ሄዱ ።

ያም ፡ ሰው ፡ ከዚያ ፡ ተነሥቶ ፡ ባልደረባቹን ፡ እየዘረ ፡ ፈልግ ፡ ስለ ፡ እጣቸው ፡ አዩ ፡ እንግዲህ ፡ ምን ፡ አደርጋለሁ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ተመለሰ ።

እነኛም ፡ ሰርቀው ፡ ይዘው ፡ የሄዱት ፡ ሁለቱ ፡ ሌቦች ፡ በከብቶቹ ፡ የመመቀኛኘት ፡ መንፈስ ፡ አደረባቸው ። አንዱ ፡ አንዱን ፡ ብገድለው ፡ ሀብቱ ፡ ለኔ ፡ ይሆን ፡ የለምን ፡ ብሎ ፡ አሰበ ። ሁለተኛውም ፡ እንደ ዚሁ ፡ ያለ ፡ ሐሳብ ፡ አደረበት ። በዚህ ፡ ተንኰል ፡ እየተሳሰቡ ፡ አብረው ፡ ሲጓዙ ፡ ሳለ ፡ ከብት ፡ ጥለን ፡ እንብላ ፡ እንጂ ፡ በረኃብ ፡ እናልቃለን ፡ ተባብለው ፡ አንድ ፡ መሲና ፡ አረዱ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እንዳችን ፡ ላሟን ፡ ስንገፋ ፡ እንዳችን ፡ እገበያ ፡ ሄደን ፡ እንጀራ ፡ እንግዛ ፡ ያለንጀራ ፡ ምን ፡ እናደርገዋለን ፡ ተባብሰው ፡ ከሁለቱ ፡ አንደኛው ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ሄደ ። እገበያም ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ሙሽ ፡ በቀሩልቀሉት ፡ የማትገሙትሙ ፡ እንጀራና ፡ ሽልጦ ፡ አገኘና ፡ ገዝቶ ፡ ለራሱ ፡ አበቃው ፡ ድረስ ፡ በላና ፡ በባልንጀራው ፡ ድርሻ ፡ ላይ ፡ መርዝ ፡ ጨመረና ፡ ፈትፍቶ ፡ እየተጎኰለ ፡ እሱ ፡ ሲሞትልኝ ፡ ከብቶቹን ፡ እኔ ፡ እወስዳለሁ ፡ በማለት ፡ በሩጫ ፡ ተመለሰ ። ጓደኛውም ፡ እንደሱው ፡ ሲመጣ ፡ ገድዬ ፡ ከብቶቹን ፡ በሙሉ ፡ እወስዳለሁ ፡ ሲል ፡ በልቡ ፡ ተንኰል ፡ አሰበ ፡ ኖሮ ፡ ላሟን ፡ ገፎ ፡ ሥጋዋን ፡ ዕንጨት ፡ ላይ ፡ ሰቅሎ ፡ እልፍ ፡ ብሎ ፡ ከመንገዱ ፡ ላይ ፡ ሲጠባበቀው ፡ ቄየ ፡ እንጀራ ፡ ያመጣውን ፡ ጓደኛውን ፡ ገና ፡ እጠገቡ ፡ ሳይደርስ ፡ በሩቁ ፡ ለምንድነው ፡ እስካሁን ፡ የቄየኸው ፡ ብሎ ፡ ተቈጣው ፤ ያም ፡ መንገዱ ፡ ሩቅ ፡ ስለ ፡ ሆነብኝ ፡ ነውና ፡ እትቈጣኝ ፡ ቢለውም ፡ ሰበብ ፡ ፈልጓልና ፡ ቃሉን ፡ እጕልቶ ፡ አከሮ ፡ ከተሰደበ ፡ በኋላ ፡ ዘያዘው ፡ ጕሪዴ ፡ እንገቱን ፡ ቀልቶ ፡ ጣለው ። ቀጥሎም ፡ ያመጣለትን ፡ እንጀራና ፡ ሽልጦ ፡ ወስዶ ፡ በላ ። ነገር ፡ ግን ፡ መርዝ ፡ ነበረበትና ፡ አፍታም ፡ ሳይቈይ ፡ ወዲያው ፡ ድብን ፡ አለ ። ሁለቱም ፡ እርስ ፡ በራሳቸው ፡ በተንኰል ፡ በምቀኝነት ፡ በልደከሙበት ፡ በለፋበት ፡ በሰው ፡ ከብት ፡ ያረዱትን ፡ እንኳ ፡ ሳይበሉለት ፡ ተላለቁ ።

አዝማሪ ፡ የሆነው ፡ በልደረባቸው ፡ እረ ፡ ዛሬ ፡ ዕዳ ፡ ከሜዳ ፡ ሲለኝ ፡ እደራ ፡ አለና ፡ ለሚስቱ ፡ አጫወታት ። እሷም ፡ እይ ፡ ቅዠት ፡ ነው ፡ አለችው ። እሱ ፡ ግን ፡ እኔ ፡ ያየሁት ፡ ሕልም ፡ ዕለቱን ፡ ነው ፡ የሚደርሰው ፡ እላት ። እንግዲያስ ፡ ከቤትህ ፡ ተጠንቅቀህ ፡ ዋል ፡ ብትለው ፡ እኔ ፡ የዛሬን ፡ ቀን ፡ የማሳልፈው ፡ በጫካ ፡ ነውና ፡ ይልቀስ ፡ ምሳዬን ፡ ቶሎ ፡ ስጪኝ ፡ ልሂድ ፡ አላት ። እንደ ፡ በላም ፡ ተነሥቶ ፡ ከዱር ፡ ገባና ፡ ጥቂት ፡ ጥሻ ፡ ለጥሻ ፡ ሲሹለከለክ ፡ ቄይቶ ፡ ላሞቹ ፡ አሉበት ፤ ሥጋው ፡ ታርዶ ፡ ከተሰቀለበት ፡ ዛፍ ፡ አቅራቢያ ፡ ቀጭ ፡ አለ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በድንገት ፡

የከብቶቹ ፡ ባለቤቶች ፡ ደረሱና ፡ ቀና ፡ ቢሉ ፡ ሥጋ ፡ ተሰቅሎ ፡ ወደ ፡ ሜክሲኮ ፡ ቢመለከቱ ፡ ያ ፡ ያስቀጣቸው ፡ ሰው ፡ ተደብቆ ፡ አገኙ ።

እሱ ፡ ግን ፡ ከብቶቹ ፡ የማን ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ እላወቀም ፤ ሥጋውንም ፡ አላየም ፡ ነበር ። እነኛ ፡ ባለከብቶቹ ፡ ግን ፡ ኡኡታቸውን ፡ አቀለጡት ። አገር ፡ ተሰብስቦ ፡ ምን ፡ ሆናችሁ ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቃቸው ፡ ይኸ ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ከብቶቻችን ፡ በጠፋብን ፡ ሰዓት ፡ እኛ ፡ ቤት ፡ መጥቶ ፡ ነበረ ፡ ኡኡ ፡ ብለን ፡ አገር ፡ እንዳይረዳን ፡ ኤትፈልጉት ፡ እኔ ፡ እፈልግላ ችኋለሁ ፡ በተገኙም ፡ ጊዜ ፡ ተገኙ ፡ ብዬ ፡ እጠራችኋለሁ ፡ ብሎን ፡ ስን ፈልግ ፡ እልኑ ፡ አለና ፡ እረ ፡ ተገኙ ፡ ብሎ ፡ ጠራን ፤ እኛም ፡ ደስ ፡ ብሎን ፡ አጠገዙ ፡ ደርሰን ፡ ብንጠይቀው ፡ አላገኘሁም ፡ አለን ። ይኸን ንም ፡ በመናገሩ ፡ ከሰን ፡ እዳኛ ፡ ብናቀርበው ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ክዶ ፡ እስቀጥቶን ፡ ነበር ፡ አሁን ፡ ግን ፡ እከብቶቻችን ፡ አጠገብ ፡ ተቀምጠ ፡ አንዲን ፡ ላም ፡ አርዶ ፡ ሥጋውን ፡ ሰቅሎ ፡ አገኘነው ። ስለዚህ ፡ ሐሰት ፡ ያለው ፡ እውነት ፡ ሆኖ ፡ ተገኝቷልና ፡ እይቀጡ ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣልናል ፡ ብለው ፡ ተናገሩ ። ሕገበኞም ፡ ይህንን ፡ ጉዳይ ፡ የሚፈታው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ወደ ፡ ዳኛ ፡ ሂዱ ፡ ብሎ ፡ አቄራኝቶ ፡ ላካቸው ።

ዳኛው ፡ ከሥር ፡ ገምሮ ፡ የነገሩን ፡ እመጣጥ ፡ ከተመለከተ ፡ በኋላ ፡ በሌባው ፡ ላይ ፡ የብዙ ፡ ዓመት ፡ እስራት ፡ ፈረደበት ። ባለቤቶቹም ፡ ከብ ቶቻቸውን ፡ ይዘው ፡ በታረደችውም ፡ ላማቸው ፡ ዋጋ ፡ ተቀብለው ፡ በደ



የከብቶቹ ፡ ባለቤቶች ፡ ደረሱና ፡ ቀና ፡ ቢሉ ፡ ሥጋ ፡ ተሰቅሎ ፡ ወደ ፡ ሜክሲኮ ፡ ቢመለከቱ ፡ ያ ፡ ያስቀጣቸው ፡ ሰው ፡ ተደብቆ ፡ አገኙት ።

ኅና ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ተመልሰው ፡ ገቡ ። አታላዩ ፡ ሌባ ፡ ግን ፡ በእስር ፡ ቤት ፡ ሳለ ፡ ታሞ ፡ ሞተ ፡ ይባላል ።

፠ አታላይ ፡ ሌላውን ፡ ያታለለ ፡ ይመስለዋል ፤ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ የሚጐዳው ፡ እሱው ፡ ራሱ ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፤ የተንኰሉን ፡ ሥራ ፡ የወጠነው ፡ ተገኙ ፡ የተባለው ፡ የግብር ፡ አበሮቹን ፡ ሁሉ ፡ ዕዳ ፡ ከፋይ ፡ ሆነ ።

ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ተንኰለኛንና ፡ አታላይን ፡ ጓደኛ ፡ አለማድረግ ፡ ይጠቅማል ።

ሴቶች ፡ ሹመት ፡ እንደ ፡ ለመኑ ።

ሴቶች ፡ ተሰብስበው ፡ መሳፍንት ፡ መኳንንትና ፡ አገረ ፡ ገዥዎችም ፡ ሁሉ ፡ በሉበት ፡ እኛስ ፡ ብንሆን ፡ ሰዎች ፡ አይደለንም ፡ ምነው ፡ አገር ፡ ግዛት ፡ ሹመት ፡ አሰይጠን ፡ ሲሉ ፡ አመለከቱ ። የተሰበሰቡት ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ ስለ ፡ ተጨነቁ ፡ ምክር ፡ አደረጉ ። ብንሾማ ቸው ፡ ሥርወትና ፡ ፍርድ ፡ አያውቁ ፡ አይሆንም ፡ ብንላቸው ፡ በየቤታችን ፡ ይበድሉናል ፡ የሚል ፡ ክርክር ፡ ተነሣ ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ወፍ ፡ እንያዝና ፡ ባገልግል ፡ ቄልፈን ፡ ከንጉሡ ፡ ዘንድ ፡ እንላክቸው ፤ ያደረሱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይሾሙ ፡ ካላደረሱ ፡ ግን ፡ ይቅ ርባቸው ፡ ብለው ፡ ወሰኑ ። ለንጉሡም ፡ ይህንኑ ፡ ሐሳብ ፡ ገለጹለት ። ወዲ ያው ፡ ይዘው ፡ ባገልግል ፡ ከተው ፡ ይህንን ፡ ዕቃ ፡ ለንጉሥ ፡ እድርሱ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ምስጢር ፡ ነውና ፡ ከፍታችሁ ፡ እንዳታዩት ፡ ብለው ፡ እስጠን ቅቀው ፡ ላኳቸው ።

እነሱም ፡ የተሰጣቸውን ፡ ዕቃ ፡ ይዘው ፡ ሲሄዱ ፡ ሳለ ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ በውስጡ ፡ ያለው ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለማወቅ ፡ ጓጉ ። በመከከላቸው ፡ አንድ ፡ እንኳ ፡ አይሆንም ፡ ባይ ፡ ጠፍቶ ፡ ባደራ ፡ የተቀበሉትን ፡ አገል ግል ፡ ከፈቱት ። ያችም ፡ ወፍ ፡ ቱር ፡ ብላ ፡ ወጥታ ፡ አመለጠች ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የሚያደርጉትን ፡ አጥተው ፡ በጣም ፡ ተቸገሩ ፤ በመጨረሻው ፡ በወፏ ፡ ምትክ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ጨምረው ፡ ቄልፈው ፡ አገልግሉን ፡ ወስደው ፡ ለንጉሡ ፡ አቀረቡለት ። ንጉሡም ፡ በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ አስቀድሞ ፡ ከመሳፍንቱ ፡ ከመኳንንቱ ፡ ካገረ ፡ ገዥዎቹና ፡ ከሹማምቶቹ ፡ ጋራ ፡ የተነጋገረበት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፤ ላኩልኝ ፡ ያልኳቸው ፡ ይህ ፡ አይደለም ፡ ወፍ ፡ እንጂ ፡ ወዴት ፡ አለች ፡ አላቸው ። እነሱም ፡ ነገሩን ፡ እንዳወቀበቸው ፡ ተረድተው ፡ እውነቱን ፡ አውጥተው ፡ በመንገድ ፡ የሠሩትን ፡ ሥራ ፡ ገልጠው ፡ ነገሩት ። ንጉሡም ፡

እንግዲያውማ ፡ በዚህ ፡ በትንሹ ፡ ነገር ፡ ያልተጠነቀቃችሁና ፡ ምስጢር ፡ የገለጻችሁ ፡ ከሳ ፡ ያለ ፡ ጎላፊነት ፡ እንዴት ፡ ሊጣልባችሁ ፡ ይቻላል ፣ ብሎ ፡ የጠየቁትን ፡ ሹመት ፡ ከለከላቸው ፡ ይባላል ።



እትዬ ፡ እትዬ ፡ ተባባሉና ፡ አገልግሎን ፡ ከፈት ፡ ቢያደር ጉት ፡ ያቺ ፡ ወሳ ፡ ተር ፡ ብላ ፡ ወጣች ።

፠ ከሴቶች ፡ ብቻ ፡ ላይሆን ፡ ከወንዶችም ፡ ውስጥ ፡ አንዳንዶች ፡ ምስጢር ፡ የማይችሉ ፡ ይገኛሉ ፡ ስለዚህ ፡ ሴት ፡ ወንድ ፡ ሳንል ፡ ምስጢር ፡ አለመቻል ፡ በደል ፡ መሆኑን ፡ መገንዘብ ፡ ይገባናል ።

በነውር ፡ የተሰደዱ ፡ ሦስት ፡ ንጹኞች ።


አንደኛው ፡ በብዙ ፡ የሚበላ ፡ ሆዳም ፡ ሁለተኛው ፡ ሌባ ፡ ሦስተኛው ፡ ሰባቂ ፡ የሆኑ ፡ ከተወለዱበት ፡ አገር ፡ ለጌታ ፡ አዳር ፡ ሄደው ፡ ትልቅ ፡ ቤት ፡ ብዙ ፡ ከብት ፡ ባዩ ፡ ቀኖር ፡ ባለቤቶቹን ፡ በሰሌንት ፡ ቅጠሩን ፡ ብለው ፡ ይለምኑ ፡ ዝመር ። ምን ፡ ምን ፡ ሥራ ፡ ታውቃላችሁ ፡ ጠባያችሁስ ፡ ምንድ ነው ፡ ቢሏቸው ፡ ሞያችን ፡ እርሻ ፡ ማረስ ፡ የጉልበት ፡ ሥራ ፡ ማናቸውንም ፡ መሥራት ፡ በቤት ፡ ውስጥ ፡ ማስተዳደር ፡ ነው ፤ ጠባያችን ፡ ግን ፡ ያንደኛችን ፡ ሰባቂነት ፡ የሁለተኛችን ፡ ሆዳምነት ፡ የሦስተኛችን ፡ ሌብነት ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ያለባቸውን ፡ ነውር ፡ ከመናገር ፡ አልሸሸጉም ። እንዲህም ፡ በማለት ፡ ሰብዙ ዎች ፡ ጌቶች ፡ እየተዘዋወሩ ፡ ቢያስታውቁ ፡ ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ነውር ፡ አለብን ፡ እያላችሁ ፡ ማን ፡ ይቀጥራችኋል ፡ አንፈልግም ፡ እያሉ ፡ ከመሰሰቸው ፡ በኋላ ፡

እንድ ፡ ንብረቱ ፡ የበዛ ፡ ቤቱ ፡ የሰፋ ፡ ያስተዳደር ፡ ዐቅድ ፡ ዐዋቂ ፡ ነኝ ፡ ባይ ፡ ጌታ ፡ እኔ ፡ አሳድራችኋለሁ ፡ ብሎ ፡ ተቀብሎ ፡ ብዙ ፡ የሚበላውን ፡ ሆዳም ፡ አዛኙ ፡ ሌባውን ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ ሰባቂውን ፡ የልፍኝ ፡ እሽከር ፡ አድርጎ ፡ ቀጠራቸው ። ይህንንም ፡ ማድረጉ ፡ ሆዳሙ ፡ አዛኙ ፡ ሲሆን ፡ እንጀራው ፡ ሥጋው ፡ ጠጁ ፡ ጠላው ፡ ማናቸውም ፡ የምግብ ፡ ድርጅት ፡ በሱ ፡ ጎላፊነት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የሚሠራው ፡ ዐይኑ ፡ ይጠግብና ፡ ከሥሥት ፡ ይድናል ፤ ምናልባትም ፡ ልቡ ፡ ቢጓጓ ፡ እንሥቼ ፡ ልብላ ፡ ቢል ፡ እንዲቀርብ ፡ በተጠየቀ ፡ ጊዜ ፡ ከዝግጅቱ ፡ ጐድሎ ፡ ቢገኝ ፡ እነወራለሁ ፡ እቀጣለሁ ፡ ሲል ፡ ከምግቡ ፡ ሆዱን ፡ ይቈጥባል ። ሌባውም ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በመዝገብ ፡ ከተረከበው ፡ ዕቃ ፡ ወይም ፡ ገንዘብ ፡ ቢጐድልበት ፡ በጎላፊነት ፡ ተረክቢልና ፡ እቀጣለሁ ፡ እዋረዳለሁ ፡ በማለት ፡ በምንቱ ፡ ጠንክሮ ፡ ይጠብቃል ። ሰባቂውም ፡ ባለሟል ፡ ሲሆን ፡ ያለሱ ፡ እልፍኝ ፡ ገቢ ፡ ምሥጢር ፡ ሰሚ ፡ የለምና ፡ ምሥጢሩ ፡ እውጭ ፡ ወጥቶ ፡ ሰው ፡ ሰምቶት ፡ ቢገኝ ፡ እቀጣለሁ ፡ ብሎ ፡ እፉን ፡ ጠብቆ ፡ ይኖራል ፡ በ ማለት ፡ ነው ።

እንደ ፡ ተባለውም ፡ ሆዳሙና ፡ ሌባው ፡ በተሰጣቸው ፡ ሥራ ፡ እም ነታቸውን ፡ ጠብቀው ፡ እደራቸውን ፡ እጥብቀው ፡ ማገልገል ፡ ያዙ ።

በተቀጠሩ ፡ በወሩ ፡ ጌታቸው ፡ እርሻ ፡ ሊያሰርሱ ፡ እመቤታቸው ፡ ደግሞ ፡ ፈትል ፡ ሊያስፈትሉ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ድግስ ፡ ይሰናዳ ፡ ዝመር ። በመጨረሻው ፡ ሥራው ፡ ለነገ ፡ ሊሆን ፡ ሌሊቱን ፡ የሠንጋ ፡ ቀኖቢታቸውን ፡ እንጥፈው ፡ ተኝተው ፡ እንቅልፍ ፡ ወስዷቸው ፡ ሳለ ፡ ያ ፡ ሰባቂ ፡ እሽከር ፡ ሙቅ ፡ ውሃ ፡ በመቤቱና ፡ በጌታው ፡ መካከል ፡ ዝግ ፡ ብሎ ፡ ቡልኳቸውን ፡ ገለጥ ፡ አድርጎ ፡ እፈሰሰ ። እነሱም ፡ በነቁ ፡ ጊዜ ፡ ያ ፡ የሠንጋው ፡ ቀኖበት ፡ ሰመምጠጥ ፡ ባለመቻሉ ፡ ውሃው ፡ ከሁለቱ ፡ መካከል ፡ እቀኖሮ ፡ ሞቃቸው ። እመቤቲቱ ፡ እሳቸው ፡ ናቸው ፡ የሸኑት ፡ ጌትዮውም ፡ እሷ ፡ ናት ፡ የሸኑችው ፡ በማለት ፡ ተማምተው ፡ ሰይነጋገሩ ፡ ሴቲቱ ፡ ተነሥተው ፡ ቀኖበቱን ፡ ገልብጠው ፡ በጨርቅ ፡ አድርቀው ፡ ገዙ ፡ ብለው ፡ ተመልሰው ፡ ተኙ ። ከንጋም ፡ ወዲህ ፡ ሥራቸውን ፡ በማሰብ ፡ ወንዱ ፡ በማለዳ ፡ ወደ ፡ እርሻቸው ፡ ሲሰማሩ ፡ እመቤትዮዋም ፡ ደግሞ ፡ የቤት ፡ ሥራቸውን ፡ ለማከናወን ፡ ተዘጋጁ ። ቀኑ ፡ ጦም ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ በልዮው ፡ ጥላቸውን ፡ በጫማቸው ፡ ሰፍረው ፡ ሰዓቱን ፡ ከወቁ ፡ በኋላ ፡ እሽከራቸውን ፡ ሄደህ ፡ ምሳ ፡ እንዲመጣ ፡ እድርግ ፡ ብለው ፡ ላኩት ። እሱም ፡ የፍጥነት ፡ ነገር ፡ መቼም ፡ ይሆንለታልና ፡ ሲሮጥ ፡ ሄዶ ፡ እመቤቱ ፡ ከተወለድኩ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ከቶ ፡ አጋጥሞኝ ፡ አያውቅም ፤ ዝሮ ፡

ሁሉን ፡ ይሰማል ፤ ዛሬ ፡ ጉድ ፡ ሰምቼ ፡ መጣሁ ፡ አላቸው ። ሴቲቱም ፡ ምንድነው ፡ ልጄ ፡ በማለት ፡ ጠየቁት ። ጌቶች ፡ የርስዎን ፡ ስም ፡ ሲያ ጠፉ ፡ ዋሷ ።



በመቤቱና ፡ በጌታው ፡ መካ ከል ፡ ገባ ፡ ብሎ ፡ ብልኣቸው ን ፡ ገለጥ ፡ አድርጎ ፡ አፈሰሰ ።

ምን ፡ ምን ፡ አያሉ ፡

ሽንታቸን ፡ ሸንችብኝ ፡ እያሉ ፡ ነዋ ፤ ዛሬ ፡ በደቦው ፡ ላይ ፡ ከዚህ ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ አይጫወቱ ፡ ብሎ ፡ አክብዶ ፡ ነገራቸው ። ሴትዮዋም ፡ ይሽንን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ተናደዱ ፡ አረሩ ፡ ከሰሉ ፤ ጨሱ ፤ እንዲያውም ፡ አንቱ ፡ የሚሏቸውን ፡ ባላቸውን ፡ አንተ ፡ ብለው ፡ እሱ ፡ የሸነውን ፡ በኔ ፡ ያመካኛል ፡ አያሉ ፡ በመናደድ ፡ ላይ ፡ ሠነው ፡ ሳሉ ፡ ምሳ ፡ ላኩ ልን ፡ ብለው ፡ ነበረ ፡ አላቸው ። እረ ፡ የምን ፡ ምሳ ፡ ነው ፡ ደግሞ ፡ ብለው ፡ በንዴት ፡ ቃል ፡ ተናገሩት ። አሽከርዮውም ፡ ሹልክ ፡ ብሎ ፡ ተመልሶ ፡ ሄደ ። ጌታው ፡ ምሳውስ ፡ ብለው ፡ ቢጠይቁት ፡ እዬዬ ፡ የምን ፡ ምሳ ፡ ነው ፡ ጌታዬ ፡ እሳቸው ፡ ለራሳቸው ፡ የርስዎን ፡ ስም ፡ እያጠለጠሉ ፡ ከሴቶቹ ፡ ጋራ ፡ መሣቅ ፡ ብቻ ፡ ሠናልዎታል ። እኔ ፡ ስለ ፡ ርስዎ ፡ በን ዴት ፡ ተቃጥዬ ፡ ልሞት ፡ ነበር ፡ አላቸው ።

—ምን ፡ አያሉ ፡ ነው ፡ እባክህ ፡

—ሽንታቸውን ፡ ዛልጋ ፡ ላይ ፡ ሸኑ ፡ እያሉ ፡ ነዋ ፡ ጌታዬ ። ሰውየውም ፡ ተናደው ፡ ሲገሠግሡ ፡ ሄደው ፡ እቤት ፡ እንደ ፡ ደረሱ ፡ ለመደብደብ ፡ የፈለጌ ፡ ቁመጣቸው ፡ ይዘው ፡ ከመኝታ ፡ ቤት ፡ ከሰገነት ፡ ውስጥ ፡ ገብ ተው ፡ ሚስታቸውን ፡ ቢጠሯቸው ፡ በነገሩ ፡ አኮርፈው ፡ ከመ ፡ ጤፍ ፡ ሳይቄጥሯቸው ፡ ችላ ፡ አሏቸውና ፡ ቄዩ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ባለቤትዮው ፡ ሽጉጣቸውን ፡ አጉርሠው ፡ እንደ ፡ ደረሱ ፡ ሚስታቸውን ፡ ደረታቸውን ፡ ብለው ፡ ገለበጧቸው ።


አሽከሩም ፡ ገና ፡ ጌትዮው ፡ ሲገቡ ፡ አይቶ ፡ እየሮጠ ፡ ሄዶ ፡ ለሴት ዮዋ ፡ ዘመዶችና ፡ ወገኖች ፡ እረ ፡ እናንተ ፡ ለመሆኑ ፡ ምን ፡ ዓለመኞች ፡ ናችሁ ፡ አለና ፡ በብስጭት ፡ ተናገራቸው ። ምነው ፡ አሉት ።

—እመቤቴን ፡ ጌቶች ፡ ገደሏቸው ።

—ለምን ፡ በምን ፡ የተነሣ ።

—ለድግሱ ፡ ጠላ ፡ አልተሸከምሽም ፡ ብለው ፡ ነዋ ፤ እኛ ፡ እያለን ፡ እሳቸው ፡ ለዚህ ፡ መታሰባቸው ፡ እይገርምም ። ታዲያ ፡ አሁን ፡ ስትመጣ ፡ ነፍሷ ፡ ወጥታልን ።

ጌታው ፡ በቀጥታ ፡ መሄዳቸውን ፡ እንጂ ፡ እመቤቲቱ ፡ መገደላቸውን ፡ አላወቀም ፡ ነበረና ፡ እኔ ፡ ስመጣ ፡ ግን ፡ ያጣጥሩ ፡ ነበር ፡ አላቸው ። ሰም ቼም ፡ ቶሎ ፡ ብለው ፡ የጦር ፡ መሣሪያቸውን ፡ አዘጋጅተው ፡ ሲነሡ ፡ እየና ፡ ቀድሞ ፡ ሲሮጥ ፡ ሄዶ ፡ ላሳዳሪው ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ እንግዲህ ፡ መሰደዳችን ፡ አልቀረም ፡ ስለዚህ ፡ ይህንን ፡ የተደገሰውን ፡ ድግስ ፡ የርስዎን ፡ ዘመዶ ችና ፡ ወገኖች ፡ ዝርያዎችንም ፡ ሰብስበን ፡ ተካፍለነው ፡ ብንሄድ ፡ አይሻ ልም ፡ ብሎ ፡ አማከራቸው ። ጌትዮውም ፡ አዎ ፡ እውነትህ ፡ ነው ፤ በል ፡ ግራዝማች ፡ አብጤንና ፡ አቶ ፡ ሽሽጉን ፡ ከነጭፍሮቻቸው ፡ ጥራ ፡ አሉት ።




በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ባለቤትዮው ፡ ሽጉጣቸውን ፡ አጉርሠው ፡ እንደ ፡ ደረሱ ፡ ሚስታቸውን ፡ ደረታቸውን ፡ ብሰው ፡ ገለበ ጧቸው ።

እሱም ፡ ሮጦ ፡ ከተባሉት ፡ ሰዎች ፡ ቤት ፡ ሲቃ ፡ እንደ ፡ ያዘው ፡ ጥልቅ ፡ አለ ። አቶ ፡ ሽሽጉም ፡ ደነገጡና ፡ ምነው ፡ ምን ፡ ሆንክ ፡ ብለው ፡ ጠየቁት ።

—የመቤቲ ፡ ወገኖችና ፡ ዘመዶች ፡ ጌቶችን ፡ ገደሏቸው ።

—ነፍሳቸው ፡ ወጥታል ።

እኔ ፡ ወደዚህ ፡ ነፍሴን ፡ አጥቼ ፡ ስሮጥ ፡ መቼም ፡ ውጪ ፡ ነፍስ ፡ ግቢ ፡ ነፍስ ፡ ሆኖ ፡ እያጣጣሩ ፡ ተኝተው ፡ ይታኰሱ ፡ ነበር ፡ አላቸው ። አቶ ፡ ሽሽጉም ፡ ግራዝማች ፡ አብጤን ፡ አስጠርተው ፡ በነፍሳቸው[redacted] ድረስ ፡ ብለው ፡ የጦር ፡ መሣሪያቸውን ፡ ያዘው ፡ ሰናፊላቸውን ፡ [redacted] ፡ ታጥቀው ፡ በፍጥነት ፡ እየገሠገሡ ፡ ሄደው ፡ የሴትዮዋ ፡ ዘመዶች ፡ ሰውዮውን ፡ ገድለው ፡ የጎታቸውን ፡ ሬሳ ፡ ለመውሰድ ፡ ሲያገላብጡ ፡ ደረሱባቸው ። ምነው ፡ ደግሞ ፡ እናንተም ፍ መጣችሁ ፡ አለና ፡ አንዱ ፡ ተኰሰ



ምነው ፡ ደግሞ ፡ እናንተም ፡ መጣችሁ ፡ አለና ፡ አንዱ ፡ ተኰሰባቸው ።

ባቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሁሉም ፡ ባለመሣሪያ ፡ ነበሩና ፡ ተጣመዱ ። ከወንድየው ፡ ወገን ፡ ጎምሳ ፡ ከሴትዮዋ ፡ ሠላሳ ፡ በድምሩ ፡ ከነባለቤቶቹ ፡ ሰማኒያ ፡ ሁለት ፡ አጫረሰና ፡ የጌታውን ፡ ቤት ፡ ይዘ ፡ ተቀመጠ ።

ጌታው ፡ ሚካኤልን ፡ ማኅበር ፡ ይጠሙ ፡ ነበርና ፡ ጥዋው ፡ ለሱ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ የጌታውን ፡ ዕጣ ፡ ለመክፈል ፡ ጠላውን ፡ እስጠምቆ ፡ ማናቸውንም ፡ እስፈላጊ ፡ ነገር ፡ ካዘጋጀ ፡ በኋላ ፡ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ የሚያስወጣ ፡ መንገድ ፡ በሠረገላ ፡ ቄፍሮ ፡ ሲጠባበቅ ፡ ማኅበረተኞቹ ፡ ሠላሳ ፡ ሆነው ፡ መጡ ። እነሱም ፡ በባልንጀራቸውና ፡ በወንድማቸው ፡ መሞት ፡ ተናደው ፡ ኖሮ ፡ ያንን ፡ ክፉ ፡ አሽከር ፡ ለመግደል ፡ ዘግተው ፡ ቤቱን ፡ እሳት ፡ ለኰሱበት ። ጊዜው ፡ ነፋስ ፡ ነበርና ፡ ቃጠሎውን ፡ ስላፋጠነው ፡ ቤቱ ፡ በቶሎ ፡ አመድ ፡ ሆነ ። ይህ ፡ አሽከር ፡ ግን ፡ በዚያ ፡ ባዘጋጀው ፡ መሸለኪያ ፡ ውስጥ ፡ በደብቅ ፡ ቄይቶ ፡ ነበርና ፡ ቤቱ ፡ ተቃጥሎ ፡ ካለቀ ፡ በኋላ ፡ ምንም ፡ ሳይነካው ፡ ከመዱ ፡ መከከል ፡ በደኅና ፡ ብቅ ፡ አለ ።

እነዚህ ፡ ማኅበረተኞች ፡ አይተው ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ዳንክ ፡ ቤት ፡ ዘግተን ፡ እሳት ፡ ለቀንብህ ፡ እልነበረምን ፡ ብለው ፡ ጠየቁት ። እሱም ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ለወደደው ፡ ከእሳት ፡ ያወጣል ፡ ከነደደው ፤ ማኅበሩንስ ፡ [redacted] ፡ ስንኳን ፡ ከዚህ ፡ ከምድሩ ፡ እሳት ፡ ይቅርና ፡ ከሰማዩ ፡ ለመዳን ፡ አይደለምን ፡ ይኸው ፡ ሚካኤልን ፡ በማመኔና ፡ በማክበሬ ፡ ከእሳት ፡ አዳነኝ ፡ አላቸው ። እነሱም ፡ ይህንን ፡ ሁሉ ፡ ሰው ፡ ያጋደለውን ፡ ቀጣፊ ፡ ያዳነ ፡ እኛንማ ፡ በቅን ፡ ዘላለም ፡ ስንጠጣውና ፡ ስናከብረው ፡ የምንኖረውን ፡ እንኳን ፡ ሊፈጀን ፡ ሞቅስ ፡ መቼ ፡ ይለናል ፡ ብለው ፡ በል ፡ እንግዲህ ፡ ይህንን ፡ ቤት ፡ ዝጋብንና ፡ እሳት ፡ ልቀቅበት ፡ ብለው ፡ ሠላሳውም ፡ ማኅበረተኞች ፡ ካንድ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ ተቃጥለው ፡ አለቁ ፡ ይበላል ።



በል ፡ እንግዲህ ፡ ይህንን ፡ ቤት ፡ ዝጋብንና ፡ እሳት ፡ ልቀቅበት ፡ ብለው ፡ ሠላሳውም ፡ ማኅበረተኞች ፡ ..... ተቃጥለው ፡ አለቁ ።

እሱንም ፡ የጌታውን ፡ ሀብት ፡ ከያዘ ፡ በኋላ ፡ በነገር ፡ እየወጋ ፡ ከሚያናድዳቸው ፡ አንዱ ፡ ሳያስበው ፡ ድንገት ፡ በጥይት ፡ ገደለው ።

※ ይዋል ፡ ይደር ፡ እንጂ ፡ ሳይደክሙ ፡ በተንኰል ፡ የሰበሰቡት ፡ ሀብት ፡ በመጨረሻው ፡ ከጉዳት ፡ ላይ ፡ መጣሉ ፡ አይቀርምና ፡ ከእንደዚህ ፡ ያለ ፡ አድራጎት ፡ መታገድ ፡ ይጠቅማል ።

ለሰበቂ ፡ ገሮህን ፡ አትስጠው ፡ የተባለውንም ፡ ማሰብ ፡ ይገባል ።

የሸ'ብና ፡ የዝንጅሮ ፡ መጣላት ።

ሸ'ብና ፡ ዝንጅሮ ፡ ተጣልተው ፡ በክስ ፡ ከዳኛ ፡ ሄዱና ፡ ነገራቸውን ፡ እየዘረዘሩ ፡ አስረዱ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዳኛው ፡ በዝንጅሮ ፡ ብፈርድ ፡ እኽሌን ፡ ሁሉ ፡ በንድ ፡ ቀን ፡ አጥፍቶብኝ ፡ ሰብሌ ፡ እንደ ፡ ዋለ ፡ በዳር ፡ ይቀራል ፡ በአያ ፡ ሸ'ቦ ፡ ብፈርድ ፡ ከብቶቼን ፡ ሁሉ ፡ በንድ ፡ ቀን ፡ አዳር ፡ ይፈጅብኛል ፡ ምንም ፡ ሀብት ፡ አይተርፈኝም ፡ እንዴት ፡ ማድረግ ፡ ይሻ ለኛል ፡ በማለት ፡ እየተጨነቀ ፡ ነገሩን ፡ ሕውጥቶ ፡ አውርዶ ፡ ይህ ፡ ጉዳ ያችሁ ፡ በሽማግሌ ፡ የሚፈጸም ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በኔ ፡ የሚያልቅላችሁ ፡ አይደለምና ፡ አገሌና ፡ አገሌ ፡ ያስ'ኮርቋችሁ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ሀገር ፡ ሽማ ግሎች ፡ ላካቸው ። ሸ'ብና ፡ ዝንጅሮም ፡ እንደ ፡ ተነገሩት ፡ ሄደው ፡ አባ ቶቻችን ፡ ሆይ ፡ እኛ ፡ ሁለታችን ፡ ተጣልተን ፡ ከዳኛ ፡ ዘንድ ፡ ሄደን ፡ ነበረ ፡ የተጣላንበትን ፡ ዘርዝረን ፡ ብንነግረው ፡ ይህ ፡ ጉዳይ ፡ ሊታይ ፡ የሚ ገባው ፡ በሽምግልና ፡ እንጂ ፡ በዳኝነት ፡ አይደለምና ፡ እነሱ ፡ ያስማሟችሁ ፡ ስላለን ፡ ታስታርቁን ፡ ብለን ፡ መጥተናል ፡ ሲሉ ፡ ነገሯቸው ። ሽማግሌ



እነሱ ፡ ያስማሟችሁ ፡ ስላሉን ፡ ታስታርቁን ፡ ብለን ፡ መጥተናል ፡ ሲሉ ፡ ነገሯቸው ።

ችም ፡ ያያ ፡ ሸ'ቦንና ፡ ያቶ ፡ ዝንጅሮን ፡ ነገር ፡ ከሰሙ ፡ በኋላ ፡ እጅግ ፡ አድርገው ፡ አዘኑ ፡ ተበሳጩም ። ዳኛው ፡ በዝንጅሮ ፡ የፈረድኩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እኽሌን ፡ ሁሉ ፡ በዳር ፡ እንደ ፡ ዋለ ፡ ያስቀርብኛል ፡ በሸ'ብም ፡ ብፈርድ ፡ ከብቶቼን ፡ ይበላብኛል ፡ ብሎ ፡ አይደለምን ፡ ወደኛ ፡ የላ ኩት ። እኛም ፡ በዝንጅሮ ፡ ብንፈርድ ፡ አዝመራችን ፡ ሁሉ ፡ በን ድ ፡ ቀን ፡ ተበልቶብን ፡ ይቀራል ፤ በሸ'ብ ፡ ብንፈርድ ፡ ከብቶቻችንን ፡ ይዘላብናል ፡ በማለት ፡ ሲጨነቁ ፡ ቈይተው ፡ በማኽል ፡ አንድ ፡ ከከብትም ፡

ከእኽልም ፡ ምንም ፡ ምን ፡ የሌለው ፡ ድኻ ፡ ሽማግሌ ፡ በሀገር ፡ ውስጥ ፡ መኖሩ ፡ ትዝ ፡ አላቸውና ፡ መቼም ፡ ምኑን ፡ ይበሉበታል ፡ በማለት ፡ ከኛ ፡ ይልቅ ፡ ምክር ፡ ዐዋቂ ፡ ቃሉ ፡ ተሰሚ ፡ የሆነ ፡ አረጋዊ ፡ ሰው ፡ ስላለ ፡ ወደሱ ፡ ሂዱና ፡ ያስታርቃችሁ ፡ አሏቸው ።

መቼም ፡ የተቸገረ ፡ ጉልበቱን ፡ አይቈጥርምና ፡ ሁለቱም ፡ ተያይ ዘው ፡ ሄደው ፡ ለተባለው ፡ ሽማግሌ ፡ ነገሩት ። ድኻ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቈ ራጥ ፡ ነውና ፡ ደግ ፡ ነው ፡ አስታርቃችኋለሁ ፡ አለና ፡ ዝንጅሮን ፡ አሁ ን ፡ ለጊዜው ፡ አያ ፡ ሸ'ቦን ፡ አስተጠይቀው ፡ ድረስ ፡ ወደዚያ ፡ አልፍ ፡ ብለህ ፡ ተቀመጥ ፡ አለው ። ራቅ ፡ ሲል ፡ አየና ፡ አያ ፡ ሸ'ቦ ፡ እረ ፡ ለ መሆኑ ፡ እንዴት ፡ ያለህ ፡ ነህ ፡ አንተን ፡ የመሰለ ፡ ጐበዝ ፡ ከዚህ ፡ ከመ ላጣ ፡ ምልጥልጥ ፡ ጋራ ፡ አደባባይ ፡ ቆመህ ፡ መነጋገርህ ፡ በጣም ፡ ይገ ርመኛል ፤ ይደንቀኛልም ፡ ድምጥህ ፡ ጐራ ፡ ዘሮ ፡ ይሰማል ፤ ጉልበትህ ፡ ፈረስም ፡ ሆነ ፡ በቅሎ ፡ ብቻ ፡ ለብቻ ፡ ይሸከማል ፤ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ዝግና ፡ እንደ ፡ ምን ፡ አድርጎ ፡ ከዚህ ፡ ከሆዳም ፡ ጋራ ፡ ቆሞ ፡ ይነጋገራል ፤ ስለዚህ ፡ አሱ ፡ እንኳ ፡ ቢዘድልህ ፡ አንተ ፡ ክሰህ ፡ ክብርህን ፡ ጠብቅ ፡ እንጂ ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ ተቋቁመህ ፡ አትሟገት ፤ ዐርፈህ ፡ ታረቅ ፡ አለው ። አያ ፡ ሸ'ቦም ፡ እውነትህ ፡ እኮ ፡ ነው ፡ ያለ ፡ እኩያዬ ፡ ቍልቍል ፡ ወር ጄ ፡ መነጋገሬን ፡ ሳስበው ፡ ያሰቅቀኛል ፡ አሁንም ፡ እንደ ፡ መከርኸኝ ፡ እኔው ፡ ራሴ ፡ ክሼ ፡ መታረቁን ፡ እመርጣለሁ ፤ ከቶ ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ ቆሜ ፡ ያየኝ ፡ ሁሉ ፡ ምን ፡ ብሎኝ ፡ ይሆን ፡ እያለ ፡ በመገረም ፡ ተነሥቶ ፡ ሲሄ ድ ፡ ዝንጅሮ ፡ በተራው ፡ ተጠራ ።

አቶ ፡ ዝንጅሮ ፡ አረ ፡ ለመሆኑ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ያለህ ፡ ነህ ፡ ከዚህ ፡ ከማይረባ ፡ ጥንበ ፡ በላ ፡ ጋራ ፡ ባደባባይ ፡ እዛውንት ፡ መከከል ፡ ቁመ ህ ፡ መነጋገርህ ፡ በጣም ፡ ይገርመኛል ፡ ለመሆኑ ፡ ሰውነትህ ፡ አፈር ፡ አይ ልብህም ፡ አንተ ፡ እከ ፡ ግርማህ ፡ እንደ ፡ እንበሳ ፡ የሚያስፈራ ፡ ነው ፤ በልጅችህ ፡ መከከል ፡ ሆነህ ፡ ጐምለል ፡ ጐምለል ፡ ስትል ፡ በአጀብ ፡ የሚጓዝ ፡ መኳንንት ፡ ትመስላለህ ፤ በተረተር ፡ ብቅ ፡ ባልክ ፡ ጊዜም ፡ እንደ ፡ ጦር ፡ ወርዋሪ ፡ ገበሬን ፡ ሁሉ ፡ ታሸብረዋለህ ፤ እንዲሁም ፡ ገና ፡ በሩቁ ፡ ስትታይ ፡ ያው ፡ መጣ ፡ እየተባልክ ፡ በሰው ፡ ዘንድ ፡ ታሪክ ፡ የሚነገርልህ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ አሁን ፡ ክብርህን ፡ አዋርደህ ፡ ከዚህ ፡ ከሆ ዳም ፡ ከጥንብ ፡ ጐታችና ፡ ከፊሪ ፡ ጋራ ፡ በመነጋገርህ ፡ አታፍርምን ፡ እረ ፡ ምን ፡ ያለህ ፡ የማታስብ ፡ ነህ ፡ ወንድሜ ፡ በማለት ፡ ተቈጥቶ ፡ አሁንም ፡ በል ፡ ያለፈው ፡ አለፈ ፡ ለወደ ፡ ፊቱ ፡ ቢዘድልህም ፡ አንተ ፡ ክሰህ ፡ ታረቅ ፤

ክብርህን ፣ አታዋርድ ፣ ብሎ ፣ ቢመክረው ፣ አቶ ፣ ዝንጀሮ ፣ አርግጥ ፣ ነው ፤ አሁን ፣ በደንብ ፣ ሆኖ ፣ ገባኝ ፣ ክብሬን ፣ በገዛ ፣ እጄ ፣ አዋርጄዋለሁና ፣ ጥፋተኛ ፣ ነኝ ፤ ክሼ ፣ መታረቁ ፣ ነው ፣ የሚሻለኝ ፣ ብሎ ፣ ሐሳቡን ፣ ተቀበለ ። ድኻው ፣ ሽማግሌ ፣ ሁለቱንም ፣ ዥብና ፣ ዝንጀሮን ፣ አንድ ፣ ላይ፣ አቃርቦ ፣ በሉ ፣ እንግዲህ ፣ እንዳልኳችሁ ፣ ትታረቁ ፣ የለምን ፣ ብሎ ፣ ቢጠይቃቸው ፣ እሺ ፣ አሉና ፣ ለጥ ፣ ብለው ፣ እጅ ፣ ነሡ ።



አያ ፣ ዥቦ ፣ እረ ፣ ለመሆኑ ፣ እንዲት ፣ ያለህ ፣ ነህ፣ አንተን ፣ የመሰለ ፣ ጉበዝ ፣ ከዚህ ፣ ከመላጣ ፣ ምል ጥልጥ ፣ ጋራ ፣ አደባባይ ፣ ቆመህ ፣ መንጋገርህ ።



አቶ ፣ ዝንጀሮ ፣ እረ ፣ ለመሆኑ ፣ እንዲት ፣ ያለህ ፣ ነህ ፣ ከዚህ ፣ ከማደረባ ፣ ጥንበ ፣ በላ ፣ ጋራ ፣ ባደባባይ ፣ አዛውንት ፣ መከከል ፣ ቆመህ ፣ መንጋገርህ ፣ በጣም ፣ ይገርማል ።

ከዚህ ፣ በኋላ ፣ ይቅር ፣ ለአግዚአብሔር ፣ ተባባሉ ፣ ብሎ ፣ ይቅር ፣ አሰኝቶ ፣ አስታርቆ ፣ "በሉ ፣ ሂዱ ፣ በየቤታችሁ ፣ ግቡ ፣ ሁለተኛ ፣ ጠብ ፣ የሚባል ፣ ነገር ፣ እንዳታነሱ" ፣ ብሎ ፣ አስማምቶ ፣ አሰናበታቸው ።

፨ ልጆቼ ፣ ሆይ ፣ በገንዘብ ፣ ለሚታመኑ ፣ ሰዎች ፣ ወደ ፣ እግዚአብሔር ፣ መንግሥት ፣ መግባት ፣ እንዴት ፣ ጭንቅ ፣ ይሆንባቸው ፣ ተብሎ ፣ ማር ፣ ፯ ፣ ቊ ፣ ሯ፬ ፣ በወንጌል ፣ ተጽፏል ። ስለዚህ ፣ ለገንዘብና ፣ ለሀብት ፣ ሳያስቡ ፣ ፍርድን ፣ መጠበቅ ፣ ለትልቅም ፣ ለትንሽም ፣ ተገቢ ፣ ተግባር ፣ ነው ።

የአራዊት ፣ ለአንበሳ ፣ ሎሌነት ፣ ማደር ።

ነብር ፣ ዥብ ፣ ቀበሮ ፣ መጠማጥ ፣ ድመት ፣ ዝንጀሮ ፣ ዐይጥና ፣ ጦጣ ፣ እነዚህ ፣ ስምንቱ ፣ ለጌታው ፣ አንበሳ ፣ ሎሌነት ፣ አደሩ ። እያንዳንዳቸውም ፣ የተለየ ፣ ሥራ ፣ ነበራቸው ። ነብር ፣ የፍየል ፣ ዥብ ፣ የአህያ ፣ ቀበሮ ፣ የበግ፣ መጠማጥ ፣ የዶሮ ፣ ዐይጥ ፣ የጐተራ ፣ ድመት ፣ የወተት ፣ ዝንጀሮ ፣ የውድማና ፣ የክምር ፣ ጠባቂ ፣ ጦጣ ፣ ደግሞ ፣ የልፍኝ ፣ አሽከርና ፣ ሙሉ ፣ ቤት ፣ አዛዥ ፣ በመሆን ፣ ሁሉም ፣ በየተግባራቸው ፣ ማገልገል ፣ ዠመሩ ።

አሜቴ ፣ ጦጢት ፣ እራትና ፣ ምሳ ፣ አቅራቢና ፣ አሳላፊ ፣ ስለ ፣ ሆነች ፣ ጌታዋ ፣ ከዋለበት ፣ ሲገባ ፣ ማታ ፣ ማታ ፣ ወሬ ፣ ይጠያቃት ፣ ነበር ። እሷም ፣ ተንኰለኛ ፣ በመሆኗ ፣ ለሁሉም ፣ ቅን ፣ ነገር ፣ አታስብላቸውም ፣ ነበር ።

ከዕለታት ፣ አንድ ፣ ቀን ፣ ድመቶ ፣ እንቅልፍ ፣ ሲወስደው ፣ አይታ ፣ የሚጠብቀውን ፣ ወተት ፣ ከጠጣች ፣ በኋላ ፣ የተረፈውን ፣ አፍስሳ ፣ የድመቱን ፣ አፍ ፣ በወተት ፣ ለቅልቃ ፣ ሄደች ።

ጥቂት ፣ ቈይታም ፣ አውሬዎቹን ፣ ሁሉ ፣ ጠርታ ፣ አቶ ፣ ድመቶ ፣ ዛሬ ፣ ያደረገውን ፣ ኑ ፣ ጉድ ፣ አዩ ፣ አለቻቸው ። እነሱም ፣ እየሮጡ ፣ ቢሄዱ ፣ አቶ ፣ ድመቶ ፣ ከንቅልፉ ፣ ነቅቶ ፣ ምን ፣ ነክኝ ፣ እያለ ፣ አፉን ፣ በምላሱ ፣ ሲያቀላጥፍ ፣ አገኙት ። ምነው ፣ በል ፣ አንተ ፣ እንደዚህ ፣ ያለ ፣ ድፍረትና ፣ የምን ፣ አለብኝ ፣ ሥራ ፣ መሥራትህ ፣ ቢሉት ፣ ምነው ፣ ምን ፣ አጠፋሁ ፣ እንዲህ ፣ ያለ ፣ ጎይለ ፣ ቃል ፣ የምትናገሩት ፣ አላቸው ። ጌታችን ፣ ወተቱን ፣ ጠብቅ ፣ ቢልህ ፣ አንተው ፣ ትጠጣው ፣ አሉት ። እረ ፣ እኔ ፣ ከእንቅልፌ ፣ ብነሣ ፣ አፌ ፣ ወተት ፣ ወተት ፣ አለኝ ፣ እንጂ ፣ አልጠጣሁም ፣ እስቲ ፣ ጮጮው ፣ ይታይ ፣ ብሎ ፣ አውርዶ ፣ ቢያይ ፣ ምንም ፣ አጣበት ። በዚህ ፣ ጊዜ ፣ ክች ፣ ብሎ ፣ ደነገጠና ፣ እንግዲህ ፣ ምን ፣ ይሻለኛል ፣ እባክህ ፣ አላቸው ። ተነሥተህ ፣ ጥፋ ፣ እንጂ ፣ ደግሞ ፣ ምን ፣ ሞያ ፣ ሠራህ ፣ ብለህ ፣ ትጠብቃለህ ፣ ሲሉ ፣ መለሱለት ። ወዲያው ፣ ተደናግጦ ፣ ከጫካ ፣ ገብቶ ፣ ተሸሸገ ።

ጌታው ፣ አንበሳ ፣ ማታ ፣ ከዱር ፣ ሲገባ ፣ ዛሬ ፣ ቤቴና ፣ ሎሌዎቼ ፣ ሁሉ ፣ ደኅና ፣ ውለዋልን ፣ ጦጢት ፣ አላት ። አዎ ፣ ጌታዬ ፣ እኔ ፣ ዘወትር ፣ ለመናገር ፣

እየፈራሁዎት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ምን ፡ ደኅና ፡ ነገር ፡ አለ ፤ ቤቱ ፡ እንዴ ፡ ሆነ ፡ ዘላለም ፡ እንደ ፡ ጠፋና ፡ እንደ ፡ ተበላሸ ፡ ነው ፡ ስትል ፡ በብስጭት ፡ ነገረችው ። እሱም ፡ እስቲ ፡ የሆነውን ፡ ንገሪኝ ፡ አላት ። ጌታዬ ፡ አቶ ፡ ድመቶማ ፡ ያደረገውን ፡ ሁሉ ፡ ብነግርዎት ፡ ተናደውና ፡ ተቈጥተው ፡ አያበሩም ። ምን ፡ አድርጎ ፡ ይሆን ፡ እባክሽን ፡ ግድ ፡ የለም ፡ ንገሪኝ ፡ አላት ። የጌታዬን ፡ ወተት ፡ ጠብቅ ፡ ቢባል ፡ እየሰረቀ ፡ መጠጣት ፡ ለምዶ ፡ ኖሮ ፡ ዛሬ ፡ የርስዎ ፡ ውቃቤ ፡ አጋልጦት ፡ ራሱን ፡ ከጮሌው ፡ ሚስጥ ፡ አግብቶ ፡ ብደርስበት ፡ ሸሽቶ ፡ ከደን ፡ ገባ ፡ አለችው ።



የድመቱን ፡ አፍ ፡ በወተት ፡ ለቅልቃ ፡ ሄደች ።

በማግስቱ ፡ አቶ ፡ ዝንጀሮን ፡ ና ፡ ምሳህን ፡ ብላ ፡ ስትል ፡ ከዐውደ-ማ ፡ ጠራችው ። ተቀምጠም ፡ ሲጋበዝ ፡ በጎዳ ፡ በኩል ፡ ሾልከ ፡ የእኽሉን ፡ ክምር ፡ በሙሉ ፡ እሳት ፡ ለኰሰችበት ። ዝንጀሮም ፡ ምሰውን ፡ በልቶ ፡ እንደ ፡ ጨረሰ ፡ ከደጅ ፡ ቢወጣ ፡ ክምሩ ፡ ተቃጥሎ ፡ አመድ ፡ ሆኖ ፡ አገኘው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ጉድ ፡ ፈላ ፡ እንግዲህ ፡ ምን ፡ እባቱን ፡ አደርጋለሁ ፡ ብሎ ፡ ተመልሶ ፡ ለጠጢት ፡ ነገራት ። እሷም ፡ ራሷን ፡ ይዛ ፡ አወይ ፡ አወይ ፡ በማለት ፡ ጮኸችና ፡ ሰማህ ፡ አቶ ፡ ዝንጀሮ ፡ እንደዚህ ፡ ያደረገህ ፡ አቶ ፡ ድመቶ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርምና ፡ ቶሎ ፡ ብለህ ፡ ሰትታይ ፡ ብትጠፋ ፡ ይሻላል ፡ አለችው ። እሱም ፡ እንደ ፡ መከረችው ፡ ፈጸመ ። በማግስቱ ፡ እንኩዬ ፡ ጠጢት ፡ ከጫካ ፡ ጭራሮ ፡ ስትለቃቅም ፡ ድመቶን ፡ አገኘችውና ፡ እንዴት ፡ ዋልክ ፡ ስትል ፡ ሰላምታ ፡ ሰጠችው ። እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ ምን ፡ ልታደርጊ ፡ መጣሽ ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቃት ፡ ዕንጨት ፡ ልለቅም ፡ ነዋ ፡ አለችው ። የቀሩትስ ፡ ቢላት ፡ ከነሱማ ፡ ባንተ ፡ ምክንያት ፡ ተኳርፈን ፡ መቼ ፡ እንነጋገራለን ፡ ስትል ፡ መለሰችለት ።

—እረ ፡ ለመሆኑ ፡ ጌታዬ ፡ ምን ፡ አሉ ፡ ተቈጡኝን ።

—ዐይጥና ፡ መጠማጥ ፡ እያቀሜጫቹ ፡ ባያሰብቁብህ ፡ ኖሮ ፡ ወን ደሜ ፡ እሳቸው ፡ እንኳን ፡ ምንም ፡ ባላሉ ፡ ነበር ።

—ለካ ፡ እነሱ ፡ ናቸዋ ፡ ጠላቾቼ ፤

—አምን ፡ ያለነሱ ፡ ምን ፡ ባለጋራ ፡ አለህ ።

—እንኩዬ ፡ ጠጢት ፡ እንደ ፡ ምን ፡ አድርጌ ፡ ብድሬን ፡ ለመመለስ ፡ እችላለሁ ፡ እስቲ ፡ ብልሃት ፡ ካንቺ ፡ እይጠፋምና ፡ ምከሪኝ ።

—አይ ፡ ወንድሜ ፡ በላገደደህ ፡ ትቸገራለህ ፤ ዐይጡትን ፡ ከጕተራ ፡ ሥር ፡ ታገኛታለህ ፤ ይዘህ ፡ ቅርጭጭ ፡ ብታደርጋት ፡ ይሆናል ፤ መጠማጥንም ፡ እሱ ፡ እንኳን ፡ ቢያያልብህ ፡ ዶሮቹንና ፡ ዕንቁላሎቹን ፡ በመ ብላት ፡ ልታጠቃው ፡ ትችላለህ ።

—እምን ፡ እውነትሽ ፡ ነው ፡ በዪ ፡ ጌቶች ፡ በቤት ፡ የማይገቡበትን ፡ ቀን ፡ ንገሪኝ ፤

—ነገም ፡ ተነገ ፡ ወዲያም ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ይሄዳሉ ፤

—እንግዲያውስ ፡ እመጣለሁ ፡ ብሊት ፡ ተሰነባብተው ፡ ተለያዩ ።

ድመቶም ፡ በማግስቱ ፡ መጥቶ ፡ ዐይጡትን ፡ እጕተራ ፡ ሥር ፡ ብቅ ፡ ጥልቅ ፡ ስትል ፡ ለቀም ፡ እድርጎት ፡ ሮጠ ፤ ደግሞ ፡ ሌሊቱን ፡ ተመልሶ ፡ ዶሮች ፡ ከሚሰፍሩበት ፡ ሰበሰብ ፡ ላይ ፡ አንዷን ፡ ሲከካ ፡ ይዟት ፡ በረረ ። ኳክ ፡ ኳክ ፡ በማለቷም ፡ ሎሌዎች ፡ ተከትለው ፡ ቢያባርሩ ፡ የያዘውን ፡ ከጣለ ፡ በኋላ ፡ በጉን ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ እየሮጠ ፡ ሄደ ፤ ወዲያው ፡ በፍጥነት ፡ የተረፉትን ፡ ዶሮች ፡ አንገት ፡ አንገታቸውን ፡ እየ ቀረጨጨ ፡ ፈጃቸው ።

አሽከሮቹም ፡ ያችን ፡ ያስጣሏትን ፡ ዶሮ ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ገቡ ። ድመቶ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ሁሉንም ፡ እንቅልፍ ፡ ሲወስዳቸው ፡ ተመልሶ ፡ ሌሊቱን ፡ የገደላቸውን ፡ ዶሮች ፡ ሬሳ ፡ ሲያግዝ ፡ አደረ ። እንኩዬ ፡ ጠጢትም ፡ በጧት ፡ ተነሥታ ፡ እነዚያን ፡ ዶሮች ፡ ብታይ ፡ ከጫ ካ ፡ ከተመለሰችው ፡ በስተቀር ፡ ሌላ ፡ አንድም ፡ አጣች ። ቶሎ ፡ ብላ ፡ የዚያችን ፡ የሞተች ፡ ዶሮ ፡ ሆድ ፡ ዕቃ ፡ ዘንጥላ ፡ ትንሽ ፡ ደም ፡ ስላገኘች ፡ እንቅልፍ ፡ እንደ ፡ ወሰደው ፡ የመጠማጡን ፡ ከንፈር ፡ ቀብታ ፡ አንገቱን ፡ በፉ ፡ አስነክሳ ፡ ሬሳውን ፡ አጠገቡ ፡ አስቀምጣ ፡ ሮጣ ፡ እቤት ፡ ገባች ። ወዲያው ፡ እንበሳው ፡ ተመኝታው ፡ ሲነሣ ፡ እይታ ፡ ጌታዬ ፡ እስቲ ፡ እንሂድና ፡ ዶሮቹን ፡ እንያቸው ፡ መቼም ፡ የሱው ፡ የመጠማጥ ፡

ዘሮች ፡ ናቸው ፡ ጠላቶቻችን ፤ ቀን ፡ ቀን ፡ እያመጣ ፡ ቤቱን ፡ ባያሳያቸው ፡ መቼ ፡ ሌሊት ፡ መጥቶ ፡ ዶሮችንን ፡ ያበክታት ፡ ነበር ፡ አለችው ።

—ቀን ፡ ይመጣሉ ፡ እንዴ ፤

—አዎን ፡ ጌታዬ ።

—ታዲያ ፡ ምን ፡ ያጋብዛቸዋል ፤



አቶ ፡ አንበሳም ፡ በዩ ፡ ለወደ ፡ ፊቱ ፡ እንዳይጠፋ ፡ እንቍጠራቸው ፡ አላትና ፡ ሄደው ፡ ቢያዩ ፡ ከቦታው ፡ አንድም ፡ ዶሮ ፡ አጡ ።

እኔ ፡ ምን ፡ ዐውቄ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ተደስተው ፡ ተሸክክተው ፡ ተሣሥቀው ፡ ነው ፡ የሚለያዩት ፡ ብላ ፡ በማቋጨት ፡ ነገረችው ። አቶ ፡ አንበሳም ፡ በዩ ፡ ለወደ ፡ ፊቱ ፡ እንዳይጠፉ ፡ እንቍጠራቸው ፡ አላትና ፡ ሄደው ፡ ቢያዩ ፡ ከቦታው ፡ አንድም ፡ ዶሮ ፡ አጡ ። በቅራቢያው ፡ የተገኘው ፡ የዘያችው ፡ ሌሊት ፡ ያስጣሏት ፡ ዶሮ ፡ ፈሳ ፡ ብቻ ፡ ሆነ ፡ ያችኑም ፡ አቶ ፡ መጠግጥ ፡ ጉርሥ ፡ አድርጓት ፡ ተኝታል ። እንደ ፡ አውነቱ ፡ ግን ፡ ሌሊቱን ፡ ሰባንን ፡ አድሮ ፡ ጧት ፡ እንቅልፍ ፡ ድብን ፡ አድርጎ ፡ ስለ ፡ ወሰደው ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲደረግ ፡ አይሰማም ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ጌታው ፡ አቶ ፡ አንበሳ ፡ እጅግ ፡ አድርጎ ፡ ተናዶ ፡ ልግደለው ፡ አላት ። አይ ፡ አይሆንም ፡ ደግሞ ፡ በነፍሰ ፡ ገዳይነት ፡ ትያዙ ፡ እንግዲያው ፡ ልሰረው ፡ አለና ፡ መጠግጥን ፡ ወስዶ ፡ ከግንድ ፡ ጋራ ፡ ከቀፈደደ ፡ በኋላ ፡ ውሻን ፡ ጠብቅ ፡ ብሎ ፡ አዘ ፡ እንኩዬ ፡ ጦጢትን ፡ አስከትሎ ፡ ሄደ ። አቶ ፡ ውሻም ፡ እንቅልፍ ፡ ሳያምረው ፡ ጠንክሮ ፡ በጥብቅ ፡ ሲጠብቅ ፡ ሰንብቶ ፡ ሰለ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ለሽንቱ ፡ ወጣ ፡ ሲል ፡ አየችና ፡ ጦጢት ፡ ሆዬ ፡ መጠግጥን ፡ ፈታ ፡ አምልጥ ፡ ነፍስህን ፡ አድን ፡ አለችው ። ዘበኛውም ፡ ከውጭ ፡

ሲመለስ ፡ መጠግጥን ፡ ሲሮጥ ፡ አየው ፤ ወዲያው ፡ ተከታትሎ ፡ ሲያባርር ፡ ሲያበር ፡ በመጨረሻው ፡ መጠግጥ ፡ ከዥቦ ፡ ጉድንድ ፡ ጥልቅ ፡ አለበት ። እሱም ፡ በጣም ፡ አዝኖ ፡ ተበሳጭቶ ፡ ነበርና ፡ አለቀውም ፡ ብሎ ፡ ተከ



መጠግጥን ፡ ወስዶ ፡ ከግንድ ፡ ጋራ ፡ ከቀፈደደ ፡ በኋላ ፡ ውሻውን ፡ ጠብቅ ፡ ብሎ ፡ አዘ ፡ እንኩዬ ፡ ጦጢትን ፡ አስከትሎ ፡ ሄደ ።

ታትሎት ፡ ገባ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አያ ፡ ዥቦ ፡ ከየት ፡ መጣችሁ ፡ አላቸው ። የራበውን ፡ ታበላለህ ፡ ቢሉን ፡ አሉት ። እንግዲያውስ ፡ አሁን ፡ የተራብኩት ፡ እኔ ፡ ነኝና ፡ በልቼ ፡ አበላችኋለሁ ፡ ብሎ ፡ ሁለቱንም ፡ ቅርጥፍ ፡ አደረጋቸው ።



አያ ፡ ዥቦ ፡ ከየት ፡ መጣችሁ ፡ አላቸው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እንኩዬ ፡ ጦጢት ፡ አያ ፡ ዥቦን ፡ ዘመቻ ፡ መሄዳችን ፡ ነውና ፡ ከራቱ ፡ አሀዮች ፡ ሁለቱን ፡ አርደህ ፡ በሁለቱ ፡ ጭነህ ፡ አንተ ፡ ቀደም ፡ ብለህ ፡ መንገድ ፡ ገምር ፡ አለችው ። እሱም ፡ የበለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ አዘ

ሸን ፡ ቃል ፡ በመቀበል ፡ እህዮቹን ፡ አርዶ ፡ ጭኖ ፡ መንገዱ ፡ በየት ፡ ነው ፡ አላት ። በዚያ ፡ በደኑ ፡ በጫካው ፡ አጠገብ ፡ ነው ፡ ምናልባት ፡ ያልደረስ ንብህ ፡ እነደ ፡ ሆነ ፡ ሲመሽብህ ፡ እንዳትፈራ ፡ ከዘመዶችህ ፡ አጠገብ ቀረብ ፡ ብለህ ፡ እደር ፡ አለችው ። አያ ፡ ኹቦም ፡ እንደ ፡ ታዘዘው ፡ ይዘ ፡ ሲጓዝ ፡ ሲጓዝ ፡ ውሎ ፡ እደኑ ፡ አጠገብ ፡ ሲደርስ ፡ መሸበት ፡ ዘመዶቹ ንም ፡ ከዘያው ፡ አገኘና ፡ አጠገባቸው ፡ ሰፈረ ።

ጌታህ ፡ ወዴት ፡ ይሄዳል ፡ አሉት ፤ ዘመቻ ፡ ነዋ ፡ አላቸው ።



ጌታህ ፡ ወዴት ፡ ይሄዳል ፡ አሉት ።

ታዲያ ፡ እኛ ፡ አንዘምትበትም ፤ ደግሞ ፡ ላንድ ፡ ጥፍራም ፡ ነው ፡ ተው ፡ ዝም ፡ በለው ፡ ተባብለው ፡ የታረዱትን ፡ አህዮች ፡ በሏቸው ፡ ደኅነ ኞቹን ፡ ደግሞ ፡ አሳድረው ፡ በማግስቱ ፡ ለመብላት ፡ ተሰብስበው ፡ ሲያሽ ከኩ ፡ እንኩዬ ፡ ጦጢት ፡ ላቶ ፡ አንበሳ ፡ ጌታዬ ፡ አያ ፡ ኹቦ ፡ ያደረገ ውን ፡ ነገር ፡ ብነግርዎት ፡ በንዴት ፡ ይሞታሉ ፡ አለችው ።

—ምን ፡ አደረገ ፡ አባክሽ ፤

—አዬ ፡ ጌታዬ ፡ አህዮቹን ፡ ሰብስቦ ፡ ወደ ፡ ደን ፡ ገብቶ ፡ እስቲ ፡ ማን ፡ አባቱ ፡ ይነካኛል ፡ እያለ ፡ ይፎክራል ፡ ሲሉ ፡ ሰማሁ ።

—በታውን ፡ ታውቂዋለሽ ፤

—አይጠፋኝም ።

እንግዲውስ ፡ በዩ ፡ ተነሽ ፡ አሳዩኝ ፡ አላትና ፡ እፊት ፡ ቀድማ ፡ እደኑ ፡ አጠገብ ፡ ሲደርሱ ፡ በሩቅ ፡ እነአያ ፡ ኹቦ ፡ አህዮቹን ፡ ዘነጣጥለው ፡ ገና ፡

አፍላ ፡ መብል ፡ ይዘው ፡ አዩ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አንደኛው ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ ለጓደኞቹ ፡ እረ ፡ ይህ ፡ የሚያምር ፡ ጕበዝ ፡ ከወዴት ፡ ይመጣል ፡ አላ ቸው ። ያም ፡ ያህዮቹ ፡ እረኛ ፡ የነበረው ፡ ኹቦ ፡ በየው ፡ ጊዜ ፡ ደን ግጦ ፡ እረ ፡ እሱማ ፡ ባለጋራችን ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ስላረጋገጠ ፡ ተዘጋጅተው ፡ ለጠብ ፡ ተደግሰው ፡ ቄዩት ። አንኩዬ ፡ ጦጢትም ፡ ጌታዬ ፡ እንግዲህ ፡ ሞትዎም ፡ ሽረትዎም ፡ ዛሬ ፡ ነውና ፡ ይበርቱ ፡ አለችውና ፡ ቶሎ ፡ ብላ ፡ ከዛፉ ፡ ላይ ፡ ፈጥ ፡ አለች ። አንበሳም ፡ ዠግንነትና ፡ ድፍረት ፡ ገንዘቡ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ተንደርድሮ ፡ ከመካከላቸው ፡ ጥልቅ ፡ አለ ፤ ወዲያውም ፡ አን ዱን ፡ ይዘ ፡ ሲተናነቀውና ፡ ሲታገለው ፡ ከቀሩት ፡ አንደኛው ፡ ተሹለክ ልኮ ፡ ሆድ ፡ ዕቃውን ፡ ዘነጠለው ፤ የቀሩትም ፡ እግሩን ፡ ዘርጥጠው ፡ አጋደሙት ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ዘረጋግፈው ፡ በልተው ፡ ፈርሱ ፡ ብቻ ፡ ሲቀራቸው ፡ እዩታ ፡ እንኩዬ ፡ ጦጢት ፡ ተመልሳ ፡ እቤቷ ፡ ገባች ።



አንበሳው ፡ ዠግንነትና ፡ ድፍረት ፡ ገንዘቡ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ተንደርድሮ ፡ ከመካከላቸው ፡ ጥልቅ ፡ አለ ።

ለቀሩት ፡ ላያ ፡ ነብሮና ፡ ለቀበሮ ፡ ጌታዬን ፡ ካያ ፡ ኹቦ ፡ ጋራ ፡ ሸ ኻቹ ፡ መጣሁ ፡ አለቻቸው ። እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ ይመጣሉ ። ኧንድ ፡ ወር ፡ በኋላ ። አያ ፡ ነብሮ ፡ ቤቱንስ ፡ ማን ፡ ይጠብቅ ፡ ብለው ፡ አዘዙ ። እንቱንና ፡ እኔን ፡ እንግዲህ ፡ አደራ ፡ ብለዋልና ፡ ስንፍ ፡ ሳናስገባ ፡ መጠበቅ ፡ አለብን ፡ አለችው ። የምር ፡ መስሎት ፡ እሺው ፡

እንዳለችው ፡ ዘብ ፡ ገብቶ ፡ ተጠንቅቆ ፡ ሲጠብቅ ፡ ቂየ ፤ ከዕለታት ፡ አንድ፡ ቀን ፡ ጠጢት ፡ አያ ፡ ነብሮ ፡ እረ ፡ ይህች ፡ እንኰዬ ፡ ቀበሮ ፡ ጉድ ፡ ታደርገናለች ፡ አለችው ። እንዴት ፡ ቢላት ፤ እሷ ፡ ከመጣች ፡ ዝምሮ ፡ ከነ ዚህ ፡ በጎች ፡ አንድም ፡ ቀን ፡ አልታረደላቸው ፤ የሚወለዱትንም ፡ እየ ቀረጠፈች ፡ ብትበላ ፡ ነው ፡ አንጂ ፡ እንዴት ፡ እስካሁን ፡ ግልገል ፡ ይታ ጣ ፡ ነበር ፤ አሁን ፡ ደግሞ ፡ በመጨረሻው ፡ እናቲቶቹን ፡ ትበላቸውና ፡ ላደራ ፡ ሰንበቃ ፡ እንዳንቀር ፡ እሠጋሊኝ ፡ ብላ ፡ መለሰችለት ።

—ታዲያ ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ ይሻለናል ፤ ያበረርናትም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጌታችን ፡ ሲመለስ ፡ ታሰጣናለች ።

ዝም ፡ ብለን ፡ እናን ፡ አድርገን ፡ ገድለን ፡ ገደል ፡ መልቀቅ ፡ ነው ፡ የሚሻለው ።

እሱም ፡ በዚሁ ፡ ተስማማ ።

ማታ ፡ ቀበሮ ፡ በጎቿን ፡ ይዛ ፡ ከዋለችበት ፡ ዱር ፡ ስትገባ ፡ ጠጢት ፡ እንኰዬ ፡ ቀበሮ ፡ ነገ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ እቤት ፡ ነው ፡ የምትውዪው ፡ አለ ቻት ።

—በጎቹንስ ፡ ማን ፡ ይጠብቃቸዋል ፤

—አያ ፡ ነብሮ ።



አያ ፡ ነብሮ ፡ እረ ፡ ይህቺ ፡ እንኰዬ ፡ ቀበሮ ፡ ጉድ ፡ ታደ ርገናለች ፡ አለችው ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ቀበሮ ፡ እሺ ፡ ብላ ፡ እጅ ፡ ነሣች ። አያ ፡ ነብሮና ፡ ጠጢትም ፡ በማግስቱ ፡ ጧት ፡ ተነሡና ፡ አተኛችበት ፡ እፍን ፡ አድር ገው ፡ ገደሏት ።

—እንግዲህ ፡ ሰው ፡ ሳያየን ፡ ወስደን ፡ ገደል ፡ እንጣላት ፡ አለችው ።

—እንዴት ፡ አድርገን ፤

—በገመድ ፡ አስረን ፡ አንተ ፡ እፊት ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ እኋላ ፡ ሆኜ ፡ እየጐተትን ፡ ነዋ ።

—በዪ ፡ ቶሎ ፡ ደኅና ፡ ገመድ ፡ አምጪ ።

ወዲያው ፡ ጠንካራውን ፡ ቀላድ ፡ ይዛ ፡ መጥታ ፡ ጥፍር ፡ አድርጋ ፡ አሰረ ቻት ። አያ ፡ ነብሮም ፡ አንቺ ፡ እጅ ፡ አለሽ ፤ እኔ ፡ በምኔ ፡ እስባታለሁ ፡ አላት ። ነብሮም ፡ ደግ ፡ መልካም ፡ ባንገቴ ፡ አግቢልኝ ፡ አላትና ፡ አጥልቃለት ፡ ሲጐ ትት ፡ እገደሉ ፡ አጠገብ ፡ ደረሱ ። እንኰዬ ፡ ጠጢትም ፡ ቂይ ፡ እንግዲህ ፡ እንዳትመለስ ፡ እናድርጋት ፡ ብላ ፡ ትልቅ ፡ ድንጋይ ፡ ከዠርበዋ ፡ ላይ ፡ ደርባ ፡ ቅፍድድ ፡ አድርጋ ፡ አሰረችና ፡ በል ፡ ይህን ፡ ጊዜ ፡ ሳብ ፡ አድርጋት ፡ አለችው ። እሱም ፡ በብዙ ፡ ድካም ፡ ሳበና ፡ እገደሉ ፡ አፋፍ ፡ ሲደርስ ፡ በርታ ፡ እንጂ ፡ አምጥተን ፡ አምጥተን ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ እንቸገር ፡ ብላ ፡ ቀደም ፡ አለችና ፡ እንዲህ ፡ አትመነችገውም ፡ አለችው ። እንዳለችው ፡ አደርጋለሁ ፡ ብሎ ፡ ምንችግ ፡ ሲያደር ፡ የድንጋዩና ፡ የቀበሮዋ ፡ ሬሳ ፡ ክብ ደት ፡ ጐትቶት ፡ ተያይዘው ፡ ገደል ፡ እልም ፡ አሉና ፡ አለቁ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የጌታዋን ፡ ንብረት ፡ በሙሉ ፡ ይዛ ፡ ቀረች ፡ ይባላል ።



ድንጋይ ፡ በዠርባዋ ፡ ላይ ፡ ደርባ ፡ ቅፍድድ ፡ አድርጋ ፡ አሰረችና ፡ በል ፡ ይህን ፡ ጊዜ ፡ ሳብ ፡ አድርጋት ፡ አለችው ።

።። ይህንን ፡ ሁሉ ፡ ጐበዝ ፡ አንዲት ፡ ተንኰለኛ ፡ ጠጣ ፡ እንዲህ ፡ አድ ርጋ ፡ በብልኀት ፡ ፈጀቻቸው ። ከነተረቱ ፡ ጠጣ ፡ ባለቤቱን ፡ ታስወጣ ፡ ይባላል ።

ስለ ፡ አንዲት ፡ የጌታ ፡ ልጅ ፡ መፅነስ ።

አንድ ፡ ታላቅ ፡ መስፍን ፡ ሀገሩን ፡ እንደ ፡ ሠም ፡ አቅልጦ ፡ እንደ ፡ ገል ፡ ቀጥቅጦ ፡ ይገዛ ፡ ነበር ። እሱም ፡ ላቅመ ፡ ሔዋን ፡ የደረሰች ፡ አንዲት ፡ ልጅ ፡ ነዘረችው ። ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀንኝ አንድ ፡ ድኻ ፡ ሰው ፡ ሎሌነት ፡ ለመግባት ፡ ደብዳቤ ፡ ጽፎ ፡ ከመንገድ ፡ ላይ ፡ ሲጠባበቅ ፡ መስፍኑ ፡ በበቅሎ ፡ ተቀምጦ ፡ ባጀብ ፡ ሆኖ ፡ በግርማ ፡ መጣ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ባለጉዳዩ ፡ ወረቀቱን ፡ በንፊት ፡ አጣብቆ ፡ እያሳየ ፡ ይጮኽ ፡ ዠመር ። ጌትዮውም ፡ አጋፋሪውን ፡ ተቀበለው ፡ ብሎ ፡ ያንን ፡ ደብዳቤ ፡ አስመጥቶ ፡ ፬መለከተው ፡ ፍሬ ፡ ነገሩ ፡ ያሽከርነት ፡ ሥራ ፡ ይሰጠኝና ፡ እያገለገልኩ ፡ ልብላ ፡ የሚል ፡ ሆነ ። የሥራ ፡ ችሎታውን ፡ ዚጠይቀው ፡ ያሽከርነት ፡ ሥራ ፡ በሙሉ ፡ ፀውቃለሁ ፡ አለ ። ታላቁም ፡ ገዢ ፡ ለድኻ ፡ አዛኝና ፡ ተቈርቋሪ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ በልፍኝ ፡ አሽከርነት ፡ እንዲሠራ ፡ ለምድረ ፡ ግቢው ፡ አዛዥ ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጠ ። በለሥልጣኑም ፡ ቶሎ ፡ ብሎ ፡ የሚሠራውን ፡ ሥራ ፡ ለይቶ ፡ አስታወቀው ።



ጌትዮውም ፡ አጋፋሪውን ፡ ተቀበለው ፡ ብሎ ፡.....

ከዕለታት ፡ እንድ ፡ ቀን ፡ በቅልጥፍናውና ፡ በሥራ ፡ ማወቁ ፡ ተደስቶ ፡ ጌትዮው ፡ አንተ ፡ ልጅ ፡ ስምህ ፡ ማነው ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ። ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ ስሜ ፡ "የኔ ፡ ነው" ፡ ሲል ፡ መለሰለት ። በማግስቱ ፡ ደግሞ ፡ ባለቤቲቷ ፡ አንተ ፡ ልጅ ፡ ስምህን ፡ ሳላውቀው ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ እንዲያው ፡ አንተ ።

ልጅ ፡ እያልኩ ፡ ነው ፡ የምጠራህ ፡ እስቲ ፡ ማን ፡ ትባላለህ ፡ ንገረኝ ፡ አሉት ፡ እመቤቴ ፡ ሆይ ፡ ስሜ ፡ "የሳቸው ፡ ነው" ፡ ብሎ ፡ በታላቅ ፡ ማክበር ፡ መለሰላቸው ። ሦስተኛ ፡ ልጃቸው ፡ ልጃገረዲቷ ፡ እንደ ፡ እናቷና ፡ እንደ ፡ አባቷ ፡ ያንን ፡ ሰው ፡ ስምህ ፡ ማነው ፡ በስምህ ፡ እንድጠራህ ፡ ብትለው ፡ "አባባ" ፡ እባላለሁ ፡ አላት ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ያ ፡ ላይን ፡ የሚያስጠይፍ ፡ ድኻ ፡ መልካም ፡ ሲበላና ፡ ደጎና ፡ ደጎና ፡ ልብስ ፡ ሲለብስ ፡ ጊዜ ፡ ሰውነቱ ፡ በጣም ፡ አማረ ፡ እንዲያውም ፡ ከነሱው ፡ ከጌቶቹ ፡ የተወለደ ፡ መሰለ ። ስለዚህም ፡ ያች ፡ ወይዘሪት ፡ ለዚያ ፡ ሰውዬ ፡ ምስጢሯን ፡ ሁሉ ፡ እየገለጠች ፡ ታጫው ፡ ተው ፡ ገ፫መር ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ከመፅነስ ፡ ደረሰች ። አባቷና ፡ እናቷ ፡ ነፍሰ ፡ ጡር ፡ መሆኗን ፡ በተረዱ ፡ ጊዜ ፡ ገልጠሽ ፡ ንገሪን ፡ ከማን ፡ ነው ፡ ያረገዝሽው ፡ ብለው ፡ ጠየቋት ። እሷም ፡ የደፈረኝ ፡ ይህ ፡ ሎሌ ፡ ነው ፡ ያረገዝኩትም ፡ ከሰው ፡ ነው ፡ እኔ ፡ መቼስ ፡ ምን ፡ ላድርግ ፡ እና ንተው ፡ በገዛ ፡ እጃችሁ ፡ ከልፍኝ ፡ አስገብታችሁ ፡ አሠለጠናችሁት ፡ አለቻቸው ። እውነቷ ፡ ነው ፡ ያደር.ጋል ፡ ጥፋተኞቹ ፡ እኛው ፡ ነን ፡ ያለ ፡ ልክ ፡ አቀረብነው ፡ ብለው ፡ ተናደውና ፡ ተቈጥተው ፡ ያንን ፡ አሽከር ፡ እጅ ፡ እግሩን ፡ አሳስረው ፡ ለቅጣቱ ፡ ውሳኔ ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሰደዱት ። ከዳኞቹም ፡ ፊት ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ግፉና ፡ በደሉ ፡ ሁሉ ፡ በነገረ ፡ ፈጅ ፡ አማካይነት ፡ በዝርዝር ፡ እንዲገለጽ ፡ ተደረገ ።



ያንን ፡ አሽከር ፡ እጅ ፡ እግሩን ፡ አሳስረው ፡ ለቅጣቱ ፡ ውሳኔ ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወሰዱት ።

ዳኞቹም ፣ ግራና ፣ ቀኙን ፣ ከዳመጡ ፣ በኋላ ፣ አንተ ፣ ሰው ፣ ይህ ንን ፣ ነገር ፣ ሠርተኸዋል ፣ ታምናለህ ፣ ወይስ ፣ ትክዳለህ ፣ ብለው ፣ ቢጠ ይቁት ፣ እኔ ፣ ድኻው ፣ በግፍ ፣ ከመታሰሬ ፣ በተቀር ፣ እንደዚህ ፣ ያለ ውን ፣ ድፍረት ፣ በጭራሽ ፣ አላደረግሁም ፣ ብሎ ፣ መለሰላቸው ።

ከዚህ ፣ በኋላ ፣ እነዚህ ፣ ዳኞች ፣ ነገሩ ፣ ለፍርድ ፣ ስላስቸገራቸው ፣ የቀን ፣ ቀጠሮ ፣ አደረጉ ። ሰውዮው ፣ ግን ፣ በእስር ፣ ቤት ፣ እንዲቈይ ፣ ታዘዘ ። በነገሩ ፣ እጅግ ፣ ስላዘኑ ፣ ጕዳዩ ፣ ዐቶሎ ፣ ውሳኔ ፣ ያገኝ ፣ ዘንድ ፣ በማሰብ ፣ ራሳቸው ፣ መስፍኑና ፣ ባለቤቲቲ ፣ በዚያው ፣ በተቀጠረበት ፣ ቀን ፣ ልጃቸውን ፣ ይዘው ፣ ከፍርድ ፣ ቤት ፣ ቀረቡ ። ዳኞቹ ፣ ወይዘሪቲን ፣ ወደ ፣ ምርመራ ፣ ከፍል ፣ ለብቻዋ ፣ ወስደው ፣ ከማነው ፣ ያረገዝሽው ፣ ብለው ፣ ቢጠይቋት ፣ "ከአባባ" ፣ ነው ፣ ብላ ፣ መለሰችላቸው ። ደግሞ ፣ መስፍኑን ፣ ይህች ፣ ልጅ ፣ ከማን ፣ ያረገዘች ፣ ይመስልዎታል ፤ ከማንስ ፣ ይጠራጠሯ ታል ፣ በማለት ፣ ቢጠይቋቸው ፣ "ከኔ ፣ ነው" ፣ ደግሞ ፣ ከሌላ ፣ ከማን ፣ አረ ገዘች ፣ ተብሎ ፣ ይታሰባል ፣ ሲል ፣ መልስ ፣ ሰጣቸው ። ደግሞ ፣ ሦስተኛ ፣ ባለቤቲቱን ፣ መቼም ፣ ምንም ፣ ቢሆን ፣ ልቦናዎ ፣ ሳያውቅ ፣ አይቀርምና ፣ ይህች ፣ ልጅዎ ፣ ከማን ፣ ያረገዘች ፣ ይመስልዎታል ፤ ይህ ፣ ነገር ፣ ስላስቸገ ረን ፣ የሚጠረጥሩትን ፣ ሰው ፣ ይንገሩን ፣ እሷቸው ። ከሌላ ፣ ከማንም ፣ ሰው ፣ አላረገዘች ፣ "ከሳቸው ፣ ነው" ፣ ብለው ፣ አረጋገጡላቸው ።

ከዚህ ፣ በኋላ ፣ ዳኞቹ ፣ ፈታቸውን ፣ ወደ ፣ እናትና ፣ አባቷ ፣ መል ሰው ፣ ታዲያ ፣ ይህ ፣ ድኻ ፣ ምን ፣ ያድርገን ፣ ብላችሁ ፣ ነው ፣ እናንተው ፣ እያወቃችሁ ፣ በመናችሁት ፣ ጥፋት ፣ ያሰራችሁት ፣ እውነትም ፣ በሥል ጣናችሁ ፣ ተመክታችሁ ፣ ነው ፣ በሉ ፣ አሁንም ፣ ያላገባብ ፣ በግፍ ፣ ስላ ሰራችሁት ፣ ሙሉ ፣ ካሳ ፣ እንዲሰጠው ፣ ወስነናል ። እርስዎም ፣ ጌታዬ ፣ ሕግ ፣ የማይፈቅደውን ፣ መጽሐፍ ፣ የማያዘውን ፣ ተግባር ፣ ሠርተው ፣ ስለ ፣ ተገኙ ፣ እስራት ፣ ይገባዎታልና ፣ ወደ ፣ ወህኒ ፣ እንዲሄዱ ፣ ፈር ደናል ፣ ብለው ፣ ድኻውን ፣ በገንዘብ ፣ አስክሰው ፣ ለቀቁት ፣ ይባላል ።

፨ ካያያዝ ፣ ይቀደዳል ፤ ካነጋገር ፣ ይፈረዳል ፣ እየተባለ ፣ የሚተረተ ውም ፣ እንደዚህ ፣ ያለ ፣ ነገር ፣ ባጋጠመ ፣ ጊዜ ፣ መሆኑን ፣ ተገንዝበ ፣ መጠንቀቅ ፣ ይገባል ።

ስለ ፡ አንድ ፡ ታማኝ ፡ አሽከር ።

ባንድ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ጌታው ፡ እጅግ ፡ አድርጎ ፡ የሚያምነው ፡ እ ሱም ፡ ጌታውን ፡ የሚወድ ፡ የሚያከብርና ፡ የሚፈራ ፡ አሽከር ፡ ነበር ። በሚያደርገውና ፡ በሚሠራውም ፡ ሁሉ ፡ የተጠነቀቀ ፡ ፈሪሀ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ ያደረበት ፡ በመሆኑ ፡ ጌታው ፡ ወደ ፡ ዘመቻ ፡ ሲሄድ ፡ አንተ ፡ እ ኔን ፡ በማገልገል ፡ የደከምህ ፡ ፈቃዴን ፡ የምትፈጽም ፡ ታማኝ ፡ አሽ ከሬ ፡ እኔ ፡ ከመርከት ፡ እስክመለስ ፡ ድረስ ፡ ቤቴ ፡ እንዳይቀዘቅዝ ፡ ግቢዬ ፡ እንዲከበር ፡ ሚስቴ ፡ እንድትታፈር ፡ በጥብቅ ፡ አደራ ፡ እልሃለሁ ። ይህ ንን ፡ የመሰለ ፡ እደራ ፡ የሚሰጠው ፡ እጅግ ፡ ለተወደደና ፡ ለታመነ ፡ አሽ ከር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለማንም ፡ ሰው ፡ አይደለምና ፡ አስብበት ፡ አለና ፡ አ ስገነዘበው ።

ይህም ፡ አሽከር ፡ አደራው ፡ እጅግ ፡ ስለ ፡ ከበደውና ፡ ከዚህም ፡ በላይ ፡ አሳዳሪውን ፡ እንደ ፡ ራሱ ፡ አድርጎ ፡ ይወደው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፤ ጌ ታዬ ፡ እርስዎ ፡ ወደ ፡ ሞት ፡ አገር ፡ ሲሄዱ ፡ እኔ ፡ መቅረት ፡ አይገባኝም ፡ ሲሆን ፡ እንደ ፡ ጋሻ ፡ ከፊትዎ ፡ ተመክቼ ፡ ጦር ፡ ቀማሽ ፡ መሆን ፡ አለ ብኝ ፤ ሴት ፡ ይመስል ፡ ከቤት ፡ መዋል ፡ ግን ፡ አይገባኝም ፡ ብሎ ፡ መ ልስ ፡ ሰጠው ። ጌትዮው ፡ ግን ፡ ያለሱ ፡ ላደራ ፡ የሚበቃ ፡ ሰው ፡ በቤቱ ፡ ስላልነበረው ፡ ንብረቱን ፡ እንዲጠብቅለት ፡ በልመና ፡ ጭምር ፡ አስገድ ደ ፡ ወዲያውም ፡ አስምሎ ፡ ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ ሁናቴ ፡ ሲሠራ ፡ እንዲቈ የው ፡ አዘዘ ። ቃሉም ፡ እንደኛ ፡ እልፍኙ ፡ ካለበት ፡ ቅጥር ፡ ግቢ ፡ ማን ም ፡ ሰው ፡ እንዳይገባ ፤ ዝለተኛ ፡ እንተም ፡ ላንድ ፡ አፍታ ፡ እንኳን ፡ ቢሆን ፡ ከበር ፡ ሳትለይ ፡ ሌት ፡ ከቀን ፡ እንድትጠብቅ ፤ ሦስተኛ ፡ ባለቤ ቴ ፡ በለቅሶም ፡ ሆነ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ምክንያት ፡ ከግቢዬ ፡ እንዳ ትወጣ ፤ አራተኛ ፡ ሚስቴ ፡ ካለችበት ፡ ቦታ ፡ "ሰው ፡ ማመኔ" ፡ ከምት ባለዋ ፡ ገረዴ ፡ በስተቀር ፡ ሌላ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ እንዳይገባ ፡ ጠንክረህ ፡ ከልክል ፡ የሚል ፡ ነው ።

ለሚስቱም ፡ ይህንኑ ፡ አስረድቶ ፡ ነግሮ ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ዘመቻ ው ፡ ሄደ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ታማኙ ፡ ሎሌ ፡ ከተቀበለው ፡ ትእዛዝ ፡ አን ዳች ፡ ነገር ፡ ሳያዛንፍና ፡ ሳያቃውስ ፡ እንደ ፡ ተባለው ፡ ሁሉ ፡ በትክ ክል ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ሲጠብቅ ፡ ቈየ ። ነገር ፡ ግን ፡ የደኅና ፡ ሰው ፡ ተቃ ዋሚ ፡ ብዙ ፡ ነውና ፡ እንድ ፡ ቀን ፡ እመቤቲቱ ፡ ሲሆን ፡ ከውጪ ፡ የሚ ያነጋግረኝ ፡ ሰው ፡ አስገባልኝ ፡ ካልሆነም ፡ አንተ ፡ እየገባህ ፡ አጫውተኝ ፡



አደራ ፡ የሚሰጠው ፡ እጅግ፡ ለተወደደና ፡ ለታመነ ፡ አሽከር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለማንም፡ ሰው ፡ አይደለምና ፡ አስብበት ።

ብላ ፡ በልመናም ፡ በማስፈራራትም ፡ ታስጨንቀው ፡ ገርመረች ። እሱ ፡ ግን ፡ እኔ ፡ ሰማይ ፡ ዝቅ ፡ መሬት ፡ ከፍ ፡ ቢል ፡ እንኳን ፡ ሌላው ፡ ይቅር ፡ ና ፡ ጌታዬ ፡ በሚያርፍበት ፡ አጐዛ ፡ ላይ ፡ ላልቀመጥ ፡ ቃል ፡ ለምድር ፡ ለሰማይ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ቀሩ ፡ ጠንካራ ፡ ሐሳቡን ፡ ገለጸላት ። ሴቲቱም ፡ በነገሩ ፡ ተበሳጭታና ፡ ተቈጭታ ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ ከቈየች ፡ በኋላ ፡ ቂይ ፡ ግድ ፡ የለም ፡ ጌታህ ፡ ሲመጣ ፡ በቁምህ ፡ ዐፈር ፡ እንዲመለስብህ ፡ ላላ ደርግ ፡ ብቀር ፡ ታዘብ ፡ ብላ ፡ አሁንም ፡ የማስፈራራት ፡ ንግግሯን ፡ ብታ ሰማው ፡ እንኳን ፡ ዐፈር ፡ አሳት ፡ ቢነድብኝ ፡ ሐሳቤ ፡ አይለወጥም ፡ ሲል ፡ ቀሩጠኛ ፡ ቃሉን ፡ ሰጣት ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሴቲቱ ፡ ያንን ፡ አሽከር ፡ የምታጠምድበትንና ፡ የምታጠፋበትን ፡ ምክንያት ፡ በማሰብ ፡ ባለ ቤቷ ፡ በሚገባበት ፡ ቀን ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ፈቃዷን ፡ እንዲፈጽም ፡ ለመ ቀበያ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ድግስ ፡ እንዲሰናዳ ፡ አዘዘች ። የወጣ ፡ ሰው ፡ መመ ለሱ ፡ ስለማይቀር ፡ ዘማቹም ፡ በተጠበቀበት ፡ ቀን ፡ በልልታና ፡ በደስታ ፡ ከቤቱ ፡ ገባ ። ወደ ፡ አዳራሽ ፡ ከመውረዱ ፡ በፊት ፡ ድንን ፡ ለመፍ ታትና ፡ ጥቂት ፡ ለማረፍ ፡ እልፍኙ ፡ ገብቶ ፡ ነበርና ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሚስቲቱ ፡ ይህንን ፡ ያልታመነ ፡ ባለጌ ፡ አሽከር ፡ አሠልጥነህ ፡ በቤትህ ፡ ትተህ ፡ ሄደህ ፡ ሲያጕላላኝና ፡ ሲያንገላታኝ ፡ ከረመ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ያንተ፡ ያንበሳው ፡ የጀግናው ፡ ሚስት ፡ ሆኜ ፡ እንደዚህ ፡ ተደፍሬ ፡ ልቅር ፡ ብላ ፡

ራሷን ፡ እያወራጨች ፡ እንባዋን ፡ እንደ ፡ ተበደሰና ፡ እንደ ፡ ተጠቃ ፡ ሁሉ ፡ አግሩ ፡ ላይ ፡ ተደፍታ ፡ በሐዘን ፡ ስሜት ፡ ትንገረው ፡ ገርመር ። የሰው፡ አእምሮና ፡ ዕውቀት ፡ የጠበበና ፡ የተወሰነ ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ የነገረ ችውን ፡ ሁሉ ፡ እውነት ፡ መስሎት ፡ ስለ ፡ ተቀበለ ፡ በነገሩ ፡ አጥብቆ ፡ ተ ናደደ ። ስለዚህም ፡ አዳራሽ ፡ ወርዶ ፡ ግብር ፡ ሲያበላ ፡ ታማኙ ፡ አሽ ከር ፡ እንደ ፡ ወትሮው ፡ ጠጋ ፡ ጠጋ ፡ ቢለው ፡ ፊት ፡ ነሥቶት ፡ ምንም ፡ ላያነ ጋግረው ፡ ቀረ ፤ እንዲያውም ፡ በፊቱ ፡ ቆሞ ፡ ባየው ፡ ጊዜ ፡ ሰውነቱ ፡ ተለ ወጠ ፤ ቀይ ፡ የነበረው ፡ ጠቈረ ።

ወዲያው ፡ ከጭፍሮቹ ፡ የታመኑ ፡ የታመኑትን ፡ ጠራና ፡ ሂዱ ፡ ከአ ትክልቱ ፡ ውስጥ ፡ ላንድ ፡ ሰው ፡ መቅበሪያ ፡ የሚሆን ፡ ጕድጓድ ፡ ቈፍሩ፤ ስትጨርሱም ፡ ንገሩኝ ፤ በኋላም ፡ እኔ ፡ የምልከውን ፡ ሰው ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የምወደው ፡ ወይም ፡ ባለሟሌ ፡ ቢሆን ፡ እንዳትምሩት ፤ አንገቱን፡ በሰይፍ ፡ ቀልታችሁ ፡ ቅበሩት ፡ ብሎ ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጠ ።

አሽከሮቹም ፡ እንደ ፡ ነገራቸው ፡ አዘጋጁና ፡ አሰናድተናል ፡ ሲሉ ፡ ላኩበት ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ያንን ፡ ታማኝ ፡ አሽከር ፡ ሂድና ፡ ከዚያ ፡ ከአት ክልቱ ፡ ውስጥ ፡ የሚሠራውን ፡ ሥራ ፡ አይተህ ፡ ና ፡ ብሎ ፡ ላከው ። እሱም ፡ ፍጹም ፡ ታዛዥ ፡ ፈቃድ ፡ ፈጻሚ ፡ ነበርና ፡ እሺ ፡ በማለት ፡ እጅ ፡ ነሥቶ ፡ ትእዛዙን ፡ ተቀበለ ።

ከቅጥር ፡ ግቢው ፡ እንደ ፡ ወጣ ፡ ቤት ፡ ተሠርቶላት ፡ በጡረታ ፡ የምትኖር ፡ አንዲት ፡ አሮጊት ፡ ስለ ፡ ጌታዋ ፡ በደኅና ፡ መመለስ ፡ ቅድ ስት ፡ ማርያምን ፡ ልታዘክር ፡ ጠበል ፡ ጠዲቅ ፡ አድርጋ ፡ ኖሮ ፡ ስለ ፡ ቅድስት ፡ ማርያም ፡ ጠበል ፡ ጠዲቋን ፡ ቀምሰህልኝ ፡ ሂድ ፡ ስትል ፡ አጥ ብቃ ፡ ለመነችው ። እሱም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፍቅር ፡ ያደረበት ፡ ደግ ፡ ሰው ፡ ነበረና ፡ ጥሪዋን ፡ አክብሮ ፡ ገባ ። ቄሱም ፡ ጸሎቱን ፡ አልጨረሱ፡ ኖሮ ፡ ከዳዊት ፡ መዝሙር ፡ ፶፩ ፡ አመንኩን ፡ ሥስት ፡ ጊዜ ፡ ድገም ፡ አት ቸኩል ፡ ደግሞ ፡ መዝሙር ፡ ፴፱ ፡ አድኅንኒ ፡ እግዚኦ ፡ እምብእሲ ፡ እኩ ይን ፡ ቀጥለህ ፡ አድርስ ፡ አሉት ።

በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ወደ ፡ ታዘዘበት ፡ በቶሎ ፡ ለመሄድ ፡ ተቸግሮ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ዘገየ ። አመቤቲቱ ፡ ግን ፡ ለሞት ፡ እንደ ፡ ተላከ ፡ ባሏ ፡ ነግሯት ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ገደሉትና ፡ እንደ ፡ ምንስ ፡ እንደ ፡ ቀበሩት ፡ ለማየት ፡ ቸኩላ ፡ ወደ ፡ አትክልቱ ፡ ውስጥ ፡ ሄደች ። እነዚያም ፡ የጌታቸውን ፡ ትእዛዝ ፡ ለመፈጸም ፡ ሰይፍ ፡ ሰይፋቸውን ፡ ታጥቀው ፡ የሚጠባበቁ ፡ አሽከሮች ፡ አመጣጧን ፡ አይተው ፡ ለካ ፡ እሷን ፡ ኖሯልና ፡ የሚልከው ፡ ብለው ፡ አንገቷን ፡ በስለት ፡ ቀንጥሰው ፡

ቀበሯት ። መታደሮቹም ፡ እንግዲህ ፡ እመቤታችንን ፡ ገድለን ፡ እቤት ፡ ገብተን ፡ እኽል ፡ የሚባል ፡ ልንቀምስ ፡ እንችልም ፡ እያሉ ፡ በየጥላው ፡ ሥር ፡ ሆነው ፡ ያዝኑ ፡ ዠመር ። በመከከል ፡ ያ ፡ ታማኝ ፡ ሎሌ ፡ መል ክቴን ፡ ሳልፈጽም ፡ ሰዓት ፡ አለፈብኝ ፡ ብሎ ፡ ሲሮጥ ፡ መጣና ፡ ቢመለ ከት ፡ የተቈፈረው ፡ ጕድጓድ ፡ ተመልሶ ፡ ተደፍኖ ፡ አየ ፤ ወዲያውም ፡ ይሽንኑ ፡ ለጌታው ፡ ለማስታወቅ ፡ እንዳመጣጡ ፡ ሮጠ ፡ ተመለሰ ።



ለካ ፡ እሷን ፡ ኖሯልና ፡ የሚ ልከው ፡ ብለው ፡ አንገቷን ፡ በበለት ፡ቀንጥበው ፡ቀበሯት ።

እቤትም ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ እንተ ፡ ከየት ፡ መጣህ ፡ ምንስ ፡ አየህና ፡ ተመለስክ ፡ ብሎ ፡ ጌታው ፡ ጠየቀው ። እሱም ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ የታዘዝ ኩትን ፡ ፈጽሜ ፡ ነው ፡ የተመለስኩት ፡ ያየሁትም ፡ የተቈፈረ ፡ ጕድጓድ ፡ መደፈኑን ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ አላገኘሁም ፡ ብሎ ፡ መለ ሰለት ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ቶሎ ፡ ብሎ ፡ አሽከሮቹን ፡ ከአትክልቱ ፡ ስፍራ ፡ አስፈልጎ ፡ የሆነውን ፡ ቢጠይቃቸው ፡ ጌታችን ፡ ሆይ ፡ በትእዛዝዎ ፡ መሠ ረት ፡ ቄፍረን ፡ ተዘጋጅተን ፡ ስንጠባበቅ ፡ እመቤታችን ፡ መጡ ፤ እኛም ፡ ግንም ፡ ወዳጇ ፡ በለሚሌ ፡ ቢሆን ፡ አትማሩ ፡ ብለው ፡ ስላዘዙን ፡ አንገታ ቸውን ፡ ቀንጥሰን ፡ ቀበርናቸው ፡ አሉት ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ጌትዮው ፡ እጅግ ፡ አድርጎ ፡ ደነገጠ ፡ አዘነም ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ የሴትዮዋን ፡ ትክክለኛ ፡ አሟሟት ፡ ማወቅ ፡ ታሪክ ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርምና ፡ በማለት ፡ አሽከሩ ፡ ተይዘ ፡ በጥብቅ ፡ እንዲጠበቅ ፡ አደረገ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የሚስቱን ፡ ሬሳ ፡ ከጕድጓድ ፡ አስወጥቶ ፡ በደንብ ፡ አስከፍኖ ፡ በሣጥን ፡ አስደርጎ ፡ ዘመድ ፡ ወዳጅ ፡ በተሰበሰበበት ፡ ሥር ዐተ ፡ ፍትሐት ፡ አስደርሶ ፡ አስቀበረ ።

የቀብሩ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ እንደ ፡ ተፈጸመም ፡ ያንን ፡ ከሞት ፤ ሥል ጣን ፡ እግዚአብሔር ፡ ያዳነውን ፡ አሽከር ፡ አስመጥቶ ፡እኔ ፡ ቤቴን ፡ ንብ ረቴን ፡ ላንተ ፡ አደራ ፡ ብዬ ፡ ወደ ፡ ዘመቻ ፡ በሄድኩበት ፡ ወራት ፡ ባለ ቤቴን ፡ ምን ፡ በድለሃት ፡ ኖሯል ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ።

እሱም ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ ቤትዎንና ፡ ንብረትዎን ፡ እንድጠብቅ ፤ ሚስ ትዎ ፡ እለቅሶም ፡ እንዳይሄዱ ፡ ከቤትም ፡ እንዳይወጡ ፡ እንድጠነቀቅ ፡ አደራ ፡ ከማለትም ፡ በላይ ፡ የጠበቀ ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጥተውኝ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ቃል ዎን ፡ አክብሬ ፡ ሰው ፡ ከልክዬ ፡ ተቀምጬ ፡ ሳለ ፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ፈቃዴን ፡ ፈጽመልኝ ፡ ብለው ፡ ጠየቁኝ ፤ ጌታዬ ፡ በለው ፡ ንብረታቸው ፡ ሲያሠለጥኑኝ ፡ በዚህ ፡ አላሠለጠኑኝምና ፡ ሰማይ ፡ ዝቅ ፡ ምድር ፡ ከፍ ፡ ቢል ፡ ይሽንን ፡ ሥራ ፡ አላደርገውም ፡ የማለት ፡ ቃል ፡ መለስኩላቸው ፤ እሳ ቸውም ፡ ቄይ ፡ ጌታህ ፡ ሲመጣ ፡ በቁምህ ፡ ዐፈር ፡ ሳላስለብስህ ፡ ብቀር ፡ እውነት ፡ እኔ ፡ ሞቻለሁ ፡ ብለው ፡ ዘቱብኝ ። እኔም ፡ ምንም ፡ ቢናገሩ ፡ ጌታ ዬ ፡ ያለጥፋቴ ፡ አይቀጡኝምና ፡ አልሰጋም ፡ ብያቸው ፡ መመለስዎን ፡ በና ፍቆት ፡ በመጠባበቅ ፡ ቄየሁ ፡ ብሎ ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ በዝርዝር ፡ አስረ ድቶ ፡ ነገረው ።

ስለዚህም ፡ ጌታው ፡ በክፉ ፡ ሥራዋ ፡ እንደ ፡ ሞተች ፡ ዐውቆ ፡ ነገሩን ፡ እንደ ፡ ጕድፍ ፡ ተመልክቶ ፡ ተወው ። አሽከሩን ፡ ግን ፡ ንጹሕ ፡ ልቡናው ንና ፡ ታማኝነቱን ፡ በበለጠ ፡ ለመረዳት ፡ ስለ ፡ ፫ለ ፡ ደጃፍ ፡ በመለሰው ፡ ማጀት ፡ በጕረሠው ፡ በማናቸውም ፡ ገንዘቡ ፡ ላይ ፡ ሾሞት ፡ እንደ ፡ ቀድ ሞው ፡ ተፋቅረው ፡ ተስማምተው ፡ አብረው ፡ ኖሩ ፡ ይበላል ።

፠ ደብ ፡ ራሱን ፡ ካረ ፡ ድጕሱን ፡ ማለት ፡ ይህ ፡ ነውና ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ፡ በንጹሕ ፡ ወንድማችሁ ፡ ክፉ ፡ አስበችሁ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፍርድ ፡ እን ዳትጠፉ ፡ ተጠንቀቁ ። ወንጌል ፡ ቅን ፡ ታማኝ ፡ እገልጋይ ፡ ሆይ ፤ በጥ ቂት ፡ ነገር ፡ የታመንህ ፡ ሆነሃልና ፡ በብዙዎች ፡ ላይ ፡ አልቄ ፡ እሾምሃ ለሁ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ አትዘንጉ ።

ሁለት ፡ አታላዮች ።

በንድ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ የሚያታልሉና ፡ የሚያከ
ስሩ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ። ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አንደኛው ፡ ማር፡
በዶጮ ፡ ሁለተኛው ፡ ደግሞ ፡ ቅቤ ፡ ባፍላል ፡ ይዘው ፡ ሁለቱም ፡ እገ
በያ ፡ ተገናኙ ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ በለማሩ፡ ባለቅቤውን ፡ ወንድም ፡



ባለማሩ ፡ ባለቅቤውን ፡ ወን
ድም ፡ምን ፡ይዘሃል ፡አለው።

ምን ፡ ይዘሃል ፡ አለው ። እሱም ፡ ቅቤ ፡ ነዋ ፡ ሲል ፡ መለሰለት ። በምን ፡
ይለወጣል ፡ ቢለው ፡ በማር ፡ አለው ። እንግዲያው ፡ እኔ ፡ ማር ፡ ይዣለ
ሁና ፡ እንላወጥ ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቀው ፡ እሺ ፡ እኔም ፡ የምፈልገው ፡ ይኸንኑ፡
ነበረ ፡ በማለት ፡ ተስማምተው ፡ እንደ ፡ ተመረገ ፡ ሳይከፍቱ ፡ ተለዋወጡ ።
የማሩ ፡ ጌታ ፡ ዶጮውን ፡ ከንገቱ ፡ በታች ፡ አተላ ፡ ከንገቱ ፡ በላይ ፡ ማር ፡
የቅቤውም ፡ ጌታ ፡ አፍላሉን ፡ ከንገቱ ፡ በላይ ፡ ቅቤ ፡ ከንገቱ ፡ በታች ፡
እበት ፡ አድርገው ፡ መርገው ፡ ኖሮ ፡ የማሩም ፡ ጌታ ፡ እኔ ፡ አታለልኩት ፡
የቅቤውም ፡ ጌታ ፡ እኔ ፡ አታለልኩት ፡ በማለት ፡ ሁለቱም ፡ ደስ ፡
ደስ ፡ እያላቸው ፡ ሌላውን ፡ ጉዳያቸውን ፡ ትተው ፡ እየተሸኸሙ ፡ ወደ

የሰፈራቸው ፡ ሄዱ ። እቤታቸውም ፡ በደረሱ ፡ ሰዓት ፡ እየከፈቱ ፡ ቢያ
ዩት ፡ የማሩ ፡ አተላ ፡ የቅቤውም ፡ እበት ፡ ሆነባቸው ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ባለ
ማሩ ፡ ባለቅቤውን ፡ ይህስ ፡ ከኔ ፡ የበለጠ ፡ ነውና ፡ አግኝቼው ፡ ጓደኛ ፡
በሆነኝ ፡ አለና ፡ ተመኘ ።

ዳግመኛ ፡ ባለማሩ ፡ ጌሾ ፡ የሚመስለውን ፡ ጠዶ ፡ የሚባለውን ፡
ቅጠል ፡ ቀርጥፎ ፡ አድርቆ ፡ በስልቻው ፡ አዘጋጅቶ ፡ ባናቱ ፡ ላይ ፡ የጌሾ ፡
ቅጠል ፡ አድርጎ ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ገበያ ፡ ወጣ ።

ሁለተኛውም ፡ አታላይ ፡ ሲናር ፡ በውስጥ ፡ ገብስ ፡ በላይ፡ አድርጎ ፡
በስልቻ ፡ ይዞ ፡ እገበያ ፡ ሄደ ። ሁለቱም ፡ ሳይተዋወቁ ፡ ተገናኙ ። የጠዶው፡
ጌታ ፡ ጌሾ ፡ በገብስ ፡ የሚለውጥ ፡ እያለ ፡ ሲዘር ፡ ባለሲናሩ ፡ ና ፡ ወዴኔ ፡
አለው ።

—ልውጫውሳ ፤

—መሳ ፡ ለመሳ ።

—ሽልቻውሳ ፤

—እኔም ፡ ያንተን ፡ አንተም ፡ የኔን ፡ አንሣ ፡ ተባባለው ፡ ሁለቱም ፡
ተለዋውጠው ፡ ይዘው ፡ ሄዱ ። እየቤታቸው ፡ ሲደርሱ ፡ ቢፈቱት ፡ የባለጌ
ሾው ፡ ጠዶ ፡ ቅጠል ፤ የባለገብሱም ፡ ሲናር ፡ ሆነባቸው ። ሁለቱም ፡ ዘየበ
ኩላቸው ፡ ሲናደዱ ፡ ሲጨሱ ፡ ውለው ፡ ቄይ ፡ ግድ ፡ የለም ፡ እሱ ፡ እንደ ፡
ተጫወትብኝ ፡ ሳልጫወትበት ፡ በማለት ፡ በየበኩላቸው ፡ ሲሮክሩ ፡ ሰነበቱ ።

ሦስተኛ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ አንደኛው ፡ ገንዘብ ፡ ሁለተኛው ፡ ዕውር ፡
አህያ ፡ ይዘው ፡ እገበያ ፡ ወጡ ። ያነን ፡ አህያ ፡ ባለወርቁ ፡ ይሸጣል ፡ ወደ ፡
ብሎ ፡ ባለቤቱን ፡ ጠየቀው ። እሱም ፡ አምን ፡ ቢለው ፡ ዋጋውን ፡ ንገረኝ ፡
አለው ።

—ኸያ ፡ ብር ።

—ርግጡሳ ፤

—ወርቅ ፡ ሲመጣ ። አህያው ፡ ታስሮ ፡ ነበረና ፡ ፍታውና ፡ እንየው ፡
ቢለው ፡ አይፈታም ፡ የተፈታ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አለቤቱ ፡ አይቆምም ፡ አለው ።

—እንግዲያው ፣ ምን ፣ ማድረግ ፣ ይሻላል ፣

ሁለት ፣ ሆናችሁ ፣ አንዳችሁ ፣ ከፊት ፣ አንዳችሁ ፣ ከኋላ ፣ በገመድ ፣ ከልሰባችሁት ፣ አምልጦ ፣ ይጠፋል ፣

—እሺ ፣ ዋጋውን ፣ በደንብ ፣ ንገረኝ ።

—መቼስ ፣ ምን ፣ ይደረጋል ፣ ይሁን ፣ ባሥራ ፣ ስድስት ፣ ብር ፣ ግዛው ። በዚሁ ፣ ተስማምተው ፣ ያም ፣ ሰውዬ ፣ ዕቁር ፣ አህያ ፣ ባሥራ ፣ ስድስት ፣ ብር ፣ ገዛና ፣ እቤቱ ፣ ሲደርስ ፣ ቢለቀው ፣ እዐያው ፣ የሰው ፣ ኩቴ ፣ እየሰማ ፣ ወደ ፣ ቤት ፣ ሮጦ ፣ ጥልቅ ፣ አለ ። እቤትም ፣ ከገባ ፣ ወዲያ ፣ ምንም ፣ ውጣ ፣ እያሉ ፣ ቢደበድቡትና ፣ ቢጠዝሉት ፣ ዕውር ፣ ስለ ፣ ሆነ ፣ ወደ ፣ ሴቶቹ ፣ ይሄድ ፣ ዝምር ። እነሱም ፣ የሚነክሳቸው ፣ መስሏቸው ፣ ሽሽተው ፣ ወደ ፣ ውጭ ፣ ሮጡ ። በዚህ ፣ ጊዜ ፣ አህያው ፣ እያሸተተ ፣ እጓዳ ፣ ገብቶ ፣ በሌ ማቱ ፣ ላይ ፣ ያለውን ፣ እንጀራ ፣ ልቅም ፣ አድርጎ ፣ በላው ።



መቼስ ፣ ምን ፣ ይደረጋል ፣ ይሁን ፣ ባሥራ ፣ ስድስት ፣ ብር ፣ ግዛው ።

ባለቤቲቱ ፣ የሆነውን ፣ አያታ ፣ ቶሎ ፣ ብላ ፣ ባሏን ፣ ጠራችውና ፣ በቀጣ ፣ ቃል ፣ ና ፣ ያመጣኸውን ፣ አህያ ፣ አስመጣልኝ ፣ አለችው ። ሰውዮውም ፣ ከቤት ፣ ገባና ፣ ከወደ ፣ ኋላው ፣ ዘሮ ፣ በዱላ ፣ ይመታው ፣ ዝምር ፣ አህያው ፣ ግን ፣ ዕውር ፣ በመሆኑ ፣ በሩ ፣ ስለ ፣ ጠፋው ፣ ቢጨንቀው ፣ የኋላ ፣ እግሩን ፣ እየሰነዘረ ፣ መራገጥ ፣ ያዘ ። ስለዚህም ፣ ሰውዮው ፣ ጥሎ ፣ ሸሸ ። ቢሆንም ፣ እንስሳው ፣ ዝላዩን ፣ ስለ ፣ ቀጠለ ፣ ጋኑን ፣ ድስቱን ፣ ማሰሮውን ፣

ጭንቀላውን ፣ ሙሃቹውን ፣ ዋዲያቱን ፣ ሁሉ ፣ ሰባብሮ ፣ በሙሉ ፣ የቤቱን ፣ ዕቃ ፣ ፈጀው ። ሰዎቹም ፣ ወይኑ ፣ እያየ ፣ ያሸነፋቸው ፣ መስሏቸው ፣ ባጉራ ፣ ደብድበው ፣ ገደሉት ።

አራተኛ ፣ ይህ ፣ ሰው ፣ ለምን ፣ ተሸነፍኩ ፣ ብሎ ፣ ተናዶ ፣ እንደ ፣ ገና ፣ ተነሥቶ ፣ እገበያ ፣ ቢወጣ ፣ አሁንም ፣ ያነኑ ፣ ሰው ፣ አህያ ፣ ሲሸጥ ፣ አገኘው ። ዛሬስ ፣ አለቀውም ፣ ብሎ ፣ ዘዴ ፣ ፈጥሮ ፣ ብድሩን ፣ ሊመልስ ፣ ማር ፣ ፈልጎ ፣ ገዛና ፣ ላንዱ ፣ ባልንጀራው ፣ ሐሳቡን ፣ ገለጠለት ። ጓደኛውም ፣ በጉዳዩ ፣ ተስማማበትና ፣ በንድነት ፣ ሄደው ፣ አህያ ፣ ሽጥልን ፣ አሉት ። እሱም ፣ ግዙ ፣ አላቸው ። ዋጋውስ ፣ ቢሉት ፣ ዐሥራ ፣ አፈት ፣ ብር ፣ አለ ። ዋጋ ፣ በዛ ፣ ብሎ ፣ አንደኛው ፣ ብሩን ፣ ይዘ ፣ ሲከራከር ፣ ሌላው ፣ ጠጋ ፣ ብሎ ፣ አህያው ፣ አፍ ፣ ውስጥ ፣ ማር ፣ ጨመረበት ። ላህያ ፣ ማር ፣ አይጥማት ፣ እንደ ፣ ተባለው ፣ ያ ፣ አህያ ፣ መረረውና ፣ ለህጩን ፣ ያንጠባጥብ ፣ ዝምር ። መላሱም ፣ ተጉለጉለ ። በዚህ ፣ ጊዜ ፣ እነዚያ ፣ ሰዎች ፣ አይ ፣ አይ ፣ መጋኛ ፣ መቶት ፣ ለሞት ፣ የደረሰውን ፣ አህያ ፣ ነው ፣ ይህንን ፣ ያክል ፣ ገንዘብ ፣ አውጥታችሁ ፣ ግዙኝ ፣ የምትለን ፣ ከቶ ፣ ማን ፣ ይታለልልህ ፣ መሰለህ ፣ ወንድሜ ፣ እያሉ ፣ አስደነገጡት ። እሱም ፣ አተኩሮ ፣ ቢያየው ፣ እውነትም ፣ የሚሞትበት ፣ መሰለው ። ባለ ወርቆቹ ፣ መለሱና ፣ በል ፣ ሽጥልን ፣ ቢድንም ፣ መልካም ፣ ቢሞትም ፣ በዕድላችን ፣ እናዝናለን ፣ አሉት ። እሺ ፣ ግዙ ፣ አለ ።

—ምን ፣ ያክል ፣

—ሦስት ፣ ብር ፣

—ሁለቱን ፣ ትተህ ፣ አንድ ፣ ብር ፣ አትሸጥልንም ፣

—ይሁን ፣ አምጡ ።

አንድ ፣ ብር ፣ ሰጥተው ፣ አህያቸውን ፣ ይዘው ፣ ወደ ፣ ቤታቸው ፣ ሄዱ ። አህያው ፣ ግን ፣ ሕመም ፣ የለበትም ፣ ነበርና ፣ ውሃ ፣ በጠጣ ፣ ጊዜ ፣ ደኅና ፣ ሆነ ።

ከዚህ ፣ በኋላ ፣ ሁለቱም ፣ አታላዮች ፣ በሥራቸው ፣ ስለ ፣ ተዋወቁ ፣ እንግዲህ ፣ ጓደኛ ፣ እንሁን ፣ አብረን ፣ የሆን ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ እንከብራለን ፣ ተብብለው ፣ ምክር ፣ አደረጉ ። በሐሳቡም ፣ ተስማምተው ፣ እንደኛው ፣ እንግዲህ ፣ ወንድሜ ፣ ተነሥተን ፣ ለሌብነት ፣ ወደ ፣ ሩቅ ፣ አገር ፣ እንሂድ ፣

ሲል ፡ ጠየቀው ። ሁለተኛውም ፡ እሺ ፡ ምን ፡ ከፋኝ ፡ አለውና ፡ ተያይ ዘው ፡ ሲሄዱ ፡ ከንድ ፡ ቃልቻ ፡ ቤት ፡ ደረሱ ። በለቤቱም ፡ ከወዴት ፡ መጥታችኋል ፡ አላቸው ።

—ከዚሁ ፡ አገር ፡ ነው ።

—ምን ፡ ትፈልጋላችሁ ፤

—ሎሌነት ፡ ለመግበት ።

እንግዲያውስ ፡ እዚሁ ፡ እኔ ፡ ቤት ፡ ኦትቀመጡምን ፡ ሥራዬም ፡ ቀላል ፡ ነው ። አንደኛችሁ ፡ አንዲት ፡ ላም ፡ መጠበቅ ፤ አንደኛችሁ ፡ ደግሞ ፡ የላሚን ፡ እበት ፡ ማውጣት ፡ ብቻ ፡ ነው ። እንደ ፡ እውነቱ ፡ ቢሆን ፡ ይህ ፡ በቂ ፡ ሥራ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ሰው ፡ የሚያስቀጥር ፡ አልነበረም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እንደማያችሁ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ስለ ፡ ሆናችሁ ፡ እኔም ፡ በተሌ ፡ በመሆኔ ፡ ቤቴንና ፡ ይልቁንም ፡ በብዙ ፡ ድካም ፡ አጠራቅሜ ፡ ከዚህ ፡ ከጋን ፡ ውስጥ ፡ ያስቀመጥኩትን ፡ ወርቅ ፡ በጥንቃቄ ፡ ትጠብቁልኛላችሁ ፡ የማለት ፡ እምነትና ፡ ተስፋ ፡ ስላደረብኝ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ሰፊ ፡ ንግግር ፡ አደረገላቸው ። እነሱም ፡ እሺ ፡ ይህንን ፡ ሁሉ ፡ አደራ ፡ ለመጠበቅ ፡ እንችላለን ፡ ሲሉ ፡ ቃል ፡ ገብተው ፡ ከዚህ ፡ ቃልቻ ፡ ቤት ፡ አሽከርነት ፡ ተቀጠሩ ።

በማግስቱ ፡ ባለቤቱ ፡ አንዱን ፡ አሽከር ፡ አንዲት ፡ ላም ፡ ሰጥቶ ፡ ወደ ፡ ዱር ፡ ሰደደው ፤ እንዱን ፡ ደግሞ ፡ ከዚያው ፡ ከቤት ፡ የዘያችን ፡ ላም ፡ እበት ፡ እንዲያወጣ ፡ አዘዘው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እበት ፡ አውጪው ፡ ከንጋቱ ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ምሽቱ ፡ ድረስ ፡ ወዛባውን ፡ ቢያወጣው ፡ ቢያወጣው ፡ አላልቅ ፡ አለው ። እረኛውም ፡ ላሚ ፡ ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ስታራውጠው ፡ ውላ ፡ ደክሞት ፡ የማታ ፡ ማታ ፡ ከብቷን ፡ ይዞ ፡ ከቤት ፡ ገባ ። ጊዜውም ፡ ስለ ፡ መሸና ፡ ብርድም ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ሁለቱ ፡ ጓደኞች ፡ እሳት ፡ ለመሞቅ ፡ ከምድጃ ፡ ዳር ፡ ተቀመጡ ። ወዲያው ፡ የዋሉበትን ፡ መወያየት ፡ ገፖመሩ ፤ እቤት ፡ የቀረውን ፡ አንደኛው ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ዋልክ ፡ አለው ። አይ ፡ እኔስ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እበቱን ፡ አውጥቼ ፡ ቀሩጭ ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ የዋልኩ ፡ አንተ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ዋልክ ፡ ብሎ ፡ መልሶ ፡ ጠየቀው ። በለላመ ፡ እኔም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ከደጎና ፡ ሣር ፡ ለቅቄ ፡ ቀሩጭ ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ የዋልኩት ፡ አለ ። እንግዲያውስ ፡ ነገ ፡ እንዘዋወር ፡ ተባብለው ፡ ሥራቸውን ፡ ተለዋወጡ ። በዚህም ፡ ስምምነት ፡ እበት ፡ ጠራጊ ፡ የነበረው ፡ ላሚን ፡ ይዞ ፡ እዱር ፡ ሄደ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ እየበረረች ፡ ቢላትም ፡ ቢያደርጋትም ፡ አቅታውና ፡ አሸንፋው ፡ ዋለች ። አረኛም ፡ የነበረው ፡ ከጧት ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ቢያወጣ ፡ ቢያወጣ ፡ እበቱ ፡ ተመልሶ ፡ ከዚያው ፡ ስለሚገኝ ፡ በከንቱ ፡ ሲደክም ፡ ዋለ ።

የማታ ፡ ማታ ፡ ሁለቱም ፡ ሲቃትቱና ፡ ሲለፉ ፡ የዋሉበትን ፡ ምስጢራቸውን ፡ ስለ ፡ ተገላለጡ ፡ እንግዲህ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ እንደዚህ ፡ ስንደክም ፡ እንኖራለን ፤ በጋን ፡ ያለውን ፡ ወርቅ ፡ ይዘን ፡ እንጥፋ ፡ እንጂ ፡ ተባባሉና ፡ በሐላቡም ፡ ስለ ፡ ተስማሙ ፡ በማግስቱ ፡ በሌሊት ፡ ተነሥተው ፡ ወርቅ ፡ ወዳለበት ፡ ጋን ፡ ሄዱ ። አንደኛው ፡ ጓደኛዬ ፡ ሰይቀድመኝ ፡ በማለት ፡ ፈጥኖ ፡ እጁን ፡ ከተተው ። ነገር ፡ ግን ፡ በጋኑ ፡ ውስጥ ፡ ቃልቻው ፡ የተራበ ፡ ዘንዶ ፡ አስቀምጠ ፡ ኖሮ ፡ እጁን ፡ ቅርጥፍ ፡ አደረገው ፡ ጨለማ ፡ ነበረና ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ አሰይ ፡ አለ ። ምነው ፡ ቢለው ፡



የተራበ ፡ ዘንዶ ፡ እጁን ፡ ቅርጥፍ ፡ አደረገው ።

የዘላለሜን ፡ አገኘሁ ፡ አለና ፡ መለሰለት ። ሁለተኛው ፡ ደግሞ ፡ የተበለጥኩ ፡ መስሎት ፡ በችኩላ ፡ እጁን ፡ ዘው ፡ ሲያደርግ ፡ ያ ፡ ዘንዶ ፡ አሁንም ፡ የዚህን ፡ እጅ ፡ ጉምድ ፡ አደረገው ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ጉድ ፡ አለ ። ጓደኛውም ፡ እየው ፡ የኔንም ፡ ጉምድ ፡ ብሎ ፡ ዱሹን ፡ አሳየው ፡ ይበላል ።

※ ስለዚህ ፡ በሰፈሩት ፡ ቀሩና ፡ መሰፈር ፡ ስለማይቀር ፡ መጠንቀቅ ፡ አለብን ። ደግሞ ፡ እጅግም ፡ ብልጠት ፡ ያደርሳል ፡ ከሞት ፡ ነውና ፡ ዘወትር ፡ በምንሠራው ፡ ሁሉ ፡ ማስተዋልና ፡ መታረም ፡ ይገባናል ።

ስለ ፡ አንድ ፡ ሽማግሌ ፡ ምርቃት ።

አንድ ፡ ሽማግሌ ፡ ሁለት ፡ ልጆች ፡ ነበሩት ። ከነዚህም ፡ አንዱ ፡ በማናቸውም ፡ ሥራው ፡ አባቱን ፡ በቅን ፡ የሚያገለግል ፡ ሲሆን ፡ ሁለተኛው ፡ ደግሞ ፡ ቅር ፡ የሚያሰኘውና ፡ የሚያበሳጨው ፡ በሥራው ፡ ሁሉ ፡ የማያስደስተው ፡ ነበረ ። ስለዚህ ፡ ሽማግሌው ፡ የሕይወቱ ፡ ፍጻሜ ፡ ዘመን ፡ መቃረቡን ፡ ተመልክቶ ፡ ሁለቱንም ፡ ልጆቹን ፡ ጠራና ፡ ልጆቼ ፡ ሆይ ፡ በቁየው ፡ ዋግና ፡ ሥርዐት ፡ መሠረት ፡ አባቶች ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ በሞት ፡ የሚለዩበት ፡ ጊዜ ፡ ሲቃረብ ፡ ሀብታቸውን ፡ ሁሉ ፡ ለልጆቻቸው ፡ ከምርቃት ፡ ጋራ ፡ መስጠት ፡ ልማዳቸው ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ እኔም ፡ ይህንኑ ፡ ዘመከተል ፡ ከልጅነት ፡ እስከ ፡ ዕውቀት ፡ ደክሜ ፡ የሰበሰብኩትን ፡ ሀብቴንና ፡ ንብረቴን ፡ ሁሉ ፡ ለማስተላለፍ ፡ እናንተን ፡ ጠርቻችኋለሁ ፡ ብሎ ፡ በጥሞና ፡ ቃል ፡ ነገራቸው ። ልጆቹም ፡ አባታችን ፡ ለሚያደርጉት ፡ ሁሉ ፡ ፈቃደኞች ፡ ነን ፡ ብለው ፡ ስለ ፡ ቀረቡት ፡ ሽማግሌው ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ አሰማቸው ።

ልጆቼ ፡ ሆይ ፡ እግዚአብሔር ፡ እፈቀደው ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያለውን ፡ ያስተዳደር ፡ ተግባር ፡ በቅሜ ፡ መጠን ፡ ስፈጽም ፡ ኖሬ ፡ ይኸው ፡ ለሚከተለው ፡ ዘመን ፡ እናንተን ፡ አትርፌያለሁ ። ስለዚህ ፡ በዕለት ፡ ተግባሬ ፡ ያገኘሁትንና ፡ ካባቴም ፡ የተሰጠኝን ፡ ሀብትና ፡ ንብረት ፡ ሁለታችሁ ፡ እለቃና ፡ ምንዝር ፡ ሆናችሁ ፡ እንድትበሉ ፡ ወስኛለሁ ፤ ይሁን ፡ እንጂ ፡ እንተ ፡ የመገሥፀሪያ ፡ ልጄ ፡ ለርስቱ ፡ አለቃ ፡ ሆነህ ፡ በሀገር ፡ ልማድ ፡ የሚገባውን ፡ ሁሉ ፡ ፈጽም ። ስለ ፡ አገልግሎትህም ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚሰት ፡ እርጧጣ ፡ የጎረ ፡ ቤት ፡ ውሻ ፡ የቤት ፡ በታች ፡ እርሻ ፡ ይሰጥህ ፡ አለው ። ልጁም ፡ ይህንን ፡ ምርቃት ፡ ተቀብሎ ፡ ጫማ ፡ ስሞ ፡ ቆመ ። ሁለተኛውን ፡ ልጁን ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ቂየው ፡ ልማድ ፡ ለርስቱ ፡ ምንዝር ፡ በመሆን ፡ ለወንድምህ ፡ እየታዘዝክ ፡ ድርሻህን ፡ ብላ ፤ ስለ ፡ አገልግሎትህም ፡ ምርቃቱ ፡ የሚሰት ፡ ወይዘሮ ፡ የጎረ ፡ ቤት ፡ ዶሮ ፡ የርሻ ፡ ጋራ ፡ ዘሮ ፡ እንዲሰጥህ ፡ ነው ፡ አለው ። ልጁም ፡ ምርቃቱን ፡ ተቀብሎ ፡ ጫማ ፡ ስሞ ፡ ቆመ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሽማግሌው ፡ ምርቃቱ ፡ ይደርባችሁ ፡ ሂዱ ፡ ብሎ ፡ አሰናበታቸውና ፡ ወጡ ። ነገር ፡ ግን ፡ ታላቁ ፡ ልጅ ፡ በተሰጠው ፡ ምርቃት ፡ ከፋው ፤ ትንሹ ፡ ደግሞ ፡ በጣም ፡ ተደሰተ ፤ በመጨረሻውም ፡ ትክክለኛውን ፡ ትርጉም ፡ ለማ

ወቅ ፡ የሁለቱም ፡ ምኞትና ፡ ፈቃድ ፡ ሆነ ።

ስለዚህም ፡ አንድ ፡ አስተያየቱ ፡ ጥልቅ ፡ ወደ ፡ ሆነ ፡ ያገር ፡ ሽማግሌ ፡ ዘንድ ፡ ሄዱ ። ላዋቂውም ፡ የመጡበትን ፡ አንድ ፡ በንድ ፡ ዘርዝረው ፡ ነገሩትና ፡ አባክህ ፡ ተርጉምልን ፡ ብለው ፡ አጥብቀው ፡ ለመኑት ፡ አሱም ፡ ልመናቸውን ፡ ተቀብሎ ፡ ቀጥሎ ፡ እንዳለው ፡ ተረጐመላቸው ።

አንደኛ ፡ እንተ ፡ ባባትህ ፡ ምርቃት ፡ ቅር ፡ የተሰኘኸው ፡ ትልቁ ፡ ልጅ ፡ በሚገባ ፡ አባትህን ፡ ደስ ፡ አሰኝተሃል ፡ ስለዚህ ፡ አባትህ ፡ የሚሰት ፡ እርጣጣ ፡ ይሰጥህ ፡ ያለህ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ እንዳይነካብህ ፡ ዘወትር ፡ ያላትን ፡ ጕልበቷን ፡ ለንብረቷ ፡ ለቤቷ ፡ እንድታውል ፡ ጠላት ፡ ባለጋራ ፡ ሳትፈጥርብህ ፡



ዘወትር ፡ ያላትን ፡ ጕልበቷን ፡ ለንብረቷ ፡ ለቤቷ ፡ እንድታውል ፡ ጠላት ፡ ባላጋራ ፡ ሳትፈጥርብህ ፡ በታማኝነት ፡ አብራህ ፡ እንድትኖር ፡ ተቃዋሚ ፡ እንዳትሆንብህ ፡ ነው ።

በታማኝነት ፡ አብራህ ፡ እንድትኖር ፡ ሲሆን ፡ ታላቁ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ መሙላድ ፡ ነውና ፡ እውነተኛ ፡ ፍሬ ፡ እንድትሰጥህ ፡ ከዚህም ፡ በላይ ፡ ተግገር ፡ እንጂ ፡ ተቃዋሚ ፡ እንዳትሆንብህ ፡ ነው ። ሁለተኛ ፡ የጎረ ፡ ቤት ፡ ውሻ ፡ ይሰጥህ ፡ ያለህ ፡ አንተ ፡ ሳታበላው ፡ ሳታሳድገው ፡ የቅርብ ፡ ጎረ ፡ ቤትህ ፡ በመሆኑ ፡ ብቻ ፡ በአጥርህ ፡ ዙሪያ ፡ እየተዘዋወረ ፡ ስሊት ፡ ሲጠብቅህ ፡ እንዲያድር ፡ ነው ። ሦስተኛ ፡ የቤት ፡ በታች ፡ እርሻ ፡ ይሰጥህ ፡ ያለህ ፡ የርሻ ፡ መሬትህ ፡ በማናቸውም ፡ ፍግ ፡ እንዲዳብርልህ ፡ እንተም ፡ ርቀህ ፡ ሳትሄድ ፡ እዚያው ፡ ቤትህን ፡ እየጠበቅህ ፡ ሥራህን ፡ እንድትሠራ ፡ በጊዜው ፡ ከጥላ ፡ እያረፍክ ፡ ሲሳይህን ፡ እንድትመገብ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ አባትህ ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጠቃሚ ፡ ምርቃት ፡ መርቆሃል ፡ ብሎ ፡ አፍታዎ ፡ ስለ ፡ ተረጐመለት ፡ የትልቁ ፡ ልጅ ፡ ሐዘን ፡ በታላቅ ፡ ደስታ ፡ ተለወጠ ።

የሁለተኛውን ፡ ልጅ ፡ ምርቃት ፡ ትርጉም ፡ ደግሞ ፡ የሚስት ፡ ወይ ዘሮ ፡ ይስጥህ ፡ ያለህ ፡ የቄንዠ ፡ ሴት ፡ ተመልከቺ ፡ ብዙ ፡ ነው ። እሷ ፡ እንኳ ፡ ፈቃዷ ፡ በይሆን ፡ በሴት ፡ አማላጅነት ፡ በመደለል ፡ ጭምር ፡ ተገዳ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ወዳጅ ፡ ታበጃለች ፤ ስለዚህም ፡ ወሬ ፡ ትለምድና ፡ ወይ ፡ እሷው ፡ ትሄድለታለች ፤ አለዘያም ፡ እሱ ፡ ይመጣል ፤ ድንገትም ፡ ብትገናኙ ፡ ትገድ ለዋለህ ፡ ወይም ፡ እርሱ ፡ ይገድልሃል ፤ እንግዲህ ፡ ጠላት ፡ ገዛችልህ ፡ ማለት ፡ ነው ። ሁለተኛ ፡ የጎረ ፡ ቤት ፡ ዶሮ ፡ ይስጥሽ ፡ ያለህ ፡ ይህቺ ፡ ቄንዠ ፡ ሚስትህ ፡ በሴት ፡ አማካይነት ፡ ያገኘችውን ፡ መጥፎ ልምድ ፡ ለመፈጸም ፡ ወደየመን ደረሱ ፡ በምትሄድበትና ፡ በምትዘርበት ፡ ጊዜ ፡ እደጅ ፡ ለወፍጮ ፡ ያሰጣችውን ፡ እኽል ፡ የጎረ ፡ ቤት ፡ ዶሮች ፡ ተሰብስበው ፡ ግማሹን ፡ በልተው ፡ ግማሹን ፡ እየጫሩ ፡ አፍስሰውት ፡ ስለሚገኝ ፡ ስትመለስ ፡ ያንን ፡ በመልቀም ፡ ቀኑ ፡ ይመሽባታል ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ የምትበላውን ፡ ምግብ ፡ ሳታሰናዳልህ ፡ ትቀርና ፤ ወደ ፡ ዋልክበት ፡ ሥራ ፡ ጦምህን ፡ ትመለሳለህ ። እቤትህ ፡ ስትገ ባም ፡ የሚቀርብልህ ፡ ምግብ ፡ አይገኝም ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አባትህን ፡ ያናደ ድከውን ፡ ያኽል ፡ አንተም ፡ እንድትናደድ ፡ ነው ። ሦስተኛ ፡ የርሽ ፡ ጋራ ፡ ዘሮ ፡ ይስጥህ ፡ ያለህ ፡ ቄንዠዋ ፡ ሚስትህ ፡ በሴት ፡ አቅራቢነት ፡ ያበዛቻቸው ፡ ወዳጆቿ ፡ ያንተን ፡ ጋራ ፡ መዘር ፡ አይተው ፡ ወደ ፡ ቤትህ ፡ እየገቡ ፡ ሀብት ህን ፡ ሲያጠፉ ፡ ሚስትህን ፡ ሥራ ፡ ሲያስፈቱና ፡ ሲያወሳልቱ ፡ እንዲውሉ ፡ በዚህም ፡ ሁናቴ ፡ ያንተ ፡ ኑሮና ፡ አስተዳደር ፡ ጉድለት ፡ የተመላበት ፡ እን ዲሆን ፡ ነው ። ይኸውም ፡ መርገሙ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ አስተክክሎ ፡ ስለ ፡ ተረጐመለት ፡ ምንገዛሩ ፡ እንደ ፡ ፈተኛው ፡ መደሰቱ ፡ ቀርቶ ፡ በሥራው ፡ እያዘነና ፡ እየተጸጸተ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ተመለሰ ፡ ይባላል ።




ለወፍጮ ፡ ያሰጣችውን ፡ እኽል ፡ የጎረ ፡ ቤት ፡ ዶሮች ፡ ተሰብስበው ፡ ግማሹን ፡ በል ተው ፡ ግማሹን ፡ እየጫሩ ፡ በመልቀም ፡ ቀኑ ፡ ይመሽባታል ።

※ አባትን ፡ ማስቀየም ፡ ፈጣሪን ፡ እንደ ፡ መበደል ፡ ያኽል ፡ ስለሚ ቈጠር ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ ያባቶቻቸውን ፡ ፈቃድ ፡ መፈጸም ፡ ቃላቸውንም ፡ መጠበቅ ፡ ይገባቸዋል ። ዋጋቸውንም ፡ የሚቀበሉት ፡ በገልግሎታቸው፡ መጠን ፡ መሆኑን ፡ አይዘንጉት ።


ስለ ፡ ዘጠኝ ፡ ቂሎች ፡ ወንድማማቾች ።

ቂሎች ፡ የሆኑ ፡ ዘጠኝ ፡ ወንድማማቾች ፡ ወደ ፡ ዘመቻ ፡ ታዘው ፡ ሲሄዱ ፡ እናታቸው ፡ ልጆቼ ፡ እንግዲህ ፡ በጦርነቱ ፡ ላይ ፡ ተለያይታችሁ፡ ከቀጥር ፡ እንዳትጐድሉ ፡ አደራ ፡ ብላ ፡ አስጠነቀቀቻቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዘጠኙም ፡ ዘጠኝ ፡ ጭብጦ ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ዘመቻው ፡ ለመጓዝ ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ ሰሉ ፡ እናታችን ፡ ከቀጥር ፡ እንዳትጐድሉ ፡ ብላ ፡ አስጠንቅቃናለችና ፡ አሁኑኑ ፡ እንቈጠር ፡ ተባባሉ ። ወዲያው ፡ ከመከከላቸው ፡ አንዱ ፡ ወንድሞቹን ፡ ደርድሮ ፡ አቁሞ ፡ ቢቈጥራቸው ፡ ስምንት ፡ ብቻ ፡ ሆኑበት ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አንደኛው ፡ ወዴት ፡ ጠፋብን ፡ ብ ለው ፡ ዘጠኙም ፡ ተጨነቁ ፤ ድንጋጤም ፡ ያዛቸው ። አቈጣጠሩን ፡ አሳ ስቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በማለት ፡ አንደኛው ፡ ደግሞ ፡ አንደዚያው ፡ ስምን ቱን ፡ ወዳንድ ፡ ወገን ፡ አቁሞ ፡ ራሱን ፡ ትቶ ፡ ቢቈጥር ፡ ያው ፡ ሆነበት ፤ የቀሩትም ፡ እንደዚሁ ፡ ያየተራ ፡ ራሳቸውን ፡ እየተዉ ፡ ቢቈጥሩ ፡ አሁ ንም ፡ ጉድለቱ ፡ ሊታረም ፡ ሳይቻል ፡ ቀረ ።



አንደኛው ፡ ወዴት ፡ ጠፋብን፡ ብለው ፡ ዘጠኙም ፡ ተጨነቁ፤ ድንጋጤም ፡ ያዛቸው ።

ስለዚህ ፡ ሁሉም ፡ ተጨንቀው ፡ በሐዘንና ፡ በትካዜ ፡ ተጨብጠው ፡ አሁን ፡ እምን ፡ ቦታ ፡ ወድቆ ፡ ቀርቶ ፡ ይሆን ፡ እያሉ ፡ ሲነጋገሩ ፡ አንድ ፡ መንገደኛ ፡ ሰው ፡ ተፍ ፡ ተፍ ፡ ሲል ፡ ደረሰ ። እሱም ፡ ሲያለቅሱና ፡ ሲ ጨነቁ ፡ አይቶ ፡ ጠጋ ፡ አላቸውና ፡ ወንድሞቼ ፡ ምን ፡ ሆናችኋል ፡ ምነው ፡ አገናችኋል ፡ ብሎ ፡ ጠየቃቸው ። ዘጠኝ ፡ ሆነን ፡ ከቤታችን ፡ ለዘመቻ ፡ ስንወጣ ፡ እናታችን ፡ ከቀጥር ፡ እንዳትጐድሉ ፡ ብላ ፡ አስጠ ንቅቃን ፡ ነበረ ፤ አሁን ፡ ከዘጠኛችን ፡ አንዱ ፡ ወንድማችን ፡ ጠፍቶብን ፡ ተጨንቀናል ፡ አሉት ። ያም ፡ ሰውዬ ፡ እኔ ፡ ባገኛላችሁ ፡ ምን ፡ ትሰጡኛላችሁ ፡ አላቸው ። እነሱም ፡ ተጨንቀዋልና ፡ ያንኑ ፡ የያዙትን ፡ አን ዳንድ ፡ ጭብጦ ፡ እንሰጣለን ፡ ሲሉ ፡ መለሱለት ። በሉ ፡ ቡጉርታ ፡ ሁኑ ፡ ብሎ ፡ አቁሞ ፡ አንድ ፡ ሁለት ፡ በማለት ፡ ቁጥሮ ፡ ዘጠኝ ፡ መሆናቸውን ፡ አረጋገጣላቸው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እነኛ ፡ ቂሎች ፡ ለካ ፡ እዚሁ ፡ እመካከ ላችን ፡ ተቀምጠ ፡ ነው ፡ እንደዚህ ፡ ስንደክምና ፡ ስናለቅስ ፡ ዝም ፡ ያለን ፡



በሉ ፡ በተርታ ፡ ሁኑ ፡ ብሎ ፡ አቁሞ ፡ አንድ ፡ ሁለት ፡ በማ ለት ፡ ዘጠኝ ፡ መሆናቸውን ፡ አረጋገጣላቸው ።

እያሉ ፡ በየበኩላቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ ይይልህ ፡ በማለት ፡ ይራገሙ ፡ ገሥጿቸው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ውል ፡ አያወላውል ፡ ነውና ፡ ያም ፡ ሰውዬ ፡ ከዘጠኙ ፡ ዘጠኝ ፡ ጭብጦ ፡ ተቀብሎ ፡ ሄደ ፡ ይባላል ።

፠ አካሄዱን ፡ አይተህ ፡ ጭብጦውን ፡ ቀማው ፤ እንዲሁም ፡ ከሞኝ ፡ ደሮ ፡ ዛቢያ ፡ ይቄረጣል ፡ እየተባለ ፡ የሚተረተው ፡ ይህን ፡ ለመሰለ ፡ መሆኑን ፡ ማስተዋል ፡ ይገባል ።

ስለ ፡ ሦስት ፡ ሴቶች ።

አንዲት ፡ ቂልና ፡ ሁለት ፡ ብልጥ ፡ ሴቶች ፡ አብረው ፡ በንዴ ፡ ቤት ፡ ሲኖሩ ፡ ቂሏና ፡ አንደኛዋ ፡ ብልጥ ፡ ልጆች ፡ ወለዱ ። ያች ፡ ያልወለደ ችው ፡ መከኒቱ ፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እነዚያን ፡ በለልጆች ፡ ሴቶች ፡ ሙክት ፡ አርጂ ፡ እቄያችኋለሁና ፡ ዕንጨት ፡ ስበሩና ፡ ኑ ፡ አለቻቸው ። እነሱም ፡ እሺ ፡ ብለው ፡ ተነሥተው ፡ መጫኛ ፡ መጫኛቸውን ፡ ይዘው ፡ ዕንጨት ፡ ለቀማ ፡ ወደ ፡ ቄላ ፡ ወረዱ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ያች ፡ መከን ፡ እነ ዚያን ፡ ልጆች ፡ አርዳ ፡ ቀቅላ ፡ እመኻታቸው ፡ ላይ ፡ ሙቀጫ ፡ አጋድማ ፡ ቄየቻቸው ።

ዕንጨት ፡ ሰባሪዎቹም ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ገቡ ፡ ልጆቻችንን ፡ እናጥባ ፡ ቢሉ ፡ ቄዩ ፡ በልታችሁ ፡ ታጠባላችሁ ፡ ብላ ፡ ከለከለች ። እነ ሱም ፡ ርቧቸው ፡ ነበርና ፡ የቀረበላቸውን ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ሲበሉ ፡ ከቄዩ ፡ በኋላ ፡ በመጨረሻው ፡ ብልጠቱ ፡ ምነው ፡ እጎቴ ፡ ሆዴ ፡ ባሰ ብኝ ፡ ልጄ ፡ ምን ፡ ሆነብኝ ፡ ይሆን ፡ እስቲ ፡ ልየው ፡ ብላ ፡ መኻታቸ ውን ፡ ገለጥ ፡ አድርጋ ፡ ብትመለከት ፡ የተጋደመው ፡ ሙቀጫ ፡ ሆኖ ፡ አገኘችው ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ ሐዘን ፡ ተሰማትና ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለማግኘት ፡ መንገድ ፡ ገፖመረች ። እየጠየቀችም ፡ ስትሄድ ፡ ስትሄድ ፡ ውላ ፡ አንድ ፡ ውሃ ፡ የምትቀዳ ፡ ሴት ፡ ስላገኘች ፡ እባክሽን ፡ እግዚአብ ሔር ፡ ያለበትን ፡ አሳይኝ ፡ ስትል ፡ ጠየቀቻት ። ውሃ ፡ ቅጂልኝና ፡ አለ ቻት ። ያንን ፡ ውሃ ፡ ስትቀዳ ፡ ስትቀዳ ፡ ዋለችና ፡ በመጨረሻው ፡ ሂጂ ፡ ያች ፡ ኮበት ፡ የምትለቀም ፡ ሴት ፡ ታሳይሽለችና ፡ ጠይቂያት ፡ ብላ ፡ ሰደ ደቻት ። ወደዚያች ፡ ማገዶ ፡ ለቃሚ ፡ ጠጋ ፡ አለችና ፡ እባክሽ ፡ የእግዚ አብሔርን ፡ ቤት ፡ አሳይኝ ፡ አለቻት ። እሷም ፡ ኩበት ፡ ልቀሚልኝና ፡ ስትል ፡ መለሰችላት ። እሺ ፡ ብላ ፡ ሰትለለች ፡ ስትለቅም ፡ ከዋለች ፡ በኋላ ፡ በመጨረሻው ፡ ሂጂ ፡ ያ ፡ ሣር ፡ የሚያግዝ ፡ ሰው ፡ ያሰይሽ ፡ ስትል ፡ አሰ ናበተቻት ። እሱን ፡ ደግሞ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ አሳየኝ ፡ ብትለው ፡ ይህንን ፡ ሣር ፡ አግኝልኝና ፡ አላት ። አሁንም ፡ እሺ ፡ ጌታዬ ፡ ብላ ፡ ስታግ ዝለት ፡ ዋለችና ፡ በመጨረሻው ፡ ሂጂ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ቅጭል ፡ ቅጭል ፡ የሚለው ፡ የሰይጣን ፡ ቤት ፡ ደግሞ ፡ ድም ፡ ድም ፡ የሚለው ፡ ነውና ፡ ድም ፡ ድም ፡ የሚለውን ፡ ትተሽ ፡ ቅጭል ፡ ቅጭል ፡ ከሚለው ፡ ግቢ ፡ አለና ፡ ሰደዳት ።

እሷም ፡ ሄዳ ፡ በሩን ፡ ትም ፡ ትም ፡ አደረገች ። እግዚአብሔርም ፡ ብቅ ፡ አለና ፡ ምን ፡ ሆንሽ ፡ ምንስ ፡ ትፈልጊያለሽ ፡ ብሎ ፡ ጠየቃት ። ልጅ ፡ ትሰጠኝ ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ አለችው ። የተቄለፈ ፡ አገልግል ፡ አምጥቶ ፡ እንቺ ፡ ይህንን ፡ ይዘሽ ፡ ሄደሽ ፡ አገርሽ ፡ ለመድረስ ፡ ስትቃረቢ ፡ ውዝ ፡ ውዝ ፡ አድርገሽ ፡ ከፈችው ፡ አለና ፡ ሰጣት ። አገልግሉን ፡ ተቀብላ ፡ ይዛ ፡ ሄዳ ፡ አገሯ ፡ ለመግባት ፡ ትንሽ ፡ ሲቀራት ፡ ውዝ ፡ ውዝ ፡ አድርጋ ፡ ብት ከፍተው ፡ ከውስጡ ፡ ምን ፡ የመሰለ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ አገኘች ። በዚህ ፡ ጊዜም ፡ የነበራት ፡ ደስታና ፡ ለፈጣሪዋ ፡ ያቀረበችው ፡ ምስጋና ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ሊገመት ፡ የሚቻል ፡ አልነበረም ። በመጨረሻውም ፡ ልጅዋን ፡ አዝላ ፡ ከቤቷ ፡ ገባች ።

ወዲያው ፡ ያች ፡ ቂል ፡ ሴት ፡ ልጅሽን ፡ ከወዴት ፡ አገኘሽው ፡ አለቻት ፤ እሷም ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰጠኝ ፡ ብላ ፡ መለሰችላት ።

—እስቲ ፡ አባክሽ ፡ ቤቱን ፡ ለኔም ፡ አሳይኝ ፤

—ሂጂ ፡ ያች ፡ ውሃ ፡ የምትቀዳ ፡ ሴት ፡ ታሳይሽ ።

እንደ ፡ ተነገራት ፡ ሄደችና ፡ አንቺ ፡ ሴት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ አሳይኝ ፡ ብላ ፡ ጠየቀቻት ። እሷም ፡ ውሃ ፡ ቀጂልኝና ፡ አለቻት ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ያንቺ ፡ ውሃ ፡ ቀጂ ፡ ነኝ ፡ ብላ ፡ ተቄጣቻት ። እንግዲያውስ ፡ ሂጂ ፡ ያች ፡ ኮበት ፡ ለቃሚ ፡ ሴት ፡ ታሳይሽ ፡ በማለት ፡ ስለ ፡ መለሰችላት ፡ ወደርሷ ፡ ቀርባ ፡ አንቺ ፡ ሴት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ አሳይኝ ፡ ብላ ፡ ጠየቀቻት ። ኮበት ፡ ልቀሚልኝና ፡ ስትል ፡ መለሰችላት ። አሁንም ፡ ያንቺ ፡ ኮበት ፡ ለቃሚ ፡ ነኝ ፡ ወይ ፡ ብላ ፡ በጎይለ ፡ ቃል ፡ ተናገረች ። በይ ፡ ተይው ፡ እኅቴ ፤ ያ ፡ ሣር ፡ የሚያግዘው ፡ ሰው ፡ ያሳይሽ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ሂጂ ፡ አለቻት ። እሺ ፡ ብላ ፡ ስትገናጀብ ፡ ሄዳ ፡ ብትጠይቀው ፡ እንደ ፡ ፊተኛው ፡ ይህንን ፡ ሣር ፡ አግዢልኝና ፡ አላት ። እሷም ፡ ምነው ፡ እኔ ፡ ያንተ ፡ ሣር ፡ ተሸክሚ ፡ ነኝን ፡ አለችው ። በይ ፡ እንግዲያው ፡ ሂጂ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ድም ፡ ድም ፡ የሚለው ፤ የሰይጣን ፡ ቤት ፡ ቅጭል ፡ ቅጭል ፡ የሚለው ፡ ነው ፡ ሲል ፡ አመለከታት ። ሄዳ ፡ ድም ፡ ድም ፡ የሚለውን ፡ ብትመታው ፡ ሰይጣን ፡ ብቅ ፡ አለና ፡ ምን ፡ ልታደርጊ ፡ መጣሽ ፡ አላት ። ልጅ ፡ ትሰጠኝ ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ ስትል ፡ መልስ ፡ ሰጠችው ። የተቄለፈ ፡ አገልግል ፡ አምጥቶ ፡ ይህንን ፡ ይዘሽ ፡ ሄደሽ ፡ ከጠራ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ስትደርሽ ፡ ውዝ ፡ ውዝ ፡ እድርገሽ ፡ ከፈችው ፡ አለና ፡ ሰጣት ። እሷም ፡ ደስ ፤ ተሰኝታ ፡

እንዳዘዛት ፡ ዕቃውን ፡ ይዛ ፡ ሄዳ ፡ ከጠራ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ስትደርስ ፡ ብት ከፍተው ፡ ከውስጡ ፡ ዘንዶ ፡ ወጣ ። ደንግጣና ፡ ፈርታ ፡ ብትሸሽም ፡ ስለ ፡ ተከተላት ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ በቅሎ ፡ ጭነው ፡ በመንገድ ፡ ሲያልፉ ፡ አገኘችና ፡ እናንተ ፡ ሰዎች ፡ እባካችሁ ፡ ስለ ፡ ነፍስ ፡ ከዘንዶ ፡ አድኑኝ ፡ አለቻቸው ።

እነሱም ፡ እሺ ፡ ብለው ፡ ከከብቶቹ ፡ መካከል ፡ ግቢ ፡ አሏት ፡ ወዲያው ፡ ያ ፡ ዘንዶ ፡ ደረሰና ፡ ባወጣላት ፡ ስም ፡ "ኮልባ ፡ ኮልቢቱን" ፡ አሳዩኝ ፡ ሳልውጣችሁ ፡ ሳልሰለቅጣችሁ ፡ ብሎ ፡ ሰዎቹን ፡ አስፈራራቸው ። እነሱም ፡ አደጋውን ፡ ሠግተው ፡ ያችውልህ ፡ ከበቅሎቹ ፡ ውስጥ ፡ አሉት ። ከዚያ ፡ ደግሞ ፡ ተነሥታ ፡ ስትሮጥ ፡ እሱም ፡ ሲከተል ፡ በጎች ፡ የሚያግዱ ፡ ልጆች ፡ አገኘችና ፡ እናንተ ፡ ልጆች ፡ እባካችሁ ፡ ከዘንዶ ፡ አድኑኝ ፡ አለቻቸው ። እነሱም ፡ ከበጎቹ ፡ ውስጥ ፡ ገብታ ፡ እንድትሸሸግ ፡ አመለከቷት ። እበጎቹ ፡ ውስጥ ፡ ከመግባቷ ፡ ያ ፡ ዘንዶ ፡ ሲሮጥ ፡ መጣና ፡ እናንተ ፡ ልጆች ፡ ዛሬ ፡ ኮልባ ፡ ኮልቢቱን ፡ በታሰዩኝ ፡ ልብ ፡ አድርጉ ፡ አለቻችሁም ፡ እውጣችኋለሁ ፡ እሰለቅጣችኋለሁ ፡ ሲል ፡ ዛተባቸው ። ያች ውልህ ፡ ብለው ፡ ስለ ፡ ገለጹለትም ፡ ወደ ፡ በጎቹ ፡ መካከል ፡ ገባ ፡ አሁንም ፡ ሸሽታ ፡ አጥብቃ ፡ አምራ ፡ ስትሮጥ ፡ አቶ ፡ ዐይጦ ፡ ሰናፈሉን ፡ ባጭር ፡ ታጥቆ ፡ ዐውድማ ፡ ጥሎ ፡ ጤፍ ፡ ሲወቃ ፡ አገኘችውና ፡ አቶ ፡ ዐይጦ ፡ እባክህ ፡ ከዘንዶ ፡ አድነኝ ፡ ብላ ፡ ለመነችው ። ገረድ ፡ ትሆኚኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነዋ ፡ አላት ። እሷም ፡ ተጨንቃለችና ፡ እሺ ፡ እሆንሃለሁ ፡ ብላ ፡ መለሰችለት ። ስለዚህ ፡ በይ ፡ ጥቂት ፡ ሰረፌ ፡ ብሎ ፡ ከጕሬው ፡ አስገብቶ ፡ አስቀመጣትና ፡ ወደ ፡ ጤፍ ፡ ውቂያው ፡ ተመለሰ ። ያም ፡ ዘንዶ ፡ ተከትሎ ፡ ሲምዘገዘግ ፡ ደረሰና ፡ አቶ ፡ ዐይጦ ፡ ኮልባ ፡ ኮልቢቱን ፡ አሳየኝ ፡ ሳልውጥህ ፡ ሳልሰለቅጥህ ፡ አለው ። ታዲያ ፡ ብትውጠኝ ፡ ብትሰለቅጠኝ ፡ ዱብ ፡ እላለሁ ፡ እንጂ ፡ ሴላ ፡ ምን ፡ አሠናለሁ ፡ ብለህ ፡ ነው ፡ አለው ። ስለዚህም ፡ በመልሱ ፡ ተናዶ ፡ ለቀም ፡ አድርጎ ፡ ጕረሠው ።

አቶ ፡ ዐይጦም ፡ እንዳለው ፡ ሁሉ ፡ ከመ ፡ ቅጽበት ፡ ሾለከና ፡ በቂጡ ፡ ዱብ ፡ አለ ። እንዲህ ፡ ከሆነ ፡ ቄይ ፡ ግድ ፡ የለም ፡ አታመልጠኝም ፡ ብሎ ፡ በጭድ ፡ ቂጡን ፡ ጠቅጥቆ ፡ ዋጥ ፡ አደረገው ። አቶ ፡ ዐይጦም ፡ ሳያታይ ፡ ቶሎ ፡ ብሎ ፡ ፊቤውን ፡ ታጥቆ ፡ ነበርና ፡ ከባሕር ፡ ሆዱ ፡ ሲደርስ ፡ ቀዶ ፡ በጕኑ ፡ ወጣ ። ዘንዶው ፡ የዋጣቸውም ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ እንዲሁ ፡ ከሆዱ ፡ ውስጥ ፡ ውልቅ ፡ ውልቅ ፡ አሉ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አቶ ፡ ዐይጦ ፡ ዘንዶውን ፡ ገፎ ፡ ሞራውን ፡ አውጥቶ ፡ ተሸክሞ ፡ ከንጉሡ ፡ ፊት ፡ ቀረበና ፡ ዘራፍ ፡ ያንተ ፡ አሽከር ፡ ያይጥ ፡ አናዳይ ፡ ዘንዶውን ፡ ገዳይ ፡ በማለት ፡ እየተንጐራደደ ፡ ሲፎክር ፡ ምድር ፡ ጠበበችው ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ወኔው ፡ ተቀስቅሶ ፡ ድንፋታው ፡ የጋለ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ጕብዝናውንና ፡ ጀግንነቱን ፡ አይቶ ፡ ንጉሡ ፡ አገር ፡ ልስጥህ ፡ ከብት ፡ ልስጥህ ፡ ልብስ ፡ ልስጥህ ፡ እያለ ፡ ቢያማርጠው ፡ ሁሉንም ፡ አይሆንልኝም ፡ አለው ። እንግዲያው ፡ ምን ፡ ልስጥህ ፡ ልብህ ፡ የፈቀደውን ፡ አንተው ፡ ንገረኝ ፡ ቢለው ፡ ከወፍጮ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ የበቄላ ፡ ጥሬ ፡ አይቶ ፡ ኖሮ ፡ ይህንን ፡ ይስጡኝ ፤ ሌላ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አልፈልግም ፡ አለና ፡ መለሰ ።

ንጉሡም ፡ የባሕሬውን ፡ ትንሽነትና ፡ የጀግንነቱን ፡ ትልቅነት ፡ አይቶ ፡ ተገርሞ ፡ ውይ ፡ ለዚህ ፡ ነው ፡ ይኸንን ፡ ያኽል ፡ የደከምከው ፡ ውሰድ ፡ አለው ። ያመጣውንም ፡ የዘንዶ ፡ ሞራ ፡ ስለ ፡ ግዳዩ ፡ ይዞ ፡ እንዲሄድ ፡ መረቀለት ። አቶ ፡ ዐይጦም ፡ ያለ ፡ መጠን ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ የበቄላውን ፡ ቅንጣት ፡ ተሸክሞ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ተመለሰና ፡ ለዚያች ፡ ከዘንዶ ፡ ላዳናት ፡ ገረድ ፡ እንቺ ፡ ይኸንን ፡ በቄላ ፡ ከክተሽ ፡ ግማሹን ፡ ንፍሮ ፡ ቀቅዪ ፤ ግማሹን ፡ ግን ፡ እንጀራ ፡ ጋግሪ ፡ አላት ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የዕለት ፡ ተግባሩን ፡ ለመፈጸም ፡ ወደ ፡ ሥራው ፡ ተሰማራ ።

እርሷም ፡ እንደ ፡ ታዘዘችው ፡ ከክታ ፡ ግማሹን ፡ በትልቅ ፡ አፍ ላል ፡ ንፍሮ ፡ ጥዳ ፤ ግማሹን ፡ እንጀራ ፡ ልትጋግር ፡ ትፈጭ ፡ ገሥመረች ። ወፍጮዋንም ፡ ጠርጋ ፡ ስታበቃ ፡ እስቲ ፡ ይኸ ፡ ንፍሮዬ ፡ ደርሶ ፡ እንደሆነ ፡ ልየው ፡ ብላ ፡ በጣቧ ፡ ቀዳችው ። ወዲያው ፡ ያችኑ ፡ አንዲቷን ፡ ፍንክች ፡ ብቅ ፡ ስትል ፡ መብሰሉን ፡ ለማወቅ ፡ ብድግ ፡ አድርጋ ፡ ወዳኛ ፡ አገባቻት ። አይ ፡ እንግዲህ ፡ ከበሰለልኝ ፡ ብላ ፡ አጠንፍፋ ፡ ብታየው ፡ ውሃ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ እኽል ፡ አጣችበት ። ስለዚህ ፡ ደነገጠች ፤ የምትሆነውንም ፡ አጣች ፤ እንግዲህ ፡ እንዴት ፡ እደርጋለሁ ፡ በመጡስ ፡ ሰዓት ፡ ምን ፡ አቀርባለሁ ፡ እያለች ፡ እያዘነች ፡ ያንን ፡ የፈጨችውን ፡ ዱቄት ፡ ለማሰናዳትና ፡ ለማቡካት ፡ ወንፈት ፡ አቅርብ ፡ ትንፋ ፡ ገሥመረች ። ዳሩ ፡ ግን ፡ የዱቄቱ ፡ ብናኝ ፡ በፍንጫዋ ፡ ገብቶ ፡ ስላስነጠሳት ፡ ዱቄቱ ፡ በሙሉ ፡ በነነ ።

ሴቲቱም ፡ በየምክንያቱ ፡ ንፍሮውም ፡ እንጀራውም ፡ ስለ ፡ ጠፋ ፡ ምን ፡ መከራ ፡ ይደርስብኝ ፡ ይሆን ፡ በማለት ፡ በሐዘንና ፡ በትካዜ ፡ ተጨበጠች ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አቶ ፡ ዐይጦ ፡ ከዋለበት ፡ ለምሳ ፡ ሲመለስ ፡ እንቺ ፡ እባክሽ ፡ እስቲ ፡ ንፍሮ ፡ ስጪኝ ፡ ርቦኛል ፡ አላት ። ምነው ፡ እሱንማ ፡ እንዳ ዘዙኝ ፡ ከክቼ ፡ በአፍላል ፡ ጥጂ ፡ መብሰልና ፡ አለመብሰሉን ፡ ለማየት ፡ በጣቧ ፡ ቀድቼ ፡ አንዲቷን ፡ ፍንክች ፡ ከቀመስኩ ፡ በኋላ ፡ ባጠነፍፊው ፡ ውሃ ፡ ብቻ ፡ ሆነብኝ ፡ አለችና ፡ ነገረችው ። እንግዲያውስ ፡ ትኩስ ፡ እንጀራ ፡ ስጪኝ ። ምነው ፡ ወፍጮዬን ፡ ጠርጌ ፡ ዱቄቱን ፡ ለማቡካት ፡ በማሰናዳት ፡ ላይ ፡ ሳለሁ ፡ በድንገት ፡ አስነጥሶኝ ፡ ትንፋሽ ፡ አብኖት ፡ ነፋስ ፡ ይዘት ፡ ሄደ ፡ አለችው ።

አቶ ፡ ዐይጦም ፡ ተቄጥቶና ፡ አኩርፎ ፡ ከቤት ፡ ወጥቶ ፡ የተመረቀበትን ፡ የጀግንነቱን ፡ ምስክርና ፡ ምልክት ፡ የሆነውን ፡ ሞራ ፡ ለብሶ ፡ ተጀንኖ ፡ ከደጅ ፡ እድንጋይ ፡ ላይ ፡ ቀጫጭ ፡ አለ ። ገረዲም ፡ ከቤት ፡ ተቀምጣ ፡ ይተዉ ፡ ጭልፊት ፡ ትወስድዎታለች ፡ ይግቡ ፡ አለችው ። እሱ ፡ ግን ፡ አንጀቱ ፡ በንዴት ፡ ተቃጥሏልና ፡ ወርፈሽ ፡ ተቀመጭ ፡ እንኳን ፡ ከጭልፊት ፡ ከዘንዶ ፡ አምልጫለሁ ፡ እያለ ፡ ይዶረር ፡ ይፎክር ፡ ገሥመር ።

ሴቲቱም ፡ እረ ፡ ይተዉ ፡ ይግቡ ፡ አይሆንም ፡ ትወስድዎታለች ፡ እያለች ፡ ስትለፈልፍ ፡ ያች ፡ ጭልፊት ፡ መጣችና ፡ ዠሮ ፡ ግንዱን ፡ ብላ ፡ ይዛው ፡ ሄደች ። እሱም ፡ ተጣራና ፡ እረ ፡ ተይ ፡ ዱላዬን ፡ አቀብይኝ ፡ አላት ። የሰንበሌጡን ፡ ነው ፡ የንቧጮውን ፡ አለችው ። እረ ፡ ተይ ፡ አቀብይኝ ፡ በማለት ፡ ተቄጣና ፡ ቱናገራት ። እሷም ፡ የጉሎውን ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ የሙጃውን ፡ ስትል ፡ ጭልፊቷ ፡ ይዛው ፡ ራቀች ። ከዚም ፡ በኋላ ፡ ተይው ፤ ተይው ፡ አርቃ ፡ ወስዳኛለች ፡ አለና ፡ ጭልፊቷ ፡ ተሸክማው ፡ ስትሄድ ፡ ሰማሽ ፡ ወይዘሮ ፡ ጭልፊት ፡ እንግዲህ ፡ እደራሽን ፡ ከጠራ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ እንጂ ፡ ከአብ ፡ ላይ ፡ አትብሊኝ ፡ በማለት ፡ ለመናት ። ደግሞ ፡ አንተ ፡ እንዳልክ ፡ ነው ፡ አለችና ፡ ከአብ ፡ ላይ ፡ ይዛው ፡ ቀጫጭ ፡ ስትል ፡ እመለጣትና ፡ ከጦሬ ፡ ውስጥ ፡ ጥልቅ ፡ ብሎ ፡ ድኖ ፡ ተመልሶ ፡ ከቤቱ ፡ ገብቶ ፡ በደኅና ፡ ኖረ ፡ ይባላል ።

፠ ያልወለደ ፡ አጋድሞ ፡ አረደ ፡ ክፉ ፡ ሥራው ፡ ይከታተለዋል ። ጨካኝና ፡ ጨለ ፡ መውጫ ፡ አያጣም ፡ ማለት ፡ ይህ ፡ ነው ።

እግዜር ፡ ሞት ፡ ክረምትና ማያ_ሪያ ፡ እንደ ፡ ለመኑ ።

እግዜር ፡ ክረምት ፡ ሞት ፡ ሦስቱ ፡ በንድነት ፡ ሲጓዙ ፡ ውለው ፡ ስለ ፡ መሸባቸው ፡ ካንድ ፡ ሰው ፡ ቤት ፡ ሄዱና ፡ እግዜር ፡ ቤቶች ፡ እንዴት ፡ ዋላ ችሁ ፡ አለ ። ሰውዬውም ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ዋልክ ፡ በማለት ፡ መለሰለት ። እባክችሁ የመሸብን ፡ መንገደኞች ፡ ነንና ፡ አውራ ፡ እንዳይበላን ፡ አሳድሩን ፡ ብሎ ፡ ለመነ ። አንተ ፡ ማነህ ፡ ከወዴት ፡ መጥተ ሃል ፡ ሲል ፡ ባለቤቱ ፡ ጠየቀ ። እሱም ፡ እኔ ፡ እግዜር ፡ ነኝ ፡ አለው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ያ ፡ ሰው ፡ ከተቀመጠበት ፡ ብድግ ፡ አለና ፡ ሽመሉን ፡ መዘ ፡ አንተ ፡ አድላዊ ፡ አንዱን ፡ ጌታ ፡ አንዱን ፡ ድኻ ፡ አንዱን ፡ በሽተኛ ፡ አንዱን ፡ ጤነኛ ፡ የምታደርግ ፤ ደግሞ ፡ አንተ ፡ ባለውለታ ፡ ሆንክና ፡ ነው ፡ ከቤቱ ፡ መጥተህ ፡ አሳድሩኝ ፡ የምትለው ፡ በል ፡ አሁን ፡ ቶሎ ፡ ብለህ ፡ ከደጇ ፡ አትሄድም ፤ የመጣኸው ፡ ይህንን ፡ ለፍቼ ፡ ያገኘሁትን ፡ ሀብቴን ፡ ልታጠፋ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እውነት ፡ አንተ ፡ ማደሪያ ፡ ተቸግረህ ፡ ነውን ፤ ዛሬ ፡ አሳር ፡ ሰይመጣ ፡ ፈጠን ፡ ብለህ ፡ ጥፋልኝ ፡ አለው ። እግዜርም ፡ እያዘነ ፡ እየተከዘ ፡ እኔንስ ፡ አባረሩኝ ፡ እስቲ ፡ አንተን ፡ እሺ ፡ ቢሉህ ፡ ለምናቸው ፡ ብሎ ፡ ክረምትን ፡ ላከው ።

ክረምትም ፡ የዚህ ፡ ቤቶች ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ዋላችሁ ፡ የመሸብን ፡ መን ገደኞች ፡ ነንና ፡ አሳድሩን ፡ ብሎ ፡ ለመነ ። ያም ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ልማዱ ፡ እንተ ፡ ማነህ ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ። እኔ ፡ ክረምት ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ ቢመልስለት ፡ ተናደደ ፡ አረረ ፡ ጨሰ ፡ አንተማ ፡ በንዱ ፡ አገር ፡ የምሕረት ፡ ዝናብ ፡ ታዘ ንባለህ ፤ ደግሞ ፡ በሌላው ፡ አገር ፡ በረዶና ፡ መብረቅ ፡ እያወረድክ ፡ አዝ መራው ፡ ከብቱ ፡ እንደ ፡ ዋለ ፡ ይቀራል ። አንዱን ፡ አገር ፡ በልግ ፡ እንዲ ሆን ፡ ታደርግና ፡ አንዱን ፡ ደግሞ ፡ ጠብታ ፡ ዝናም ፡ ነፍገህ ፡ ታደርቀዋለህ ፤ ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ሰዉንም ፡ ከብቱንም ፡ በውሃ ፡ ጥም ፡ በረኃብ ፡ ትፈጃ ለህ ፤ አንተ ፡ ሁሉን ፡ የምታጠቃ ፡ ወንበዴ ፡ ምን ፡ ለማድረግ ፡ ነው ፡ ከደጇ ፡ የመጣኸው ፡ ብሎ ፡ አዋርዶና ፡ ገላምጦ ፡ አባረረው ።

ክረምትም ፡ የደረሰበትን ፡ ዘለፋና ፡ ተግሣጽ ፡ ለጓደኞቹ ፡ ገልጾ ፡ ነገራቸው ። ታዲያ ፡ እዚህ ፡ ተቀምጠን ፡ ሽብ ፡ ይበላን ፤ እስቲ ፡ እባ ክህ ፡ አንተ ፡ ሂድና ፡ ለምን ፡ ብሎ ፡ ሞትን ፡ አዘዘው ። እሱም ፡ አን ተን ፡ ፈጣሪውን ፡ እግዜርን ፡ ሰውነቱን ፡ ከመከራ ፡ የምታድነውን ፡ እንቢ ፡ በማለት ፡ አዋርዶና ፡ ገላምጦ ፡ ያባረረ ፡ አንተንም ፡ ክረምትን ፡ እኽል ፡ የምታበቅልለትን ፡ የሚጠጣውን ፡ ውሃ ፡ የምታፈልቅለትን ፡ የሰደበና ፡ ያባረረ ፡ እኔን ፡ መች ፡ እሺ ፡ ይለኛል ። እንዲያውም ፡ ዘመዶ ቹን ፡ እናቱን ፡ አባቱን ፡ ልጆቹን ፡ ገድዬ ፡ አሳድረኝ ፡ ብለው ፡ ደብድቦ ፡ ይገድለኛል ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ ትእዛዙ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ሆነበት ፡ ተን ሥቶ ፡ ሲፈራና ፡ ሲቸር ፡ ሄደና ፡ የዚህ ፡ ቤቶች ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ዋላችሁ ፡ አለ ። ሰውየውም ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ እንዴት ፡ ዋልክ ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ። ወዲያው ፡ እባክችሁ ፡ የመሸብን ፡ መንገደኞች ፡ አሳድሩን ፡ በማለት ፡ ልመና ፡ አቀረበለት ። አንተ ፡ ማነህ ፡ ቢለውም ፡ እኔ ፡ ሞት ፡ ነኝ ፡ አለው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ባለቤቱ ፡ ደንግጦ ፡ ከተቀመጠበት ፡ ብድግ ፡ ብሎ ፡ ነምር ፡ ጌታዬ ፡ ከወዴት ፡ መጣህ ፡ ፍርድህ ፡ እንደ ፡ ሚዛን ፡ የተስ ተካከለ ፡ እንተንማ ፡ ያላሳደርኩ ፡ ማንን ፡ አሳድራለሁ ፤ አንተ ፡ ድኻ ፡ በለጸጋ ፡ ትንሽ ፡ ትልቅ ፡ ሳትል ፡ ሁሉን ፡ እኩል ፡ የምታደርግ ፡ ያስቀ መጥከውን ፡ የማትረሳ ፡ ጌታ ፡ ካንተ ፡ ሌላ ፡ ማንን ፡ ያሳድርል ፡ ብሎ ፡ በትሩን ፡ ተቀብሎ ፡ ከቤት ፡ አስገብቶ ፡ ምንጣፍ ፡ አንጥፎ ፡ ከመልካም ፡ ድንክ ፡ አልጋ ፡ ላይ ፡ አስቀመጠው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሞት ፡ ሁለት ፡ በል ደረቦች ፡ ከውጭ ፡ አሉኝ ፡ አለው ። ምነው ፡ ያንተ ፡ ጓደኞች ፡ ሆነው ፡ እስካሁን ፡ ከውጭ ፡ መቀመጣቸው ፡ ቤቱ ፡ ሰፊ ፡ በል ፡ አሁንም ፡ ጥራ ቸው ፡ ብሎ ፡ በትሕትና ፡ አስታወቀው ። ሞትም ፡ እግዜርንና ፡ ክረምትን ፡ ጠርቶ ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ እንቢ ፡ ካላቸው ፡ ሰው ፡ ቤት ፡ ከስገባቸው ፡ በኋላ ፡ ሰውየው ፡ ተጨንቆ ፡ ሁሉንም ፡ በታላቅ ፡ ከበሬታ ፡ አሳደራቸው ፡ ይባላል ።

※ ማናቸውም ፡ ፍጥረት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ መሆኑ ፡ ቢታወቅም ፡ ይህ ፡ ምሳሌ ፡ ሰውን ፡ ከሞት ፡ የበለጠ ፡ የሚያስፈራው ፡ እንደ ፡ ሌለ ፡ ያስረዳል ።

ስለ ፡ አንድ ፡ መሀይምን ፡ መነኩሴ ፡ ጸሎት ።

አንድ ፡ ትምህርት ፡ የሌላቸው ፡ መሀይምን ፡ መነኩሴ ፡ በንድ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። የዘወትር ፡ ጸሎታቸውም ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ ማለት ፡ ነበረ ። ባቅራቢያቸውም ፡ እጅግ ፡ ሀብታም ፡ የሆኑ ፡ ሦስት ፡ ልጆች ፡ የወለዱ ፡ በልፍ ፡ ሚስት ፡ ያገኙ ፡ ነበር ። ይህም ፡ ባለጸጋ የድኻን ፡ ርስት ፡ በግፍ ፡ የሚነጥቅ ፡ ከደንብ ፡ የወጣ ፡ የብር ፡ ወለድ ፡ የሚቀበል ፡ ተበዳሪዎቹንም ፡ የሚያስርና ፡ የሚያስጨንቅ ፡ ጨካኝ ፡ ሰው ፡ ነበረ ።

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ሞት ፡ የሚያደርስ ፡ ብርቱ ፡ ሕመም ፡ ስላገኘው ፡ ሚስቱ ፡ እኻህን ፡ መነኩሴ ፡ ባሌ ፡ እንዲድን ልኝ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለምኑልኝ ፡ አለቻቸው ። እሳቸውም ፡ እሺ ፡ ብለው ፡ የዘወትር ፡ ጸሎታቸው ፡ ነውና ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ እያሉ ፡ ይጸልዩ ፡ ገ/መር ። ወዲያው ፡ የባሏን ፡ ሥራ ፡ ታውቃለችና ፡ ምንድነው ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ የሚሉት ፡ ደኅና ፡ እድርገው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይለምኑለት ፡ እንጂ ፡ አለቻቸው ። መነኩሴው ፡



ምንድነው ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ የምትሉት ፡ ደኅና ፡ አድርገው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይለምኑለት ፡ እንጂ ።

ግን ፡ ሌላ ፡ ጸሎት ፡ አያውቁምና ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ እያሉ ፡ ሲለምኑለት ፡ ሕመሙ ፡ ጠነከረበትና ፡ ሞተ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሚስቲቱ ፡ እኚህ ፡ ደንቁሮ ፡ መነኩሴ ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ እያሉ ፡ ባሌን ፡ አስገደሉት ፤ ቄይ ፡ እኔም ፡ አደርግላቸዋለሁ ፡ ብላ ፡ ዘዴ ፡

መፈለግ ፡ ያዘች ። አስባም ፡ አልቀረች ፤ ጥቂት ፡ በጥቂት ፡ ምግብ ፡ ትልክላቸው ፡ ገ/መር ። ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ባሌ ፡ የሞተውን ፡ ሞት ፡ ይመኙ ፡ ብላ ፡ በስውር ፡ መርዝ ፡ የተጨመረበት ፡ ምግብ ፡ ላከችላቸው ። እሳቸውም ፡ እምጭውን ፡ አሽከር ፡ አቀጣጥሮ ፡ ስጨርስ ፡ እበላዋለሁና ፡ በል ፡ እዚያ ፡ አጉረውና ፡ ሂድ ፡ አሉት ።

ሦስት ፡ የሚቹ ፡ ልጆች ፡ ለአደን ፡ ወደ ፡ በረሓ ፡ ወርደው ፡ ኑሮ ፤ ሲመለሱ ፡ በጣም ፡ ስለ ፡ ራበቸው ፡ የመነኩሴው ፡ ቤት ፡ እመድረሻቸው ፡ ላይ ፡ ነበርና ፡ ፈጥነው ፡ ከሳቸው ፡ ዘንድ ፡ ገብተው ፡ አባታችን ፡ ሆይ ፡ አጥብቆ ፡ ርቦናልና ፡ የሚበላ ፡ ነገር ፡ ያገኙልናልን ፡ ሲሉ ፡ ጠየቋቸው ። እመቤቲ ፡ የላኩልኝ ፡ ድርጎዬ ፡ እንሆ ፡ ተቀምጧልና ፡ እሱን ፡ ተመገቡ ፡ አሏቸው ።



እመቤቲ ፡ የላኩልኝ ፡ ድርጎዬ ፡ እንሆ ፡ ተቀምጧልና ፡ እሱን ፡ ተመገቡ ፡ አሏቸው ።

ልጆቹም ፡ ተርበው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ፈጥነው ፡ ወስደው ፡ በሉና ፡ ጥቂት ፡ ሳይቁዩ ፡ ሦስቱም ፡ ሞቱ ። ወዲያው ፡ ተጮኸና ፡ እናታቸውም ፡ ሰምታ ፡ ሐዘኗ ፡ የመረረ ፡ ለቅሶዋም ፡ የከበደ ፡ ሆነ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የልጆቹ ፡ ዘመዶች ፡ መነኩሴውን ፡ ለመግደል ፡ ይጋበዙ ፡ ገ/መር ፤ እሷ ፡ ግን ፡ በገዛ ፡ ሥራዬ ፡ ነውና ፡ አትንኳቸው ፡ ብላ ፡ አስጥላ ፡ ከሞት ፡ አተረፈቻቸው ፡ ይባላል ።

። ሥራ ፡ ለሠሪው ፡ እሾኽ ፡ ላጣሪው ፡ ነውና ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ አደጋ ፡ እንዳይደርስብን ፡ በምንሠራው ፡ ሁሉ ፡ ማስተዋልና ፡ መጠንቀቅ ፡ ይገባናል።

የመልካም ፡ ሥራ ፡ ዋጋ ።

ባንድ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡ የሚሠራ ፡ አንድ ፡ ደግ ፡ ንጹሕ ፡ ሰው ፡ ነበረ ። ይህም ፡ ሰው ፡ ገንዘብ ፡ የሌለው ፡ ድኻ ፡ በመሆኑ ፡ ላንድ ፡ ባሰጸጋ ፡ ሎሌነት ፡ አድሮ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ያኽል ፡ ከገለገለ ፡ በኋላ ፡ ጌታው ፡ የድካምህን ፡ ዋጋ ፡ ምን ፡ ልክፈልህ ፡ ሲል ፡ ጠየቀው ።

—አንድ ፡ አሞሌ ፡ ጨው ።

—አንድ ፡ አሞሌ ፡ እንዴት ፡ ይበቃሃል ።

—የእግዚአብሔር ፡ ጸጋና ፡ ረድኤት ፡ ከለበት ፡ አያንሰኝም ።

የተሰጠውን ፡ ተቀብሎ ፡ ወስዶ ፡ ስምንት ፡ ቀን ፡ ከባሕር ፡ ውስጥ ፡ አቄይቶ ፡ ቢያየው ፡ ሚሙቶ ፡ ውሃ ፡ ብቻ ፡ ሆኖ ፡ አገኘው ። አዬ ፡ ይህ ፡ ጨው ፡ የሚሟው ፡ በንጹሕ ፡ ጌታዬን ፡ ሳላገለግለው ፡ እንዲያው ፡ በደባ ፡ ብወስደው ፡ ይሆናል ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ተመልሶ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ሠራ ። የድክሙንም ፡ ዋጋ ፡ አንድ ፡ አሞሌ ፡ ተቀብሎ ፡ እንደ ፡ ፊተኛው ፡ ወስዶ ፡ ስምንት ፡ ቀን ፡ በባሕር ፡ ውስጥ ፡ አቄይቶ ፡ ቢያየው ፡ ሚሙቶ ፡ ሊያልቅ ፡ ትንሽ ፡ ቀርቶት ፡ አገኘው ። አሁንም ፡ በንጹሕ ፡ ባላገለግል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሁሉስ ፡ ይድንልኝ ፡ አልነበረምን ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ተመልሶ ፡ ለዚሁ ፡ ለጌታው ፡ አሽከርነቱን ፡ ቀጠለ ። ባመቱም ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ አንድ ፡ አሞሌ ፡ ተሰጠውና ፡ ከባሕር ፡ ቢጨምረው ፡ ሚሶ ፡ የሚሆነው ፡ ሳይሟሟ ፡ ቀረ ። አሁንም ፡ በደልና ፡ ግፌ ፡ በዝቶ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሁሉስ ፡ ይተርፍልኝ ፡ አልነበረምን ፡ በማለት ፡ ወዳገልግሎቱ ፡ ተመለሰ ። በፈተኛው ፡ ዓመት ፡ ይህንኑ ፡ ደመወዙን ፡ ተቀብሎ ፡ ከባሕር ፡ ቢጨምረው ፡ ግማሹ ፡ ሚሙቶ ፡ ግማሹ ፡ ድኖ ፡ አገኘው ። አሁንም ፡ በደሌ ፡ ባያልቅልኝ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ጌታውን ፡ በቅን ፡ ለመርዳት ፡ ተጣጣረ ፤ ከመትም ፡ በኋላ ፡ ያንኑ ፡ የድክሙን ፡ ዋጋ ፡ ወስዶ ፡ ከውሃ ፡ ውስጥ ፡ ጣለና ፡ በስምንት ፡ ቀኑ ፡ ቢመለስ ፡ የጸነው ፡ ክፍል ፡ በዝቶ ፡ የሟሟው ፡ አንሶ ፡ አየ ። የሰውዮው ፡ ቅን ፡ አገልግሎት ፡ እየቀጠለ ፡ በሄደ ፡ ቍጥር ፡ ያሞሌው ፡ መሟሟት ፡ እየተቀነሰ ፡ ስለሚሄድ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በፈተኛው ፡ ዐይነት ፡ ሲሞክር ፡ ቄይቶ ፡ በሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ ምንጸውን ከውሃው ፡ ቢጥለው ፡ ጨርሶ ፡ ሳይሟሟ ፡ ቀረ ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ይህ ፡ በንጹሕ ፡ ያገለገልኩበት ፡ ጥሩ ፡ ገንዘቤ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ጌታውን ፡ ተሰናብቶ ፡ ጫማውን ፡ ስሞ ፡ ይዞ ፡ አገሩ ፡ ገባ ። ይህንንም ፡ አሞሌ ፡ ሲራራ ፡ ጫኝ ፡ ነጋዴዎች ፡ ወደ ፡ ንግድ ፡ ሲሄዱ ፡ እንዲወስዱለትና ፡ ዕቃ ፡ እንዲገዙለት ፡ ለመናቸው ። እነሱም ፡ ንቀው ፡ በዚህ ፡ ባንድ ፡

ጨው ፡ ምን ፡ እንገዛበታለን ፡ ለመሆኑስ ፡ ምን ፡ ያወጣል ፡ ንገረን ፡ አሉት ። ጌቶቹ ፡ ማናቸውንም ፡ ያገኛችሁትን ፡ እንደወጣ ፡ ሸጣችሁ ፡ ግዙልኝ ፡ ሲል ፡ አሳሰባቸው ። ከንግዱም ፡ አገር ፡ ደርሰው ፡ የሚፈልጉትን ፡ ዕቃ ፡ ሁሉ ፡ ለራሳቸው ፡ ገዝተው ፡ በየአጋሰላቸው ፡ ጭነው ፡ ካበቁ ፡ በኋላ ፡ ሊጓዙ ፡ ሲሉ ፡ ያቺ ፡ የሱ ፡ ጨው ፡ እመደብር ፡ ውስጥ ፡ ሰቃ ፡ ተጭኗት ፡ ተረስታ ፡ ተገኘች ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ነጋዴዎቹም ፡ ተናደው ፡ አሁን ፡ እንግዲህ ፡ ምን ፡ ይሻለናል ፡ ያ ፡ ድኻ ፡ አደራ ፡ ሲለን ፡ ውሎ ፡ ገበያው ፡ ተፈታ ፡ ምን ፡ እንገዛለታለን ፡ እያሉ ፡ እያዘኑ ፡ መንገዳቸውን ፡ ቀጠሉ ።

ጥቂት ፡ ቀንም ፡ እንደ ፡ ተጓዙ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ድመት ፡ ይዞ ፡ በመንገድ ፡ ሲሄድ ፡ አገኙ ። የተሰጣቸውን ፡ አደራ ፡ ሳያፈጽሙ ፡ በመቅረታቸው ፡ ተቈጭተው ፡ ነበርና ፡ ተመከከረው ፡ እኛ ፡ ምን ፡ ቸገረን ፡ ያወጣውን ፡ ያውጣ ፡ ብሎናል ፡ ብለው ፡ በለድመት ፡ ትሸጣለችን ፡ አሉት ።

—ኣምን ፡ ጌቶች ።

—ዋጋዋስ ፡ ምንድነው ፡

—አንድ ፡ አሞሌ ።

እንግዲህ ፡ ይህ ፡ አሞሌ ፡ ከድመት ፡ ሌላ ፡ ሊገዛ ፡ አልቻሰም ፡ ብለው ፡ እሷኑ ፡ ገዝተው ፡ በጥንቃቄ ፡ እንደ ፡ ያዙ ፡ ሲጓዙ ፡ ውለው ፡ ከሰለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ዐይጥ ፡ ከሰበት ፡ አገር ፡ ደረሱ ። ለመስፈርም ፡ ሲዘጋጁ ፡ አይተው ፡ ያገሩ ፡ ሰዎች ፡ ይህ ፡ ቦታ ፡ እጅግ ፡ ዐይጥ ፡ የበዛበት ፡ ነውና ፡ ሰቃችሁን ፡ አያሰድርላችሁም ፤ በሌላው ፡ በኩል ፡ ግን ፡ የሚያሠጋ ፡ ነገር ፡ የለም ፤ አሏቸው ። ነጋዴዎቹም ፡ ሌላ ፡ የሚያሠጋ ፡ ከሌለ ፡ ላይጡስ ፡ መድኀኒቱን ፡ ይዘናል ፡ ብለው ፡ ጭነቱን ፡ አራግፈው ፡ ድመቲቱን ፡ በሰቃው ፡ አጠገብ ፡ አኖሯት ። እሷም ፡ ስትከላከል ፡ እድሬ ፡ ኖሮ ፡ ከበላችው ፡ በስተቀር ፡ የገደለችው ፡ ያይጥ ፡ ሬሳ ፡ ቍጥሩ ፡ የበዛ ፡ ሆኖ ፡ ተገኘ ።

ጧት ፡ ያገሩ ፡ ሰዎች ፡ ነጋዴዎቹ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ እንዳደሩ ፡ ለመጠየቅ ፡ ወደ ፡ ሰፈራቸው ፡ ቢመጡ ፡ ተልክ ፡ ያለፈ ፡ ዐይጥ ፡ ሞቶ ፡ ድመቲቱም ፡ በዚያው ፡ አቅራቢያ ፡ ተኝታ ፡ አዩ ። እንደ ፡ ምን ፡ አድርጎ ፡ ሰቃችሁ ፡ ተርፎላችሁ ፡ አደረ ፤ ይህንስ ፡ ያኽል ፡ ዐይጥ ፡ በምን ፡ ገደላችሁ ፡ ሲሉ ፡ ጠየቋቸው ። ይህቺ ፡ የምታይዋት ፡ ድመት ፡ ነች ፡ እንደዚህ ፡ አድርጋ ፡ የፈጀቻቸው ፡ ብለው ፡ ቢመልሱላቸው ፡ እባክችሁ ፡ ይህቺኑ ፡ ድመት ፡ ሽጡልን ፡ ብለው ፡ ለመኗቸው ። እነሱም ፡ ለጊዜው ፡ ያደረ ፡ ገንዘብ ፡ ናትና ፡ አንሸጥም ፡ ሲሉ ፡ ተከራከሩ ። በመጨረሻው ፡ ልመና ፡ ስለ ፡ በዛ ፡

አንድ ፡ መቶ ፡ የቀንድ ፡ ከብት ፡ ከልሰጣችሁን ፡ አንሸጥም ፡ አሏቸው ። ለዚህ ፡ ነው ፡ ችግሩ ፡ ብለው ፡ በነፍስ ፡ መከፍ ፡ አንዳንድ ፡ ከብት ፡ ቢያዋጡ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ አገኙ ። ስለዚህ ፡ ነጋዴዎቹ ፡ ይህንን ፡ ያክልስ ፡ ከብት ፡ ከተገኘ ፡ ይውሰዱ ፡ ብለው ፡ ሰዉቸውና ፡ እነሱም ፡ ከብቶቹን ፡ ይዘው ፡ አገራቸው ፡ ገቡ ።

እቤታቸው ፡ በደረሱ ፡ ማግስት ፡ ለባለአሞሌው ፡ በሰጠኸን ፡ ጨው ፡ ሁለት ፡ ላሞች ፡ ለሙጠንልሃልኝ ፡ ተቀበለን ፡ አሉት ። በደባ ፡ ለራሳቸው ፡ ያስቀረቸው ፡ ዘጠና ፡ ስምንቱ ፡ ከብቶች ፡ ግን ፡ እግዚኽ ፡ አርኍደው ፡ ወደ ፡ ምሳግ ፡ ተመልሰው ፡ ከተኙ ፡ በኋላ ፡ መነሣት ፡ ተስኗቸው ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ውለው ፡ አደሩ ። በማግስቱ ፡ ነጋዴዎቹ ፡ ተመክክረው ፡ እነዚህ ፡ መነሣት ፡ አቅታቸው ፡ የተኙትም ፡ ከብቶች ፡ ጥሩ ፡ ገንዘብችህ ፡ ናቸውና ፡ ውሰድልን ፡ አሉት ። ያም ፡ ደግ ፡ ሰው ፡ የኔ ፡ አንድ ፡ አሞሌ ፡ ጨው ፡ እንኳን ፡ ይህንን ፡ ሁሉ ፡ ከብትና ፡ ቀድሞ ፡ የወሰድኳቸውንም ፡ ሁለቱንም ፡ አይገዛ ፡ ቅድሙኑ ፡ ቅር ፡ ሊለኝ ፡ ነው ፡ የተቀበል ኳችሁ ፡ ብሎ ፡ አስቸገራቸው ። እነሱም ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውሰድ ፡ ብለው ፡ ቢያስገድዱት ፡ እሺ ፡ ብሎ ፡ ለበቁን ፡ ቄርጠ ፡ ቢመታቸው ፡



ውሰድ ፡ ብለው ፡ ቢያስገድዱት ፡ እሺ ፡ ብሎ ፡ ለበቁን ፡ ቄርጠ ፡ ቢመታቸው ፡ ሁሉም ፡ ተነሡ ።

ሁሉም ፡ ተነሡ ። ይህም ፡ የዋህ ፡ ሰው ፡ ከብቶቹን ፡ በሙሉ ፡ ይዘ ፡ እቤት፡ ገባና ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጸጋና ፡ በረከት ፡ ያለበት ፡ ሰብአዊ ፡ ኑሮውን ፡ ቀጠለ ።

፨ ልጆች ፡ ሆይ ፡ ጓደኞችህ ፡ በኑሮህ ፡ ይቀኑብሃል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ የለጠህን ፡ ጸጋ ፡ ማንም ፡ ሊወስድብህ አይችልም ፡ ተብሎ ፡ በመጽሐፍ ፡ የተጻፈው ፡ ስለዚህ ፡ መሆኑን ፡ አስቡ ።

ስለ ፡ አንድ ፡ መንገድ ፡ የሄደ ፡ ሰው ።

አንድ ፡ ባለትዳር ፡ ሰው ፡ ባንድ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ይኖር ፡ ነበርና ። ከሰለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ከልጆቹና ፡ ከሚስቱ ፡ ከቤተ ፡ ሰቦቹ ፡ ሁሉ ፡ ተሰነባብቶ ፡ ወደ ፡ ሩቅ ፡ አገር ፡ ሄደ ። ብዙ ፡ ወራትም ፡ ካሳለፈ ፡ በኋላ ፡ ወዳ ገሩ ፡ ተመለሰ ። ከቤቱም ፡ አቅራቢያ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ከጎረ ፡ ቤቶቹ ፡ ተገናኝንና ፡ ይነጋገራቸው ፡ ገፖመረ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሦስት ፡ ሰዎች ፡ ከቤቱ ፡ ገብተው ፡ ከሚስቱ ፡ ጋራ ፡ ይጨዋወቱ ፡ ነበርና ፡ ድምፁን ፡ ሰምተው ፡ ይነገጡ ። አንዱ ፡ ተንጠላጥሎ ፡ ወደ ፡ ጣራው ፡ ወጥቶ ፡ እዋልታው ፡ ሥር ፡ ከባላው ፡ ላይ ፡ ተቀመጠ ። ሁለተኛው ፡ ሸሽቶ ፡ ወደ ፡ ጓዳ ፡ ገባ ። ሦስተኛው ፡ ደግሞ ፡ ሮጦ ፡ አልጋ ፡ ውስጥ ፡ ተሸሸገ ።

ባለቤቱም ፡ ናፍቆ ፡ ነበርና ፡ ከቤቱ ፡ ገብቶ ፡ ሚስቱን ፡ ልጆቹንና ፡ ቤተ ፡ ሰቦቹን ፡ ሁሉ ፡ በሙሉ ፡ ስሞ ፡ በደኅና ፡ ስለ ፡ መግባቱ ፡ አንተ ፡ የላይኛው ፡ ሁሉንም ፡ ታውቃለህ ፡ ላንተ ፡ ምን ፡ ይሰወርሃል ፡ እያለ ፡ ፈጣሪውን ፡ ሲያመሰግን ፡ እባላው ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ እረ ፡ እኔ ፡ ብቻ ፡



አንተ ፡ የላይኛው ፡ ሁሉንም ፡ ታውቃለህ ፡ ላንተ ፡ ምን ፡ ይሰወርሃል ፡ እያለ ፡ ፈጣሪውን ፡ ሲያመሰግን ፡ እባላው ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ እረ ፡ እኔ ፡ ብቻ ፡ አይደለሁም ፡ አለ ።

አይደለሁም ፣ አለ ። ከጓዳ ፣ ያለው ፣ ደግሞ ፣ ኋላ ፣ ማንን ፣ ልትጨምር ፣ ነው ፣ ሲል ፣ ተናገረ ። አልጋ ፣ ውስጥ ፣ ገብቶ ፣ የተሸሸገው ፣ ደግሞ ፣ ያስለፍልፍ ፣ ቀምሳችኋል ፣ ወንድሞቼ ፣ እንደኔ ፣ አስችሏችሁ ፣ ዝም ፣ ብትሉ ፣ ምን ፣ ችገራችሁና ፣ የቂጥ ፣ የባጡን ፣ ትለፈልፋላችሁ ፣ ተባብ ለው ፣ ከየተሸሸገበትና ፣ ዙተደበቁበት ፣ አምልጠው ፣ ሄዱ ፣ ይባላል ።

። ጥፋተኛ ፣ ማንም ፣ ሰይከታተለው ፣ ፈራው ፣ ያሳደዋል ። ተረት ፣ የጊዮርጊስን ፣ መገበሪያ ፣ የበላ ፣ ይለፈልፋል ፣ ቢለው ፣ ምነው ፣ እኔ ፣ አለ ፈልፍ ፣ አለ ፣ ይባላል ።

ስለ ፣ ባልና ፣ ሚስት ፣ መተነኪነኮል ።

አንድ ፣ ወንድና ፣ እንዲት ፣ ሴት ፣ በባልና ፣ ሚስትነት ፣ ከኖ ፣ ያለ ፣ ሀብት ፣ አግኝተው ፣ ይኖሩ ፣ ነበር ። ነገር ፣ ግን ፣ ምንም ፣ የትዳራቸው ፣ መሚሚቅ ፣ የሚያስደስት ፣ ቢሆን ፣ ሚስቱ ፣ ሀያጅ ፣ በመሆኗ ፣ ባልዮው ፣ እጅግ ፣ ያዝንና ፣ ይበሳጭ ፣ ነበር ። ከንዴትም ፣ የተነሣ ፣ ለቤቱ ፣ ማሰቡ ፣ ቀረና ፣ ለርሷ ፣ መጥፊያ ፣ ብቻ ፣ ይፈልግ ፣ ገሾመር ።

ልዩ ፣ ልዩ ፣ ብልኀትና ፣ ዘዴ ፣ ከሰበና ፣ ከቀደ ፣ በኋላ ፣ ሀይኔን ፣ አመ መኝ ፣ ብሎ ፣ ተኛ ። ተኝቶም ፣ ሳለ ፣ ሕመሙ ፣ ጠናብኝ ፣ በማለት ፣ ወይኔ ፣ ቀኑ ፣ ልቀቁኝ ፣ ገደል ፣ ልግባ ፣ እያለ ፣ ብዙ ፣ ጊዜ ፣ ቈየ ። ሰም ቹም ፣ መድኀኒት ፣ እናድርግልህ ፣ ሲሉት ፣ ዐይኑ ፣ ቀኑጭ ፣ ብሎ ፣ አለ መታመሙ ፣ እንዳይታወቅበት ፣ ቃሪያ ፣ በርበሬ ፣ ያድፈጠጥና ፣ እዩት ፣ አሁን ፣ ይድን ፣ ይመስላችኋል ፣ እያለ ፣ በማታለል ፣ ብዙ ፣ ጊዜ ፣ ባልጋ ፣ ላይ ፣ ከቈየ ፣ በኋላ ፣ ሲነሣ ፣ ይኸውላችሁ ፣ እንደ ፣ ፊራሁት ፣ ዐይኔን ፣ ከለለኝ ፣ ምንም ፣ አላይም ፣ አለኝ ፣ ይላቸው ፣ ገሾመር ። ሰምቹም ፣ እውነት ፣ መስሏቸው ከቤቱ ፣ እየመጡ ፣ ከመጠየቅ ፣ አላቋረጡም ። ዐይኑም ፣ ጠፋ ፣ ከተባለ ፣ ወዲህ ፣ ጊዜው ፣ እየረዘመ ፣ በመሄዱ ፣ በመጨረሻው ፣ ስዋ ፣ ጠባቂ ፣ ሆኖ ፣ እበር ፣ ላይ ፣ ቀኖጭ ፣ እያለ ፣ ረኽርም ፣ ሸንበቆ ፣

ይዞ ፣ እሽ ፣ እያለ ፣ ዶሮና ፣ ወፍ ፣ መከልከል ፣ ገሾመረ ። ሚስቱንም ፣ ስት ገባና ፣ ስትወጣ ፣ ያላወቀ ፣ በማስመሰል ፣ በዶሮ ፣ መጠበቂያ ፣ እግሯን ፣ መጨርገዱን ፣ አላቋረጠም ።



ረኽርም ፣ሸንበቆ ፣ ይዞ ፣ እሽ ፣ እያለ ፣ ዶሮና ፣ ወፍ ፣ መከልከል ፣ ገሾመረ ።

እንደዚሁ ፣ ሲል ፣ አንድ ፣ ቀን ፣ አንደኛውን ፣ የሚስቱን ፣ ወዳጅ ፣ በሩቅ ፣ ሲመጣ ፣ አየውና ፣ ወደ ፣ ሰውር ፣ መሆኔ ፣ ሰው ፣ አለማየቱ ፣ ጠላቱ ፣ ሲመጣ ፣ ምነው ፣ ጠፋች ፣ ሰቱ ፣ እያለ ፣ የንዴት ፣ እንጉርጉሮ ፣ ሲያደርግ ፣ ያ ፣ ሰው ፣ ደላየው ፣ መስሎት ፣ ባጠገቡ ፣ አልፎ ፣ እቤቱ ፣ ጥልቅ ፣ አለና ፣ ከጋን ፣ ሥር ፣ ተደበቀ ። ይህም ፣ ዐይነ ፣ ስውር ፣ ነኝ ፣ ባይ ፣ ከተቀመጠበት ፣ ደኝኖ ፣ ወደ ፣ ቤቱ ፣ እያዳበሰ ፣ ገባና ፣ ነፍጡን ፣ ከተሰቀለበት ፣ አውርዶ ፣ ወደዚያው ፣ ወደ ፣ በር ፣ ተመለሰ ። በዚህ ፣ ጊዜ ፣ እንዲጋጣሚ ፣ ወንድ ፣ ልጁ ፣ ከረኝነት ፣ ለምሰው ፣ መጣ ። አባትየውም ፣ ልጁ ፣ ሆይ ፣ እስካሁን ፣ ድረስ ፣ የወታደርነት ፣ ሚያ ፣ ሳላስተምርህ ፣ መቅረቴ ፣ ይቈጨኛልና ፣ እስቲ ፣ ከዝ ናሬ ፣ ላይ ፣ ጥይት ፣ አምጣ ፤ በጭፍኔም ፣ ቢሆን ፣ ላሳይህና ፣ ልመት ፣ አለው ። ልጁም ፣ አባቱ ፣ እንዳዘዘው ፣ እቤት ፣ ገብቶ ፣ ጥይቱን ፣ አመጣለት ። ደግሞ ፣ ለጠመንጃው ፣ ማስደገፊያ ፣ የሚሆን ፣ ነገር ፣ አምጣ ፣ አለው ። እሱም ፣ መቀጫ ፣ ስላቀረበለት ፣ መሣሪያውን ፣ ከዚያ ፣ ላይ ፣ አስደግፎ ፣ ማነጣጠር ፣ ያስተምረው ፣ ገሾመር ። በመጨረሻው ፣ ዐላማው ፣ ልክ ፣ በገባህ ፣ ጊዜ ፣ ስትስበው ፣ ትመታለህ ፣ አለና ፣ ይህ ፣ ዐይነ ፣ ስውር ፣ ነኝ ፣ ያለ ፣ ሰው ፣ በልጁ ፣ ጣት ፣ ላይ ፣ የርሱን ፣ ደርበ ፣ ቃታውን ፣ ሰብ ፣ ቢያደርግ ፣ የተሸሸ ገውን ፣ ሰው ፣ ከነጋኑ ፣ መታው ።

—ልጄ ፣ ምን ፣ መታህ ፤

—እረ ፣ አባባ ፣ ሰው ፣ ይመስለኛል ፤

—ከየት ፣ የመጣ ፣ ቀጣፊ ፣ ውሸታም ።

—እስቲ ፣ ና ፣ ዳብስና ፣ እየው ።

—በርግጥ ፣ ሰው ፣ ሞቷል ።

ተው ፣ እነ ፣ ቢለውም ፣ አባባ ፣ ሙት ፣ አንተም ፣ አትሙት ፣ እኔ ፣ ልሙት ፣ ፀፈር ፣ ያድርገኝ ፣ ሰው ፣ ሞቷል ፣ ሲል ፣ መለሰለት ። አባቱም ፣ እንደማያይ ፣ ሰው ፣ እየተደናበረ ፣ ተጠጋናት ቢዳብስ ፣ ሰው ፣ ስለ ፣ ሆነበት ፣ እረ ፣ ጉድ ፣ ፈላብኝ ፣ ለመሆኑ ፣ ማነው ፣ ታው ቀዋለህን ፣ አለው ። ልጁም ፣ አዎን ፣ እገሌ ፣ የሚባለው ፣ ጎረ ፣ ቤታችን ፣ ነው ፣ ሲል ፣ መለሰለት ።



ታታውን ፣ ሳብ ፣ ቢያደርገው ፣ የተደበቀውን ፣ ሰው ፣ ከንጉሥ ፣ መታው ።

ስለዚህ ፣ ጉድ ፣ ጉድ ፣ እያለ ፣ ሲገረም ፣ ሚስቱ ፣ ከሄደችበት ፣ መጣች ። እንደ ፣ ደረሰችም ፣ የወዳጅዋን ፣ ፈሳ ፣ እማጀች ፣ ዓብታ ፣ ባየች ፣ ጊዜ ፣ ኡኡ ፣ ብላ ፣ ጮኸች ። እሱም ፣ እረ ፣ ተይ ፣ በገዛ ፣ ጉድሽ ፣ ትጮኺ ያለሽ ፣ አስቦ ፣ ነገሩን ፣ አይቶ ፣ ለይቶ ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ እረ ፣ እባክሽ ፣ ዝም ፣ በይ ፣ ምን ፣ ነካው ፣ ልትይ ፣ ነው ፣ የገዛ ፣ ልጅሽ ፣ እማራለሁ ፣ ብሎ ፣ ነው ፣ ተኩሶ ፣ የገደለው ፣ አሁን ፣ አንቺ ፣ ኡ ፣ ኡ ፣ ብለሽ ፣ ማንን ፣ ልታሲዝ ፣ ነው ፣ አለና ፣ ተቁጣት ። እሷም ፣ ታዲያ ፣ የዘነ ፣ ሆነ ፣ አሁን ፣ ምን ፣ ማድረግ ፣ ይሻለ ናል ፣ ለዘመዶቹስ ፣ ምን ፣ እመልሳለሁ ፣ ብላ ፣ ምክር ፣ ጠየቀችው ። እሱም ፣ ባለቤቱ ፣ ነፍጡን ፣ ጥረግልኝ ፣ ብሎ ፣ ሰጥቶት ፣ ስለ ፣ ነበረ ፣ ሲወለውል ፣ ወይም ፣ ሲፈትሽ ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ አላወቅነውም ፣ ጥይቱ ፣ በርቆ ፣ ሞቶ ፣ አገኘነው ፣ ብለን ፣ ለዘመዶቹ ፣ እንንገር ፣ አላት ። እሷም ፣ እሺ ፣ ብላ ፣ እንዳዘዛት ፣ ሄዳ ፣ ለዘመዶቹ ፣ አሚሚቱን ፣ አስረዳች ። እግዚአብሔር ፣ ያመጣብንን ፣ ነገር ፣

መቼስ ፣ ምን ፣ እናደርጋለን ፣ ብለው ፣ የሚቹ ፣ ወገኖች ፣ ሁሉ ፣ ተሰብ ስበው ፣ ሬሳቸውን ፣ መስደው ፣ ቀበሩ ።

የሚስቱም ፣ ዘመዶች ፣ እናቲ ፣ አባቲ ፣ ወንድሟም ፣ የደረሰውን ፣ አደጋ ፣ ሰምተው ፣ ከቤት ፣ መጡ ፣ ነገር ፣ ግን ፣ ሬሳው ፣ ወደ ፣ ቤተ ፣ ክርስቲ ያን ፣ ከሄደ ፣ ቁይቶ ፣ ነበርና ፣ መቀበሩን ፣ ስለ ፣ ሰሙ ፣ አማቾቹን ፣ ፀይ ኑን ፣ እንደ ፣ ምን ፣ እንደ ፣ ሰነበተ ፣ ለመጠየቅ ፣ ወደ ፣ ቤት ፣ ሄዱ ። ፀይነ ፣ ስውሩንም ፣ ብቻውን ፣ ኩርምት ፣ ብሎ ፣ ተኝቶ ፣ አገኙት ። ሰላምታም ፣ ከተሰጣጡ ፣ በኋላ ፣ ጥቂት ፣ ዐረፍ ፣ ብለው ፣ እንዲያነጋግሩት ፣ ጠየቃቸው ።

ሚስቱ ፣ ባለቤቷን ፣ ለመግደል ፣ አስባ ፣ በገንፎ ፣ ውስጥ ፣ መርዝ ፣ አድርጋ ፣ በራበህ ፣ ጊዜ ፣ የምትመገበው ፣ አሰናድቼ ፣ ትቼልሃለሁና ፣ እን ድትበላ ፣ ብላው ፣ ነበር ። እሱ ፣ ግን ፣ ልትገድለው ፣ እንደ ፣ ተሰናዳች ፣ ሀሙቆ ፣ ብድሩን ፣ ለመመለስ ፣ ለአማቾቹ ፣ ባለቤቱ ፣ ምሳዩን ፣ አዘጋጅ ታልኝ ፣ ስለ ፣ ሄደች ፣ እባካችሁ ፣ ከንዳ ፣ አምጡና ፣ ብሉ ፣ ብሎ ፣ አጥ ብቆ ፣ ለመናቸው ። ከድካምም ፣ በላይ ፣ ረኃብ ፣ ስለ ፣ ነበረባቸው ፣ ገን ፎውን ፣ አንሥተው ፣ በሉት ። ዳሩ ፣ ግን ፣ ምንም ፣ ያህል ፣ ሳይቈዩ ፣ ሦስቱም ፣ ከዚያው ፣ ከተቀመጡበት ፣ ፍንግል ፣ ፍንግል ፣ ብለው ፣ ቀሩ ፣ በዚህ ፣ ጊዜ ፣ የልቡን ፣ ስላደረሰ ፣ ደስታው ፣ ከልክ ፣ ያለፈ ፣ ሆነ ።



ዳሩ ፣ ግን ፣ ምንም ፣ ያህል ፣ ሳይቈይ ፣ ሦስቱም ፣ ከዚያው ፣ ከተቀመጡበት ፣ ፍንግል ፣ ፍንግል ፣ ብለው ፣ ቀሩ ።

ለቀስተኛው ፣ ሲበተን ፣ ሚስቱ ፣ ወደ ፣ ቤቷ ፣ ብትመጣ ፣ ዘመዶ ቿን ፣ ሞተው ፣ ተዘርረው ፣ አገኘቻቸው ። አሁንም ፣ ቍቁታዋን ፣ ለቀቀ ችው ፣ እሱም ፣ እንደ ፣ ተኛ ፣ ምነው ፣ ምን ፣ ሆንሽ ፣ አላት ። ለነ ፣ አንተ ፣ ገፊያችን ፣ ነህ ፣ ብላ ፣ እሪታዋንና ፣ ቍቁታዋን ፣ እያከታተለች ፣

መንደሩን ፣ አሸበረችው ። ምነው ፣ ምንድነው ፣ ነገሩ ፣ ሲል ፣ ደግሞ ፣ ቢጠይ
ቃት ፣ አባባስ ፣ እማማስ ፣ ጋሽዬስ ፣ ሞተው ፣ የሰምን ፣ አለችው ። በዚህ ፣
ጊዜ ፣ እሱ ፣ በዩ ፣ ገመድ ፣ ስፈጪኝ ፣ ታንቄ ፣ እሞታለሁ ፣ እንግዲህ ፣ ምኑን ፣
ቆምኩት ፣ አላት ። በጣም ፣ ተናዳለችና ፣ ገመዱን ፣ እንሥታ ፣ ሰጠችው ፣
እባክሽ ፣ አይታየኝም ፣ አንቺው ፣ አዘጋጅልኝ ፣ አላት ። እጓሮ ፣ ዘራ ፣
ከመ·ቀጫ ፣ ላይ ፣ ቁማ ፣ እብሰና ፣ ዛፍ ፣ ላይ ፣ በጠለፈች ፣ ጊዜ ፣ በዩ ፣
አንገትሽን ፣ አግብተሽ ፣ ልክ ፣ መሆኑን ፣ ሞክሪልኝ ፣ ሲል ፣ ለመናት ፣
አንገቷንም ፣ ስታገባ ፣ አይቶ ፣ ያንን ፣ መ·ቀጫ ፣ ግፍትር ፣ አደረገው ፣
ስለዚህም ፣ እሷው ፣ ታንቃ ፣ ሞተች ። ።በዚህ ፣ አካኋን ፣ በላጋሮቹን ፣



አንገቷንም ፣ ስታገባ ፣ አይቶ ፣ ያንን ፣ መ·ቀጫ ፣ ግፍትር ፣ አደረገው ፣ ስለዚህም ፣ እሷው ፣ ታንቃ ፣ ሞተች ።

ከጨረሰ ፣ በኋላ ፣ ልጁን ፣ ምራኝ ፣ ብሎ ፣ ወደ ፣ ጠበል ፣ ሄደ ። ከዚያም ፣
አንድ ፣ ሳምንት ፣ ያክልም ፣ እንደ ፣ ተቀመጠ ፣ ልጇ ፣ እረ ፣ ዐይኔ ፣ በራ
ልኝ ፣ እልል ፣ ዘል ፣ አለው ። ደግሞ ፣ በማግስቱ ፣ ዘይኔ ፣ ማረጋገጥ ፣
ያዘ ፣ ያች ፣ ተጭና ፣ የቆመችው ፣ አህያ ፣ እይደለችምን ፣ ብሎ ፣ ልጁን ፣ ጠየ
ቀው ። እውን ፣ ስላለውም ፣ ዘይኔ ፣ በራልኝ ፣ እልል ፣ በል ፣ ብሎ ፣ ወደ ፣
ቤቱ ፣ ተመልሶ ፣ ሌላ ፣ ሚስት ፣ አግብቶ ፣ በሰላም ፣ ኖረ ፣ ይባላል ።

። መልካም ፣ ሴት ፣ ጎይለኛውን ፣ ወንድ ፣ ታገርመዋለች ፣ ክፉ ፣ ሴት ፣
ግን ፣ መልከመ·ን ፣ ወንድ ፣ ብስፈጪና ፣ ተቄጪ ፣ ታደርገዋለች ። መል
ካም ፣ ሴት ፣ ለባሏ ፣ ዘውድ ፣ ናት ፣ የተባለውም ፣ ስለዚህ ፣ ነው ።

ስለ ፡ ሁለት ፡ ቂሎች ፡ ልጅ ፡ መውለድ ።።

ሁለት ፣ ቂሎች ፣ ተጋብተው ፣ ብዙ ፣ ዘመን ፣ አብረው ፣ ከኖሩ ፣ በኋላ ፣
በመጨረሻው ፣ ሴቲቱ ፣ በነሰች ፣ እርግዝናዋም ፣ እየገፋ ፣ ስለ ፣ ሄደ ፣ ባሏ ፣
ሆድሽ ፣ ከብዷል ፣ የመውለጃሽ ፣ ቀን ፣ ሰይደርስ ፣ አይቀርምና ፣ ሄደሽ ፣
ለጠላጆችሽ ፣ ንገሪያቸው ፣ አላት ። እሷም ፣ ተነሥታ ፣ ሄዳ ፣ እምዬ ፣ ይኸው
ልሽ ፣ ልጅ ፣ ልወልድ ፣ ነው ፣ ግን ፣ ሆዴ ፣ በጣም ፣ ስለ ፣ ከበደ ፣ ፍራት ፣
ፍራት ፣ ይሰኛል ፣ እንዴት ፣ እሆን ፣ ይሆን ፣ ብላ ፣ ሰናቷ ፣ አዋየቻት ። ወላ
ጅዋም ፣ ልጂ ፣ አይዞሽ ፣ አትፍሪ ፣ መውለድ ፣ በንቺ ፣ ብቻ ፣ አልተገሥመ
ረም ፣ እስከዚያው ፣ ድረስ ፣ ማታ ፣ ማታ ፣ ሆድሽን ፣ በቅባት ፣ ቀስ ፣ ቀስ ፣
እያልሽ ፣ እሽው ፣ አለችና ፣ አንድ ፣ ቅል ፣ ቅቤ ፣ ሰጠቻት ።

ተመልሳ ፣ ወደ ፣ ቤቷ ፣ ስትሄድ ፣ ያባቷ ፣ መሬት ፣ የጠፍ ፣ ቄረን ፣
መረሬ ፣ ስሰ ፣ ሆነ ፣ ሥንጥቅጥቅ ፣ ብሎ ፣ አየችው ። በዚህ ፣ ጊዜ ፣ እዬ ፣
ጉድ ፣ ዋ ፣ ያባቴ ፣ መሬት ፣ ድርቅ ፣ ይዘኝ ፣ ተሠነጣጥቀሃል ፣ ብላ ፣ የተሰ
ጣትን ፣ ቅቤ ፣ እየዛቀች ፣ የመሬቱን ፣ ንቃቃት ፣ ትቀባ ፣ ገሥመር ። የያዘች
ውም ፣ እንዳለቀ ፣ ጉዘዋን ፣ ቀጥላ ፣ እቤቷ ፣ ስትገባ ፣ ለባሏ ፣ እምዬ ፣ ለሆዴ ፣
መታሸ ፣ አንድ ፣ ቅል ፣ ቅቤ ፣ ሰጥታኝ ፣ ይዣ ፣ ስመጣ ፣ ያባቴ ፣ መሬት ፣
ተሠነጣጥቆ ፣ ባገኘው ፣ ጨርሶ ፣ እንዳይበላሽ ፣ በማለት ፣ ቀባሁት ፣ ብላ ፣
ነገረችው ። እሱም ፣ ዕሰይ ፣ ጐሽ ፣ ደግ ፣ አደረግሽ ፣ አበጀሽ ፣ ብሎ ፣
አመሰገናት ።

ትንሽ ፣ ቀን ፣ ሰንብተው ፣ ወንድ ፣ ልጅ ፣ ወለዳ ፣ ስለዚህም ፣ ሴቲቱ ፣
ባሏን ፣ ሂድና ፣ ለነማማና ፣ ለናበባ ፣ በደኅና ፣ ወንድ ፣ ልጅ ፣ መገላገሌን ፣
የምሥራች ፣ ብለህ ፣ ንገራቸው ፣ ስትል ፣ ላከቸው ። እንዳሰችውም ፣ ሄደ ፣
የምሥራች ፣ ልጅ ፣ አገኘሁ ፣ አላቸው ። እናትና ፣ አባቷም ፣ የልጃቸውን ፣
በደኅና ፣ መገላገል ፣ ከሰሙ ፣ በኋላ ፣ ደስ ፣ ብሏቸው ፣ ደግ ፣ ደግ ፣ ልጇ ፣
ይኸው·ልህ ፣ መውለድ ፣ ደግ ፣ ነው ፣ እንግዲህ ፣ እረኛ ፣ አገኘህ ፣ ዐረፍክ ፣
ሲሉ ፣ መለሱለት ። እሱም ፣ አዎ ፣ እረኛ ፣ በጣም ፣ ቸግሮኝ ፣ ነበር ፣ አለና ፣
ስመ·ን ፣ ግን ፣ ልበለው ፣ ብሎ ፣ ጠየቃቸው ። ሞኝ ፣ ነህ ፣ ልጇ ፣ ምን ፣ አስ
ቸኰለህ ፣ ያደርሰናል ፣ ዋናው ፣ ልጅ ፣ መገኘቱ ፣ ብቻ ፣ ነው ፣ አሉት ።

እሱ ፡ ግን ፡ ሞኝነህ ፡ በልና ፡ ጥራው ፡ ያሉት ፡ መስሎት ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ተመልሶ ፡ ሞኝነህ ፡ ሞኝነህ ፡ ሞኝነህ ፡ እያለ ፡ ሲሄድ ፡ በመንገዱ ፡ ላይ ፡ የገበስ ፡ ገለባ ፡ ያለበት ፡ ውድማ ፡ አጋጠመውና ፡ አቋርጬው ፡ እሄዳለሁ ፡ ሲል ፡ አዳልጦት ፡ ወደቀ ። ከድንጋጤውም ፡ የተነሣ ፡ ሞኝነህ ፡ የሚባለው ፡ ቃል ፡ ጠፋበት ። ወዲያው ፡ ተነሥቶ ፡ ይኸ ፡ ገለባ ፡ የልጄን ፡ ስም ፡ መሰደብኝ ፡ እረ ፡ የታባቱ ፡ አያመጣውም ፡ አይመልሰውም ፡ እያለ ፡



ይህ ፡ ገለባ ፡ የልጄን ፡ ስም ፡ መሰደብኝ ፡ እረ ፡ የታባቱ ፡ አያመጣውም ፡ አይመልሰውም ፡ . . . . .

በያዘው ፡ ዱላ ፡ ሲደበድብ ፡ የገለባው ፡ ባለቤት ፡ ከሩቅ ፡ ሆኖ ፡ አይቶ ፡ ኖሮ ፡ ወደሱ ፡ እየሮጠ ፡ ሄደ ፡ አንተ ፡ ሰውዬ ፡ እረ ፡ በመንግሥት ፡ አምላክ ፡ ለምን ፡ ገለባዬን ፡ ታደቀዋለህ ፡ አለው ። የልጄን ፡ ስም ፡ መስደብኝ ፡ ነዋ ፡ ታዲያ ፡ አሁን ፡ ልተወው ፡ ነው ፡ ሲል ፡ መለሰለት ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ባለቤቱ ፡ ሞኝነህ ፡ ምንድነው ፡ የምትለው ፡ ቢለው ፡ ለካ ፡ አንተ ፡ መስደቡው ፡ ኖሯል ፡ በል ፡ ተወው ፡ ብሎ ፡ ሞኝነህ ፡ ሞኝነህ ፡ እያለ ፡ መንገዱን ፡ ቀጠለ ።

እቤቱ ፡ ሲደርስ ፡ የላከችኝን ፡ ሁሉ ፡ ለቤቶችሽ ፡ አድርሻለሁ ፡ እነሱም ፡ ደግ ፡ ሀረፋችሁ ፡ አረኛ ፡ አገኛችሁ ፡ አሉኝ ፡ ስመንም ፡ ሞኝነህ ፡ ብለው ፡ እውጥውለታል ፡ ብሎ ፡ ነገራት ። ያላቸው ፡ እንደ ፡ ቀንጃ ፡ በረ ፡ ብቻ ፡ ነበርና ፡ ሚስቱ ፡ መልካም ፡ በረያችንን ፡ የሚያግድልን ፡ ተቸግረን ፡ ነበር ፡ ስትል ፡ መልስ ፡ ሰጠችው ። በተወለደ ፡ በሦስተኛ ፡ ቀኑ ፡ ባልየው ፡ በደ ፡ እንግዲህ ፡ ለሞኝነህ ፡ ምሳውን ፡ ስጪውና ፡ በረውን ፡ ያሰማራና ፡ ይጠብቅ ፡

አላት ። ስለዚህም ፡ በማለዳ ፡ ተነሥታ ፡ ሽሮዋን ፡ አንደክድካ ፡ ያደረውን ፡ እንጀራ ፡ በቆለምሽሽ ፡ አድርጋ ፡ ሞኝነህ ፡ እንካ ፡ ምሳህን ፡ ብላና ፡ በሬውን ፡ ጠብቅ ፡ ብላ ፡ አቀረበችለት ። ይህም ፡ ሕፃን ፡ የጪት ፡ ብርድ ፡ ካንጀቱ ፡ ገብቶ ፡ ስላንጠረጠረው ፡ እምሮ ፡ ያለቅስ ፡ ገሞረ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እናቱ ፡ ሕፃኑ ፡ እንጀራውንም ፡ ባለመብላቱ ፡ ተናዳ ፡ አባቱ ፡ ወደሚገኝበት ፡ ሄዳ ፡ እረ ፡ ልጄ ፡ አያለቀሰ ፡ አልበላም ፡ ብሎ ፡ እንቢ ፡ አለ ፡ አለችና ፡ ነገረችው ። አባትየውም ፡ ይህንን ፡ እንደ ፡ ሰማ ፡ ገና ፡ ካዙኑ ፡ ኩርቶ ፡ አልታዘዝም ፡ ያለ ፡ ጥቂት ፡ ቀንማ ፡ ከቂየ ፡ በኋላ ፡ መቼ ፡ ሰው ፡ ጉዳይ ፡ ይላል ፡ ብሎ ፡ ተንደርድሮ ፡ እቤቱ ፡ ቢገባ ፡ እንደ ፡ ተባለው ፡ ሲያለቅስ ፡ አገኘው ። አንተ ፡ ምን ፡ ሆነህ ፡ ነው ፡ የምታለቅሰው ፡ እንጀራው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቀርበልሃል ፡ መቧያውም ፡ ተደርጎልሃል ፡ ለምን ፡ ከብት ፡ ጠብቅ ፡ አሉኝ ፡ በማለት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቀው ፡ መልስ ፡ ስላጣ ፡ እረ ፡ እባክሽ ፡ እንጀራውን ፡ ካጠገቡ ፡ አንሺልኝ ፡ ጠግቦ ፡ እነ ፡ ነው ፡ አላት ። እንደ ፡ ታዘዘችውም ፡ ቆለምሽሹን ፡ አነሣች ።

ወዲያው ፡ አባቱ ፡ በል ፡ ከጠገብክ ፡ አሁን ፡ ተነሣ ፡ ውጣና ፡ በሬውን ፡ ወደ ፡ ስምሪት ፡ ይዘኸው ፡ ሂድ ፡ ሰል ፡ ዘነደለ ፡ ቃል ፡ ቢያዝም ፡ ሕፃኑ ፡ ምንም ፡ መልስ ፡ ሳይመልስለት ፡ ቀረ ። የታባቱ ፡ እረ ፡ ለመሆኑ ፡ እንዴት ፡ ንቆኛል ፡ እኔ ፡ ቆሜ ፡ ስናገረው ፡ መልስ ፡ እንኳን ፡ የማይሰጠኝ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ የተጋደመው ፡ ሲል ፡ በመቄጣት ፡ አንጠል ጥሎ ፡ ወስዶ ፡ በል ፡ ተኳላ ፡ ተኳላ ፡ እየተከተልክ ፡ በቅው ፡ አግድ ፡ የሰው ፡ እኽል ፡ እንዳታስበላና ፡ ስሜን ፡ እንዳታስነካው ፡ ተጠንቀቅ ፡ አለና ፡ ከበሬው ፡ ሾራት ፡ ጋራ ፡ በእጁ ፡ አቆራኝቶ ፡ ለቀቀው ።



በል ፡ ተኳላ ፡ ተኳላ ፡ እየተከተልክ ፡ በቅው ፡ አግድ ፡ የሰው ፡ እኽል ፡ እንዳታስበላና ፡ ስሜን ፡ እንዳታስነካው ፡ ተጠንቀቅ ።

በሬውም ፡ ተጠምቶ ፡ ኖሮ ፡ ከምሳግ ፡ ተነሥቶ ፡ ያንን ፡ ልጅ ፡ በኽረ-ቱ ፡ እንጠልጥሎ ፡ እያወዛወዘ ፡ ወደ ፡ ወንዝ ፡ ወረደ ፡ ውሃው-ንም ፡ ጠጥቶ ፡ በያረኽ ፡ እየለቃቀመ ፡ በየቀጥቋጦው ፡ ሥር ፡ ሲሄድ ፡ ልጁን ፡ ጋሬጣ ፡ ስለ ፡ ያዘው ፡ ከጁ ፡ በቀር ፡ ሰውነቱ ፡ ተገንጥሎ ፡ ቀረና ፡ የማታ ፡ ማታ ፡ ከብት ፡ ሲገባ ፡ እንስሳው ፡ የሕፃኑን ፡ እጅ ፡ በሬ-ራው ፡ እንጠልጥሎ ፡ ከቤት ፡ ገባ ። ወላጆቹም ፡ ከበሬው ፡ ኽራት ፡ ላይ ፡ እጁን ፡ ብቻ ፡ አግኝተው ፡ ሌላውን ፡ ሰውነቱን ፡ ስላጡት ፡ እባ-ትየው ፡ ለምን ፡ ታዘዝኩ ፡ እነ ፡ ነው ፡ አሞርፎ ፡ እጁን ፡ ልክ ፡ መቅ-ረቱ ፡ የታባቱ ፡ ሄዶ ፡ ይሆን ፡ አለና ፡ ተናዶ ፡ ሽመሉን ፡ መዘ ፡ ወደ ፡ አፋፍ ፡ ብቅ ፡ ብሎ ፡ እረ ፡ ሞኝነህ ፡ በማለት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተጣራ ። የሚመልስለትም ፡ ቢያጣ ፡ ወደ ፡ ወንዝ ፡ ወርዶ ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ፈላለገ ፡ እቀጥቋጦ ፡ ሥር ፡ ወድቆ ፡ በፋ ፡ ቀጫጭ ፡ ሞልቶበት ፡ አገኘው ።

ደግሞ ፡ የማንን ፡ ኑግ ፡ ሰርቀህ ፡ ነው ፡ ስትቅምልኝ ፡ የዋልከው ፡ ካሁኑ ፡ ሌብነት ፡ ተማርክ ፡ ብሎ ፡ በያዘው ፡ ዘንግ ፡ ሰውነቱ ፡ ስየብጭው ፡ ተበጣጥሶ ፡ እስቲወድቅ ፡ ድረስ ፡ ደብድቦ ፡ ጥሎት ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ተመ-ለሰ ። ሚስቱም ፡ ማግኘትና ፡ አለማግኘቱን ፡ ስትጠባበቅ ፡ ነበረችና ፡ ሲመጣ ፡ እህ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ሆንክ ፡ አገኘኸውን ፡ ወይስ ፡ እንደ ፡ ጠፋ ፡ ቀረ ፡ አለችው ። እንቺ ፡ ደግሞ ፡ እሱ ፡ መቺ ፡ ለጤናው ፡ ነው ፡ የተወ-ለደው ፡ ከዚህ ፡ ምሳውን ፡ አልበላም ፡ ብሎ ፡ ሄዶ ፡ እዚያ ፡ ሲደርስ ፡ የሰው ፡ ኑግ ፡ ሰርቆ ፡ ሰውም ፡ እንዳያየው ፡ ከቀጥቋጦ ፡ ሥር ፡ ወስዶ ፡ ተሸሽጎ ፡ ሲበላ ፡ በሩቅ ፡ እየሁት ። በነገሩም ፡ በጣም ፡ ስለ ፡ ተናደድኩ ፡ ዝግ ፡ ብዬ ፡ ተጠግቼ ፡ ልቡ ፡ እስኪጠፋ ፡ በያዝኩት ፡ ሽመል ፡ ደብ-ድቤ ፡ ጥዬው ፡ መጣሁ ፡ ብሎ ፡ መለሰላት ።

በማግስቱ ፡ የሚስቱ ፡ እናት ፡ ልጃቸውን ፡ ለመጠየቅ ፡ ያራስ ፡ ጥሬ ፡ ይዘው ፡ መጥተው ፡ እንዴት ፡ ሰንብተሻል ፡ እንኳን ፡ ማርያም ፡ ማረችሽ ፡ ሕፃኑስ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ጥያቄ ፡ እንደ ፡ ገቦመሩ ፡ እዬ ፡ እምዬ ፡ ሞኝነህን ፡ ነው ፡ የሱማ ፡ ታሪክ ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ ትናንትና ፡ በተወለደ ፡ በሦስ-ተኛው ፡ ቀን ፡ በሬያችንን ፡ እንዲጠብቅ ፡ እረኝነት ፡ ብንሰደው ፡ የሰው ፡ ኑግ ፡

ሰርቆ ፡ ሲበላ ፡ ተገኘ ። በዚህም ፡ እባትየው ፡ እጅግ ፡ ተናዶ ፡ ከተሸሸገበት ፡ ደርሶ ፡ ደብድቦ ፡ ጥሎት ፡ መጣ ፡ ብላ ፡ ነገረቻቸው ። እዬ ፡ ጉድ ፡ እዬ ፡ ጉድ ፡ ሁለት ፡ ጥፋ ፡ ከገር ፡ ጥፋ ፡ እንዲህ ፡ ሆነና ፡ ቀረ ፡ ብለው ፡ በጣም ፡ ተናደው ፡ ተመልሰው ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ሄዱ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከገር ፡ ጥፋ ፡ ብለው ፡ ናልና ፡ እንግዲህ ፡ ሥንቃችንን ፡ አሰናጂ ፡ አላት ። እሷም ፡ እንደ ፡ ነገራት ፡ ለመንገዳቸው ፡ የሚሆነውን ፡ ሥንቅ ፡ ሁለት ፡ ላዳን ፡ ገብስ ፡ በሶ ፡ አደረ-ገችና ፡ አሰናድቻለሁ ፡ አለችው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከገር ፡ ለመጥፋት ፡ ጉዟቸውን ፡ ቀጥለው ፡ ሲሄዱ ፡ ሲሄዱ ፡ ውለው ፡ ሰባት ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ ከንድ ፡ ባሕር ፡ አጠገብ ፡ ደረሱ ። እነሱም ፡ ርቧቸው ፡ ነበርና ፡ ውሃ ፡ ከገኘን ፡ በሷችንን ፡ ከዚህ ፡ እናበስብ-ስና ፡ ምሳችንን ፡ እንብላ ፡ ተባብለው ፡ ወደ ፡ ባሕሩ ፡ ተጠግተው ፡ ዐረፉ ። ወዲያውም ፡ ባልዮው ፡ ስልቻቸውን ፡ ፈታና ፡ ሚስቱን ፡ በይ ፡ እባክሽ ፡ ቶሎ ፡ አበስብሽና ፡ በልተን ፡ እንድንሄድ ፡ አላት ። እሷም ፡ ማበስበሻ ፡ ዕቃ ፡ ስላልነበራት ፡ በሶውን ፡ እባሕሩ ፡ ላይ ፡ እየጨመረች ፡ ለማበስበስ ፡ ብትሞክር ፡ ውሃው ፡ በመብዛቱ ፡ እየቀጠነ ፡ የሚጨበጥ ፡ ነገር ፡ ጠፋ ። ወዲያው ፡ ዱቄቱ ፡ አንሶ ፡ እከ ፡ ነው ፡ ያስቸገረው ፡ አለችና ፡ ስልቻውን ፡ በሙሉ ፡ ከባሕሩ ፡ ላይ ፡ ዘረገፈችው ። እሁንም ፡ ምንም ፡ ሳይሆንላት ፡ ቀረ ፤ ለምልክት ፡ ያኽል ፡ ብቻ ፡ ዱቄቱ ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ እየተንሳፈፈ ፡ ተበ-ታትኖ ፡ ጠፋ ። በመጨረሻውም ፡ ባልዮው ፡ እንዴ ፡ በሷችንን ፡ ወስዶ ፡ ጨረሰው ፡ አይደለምን ፡ ግቢና ፡ እውጪው ፡ አላት ። እሷም ፡ የባሏን ፡ ቃል ፡ ሰምታ ፡ ዘላ ፡ ከባሕሩ ፡ ገባች ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አልወጣችም ። ቢያዳም-ጥና ፡ ቢመለከትም ፡ የማትመለስ ፡ መሆኗን ፡ አይቶ ፡ እኔ ፡ እዚህ ፡ በችጋር ፡ ስሞት ፡ እሷ ፡ ብቻዋን ፡ እዚያ ፡ ተሸሽጋ ፡ ትበላለች ፡ መሰለኝ ፡ በደኅናዋ ፡ አልቂየችም ፤ እረ ፡ እባክሽ ፡ ይዘሽ ፡ ውጪ ፡ እያለ ፡ ቢጣራ ፡ ቢጣራ ፡ የሚ-መልስለት ፡ አጣ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በንዴት ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ድንጋይ ፡ አን-ሥቶ ፡ ከባሕሩ ፡ ላይ ፡ ጣለ ፤ ወዲያው ፡ ግንባሯ ፡ ተመቶ ፡ ኖሮ ፡ ደመ ፡ ከውሃው ፡ ላይ ፡ ተናኘ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ባሕሩ ፡ ቀልቶ ፡ በማየቱ ፡ ለካ ፡ እሷ ፡ ድልኩን ፡ ከበሶው ፡ ጋራ ፡ እየበጠበጠች ፡ ትበላለች ፡ እኔ ፡ ብቻ-ዬን ፡ እዚህ ፡ ችጋር ፡ ስሞት ፡ ብሎ ፡ ዘለለና ፡ ከባሕሩ ፡ ውስጥ ፡ ድር ግም ፡ አለ ፡ ይባላል ።

፨ እጅግ ፡ ቂልነት ፡ ያደርሳል ፡ ከሞት ።

የሚስት ፡ ዐይነት ፡ ሦስት ፡ ነው ።

ሚስት ፡ ይስማው ፡ አገር ፡ ትሁን ፡ ባዕ ፡ እናት ፡ ለምኔ ፡ በመባ
ልም ፡ አንዷ ፡ ክንዷ ፡ በጠባይም ፡ በምግባርም ፡ ትለያለች ።

የይስማው ፡ አገር ፡ የንብረት ፡ አያያዝ ፡ ዘዴ ፡ እንደሚከተለው ፡
ነው ፡—

መገሥመሪያ ፡ ጧት ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ገና ፡ ኻመኝታው ፡ ሳይነሣ ፡ አስቀ
ድማ ፡ ብድግ ፡ ትልና ፡ ወደ ፡ ጎረ ፡ ቤት ፡ ሄዳ ፡ አስፈላጊው ፡ ዕቃ ፡ በቤት ፡
እያለ ፡ ዛሬ ፡ ጥንስስ ፡ እጠነስሳለሁና ፡ እባክችሁ ፡ መጠንሰሻ ፡ ገንቦ ፡
ወይም ፡ ዶጮ ፡ አውሱኝ ፡ ብላ ፡ ትጠይቃለች ። በሁለተኛውም ፡ እቤት ፡
ገበር ፥ ምጣድ ፡ እያለ ፡ እንኵሮ ፡ አነኵራለሁና ፡ ምጣድ ፡ አውሱኝ ፡
ትላለች ። ሦስተኛ ፡ በማግስቱ ፡ ውሃ ፡ እምላለሁና ፡ ድፍድፍ ፡ ቅመሱ
ልኝ ፡ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ሲሆነው ፡ ጠላ ፡ እሞላለሁና ፡
ቅናሽ ፡ ቅመሱልኝ ፡ ትላለች ። በመጨረሻውም ፡ አቀጣጥና ፡ ሞልታ ፡
ጋኑን ፡ ትመርግና ፡ ጠላው ፡ ሲደርስ ፡ አስቀድማ ፡ እንደ ፡ ተለመደው ፡
አጎረ ፡ ቤት ፡ ሄዳ ፡ ዛሬ ፡ ጋኑን ፡ ከፍቼ ፡ ጠላ ፡ ስለ ፡ ማነሣ ፡ ኑ ፡ ቅመሱ ፡
ብላ ፡ ትጠራለች ። መገሥመሪያ ፡ ለመጣው ፡ ሁሉ ፡ አንዳንድ ፡ አንከላ ፡
ከሰጠች ፡ በኋላ ፡ የተረፈውን ፡ ከቅራሪው ፡ ደባልታ ፡ ለዚያ ፡ ላቡን ፡ ለሚ
ያፈስ ፡ ባሏ ፡ ታቀርብለታለች ። በጭሩ ፡ የሚያስፈልጋት ፡ ማናቸውም ፡
ዕቃና ፡ መሣሪያ ፡ ተሟልቶ ፡ በቤት ፡ ሲገኝ ፡ አጎረ ፡ ቤት ፡ ሄዳ ፡ ሰታወራና ፡



ዛሬ ፡ ጋኑን ፡ ከፍቼ ፡ ጠላ ፡ ስለማነሣ ፡ ኑ ፡ ቅመሱ ፡

ሰው ፡ ሰይሰማው ፡ ከቶ ፡ የምታደርገው ፡ ነገር ፡ የለም ። ስለዚህም ፡ የዚ
ህች ፡ ዐይነት ፡ ሚስት ፡ በማናቸውም ፡ ረገድ ፡ ሰቤቷና ፡ ለባሏ ፡ ጠንቅ ፡
ከመሆን ፡ በቀር ፡ ጠቃሚነት ፡ የላትም ።

ሁለተኛ ፡ የትሁን ፡ ባዕ ፡ ሥራና ፡ ኑሮ ፡— ትሁን ፡ ባዕ ፡ የምትባ
ለው ፡ ሚስት ፡ ባል ፡ አግብታ ፡ በትዳር ፡ ስትኖር ፡ ልጆች ፡ ትወልዳለች ፡
ባሏ ፡ ጢት ፡ በረቱን ፡ ከፍቶ ፡ በሮቹን ፡ አስወጥቶ ፡ ሲያበላ ፡ እርፍዶ ፡
መሸት ፡ ላያገኝ ፡ ወደ ፡ ሥራው ፡ ሄዶ ፡ አርፍዶ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሲመ
ለስ ፡ እይታ ፡ ከልጆቿ ፡ ጋራ ፡ አልጋ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተጋደመች ፡ ትቄ
ይና ፡ አንደኛውን ፡ ሕፃን ፡ ድብን ፡ አድርጋ ፡ ትቄነጥጠዋለች ፡ እሱም ፡
ያመውና ፡ ምርር ፡ ብሎ ፡ ያለቅሳል ።

ወዲያው ፡ ይኸው ፡ልህ ፡ አፍክን ፡ የምታሚሸበት ፡ እኸል ፡ እንዳላ
ሰናዳ ፡ ልጆቹ ፡ አውከውኝ ፡ እላስነሣ ፡ እሉኝ ፡ ትለዋለች ። ያልታደለ
ው ፡ ሰው ፡ አንጀቱ ፡ እንደ ፡ ተጣጠፈ ፡ ሞፈር ፡ ቀንበሩን ፡ ተሸክሞ ፡
ወደ ፡ እርሻው ፡ ይሄዳል ። ምናልባት ፡ አስባ ፡ እሰናድታ ፡ ይዛልኝ ፡
ትመጣ ፡ ይሆናል ፡ በማለትም ፡ ፊቱን ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ መለኸ ፡ አድርጎ ፡
ሲያርስ ፡ ይውላል ። በቀትርም ፡ የሚመገበው ፡ ሲያጣ ፡ ይደክመውና ፡
ጥቂት ፡ እንዲግጡ ፡ በሮቹን ፡ ፈትቶ ፡ ይሰቅና ፡ ከጥላ ፡ ሥር ፡ ከረፈ ፡ በኋላ ፡
እንደ ፡ ገና ፡ ጠምዶ ፡ ሲያርስ ፡ ያመሻል ። ነገር ፡ ግን ፡ እኸል ፡ ባለማግኘቱ ፡
ይደክምና ፡ ተበሳጭቶ ፡ ገና ፡ ገበሬዎቹ ፡ ሰይፈቱ ፡ በጊዜ ፡ በሮቹን ፡ ይለ
ቃል ፡ ከንዬቱም ፡ የተነሣ ፡ ዛሬ ፡ በዚህ ፡ ጅራፍ ፡ ልባ ፡ እስኪጠፋ ፡
ገርፌ ፡ አባርራለሁ ፡ እያለ ፡ በመፎከር ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ይሄዳል ፡ ነገር ፡ ግን ፡
ሲተኙ ፡ የመምጫውን ፡ ሰዓት ፡ ስለምታውቅ ፡ ምጣዱን ፡ ጥዳ ፡ ጨሱ ፡
ሲግፈጠፈጥ ፡ ልጆቿን ፡ በምድጃው ፡ ዙሪያ ፡ ታደርግና ፡ ሁሉንም ፡ በተራ ፡
ልምዝግ ፡ እያደረገች ፡ ትቄነጥጣቸዋለች ። እነሱም ፡ ሰርር ፡ እያሉ ፡ በሚያ
ለቅሱበት ፡ ጊዜ ፡ አዉትዮው ፡ ሲደርስ ፡ ሥራ ፡ እታሠሩኝ ፡ እንግዲህ ፡
እናንተ ፡ ምን ፡ ልሁነው ፡ ምን ፡ ላድርጋችሁ ፡ ሊጠን ፡ ቀድቼ ፡ ልስጣች
ሁ ፡ . . . . .



ሥራ ፡ እታሠሩኝ ፡ እንግዲህ ፡ እናንተ ፡ ምን ፡ ልሁነው ፡ ምን ፡ ላድርጋችሁ ፡ ሊጠን ፡ ቀድቼ ፡ ልስጣችሁ ፡ . . . . .

እያለች ፡ ስትብሳጭ ፡ ያገኛታል ። ተናዶ ፡ እገርፋለሁ ፡ ብሎ ፡ የነበረውም ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ያዝንና ፡ አሁን ፡ እሷን ፡ ያበረርኩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ልጆቹን ፡ ምን፡ አደርጋቸዋለሁ ፡ ምን ፡ አባቱ ፡ እነሱ ፡ ከሚበደሉና ፡ የእንጀራ ፡ እናት ፡ ፊት ፡ ከሚገርፋቸው ፡ እኔው ፡ ራሴ ፡ ልጐዳ ፡ "ትሁን ፡ በል" ፡ ትቀመጥ ፡ ይልና ፡ እንደ ፡ ዋለ ፡ ምሳውን ፡ ሳይበላ ፡ አጣፊኙን ፡ ተከናንቦ ፡ ለበሮቹና ፡ ለላ ሞቹ ፡ በግርግም ፡ ገለባ ፡ ሊሰጥ ፡ ይወጣል ። ከመሸም ፡ በኋላ ፡ ከብቶቹን ፡ እበረት ፡ አጕሮ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ይገባና ፡ ያገኘውን ፡ አሹቱንም ፡ ምኑንም ፡ በልቶ ፡ እግሩንም ፡ ሳይታጠብ ፡ ከነጭቃውና ፡ ይተኛል ። ዘለዓለም ፡ ሕይወቱ ፡ አለፈ ፡ ድረስ ፡ እንደዚሁ ፡ ሲበሳጭና ፡ ሲገዳ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ የትዳርን ፡ ዐቅድና ፡ ዘዴ ፡ ሳያይ ፡ ይኖራል ።

ሦስተኛ ፡ እናት ፡ ለምኔ ፡— የዚችም ፡ የትዳሯና ፡ የኑሮዋ ፡ ዘዴ ፡ እንደሚከተለው ፡ ይዘረዘራል ። ቀደም ፡ ብላ ፡ ተነሥታ ፡ ለባሏ ፡ መ·ሽት፡ ለቤ ፡ አሰናድታ ፡ ከመኝታው ፡ ቀስቅሳ ፡ ታቀርብለች ። እሱም ፡ የተዘጋጀለትን ፡ እስቲበላ ፡ በረቱን ፡ ከፍታ ፡ የእርሻ ፡ በሮቹን ፡ ወደ ፡ ጓሮ ፡ አዙራ ፡ ታግጥለታለች ። ሞፈሩን ፡ አንሥቶ ፡ ወደ ፡ እርሻው ፡ ለመሄድ ፡ ሲዘጋጅ ፡ ቶሎ ፡ ብላ ፡ ቀምበሩን ፡ ተሸክማ ፡ ትሸኘዋለች ፤ እንደ ፡ ተመ ለሰችም ፡ ላሞቹን ፡ ከጥጆቹ ፡ አገናኝታ ፡ ወተቱን ፡ አልባ ፡ ከበቃች ፡ በኋላ ፡ ከብቶቹን ፡ ከመሰማራታቸው ፡ በፊት ፡ ለረኞቹ ፡ መ·ሽታቸውን ፡ ትሰጣቸዋለች ።

የምሳ ፡ ሰዓት ፡ ሲደርስ ፡ ደግሞ ፡ የባሏን ፡ ምግብ ፡ በደኅና ፡ አገል ግል ፡ ፈትፍታ ፡ የሚጠጣውንም ፡ ጠላ ፡ በቡይት ፡ ይዛ ፡ እርሻው ፡ ድረስ ፡ ትሄዳለች ። እስቲበላ ፡ ድረስም ፡ በሮቹን ፡ ወደ ፡ ወንዝ ፡ ወስዳ ፡ ውሃ ፡ አጠጥታ ፡ ሣር ፡ አግጣ ፡ ታቀርብለታለች ። እሱም ፡ ይህች ፡ መልከም ፡ ሚስቱ ፡ በመጣችለት ፡ ምሰና ፡ መጠጥ ፡ እየተደሰተ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ጠምዶ ፡ ሲያርስ ፡ ያመሸል ። ዕቃዋን ፡ ይዛ ፡ ስትመለስ ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ የምታ ገኘውን ፡ ማገዶ ፡ ትለቃቅምና ፡ ወደ ፡ ቤቷ ፡ ገብታ ፡ መቂያውንና ፡ (መክሰስ) ፡ እራቱን ፡ ታሰናዳለታለች ፤ በተረፈውም ፡ ጊዜ ፡ ስፌት ፡ ትሰ ፋለች ፡ ወይም ፡ ጥጥ ፡ ትሠራለች ።

መሸት፡ ሲል ፡ ታያናም ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ወጥታ ፡ ከመንገድ ፡ ላይ ፡ ቀም በሩን ፡ ከባሏ ፡ ተቀብላ ፡ እያጫወተችው ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ትገባለች ። ለበሮቹ ፡ አስቀድማ ፡ ገለባ ፡ እቅርብ ፡ ወዲያው ፡ ለባሏ ፡ መቂያውን ፡ ከበሬ ፡ ጠላ ፡ ጋራ ፡ ከሰጠችው ፡ በኋላ ፡ የማታ ፡ ሥራዋን ፡ ታሰናዳለች ። ከብቶቹም ፡ ከዱር፡ ሲገቡ ፡ ከረኞቹ ፡ ተቀብላ ፡ የቀንድ ፡ ከብቱን ፡ ከበረት ፡ በግና ፡ ፍየሉን ፡ ከጋጣ፡ ታጕራለች ። ባሏንም ፡ ጥቂት ፡ ዕረፍት ፡ እንዳደረገ ፡ አይታ ፡ ከብቶቹን ፡ አውሬ፡ እንዳይበላቸው ፡ የላላውን ፡ አጥር ፡ ውጣና ፡ አጠባብቅ ፡ ትለዋለች ። እሱም፡ ደስ ፡ እያለው ፡ በጓሮ ፡ ያስቀመጠውን ፡ እረግ ፡ ወይም ፡ ገመድ ፡ በውሃ ፡ ያርስና ፡ የላላውን ፡ አጥርና ፡ በር ፡ ያጠባብቃል ። ጨርሶ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሲገ ቢም ፡ ውሃ ፡ በሰ·ስኮስት ፡ ታሞቅና ፡ እግሩን ፡ አጥባ ፡ በቅባት ፡ ታሽለታለች ። እራት ፡ ከበሉም ፡ በኋላ ፡ ቄጡን ፡ እንጥፋ ፡ ታስተኛውና ፡ የቀረትን ፡ ሥራ፡ ታጠናቅቃለች ። የምትተኛውም ፡ ዐሥር ፡ ልቃቂት ፡ አውጥታ ፡ ስትጨርስ ፡ ነው ።

በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ደስታ ፡ ሲኖሩ ፡ ሳለ ፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ወንድ ዮው ፡ እሑድ ፡ ለት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስሞ ፡ ሲመለስ ፡ በጣም ፡ አድርጎ ፡ የሚወደውን ፡ የዱሮ ፡ ጓደኛውን ፡ አመንገድ ፡ ላይ ፡ አገኘና ፡ ወረፍ ፡ ብለህ፡ ውሃ ፡ ጠጥተህ ፡ ትሄዳለህና ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ እንግባ ፡ ብሎ ፡ ለመነው ። እሱም፡ ሳይግደረደር ፡ እሺ ፡ አለው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ምናልባት ፡ የሚበላውና ፡ የሚ ጠጣው ፡ ይታጣ ፡ ይሆን ፡ እያለ ፡ በልቡ ፡ በመጨነቅ ፡ ሲያወጣ ፡ ሲያወርድ ፡ ከቤቱ ፡ ደረሰና ፡ እንግዳውን ፡ እማደያ ፡ አስቀምጦ ፡ ወደ ፡ ሚስቱ ፡ ሄዶ ፡ እጎቱ ፡ ሆይ ፡ ጉድ ፡ ፈላብን ፡ ዛሬ ፤ የዱሮ ፡ ጓደኛዬን ፡ እመንገድ ፡ አግኝቼ ፡ ስግደረደር ፡ ብጋብዘው ፡ እንቢ ፡ ሳይለኝ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ተከትሎኝ ፡ መጣ ፡ እንግዲህ ፡ ምን ፡ ላድርገው ፡ ላንቺም ፡ ምንም ፡ አልሰጠሁሽ ፡ አላት ። እሷም፡ አይዘህ ፡ ሞልቷል ፡ አንተ ፡ ብቻ ፡ ደኅና ፡ ሁን ፡ እንጂ ፡ ግድ ፡ የለህም ፡ ሂድና ፡ እንግዳውን ፡ አጫውተው ፡ ብላ ፡ ወዲያው ፡ ድስቷን ፡ ጥዳ ፡ ወጡን ፡ አድርሳ ፡ እፍ ፡ ማሚሽ ፡ ሰጠቻቸው ። በየጃቸውም ፡ አንዳንድ ፡ ሽክና ፡ ጠላ ፡ አሲያዘጋቸው ፤ ቡናም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ወቅጣ ፡ ስለምታስቀምጥ ፡ እነሱ ፡ እስቲበሉ ፡ ውሃውን ፡ ጥዳ ፡ አፍልታ ፡ ወዲያው ፡ አመጣች ። ቀጥሎም ፡ አዲስ ፡ የተመረገ ፡ ጠላ ፡ ስለ ፡ ነበራት ፤ በዶጮ ፡ ሞልታ ፡ በሉ ፡ እየተጫወ ታችሁ ፡ ጠጡ ፡ ብላ ፡ አቀረበችላቸው ። ወደ ፡ ደጅም ፡ ወጣ ፡ አለችና ፡ ባሏን ፡ ጠቅሳ ፡ ጠርታ ፡ ለጓደኛህ ፡ አንድ ፡ በግ ፡ አረድለት ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ይደር ፡ አለችው ። እሱም ፡ እሺ ፡ ብሎ ፡ ቃሏን ፡ ተቀብሎ ፡ ከበጎቹ ፡ ማኽል ፡ ደኅና ውን ፡ መ·ክት ፡ መርጦ ፡ አረደ ። ባለቤቲቱም ፡ ቶሎ ፡ ብላ ፡ አፋጥና ፡ ዱለ

ቱን ፡ አዘጋጅታ ፡ ወጡን ፡ በያይነቱ ፡ ከሠራች ፡ በኋላ ፡ ገበታ ፡ ጥላ ፡ እንግዳ ውን ፡ በመልካም ፡ አኳኋን ፡ አንድም ፡ ነገር ፡ ሳይጐድል ፡ ጋበዘችው ። አድሮ ፡ እንዲሄድም ፡ ስለ ፡ ተጠየቀ ፡ የናፍቆቱን ፡ ያክል ፡ ሲጫወት ፡ አምሽቶ ፡ እኩለ ፡ ሌሊት ፡ ሲሆን ፡ ከድንክ ፡ ላይ ፡ ተንጥፎለት ፡ ተኛ ።

ባለቤቲቷም ፡ ቀደም ፡ ብላ ፡ ተነሥታ ፡ ወጡን ፡ ሠርታ ፡ ከሰፋቻ ቸው ፡ አገልግሎች ፡ በንዱ ፡ ሥንቁን ፡ ፈዘጋጀችለት ፤ ስለ ፡ ፅቃውም ፡ ሳይቈጫት ፡ ባይመለስ ፡ ግድ ፡ የለም ፡ ነገ ፡ ሰፍቼ ፡ እተካዋለሁ ፤ አክር ማው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከደጇ ፡ ነው ፡ እቀጨቅለሁ ፡ እያለች ፡ ራሷን ፡ በራሷ ፡ አጽናንታ ፡ መንገድ ፡ በዊት ፡ ነውና ፡ ተነሡ ፡ ብላ ፡ መንገደኛውን ፡ ቀሰቀ ሰች ። ባሏንም ፡ ተነሥተህ ፡ ሽንው ፡ ብላ ፡ አስነሣችው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ላፍ ፡ ማሟሻ ፡ ካሰናዳችው ፡ ምግብ ፡ አቀረበችለት ።



ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ላፍ ፡ ማሟሻ ፡ ካበናዳችው ፡ ምግብ ፡ አቀረ በችለት ።

ለመሄድ ፡ ሲነሣም ፡ ለመሸኘት ፡ እመንገድ ፡ ድረስ ፡ ወጥታ ፡ በሚለያዩበት ፡ ሰዓት ፡ ባሏን ፡ ወደ ፡ ጐን ፡ ጠርታ ፡ ደክሞት ፡ ሲያርፍ ፡ የሚበላው ፡ ምሳ ውን ፡ በዚህ ፡ አገልግል ፡ አድርጌለታለሁ ፡ የሚጠጣውንም ፡ ጠላ ፡ በዚህ ፡ ቅል ፡ ሞልቼለታለሁና ፡ እንኳ ፡ አሲዘው ፡ ብላ ፡ ደብቃ ፡ የያዘችውን ፡ ሰጠ ችው ። አሱም ፡ እጅግ ፡ ተደስቶ ፡ ለእንግዳው ፡ ይሸውልህ ፡ ወንድሜ ፡ ባለ ቤቱ ፡ አስባ ፡ ሥንቅ ፡ አዘጋጅታልሃለች ፡ ብሎ ፡ አገልግሉንና ፡ ቅሉን ፡ ሰጠው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በሁሉም ፡ ፊት ፡ ላይ ፡ የሚነበበው ፡ የደስታ ፡ መጠን ፡ ከቶ ፡ ወሰን ፡ አልነበረውም ።

መንገደኛውንም ፡ ሸኝተው ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ሲመለሱ ፡ ባልዮው ፡ ይህችን ፡ ሴት ፡ በምን ፡ ልመስላት ፡ በእጉቴ ፡ እንዳልመስላት ፡ እጉቴም ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ አታደርግልኝ ፤ በናቴ ፡ ልመስላትን ፡ እይ ፡ እናቴም ፡ ብትሆን ፡ ይህንን ፡ አታደርገውም ፤ በጭራሽ ፡ ተመሳሰይ ፡ የሌላት ፡ ናት ። እረ ፡ የምን ፡ እናት ፡ እንዲያው ፡ በጭሩ ፡ እናት ፡ ለምኔ ፡ ልበላት ፡ እንጂ ፡ እያለ ፡ ሲናገር ፡ እረኞች ፡ ከብት ፡ ሲጠብቁ ፡ ሰምተው ፡ ኖሮ ፡ አመንደር ፡ ወስደው ፡ አቶ ፡ እገሌ ፡ ዛሬ ፡ ሚስቱን ፡ እናት ፡ ለምኔ ፡ ሲል ፡ ሰማነው ፡ ብለው ፡ ተናገሩ ፡ ይባላል ።

፨ በትዳሯ ፡ የቀጠበን ፡ ዘዴ ፡ የማታውቅ ፡ ለባሏ ፡ የማታስብና ፡ የማ ትጨነቅ ፡ ሚስት ፡ እንደ ፡ ሌለች ፡ ያክል ፡ ሆና ፡ ትቈጠራለች ።

በባልና ፡ በሚስት ፡ መካከል ፡ መተሰሰብና ፡ እውነተኛ ፡ ፍቅር ፡ ሲኖር ፡ ግን ፡ ትዳር ፡ እየሞቀ ፡ ጋብቻውም ፡ እየደመቀ ፡ ፍሬያማ ፡ ከመ ሆን ፡ ይደርሳል ።

ወላድ ፡ እንደ ፡ ተመክችና ፡ መክንን ፡ እንደ ፡ ናቀች ።

ሁለት ፡ በዕድሜ ፡ እኩል ፡ የሆኑ ፡ ባልቴቶች ፡ በንድ ፡ ቀበሌ ፡ ይኖሩ፡ ነበር ። ከነዚህም ፡ አንደኛዪቱ ፡ ትዳራቸው ፡ የሞቀና ፡ የደመቀ ፡ ሰባት፡ ወንዶች ፡ ልዶች ፡ ሲኖሯት ፡ ሌላዋ ፡ የዕለት ፡ ራት ፡ የጣት ፡ ቀለበት ፡ ያጣች ፡ ልጅ ፡ የሌላት ፡ መክን ፡ ድኻ ፡ ነበረች ።

ስለዚህም ፡ ባለሰባት ፡ ልጅዋ ፡ ያልወለደችውን ፡ አሮጊት ፡ በተገ ናኙ ፡ ቊጥር ፡ አንድ ፡ እንኳን ፡ ልጅ ፡ የለሽ ፡ ማን ፡ ጦሮ ፡ ይቀብርሻል ፤ ጧሪ ፡ አጥተሽ ፡ ኾብ ፡ ይበላሻል ፡ እንጂ ፡ እያለች ፡ ዘወትር ፡ በሁራትና ፡



እባክሽ ፡ እጉቴ ፡ ይህንን ፡ አትበይ ፡ ቀባሪ ፡ በፈጣሪ ፡ የተባበውን ፡ አትዘንጊ ፡

በትዕቢት ፣ ትናገራት ፣ ነበር ። መካኗ ፣ ግን ፣ በትዕግሥትና ፣ በጽሞና ፣ ቃል ፣ እምነቷን ፣ በፈጣሪዋ ፣ ላይ ፣ አድርጋ ፣ የምትሰጠው ፣ መልስ ፣ እባክሽ ፣ እኅቱ ፣ ይህንን ፣ አትበይ ፣ ቀባሪ ፣ በፈጣሪ ፣ የተባለውን ፣ አት ዘንጊ ፣ የሚል ፣ ነበር ።

ብዙ ፣ ዘመንም ፣ ከቄዩ ፣ በኋላ ፣ ኤርጅናው ፣ በጣም ፣ ስለ ፣ ተጫ ጫናቸው ፣ ሁለቱም ፣ ጉፍጥጥ ፣ ብለው ፣ ከቤት ፣ ዋሉ ። በዚህ ፣ ጊዜ ፣ ወላጂ ፣ እኔንስ ፣ ልጆቼ ፣ ጦረው ፣ ይቀብሩኛል ፣ ብላ ፣ አንደ ፣ ተናገረችው ፣ ሰባቱ ፣ ልጆቿ ፣ ወር ፣ ተራ ፣ ገብተው ፣ ይጦሯት ፣ ገቦመር ። መካኗ ፣ ግን ፣ ጧሪ ፣ ወገን ፣ ስላልነበራት ፣ ለነፍሷ ፣ ያለ ፣ ጥሬውንም ፣ ብስሉ ንም ፣ ትንሽ ፣ ትንሽ ፣ እየተዘከራት ፣ የሌሊት ፣ ቍሩን ፣ የቀን ፣ ሐሩ ሩን ፣ ታግሣ ፣ በደሳሳ ፣ ጕጦ ፣ ተኩራምታ ፣ መኖር ፣ ያዘች ። የሰባቶች ፣ እናት ፣ የምትጦረው ፣ አንድ ፣ ወር ፣ ካንዱ ፣ ልጅዋ ፣ ዘንድ ፣ አንድ ፣ ወር ፣ ደግሞ ፣ ከሌላው ፣ እያለች ፣ እያፈራረቀች ፣ በተራ ፣ ከሰባቱም ፣ ቤት ፣ ነበር ። እነዚህም ፣ ልጆች ፣ ዘየወሩ ፣ መጨረሻ ፣ እየወሰዱ ፣ የሚቀባዘ ሉበት ፣ ካንድ ፣ ትልቅ ፣ ወርካ ፣ ሥር ፣ ነበር ። ስለዚህም ፣ ወር ፣ ተራ ውን ፣ የጨረሰው ፣ ልጅ ፣ እናቱን ፣ አዝሎ ፣ ወስዶ ፣ ከዚያ ፣ ከዛፍ ፣ ሥር ፣ አስቀምጧት ፣ ይመለሳል ። ተከታዩ ፣ በተራው ፣ ቀኑን ፣ ዐውቆ ፣ መጥቶ ፣ አዝሎ ፣ ይወስድና ፣ እቤቱ ፣ ከሰነበታት ፣ በኋላ ፣ በዚያው ፣ በቀኑ ፣ ከተ ለመደው ፣ ቦታ ፣ መልሶ ፣ አስቀምጧት ፣ ይመለሳል ። እንደዚህ ፣ በማ ድረግ ፣ እናታቸውን ፣ በትጋትና ፣ በጥንቃቄ ፣ በመፈራረቅ ፣ ሲጦሩ ፣ ሳለ ፣ አንድ ፣ ቀን ፣ አንደኛው ፣ ልጅ ፣ ወር ፣ ተራውን ፣ ጨርሶ ፣ በዚ ያችው ፣ ዘቀኗ ፣ ከዛፉ ፣ ሥር ፣ አስቀምጧት ፣ ተመለሰ ።

ተቀባዩ ፣ ግን ፣ ጊዜውን ፣ ዘንግቶት ፣ ኖሮ ፣ ሳይሄድ ፣ ዝም ፣ ብሎ ፣ ከቤቱ ፣ አደረ ። ይሁን ፣ እንጂ ፣ በማግስቱ ፣ ጧት ፣ ቢያስታውሰው ፣ ቀኑ ፣ ትላንትና ፣ መሆኑ ፣ ትዝ ፣ ስላለው ፣ ደንግጦ ፣ እናቱን ፣ ለያመጣ ፣ ገሠገሠ ። ነገር ፣ ግን ፣ ኧረ ፣ በልቷት ፣ እጅና ፣ እግሯን ፣ ብቻ ፣ አገኘ ።



እኔ ፣ ቀኑ ፣ ዛሬ ፣ መስሎኝ ፣ ረስቼው ፣ ሳልሄድ ፣ አድሬ ፣ አውን ፣ ትዝ ፣ ብሎኝ ፣ እናታችንን ፣ ለማምጣት ፣ ወደ ፣ ወርካው ፣ ብሮጥ ፣ ኧረ ፣ በልቷት ፣ ደረስኩ ፣ ብሎ ፣ ነገራቸው ። ይህንን ፣ ከባድ ፣ ወሬ ፣ በመስማታቸው ፣ ሁሉም ፣ ደነገጡ ፣ አዘኑም ። አሁን ፣ ታዲያ ፣ ምን ፣ ይበጀናል ፣ የሰባ ቶቹን ፣ እናት ፣ ኧረ ፣ በላት ፣ ተብሎ ፣ ቢሰማ ፣ አገር ፣ ጉድ ፣ አይለንም፤ ለዚህ ፣ መድኀኒቱ ፣ ሰው ፣ ሳያይና ፣ ሳይሰማ ፣ አጎረቤታችን ፣ ያለችውን፣ ድኻ ፣ አሮጊት ፣ አምጥተን ፣ እናታችን ፣ ናት ፣ ብለን ፣ መጦርና ፣ መቅ በር ፣ ነው ፣ ሲሉ ፣ መክረውና ፣ ዘክረው ፣ ተስማሙ ።

አጋር ፣ ወገን ፣ አጥታ ፣ ትሠቃይ ፣ የነበረችውም ፣ ሴት ፣ በወር ፣ ተራ ፣ ስትጦር ፣ ከኖረች ፣ በኋላ ፣ ከዚህ ፣ ዓለም ፣ ተለየች ። በሞተችም ፣ ጊዜ ፣ እነዚያ ፣ ሰባት ፣ ልጆች ፣ እናታችንን ፣ አላቅሱን ፣ ብለው ፣ ዘመድ፣ አዝማዳቸውን ፣ ወገናቸውን ፣ ሁሉ ፣ ከቅርብም ፣ ከሩቅም ፣ አስጠርተው ፣ እምዬ ፣ እምዬ ፣ በማለት ፣ እያለቀሱ ፣ ከሀናቱም ፣ ከያድባራቱ ፣ አልበሳ ቱን ፣ ለብሰው ፣ መጥተው ፣ ሥርዐተ ፣ ፍትሐቱ ፣ ከተፈጸመ ፣ በኋላ ፣ ግብአተ ፣ መሬት ፣ ሆኖ ፣ የተሰበሰበው ፣ አልፍ ፣ አእላፍ ፣ ሕዝብ ፣ ተሰነባብቶ ፣ ተለያየ ፣ ይባላል ።

፠ ስለዚህ ፣ ሳይጠራጠሩ ፣ እምነትን ፣ በእግዚአብሔር ፣ ላይ ፣ ከደረጉ ፣ ዘንድ ፣ ማናቸውም ፣ ነገር ፣ መልክዎ ፣ ፍዳሜ ፣ እንደሚያገኝ ፣ የተረ ጋገጠ ፣ መሆኑን ፣ መገንዘብ ፣ ይገባል ። ቀባሪ ፣ በፈጣሪ ፣ ተብሎ ፣ የሚነገረ ውም ፣ ይህ ፣ ነው ።

ስለ ፡ አንድ ፡ ንጉሥ ፡ የዘመን ፡ ሁናቴ ፡ መጠየቅ ።

በዱሮ ፡ ጊዜ ፡ በንድ ፡ አገር ፡ አንድ ፡ ገናና ፡ ንጉሥ ፡ ነበረ ፡ ይባ ላል ። ይህም ፡ ንጉሥ ፡ በያመቱ ፡ ዘንድሮ ፡ ዘመኑ ፡ ምንድን ፡ ነው ። የበሽታ ፡ የጦር ፡ የረኃብ ፡ ወይስ ፡ የጥጋብ ፡ ነውን ፡ እያለ ፡ የሚጠይቅው ፡ አንድ ፡ ፈላስፋ ፡ ወዳጅ ፡ ነበረው ። ይህም ፡ ሀዋቂ ፡ ማእምር ፡ በያመቱ ፡ በየጊዜው ፡ ሁሉ ፡ የሚሆነውንና ፡ የሚደረገውን ፡ እየገለጸ ፡ ስለሚያስረዳውና ፡ ነገሩም ፡ እየደረሰ ፡ ሕውነት ፡ እየሆነ ፡ ተገኝቶ ፡ ተመ ስግናና ፡ ተከብሮ ፡ ሲኖር ፡ መቼም ፡ ሰው ፡ ከሦኑ ፡ ዘንድ ፡ መሞትና ፡ ዐፈር ፡ መሆን ፡ አይቀርምና ፡ ድንገት ፡ ሳይታሰብ ፡ በሞት ፡ ተለየ ። ከዚ ህም ፡ የተነሣ ፡ የዘመኑን ፡ ሁናቴ ፡ በውቆ ፡ ለንጉሡ ፡ ምሥጢሩን ፡ ገልጠ ፡ የሚነግረው ፡ ሰው ፡ ታጣ ። ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ መኳንን ቱንና ፡ መሰፍንቱን ፡ ያገር ፡ ባላባቶችን ፡ ጕምቲ ፡ ጕምቲ ፡ የሆኑትን ፡ ሽማግሎች ፡ ሰብስቦ ፡ እረ ፡ እናንተ ፡ ሆይ ፡ ይህ ፡ የሞተ ፡ ፈላስፋ ፡ ልጅ ፡ የለውምን ፡ ብሎ ፡ ጠየቃቸው ። እነሱም ፡ በንድ ፡ ቃል ፡ ሆነው ፡ መኖርስ ፡ አለው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ገና ፡ ሕፃን ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ንጉሡ ፡ ያሰቡትን ፡ ወውቆ ፡ ለመናገር ፡ የሚችል ፡ አይመስለንም ፡ እንጂ ፡ አሉ ።

ንጉሡም ፡ በነገሩ ፡ ዘጣም ፡ ተጨንቋልና ፡ ልጅስ ፡ ከለው ፡ ምንም ፡ ሕፃን ፡ ቢሆን ፡ ያዋቂ ፡ ልጅ ፡ ሀዋቂ ፡ ነውና ፡ ሂዳችሁ ፡ ጥሩልኝ ፡ ብሎ ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጠ ። ወዲያው ፡ መልክተኞቹ ፡ ገሥግሠው ፡ ሂደው ፡ ያንን ፡ ልጅ ፡ ንጉሡ ፡ በእግር ፡ በፈረስ ፡ ያስፈልጉሃልና ፡ ተነሥ ፡ ተከ ተለን ፡ ብለው ፡ አስጨንቀው ፡ ወጥረው ፡ ያዙት ። እሱም ፡ ሊገድሉኝ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ መቼ ፡ ለጤና ፡ ነው ፡ የተጠራሁት ፡ በማለትና ፡ በማሰብ ፡ እንባው ፡ በቁመቱ ፡ ሙሉ ፡ እስቲለክ ፡ እያለቀሰና ፡ እየደነፋቀ ፡ ከሰዎቹ ፡ ጋራ ፡ አብሮ ፡ ለመሄድ ፡ ተነሣ ።

እመንገድም ፡ ሲደርስ ፡ እንዲት ፡ ተኵላ ፡ ከጕሬዋ ፡ ብቅ ፡ ብላ ፡ ምን ፡ ሆነህ ፡ ታለቅሣለህ ፡ ብላ ፡ ጠየቀችው ። ንጉሡ ፡ የዘመኑን ፡ ሁናቴ ፡ ሊጠይቁኝ ፡ ስላስጠሩኝ ፡ ከልጅነት ፡ የተነሣ ፡ ዕውቀቱ ፡ በማነሱ ፡ የምመልሰው ፡ መልስ ፡ ሳጣ ፡ ይገድሉኛል ፡ ብዬ ፡ ፈርቼ ፡ ነው ፡ ከዚህስ ፡ የበለጠ ፡ ምን ፡ ነገር ፡ አለ ፡ ሲል ፡ ለጠያቂዋ ፡ መለሰላት ። ተኵላዋም ፡ ነገሩን ፡ በቀጥታ ፡ በአርምሞ ፡ ከሰማች ፡ በኋላ ፡ አይ ፡ ለዚህ ፡ ነው ፡ የምታለ

ቅሰው ፡ አይዘህ ፡ አትሞትም ፤ ንጉሡ ፡ ሲጠይቅህ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ ዘንድሮ ፡ የጦር ፡ ዘመን ፡ ነው ፡ በላቸው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ይህንን ፡ ነግረሃቸው ፡ ስትመለስ ፡ የምበላው ፡ ቸግሮኛልና ፡ ሥጋ ፡ ይዘህልኝ ፡ ና ፡ አለችና ፡ ነጒችው ።

እሱም ፡ በሰጠችው ፡ ምክር ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ መንገዱን ፡ ቀጠለ ። ከቤተ ፡ መንግሥቱም ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ ከንጉሡ ፡ ፊት ፡ ቀርቦ ፡ እጅ ፡ ነሥቶ ፡ ቆመ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ አንተ ፡ እኮ ፡ የዚያ ፡ የሞተው ፡ የወዳጁ ፡ ልጅ ፡ ነህ ፡ ብሎ ፡ እንዳይበባ ፡ ከጽናናው ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ጠራበት ፡ ምክን ያት ፡ ተመልሶ ፡ ዘመኑ ፡ የምን ፡ ዘመን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሚነግረኝ ፡ ሰው ፡ አልተገኘም ፡ አንተ ፡ ምንም ፡ ሕፃን ፡ ብትሆን ፡ ያዋቂ ፡ ልጅ ፡ ነህና ፡ ስለማ ይታጣህ ፡ እንደ ፡ አባትህ ፡ በትክክል ፡ መርምረህ ፡ ገልጠህ ፡ እንድትነ ግረኝ ፡ እፈልጋለሁ ፡ ብሎ ፡ አስረድቶ ፡ ነገረው ። ይህም ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡



አንተ ፡ እኮ ፡ የዚያ ፡ የሞ ተው ፡ የወዳጁ ፡ ልጅ ፡ ነህ ፡ ብሎ ፡ እንዳይበባ ፡ ከጽናናው ፡ በኋላ ፡ መርምረህ ፡ ገልጠህ ፡ እንድትነግረኝ ፡ እፈልጋለሁ ፡

ተመከረው ፡ ቀጥ ፡ ሰጥ ፡ ብሎ ፡ ሳይፈራ ፡ ሳያፍር ፡ ሳይደነግጥ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ ይህ ፡ የዘንድሮው ፡ ዘመን ፡ የጦር ፡ ዘመን ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ። ንጉሡም ፡ ነገሩን ፡ ከሰማው ፡ በኋላ ፡ በታላቁ ፡ አዳራሽ ፡ መሰፍንቱን ፡ መኳንንቱን ፡ የሠገሩን ፡ ባላባቶች ፡ ሽማግሎቹንም ፡ ሰብስቦ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግብዣ ፡ አደረገ ። ልጁንም ፡ እንዳባቱ ፡ አክብሮ ፡ አበላው ። በመጨረሻ ውም ፡ ስለ ፡ መግለጫው ፡ ምስጋና ፡ አድርጎለት ፡ ስንብት ፡ ሰጠው ። ልጁም ፡ ተኵላዋ ፡ አምጣልኝ ፡ ያለችውን ፡ ሥጋ ፡ ትቶ ፡ እንዲያውም ፡ የት ፡ አባቷ ፡ ደግሞ ፡ የእሷ ፡ ሥጋ ፡ ተሸከሚ ፡ ነኝ ፡ መቼ ፡ ሥራ ፡ አጣሁ ፡ ብሎ ፡ በበጎው ፡ ወረታዋ ፡ ፈንታ ፡ ክፉ ፡ አስቦ ፡ ለመግደል ፡ ጦር ፡ በጉያው ፡ ደብቆ ፡ ይዞ ፡ ሄደ ። ተኵላይቱ ፡ ግን ፡ በቁም ፡ ነገሩ ፡ አስቦ ፡ ይዘልኝ ፡ ይመጣል ፡

በማለት ፣ እንሬዋ ፣ አጠገብ ፣ ተቀምጣ ፣ ትጠብቀው ፣ ነበረና ፣ ዝግ ብሎ ፣ ሰላማዊ ፣ መስሎ ፣ ተጠግቶ ፣ ያንን ፣ የያዘውን ፣ ሰር ፣ ወረወረ ባት ፣ በዚህ ፣ ጊዜ ፣ ቶሎ ፣ ብላ ፣ እጅድንድ ፣ ጥልቅ ፣ ብላ ፣ ሳይወጋት ፣ አመለጠችው ። እንደላገኛትም ፣ ባወቀ ፣ ጊዜ ፣ ተነሥቶ ፣ ወዳገሩ ፣ ገባ ።

ያ ፣ ንጉሥ ፣ እንደ ፣ ልማዱ ፣ በመተ ፣ ያንን ፣ ልጅ ፣ ሂዳችሁ ፣ እም ቡልኝ ፣ ሲል ፣ ሹሩሮቹን ፣ ላካቸው ። እነሱም ፣ በታዘዙት ፣ መሠረት ፣ ሄደው ፣ ንጉሥ ፣ የዘመኑን ፣ ቡናቱ ፣ ሊሸይቁህ ፣ ፈልገዋልና ፣ በቶሎ ፣ ተነሣ ፣ በማለት ፣ አሳደፉት ። በዚህ ፣ ጊዜ ፣ ልጁ ፣ ተፈጌነቱ ፤ የሚሆነው ንም ፣ አሳ ። እንግዲህ ፣ እንደ ፣ ተ ፣ እ ፣ ናስው ፣ በርግጡ ፣ ዛሬ ፣ ሞት ፣ አልቀረልኝም ፣ ያች ፣ ተኩላ ፣ እንኳ ፣ እንዳትነግረኝ ፣ ከዚህ ፣ በፊት ፣ በጎ ፣ በሠራችልኝ ፣ ፈንታ ፣ እኔ ፣ ሙለታ ፣ ቢሱ ፣ ለመግደል ፣ በጭከኔ ፣ ሰር ፣ ወርውሬ ፣ ሳትኳት ፣ ከእንግዲህ ፣ ወዲህ ፣ ማን ፣ ያስጠጋኛል ፣ ወዮ ልኝ ፣ እያለ ፣ በማልቀስ ፣ ከሰምዙ ፣ ጋራ ፣ እብዙ ፣ ሲሄድ ፣ ያ ፣ ተኩላ ፣ እንደዘያው ፣ እንደ ፣ ልማዱ ፣ ከሬዋ ፣ አፍ ፣ ላይ ፣ ተቀምጣ ፣ ቂየችው ። ግን ፣ በጭንቅ ፣ ላይ ፣ ስለ ፣ ሆነ ፣ ለቅሶውን ፣ አላቋረጠም ፣ ነበረና ፣ አው ንም ፣ በአፈ ፣ ብእሲ ፣ ምን ፣ ያስለቅስሃል ፣ ምነው ፣ ምን ፣ ነገር ፣ አገኘህ ፣ ስትል ፣ ጠየቀችው ። እሱም ፣ ከዚህ ፣ ቀደም ፣ ባለፈው ፣ ዓመት ፣ ደርሶ በት ፣ የነበረውን ፣ የጭንቀትና ፣ የጥበት ፣ ነገር ፣ መልሶ ፣ ነገራት ። ያችም ፣ አእማሪት ፣ የሆነች ፣ ተኩላ ፣ አይዞህ ፣ አትፍራ ፣ አትደንግጥ ፣ የሞት ፣ ፍርሀትም ፣ በጭራሽ ፣ እይግባህ ፣ ሄደህ ፣ በጠየቀህ ፣ ሰዓት ፣ ዘንድሮ ፣ የበሽታና ፣ የመቅሠፍት ፣ ዘመን ፣ ነውና ፣ ስለ ፣ በሽታው ፣ ብቻ ፣ ተጠን ቀቅ ፣ ብለህ ፣ ንገረው ፤ አንተም ፣ ከንጉሡ ፣ ተሰናብተህ ፣ ወደ ፣ ሀገርህ ፣ በምትመለስበት ፣ ወራት ፣ ሥጋ ፣ ይዘህልኝ ፣ ና ፣ ብላ ፣ በጥብቅ ፣ ከሳሰበ ችው ፣ በኋላ ፣ ሸኘችው ።

ይህም ፣ የፈላስፋ ፣ ልጅ ፣ ከሞት ፣ የሚድንበትን ፣ ብልኅ ፣ ሀዋቂ ፣ ተብሎ ፣ በንጉሡ ፣ በመሰናበቱና ፣ በመኳንንቱ ፣ ፊት ፣ የሚከበርበትን ፣ የምስጋና ፣ ዋጋ ፣ የሚቀበልበትን ፣ የምሥጢር ፣ መፍቻ ፣ ከዚህች ፣ ምክር ፣ ዐዋቂ ፣ ከሆነች ፣ ተኩላ ፣ በማግኘቱ ፣ ተደስቶና ፣ ፈንጥዞ ፣ በተ ላኩት ፣ ጭፍሮች ፣ ታጅቦ ፣ እቤተ ፣ መንግሥቱ ፣ ደረሰ ። መምጣቱም ፣ ለንጉሡ ፣ በተነገረውና ፣ በሰማ ፣ ጊዜ ፣ ከልፍኙ ፣ አስጠርቶ ፣ እህ ፣ ወዲጄ ፣ ይህ ፣ ዘመናችን ፣ የምን ፣ ዘመን ፣ ያመስልሃል ፣ በማለት ፣ ጠየቀው ። "የያዘ ፣ ፈርዛዛ ፣ ነው" ፣ እንደሚባለው ፣ ሁሉ ፣ ልጁም ፣ በተጠየቀ ፣

ጊዜ ፣ ከንጉሡ ፣ ብሩህ ፣ ገጽ ፣ እንዳር ፣ አደግድጎ ፣ ቆሞ ፣ ዘንድሮ ፣ የያዝ ነው ፣ ዘመን ፣ የበሽታ ፣ ጊዜ ፣ ነውና ፣ መጠንቀቅ ፣ ያስፈልጋል ፤ ያለበ ሽታ ፣ ግን ፣ ምንም ፣ የሚጐዳን ፣ ነገር ፣ በዘመኑ ፣ የለበትም ፣ ብሎ ፣ በመኩራራት ፣ መለሰ ።

ንጉሡም ፣ በነገሩ ፣ ደንግጦ ፣ አዘነ ፤ ተከዘ ፤ በመጨረሻውም ፣ እን ደዘያው ፣ ባለፈው ፣ ዓመት ፣ እድርጎት ፣ እንደ ፣ ነበረው ፣ ሁሉ ፣ መሳፍ ንቱ ፣ መኳንንቱ ፣ በተቀመጡበት ፣ ሰራዊቱን ፣ ግብር ፣ ሲያበላ ፣ ልጁንም ፣ በማዕርግ ፣ አስቀምጦ ፣ ጋበዘውና ፣ ወደ ፣ ሀገሩ ፣ እንዲገባ ፣ አሰናበተው ።

ልጁም ፣ ለተኩላዋ ፣ ሥጋ ፣ ይገርልሽ ፣ እመጣለሁ ፣ ያለውን ፣ ቃል ፣ ዐጥፎ ፣ የታባቲ ፣ ደግሞ ፣ ለርሷ ፣ ሥጋ ፤ በእላት ፣ ማቃጠል ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ ብሎ ፣ እሳትና ፣ ጭድ ፣ ይዞ ፣ ሄደ ። ተኩላዋም ፣ የጠየቀችውን ፣ ምግብ ፣ በውነት ፣ ያመጣላት ፣ መስሏት ፣ በደንብ ፣ ተቀምጣ ፣ ትጠብቀው ፣ ነበርና ፣ እሳትና ፣ ጭዱን ፣ ይዞ ፣ ሲንቀረዶድ ፣ አይታና ፣ ተመልክታ ፣ ዘላ ፣ ከሬዋ ፣ ጥልቅ ፣ አለች ። በዚህ ፣ ጊዜ ፣ በጭስ ፣ ታፍና ፣ ትሙት ፣ በማለት ፣ የያዘውን ፣ ጭድ ፣ እጎሬዋ ፣ ውስጥ ፣ ጠቅጥቆ ፣ በእሳት ፣ አያ



የታባቲ ፣ ደግሞ ፣ ለርሷ ፣ ሥጋ ፣ በእሳት ፣ ማቃጠል ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ ብሎ ፣ እሳትና ፣ ጭድ ፣ ይዞ ፣ ሄደ ።

ይዞ ፣ ተነሥቶ ፣ መንገዱን ፣ ቀጠለ ። ነገር ፣ ግን ፣ ተኩላይቱ ፣ በሌላ ፣ በኩል ፣ መውጫ ፣ ቀዳዳ ፣ ስለ ፣ ነበራት ፣ ሾልክ ፣ ከመቃጠልና ፣ ከመ ሞት ፣ ዳነች ።

የበሽታው ፣ ዓመት ፣ አልፎ ፣ አዲሱ ፣ ዘመን ፣ ሲገባ ፣ እንደዘያው ፣ እንደ ፣ ልማዱ ፣ ንጉሡ ፣ ያንን ፣ ልጅ ፣ ሄዶ ፣ የሚጠራ ፣ ባለጭፍራ ፣ ሽምበል ፣ ሰደደ ። መላክተኛውም ፣ ከሚኖርበት ፣ አገር ፣ ደርሶ ፣ ንጉሡ ፣

በፍጥነት ፡ ድረስ ፡ ብለውሃልና ፡ ተነሣ ፡ ታጠቅና ፡ እንሂድ ፡ አለው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ልጁ ፡ ዛፊስ ፡ በርግጡ ፡ ሕይወቴ ፡ የሚያልፍበት ፡ ዘመን ፡ ደረሰ ፤ እንግዲህ ፡ ከቶ ፡ መዳን ፡ የለኝም ፡ ብሎ ፡ ተስፋውን ፡ ፈጽሞ ፡ ቈረጠ ። ያች ፡ ተኵሳ ፡ እንኳ ፡ ከሞት ፡ እንዳታድነኝ ፡ ስለ ፡ በጎ ፡ ሥራዋ ፡ በፊት ፡ በጦር ፡ ሳትኳት ፤ በሁለተኛው ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ጒድጓዷን ፡ ጭድ ፡ ጠቅጥቄ ፡ በጭስ ፡ አፍኜ ፡ ገደልኳት ፤ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ሞት ፡ አልቀረልኝም ፡ እያለ ፡ ማልቀስ ፡ ያዘ ። ትኈዛዝ ፡ ነውና ፡ መሄድ ፡ ግድ ፡ ሆኖበት ፡ ፊቱን ፡ አጥቍሮ ፡ አደምኖ ፡ እያነባ ፡ ሲጓዝ ፡ ሳለ ፤ አሁንም ፡ ያችው ፡ ተኵሳ ፡ ከመንገድ ፡ ዳር ፡ ተቀምጣ ፡ አገኛትና ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ ሁሉ ፡ ምን ፡ ሆንክ ፡ ብላ ፡ ብትጠይቀው ፡ ሳትቃጠል ፡ በመዳኗ ፡ በጣም ፡ ተገርሞ ፡ ስለ ፡ ራሱ ፡ ሁኔታ ፡ ያለበትን ፡ ሥጋት ፡ ነገራት ። ተኵሳይቱም ፡ አይዞህ ፡ አትሞትም ፡ ዘንድሮ ፡ የጥጋብ ፡ ዘመን ፡ ነው ፡ ብለህ ፡ ንገረው ፡ ካለች ፡ በኋላ ፡ በመምጫህ ፡ ሰዓት ፡ ሥጋ ፡ ይዘህልኝ ፡ ና ፡ ስትል ፡ አደራ ፡ ጭምር ፡ አሳሰበችው ።

በጎውን ፡ ውለታ ፡ በክፋት ፡ የሚመልሰውም ፡ ወጣት ፡ ሄዶ ፡ የጥጋብ ፡ ዘመን ፡ ነው ፡ ሲል ፡ ያለድንጋጤና ፡ ማፈር ፡ ከንጉሡ ፡ ዙፋን ፡ ፊት ፡ ቀርቦ ፡ በገሀድ ፡ ተናገረ ። ንጉሡም ፡ የጥጋብ ፡ ዘመን ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ በማብሠሩ ፡ ይኸንኑ ፡ ሕዝቡ ፡ በሙሉ ፡ እንዲሰማው ፡ መለከት ፡ አስነፋ ፤ ንጋሪትም ፡ አስጮኸ ። ሰራዊቱ ፡ በተነገረው ፡ ትንቢት ፡ እንዲደሰት ፡ ከደረገም ፡ በኋላ ፡ ልጁን ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ክብር ፡ ሰጥቶ ፡ ሸልሞ ፡ መሰናበቻውን ፡ መኳንንቱን ፡ የሀገር ፡ ሽማግሌዎቹን ፡ በሙሉ ፡ ሰብስቦ ፡ ደስታ ፡ የተመላበት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግብር ፡ አደረገ ። ወጣቱም ፡ ግብር ፡ ምላሽ ፡ ሲሆን ፡ ለተደረገለት ፡ ክብር ፡ መሬት ፡ ስሞ ፡ ተሰናብቶ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ለመሄድ ፡ ተነሣ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ያች ፡ ተኵሳ ፡ ዘለዓለም ፡ ከጉድ ፡ ከመከረ ፡ ታወጣኛ ለች ፡ እኔ ፡ ግን ፡ ዘወትር ፡ ክፋትና ፡ ተንኰል ፡ ከማሰብ ፡ በቀር ፡ የሠራሁላት ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ የለም ። አስቲ ፡ አሁን ፡ እንኳ ፡ ያንን ፡ ያለችኝን ፡ ልውሰድላት ፡ ብሎ ፡ ሥጋውን ፡ ይዞ ፡ ሄደና ፡ ይኸው ፡ የጠየቀችኝን ፡ ይዤልሽ ፡ መጥቻለሁ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አንቺ ፡ ለኔ ፡ ዘወትር ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ ስትሠሪልኝ ፡ ሳለ ፡ እኔ ፡ ያንቺን ፡ መልካሙን ፡ ሥራ ፡ በክፋት ፡ መልሼ ፡ በፊተኛው ፡ ጊዜ ፡ በጦር ፡ ልገድልሽ ፡ ብወረውር ፡ በቅንነትሽ ፡ አምላክ ፡ ከመሞት ፡ አዳንሽ ፤ ሁለተኛ ፡ ደግሞ ፡ የፊቱ ፡ ጥፋቱና ፡ በደሌ ፡ አልበቃ ፡ ብሎኝ ፡ ጐፈሽን ፡ በጭድ ፡ ጠቅ

ጥቄ ፡ አሳትን ፡ ያኽል ፡ ባለጋራ ፡ ብለቅብሽም ፡ ከደግነትሽና ፡ ከእውነተኛነትሽ ፡ የተነሣ ፡ ሳትቃጠይ ፡ ዳንሽ ፤ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሊሆን ፡ የቻለው ፡ ቅን ፡ ልቡና ፡ ስላለሽ ፡ ነውና ፡ አሁንም ፡ በለፈው ፡ የበደልኩሽን ፡ በደል ፡ ሁሉ ፡ ይቅር ፡ ብለሽ ፡ ዛሬ ፡ ያመጣሁልሽን ፡ ሥጋ ፡ ተቀበይኝ ፡ አላት ።



ባለፈው ፡ የበደልኩሽን ፡ በደል ፡ ሁሉ ፡ ይቅር ፡ ብለሽ ፡ ዛሬ ፡ ያመጣሁልሽን ፡ ሥጋ ፡ ተቀበዪኝ ፡ አላት ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሰማህ ፡ ወንድሜ ፡ ነቃ ፡ ብለህ ፡ አዳምጠኝ ፡ ልንገርህ ። በፊተኛው ፡ ጊዜ ፡ ጠረ ፡ የወረወርክብኝ ፡ ዘመኑ ፡ የጦርነት ፡ ዘመን ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ነው ፤ በሁለተኛው ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ በጭድ ፡ አድርገህ ፡ አሳት ፡ የለቀቅህብኝ ፡ የበሽታ ፡ ዘመን ፡ በመሆኑ ፡ ነው ። አሁን ግን ፡ በሦስተኛው ፡ ጊዜ ፡ ቃሌን ፡ ፈጽመህ ፡ ሥጋውን ፡ ይዘህልኝ ፡ መምጣትህ ፡ ዘመኑ ፡ ጥጋብ ፡ በመሆኑ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እውነት ፡ አንተ ፡ ከቀድሞ ፡ ክፋትህ ፡ ተመልሰህና ፡ ለኔ ፡ አዝነህ ፡ አይደለም ። ከዚህ ፡ ቀድሞም ፡ የበደልኝ ፡ ዘመን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አንተ ፡ አይደለህም ፤ አሁንም፡ የሰጠኝ ፡ ዘመኑ ፡ እንጂ ፡ አንተ ፡ አይደለህም ፤ የሚሰጥም ፡ የሚነሣም ፡ ዘመን ፡ ነው ፤ የሰው ፡ ደግነቱም ፡ ክፋቱም ፡ እንደ ፡ ዘመኑና ፡ እንደ ፡ ጊዜው ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ አንተ ፡ ጥፋት ፡ ወይም ፡ በደል ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ አልሠራህም ፡ ብሳ ፡ የጊዜን ፡ ደግነትና ፡ ክፋት ፡ ትርጓሜ ፡ ገልጣ ፡ ነገረችው ፡ ይበላል ።

፨ የተወደዳችሁ ፡ ወጣቶች ፡ ሆይ ፡ ከናት ፡ ቀን ፡ ይሸላል ፡ የተበለው ፡ ያበቶች ፡ ተረት ፡ ፍሬ ፡ ያለው ፡ በጠነከረ ፡ መሠረት ፡ ላይ ፡ የተቋቋመ ፡ መሆኑን ፡ አስተውሉ ።

ስለ ፡ አንዲት ፡ ልጃገረድ ፡ መታፈኗት ።

አንድ ፡ የሀገር ፡ ቀንደኛ ፡ የሆነ ፡ ትልቅ ፡ ባለጠጋ ፡ ሽማግሌ ፡ ሰው ፡ አንዲት ፡ መልከ ፡ መልካም ፡ ልጃገረድ ፡ ልጅ ፡ ነበረችው ። ልጅቷም ፡ በጣም ፡ ስላደገች ፡ ትልቁ ፡ እየኰራ ፡ ትንሹም ፡ እየፈራ ፡ ጠያቂ ፡ አጥታ ፡ ባባቷ ፡ ቤት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ቁየች ። ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀንም ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ሊያጓቷት ፡ መጡ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አንደኛውን ፡ አስቀድማ ፡ ስለ ፡ ጠባዩ ፡ ስለ ፡ ባሕሬው ፡ ብዙ ፡ ትሰማ ፡ ኖሮ ፡ ይህ ፡ እገ ፡ የሚባለው ፡ ሰው ፡ አይደለምን ፡ ብላ ፡ ጠየቀች ።

ሰዎቹም ፡ እሱ ፡ መሆኑን ፡ አረጋገጡላት ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በሌላ ፡ ቀን ፡ ሁለቱም ፡ ፊላጊዎች ፡ ወደ ፡ አባቷ ፡ በየበኩላቸው ፡ አማላጅ ፡ ልከው ፡ ልጅህን ፡ ስጠን ፡ ብለው ፡ አጥብቀው ፡ ለመኑት ፡ አስቸገሩትም ። አባትዮው ፡ የልጅቱን ፡ አስተያየት ፡ ለመገመትና ፡ ለማወቅ ፡ ሲል ፡ ቀን ፡ ወስኖ ፡ ሁለቱንም ፡ ጠያቂዎች ፡ ጠራቸውና ፡ መርፌና ፡ ክር ፡ ሰጥቶ ፡ እነዚህን ፡ ቁመትና ፡ ወርዳቸው ፡ እኩል ፡ የሆኑ ፡ ሸማዎች ፡ እኩል ፡ ዠምሩና ፡ ቀድሞ ፡ ሰፍቶ ፡ ለጨረሰው ፡ ልጄን ፡ እሰጣለሁ ፡ ብሎ ፡ የፊተና ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጣቸው ። ወዲያው ፡ ሁለቱም ፡ ተወዳዳሪዎች ፡ እንደ ፡ ተባለው ፡ መስፋት ፡ ዠመሩ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ያ ፡ ልጅቱ ፡ በጎለ ፡ ናዋ ፡ ፈቅዳው ፡ የነበረው ፡ ሰው ፡ በረኸዞም ፡ ክር ፡ ይሰፋ ፡ ነበርና ፡ ክሩ ፡ እየተተበተበ ፡ እንዳያስቸግረውና ፡ በፈተናው ፡ እንዳይወድቅበት ፡ አስቦ ፡




እነዚህን ፡ ቁመትና ፡ ወር ዳቸው ፡ እኩል ፡ የሆኑ ፡ ሸማዎች ፡ እኩል ፡ ዠምሩና ፡ ቀድሞ ፡ ሰፍቶ ፡ ለጨረሰው ፡ ልጄን ፡ እሰጣለሁ ፡

ወዲያ ፡ እንደሚሄድ ፡ ሰው ፡ በፊቱ ፡ አንድ ፡ ዕቃ ፡ ይዛ ፡ አለፍ ፡ ስትል ፡ ጠቀስ ፡ አድርጋ ፡ ሰውዬው ፡ ክር ፡ ባጭር ፡ አለችው ። እሱም ፡ ነገሯ ፡ ቶሎ ፡ ገባውና ፡ ያንን ፡ ረዥም ፡ ክር ፡ በጥሶ ፡ ባጭር ፡ ባጭሩ ፡ አድርጎ ፡ ስለ ፡ ሰፋ ፡ ቀድሞ ፡ ለመጨረስ ፡ ቻለ ። ስለዚህም ፡ አባትዮው ፡ ልጅቷን ፡ ላንተ ፡ ሰጥቼሃለሁ ፡ ብሎ ፡ መረቀለትና ፡ አሸናፊው ፡ ጫማ ፡ ስሞ ፡ ሄደ ፡ ይባላል ።

፨ ፍቅር ፡ ያደረበት ፡ ይሉኝታ ፡ አያውቅም ።

የሁለት ፡ ድመቶች ፡ ፍቅርና ፡ ጠብ ።

ሁለት ፡ ድመቶች ፡ በጓደኛነት ፡ ፍቅራቸው ፡ በጣም ፡ የጠነከረ ፡ ሆኖ ፡ ሲኖሩ ፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ረኃብ ፡ ጠንቶባቸው ፡ ምግብ ፡ ለመፈለግ ፡ በሌሊት ፡ ተነሥተው ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ሲንከራተቱ ፡ ከንድ ፡ ባለጸጋ ፡ ቤት ፡ ደረሱ ። ወዲያው ፡ በመስኮት ፡ ዘለው ፡ አንደ ፡ ገቡ ፡ ከገቢታ ፡ ላይ ፡ ሥጋ ፡ ስላገኙ ፡ እጅግ ፡ ተደሰቱው ፡ ዐቅማቸው ፡ በቻለላቸው ፡ መጠን ፡ በየአፋቸው ፡ አንሥተውለት ፡ ተመልሰው ፡ በገቡበት ፡ መስኮት ፡ ወጡ ።



እጅግ ፡ ተደሰተው ፡ በትማቸው ፡ ይቻለላቸው ፡ መጠን ፡ በየአፋቸው ፡ አንሥተውለት ፡ ተመልሰው ፡ በገቡበት ፡ መስኮት ፡ ወጡ ።

ከዚያ ፡ በኋላ ፡ አንደኛው ፡ ድመት ፡ የያዘው ፡ ምግብ ፡ ከሌላው ፡ የበለጠ ፡ በመሆኑ ፡ ባለጥቂቱ ፡ ደባልቀን ፡ እንብላ ፡ ሲል ፡ ብዙ ፡ ሥጋ ፡ የያዘውን ፡ ጠየቀው ። እሱም ፡ የኔ ፡ ብዙ ፡ ያንተ ፡ ትንሽ ፡ ነው ፤ በምን ፡ ምክንያት ፡ እደባልቃለሁ ፡ አልፈልግም ፡ ሲል ፡ የእንቢታ ፡ ቃሉን ፡ መለሰለት ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ዥቀራቹው ፡ ሁሉ ፡ ቀረና ፡ ተጣሉ ፤ በጥ ዥራቹው ፡ መበጫጨር ፡ ገጠመሩ ። ጠባቹው ፡ የበረታ ፡ ሆኖ ፡ እንደዚሁ ፡ በመተናነቅ ፡ ላይ ፡ እንዳሉ ፡ አንድ ፡ ቀበሮ ፡ በቅጥቋጦ ፡ ተከልሎ ፡ ይመለከታቹው ፡ ኖሮ ፡ ወደነሱው ፡ ቀረብ ፡ አለና ፡ ለምን ፡ ትጣላላችሁ ፡ ሲል ፡ ጠየቃቹው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ያ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሥጋ ፡ የያዘው ፡ እን ደዚህ ፡ ሲል ፡ መለሰለት ፡ ጌታው ፡ አቶ ፡ ቀበሮ ፡ ይህ ፡ ጓደኛዬ ፡ እኔ ፡ በደረቅ ፡ ውድቅት ፡ ነፍሴን ፡ ሸፈጭ ፡ ያመጣሁትን ፡ ሥጋ ፡ አብረን ፡ እን ደባልቅ ፡ ስላለኝ ፡ አንተ ፡ ያመጣኸው ፡ ትንሽ ፡ ነውና ፡ ለየብቻችን ፡ እንብላ ፡ ብለው ፡ እንቢ ፡ ብሎ ፡ በዚሁ ፡ ነው ፡ የተጣላነው ፡ አለው ። ይግሞ ፡ በተራው ፡ ባለአንስተኛውን ፡ እህ ፡ አንተስ ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቀው ፡ የበለጠውን ፡ ነጥቆ ፡ ወሰደና ፡ አላበላህም ፡ በማለቱ ፡ ነው ፡ የተጣላነው ፡ ሲል ፡ መለሰለት ።

ቀበሮም ፡ ከርከራቹውን ፡ በዝርዝር ፡ ከዳመጠ ፡ በኋላ ፡ ሰማች ሁኝ ፤ እንግዲህ ፡ የዚህ ፡ ቀበሌ ፡ ዳኝነት ፡ የኔ ፡ ነውና ፡ ኑ ፡ ሥርዐቱን ፡ አይላችኋለሁ ፡ ብሎ ፡ ከዛፍ ፡ ሥር ፡ ሄዶ ፡ ተቀመጠ ፡ ቀጥሎም ፡ ይህ ንን ፡ የተጣላችሁበትን ፡ ሥጋ ፡ ለማከፋፈል ፡ መመዘን ፡ ስለሚያስፈልግ ፡ ሚዛን ፡ አምጡ ፡ አላቹው ። እነሱም ፡ በታዘዙት ፡ መሠረት ፡ ፈልገው ፡ አምጥተው ፡ አቀረቡለት ።

አቶ ፡ ቀበሮም ፡ ያንን ፡ ሥጋ ፡ ከሚዛን ፡ ላይ ፡ ቢያደርገው ፡ ያንደኛው ፡ ወገን ፡ መብለጡን ፡ ተረዳው ፤ ስለዚህም ፡ ዳኛ ፡ ነኝ ፡ አስ ተካክላለሁ ፡ በማለት ፡ ከዚህም ፡ ላይ ፡ ጉረሠለት ፤ ግን ፡ ሚዛኑን ፡ ቢመ ለከተው ፡ እንደ ፡ ዱሮው ፡ ሆኖ ፡ አገኘው ። እንደ ፡ ፊተኛው ፡ አኳኋን ፡ አስተካክላለሁ ፡ በማለት ፡ ደግሞ ፡ ነጨለት ፤ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ሚዛኑ ፡ መተከክል ፡ ስላልቻለ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ከዚህኛው ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ከወዲያኛው ፡ እያለ ፡ በመብላቱ ፡ ሥጋው ፡ እያደር ፡ እያነሰ ፡ ሄደ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እነኛ ፡ የተጣሉ ፡ ድመቶች ፡ ጨርሰ ፡ ሊበላቹው ፡ መሆኑን ፡ ስለ ፡ ተረዱት ፡ ጌታው ፡ አቶ ፡ ቀበሮ ፡ እንግዲህ ፡ ዳኝነትህን ፡ አየ ነው ፡ ስጠንና ፡ እኛው ፡ ተስማምተን ፡ እንበላዋለን ፡ አሉት ። ቀበሮው ፡ ግን ፡

ቀድሞውን ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ ተስማምቶ ፡ መብላት ፡ አሁንማ ፡ ዳኝነት ፡ አይደለምን ፡ እኔስ ፡ ጢት ፡ ገምሬ ፡ በናንተ ፡ ዳኝነት ፡ ስጨነቅ ፡ ስለፋ ፡ ስደክም ፡ የዋልኩ ፡ መሆኔን ፡ እጣችሁትን ። ይህስ ፡ የተረፈው ፡ የለፋሁበት ፡



ዳኛ ፡ ነኝ ፡ አስተካክላለሁ በማለት ፡ ከዚህም ፡ ላይ ጉረሠለት ።

የዳኝነቱ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ወስጀዋለሁና ፡ በየበአታችሁ ፡ ሂዱ ፡ ብሎ ፡ አሰና በታቹው ። ድመቶቹም ፡ የተጣሉበትን ፡ ሥጋ ፡ ለባዕድ ፡ አስረክበው ፡ ያለጥቅም ፡ ቀሩ ፡ ይበላል ።

፨ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ በመመኘትና ፡ በመጣጣር ፡ በከርከ ርና ፡ በመግት ፡ በከንቱ ፡ ጊዜያቹውን ፡ የሚያጠፉ ፡ ሁሉ ፡ ያንኑ ፡ በጃ ቹው ፡ የያዙትን ፡ ከማጣት ፡ ይደርሳሉ ።

አስተዋዮች ፡ አባቶቻችንም ፡ ከደኅና ፡ መግት ፡ ሰነፍ ፡ ዕርቅ ፡ ይሻ ላል ፡ ብለው ፡ የሚመክሩን ፡ ስለዚህ ፡ ነው ።

ስለ ፡ ሁለት ፡ ንደኞች ።

ሁለት ፡ ከልብ ፡ የሚተማመኑ ፡ ባልንጀሮች ፡ በየጊዜው ፡ ይገጥማ ቸው ፡ የነበረውን ፡ ችግር ፡ ሁሉ ፡ በመረዳዳት ፡ እያቃለሉ ፡ ትዳር ፡ ይዘው ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። ይልቁንም ፡ አንደኛው ፡ የንደኛ ፡ ፍቅር ፡ በጣም ፡ ይጸ ናበት ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ወዳጁ ፡ የሚጠይቀውን ፡ ሁሉ ፡ ያላንድ ፡ ቅሬታ ፡ ይፈቅድለት ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ሁለቱም ፡ ይሱኝታ ፡ ቢስ ፡ በመ ሆኑ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ያገር ፡ ሽማግሎች ፡ ሰበሰበና ፡ አዘቶቹ ፡ ሆይ ፡ ዛሬ ፡ የማስቸግራችሁ ፡ ይህ ፡ ባልንጀራዩ ፡ ያጎባት ፡ ሴት ፡ በውበት ፡ በደም ግባት ፡ በቅርጽና ፡ በረማመድ ፡ ያማረች ፡ ከመሆኗም ፡ በላይ ፡ ያይኗ ፡ አገላለጥና ፡ አከዳደን ፡ ልቤን ፡ ስለ ፡ ነደፈው ፡ ለወንድሜ ፡ ነግራችሁ ፡ ይህችን ፡ ው-ብ ፡ ሴት ፡ እንዳገኝ ፡ አድርጉልኝ ፡ ሲል ፡ ልመናውን ፡ አቀ ረበላቸው ። ።

ሽማግሎችም ፡ ይህ ፡ ዐይነት ፡ ሐሳብ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ተሰምቶ ፡ ያልታወቀ ፡ በመሆኑና ፡ እንግዳ ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ሆነባቸው ፡ ተደንቀው ፡ እኛ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ እንዲሰማ ፡ እናደርጋለን ፡ እንጂ ፡ እንዲሰያዩ ፡ አንሠራም ፡ ብለው ፡ ተቈጡ ። እሱ ፡ ግን ፡ ንግግሩን ፡ በማለዘዝና ፡ በማ ለስለስ ፡ ሄዳችሁ ፡ አባክህ ፡ ሚስትህን ፡ ለእገሌ ፡ ለኛ ፡ ስትል ፡ ስጥልን ፡ በሉት ፡ እንጂ ፡ ወንድሜ ፡ የለመንኩትን ፡ እንደማይነሣኝ ፡ ዐውቃለሁ ፡ ሲል ፡ ደግሞ ፡ አስጨንቆ ፡ ጠየቃቸው ። ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሽማግሎቹ ፡ እንደ ፡ ምንም ፡ ሲፈሩ ፡ ሲቸሩ ፡ ሄደው ፡ ከሰውየው ፡ አጥር ፡ ግቢ ፡ ሲደርሱ ፡ ሁለቱ ፡ አንተ ፡ ተናገር ፡ አንተ ፡ ተናገር ፡ በማለት ፡ አምበጓሮ ፡ እንሥተው ፡ ተማተው ፡ ቈለለው ፡ ተመለሱ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ የተረፉት ፡ አማላጆች ፡ በድፍረት ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ገብተው ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ነገሩ ፡ አሰቃቂ ፡ ቢሆን ፡ ዛሬ ፡ አንተን ፡ ወንድማችንን ፡ የምናስቸግርህ ፡ ለዚህ ፡ ለአብሮ ፡ አደግ ፡ ጓደኛህ ፡ ሚስትህን ፡ እንድትለቅለት ፡ ነው ፡ በማለት ፡ የመጡበትን ፡ ጉዳይ ፡ ዘር ዝረው ፡ ገለጹለት ። ይሁን ፡ እሺ ፡ ለናንተ ፡ ስል ፡ ሚስቴን ፡ ለወንድሜ ፡ እተዋለሁ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ለኔ ፡ ደግሞ ፡ ከናንተ ፡ አንዳችሁ ፡ ሚስቶች ሁን ፡ እንድትለቁልኝ ፡ አለምናችኋለሁ ፡ ብሎ ፡ መልስ ፡ ሰጣቸው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሽማግሎቹ ፡ በሚስት ፡ የለም ፡ ዋዛ ፡ ብለው ፡ ከቤት ፡ ወጥተው ፡ ሄዱ ፡ ይጣላል ።

። ስለዚህ ፡ እነሱ ፡ ራሳቸው ፡ ሊያደርጉት ፡ የማይችሉትንና ፡ የማይ ፈቅዱትን ፡ ነገር ፡ እንዲፈጽሙላቸው ፡ ሌሎችን ፡ የሚጠይቁ ፡ ሽማግ ሎች ፡ ይህንን ፡ የመሰለ ፡ ቅሬትና ፡ ትዝብት ፡ እንዳያተርፉ ፡ መጠንቀቅ ፡ እንዳለባቸው ፡ ይጠቁ ።

አንድ ፡ አሮጌ ፡ ውሻና ፡ ቀበሮ ።

ዕድሚውን ፡ ሙሉ ፡ በቅንነትና ፡ በታማኝነት ፡ ለጌታው ፡ ሲያገለ ግል ፡ የኖረ ፡ አንድ ፡ አሮጌ ፡ ውሻ ፡ ጊዜ ፡ ሞቱ ፡ ሲደርስ ፡ ክቅሙ ፡ ማነስ ፡ የተነሣ ፡ የዘበኝነት ፡ ሥራውን ፡ እርግፍ ፡ አድርጎ ፡ ትቶ ፡ በም ግብ ፡ ሰዓት ፡ ብቻ ፡ ዐይኑን ፡ እያንከራተተ ፡ ቤት ፡ ለቤት ፡ መልከስከስ ፡ ዠመረ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አሳዳሪው ፡ የሆኑት ፡ ጌቶቹ ፡ በከንቱ ፡ እሱን ፡ ከም ንቀልብ ፡ ብንገድለውና ፡ በምትኩ ፡ ቡችላ ፡ ብናሳድግ ፡ የተሻለ ፡ ነው ፡ አያሉ ፡ ሲመካከሩ ፡ በመስማቱ ፡ እጅግ ፡ አዘነና ፡ ወደ ፡ መናፈሻ ፡ ወጥቶ ፡ የዳሮ ፡ አገልግሎቱን ፡ እያስታወሰ ፡ ማልቀስ ፡ ያዘ ። እንዳጋጣሚ ፡ ቀበሮ ፡ እግረ ፡ መንገዷን ፡ በዘያው ፡ በኩል ፡ ታልፍ ፡ ነበርና ፡ የውሻው ፡ ሁኔቴ ፡ ስላሳዘናት ፡ ጠጋ ፡ ብላ ፡ ያምን ፡ ምክንያት ፡ እንዳዘነና ፡ እንደ ፡ ተከዘ ፡ ጠየቀችው ። እሱም ፡ ጌቶቹ ፡ የሞት ፡ ሴራ ፡ እንደ ፡ ቋጠሩበት ፡ ነገራት ።

ቀበሮዋ ፡ በነገሩ ፡ በጣም ፡ ተደነቀችና ፡ አቶ ፡ ውሻን ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ቢጉኑና ፡ በኔ ፡ ዘር ፡ መከከል ፡ ቂም ፡ በቀል ፡ ቢኖር ፡ በስተር ጅና ፡ መጠቃትህ ፡ በጣም ፡ አሳዝኖኛልና ፡ ከሞት ፡ የምትድንበትን ፡ ዘዴ ፡ ልምከርህ ፡ አለችው ። አሮጌውም ፡ ዘበኛ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ተስፋ ፡ በማ ግኘቱ ፡ ከሐዘኑ ፡ ተጽናና ፤ በእንዴት ፡ ያለ ፡ ጥበብ ፡ ከዚህ ፡ አደጋ ፡ ልድን ፡ እችላለሁ ፡ ሲል ፡ ጠየቃት ።

ከጌቶችህ ፡ ምሕረት ፡ ለማግኘት ፡ ብትፈልግ ፡ ነገ ፡ ዉት ፡ በለቤ ቶቹ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ በሚወጡበት ፡ ሰዓት ፡ እኔ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ልምጣና ፡ ሕፃኑን ፡ ልጃቸውን ፡ ልውሰደው ፤ በዘያ ፡ ጊዜ ፡ አንተ ፡ እንደ ፡ ምንም ፡ ብለህ ፡ እየተጉተትህ ፡ ተከተለኝ ፤ አሳዳሪዎችህ ፡ ወሮታህን ፡

እንዲያውቁልህም ፣ ከዚህ ፣ በታች ፣ ከሚገኘው ፣ ፈፋ ፣ አጠገብ ፣ ስደርስ ፣ የያዝኩትን ፣ ጥይልህ ፣ ጥቂት ፣ ራቅ ፣ ብዬ ፣ እቆማለሁ ፣ አንተም ፣ እንደ ፣ ዐመልህ ፣ ከሕፃኑ ፣ ፊት ፣ ሆነህ ፣ ፊትህን ፣ ወደኔ ፣ አዙረህ ፣ ጩኽ ፤ ጌቶችህ ፣ ይህንን ፣ በማየት ፣ ያምሩሃል ፣ ስትል ፣ መለሰችለት ።

ውሻውም ፣ ይህንን ፣ ጠቃሚ ፣ ምክር ፣ በማግኘቱ ፣ ተደስቶ ፣ ወደ ፣ ቤቱ ፣ ተመለሰ ።

ኗ

በማግስቱ ፣ ጧት ፣ በቀጠሮው ፣ ሰዓት ፣ በለቤቶቹ ፣ ወደ ፣ ውጭ ፣ ሄደው ፣ ሳሉ ፣ ቀበሮዋ ፣ ሕፃኑን ፣ መሰደችና ፣ ከተባባሉበት ፣ ቦታ ፣ ስትደርስ ፣ ጥላው ፣ ፈቀቅ ፣ ብላ ፣ ቆመች ። ውሻውም ፣ እንደ ፣ መከረችው ፣ እየተጐተተ ፣ ሄዶ ፣ በልጇ ፣ አጠገብ ፣ ሆኖ ፣ ፊቱን ፣ ወደ ፣ ቀበሮዋ ፣ መልሶ ፣ ቃሉን ፣ እያጋነነ ፣ መጮኽ ፣ ያዘ ። በዚህ ፣ ጊዜ ፣ ጌቶቹ ፣ እየሮጡ ፣ ሲደርሱ ፣ ለመግደል ፣ ያሰቡት ፣ ውሻ ፣ ልጃቸውን ፣ ከቀበሮ ፣ አፍ ፣ አስጥሎ ፣ ሲደነፋ ፣ አገኙት ። ስለዚህም ፣ በደረገው ፣ ጅብዱ ፣ እጅግ ፣ ተደ



ለመግደል ፣ ያሰቡት ፣ ውሻ ፣ ልጃቸውን ፣ ከቀበሮ ፣ አፍ ፣ አስጥሎ ፣ ሲደንፋ ፣ አገኙት ።

ስተው ፣ እስከ ፣ ዕለተ ፣ ሞቱ ፣ ድረስ ፣ በመልካም ፣ አድርገው ፣ ሲቀል ቡት ፣ ኖሩ ፣ ይባላል ።

፨ ጥቃትን ፣ በመጥላት ፣ ብቻ ፣ ተመልሰው ፣ ከጠላቶቻቸው ፣ ጋራ ፣ የሚመክሩና ፣ የሚተባበሩ ፣ ብዙ ፣ ሰዎች ፣ ይገኛሉ ። መልካም ፣ ምክር ፣ ከሞት ፣ ያድናል ። ያገለገለን ፣ ዋጋ ፣ አለመንሣትና ፣ ወሮታውን ፣ አለመርሳት ፣ ያስተዋይ ፣ ተግባር ፣ ነው ።

ክብር ፣ ለማግኘት ፣ አስበ ፣ አደን ፣ ስለ ፣ ሄደ ፣ ሰው ።

ከጥንት ፣ ሰ,ያያዝ ፣ በመጣው ፣ ልምድ ፣ ወትሮ ፣ ወንድ ፣ ልጅ ፣ ጀግን ነቱን ፣ የሚገልጠው ፣ የሰው ፣ ድምፅ ፣ ከማይሰማበት ፣ ምድረ ፣ በዳ ፣ ሄዶ ፣ ባለግርማ ፣ የሆኑትን ፣ አስፈሪና ፣ አሥጊ ፣ አራዊት ፣ ገድሎ ፣ ሲመለስ ፣ ነበር ። ያዳኞችም ፣ ሚስቶች ፣ የተለየ ፣ ክብር ፣ ስለ ፣ ነበራቸው ፣ በማናቸውም ፣ ነገር ፣ አውራ ፣ ካልገደሉት ፣ ሰዎች ፣ ሴቶች ፣ ቅድሚያ ፣ ነበራቸው ።

ስለዚህም ፣ የሚስቱ ፣ መጠቃትና ፣ የሱም ፣ ከጀግኖች ፣ ተራ ፣ መለየት ፣ የቈጨው ፣ አንድ ፣ ሰው ፣ ወደ ፣ በረሓ ፣ ሄደና ፣ አንበሳ ፣ ሲፈልግ ፣ ዋለ ። ዘመጨረሻው ፣ ጊዜው ፣ ስለ ፣ መሸበትና ፣ ሳያቀናውም ፣ ቀርቶ ፣ መመለስ ፣ ግድ ፣ ስለ ፣ ሆነበት ፣ ካንድ ፣ ፈፋ ፣ ውስጥ ፣ ለማደር ፣ አሰበ ። ዳሩ ፣ ግን ፣ ስፍራው ፣ ጉብር ፣ የማያጣ ፣ በመሆኑ ፣ ስለ ፣ ሠጋ ፣ ለመከላከያ ፣ የያዘውን ፣ ሽክሻካ ፣ ዝተት ፣ ደርቦ ፣ ተኛ ። መንፈቀ ፣ ሌሊት ፣ ሲሆን ፣ ቀና ፣ ብሎ ፣ ቢመለከት ፣ የለበሰው ፣ ማቅ ፣ ከሰውነቱ ፣ ተንሸራቶ ፣ ወርዶ ፣ ኖሮ ፣ እግሩ ፣ ላይ ፣ አንዳች ፣ ነገር ፣ ተከብሶ ፣ አየ ። በዚህም ፣ ጊዜ ፣ መላው ፣ ሰውነቱ ፣ እንዳ ይንቀሳቀስበት ፣ በመጠንቀቅ ፣ ራሱን ፣ ብቻ ፣ ቀና ፣ አድርጎ ፣ አተኵሮ ፣ ቢመለከት ፣ ሊዘል ፣ የሚዘጋጅ ፣ አውሬ ፣ ያለ ፣ መሰለው ። ወዲያው ፣ ድምፅ ፣ ሳያሰማ ፣ በዝግታ ፣ ነኑሩን ፣ አቀባበለና ፣ ቃታውን ፣ ሰብ ፣ ቢያደርገው ፣ የአግሩ ፣ ሁለት ፣ ጣቶች ፣ ተቈርጠው ፣ ወደቁ ። በማግስቱ ፣ በደረሰበት ፣ አደጋ ፣ እያዘነ ፣ ደሙን ፣ እያዘረ ፣ ወደ ፣ ሰፈሩ ፣ ተመለሰ ። ከቤቱም ፣ አንደ ፣ ደረሰ ፣ ጎረ ፣ ቤቶቱ ፣ መጡና ፣ እንደ ፣ ምን ፣ ሆንክና ፣ መጣህ ፣ እደኑስ ፣ ቀናህን ፣ ብለው ፣ ቢጠይቁት ፣ አምን ፣ ቀንቶኛል ፣ እግሬን ፣ አድኜ ፣ መጣሁ ፣ አለ ፣ ይባላል ።

፨ ልጆች ፣ ሆይ ፣ በጥንቃቄና ፣ በማስተዋል ፣ መሥራት ፣ ከጉዳት ፣ አድኖ ፣ ክብርን ፣ የሚያስገኝ ፣ መሆኑን ፣ አትዘንጉ ።

በጎረ ፡ ቤት ፡ ያለውን ፡ ሌባ ፡ ያሸነፈ ፡ ወይን ፡ ስውር ።

ባንድ ፡ አገር ፡ አንድ ፡ ሀብታም ፡ የሆነ ፡ ወይን ፡ ስውር ፡ ሰው ፡ ነበር ። እሱም ፡ ለደንበኛው ፡ ጉሮ ፡ ከሚያስፈልገዉ ፡ በላይ ፡ ተቀማጭ ፡ የሚሠጥ ፡ ብዙ ፡ ብርና ፡ ወርቅ ፡ ነበረው ፡ ላደረ ፡ የሚበቃ ፡ ልጅ ፡ ወይም ፡ ዘመድ ፡ ዘግጣቱ ፡ ይህንኑ ፡ በክረጠት ፡ እየቋጠሬ ፡ ቸመንተራስ ፡ ሲኖር ፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ የሰው ፡ ድምፅ ፡ ሰሙር ፡ ሲል ፡ የሚያየኝ ፡ የለም ፡ በማለት ፡ ብርና ፡ ወርቁን ፡ ወስጾ ፡ ከንር ፡ እነባ ፡ ሥር ፡ ቀበረው ። ነገር ፡ ግን ፡ ጎረ ፡ ቤቱ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ይመለከተው ፡ ኖሮ ፡ ወፈር ፡ አልብሶ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሲመለስ ፡ የደበቀውን ፡ ዕቃ ፡ ከነጭንቅላው ፡ አውጥቶ ፡ ወሰደበት ።

ያህም ፡ ወይን ፡ ስውር ፡ ብዙ ፡ ቀኖች ፡ ያንክል ፡ አሳልፎ ፡ እቀበረበት ፡ ሄደ ፡ እየዳበሰ ፡ ያስቀመጠውን ፡ ቢፈልግ ፡ ስፍራው ፡ ተቄፍሮ ፡ ብሩና ፡ ወርቁ ፡ ከነጭንቅላው ፡ ተወስዶበት ፡ አገኘ ። ገንዘብ ፡ የልብ ፡ ሥር ፡ በመ ሆኑና ፡ የለፋበትና ፡ የደከመበት ፡ ሀብቱ ፡ ሁሉ ፡ በመጥፋቱ ፡ እጅግ ፡ ይና ደድና ፡ ያዝን ፡ ይተክዝ ፡ ዠመረ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ጉዳዩን ፡ ለማንም ፡ ሰይ ገልጥ ፡ አቄይቶ ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ወዋቂ ፡ ዘንድ ፡ ሄደ ። ወዋቂውም ፡ ዘምን ፡ ምክንያት ፡ ወደሌ ፡ ዘንድ ፡ መጣህ ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ። እሱም ፡ በብዙ ፡ ድከም ፡ ያጠራቀምኩትን ፡ ብርና ፡ ወርቅ ፡ ከቤቱ ፡ ጎሮ ፡ እነባ ፡ ሥር ፡ ሰው ፡ ሳያየኝ ፡ ቀብሬ ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ጥቂት ፡ ቀኖች ፡ ከለፉ ፡ በኋላ ፡ ለማየት ፡ ዘመለስ ፡ ቢታው ፡ ተቄፍሮ ፡ ገንዘቡ ፡ ከነጭንቅላው ፡ ተወስዶ ፡ አገኘሁት ። ስለዚህ ፡ አንተ ፡ ምሥጠር ፡ የሚገለጽልህ ፡ መሆኑን ፡ በመስማቱ ፡ የገንዘ ቤን ፡ ሌባ ፡ እንድትነግረኝና ፡ ባለጋራዬን ፡ እንዳውቀው ፡ በማለት ፡ ነው ፡ የመጣሁት ፡ ሲል ፡ መለሰለት ።

ፈላስፋውም ፡ ጉዳዩን ፡ ከመረመረና ፡ ካጠና ፡ በኋላ ፡ ጎረ ፡ ቤትህን ፡ ሂደህ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ካንድ ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ብርና ፡ ወርቅ ፡ ይብቁ ፡ ነበር ፡ አውን ፡ ደግሞ ፡ ያልተቀበረ ፡ ብዙ ፡ ብር ፡ በቤቱ ፡ ስላለ ፡ ከዚያው ፡ ከቀድሞው ፡ ገንዘቤ ፡ ጋራ ፡ በጉድጓድ ፡ ውስጥ ፡ ልሸሽገውን ፡ ወይስ ፡ ለብቻ ፡ ማስቀመጥ ፡ ይሻላል ፡ ብለህ ፡ አማክረው ። የሚሰጥህንም ፡ መልስ ፡ ሰምተህ ፡ ቃሉን ፡ ተከታትለህ ፡ እንደሚልህ ፡ ፊጽም ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የጠ ፋውን ፡ ገንዘብህን ፡ ታገኘዋለህ ፡ ብሎ ፡ ጠቃሚ ፡ ምክር ፡ ሰጠው ። ወይን ፡

ስውሩም ፡ በገንው ፡ ሐሳብ ፡ እጅግ ፡ ተደስቶ ፡ ፈላስፋውን ፡ ተሰናብቶ ፡ ከቤቱ ፡ እንደ ፡ ገባ ፡ እንደ ፡ ተመከረው ፡ ለጎረ ፡ ቤቱ ፡ ሰግህን ፡ ወን ድሜ ፡ መቼም ፡ ለክፉውም ፡ ሆነ ፡ ለደጉ ፡ ፈጥነህ ፡ የምትደርስልኝ ፡ ጎረ ፡ ቤቱ ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ ከንተም ፡ በቀር ፡ የማምነውና ፡ የምተማመንበት ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ሌለኝ ፡ ከማንም ፡ የተሰወረ ፡ አይደለም ፡ ስለዚህ ፡ የልቤን ፡ ሐሳብ ፡ ላንተው ፡ ማከፈል ፡ ይገዘኛል ። ከንድ ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ በጉድጓድ ፡ ውስጥ ፡ ያኖርኩት ፡ ብዙ ፡ ብርና ፡ ወርቅ ፡ አለ ፤ አውንም ፡ በማ ጥን ፡ የተቀመጠ ፡ ሌላ ፡ ወርቅ ፡ ስላለኝ ፡ ይህንን ፡ ከዚያው ፡ ከቀድሞው ፡ ጋራ ፡ ደባልቁ ፡ ልቅበረውን ፡ ወይስ ፡ ለብቻ ፡ እሌላ ፡ ቦታ ፡ ላስቀም ጠው ፡ እስቲ ፡ ምክር ፡ ስጠኝ ፡ ሲል ፡ አሳሰበው ።

ጎረ ፡ ቤቱም ፡ ለምን ፡ ብለህ ፡ ለየብቻው ፡ ትቀብራለህ ፡ ከዚያው ፡ ጋራ ፡ ብትደባልቀው ፡ ይሻልሃል ፡ እንጂ ፡ አንተ ፡ ወይን ፡ ስውር ፡ በያለ በትማ ፡ ሲሆን ፡ ይጠፋብህ ፡ የለምን ፡ ስለዚህ ፡ ከዚያው ፡ ከፊተኛው ፡ ጋራ ፡ አስቀምጠው ፡ ብሎ ፡ ይህንን ፡ አስተያየት ፡ እንደ ፡ መልካም ፡ ወዳጅ ፡ እበረከተው ።

ሀይን ፡ ስውሩም ፡ በምክሩ ፡ እንደ ፡ ተደሰተ ፡ ወይነት ፡ እሺ ፡ አለና ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ተመለሰ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ጎረ ፡ ቤቱ ፡ አዲሱንም ፡ ጨምሬ ፡ እወስዳለሁ ፡ ብሎ ፡ በማሰብ ፡ በፊት ፡ የሰረቀውን ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ ከነጭ ንቅላው ፡ እነበረበት ፡ ወስዶ ፡ ቀበረው ። ወዲያው ፡ እንዳይታይ ፡ ሆኖ ፡ ከትክልት ፡ ውስጥ ፡ ተደብቆ ፡ እንደ ፡ ልማዱ ፡ ወይን ፡ ስውሩን ፡ ይጠባ በቀው ፡ ዠመር ።

ባለጸጋውም ፡ ዕውር ፡ ጥቂት ፡ እንደ ፡ ቈየ ፡ ባሸሞ ፡ የተመላ ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ከረጢት ፡ ተሸክሞ ፡ መጣና ፡ ወደ ፡ ቀደምቱ ፡ ስፍራ ፡ ተጠግቶ ፡ ጉድጓዱን ፡ ዳበሰው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የጠፋውን ፡ ብርና ፡ ወርቁን ፡ ከነ ማሰሮው ፡ እንዳለ ፡ ዘመሉ ፡ አገኘው ፡ ስለዚህም ፡ የደከመበትንና ፡ የለ ፋበትን ፡ ቅርሱን ፡ በማግኘቱ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኖ ፡ ሌባውም ፡ ጎረ ፡ ቤቱ ፡ መሆኑን ፡ ተረድቶ ፡ በጉድጓዱ ፡ ያሸዋውን ፡ ከረጢት ፡ ቀብሮ ፡ ገንዘቡን ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ገባ ።

ሌባው ፣ ግን ፣ ወይን ፣ ስውሩ ፣ ከተመለሰ ፣ በኋላ ፣ የተቀበረውን ፣ ቁፍሮ ፣ ቢያይ ፣ ጭንቀላው ፣ ተመለዶ ፣ ከረጢቱ ፣ የያዘው ፣ አሸዋ ፣ ሆኖ ፣ አገኘው ።



በዚህ ፣ ጊዜ ፣ ሌባው ፣ ጎረ ፣ ቤቱ ፣ መሆኑን ፣ ተረድቶት ፣ አሸዋውን ፣ ቀብሮ ፣ ገንዘቡን ፣ ይዞ ፣ ወደ ፣ ቤቱ ፣ ገባ ።

ስለዚህም ፣ የእግዚአብሔር ፣ ፍርድ ፣ ምን ፣ ጊዜም ፣ ስለማይገ ድል ፣ ሁለቱም ፣ ዋጋቸውን ፣ ተቀብለው ፣ በየቤታቸው ፣ እንደየሥራ ቸው ፣ ሐዘንም ፣ ደስታም ፣ አደረጉ ፣ ይባላል ።

፨ የቁጡን ፣ አወርድ ፣ ብላ ፣ የብብቷን ፣ ጣለች ፣ እየተባለ ፣ የሚተ ረተው ፣ በዚህ ፣ ይተረጐማል ።

ሕመምተኛ ፣ ሰውና ፣ ሚስቱ ።

ብዙ ፣ ዘመን ፣ ሕመም ፣ ያልተለየው ፣ አንድ ፣ ሰው ፣ ነበር ፣ ይህም ፣ ሕመምተኛ ፣ የሰለት ፣ ምግቡን ፣ የሚያገኘው ፣ ሚስቱ ፣ የፈጫይ ፣ የፈታይ ፣ እየዋለች ፣ በምታገኘው ፣ ገንዘብ ፣ ነበር ። ከሰለታት ፣ አንድ ፣ ቀን ፣ ይህች ፣ ሴት ፣ ዕንጨት ፣ ለመሰበር ፣ ወደ ፣ ጫካ ፣ ሄዳ ፣ ሳለች ፣ ድክም ፣ ተሰማ ትና ፣ ከንድ ፣ ገላላ ፣ ድንጋይ ፣ ላይ ፣ ወረፍ ፣ አለች ። ጥቂት ፣ ከቂየችም ፣ በኋላ ፣ ስትነሣ ፣ ድንጋዩን ፣ ስትረግጠው ፣ ቢፈንቀል ፣ ከውስጡ ፣ ብዙ ፣



ጥቂት ፣ ከቂየችም ፣ በኋላ ፣ ስትነሣ ፣ ድንጋዩን ፣ ስትረግጠው ፣ ቢፈነቀል ፣ ከውስጡ ፣ ብዙ ፣ ወርቅ ፣ አየች ።

ወርቅ ፣ አየች ። በዚህም ፣ ጊዜ ፣ ከደስታዋ ፣ ብዛት ፣ የተነሣ ፣ ወርቁንም ፣ ሳትይዝ ፣ ወደ ፣ ቤት ፣ እየሮጠች ፣ ሄደችና ፣ በበሽታ ፣ ለተጨበጠው ፣ ባሏ ፣ ወርቅ ፣ ማግኘቷን ፣ ነገረችው ።

ሕመምተኛው ፣ በእግዚአብሔር ፣ ላይ ፣ ከፍ ፣ ያለ ፣ እምነት ፣ ነበረውና ፣ ሰማሽ ፣ እጎቴ ፣ በርግጥ ፣ አምላክ ፣ ይህንን ፣ ወርቅ ፣ ለኛው ፣ ብሎት ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ እስከ ፣ ቤታችን ፣ ድረስ ፣ ያመጣልናልና ፣ አሁን ፣ አንቺ ፣ ሄደሽ ፣ አታም ጪው ፣ አላት ። ባለቤቲቷ ፣ ግን ፣ አላስችል ፣ ስላላት ፣ ወደ ፣ ባሏ ፣ ወንድም ፣ ዘንድ ፣ ሄዳ ፣ ወርቅ ፣ ማግኘቷን ፣ ከነበታው ፣ ዘርዝራ ፣ ነገረችው ። ሰውዬው ፣ ምንም ፣ በለጸጋ ፣ ቢሆን ፣ ወርቁን ፣ ለራሱ ፣ የማድረግ ፣ ሐሳብ ፣ ስላደረበት ፣ አብረን ፣ ወርደን ፣ አማሳሻለሁና ፣ እኔ ፣ መጥቼ ፣ እስክጠራሽ ፣ ድረስ ፣ ከቤ ትሽ ፣ ቁይኝ ፣ አላት ። እሺ ፣ ብላ ፣ ስትጠባበቀው ፣ ወዲያው ፣ ጊዜ ፣ ሳይሰጥ ፣ በጉን ፣ እየሮጠ ፣ ሄዶ ፣ ወርቁን ፣ ወሰደው ። ከቤቱ ፣ ሲደርስ ፣ ያስቀመጠ በትን ፣ ከረጢቱን ፣ ፈትቶ ፣ ቢያየው ፣ በውስጡ ፣ አባብ ፣ ተጠቅልሎ ፣ አገኘ ።

በዚህም ፣ ጊዜ ፣ የበሽተኛው ፣ ወንድም ፣ ሚስት ፣ የሱን ፣ ሀብት ፣ የሚያጠፋ ፣ ሙተት ፣ ያስደረገችበት ፣ መሰለውና ፣ ይህንን ፣ አባብ ፣ ወስጂ ፣ ሌሊት ፣ ከመኝታቸው ፣ ላይ ፣ እጥለዋለሁ ፣ ሲል ፣ አሰበ ። እንዳሰበውም ፣ ሁሉ ፣ መንፈቀ ፣ ሌሊት ፣ ሲሆን ፣ በልጋቸው ፣ አቅጣጫ ፣ የቤታቸውን ፣ ክዳን ፣ ሚሩን ፣ ገለጥ ፣ አድርጎ ፣ ከረጢቱን ፣ እንደ ፣ ታሰረ ፣ አላያቸው ፣ ላይ ፣ ወርውሮ ፣ ወደ ፣ ቤቱ ፣ ተመለሰ ።

እነሱም ፡ ምንም ፡ ለጊዜው ፡ ቢደነግጡ ፡ የወደቀባቸውን ፡ ተነሥ ተው ፡ ቢያዩት ፡ ወርቅ ፡ የተመላበት ፡ ከረጢት ፡ ሆኖ ፡ አገኙት ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ በሽተኛ ፡ ሰው ፡ ለሚስቱ ፡ እኔ ፡ ያልኩሽ ፡ ነገር ፡ ደረሰ ፡ ቀን ፡ ላምጣው ፡ ብትዪኝ ፡ ለኛ ፡ ካለው ፡ እግዚአብሔር ፡ ያመጣዋል ፡ እንዳልኩሽ ፡ ይሽው ፡ አምላክ ፡ በጃችን ፡ ሰጠን ፡ አለና ፡ በእምነት ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ትልቅ ፡ ኃይል ፡ አስረዳት ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ለወርቁ ፡ መድኂኒት ፡ ገዝቶ ፡ ከሕመሙ ፡ ተፈ ውሶ ፡ ድኖ ፡ በዓለም ፡ በደስታ ፡ ከነባለቤቱ ፡ ፈጣሪውን ፡ እያመሰገነ ፡ ትዳሩን ፡ አደርጅቶ ፡ ኖረ ፡ ይበላል ።

፠ እግዚአብሔር ፡ ላንዱ ፡ ያዘዘለትን ፡ ሌላው ፡ ሊወስደው ፡ አይችልም ፡ ከዚህ ፡ ላይም ፡ እምነት ፡ ተራራ ፡ ይፈንቅላል ፡ ባሕር ፡ ይከፍላል ፡ የተ ባለውን ፡ አለመዘንጋት ፡ ይገባል ።

አንድ ፡ ቀላዋጭ ፡ ሰው ።

ዕድሜ ፡ ልኩን ፡ በቅልውጥ ፡ የሚኖር ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበር ። እሱም ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ በካባቢው ፡ ያሉት ፡ ሰዎች ፡ እኽል ፡ ውሃ ፡ የሚ ቀምሱበትን ፡ ሰዓት ፡ እየጠበቀ ፡ በየተራ ፡ ጎረ ፡ ቤቶቹን ፡ ያስቸግር ፡ ነበር ።

ነገር ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ በሀገሩ ፡ ውስጥ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የእኽል ፡ ችግር ፡ ስለ ፡ ገባ ፡ እንኳን ፡ ለውጭ ፡ ሰው ፡ ለመስጠት ፡ ይቅርና ፡ ለራስም ፡ የሚበላ ፡ ለማግኘት ፡ አዳጋች ፡ ሆነ ።

ስለዚህም ፡ ጎረ ፡ ቤቶቹ ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ ሰለቹትና ፡ በማጣታቸውም ፡ ጭምር ፡ ስለ ፡ ተመረሩት ፡ ከውጭ ፡ የሰላምታ ፡ ድምፅ ፡ ባሰማቸው ፡ ጊዜ ፡

ቶሎ ፡ ብለው ፡ ገበታቸውን ፡ ያነሡና ፡ አፋቸውን ፡ ጠራርገው ፡ ነወር ፡ አቶ ፡ እገሌ ፡ ምሳችንን ፡ ከበላን ፡ በኋላ ፡ መጣህ ፡ ምነው ፡ ትንሽ ፡ ቀደም ፡ ባልክ ፡ ኖሮ ፡ ደኅና ፡ ነበር ፡ እያሉ ፡ የማያበሉት ፡ ሆኑ ።

በእንደዚህም ፡ ያለ ፡ ሁናቴ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሲቸገር ፡ ከቄየ ፡ በኋላ ፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ከንደኛው ፡ ጎረ ፡ ቤት ፡ ገንፎ ፡ ተገንፍቶ ፡ ሲቀ ርብ ፡ ይህ ፡ ቀላዋጭ ፡ ድንገት ፡ ከበር ፡ ላይ ፡ ከተፍ ፡ አለ ። ባለቤትዮ ውም ፡ ቶሎ ፡ ብሎ ፡ ምግብ ፡ ያለበትን ፡ ጣባ ፡ አንሥቶ ፡ ከጉያው ፡ ውስጥ ፡ ሸሸገና ፡ ጋቢውን ፡ ተከናንቦ ፡ ተመለከተው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ በእንፋሎቱ ፡ መውጣት ፡ እንግዳው ፡ ሰውዬ ፡ በባለቤቱ ፡ ጉያ ፡ ውስጥ ፡ ገንፎ ፡ መኖሩን ፡ ለማወቅ ፡ ችሏል ። ስለዚህም ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ጨዋታ ፡ አመጣ ። ዛሬ ፡ ከቶ ፡ እገሌ ፡ ቤት ፡ ብሄድ ፡ ገንፎ ፡ አስገንፍቶ ፡ ሲበላ ፡ ደረስኩ ፤ ጻሩ ፡ ግን ፡ ሊነፍገኝ ፡ ፈልጎ ፡ ኖሮ ፡ እንዳላይበት ፡ ከጉያው ፡ አግብቶ ፡ ደበቀው ፤ እኔም ፡ ምሥጢሩ ፡ ስለ ፡ ገባኝ ፡ ቀስ ፡ አልሁና ፡ ጋቢውን ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ገለጥ ፡ በደርገው ፡ ያን ፡ ገንፎ ፡ የተ መላውን ፡ ጣባ ፡ ቅቤ ፡ እንዳረገዘ ፡ አገኘሁት ፡ አለና ፡ እንደ ፡ ማሰየት ፡ ዐይነት ፡ አድርጎ ፡ የለመዱውን ፡ ጋቢ ፡ ይዘ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ አለው ፤ ከዚ ህም ፡ የተነሣ ፡ ጣባው ፡ ታየበት ።



የሰውዬውን ፡ ጋቢ ፡ ይዘ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ አለው ፡ ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ጣባው ፡ ታየበት ።

በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ዘዴ ፡ እረ ፡ አንተም ፡ ይዘሃልና ፡ ብሎ ፡ ገንፎ ውን ፡ በልቶ ፡ ሄደ ፡ ይባላል ።

፠ ተረት ፤ አጉንብሶ ፡ በላን ፡ ተኝተህ ፡ ቀላውጠው ።

የታማኝ ፡ ወዳጆች ፡ መከዳዳት ።

ባንድ ፡ አገር ፡ የሚተማመኑ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ። ከነዚህም ፡ አንደኛው ፡ በሀብቱ ፡ የገነነ ፡ በሽምግልናው ፡ የተከበረ ፡ ሲሆን ፡ ሁለተኛው ፡ ደግሞ ፡ እየሠረ ፡ ከሚያፈራው ፡ ከዕለት ፡ ምግቡ ፡ ከመች ፡ ልብሱ ፡ የሚተርፈውን ፡ ገንዘቡን ፡ እየወሰደ ፡ ባጁረ ፡ ስም ፡ አኑርልኝ ፡ እያለ ፡ ለባለጸጋው ፡ የሚሰጥ ፡ ነበር ። ያም ፡ ታማኝ ፡ መሰዩ ፡ ሽማግሌ ፡ ያደራውን ፡ ገንዘብ ፡ እየተቀበለ ፡ ሲያስቀምጥለት ፡ ቂይቶ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ባለ ገንዘቡ ፡ ለዕለት ፡ ችግሩ ፡ ከኖረው ፡ ሐሰብ ፡ ላይ ፡ ጥቂት ፡ እንዲሰጠው ፡ ቢጠይቀው ፡ ምን ፡ ሰጠኸኝና ፡ ትጠይቀኛለህ ፡ አላየሁም ፡ ብሎ ፡ ጨርሶ ፡ ክዶው ፡ እየተመላለሰ ፡ በማሳዘን ፡ ቢለምነውም ፡ አላዘነለትም ፡ አልራራለትም ።

ቊርጡንም ፡ ካወቀ ፡ በኋላ ፡ ላገሩ ፡ ዳኛ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ሄዶ ፡ አመለከተ ፡ ዳኛውም ፡ ስትሰጠው ፡ ያየህ ፡ ምስክር ፡ የሚሆን ፡ ሰው ፡ አለህን ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቀው ፡ ከኔና ፡ ከሱ ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ አልነበረም ፡ አለው ። እንግዲያስ ፡ እኔ ፡ እጠይቅልሃለሁና ፡ ከሦስት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ተመልሰህ ፡ እንድትመጣ ፡ ብሎ ፡ አስታወቀው ።

ብልኑ ፡ ዳኛ ፡ እደረ ፡ አስቀግጬን ፡ ሰው ፡ ጠርቶ ፡ አሁን ፡ ያስጠራሁህ ፡ እኔ ፡ በድንገት ፡ ከዚህ ፡ አገር ፡ ከሸሙቱ ፡ ተሸሬ ፡ መሄዴ ፡ ነው ፤ ብጠይቅም ፡ ባስጠይቅም ፡ ታማኝ ፡ ሽማግሌ ፡ ባገር ፡ ያለኸው ፡ አንተ ፡ መሆንህን ፡ ሰማሁ ፡ ስለዚህ ፡ ዕቃዬንና ፡ ያለኝን ፡ ገንዘቤን ፡ በሙሉ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ አንሥቼ ፡ ለመሄድ ፡ ስለማይቻለኝ ፡ አንተ ፡ ዘንድ ፡ እንድታስቀምጥልኝና ፡ በየጊዜው ፡ ሰው ፡ ስልክ ፡ እንድትሰጥልኝ ፡ አለምንሃለሁ ፡ አለው ።

ሽማግሌውም ፡ እንግዲህ ፡ ይህ ፡ ያገር ፡ ዳኛ ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በደረ ፡ የሚያስቀምጠው ፡ ገንዘብ ፡ በብዙ ፡ ሺ ፡ የሚቈጠር ፡ ዕቃውም ፡ ከያንቱ ፡ ብዛት ፡ ጋራ ፡ የበረከተ ፡ ይሆናልና ፡ ይኸን ፡ ተቀብዬ ፡ አላየሁም ፡ ብዬ ፡ በለሀብት ፡ በለገንዘብ ፡ እሠናለሁ ፡ ብሎ ፡ ደስ ፡ አለውና ፡ ለዳኛው ፡ እሺ ፡ ጌታዬ ፡ ሲል ፡ መልስ ፡ ሰጠው ።

ከሦስት ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ ያ ፡ ባለገንዘብ ፡ ለዳኛው ፡ በቀጠሮዬ ፡ መጥቻለሁ ፡ ብሎ ፡ አመለከተው ። እንግዲህ ፡ ሂድና ፡ አንዳችም ፡ ነገር ፡ ሳትጨምር ፡ ባገሩ ፡ ዳኛ ፡ ልከስህ ፡ ነውና ፡ ገንዘቤን ፡ ስጠኝ ፡ በለው ፤ በዚያም ፡ ጊዜ ፡ ገንዘብህን ፡ በሙሉ ፡ አንድም ፡ ሳያስቀር ፡ ጨርሶ ፡ ይሰጥሃል ፡ አለው ።

እንደ ፡ ተባለውም ፡ ሁሉ ፡ ሄዶ ፡ ቢጠይቀው ፡ ይህን ፡ አልሰጥም ፡ ያልኩት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለዳኛው ፡ ሲነግረው ፡ ከሐዲነቱን ፡ ያውቅብኝና ፡ የሱን ፡ ብዙውን ፡ ገንዘብና ፡ ዕቃ ፡ ያስቀርብኛል ፡ ሲል ፡ ገንዘቡን ፡ በሙሉ ፡ አውጥቶ ፡ ሰጠው ፡ ይባላል ።



ከሐዲነቱን ፡ ያውቅብኝና ፡ የሱን ፡ ብዙውን ፡ ገንዘብና ፡ ዕቃ ፡ ያስቀርብኛል ፡ ሲል ፡ ገንዘቡን ፡ በሙሉ ፡ አውጥቶ ፡ ሰጠው ።

※ በጥቂት ፡ ያልታመነ ፡ ስብዙ ፡ አይታመንም ።

ብልህ ፡ ዳኛ ፡ የሕዝብ ፡ እረኛ ።

ስለ ፡ ሦስት ፡ ደንቈሮዎች ።

አንዲት ፡ ዝሮዋ ፡ የማይሰማ ፡ ሴት ፤ ልጅ ፡ ወልዳ ፡ ሕፃኑ ፡ ገና ፡ ሳያድግ ፡ ባሏ ፡ ድንገት ፡ ስለ ፡ ሞተ ፡ ከባሏም ፡ ሀገ ፡ ከርሷ ፡ ወገን ፡ የሚረዳ ፡ ዘመድ ፡ ዘማጣቷ ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ካለ ፡ ችግር ፡ ላይ ፡ ወደቀች ።

የለበሰችውም ፡ ልብስ ፡ ከላይም ፡ ከታችም ፡ በቂሟ ፡ አለቀባት ፡ ልጅዋንም ፡ የምትታቀፍበት ፡ ፈቤርቅ ፡ ኧጥታ ፡ በእንቀልባ ፡ ብቻ ፡ እያዘለች ፡ በረኃብም ፡ እየተሣቀየች ፡ ስትኖር ፡ ችግሩ ፡ በጣም ፡ ስለ ፡ ጸናባት ፡ ካንድ ፡ ሀብታም ፡ ቤት ፡ እረኝነት ፡ ተቀጥራ ፡ ትሠራ ፡ ዠመር ።

ከብት ፡ ጠንቅቃ ፡ ከመጠበቋ ፡ ሌላ ፡ ሌሊት ፡ እየተነሣች ፡ ጕርሦ ፡ በመሰለቅ ፡ ስላገለገለች ፡ ይህ ፡ ባለጸጋ ፡ አንድ ፡ እናቱ ፡ የሞተችበት ፡ የፍየል ፡ ግልገል ፡ በካብችሽ ፡ ቢያድግልሽ ፡ ብሎ ፡ ሰጣት ። እሷም ፡ የጊታዋን ፡ ጫማ ፡ ስማ ፡ ወስዳ ፡ ግልገሉን ፡ ከምትበላው ፡ በማብላት ፡ እረኝነትም ፡ በሄደች ፡ ጊዜ ፡ ቅጠል ፡ እየቈረጠች ፡ በመስጠት ፡ ዘይንብ ፡ አሳደገችው ።

ይህም ፡ ፍየል ፡ ዘእክል ፡ በማደጉ ፡ ምክንያት ፡ ሌባ ፡ ሆነና ፡ በማቢያም ፡ በጎረ ፡ ቤትም ፡ ዘንድ ፡ ስጥ ፡ አላሰጣ ፡ አለ ። ከፍየሎችም ፡ እየተነጠለ ፡ ባጥር ፡ እየዘለለ ፡ ስጥ ፡ እየቃመና ፡ ቤትም ፡ እያጠፋ ፡ ስላስቸገረ ፡ አንዱ ፡ የተናደደ ፡ ጎረ ፡ ቤት ፡ በድንጋይ ፡ ወርውሮ ፡ አንድ ፡ እግሩን ፡ ሰበረበት ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ በሰድሳ ፡ ብታዝንም ፡ ተስፋ ፡ ባለመቊረጥ ፡ ሰበራውን ፡ በመላሚያ ፡ አስጠግና ፡ በማስታመም ፡ አዳነችው ።

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ልጅዋን ፡ ይዛ ፡ ካንድ ፡ ፈፋ ፡ ውስጥ ፡ ገብታ ፡ ከሸም ፡ እየለቀመች ፡ ስትበላ ፡ እረኛ ፡ ላይ ፡ አሰምርታቸው ፡ የነበሩት ፡ ከብቶች ፡ በሙሉ ፡ ጠፉባት ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ደንግጣ ፡ እየሮጠች ፡ ወዳፋፍ ፡ ብቅ ፡ ብላ ፡ አሸቄልቊላ ፡ ብትመለከት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ያማውን ፡ አስልቶ ፡ ዳገቱን ፡ ሲቈፍር ፡ አየችው ። ፈጥና ፡ ተጠግታ ፡ እባክህ ፡ ወንድሜ ፡ ከብቶች ፡ ጠፍተው ፡ በኛልና ፡ ምናልባት ፡ አይተህ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሄዱበትን ፡ አቅጣጫ ፡ አሳየኝ ፡ በውታዚህ ፡ የተገኙልኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አንድ ፡ እግረ ፡ ሰባራ ፡ ፍየል ፡ አለኝና ፡ እሱን ፡ እሰጥሃለሁ ፡ ስትል ፡ ቃሏን ፡ ሰጠች ።

ሰውዬውም ፡ ደንቈሮ ፡ ኖሮ ፡ ዛሬ ፡ ከየት ፡ ዠምረኽ ፡ ቈፈርክ ፡ ያለችው ፡ መስሎት ፡ ዉሏ ፡ ወደ ፡ ዠመረበት ፡ በጣቱ ፡ አመለከታት ።

ሴትዮዋም ፡ ወደዚያ ፡ አልፈውልሻል ፡ ያላት ፡ መስሏት ፡ በእጁ ፡ ወዳሳያት ፡ ተጓዘች ። ወዲያው ፡ እንደ ፡ አጋጣሚ ፡ ከብቶቹን ፡ በሙሉ ፡ ተሰብስበው ፡ ካንድ ፡ ቦታ ፡ አገኝቷቸው ።



ዛሬ ፡ ከየት ፡ ዠምረህ ፡ ቈፈርህ ፡ ያለችው ፡ መስሎት ፡ ዉሏ ፡ ወደ ፡ ዠመረበት ፡ በጣቱ ፡ አመለከታት ።

ስለዚህ ፡ ተደስታ ፡ ያንን ፡ ሰባራ ፡ ፍየል ፡ ወስዳ ፡ ለዚያ ፡ ቈፋሪ ፡ አንተው ፡ እንዳመለከትከኝ ፡ ከብቶቹን ፡ አገኘኋቸው ፤ እኔም ፡ ምንም ፡ ችግረኛ ፡ ድኻ ፡ ብሆን ፡ የተናገርኩትን ፡ ቃሌን ፡ አላጥፈውምና ፡ አንከ ፡ ውሰድ ፡ ብላ ፡ ሰባራውን ፡ ፍየል ፡ አቀረበችለት ።


በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ፍየሌን ፡ ሰበርክ ፡ አለችኝ ፡ ብሎ ፡ ያንቺን ፡ ፍየል ፡ የት ፡ አግኝቼ ፡ ነው ፡ የሰበርኩት ፡ አልነካሁትም ፡ የመታ ብሽ ፡ አንዳለ ፡ ፈልጊው ፡ እያለ ፡ ሲናገርና ፡ ሁለቱም ፡ ቁመው ፡ ሲጨቃጨቁ ፡ አንድ ፡ መንገደኛ ፡ ሰው ፡ መጣ ። እሱም ፡ በጠቡ ፡ መክረር ፡ ምክንያት ፡ ሰውዬው ፡ ተናዶ ፡ ሴቲቱን ፡ ይደበድባት ፡ ይሆን ፡ በማለት ፡ ሰግቶ ፡ ሁለቱንም ፡ ወደ ፡ ዳኛ ፡ ወስዶ ፡ ተጣልተው ፡ ሲፋጁ ፡ አገኘኋቸው ፡ ብሎ ፡ አቀረባቸው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይህቺ ፡ ባለፍየል ፡ ሴት ፤ ዳኛ ፡ ሆይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያሳያዎ ፡ መላክ ፡ ይንገርዎ ፡ ከብቶች ፡ ጠፍተውብኝ ፡ ስፈልግ ፡ ይህን ፡ ሰው ፡ አግኝቼ ፡ ብጠይቀው ፡ በዚህ ፡ በኩል ፡ አለፉልሽ ፡ ብሎ ፡ ነገረኝ ፡ እኔም ፡ የሄዱበትን ፡ ስላመለከተኝ ፡ በዕድልህ ፡ ከብቶቹን ፡ በሙሉ ፡ ያገኘሁ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አንድ ፡ ሰባራ ፡ ፍየል ፡ አለኝና ፡ እሱን ፡ እሰጥሃለሁ ፡ ብዬ ፡ ቃል ፡ ገብቼለት ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ የጠፉትን ፡ በማግኘቴ ፡ ያንኑ ፡ ያልኩትን ፡ አምጥቼ ፡ ውሰድ ፡ ብለው ፡ ዳኛና ፡ ፍየል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ይህንን ፡ አልቀበልሽም ፡ አለኝ ፡ እኔም ፡ ያለኝ ፡ ይኸው ፡ ነው ፡ እሰጣለሁ ፡ ያልኩትም ፡ ይኸው ፡ በመሆኑ ፡ ፍርዱን ፡ ያውልኝ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ርስም ፡

ይኸው ፡ ቀርቢያለሁ ፡ ብላ ፡ ስታመለክት ፡ ልጅዋ ፡ ተርበ ፡ ኖሮ ፡ ምርር ፡ ብሎ ፡ ያለቅስ ፡ ዝመረ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አንቀልባዋን ፡ ፈትታ ፡ ከገቦ ፡ ባዋ ፡ አውርዳ ፡ በደረቷ ፡ ታቅፋ ፡ እሽ ፡ እሽ ፡ እያለች ፡ ማጥባት ፡ ያዘች ።

ቄሳሪው ፡ ደግሞ ፡ በበኩሉ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ አመለከተ ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ ይህች ፡ ሴት ፡ እሥራዔል ፡ ድረስ ፡ መጥታ ፡ ዛሬ ፡ ከኔጋ ፡ ከየት ፡ እስከ ፡ የት ፡ ቄፈርክ ፡ ብላ ፡ ብትጠይቀኝ ፡ ከዚህ ፡ እስከዚያ ፡ ብዬ ፡ መለስኩላት ። ሰላምታ ፡ ሰጥታኝ ፡ ከለፈች ፡ ቹኋላ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ከብቶች ፡ እየነዳች ፡ ተመልሳ ፡ መጥታ ፡ አንካሳ ፡ ፍያሳን ፡ ይዛ ፡ ይህን ፡ የሰበር ከው ፡ አንተ ፡ ነህና ፡ ከፈለኝ ፡ ብላ ፡ ወይኗን ፡ አፈጠጠችብኝ ። እኔም ፡ አልሰበርኩም ፡ በማለት ፡ በዚሁ ፡ ተጣልተን ፡ ይኸው ፡ ወደዚህ ፡ ሽንጎ ፡ ለመምጣት ፡ በቃን ፡ ብሎ ፡ የልቡን ፡ ሐሳብ ፡ ለዳኛው ፡ አመለከተ ።

ዳኛውም ፡ ገሮው ፡ የማያጣራ ፡ ነበርና ፡ ሴትየዋ ፡ ሕፃን ፡ ልጅ ፡ አገላ ፡ በመምጣቷና ፡ ልጁም ፡ ሲያለቅስ ፡ በማየቱ ፡ ብጽ ፡ ለሰውዬው ፡ ዳቃላ ፡ ወልዳ ፡ አላሳደግም ፡ (ቀለብ ፡ አልሰጥም) ፡ በማለት ፡ የተጣሉ ፡ መስሎት ፡ ከተቀመጠበት ፡ ብድግ ፡ ብሎ ፡ ባዲሊ ፡ ያድላበት ፡ በሐሰ ተኛ ፡ ሰይፍ ፡ ሞት ፡ ይፈረድበት ፡ ይህ ፡ ልጅ ፡ ወይኑም ፡ ጥርሱም ፡ ደም ፡ ግባቱም ፡ አንተኑ ፡ ይመስላል ፡ መልኩም ፡ ይመሰክራል ፡ ስለዚህ ፡ ማሳ ደጊያውን ፡ ቀለብ ፡ ልትሰፍር ፡ ይገባሃል ፡ ሲል ፡ በላመለከቱት ፡ ፈረደ ፡ ይጠላል ።



ይህ ፡ ልጅ ፡ ወይኑም ፡ ጥርሱም ፡ ደም ፡ ግባቱም ፡ አንተኑ ፡ ይመስላል ፡ መልኩም ፡ ይመሰክራል ፡ ግባደጊያውን ፡ ቀለብ ፡ ልትሰፍር ፡ ይገባሃል ።

፨ ልጆች ፡ ሆይ ፡ ያልሰማ ፡ ገሮ ፡ ከጎረ ፡ ቤት ፡ ያጣላል ፡ ተብሎ ፡ የሚተረተው ፡ ስለዚህ ፡ ነውና ፡ በምትሠሩት ፡ ሁሉ ፡ ማስተዋልና ፡ መግባት ፡ እንዲኖራችሁ ፡ በውል ፡ ተጠንቀቁ ።

ሲሰማ ፡ የገበን ፡ ሲያይ ፡ ቅበረው ።

በንድ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ሚስት ፡ አግብቶ ፡ በሕግና ፡ በሥርዐት ፡ የሚኖር ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበር ። እሱም ፡ ፈጣሪ ፡ ብዙ ፡ ተባዙ ፡ ምድርንም ፡ ምዷት ፡ ብሎ ፡ ለዶጋቹ ፡ ለነአብርሃም ፡ የሰጠው ፡ ቃል ፡ ተፈጽሞለት ፡ ብዙ ፡ ልጆች ፡ ወለደ ።

ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ ክብረትና ፡ ድኽነት ፡ ሹመትና ፡ ሽረት ፡ ስለሚፈራረቁበት ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ በሚኖርበት ፡ አገር ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ረኃብ ፡ ስለ ፡ መጣ ፡ በቀኑጥር ፡ ለበዙ ፡ ልጆቹ ፡ ለልብሳቸውና ፡ ለጉርሣቸው ፡ የሚያደርገው ፡ ችገረው ። ስለዚህም ፡ ሰውዬው ፡ ጉልበታም ፡ ለትዳሩ ፡ ታታሪ ፡ ነበርና ፡ ልጆቼና ፡ ሚስቴ ፡ በችጋር ፡ ከሚያልቁ ፡ ጥጋብ ፡ ወደ ፡ ሆነበት ፡ አገር ፡ ተሰድጄ ፡ የሞያተኛ ፡ እየሠራሁ ፡ በበላቸውና ፡ ነፍሳቸውን ፡ በድን ፡ ይሸለኛል ፡ ብሎ ፡ አሰበ ፡ ወዲያው ፡ ምኞቱን ፡ በተግባር ፡ ለመግለጥ ፡ ጓዙን ፡ ጠቅልሎ ፡ ሚስቱንና ፡ ልጆቹን ፡ አስከትሎ ፡ እኽል ፡ ወዳለበት ፡ አገር ፡ ጉዞ ፡ ዠመረ ።

ብዙ ፡ ቀንም ፡ ከተጓዙ ፡ በኋላ ፡ ካንድ ፡ አገር ፡ ሲደርሱ ፡ በዚያ ፡ የሚገኙትን ፡ ባላገሮች ፡ እኽል ፡ እንደ ፡ ልብ ፡ የሚገኝበትን ፡ ስፍራ ፡ አንዲነግሯቸው ፡ ጠየቁ ። ሰዎቹም ፡ በአሻጋሪያቸው ፡ የሚገኘውን ፡ ተራራማ ፡ የሆነ ፡ አገር ፡ አሳይተው ፡ ይህ ፡ ቀበሌ ፡ እኽል ፡ በጣም ፡ ያውቃል ፡ የጥጋብ ፡ አገር ፡ ነው ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ሕግ ፡ ሥርዐትና ፡ ዳኛ ፡ የለበትም ፡ የባለጌና ፡ የግፈኛ ፡ ሰፈር ፡ ነው ፤ ደግሞ ፡ ከርሱ ፡ ተያይዞ ፡ የሚገኘው ፡ ወረዳ ፡ እኽል ፡ እንደ ፡ ልብ ፡ አያመችም ፤ ሆኖም ፡ ሕግ ፡ ሥርዐትና ፡ ዳኛ ፡ አለበት ፡ ሲሉ ፡ የህገሩን ፡ ባህል ፡ ገልጸው ፡ ነገሩት ።

ይህም ፡ ሰው ፡ ነገራቸውን ፡ በአርምሞ ፡ ከደመጠ ፡ በኋላ ፡ የራበው ፡ ይጠግብ ፡ አይመስለውምና ፡ እኔ ፡ ሕግ ፡ ሥርዐትና ፡ ዳኛ ፡ በይኖር ፡ ምን ፡ ችገረኝ ፡ እኔ ፡ እንደ ፡ ሆንኩ ፡ ርስት ፡ ጉልት ፡ ሀብት ፡ ንብረት ፡ የሌለኝ ፡ ድኻ ፡ ነኝ ፤ የምፈልገው ፡ በጉልበቴ ፡ ደክሜ ፡ የሞያተኛ ፡ ውዬ ፡ ለመብላት ፡ ብቻ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ከሰው ፡ ጋራ ፡ በምን ፡ እገናኝና ፡ እጣላለሁ ፡ ብሎ ፡ ዳኛ ፡ ሥርዐትና ፡ ሕግ ፡ ወደሌለበት ፡ አገር ፡ ለመሄድ ፡ ቊርጥ ፡ ሐሳብ ፡ አደረገ ።

አስቦም ፡ ሳይቀር ፡ ጓዙን ፡ ይዞ ፡ ከመረጠው ፡ ቀበሌ ፡ ገባ ። ለጊዜውም ፡ መኖሪያ ፡ የሚሆነው ፡ ጉጦ ፡ ቀልሶ ፡ የሞያተኛ ፡ እየሠራ ፡ ሚስቱንና ፡ ልጆቹን ፡ እየመገበ ፡ ከችጋር ፡ ሊያድናቸው ፡ ቻለ ።

ጥቂት ፡ ወራት ፡ እንደ ፡ ተቀመጠም ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ የቤተ ፡ ሰቡን ፡ ብዛት ፡ ተመልክቶ ፡ አንድ ፡ ያገራው ፡ ሰው ፡ ከወዴት ፡ አገር ፡ እንደ ፡ መጣና ፡ አብረውትስ ፡ ያሉት ፡ ሰዎች ፡ ምናቸ ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ ጠየቀው ። እሱም ፡ ይህች ፡ ሚስቴ ፡ ናት ፡ የቀሩትም ፡ ልጆቹ ፡ ናቸው ፡ በማለት ፡ ለጥያቄው ፡ መለሰለት ። እውነት ፡ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ያንተው ፡ ልጆች ፡ ናቸውን ፡ ሲል ፡ ደግሞ ፡ በመገረም ፡ አጥብቆ ፡ ጠየቀው ። አዎን ፡ የኔው ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ ስላረጋገጠለት ፡ እኔ ፡ አጄዲ ፡ ልጅ ፡ እንኳ ፡ አጥቼ ፡ አንተ ፡ የበለጠህ ፡ አባት ፡ ሆነሃል ፡ በል ፡ ሚስትህን ፡ ስጠኝና ፡ እኔም ፡ ልውሰድላት ፡ አለው ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አምላክ ፡ በመለኮቱ ፡ ንጉሥ ፡ በመንግሥቱ ፡ ጉል ማሳ ፡ በሚስቱ ፡ ቢገበብቸው ፡ ቀናእያን ፡ ናቸው ፡ እንደ ፡ ተባለው ፡ እንደ ፡ ተደርጎ ፡ ሚስቱን ፡ እሰጥሃለሁ ፡ አልሰጥም ፡ አለው ። ወዲያው ፡ ክርክሩ ፡ እየከረረ ፡ በመሄዱ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጠብ ፡ አበቀሉ ፤ በመጨረሻውም ፡ የሀገሩ ፡ ተወላጅ ፡ አልሰጥም ፡ ታልከኝ ፡ ወደ ፡ ዳኛ ፡ እንድረስ ፡ እንጂ ፡ አልተውም ፡ ብሎ ፡ አስቸገረው ። ስደተኛውም ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ ዳኛው ፡ ያለሕግ ፡ ሚስትህን ፡ ስጥ ፡ እይለኝም ፡ ብሎ ፡ ስለ ፡ ተማመነ ፡ ሁለቱም ፡ ተያይዘው ፡ እፍርድ ፡ ቤት ፡ ሄዱ ።

በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ሚስትህን ፡ ስጠኝ ፡ ልውሰድላት ፡ በዩ ፡ ሰው ፡ ለዳኛው ፡ እግዚአብሔር ፡ ያሳይዎ ፡ መላክ ፡ ይንገርዎ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ተሰዶ ፡ መጥቶ ፡ በገራችን ፡ ከተቀመጠ ፡ አያሌ ፡ ጊዜ ፡ ሆኖታል ፤ ብዙ ፡ ጓዝም ፡ ስላለው ፡ አብረውህ ፡ ያሉት ፡ ወጣቶች ፡ ምኖችህ ፡ ናቸው ፡ ብዬ ፡ ብጠይቀው ፡ ልጆቼ ፡ ናቸው ፡ አለኝ ፤ እንግዲያው ፡ እኔ ፡ ልጅ ፡ የለኝም ፡ ሚስትህን ፡ ስጠኝና ፡ ትውለድልኝ ፡ ብለው ፡ እንቢ ፡ አሻፈረኝ ፡ አለኝ ፤ እኔም ፡ ለራሱ ፡ ብቻ ፡ እሰቢ ፡ ምቀኛም ፡ መሆኑን ፡ ስለ ፡ ተረዳሁ ፡ እንደ ፡ ፀሐይ ፡ የሚያበራው ፡ ፍርድዎ ፡ ይህንኑ ፡ ግፍ ፡ ተመልክቶ ፡ እንደሚያሰጠኝ ፡ በማመን ፡ ይኸው ፡ ክገናናው ፡ ችሎትዎ ፡ ቀርቤ ፡ እገኛለሁ ፡ ሲል ፡ አመለከተ ።

ዳኛውም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በመገረም ፡ ቂይቶ ፡ እረ ፡ ለመሆኑ ፡ አንተ ፡ ከወዴት ፡ አገር ፡ የመጣህ ፡ ሰው ፡ ነህ ፡ ሕግና ፡ ሥርዐት ፡ ያልሰማህና ፡ ያላየህ ፡ ምቀኛ ፡ አያሌ ፡ ልጆች ፡ አያሉህ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ እንኳ ፡ ልውለድ ፡ ቢል ፡ የምትከለክለው ፡ ምን ፡ ጉድ ፡ ነህ ፤ በል ፡ አሁንም ፡ ሚስ

ትህን ፡ እንድትሰጠው ፤ ትእዛዜን ፡ ሳትፈጽም ፡ ብትቀር ፡ ግን ፡ የሚደርስብህ ፡ ቅጣት ፡ ከባድ ፡ ይሆናል ፡ ሲል ፡ ይግባኝ ፡ የሌለው ፡ ውሳኔ ፡ ሰጠ ።

ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ሚስቱን ፡ አስረክቦ ፡ በመናደድና ፡ በማዘን ፡ ልጆቹን ፡ ይዞ ፡ እንደ ፡ ተቀመጠ ፡ ድንገት ፡ እንደ ፡ ጉንፋን ፡ እድርጎ ፡ አመመውና ፡ እመንገድ ፡ አጠገብ ፡ በሠራው ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ተኛ ። ይኸውም ፡ የታመመበት ፡ ቀን ፡ ሰኞ ፡ ገርምሮ ፡ ነበርና ፡ ያገሩ ፡ ሰዎች ፡ ሲተላለፉ ፡ ምን ፡ ሆነሃል ፡ ብለው ፡ ሲጠይቁት ፡ አሞኛል ፡ ይላቸው ፡ ነበር ።

በዚህም ፡ አኳኋን ፡ ከሰኞ ፡ እስከ ፡ እሑድ ፡ ደረሰ ። እሑድ ፡ ያገሩ ፡ ሰዎች ፡ ተሰብስበው ፡ ከስደተኛው ፡ ዘንድ ፡ ሄደው ፡ ተነሣ ፡ ትችል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተከተለን ፡ ያለዚያም ፡ በወሰሳም ፡ ሆነ ፡ በታሬዛ ፡ ተሸክመን ፡ ወስደን ፡ እንቅበርህ ፤ እኛ ፡ በሥራ ፡ ቀን ፡ ትሞትና ፡ የመንግሥቱ ፡ ሐዳድ ፡ ይቀርብናል ፡ ብለን ፡ እስበን ፡ ነበር ፡ ግን ፡ የንጉሡ ፡ አምላክ ፡ ከእሑድ ፡ አድርሶሃልና ፡ ዛሬ ፡ በበዓል ፡ እንቅበርህ ፡ አሉና ፡ ነገሩት ።

እሱም ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ ሳልሞት ፡ ደኅናውን ፡ ሰው ፡ በቁሜ ፡ የምትቀብሩኝ ፡ አልቀበርም ፡ አላቸው ። እንዲህ ፡ ታልክ ፡ ለምን ፡ ተኝተህ ፡ ሰነበትክ ፡ አሁን ፡ በሥራ ፡ ቀን ፡ ሞተህ ፡ የንጉሥ ፡ ሐዳድ ፡ ልታስቀር ፡ ነውን ፡ እንቀብርሃለን ፡ እንጂ ፡ አይቀርም ፤ እንዚ ፡ ታልክ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ችሎት ፡ ሄደን ፡ እንፋረድ ፡ አንተ ፡ እንደ ፡ ሆንክ ፡ መቼም ፡ ተኝክ ለኛ ፡ ነህ ፤ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ አቶ ፡ እገሌ ፡ ከሚስትህ ፡ ልውለድ ፡ ቢልህ ፡ እምቢ ፡ ብለኸው ፡ ፍርዱ ፡ እንደ ፡ ፀሐይ ፡ ብርሃን ፡ የተገለጠለው ፡ ዳኛችን ፡ በይኖብህ ፡ ነው ፡ የሰጠኸው ፡ አሉት ።

ከዳኛ ፡ እንድረስ ፡ ካላችሁስ ፡ እንቢ ፡ አልልም ፡ አለና ፡ ተያይዘው ፡ ሄዱ ።

ከችሎቱም ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ዳኛ ፡ ሆይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያሳይዎ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ በገራችን ፡ በስደተኝነት ፡ የተቀመጠ ፡ ነው ፤ እንሆ ፡ አሁን ፡ ከሰኞ ፡ ገርምሮ ፡ ታሞ ፡ ተኝቶ ፡ ሰነበተ ፤ እኛም ፡ ድንገት ፡ ይሞትና ፡ የመንግሥት ፡ ሐዳድ ፡ ይቀርብናል ፡ ብለን ፡ አስበን ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በውቃቢዎ ፡ እስከ ፡ እሑድ ፡ ደረሰ ። ስለዚህም ፡ ዛሬ ፡ ተሰብስበን ፡ እንቅበርህ ፡ ብንለው ፡ አሻፈረኝ ፡ ብሎ ፡ አስቸገረን ፤ ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ ፀሐይ ፡ ፍርድዎን ፡ ለመስማት ፡ ይኸው ፡ ያዘነው ፡ መጥተናል ፡ ሲሉ ፡ አመለከቱ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዳኛው ፡ ይኸማ ፡ ከዚህ ፡ ቀደሞስ ፡ ሚስቱን ፡ አል ሰጥም ፡ ብሎ ፡ ያስቸገረው ፡ አይደለምን ፡ መቼ ፡ አጣሁት ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ምቀኛ ፡ ተንኰለኛ ፡ ሕግና ፡ ሥርዐት ፡ የማያውቅ ፡ ሰው ፡ በምን ፡ አገራችን ፡ ገባብን ፡ ደግሞ ፡ ተኝቶ ፡ ሰንብቶ ፡ አውንም ፡ አልቀበርም ፡ ማለትን ፡ ከምን ፡ አመጣው ፡ በሥራ ፡ ቀን ፡ ሞቶ ፡ የመንግሥት ፡ ሐዲድ ፡ ሊያስቀር ፡ አይደለምን ፡ በሉ ፡ አሁን ፡ ወስዳችሁ ፡ ቅበሩት ፡ ብሎ ፡ ስለ ፡ ፈረደላቸው ፡ የዳኛውን ፡ ፍርድ ፡ ኢምስማነው ፡ ወስደው ፡ ቀበሩት ፡ ይባላል ።

ይህ ፡ ሰው ፡ ለሆዱ ፡ ብቻ ፡ ከማሰብ ፡ ሕግ ፡ የለበትም ፡ ሲሉትና ፡ ሲመኙ ከሩት ፡ ሰምቶ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ ባልደረሰበትም ፡ ነበር ። ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ሕግና ፡ ሥርዐትን ፡ ገንዘብ ፡ ካደረጉ ፡ የፊልጉትን ፡ ማግኘት ፡ አዳጋች ፡ አይሆንም ፤ ሕግን ፡ ያልፈለገ ፡ ግን ፡ ፍርድ ፡ አጥቶ ፡ ይሞታል ።

* ሲለማ ፡ የገባን ፡ ሲያይ ፡ ቅበረው ፡ ተብሎ ፡ የሚነገረውም ፡ ይህንን ፡ የመሰሰለው ፡ ነገር ፡ ባጋጠመ ፡ ጊዜ ፡ መሆኑን ፡ አስተዋይና ፡ ተመል ካች ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ መገንዘብ ፡ ይገባዋል ።

ያንድ ፡ ተማሪ ፡ በብልሃት ፡ ዳቦ ፡ ማግኘት ።

አንድ ፡ ቀን ፡ አንድ ፡ የተራበ ፡ ተማሪ ፡ የዕለት ፡ ምግብ ፡ ለማግኘት ፡ ሲል ፡ ካንድ ፡ ቤት ፡ ደጃፍ ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጠራ ። ባለ ቤትዮዋም ፡ ተልባ ፡ ዘገነችና ፡ ተዘከረችው ። ነገር ፡ ግን ፡ ተማሪው ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ ዳቦ ፡ እየጋገረች ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ ድልኽ ፡ በቅቤ ፡ እየመታች ፡ ካንድ ፡ ጉልማሳ ፡ ጋራ ፡ ስትሳሳቅ ፡ ስላየ ፡ የነገሩን ፡ ፍጻሜ ፡ ለማወቅና ፡ ለመ ረዳት ፡ ሲል ፡ እንዳላወቀ ፡ አስመስሎ ፡ የተሰጠውን ፡ ተልባ ፡ አፍስሶ ፡ ይለቅም ፡ ገ/መር ።

ሴትዮዋም ፡ አፍላ ፡ ጨዋታ ፡ ሆኖ ፡ መንፈሷ ፡ ስለ ፡ ረካና ፡ የፍ ቅር ፡ ትዝታዋ ፡ ስለ ፡ ተጋጋለ ፡ ተማሪውን ፡ እባክህ ፡ እዚህ ፡ እበር ፡ ላይ ፡ አትግበስበስብኝ ፡ ሂድልኝ ፡ አለችው ። እሱም ፡ እመቤቴ ፡ አይቁጡ ፡



ተማሪውን ፡ እባክህ ፡ እዚህ ፡ እበር ፡ ላይ ፡ አትግበስበብኝ ፡ ሂድልኝ ፡ አለችው ።

የፈሰሰውን ፡ ሰብስቤ ፡ እሄድልዎታለሁ ፡ እያለ ፡ ተልባውን ፡ ሲለቃቅም ፡ ባልዮው ፡ ከውጭ ፡ ከተፍ ፡ አለ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ያ ፡ የመንደር ፡ ወስ ላታ ፡ ዘለለና ፡ እንዳ ፡ ተደበቀ ።

ባለቤቱም ፡ ላቡን ፡ እየጠረገ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሲገባ ፡ ድልኽ ፡ በቅቤ ፡ ተመቶ ፡ ዳቦ ፡ ተሰናድቶ ፡ አየና ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ለማነው ፡ ብሎ ፡ ሚስ ቱን ፡ ጠየቃት ። እሷም ፡ ይህ ፡ ተማሪ ፡ አምሮኛል ፡ ብሎ ፡ ስለ ፡ ማር ያም ፡ ዳቦ ፡ በቅቤና ፡ በድልኽ ፡ አሰናድልኝ ፡ ስላለኝ ፡ ለነፍሴ ፡ ይሆነ ኛል ፡ ብዬ ፡ አዘጋጀሁለት ፡ ስትል ፡ መለሰችለት ። ወዲያው ፡ ባልዮው ፡ ለማኙን ፡ ጠራና ፡ ዳቦህ ፡ በስሎልሃልና ፡ ና ፡ ይዘህ ፡ ሂድ ፡ አለው ። ተማ ሪውም ፡ በደስታ ፡ ሲሮጥ ፡ ገብቶ ፡ የተሰናዳውን ፡ ምግብ ፡ ለመውሰድ ፡ ጠጋ ፡ እንዳለ ፡ ባሏ ፡ ዘወር ፡ ሲልላት ፡ አይታ ፡ በጥቅሻ ፡ አነጋገር ፡ ተማሪ ፡



እረ ፡ ብሞት ፡ ብሏት ፡ በአ ዠፋዳው ፡ አደረገና ፡ ሴትየዋ ፡ ዐይኗ ፡ ሲንከራተት ፡ በሩን ፡ ትቶ ፡ እሮ ፡ ነሥቶ ፡ ወደ ፡ ጓዳ ፡ ገባ ።

እሁለት ፡ ብትለው ፡ እረ ፡ ብሞት ፡ ብሷት ፡ በአኮፋዳው ፡ አደረገና ፡ ሴት ዮዋ ፡ ወይኗ ፡ ሲንከራተት ፡ በሩን ፡ ትቶ ፡ እጅ ፡ ነሥቶ ፡ ወደ ፡ ጓዳ ፡ ገባ ።

ስለዚህም ፡ ባለቤቱ ፡ ምን ፡ ሆንክ ፡ ተሜ ፡ በሩን ፡ ትተህ ፡ ወደ ፡ ማጆት ፡ የምትሄደው ፡ ቢለው ፤ ቅድም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በዚህ ፡ ሲያልፍ ፡ አይቼ ፡ ነበር ፡ ምናልበት ፡ ተሳስቼ ፡ ይሆን ፡ ጌታዬ ፡ ሲል ፡ መለሰለት ። ባለቤቱም ፡ በነገሩ ፡ ተገርሞና ፡ ተደንቆላ ወደ ፡ ማጆት ፡ ቢገባ ፡ ያንን ፡ ወንደ ፡ ላጤ ፡ ከጋን ፡ ማኽል ፡ ተወትፎ ፡ አገኘው ። ወዲያው ፡ ተናደ ደና ፡ ሽመሉን ፡ መዘ ፡ ለመምታት ፡ ሲዘጋጅ ፡ የተደበቀው ፡ ስለ ፡ ተነሣ ፡ ግብ ፡ ግብ ፡ ተያያዙ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የበላ ፡ ባለውለታ ፡ ነውና ፡ ተማ ሪው ፡ ለባለቤቱ ፡ ረድቶ ፡ የወለላታውን ፡ እግር ፡ ዘርጥጦ ፡ ከጣሉት ፡ በኋላ ፡ ክርስቶስ ፡ ለተበደለ ፡ እርዳ ፡ ብሎ ፡ ዳቦውን ፡ ተሸክሞ ፡ መን ገዱን ፡ ቀጠለ ፡ ይባላል ።



የወበላታውን ፡ እግር ፡ ዘር ጥጦ ፡ ከጣሉት ፡ በኋላ ፡ ዳቦ ውን ፡ ተሸከሞ ፡ መንገዱን ፡ ቀጠለ ።

፨ እግዚአብሔር ፡ ሲሰጥ ፡ ምክንያት ፡ ያዛል ፤ የወለላታም ፡ ሥራ ፡ ከቀን ፡ ብዛት ፡ ይገለጣል ።

ኦራዊትን ፡ በጓደኝነት ፡ ስላስከተለ ፡ ሰው ።

በንድ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ይቀመጥ ፡ የነበረ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አያ ፡ ዝንጀሮን ፡ እባብንና ፡ ዐይጡትን ፡ አስከትሎ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አገር ፡ ለመሄድ ፡ መንገድ ፡ ጀመረ ።

እነዚህንም ፡ ሦስት ፡ አውሬዎች ፡ ይዘ ፡ ከጪት ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ሲጓዝ ፡ ውሎ ፡ ቀኑ ፡ ስለ ፡ መሸበት ፡ መንደር ፡ ወዳለበት ፡ ተጠግቶ ፡ የሚ ያድርበት ፡ ቦታ ፡ ሲፈልግ ፡ አንድ ፡ ሀብታም ፡ ባለጸጋ ፡ ቡልከውን ፡ አጣ ፍቶ ፡ ከደጁ ፡ ተቀምጦ ፡ አገኘ ። ከመሬት ፡ ወድቆ ፡ ሰላምታ ፡ ከቀረበለት ፡ በኋላ ፡ እባክህን ፡ ወንድሜ ፡ አሳድረን ፡ ብሎ ፡ ማረፊያ ፡ ቦታ ፡ ይሰጣቸው ፡ ዘንድ ፡ ለመነው ። ይህም ፡ ባለጸጋ ፡ አንተስ ፡ ብታድርም ፡ እኛ ፡ የምንበላውን ፡ ልትበላና ፡ የምንጠጣውንም ፡ ልትጠጣ ፡ ትችላለህ ፡ አብረውህ ፡ ከሉትም ፡




እባክህን ፡ ወንድሜ ፡ አሳድ ረን ፡ ብሎ ፡ ማረፊያ ፡ ቦታ ፡ ይሰጣቸው ፡ ዘንድ ፡ ለመነው ።

ተከታዮችህ ፡ ውስጥ ፡ ዐይጥም ፡ ብትሆን ፡ ከጐተራ ፡ (ከሪቅ) ፡ አጠገብ ፡ ብታ ድር ፡ የምትመገበው ፡ ጥራጥሬ ፡ ታገኛለች ፤ ዝንጀሮም ፡ ያገኘውን ፡ ሣሩንም ፡ ቅጠሉንም ፡ በልቶ ፡ ያድራል ፤ እረ ፡ ይህንን ፡ ክፉ ፡ መርዘኛ ፡ ጠላት ፡ ምን ፡ ላበላውና ፡ ወዴትስ ፡ ላሳድረው ፡ እችላለሁ ፡ ብለህ ፡ ይዘህብኝ ፡ መጣህ ፡ ብሎ ፡ በቁጣ ፡ ቃል ፡ መለሰለት ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ለመናገር ፡ የማይ ችል ፡ ጽምው ፡ እባብ ፡ ልሳኑ ፡ ሰብእ ፡ ተሰጥቶት ፡ ጌታዬ ፡ እረ ፡ እባክህ ፡ እኔንም ፡ ከጓደኞቼ ፡ አትለየኝ ፡ አብረህ ፡ አሳድረኝ ፡ ስለ ፡ ምግቤም ፡ ጉዳይ ፡

ቢሆን ፣ የእኔ ፣ እራትና ፣ ምሳ ፣ ይህ ፣ የምትረግጠው ፣ ዐፈር ፣ ነው ፤ ደግሞ ፣ በተንኰልም ፣ ቢሆን ፣ ስከፋ ፣ ብውል ፣ ከዚህ ፣ አስከትሎኝ ፣ ከመጣው ፣ አጠገብ ፣ ከቆመው ፣ ሰው ፣ አልብስም ፣ አለና ፣ እንዲያሳድረው ፣ ለመነው ። ከዚህ ፣ በኋላ ፣ ባለቤቱ ፣ በእባቡ ፣ አነጋገር ፣ ደንግጦ ፣ ተገርሞ ፣ በአንግድነት ፣ የመጣውን ፣ ሰውና ፣ አብረውትም ፣ ያሉትን ፣ ሦስት ፣ አውሬዎች ፣ እንደ ፣ ባልትናው ፣ መጠን ፣ አስተናግዶ ፣ ከቤቱ ፣ አሳድሮ ፣ ሲነጋ ፣ ዉት ፣ ወደሚሄዱበት ፣ ሸኛቸው ። በዚያኑ ፣ ቂን ፣ አንድ ፣ ነገረኛ ፣ ሰው ፣ ካገረ ፣ ገዢው ፣ ዘንድ ፣ ሄዶ ፣ በሰው ፣ ዘንድ ፣ ክልክል ፣ የሆኑትን ፣ አውሬዎች ፣ አሳድሯል ፣ ብሎ ፣ ነግሮ ፣ ኖሮ ፤ በዋጠቅ ፣ ተይዞ ፣ እንዲቀርብለት ፣ ባለ ሥልጣኑ ፣ ለጭቃ ፣ ሹመ ፣ የሚያስቸኩል ፣ ትእዛዝ ፣ ሰጠ ።

ጭቃ ፣ ሹመም ፣ ሳይውል ፣ ሳያድር ፣ ገሥግሦ ፣ ደርሶ ፣ ያንን ፣ ባለጸጋ ፣ ሰው ፣ በወታደር ፣ እጁን ፣ አሲዞ ፣ ሲያክተፋትፍ ፣ ለገዢው ፣ አደረሰለት ። ይኸም ፣ ባለሥልጣን ፣ ወዲያው ፣ ከችሎቱ ፣ ተቀምጦ ፣ የዚህን ፣ አራዊት ፣



ይህም ፣ ባለሥልጣን ፣ ወዲያው ፣ ከችሎቱ ፣ ተቀምጦ ፣ ፈረደ ።

ያሳደረ ፣ ሰው ፣ ንብረትና ፣ ሀብት ፣ በሙሉ ፣ ለመንግሥት ፣ እንዲገባ ፣ ፈረደ ። ባለጸጋውም ፣ ያለ ፣ ከብቱንና ፣ ንብረቱን ፣ ከተወረሰ ፣ በኋላ ፣ በሰጠሁበት ፣ እጄ ፣ ለምኜ ፣ ተቀብዬ ፣ በተከበርኩበት ፣ አገር ፣ ተዋርጄ ፣ ደኸይቼ ፣ አልቀመጥም ፣ በማለት ፣ ወደ ፣ ስደት ፣ ለመሄድ ፣ ብዙ ፣ ቀናት ፣ በጉዞ ፣ ካሰለፈ ፣ በኋላ ፣ ከመንገድ ፣ ዳር ፣ አንዲት ፣ ወፍራም ፣ ዐይጥ ፣ አየ ። ወደርሷ ፣ ተጠግቶ ፣ ሰማሽ ፣ ዐይጢት ፣ ይኸውልሽ ፣ ከዚያ ፣ ሰው ፣ ጋራ ፣ ሆናችሁ ፣ በመጣችሁ ፣ ጊዜ ፣ አንቺንና ፣ አያ ፣ ዝንጀሮን ፣ እንዲሁም ፣ እባብን ፣ ከቤቴ ፣ ስላሳደርኩ ፣

ደኃፍ ፣ በመለስ ፣ ማጀት ፣ በጐረሥ ፣ ያለው ፣ ሀብቴ ፣ ንብረቴ ፣ ተወርሶ ፣ ካገር ፣ እንድወጣ ፣ ተፈረደብኝ ፤ በዚህ ፣ ምክንያት ፣ ጕዳትና ፣ ችግር ፣ ስለ ፣ ደረሰብኝ ፣ የችሎታሽን ፣ ያኽል ፣ እርዳታ ፣ አድርጊልኝ ፣ ሲል ፣ ጥያቄ ፣ አቀረበላት ። እሷም ፣ ጌታዬ ፣ ሆይ ፣ እኔ ፣ የምኖረው ፣ መሬት ፣ ጭሬ ፣ ለቅሜ ፣ ነው ፤ አንተን ፣ የምረዳበት ፣ ምን ፣ ዐቅም ፣ አለኝ ፣ ብለህ ፣ ነው ፤ ነገር ፣ ግን ፣ አንድ ፣ ቦታ ፣ ላይ ፣ ያየሁት ፣ የተቀበረ ፣ ዕቃ ፣ አለና ፣ መቄፈሪያ ፣ የሚሆን ፣ አንካሴ ፣ ይዘህ ፣ ተከተለኝ ፣ አለችው ። ይህም ፣ ሰው ፣ ቃሏን ፣ ሰምቶ ፣ መቄፈሪያውን ፣ ይዞ ፣ ተከተለ ። ዐይጢትም ፣ አንድ ፣ ዱሮ ፣ ከተማ ፣ ተሠርቶበት ፣ ወደ ፣ ነበረ ፣ ስፍራ ፣ ወስዳ ፣ እዚህ ፣ ላይ ፣ ቁፍር ፣ ስትል ፣ አመለከተችው ። እንደ ፣ ተነገረውም ፣ ጥቂት ፣ ሰዓት ፣ ከቈፈረ ፣ በኋላ ፣ አንድ ፣ ማሰሮ ፣ ወርቅና ፣ ብር ፣ አገኘ ። በዚህም ፣ እጅግ ፣ ተደስቶ ፣ ጠቋሚዋን ፣ ስላደረገችለት ፣ ርዳታ ፣ ብዙ ፣ ከመሰናት ፣ በኋላ ፣ አሀያና ፣ በቅሎውን ፣ ገዝቶ ፣ ጕዞውን ፣ ወደ ፣ ፊት ፣ ቀጠለ ። ጥቂት ፣ እንደ ፣ ሄደም ፣ ያንን ፣ ከአውሬዎቹ ፣ ጋራ ፣ አሳድሮት ፣ የነበረውን ፣ ሰው ፣ አገኘና ፣ አንተንና ፣ አናያ ፣ ዝንጀሮን ፣ ከቤቴ ፣ በማሰደሬ ፣ የደረሰብኝ ፣ አደጋና ፣ ችግር ፣ እጅግ ፣ አሰቃቂ ፣ ነው ፣ ካለው ፣ በኋላ ፣ ዐይጥ ፣ ያደረገችለትን ፣ ከፍተኛ ፣ ውለታ ፣ በሰፈው ፣ ገለጸለት ፤ ቀጥሎም ፣ ወንድሜ ፣ አንተም ፣ በበኩልህ ፣ ችሮታህን ፣ አድርግልኝ ፣ ብሎ ፣ ልመናውን ፣ አቀረበለት ። እሺ ፣ መልካም ፣ ነው ፣ ከብቶችህ ፣ ከነ ጭነታቸው ፣ ከዚህ ፣ ይረቁ ፣ ብሎ ፣ የሚበላውን ፣ እኽል ፣ እንኳ ፣ ሳይ ሰጠው ፣ የሚጠቅምህ ፣ ነገር ፣ ስላሰ ፣ አንድ ፣ ጊዜ ፣ አይተኸው ፣ ትመለሳለህና ፣ እንሂድ ፣ ብሎ ፣ እገደል ፣ አፋፍ ፣ ሲደርሱ ፣ ወርውሮት ፣ ተመለሰ ።



ሰውዬውን ፣ ወዲያው ፣ እገደል ፣ አፋፍ ፣ ሲደርሱ ፣ ወርወሮት ፣ ተመለሰ ።

ያም ፡ ሰው ፡ በዚያ ፡ ገደል ፡ ተንከባሎ ፡ እሥር ፡ ሲደርስ ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ዝንጀሮ ፡ ዠርባ ፡ ላይ ፡ ወደቀ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ዝንጀሮው ፡ ሁሉ ፡ እየተጨጫኸ ፡ ከበ ፡ ከወዴት ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ ከመረመረ ፡ በኋላ ፡ ከመከላቸው ፡ አንዱ ፡ እቤቱ ፡ ባደረ ፡ ጊዜ ፡ የዋለለትን ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ በማስታወስና ፡ በማሰብ ፡ መቶ ፡ የሚሆኑ ፡ ጓደኞቹን ፡ ይዞ ፡ ተሸክሞ ፡ አፋጥ ፡ እወጣው ። ከሞት ፡ በመዳኑ ፡ ለፈጣሪው ፡ ምስጋና ፡ አቅርቦ ፡ ላያ ፡ ዝንጀሮ ፡ አራዊት ፡ ከቤቱ ፡ በማሰደሩ ፡ ያገኘውን ፡ መከራ ፡ ተሰዶ ፡ አገር ፡ ለቆ ፡ ሲሄድ ፡ ወይጥ ፡ ያደረገችለትን ፡ መልካም ፡ ርዳታ ፡ ያንን ፡ ገደል ፡ የሰደደውን ፡ ሰው ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ዘርዝሮ ፡ ነገረውና ፡ በች ሎታው ፡ መጠን ፡ የገንዘብ ፡ እርጥባን ፡ እንዲያደርግለት ፡ አጥብቆ ፡ ለመነው ።

ዝንጀሮም ፡ እኔ ፡ ገንዘብ ፡ የለኝም ፤ የማይሆንልኝንም ፡ አልናገር ፤ ይሁን ፡ አንጂ ፡ በዚህ ፡ ባሻጋሪያችን ፡ ያሉት ፡ ሕዝቦች ፡ አዝመራ ፡ የደረሰበት ፡ ወራት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እኔና ፡ ወገኖቼ ፡ ብዙ ፡ እድርገን ፡ ልናውካቸው ፡ እንችላለን ። እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ባልንጀሮቼን ፡ ይገር ፡ ላንተ ፡ ስል ፡ አሰደዳለሁና ፡ አንተ ፡ ላገሩ ፡ ሰዎች ፡ ሰብላችሁን ፡ ዝንጀሮ ፡ እንዳይበላባቸው ፡ ድግምት ፡ ዐውቃለሁ ፡ ብለህ ፡ ገንዘብ ፡ ከሕዝቡ ፡ ላይ ፡ ተቀበል ፤ ለጊዜው ፡ የተናገርከው ፡ እውነት ፡ እንዲመስልልህና ፡ እንዲረዳህም ፡ እኛ ፡ ዛሬና ፡ ነገ ፡ በጣም ፡ እድርገን ፡ ሕዝቡን ፡ አናስቸግረዋለን ፡ ሲል ፡ ምክር ፡ ሰጠው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይህ ፡ ዝንጀሮ ፡ ከነጅሮቹ ፡ በየማሳው ፡ እየገባ ፡ ነዶውን ፡ ከተከመረበት ፡ እየዘረጠጠ ፡ ተሸክሞ ፡ መሄድ ፡ ሲገምር ፡ አገራው ፡ በያለበት ፡ መጨጫኸ ፡ ያዘ ። ይህ ፡ ከዝንጀሮው ፡ ጋራ ፡ ስምምነት ፡ ያደረገ ፡ ሰው ፡ ሕዝቡን ፡ ገንዘብ ፡ ለኔ ፡ ብትሰጡኝ ፡ መድኀኒት ፡ ዐውቅ ፡ ነበር ፡ አላቸው ። ይህ ፡ ከሆነማ ፡ በማለት ፡ የድካሙን ፡ ዋጋ ፡ ለመስጠት ፡ በንድነት ፡ በተስማሙ ፡ ጊዜ ፡ ዝንጀሮው ፡ ከመናጠቁ ፡ ስለ ፡ ታገሡ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሳይቀር ፡ በነፍስ ፡ ወከፍ ፡ ሁሉም ፡ ገንዘብ ፡ አዋጥተው ፡ ስደተኛውን ፡ ሰው ፡ በንድ ፡ ጊዜ ፡ ጌታ ፡ አደረጉት ።

እሱም ፡ ከሕዝብ ፡ ባገኘው ፡ ገንዘብ ፡ ብዙ ፡ አህዮችና ፡ በቅሎዎች ፡ ልብስም ፡ ከገዛ ፡ በኋላ ፤ እንደ ፡ ልማዱ ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አገር ፡ ሲጓዝ ፡ እባብን ፡ ከመንገዱ ፡ ላይ ፡ አገኘው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የደረሰበትን ፡ ችግርና ፡ ፈተና ፡ ሁሉ ፡ ለነአያ ፡ ዝንጀሮ ፡ በነገራቸው ፡ ሁኔቱ ፡ በሙሉ ፡ ዘርዝሮ ፡ ከገለጸለት ፡ በኋላ ፡ ያ ፡ በእንግድነት ፡ አሳድሮት ፡ የነበረው ፡ ሰው ፡ አስቀድሞ ፡ እባቡ ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፡ ሁሉ ፡ ክፋቱን ፡

እንደ ፡ ፈጸመበት ፡ ዐይጥና ፡ ዝንጀሮ ፡ ግን ፡ በዘመነ ፡ ሕይወቱ ፡ የማይዘነጋ ፡ ውለታ ፡ እንደ ፡ ዋሉለት ፡ አስረድቶ ፡ በል ፡ አንተም ፡ እንደ ፡ ጓደኞችህ ፡ የምታደርገውን ፡ ችሮታ ፡ ስጠኝ ፡ ሲል ፡ ጠየቀው ።

እባቡም ፡ እኔ ፡ ንብረትና ፡ ሀብት ፡ ስለሌለኝ ፡ ምንም ፡ የምረዳህ ፡ ነገር ፡ የለኝም ፤ ቢሆንም ፡ በስተሰሜን ፡ በኩል ፡ በሚታይህ ፡ ተራራ ፡ ባሻገር ፡ ባለው ፡ ታላቅ ፡ ከተማ ፡ የሚኖረው ፡ ንጉሥ ፡ በጣም ፡ የሚወዳትን ፡ አንዲት ፡ ቅንጣት ፡ ልጁን ፡ ለመዳር ፡ ይዘጋጃልና ፡ ይህችን ፡ ልጅ ፡ እኔ ፡ እንደ ፡ ምንም ፡ በርትቼ ፡ በመርዝ ፡ ልነድፋት ፡ እችላለሁ ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አንተ ፡ ይህችን ፡ መድኀኒት ፡ አጥብቀህ ፡ ያዝና ፡ በታመመች ፡ ሰዓት ፡ አድናታለሁ ፡ በማለት ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ዘንድ ፡ ቅረብ ፤ ከተፈወሰችም ፡ በኋላ ፡ ላንተው ፡ እንዲድርልህ ፡ ጠይቀው ፡ አለው ። ይህንንም ፡ ተነጋግረው ፡ ከበቁ ፡ በኋላ ፡ ተያይዘው ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ሄዱና ፡ ሰውዬው ፡ እውጫ ፡ ሆኖ ፡ ሲጠባበቅ ፡ እባቡ ፡ ግንቡን ፡ ሰርስሮ ፡ ገብቶ ፡ ልጅቷን ፡ ከተኛችበት ፡ ነደፋት ። ወዲያው ፡ ዘመዶቿ ፡ መሳፍን



እባቡ ፡ ግንቡን ፡ ሰርስሮ ፡ ገብቶ ፡ ልጅቷን ፡ ከተኛችበት ፡ ነደፋት ።

ቱና ፡ መኳንንቱ ፡ ጭምር ፡ ተጠርተው ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ትልቅ ፡ ጭንቅ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፤ ስደተኛው ፡ ሰው ፡ ንጉሥ ፡ ይህችን ፡ የታመመች ፡ ልጃቸውን ፡ ለሚስትነት ፡ ቢመርቁልኝ ፡ እኔ ፡ አድናት ፡ ነበር ፡ ብሎ ፡ ላሽከሮች ፡ አወራ ። ይኸውም ፡ ከንጉሡ ፡ ዦሮ ፡ ስለ ፡ ደረሰ ፡ ቤተ ፡

መንግሥቱ ፣ በታላቅ ፣ ሐዘን ፣ ላይ ፣ ነበርና ፣ አስጠርቶ ፣ እረ ፣ ከሆነልህ ፣ ምን ፣ ከፋኝ ፣ እንዲያውም ፣ የፌተኛው ፣ እጮኛዋ ፣ ዕድል ፣ እላማረምና ፣ አንተው ፣ ታገባታለህ ፣ ከዚህም ፣ በላይ ፣ ብዙ ፣ ርስት ፣ ጉልት ፣ ሀብት ፣ ንብረት ፣ እሰጥሃለሁ ፣ ብሎ ፣ ቃል ፣ ኪዳን ፣ ገባለት ። እሱም ፣ በያዘው ፣ መደጎኒት ፣ ልጅቷን ፣ ፈጥኖ ፣ እዳናት ። ከዚህ ፣ በኋላ ፣ በቄየው ፣ ወግና ፣ ሥርዐት ፣ መሠረት ፣ ጋብቻው ፣ ተፈጽሞ ፣ በጌትነት ፣ ትዳሩን ፣ እመቆ ፣ ቤቱን ፣ አደርጅቶ ፣ በሰላም ፣ ኖረ ፣ ይባላል ።

፨ እባብ ፣ የተናገረው ፣ ደረሰ ፤ ከሰው ዬው ፣ በስተቀር ፣ አራዊቱ ፣ በሙሉ ፣ ውለታቸውን ፣ እንደ ፣ ተቻላቸው ፣ መልሰዋል ፤ ሰውዬው ፣ ግን ፣ እኽል ፣ ላበደረ ፣ ዐፈር ፣ ወርቅ ፣ ላበደረ ፣ ጠጠር ፣ እንደ ፣ ተባለው ፣ ሁሉ ፣ በለውለታውን ፣ ገደል ፣ በመጣሉ ፣ ውሎ ፣ ቢያድርም ፣ ቅሉ ፣ ፍርዱን ፣ መቀበሉ ፣ የማይቀር ፣ ነው ። ሰው ፣ በተፈጥሮው ፣ አስተዋይና ፣ ዐዋቂ ፣ ሆኖ ፣ ሳለ ፣ እንስሳት ፣ ያደረጉትን ፣ ርኅራኄ ፣ ያኽል ፣ ሳይኖረው ፣ ቀርቶ ፣ በለውለታ ፣ ስደተኛውን ፣ ገደል ፣ መጣሉ ፣ የተገባ ፣ እይደለም ።

ስለ ፡ አንድ ፡ አንበሳና ፡ ዝንጆሮ ።

አንድ ፡ እንበሳ ፡ ከእንስት ፡ ጓደኛው ፡ ጋር ፡ በዋሻ ፡ ውስጥ ፡ ይኖር ፡ ነበር ፤ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ለአደን ፡ ወደ ፡ ሩቅ ፡ ሄዶ ፡ ሳለ ፡ አንድ ፡ ገመሬ ፡ ዝንጆሮ ፡ ወደ ፡ አራዊት ፡ ንጉሥ ፡ ሰፈር ፡ ሄዶ ፡ ከሁፋኑ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፤ ትከሻውን ፡ እየነቀነቀ ፡ በመኩራራት ፡ ሲናገር ፡ እንስቲቱ ፡ አንበሳ ፡ እንዲህ ፡ ስትል ፡ ጠየቀችው ።

ጥ ፡ እረ ፡ ግንባርዎን ፡ ምን ፡ እንዲህ ፡ አጠቁረው ፤

መ ፡ በየቀኑ ፡ ከምሥራቅ ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ስለምዘምት ፡ የፀሐዩ ፡ ኃይል ፡ ነዋ ።

ጥ ፡ እጅዎንስ ፡ ምን ፡ አጠቁረው ፤

መ ፡ በቀኝ ፡ እጂ ፡ ጦር ፡ በግራ ፡ እጂ ፡ ልጓም ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ በመያዜ ፡ ነዋ ።

ጥ ፡ እግርዎንስ ፤

መ ፡ ከጧት ፡ እስከማታ ፡ ርከብ ፡ በመቄንጠጥ ፡ ነዋ ።

ጥ ፡ እረ ፡ ከሆነስ ፡ ሆነና ፡ መቀመጫዎን ፡ ምን ፡ አቈሰለው ፤

መ ፡ የፈረሱ ፡ ኮርቻ ፡ ነዋ ።

ጥ ፡ ስምዎስ ፡ ማን ፡ ይባላል ፤

መ ፡ ሽኩር ፡ መንዲስ ፡ (መብረቁ) ፡ ብሎ ፡ እስረዳና ፡ ነገም ፡ ተመልሶ ፡ እንደሚገበኛት ፡ ቃሉን ፡ ሰጥቶ ፡ ስንብት ፡ በመጠየቅ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ተመልሶ ፡ ሄደ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አንበሳው ፡ ከሄደበት ፡ ጫካ ፡ ሲያድን ፡ ውሎ ፡ ሰቤተ ፡ ሰቡም ፡ የሚሆነውን ፡ ድርሻ ፡ ይዞ ፡ ከቤቱ ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ አንበሳይቱ ፡ ንቀት ፡ በሞላበት ፡ አስተያየት ፡ ተቀበለችው ። እሱም ፡ የወትሮ ፡ ጠባይዋ ፡ በመለወጡ ፡ ተገርሞ ፡ ውዲቱ ፡ ሚስቱ ፡ ሆይ ፡ ጠባይሽ ፡ ዛሬ ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ተለወጠብኝ ፡ ምንስ ፡ አግኝቶሽ ፡ ይሆን ፡ ሲል ፡ ጠየቃት ።

እርስዎም ፡ ወንድ ፡ ነኝ ፡ ይሉ ፡ ይሆናል ፡ ደግሞ ፡ አሁን ፡ መጠየቅዎ ፡ አይገርምም ፡ ከጧት ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ዕድሜ ፡ ልኩን ፡ ከጦርነት ፡ ሳይለይ ፡ የሚኖር ፡ ጀግና ፡ ገና ፡ ዛሬ ፡ ነው ፡ ያየሁት ፡ ብላ ፡ መለሰችለት ።

አንበሳውም ፡ በመገረም ፡ ለመሆኑ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ያለ ፡ ወንድ ፡ ነው ፡ እስቲ ፡ ሁኔታውን ፡ በዝርዝር ፡ ንገሪኝ ፡ ሲል ፡ ጠየቃት ፤ እሷም ፡ የኃይሉን ፡ ብርታትና ፡ የግርማውን ፡ አስፈሪነት ፡ አስረዳችው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የሚመጣበት ፡ ቀንና ፡ ሰዓት ፡ መቼ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ጠየቃት ። እሷም ፡ ነገ ፡ ከቀኑ ፡ በአራት ፡ ሰዓት ፡ ብላ ፡ ስላስረዳችው ፡ እድኖ ፡ ከመጣው ፡ ሥጋ ፡ ድርሻዋን ፡ ሰጥቶ ፡ በሰላም ፡ አደሩ ። በባለቤቱ ፡ የተናቀው ፡ አንበሳ ፤ በማግስቱ ፡ ከቀጠሮው ፡ ሰዓት ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ከዝናው ፡ በስተቀር ፡ በመልክ ፡ ያላወቀውን ፡ ጀግና ፡ ለማየትና ፡ ለማወቅ ፡ ከሰፈሩ ፡ ሳይርቅ ፡ ከፍ ፡ ከለ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ይጠባበቀው ፡ ዠመረ ። የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ሲደርስም ፡ ገመሬው ፡ ዝንጆሮ ፡ ጉምሰል ፡ ጉምሰል ፡ እያለ ፡ ወደ ፡ ዋሻው ፡ ሲገባ ፡ አየ ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ትላንት ፡ ሲነገርለት ፡ የዋለው ፡ ጀግና ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዐወቀ ፡ ሳያንኰሻኰሽ ፡ በዝግታ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ አመራ ።

ዝንጀሮው ፡ ከአንበሳው ፡ ዋሽ ፡ ደርሶ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ዋላችሁ ፡ ከማ ለቱ ፡ አንበሳይቱ ፡ ብድግ ፡ ብላ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ ደኅና ! ፡ ይግቡ ፡ ብላ ፡ በአክብሮት ፡ ተቀበለችው ። እሱም ፡ እንደ ፡ ልማዱ ፡ ከአንበሳው ፡ አል ጋ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ያንኑ ፡ የወንድነቱን ፡ ሥራ ፡ ማውራት ፡ ሲዝምር ፡ ጌታው ፡ አንበሳ ፡ ደርሰው ፡ ከደጃፉ ፡ ቆሙ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ዝንጀሮው ፡ እንበሳውን ፡ በማየቱ ፡ እንኳንስ ፡ ጨዋታውን ፡ ሊቀጥል ፡ እንዲያውም ፡ ከድንጋጤው ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ውርጭ ፡ እንዳጠቃው ፡ ሁሉ ፡ ይንዘፈ ዘፍ ፡ ዝምር ። አንበሳይቱም ፡ ሁኔቴውን ፡ ታመልክታ ፡ ምነው ፡ አንቱ ፡ ዝም ፡ አሉ ፤ ይጫወቱ ፡ እንጂ ፡ ምን ፡ ሆኑ ፡ ምንስ ፡ አገኝዎት ፡ ብላ ፡ ደጋግማ ፡ ጠየቀችው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ መልስ ፡ ባለማግኘቷ ፡ ተገርማ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ብትመለከት ፡ ባሏን ፡ አበሩ ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ አየችው ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ የደረሰውን ፡ መለዋወጥ ፡ ተመልክታ ፡ በመገረም ፡ ላይ ፡ ሁና ፡ ሰለች ፡ አንበሳው ፡ ዘው ፡ ብሎ ፡ ገባና ፡ ትናንት ፡ የነገርሽኝ ፡ ጀግና ፡ እርሱ ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ ሌላ ፡ ብሎ ፡ ሚስቱን ፡ ጠየቃት ። እሷም ፡ አዎን ፡ እሱ ፡ ነው ፡ ብላ ፡ አረጋገጠች ። እውነተኛ ፡ ባለግርማ ፡ የሆነው ፡ አን በሳ ፡ ወደ ፡ ዝንጀሮው ፡ ፊቱን ፡ መለስ ፡ አድርጎ ፡ ማን ፡ ትበላለህ ፡ አለው ።



የወንድነቱን ፡ ሥራ ፡ ማውራት ፡ ሲጀምር ፡ ጌታው ፡ አንበሳ ፡ ደርሰው ፡ ከደጃፉ ፡ ቆሙ ።

ዝንጀሮውም ፡ ናላው ፡ ዙሮ ፡ በሚገኝበት ፡ የጭንቅ ፡ ሰዓት ፡ ይህ ፡ ጥያቄ ፡ ስለ ፡ ተደረገለት ፡ ብስብሱ ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ። ከፍርሀቱ ፡ ከመንቀጥቀጡና ፡ ከጭንቀቱም ፡ የተነሣ ፡ ሰውነቱ ፡ ስቶ ፡ በርስሐቱ ፡ ተጨማልቆ ፡ ይታይ ፡ ነበር ።

ምን ፡ ልትፈልግ ፡ መጣህ ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቀው ፡ ዓምና ፡ የበላኸ ውን ፡ ልጄን ፡ ለጤና ፡ ያድርግልህ ፡ ለማለት ፡ ነው ፡ አለው ። አንበሳውም ፡ ሥቆ ፡ ሚስቱን ፡ ጀግና ፡ ነው ፡ ብለሽ ፡ ስሙን ፡ እያጋነንሽ ፡ የነገርሽኝ ፡ ይህ ፡ የምታይው ፡ ውዳቂ ፡ አይደለምን ፡ አላት ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ትልቅነቱን ፡ ለማሰየት ፡ ሲል ፡ አንዳች ፡ የማጥቃት ፡ ሥራ ፡ ሰይሠራ ፡ ዝንጀሮውን ፡ በሰላም ፡ አንዲሄድ ፡ ፈቅዶ ፡ አሰናበተው ።

እንስቲቱ ፡ አንበሳም ፡ ከባሏ ፡ ከአራዊት ፡ ንጉሥ ፡ በላይ ፡ ጕበዝና ፡ ጀግና ፡ የሌለ ፡ መሆኑን ፡ ስለ ፡ ተረዳችው ፡ ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ዝምሮ ፡ ዕጥፍ ፡ ከበሬታ ፡ አደረገችለት ፡ ይበላል ።

※ እውነተኛውን ፡ ነገር ፡ በሐሰት ፡ ለውጦ ፡ መገንት ፡ ለጊዜው ፡ የሚጠቅም ፡ መስሎ ፡ ቢታይም ፡ የኋላ ፡ ኋላ ፡ ስለሚገለጽ ፡ ከባሰ ፡ ውርደት ፡ ላይ ፡ ይጥላልና ፡ ከእንደዚህ ፡ ያለው ፡ ተግባር ፡ መራቅ ፡ ይገባል ።

ስለ ፡ አንድ ፡ ሰውና ፡ አንበሳ ።

ላንድ ፡ ያንበሳ ፡ ግልገል ፡ እናቱ ፡ ከልጅነቱ ፡ ዝምራ ፡ ከቀይ ፡ ምላ ሱና ፡ ከጥቁር ፡ ራሱ ፡ (ሰው) ፡ ተጠንቀቅ ፡ እያለች ፡ ታስጠናውና ፡ ትመ ክረው ፡ ነበር ። ይህ ፡ ግልገል ፡ አንበሳ ፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ፍየ ልን ፡ ስታልፍ ፡ አይቶ ፡ ወዲት ፡ ትሄጃለሽ ፡ እንቺስ ፡ ማን ፡ ትበያለሽ ፡ ብሎ ፡ ጠየቃት ።

እሷም ፡ ፍየል ፡ እበላለሁ ፤ ሰው ፡ የሚበል ፡ ወገኖቼን ፡ የፈጀና ፡ እያረደ ፡ የሚበላ ፡ ጠላት ፡ ባገር ፡ ስላለ ፡ ከሱ ፡ ለማምለጥ ፡ እሸሻለሁ ፡ አለች ። በግንና ፡ በሬንም ፡ በተራ ፡ አገናና ፡ ቢጠይቃቸው ፡ እነሱም ፡ እንደ ፡ ፍየሊቱ ፡ መለሱለት ።

እንደዚሁ ፡ ዝኖንንም ፡ በጠገቡ ፡ ሲያልፍ ፡ ጠየቀው ። ሰው ፡ የሚ በል ፡ ጠላት ፡ ወገኖቼን ፡ እያደነ ፡ ስለ ፡ ጨረሳቸው ፡ ለማምለጥ ፡ እሸሻ

ለሁ ፡ አለው ። ሌሎቹም ፡ የዱር ፡ አራዊት ፡ እየተጠየቁ ፡ ይህንኑ ፡ የመ
ሰለ ፡ መልስ ፡ ሰጡት ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጕዳዩን ፡ ሰምቶ ፡ በመገረም ፡ ከሰው ፡ ጋራ ፡ የሚያ
ጋጥመውን ፡ ጊዜ ፡ ሲጠባበቅ ፡ ቈየ ። ሰው ፡ የሚባለውም ፡ ፍጥረት ፡
ግዙፍነቱ ፡ ከዝኖን ፡ በላይ ፡ ይመስለው ፡ ነበር ፤ አንበሳውም ፡ እያደገና ፡
እየጐረመሰ ፡ ሄደ ። ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አጭር ፡ ቀጭን ፡ የሆነ ፡
አንድ ፡ ሰው ፡ ጓዙን ፡ ይዘ ፡ ባጠገቡ ፡ ሲያልፍ ፡ አየ ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፡
አንተ ፡ ማን ፡ ትባላለህ ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ፡ እሱም ፡ ሰው ፡ አባላለሁ ፡
ብሎ ፡ መለሰለት ።

ሰው ! ፡ ሰው ! ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ አንተን ፡ ሁሉም ፡ ክፉ ፡ ነው ፡ የሚ
ሉህ ፡ ሲል ፡ ጠየቀው ። ሰውየውም ፡ እኔስ ፡ ክፉ ፡ አይደለሁም ፡ ቤት ፡
ለቸገራቸው ፡ ቤት ፡ ገንዘብ ፡ ለቸገራቸው ፡ ገንዘብ ፡ እኽል ፡ ለቸገረው ፡
እኽል ፡ ከመስጠት ፡ በቀር ፡ በማንም ፡ ላይ ፡ ቢሆን ፡ ክፉ ፡ ሠርቼ ፡ አላው
ቅም ፡ ሲል ፡ መለሰለት ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አንበሳው ፡ በል ፡ እንግዲያው ፡
እኔ ፡ የምኖርበት ፡ አንድ ፡ ቤት ፡ ሥራልኝ ፡ አለው ። ሰውየውም ፡ ትልቅ ፡
ሣጥን ፡ ባጋሰሰ ፡ ጭኖ ፡ ይዘ ፡ ነበርና ፡ እንሆ ፡ እንደ ፡ ቤት ፡ ሆኖ ፡ ሊያገለግ
ልም ፡ ሳይችል ፡ አይቀርምና ፡ ከዚህ ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ ይስማማዎት ፡ እን
ደ ፡ ሆነ ፡ ይሞክሩት ፡ ብሎ ፡ ከፈተለት ። አንበሳውም ፡ እሣጥኑ ፡ ውስጥ ፡ እን
ደ ፡ ገባ ፡ መክደኛውን ፡ ገጥሞ ፡ ቁለፈበትና ፡ አሳት ፡ ላይ ፡ ውሃ ፡ ጥዶ ፡ ያፈሳ ፡
ዠመር ። አንበሳውም ፡ ምነው ፡ አንተ ፡ ከፈትልኝ ፡ እንጂ ፡ አለው ። ሰው
የውም ፡ እሺ ፡ ጌታዬ ፡ አቶ ፡ አንበሳ ፡ አሁን ፡ እከፍትልዎታለሁ ፡ ብሎ ፡
መለሰ ፤ ውሃውም ፡ ተንተክትክ ፡ እንደ ፡ ፈሳ ፡ እጕኑ ፡ ላይ ፡ በተቀነበበ ፡ ፋጋ ፡
(ቅል) ፡ እየቀዳ ፡ አንበሳው ፡ እሣጥኑ ፡ ውስጥ ፡ እንዳለ ፤ ጠጉሩ ፡ እስኪመ
ለጥ ፡ ድረስ ፡ ውሃውን ፡ በቀዳዳው ፡ ለቀበት ። አንበሳውም ፡ ሥቃይ ፡
ስለ ፡ በዛበት ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ድምፅ ፡ ጮኸ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የፈላውን ፡ ውሃ ፡
በላዩ ፡ ላይ ፡ ጨረሰና ፡ ሣጥኑን ፡ ቢከፍተው ፤ አንበሳው ፡ ጠጉሩ ፡ አልቆ ፡
እንደ ፡ ተመላለጠ ፡ ከሣጥኑ ፡ ወጥቶ ፡ ሸሸ ። ከወገኖቹ ፡ እንደ ፡ ተቀላቀለም ፡
ሰው ፡ የሚባል ፡ በላጋራችን ፡ እንዞ ፡ እንዳህ ፡ እደርጎ ፡ ሰደደኝ ፤ ወገኔ ፡
የሆንክ ፡ ሁሉ ፡ ይህን ፡ ብድር ፡ በዚያ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ክል መለስክልኝ ፡
በቀር ፡ የዝምድናህን ፡ ልክና ፡ መጠን ፡ ላውቅልህ ፡ አልችም ፡ በ"ለት ፡
ድምፁን ፡ ከፍ ፡ አደርጎ ፡ ስላሰማ ፤ አንበሳዎቹ ፡ በሙሉ ፡ ተሰብስበው ፡

ምራን ፡ እንሄዳለን ፤ አጥቂ ፡ ጠላትህንም ፡ እናጠፋልሃለን ፡ በማለት ፡ ቃላ
ቸውን ፡ ሰጡት ።

ባለጋራ ፡ ነው ፡ ወደሚሉት ፡ ሰው ፡ ሁሉም ፡ አብረው ፡ ሲገሠግሡ ፤
ያ ፡ ሰውም ፡ በበኩሉ ፡ ብድር ፡ የሚመልስ ፡ ጠላት ፡ ይመጣብኛል ፡
በማለት ፡ አስቀድሞውኑ ፡ ስለ ፡ ጠረጠረ ፡ ከትልቅ ፡ ዛፍ ፡ ላይ ፡ ወጥቶ ፡
አገኙት ። አንበሶቹም ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ ዛሬ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ አያመልጠ
ንም ፤ እርስ ፡ በርሳችን ፡ እየተነባበርን ፡ ተቀጣጥለን ፡ አለበት ፡ ደርሰን ፡
እናወርደዋለን ፡ በማለት ፡ ተስማሙ ። ተጠቂውም ፡ አንበሳ ፡ ብድሩን ፡
ለመመለስ ፡ እንዲመቸው ፡ በመጨረሻው ፡ ጫፍ ፡ እንዲሆን ፡ መከሩት ፤
እሱ ፡ ግን ፡ እኔ ፡ ከታች ፡ ሆኜ ፡ እሸከማችኋለሁና ፡ እናንተ ፡ በኔ ፡ ላይ ፡
ተረባርባችሁ ፡ በመቀጣጠል ፡ ደርሰችሁ ፡ አጥቂ ፡ ጠላታችንን ፡ ብትይ
ዙት ፡ ይሻላል ፡ ሲል ፡ አሳሰባቸው ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ጠጕርህ ፡ በፍላት ፡ ተገሸልጦ ፡ ገላህ ፡ ቁስሉ ፡
እኛን ፡ ሁሉ ፡ ችለህ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ትሸከመናለህ ፡ ሲሉ ፡ መለሱለት ።
እሱም ፡ እችላለሁ ፡ በኔ ፡ በኩል ፡ አትሥጉ ፡ አላቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡
እሱ ፡ ከታች ፡ እነሱ ፡ ከላይ ፡ እየተቀጣጠሉ ፡ ሊደርሱበት ፡ ጥቂት ፡ ሲቀ
ራቸው ፡ ዘየ ፡ ጊዜ ፤ ሰውየው ፡ እንደ ፡ መጣራት ፡ "ፋጋውን" ፡ አቀብ
ሉኝ ፡ ብሎ ፡ ቃሉን ፡ አከሮ ፡ አሰማ ፤ መላጣው ፡ አንበሳም ፡ የፋጋን ፡ ድምፅ ፡
በመስማቱ ፡ አሁንም ፡ በፈላ ፡ ውሃ ፡ የሚያቃጥለው ፡ መስሎት ፡ በላዩ ፡
ላይ ፡ የነበሩትን ፡ አንበሶች ፡ በኃይል ፡ ገለባብጦ ፡ ጣላቸውና ፡ ፈረጠጠ ።



አሁንም ፡ በፈላ ፡ ውሃ ፡ የሚ
ያቃጥለው ፡ መስሎት ፡ በላ
ይ ፡ ላይ ፡ የነበሩትን ፡ አንበ
ሶች ፡ በኃይል ፡ ገለባብጦ ፡
ጣላቸውና ፡ ፈረጠጠ ።

እነሱም ፣ ምን ፡ መዓት ፣ ወረደብን ፣ በማለት ፣ ቍስለኛውን ፣ አን በሳ ፣ ተከትለው ፣ ሸሹ ፤ ሰውዮውም ፣ በእንደዚህ ፣ ያለ ፣ ዘዴ ፣ ከሞት ፣ ዳነ ፣ ይባላል ።

አራዊት ፣ ምንም ፣ ግዙፍ ፣ ወይም ፣ ኃይለኛ ፣ ወይም ፣ ደግሞ አስፈሪ ፣ ቢሆኑ ፣ የሰው ፣ ልጅ ፣ በተፈጥሮ ፣ ባገኘው ፣ ዕውቀቱ ፣ ማናቸ ውንም ፣ በጥበቡና ፣ በብልኀቱ ፣ ያሸንፋቸዋል ።

፨ አንዳንድ ፣ ጊዜም ፣ ጠላት ፣ ከመሣሪያ፥ ይልቅ ፣ በመንፈስ ፣ ኃይል ፣ የበለጠ ፣ ይጠቃል ።

—ደፋርና ፣ ጠሲ ፡ መውጫ ፣ አያጣም ፤

—ቦር ፣ ከፈታው ፣ ወሬ ፣ የፈታው ፣ ይበልጣል ፤

—ከትልቅ ፣ ጉልበት ፣ ትንሽ ፣ ብልኀት ፣ እየተባለ ፣ የሚተረተውም ፣ ይኸንን ፣ የመሰሰለ ፣ ነገር ፣ ቢጋጠመ ፣ ጊዜ ፡ መሆኑን ፣ መገንዘብ ፣ ይገባል ።

ጠበል ፣ የሄደች ፣ ፍየል ።

አንዲት ፣ ፍየል ፣ አያሌ ፣ ዘመን ፣ ብቻዋን ፣ ትኖር ፣ ነበር ። ከብቸ ኛነቷም ፣ ብዛት ፣ የተነሣ ፣ ብዙ ፣ ነገር ፣ በማሰብ ፣ በመጨነቅና ፣ በመሥ ጋት ፣ አካሏ ፣ እየከሰሰ ፤ ዐይኗዋ ፣ እየደከመ ፣ ስለ ፣ ሄደ ፣ ሕመም ፣ በጣም ፣ አድርጎ ፣ ያጠቃት ፣ ዠመር ። ከሚያሠቃያትም ፣ ደዌ ፣ ለመዳን ፣ ወደ ፣ ጠበል ፣ ለመሄድ ፣ ቍርጥ ፣ ሐሳብ ፣ አደረገች ። ጉዞዋንም ፣ ዠምራ ፣ ሳለች ፣ በምትሰነብትበት ፣ ጊዜ ፣ ሁሉ ፣ አንድ ፣ ጓደኛ ፣ ማግኘት ፣ አስፈላጊዋ ፣ መሆኑ ፣ ተሰማትና ፣ አንዲት ፣ ጤናዋ ፣ የተሰናከለ ፣ የምታውቃትን ፣ በግ ፣ ይዛ ፣ ለመሄድ ፣ ተመኘች ። እግዚአብሔር ፣ የለመኑትን ፣ የማያስ ቀር ፣ በመሆኑ ፤ ጥቂት ፣ እንደ ፣ ሄደች ፣ በጊቱን ፣ ከመንገድ ፣ ዳር ፣ ተኝታ ፣ አገኘቻት ። በጊቷም ፣ ትሑትና ፣ ግብረ ፣ ገብነት ፣ ያላት ፣ ፍጥረት ፣ ነበረ ችና ፣ ከተኛችበት ፣ ብድግ ፣ ብላ ፣ እጎቴ ፣ ፍቅሬ ፣ እመት ፣ ፍየሊት ፣ ሆይ ፣

ወዴት ፣ ትሄጃለሽ ፣ ስትል ፣ ጥያቄ ፣ አቀረበችላት ። ፍየሏም ፣ አንድ ፣ ወሬ ፣ ሰምቼ ፣ ልነግርሽ ፣ ነው ፣ የመጣሁት ፣ አለቻት ።

በግም ፣ በድንጋጤ ፣ ከቶ ፣ እኔን ፣ የሚያስፈልግ ፣ ምን ፡ ጉዳይ ፣ አግኝ ቶሽ ፣ ይሆን ፣ እጎቴ ፤ ፍየል ፣ በግን ፣ ትክ ፣ ብላ ፣ እያየች ፣ ይኸውልሽ ፣ አንድ ፣ አዲስ ፣ ጠበል ፣ ፈልቆ ፣ ፍጥረት ፣ ሁሉ ፣ እየሄደ ፣ ይፈወሳል ፣ አሉኝ ፤ እሁንም ፣ እኔና ፣ አንቺ ፣ ሄደን ፣ ከበሽታችን ፣ ድነን ፣ እንድን መጣ ፣ ልነግርሽ ፣ ነው ፣ የመጣሁት ፣ አለቻት ።

በግም ፣ በጉዳዩ ፣ ጥቂት ፣ አሰበችበትና ፣ እኔ ፣ ለራሴ ፣ አቅመ ፣ ቢስ ፣ ነኝ ፤ እንችም ፣ ሰውነትሽ ፣ አልቋል ፤ መንገድ ፣ የምትችይ ፣ አይመስለ ኝም ፤ ከዚህ ፣ በስተቀር ፣ ደግሞ ፣ እኛ ፣ እንስሳት ፣ ብዙ ፣ ጠላት ፣ ስላ ለብን ፣ የዱር ፣ አውሬ ፣ ያገኘን ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ አይለቀንም ፤ ስለዚህ ፣ እኔ ፣ በፍጹም ፣ እግሬን ፣ አላነሳውም ፤ ላንቺም ፣ ይህ ፣ ነገር ፣ ቢቀርብሽ ፣ መል ካም ፣ ነው ፣ ስትል ፣ ሐሳቧን ፣ አቀረበችላት ። ፍየልም ፣ ምንም ፣ አትፍሪ ፣ የሚመጣውን ፣ ነገር ፣ ሁሉ ፣ በኔ ፣ ላይ ፣ ጣይው ፣ ብላ ፣ በጊቷን ፣ ስላደ ፋፈረቻት ፣ ተስማሙና ፣ መንገዳቸውን ፣ ቀጠሉ ።

ጥቂት ፣ እንደ ፣ ሄዱም ፣ ከጠጣ ፣ ጋራ ፣ ተገናኙና ፣ እሷም ፣ ዛሬ ፣ ምን ፣ እግር ፣ ጣላችሁና ፣ ከዚህ ፣ መጣችሁ ፣ ስትል ፣ ጠየቀቻቸው ። ፍየ ልም ፣ በበግና ፣ በራሷ ፣ ስም ፣ ሆና ፣ እንዲህ ፣ ስትል ፣ መለሰች ። እግዚ አብሔር ፣ የምድር ፣ አራዊት ፣ ሁሉ ፣ በድለውኛልና ፣ ነገ ፣ ሰማይን ፣ ደፍቼ ፣ ላጠፋቸው ፣ ነውና ፣ አንድ ፣ ቦታ ፣ ተሰብስበው ፣ እንዲጠብቁኝ ፣ እየዘራችሁ ፣ ለሁሉም ፣ ንገሩ ፣ ስላለን ፣ በጫካው ፣ በደኑና ፣ በሸለቆው ፣ ይኸውና ፣ እየዘርን ፣ እንለፋለን ፤ ዳሩ ፣ ግን ፣ አንቺ ፣ ወዳጃችን ፣ ስለ ፣ ሆ ንሽ ፣ እንድትጠፊ ፣ አንፈልግምና ፡ ቶሎ ፣ ብለሽ ፣ አምልጪ ፣ አለቻት ። ጠጣም ፣ በዚህ ፣ ነገር ፡ ደንግጣ ፣ ከዛፍ ፣ ወደ ፣ ዛፍ ፣ እየዘለለች ፣ ስትሸሽ ፣ ፍየልና ፣ በግ ፣ መንገዳቸውን ፣ ቀጠሉ ። ጥቂት ፣ እንደ ፣ ተጓዙም ፣ ዝንጅ ሮንና ፣ ጉሬዛን ፣ ለየብቻቸው ፣ አገኟቸው ፤ እነሱም ፣ ጠጣን ፣ ባታለሉ በት ፣ አኳኋን ፣ አሞኝተዋቸው ፣ ሄዱ ። ደግሞም ፣ እንደዚሁ ፣ ለአንበሳ ፣ ለነብር ፣ ለሸኮ ፣ ሰማይ ፣ የሚወድቅ ፣ መሆኑን ፣ እያስረዱ ፣ ከተጓዙ ፣ በኋላ ፤ በመጨረሻው ፣ እጠበሉ ፣ ቦታ ፣ ደረሱ ። ከጠበሉም ፣ ሰንብተው ፣

ተጠምቀውና ፣ ጠጥተው ፣ ፈውስ ፣ ካገኙ ፣ በኋላ ፣ ወደ ፣ መኖሪያቸው ፣ ለመመለስ ፣ አሰቡና ፣ መንገዳቸውን ፣ ጀመሩ ።



ከጠበሉም ፣ በንብተው ፣ ተጠምቀውና ፣ ጠጥተው ፣ ፈውስ ፣ ካገኙ ፣ በኋላ ፣ ወደ መኖሪያቸው ፣ ለመመለስ ፣ አሰቡና ፣ መንገዳቸውን ፣ ጀመሩ ።

ሲጓዙ ፣ ውለው ፣ ጀምበር ፣ ስለ ፣ ጠለቀባቸው ፣ አንድ ፣ ትልቅ ፣ ቋጥኝ ፣ ላይ ፣ ወጥተው ፣ ለማደር ፣ ከፍየሊቱ ፣ ጠቃሚ ፣ ሐሳብ ፣ መነጨ ፣ በግ ፣ ግን ፣ እኔ ፣ በጣም ፣ ደክሞኛል ፣ እዚያ ፣ ላይ ፣ ለመውጣት ፣ ያቅተኛል ፣ ደግሞም ፣ አውሬ ፣ ይበላኛል ፣ ፈራሁ ፣ አለች ። ይሁን ፣ እንጂ ፣ ደፋሯ ፣ ፍየል ፣ አይዞሽ ፣ ኦትፍሪ ፣ ስትል ፣ አደፋፈረቻትና ፣ ከቋጥኙ ፣ ላይ ፣ ወጥተው ፣ ተኙ ። ነገር ፣ ግን ፣ እነዚያ ፣ የተታለሉት ፣ አውሬዎች ፣ ሰማይ ፣ እንዳይጫናቸው ፣ በመሥጋት ፣ ከቋጥኙ ፣ ሥር ፣ ተሸሽገው ፣ ኖሮ ፣ ጠጣ ፣ እንዲህ ፣ ስትል ፣ ወሬ ፣ ገመረች ። ትላንት ፣ እከ ፣ ፍየል ፣ እንኳ ፣ ባቅሟ ፣ ሰማይ ፣ ይወድቃል ፣ ራስሽን ፣ አውጭ ፣ ብላ ፣ አታለለችኝ ። በዚህ ፣ ጊዜ ፣ ሁሉም ፣ በየተራ ፣ እኔንም ፣ እኔንም ፣ እያሉ ፣ ሲወያዩ ፣ በጊት ፣ ከመዳከሚ ፣ ብዛት ፣ የተነሣ ፣ ወዲያው ፣ ከመተኛታቸው ፣ ከባድ ፣ እንቅልፍ ፣ ይዟት ፣ ነበርና ፣ ስትንጠራራ ፣ ከቋጥኙ ፣ ላይ ፣ ተንሸራታ ፣ ወደቀች ። ፍየሊት ፣ ሁኔታውን ፣ ሁሉ ፣ ነቅታ ፣ ታዳምጥ ፣ ነበርና ፣ ድምፅዋን ፣ ከፍ ፣ አድርጋ ፣ ይኸውላችሁ ፣ አንዱ ፣ የሰማይ ፣ ስባሪ ፣ ወደቀ ፣ አለች ። አውሬዎቹም ፣ በሥጋት ፣ ላይ ፣ ነበሩና ፣ እባብ ፣ ያየ ፣ ልጥ ፣ ቢያይ ፣ በረየ ፣ እንደሚባለው ፣ ሁሉ ፣ እውነት ፣ ስለ ፣ መሰላቸው ፣ ሁሉም ፣ በየፊናቸው ፣ እየሮጡ ፣ ጠፉ ።

በጊት ፣ ከቋጥኙ ፣ ላይ ፣ በመውደቅ ፣ ብዙ ፣ አልተጐዳችም ፣ ነበርና ፣ ሌሊቱን ፣ ያለሥጋት ፣ አሳልፈው ፣ ሲንጋጋላቸው ፣ ጧት ፣ መንገዳቸውን ፣ ቀጥለው ፣ ስለ ፣ ፈጸሙት ፣ ዘዴ ፣ በአደናቆት ፣ እየተጫወቱ ፣ የማታ ፣ ማታ ፣ በደኅና ፣ እየሰፈራቸው ፣ ገቡ ፣ ይባላል ።

፠ —ከእንስሳትም ፣ ማኽል ፣ በብልኅነት ፣ አንዱ ፣ ከንዱ ፣ ይበልጣል ።

ፍየል ፣ ከሚያሠጓት ፣ ባለጋራዎቿ ፣ አደጋ ፣ በጥበብና ፣ በዘዴ ፣ አምልጣ ፣ ከተመኘችው ፣ ጠበል ፣ ደርሳ ፣ በሽታዋን ፣ ድና ፣ እቤቷ ፣ ለመመለስ ፣ በቃች ።

—ከትልቅ ፣ ጕልበት ፣ ትንሽ ፣ ብልኅት ፣ የሚበለውም ፣ ስለዚህ ፣ ነው ።

ስለ ፡ አንድ ፡ ተንኰለኛ ፡ ሰው ፡ና ፡ ስለ ፡ አንድ ፡ ገበሬ ፡ ንጹኅነት ።

በንድ ፣ አገር ፣ አንደኛው ፣ በርሻ ፣ ሥራ ፣ ሁለተኛው ፣ በተንኰል ፣ ሥራ ፣ የሚተዳደሩ ፣ ሁለት ፣ ሰዎች ፣ ነበሩ ። ከዕለታት ፣ አንድ ፣ ቀን ፣ ጊዜ ፣ አጋጥሟቸው ፣ እነዚህ ፣ ሁለት ፣ ሰዎች ፣ ጓደኛ ፣ በመሆን ፣ እየተጨዋወቱ ፣ ሲያዘግሙ ፣ ይህ ፣ የተንኰል ፣ በኵር ፣ ልጅ ፣ የሆነ ፣ ሰው ፣ ለዚህ ፣ መልካም ፣ ሠራተኛ ፣ ያልሆነ ፣ ምክር ፣ ሰጥቶ ፣ ንብረቱን ፣ ለማፍረስና ፣ ለማንከራተት እንደዚህ ፣ የሚል ፣ ሐሳብ ፣ አቀረበለት ።

ሰማህ ፣ ወይ ፣ ወዳጄ ፣ አጥብቆ ፣ መሥራት ፣ ጥቅም ፣ መሆኑን ፣ ስለ ፣ ተረዳሁ ፣ ወዲያና ፣ ወዲህ ፣ እየተዘዋወርሁ ፣ ካንተ ፣ ከትጉሁ ፣ ገበሬ ፣ ኑሮ ፣ የተሻለ ፣ እኖራለሁ ፤ ስለዚህ ፣ አንተም ፣ እንደዚህ ፣ ወይነት ፣ ኑሮ ፣ አንድትኖር ፣ ሚስትህን ፣ ፈተህ ፣ በሮችህን ፣ ሸጠህ ፣ ከእኔ ፣ ጋራ ፣ ሁን ፣ አለው ። ይህም ፣ ገበሬ ፣ በመዘር ፣ ብቻ ፣ ጥቅም ፣ ይገኝ ፣ መስሎት ፣ መልካም ፣ ሚስቱን ፣ ፈቶ ፣ የርሻ ፣ በሮቹን ፣ ሸጦ ፣ የተንኰለኛው ፣ ሰው ፣ ጓደኛ ፣ ሆኖ ፣ በመዘር ፣ ገንዘብ ፣ ሥር ፣ የለውም ፣ እንደሚባለው ፣ ሁሉ ፣ የሰበሰበውን ፣ ገንዘብ ፣ በሙሉ ፣ ለምግብና ፣ ለመጠጥ ፣ ወጪ ፣ አድርጎ ፣ ጨረሰ ። ከዚህ ፣ በኋላ ፣ የገንዘቡን ፣ ማለቅ ፣ ተንኰለኛው ፣ መከር ፣ ስለ ፣ ተረዳው ፣ ከወህኒ ፣ ቤት ፣ እንዳመለጠ ፣ አስረኛ ፣ ሸሽቶ ፣ ተለየው ።

በዚህ ፣ ጊዜ ፣ ይህ ፣ መልካም ፣ ሠራተኛ ፣ የነበረው ፣ ሰው ፣ ዙሪ
ያው ፣ ገደል ፣ ስለ ፣ ሆነበት ፣ በበሮቹ ፣ አርሽ ፣ ያልሆነልኝን ፣ በሮቼን ፣
ሸፈጡ ፣ መልካም ፣ ሚስቱን ፣ ፈትቹ ፣ የተሻለ ፣ አገኛለሁ ፣ ስል ፣ እንደ
ዚህ ፣ ያለ ፣ ጉስቁሉና ፣ ላይ ፣ ወደቅሁ ፣ በግለት ፣ ራሱን ፣ ዘራሱ ፣ እየ
ወቀሠ ፣ ተንኰለኛ ፣ መካሩን ፣ ወረተኛ ፣ ጓደኛ ፣ እያማረረ ፣ ባገር ፣ የመ
ኖር ፣ ተስፋውን ፣ ቁርጦ ፣ ወደ ፣ አንዱ ፣ አገር ፣ ለመሰደድ ፣ አሰበ ። ጉዞ
ውንም ፣ ቀጥሎ ፣ ከነበረበት ፣ አገር ፣ ብዙ ፣ ርቆ ፣ ከሄደ ፣ በኋላ ፣ ላንድ ፣
ሀብታም ፣ ገበሬ ፣ ተቀጥሮ ፣ በዚያ ፣ ሙጥፎ ፣ መከር ፣ የተወውን ፣ የእ
ርሻ ፣ ተግባር ፣ ቀጥሎ ፣ ያገለግል ፣ ዝመር ። አንድ ፣ ዓመት ፣ ከሠራ ፣
በኋላ ፣ ከጌታው ፣ ምንዳውን ፣ ተቀብሎ ፣ ፈቃድ ፣ ጠይቆ ፣ ጥሎት ፣ የመ
ጣውን ፣ አገር ፣ ለማየት ፣ ሄደ ። ብዙ ፣ መንገድም ፣ ተጉዞ ፣ ታላቅ ፣
በረሓ ፣ ወደ ፣ ሆነው ፣ ስፍራ ፣ ሲደርስ ፣ ከወደ ፣ ኋላው ፣ አንተ ፣ ሰው ፣
አትቸኩል ፣ አትቸኩል ፣ የሚል ፣ ድምፅ ፣ ስለ ፣ ሰማ ፣ በዚህ ፣ አልሆነ ፣
ስፍራ ፣ ላይ ፣ የምን ፣ ድምፅ ፣ ነው ፣ የተሰማኝ ፣ በማለት ፣ ግራና ፣ ቀኝ ፣
ቢመለከት ፣ ምንም ፣ ሳያገኝ ፣ በመቅረቱ ፣ መንገዱን ፣ ቀጠለ ። ሁለተኛ ፣
ጊዜ ፣ እየደጋገመ ፣ አንተ ፣ ሰው ፣ አትቸኩል ፣ አትቸኩል ፣ እያለ ፣ አስ
ቸገረው ። እሱም ፣ የሰው ፣ ወሬ ፣ ሰምቼ ፣ በችኰላ ፣ ሚስቴን ፣ ፈትቼ ፣
በሮቼን ፣ ሸፈጡ ፣ ጉስቁሉና ፣ ላይ ፣ ወደቅሁ ። እዚህ ፣ እፈቴ ፣ ባለው ፣
በረሓ ፣ ላይ ፣ ከሚደርስብኝ ፣ አደጋ ፣ ሊከለክልልኝ ፣ ከእግዚአብሔር ፣
የተላከ ፣ መልአክ ፣ የሚያሰማኝ ፣ ድምፅ ፣ ይሆናል ፣ በማለት ፣ ራሱን ፣
አጽናንቶ ፣ ወደ ፣ ፊቱም ፣ ሳይሄድ ፣ ወደ ፣ ኋላውም ፣ ሳይመለስ ፣ ከመንገዱ ፣
ዳር ፣ እጥላ ፣ ሥር ፣ ወረፈ ። እምብዛም ፣ ሳይቈይ ፣ ወዲያው ፣ ከባድ ፣
ዝናም ፣ ስለ ፣ መጣ ፣ ለመጠለል ፣ በአሸጋጋሪ ፣ ወደ ፣ አየው ፣ ዋሻ ፣ አም
ርቶ ፣ ዝናሙ ፣ መጣል ፣ ሲዝምር ፣ እዚያች ፣ እዋሻ ፣ ውስጥ ፣ ሮጠ ፣
ገባ ። ጥግ ፣ ከያዘ ፣ በኋላ ፣ ወደ ፣ ውስጥ ፣ ሲመለከት ፣ ትልቅ ፣ ዘንዶ ፣
ተጠቅልሎ ፣ ተኝቶ ፣ ስላየ ፣ ዘድንጋጤ ፣ ባሕር ፣ ተውጦ ፣ በመንቀጥ
ቀጥ ፣ ወይ ፣ አትቸኩል ፣ አትቸኩል ፣ ለዘንዶ ፣ ዳረገኝ ፣ እያለ ፣ ከዋ
ሻው ፣ ለመውጣት ፣ ሲያስብ ፣ በንድ ፣ በኩል ፣ አትቸኩል ፣ ያለኝ ፣
ከዚሁ ፣ ዘንዶ ፣ ሊያድነኝ ፣ ይሆናል ፣ ቢያየኝ ፣ ኖሮ ፣ እስካሁን ፣ ዝም ፣
አይለኝም ፣ ነበር ፣ ነገር ፣ ግን ፣ ባለግየቱ ፣ ዝም ፣ ብሏል ። እሁን ፣ ስወጣ ፣
ያየኝና ፣ ተወርውሮ ፣ ይዘ ፣ ይውጠኛል ፣ በማለት ፣ እነበረበት ፣ ጥግ ፣

ተለጥፎ ፣ እንደ ፣ ቆመ ፣ በሸጋጋሪ ፣ ከዘንዶው ፣ ራስጌ ፣ አንድ ፣ መጠ
ነኛ ፣ ገንቦ ፣ አየ ። ወዲ ፣ ግሩም ፣ አትቸኩል ፣ የዘንዶ ፣ ባልደረባ ፣
አደረገኝ ፣ ደግሞስ ፣ ይህ ፣ ገንቦ ፣ ምን ፣ ይሆን ፣ እያለ ፣ የመዳን ፣ ተስፋውን ፣
ቈርጦ ፣ ወጥመድ ፣ ውስጥ ፣ እንደ ፣ ገባ ፣ ነብር ፣ ሞቱን ፣ ሲጠባበቅ ፣ ይህ ፣ የ
በጋ ፣ ዝናም ፣ ወዲያው ፣ አባራና ፣ ፀሓይዋ ፣ ታ ፣ ብላ ፣ ስለ ፣ ወጣች ፣ ዘን
ዶው ፣ በጠገበ ፣ ሰው ፣ መኖሩን ፣ ሳይመለከት ፣ ለመሞቅ ፣ ተወርውሮ ፣
ከዋሻው ፣ ወጣ ። በዚህ ፣ ጊዜ ፣ ሰውዬው ፣ ከዘንዶው ፣ አፍ ፣ ከመለጥኩ ፣
ወደ ፣ ቤቱ ፣ ልፈርጥ ፣ ሳይል ፣ በሸጋጋሪ ፣ ያያትን ፣ ገንቦ ፣ ተጠግቶ ፣
ተመለከተ ። እሷም ፣ ሙሉዋን ፣ ሻሽ ፣ የመሰለ ፣ ብር ፣ ይዛ ፣ ስላገኝ ፣
ተጫኖት ፣ የነበረው ፣ የድንጋጤ ፣ ሰመመን ፣ በደስታና ፣ በብርታት ፣ ተለ
ውጦ ፣ የለበሰውን ፣ ነጠላ ፣ ዘርግቶ ፣ ክገንቦው ፣ ውስጥ ፣ ብሩን ፣ ዘርግፎ ፣ ከተ
ሸከመ ፣ በኋላ ፣ አትቸኩል ፣ ይህን ፣ ሰጠኝ ፣ እያለ ፣ እየፈነጠዘ ፣ ወደ ፣
አገሩ ፣ መንገዱን ፣ ቀጠለ ።

እዚህ ፣ ትገባለች ፣ የማትባል ፣ ፈፋ ፣ በዝናሙ ፣ ምክንያት ፣ ሞ
ልታ ፣ ስላገኛት ፣ ብሩን ፣ ከቅሸው ፣ አውርዶ ፣ ልብሱን ፣ አውልቆ ፣
ምርኩዙን ፣ ይዘ ፣ ለመሰለል ፣ ሲጠጋ ፣ የውሃው ፣ ኃይል ፣ የያዘውን ፣
ምርኩዝ ፣ ነጥቆ ፣ ወሰደበት ። በዚህ ፣ ጊዜ ፣ ደፍሬ ፣ ገብቼ ፣ ቢሆን ፣ እኔ
ንም ፣ እንደ ፣ በትሬ ፣ ያመስደኝ ፣ ነበር ። ብሎ ፣ ወደ ፣ ኋላው ፣ ተመልሶ ፣
ልብሱን ፣ ለብሶ ፣ እወንዙ ፣ ዳር ፣ ቀሩዲ ፣ ብሎ ፣ የውሃውን ፣ መጉደል ፣
ይጠባበቅ ፣ ዝመር ።

ከዚህ ፣ ቀጥሎ ፣ ያ ፣ የተንኰል ፣ ምክር ፣ መከሮ ፣ ትዳሩን ፣ አስፈ
ርሶ ፣ ሰውነቱን ፣ አጕስቍሎ ፣ እንዲሰደድ ፣ ያደረገው ፣ ተንኰለኛ ፣ ጓደ
ኛው ፣ መልካም ፣ መልካም ፣ ልብሱን ፣ ለብሶ ፣ ዝናሩን ፣ ታጥቆ ፣ ጠመ
ንጃውን ፣ አንግቶ ፣ ብዙ ፣ ብር ፣ በከረጢት ፣ ይዘ ፣ ከማዶ ፣ ሲመጣ ፣ ያች ፣
ፈፋ ፣ ከመጠን ፣ በላይ ፣ በሆነ ፣ እኳኋን ፣ ሞልታ ፣ ስላገኛት ፣ ዝና
ሩንና ፣ ጠመንጃውን ፣ አስቀምጦ ፣ ውሃውን ፣ ለመሰለል ፣ እንደ ፣ ገባ ፣ ያል
ታሰበ ፣ ድንገተኛ ፣ ደራሽ ፣ ውሃ ፣ መጥቶ ፣ ወሰደው ።



በደረሰው ፡ ድንገተኛ ፡ አደጋ ፡ እያዘን ፡ እኔም ፡ ገብቼ ፡ ቢሆን ፡ እንደዚህ ፡ ሰው ፡ ሄጂ ፡ ነበር ።

ይህ ፡ ወዲህ ፡ ማዶ ፡ ሆኖ ፡ የውሃውን ፡ መጉደል ፡ ይጠባበቅ ፡ የነበረው ፡ በሰውዬው ፡ ላይ ፡ በደረሰው ፡ ድንገተኛ ፡ አደጋ ፡ እያዘነ ፡ እኔም ፡ ገብቼ ፡ ቢሆን ፡ እንደዚህ ፡ ሰው ፡ ሄጂ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ እት ፫ኩል ፡ በጣም ፡ ረዳኝ ፡ እያለ ፡ ሲደሰት ፡ ጐርፉም ፡ ወዲያው ፡ ስለ ፡ ጐደለ ፡ በነጠላው ፡ የያዘውን ፡ ብር ፡ ተሸክሞ ፡ ተሸገረ ። የዚያንም ፡ ሰው ፡ ከረጢት ፡ ፈቶ ፡ ቢመለከተው ፡ ወርቅ ፡ ሆኖ ፡ አገኘው ። ይህንንም ፡ ከያ ዘው ፡ ብር ፡ ጋር ፡ ቀላቅሎ ፡ ዝናሩን ፡ ታጥቆ ፡ ጠመንጃውን ፡ አንግቶ ፡ ትልቅ ፡ መኳንንት ፡ ሆኖ ፡ አት፫ኩል ፡ ይህን ፡ ሰጠኝ ፡ እያለ ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ እየተደሰተ ፡ ጉዘውን ፡ ቀጥሎ ፡ አገሩ ፡ ገባ ።

ከዚያም ፡ ባገኘው ፡ ገንዘብ ፡ ከብትና ፡ ርስት ፡ ገዝቶ ፡ ንብረትና ፡ ቤቱን ፡ አስፋፍቶና ፡ አደርጅቶ ፡ ዘመኑን ፡ በተድላና ፡ በደስታ ፡ አሳለፈ ፡ ይባላል ። (ከጋዜጣ ፡ የተቀዳ) ፡

※ ስለዚህ ፡ የግፍ ፡ ሠሪዎችና ፡ ተንኩል ፡ መካሮች ፡ ውድቀትና ፡ አጠፋፍ ፡ ቢዘገይም ፡ የማ ይቀር ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የሚገጥመውን ፡ ፈተና ፡ ሁሉ ፡ በትዕግሥት ፡ ማሳለፍ ፡ ይገባል ።

በወፍ ፡ ፍቅር ፡ የሞተ ፡ እረኛ ።

የወላጆቹን ፡ ከብቶች ፡ የሚጠብቅ ፡ አንድ ፡ ልበ ፡ ርኅሩኅ ፡ ልጅ ፡ ነበር ። ይህ ፡ እረኛ ፡ ግጦሽ ፡ የሚያበላበት ፡ ቦታ ፡ ከቤቱ ፡ ሩቅ ፡ በመ ሆኑ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ጧት ፡ ጧት ፡ ምሳውን ፡ ባገልግል ፡ ይዘ ፡ መሄድ ፡ ግዴታው ፡ ነበር ። ከብቶቹን ፡ ከሚጠብቅበት ፡ መስክ ፡ አጠገብ ፡ ዘሚገ ኘው ፡ ባንድ ፡ ትልቅ ፡ ሾላ ፡ ላይም ፡ ብዙ ፡ አሰዋፍ ፡ ጐጇቸውን ፡ ሠር ተውበት ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ፡ ይባላል ። ከወፎቹ ፡ መከከል ፡ የላቡዋ ፡ ቀለም ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ መልክ ፡ ያለው ፡ አንዲት ፡ የምታምር ፡ ወፍ ፡ ነበረች ። ልጁም ፡ ለዚያች ፡ ወፍ ፡ ሶረኔ ፡ የሚባል ፡ ስም ፡ ካወጣላት ፡ በኋላ ፡

"የደጋ ፡ ሶረኔ ፡ የቄላ ፡ ሶረኔ ፡ ነይ ፡ እሽክምክም ፡ ከኔ" ፡

እያለ ፡ በመጥራት ፡ ከሚመገበው ፡ እንጀራ ፡ እንድትበላ ፡ እስለመዳት ። ወፈ፫ም ፡ ልጆቿና ፡ ዘመዶቿ ፡ አብረው ፡ መጥተው ፡ ምሳውን ፡ ከተ ካፈሉት ፡ በኋላ ፡ ከልጁ ፡ ጋር ፡ ስትጫወት ፡ ውላ ፡ ሲመሽ ፡ እሱም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሲሄድ ፡ እሷም ፡ ወደ ፡ ጐጇዋ ፡ ትገባለች ። በዚህ ፡ አኳ ኋን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ካሰለፉ ፡ በኋላ ፡ እረኛው ፡ ልጅ ፡ ምግቡን ፡ ለአዕ ዋፍ ፡ ከማካፈሉ ፡ ምክንያት ፡ የተነሣ ፡ እየከሳ ፡ አካሉ ፡ እየቀጨጨና ፡ እየተጐዳ ፡ በመታየቱ ፡ ወላጆቹም ፡ ሰውነቱ ፡ እየኰሰሰ ፡ በመሄዱ ፡ እጅ ግ ፡ እዝነውና ፡ ሠግተው ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ታናሽ ፡ ወንድሙን ፡ ወንድ ምህ ፡ ከሚውልበት ፡ ሂድና ፡ ፌት ፡ ለፌት ፡ ሳትታይ ፡ የሚያደርገውን ፡ አይተህ ፡ ተመለስ ፡ ብለው ፡ ሰደዱት ።

እሱም ፡ በየጫካው ፡ እየተሹለከለከ ፡ በየገደሉ ፡ እየተንሸራተተ ፡ ወንድሙ ፡ የሚሠራውን ፡ ሁሉ ፡ ሲመለከት ፡ ውሎ ፡ የምሳ ፡ ሰዓት ፡ ሲደ ርስ ፡ ያ ፡ ወንድሙ ፡ አገልግሉን ፡ ከፍቶ ፡ ከዚያ ፡ ሾላ ፡ ሥር ፡ ከጥላ ፡ ተቀምጠ ፡ —

"የደጋ ፡ ሶረኔ ፡ የቄላ ፡ ሶረኔ ፡ ነይ ፡ እሽክምክም ፡ ከኔ" ፡

እያለ ፡ ሲጣራ ፡ ሰማ ። ወፍም ፡ ድምፀን ፡ ታውቅ ፡ ነበርና ፡ ከንደኞቿ ፡ ጋራ ፡ አንዣባ ፡ መጥታ ፡ ከአገልግሉ ፡ ከንፈር ፡ ላይ ፡ ዐርፋ ፡ ልጁ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ እንኳ ፡ ሰይጐርሥ ፡ እነሱን ፡ እነሱን ፡ ሲመለከት ፡ በልተ ውበት ፡ ሲሄዱ ፡ ሶረኔም ፡ እንደ ፡ ልማዷ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ስትጫወት ፡ ያ ፡ ታናሽ ፡ ወንድሙ ፡ ተደብቆ ፡ ይመለከት ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ የ[illegible] ፡ ማታ ፡

የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ ከጠና ፡ በኋላ ፡ ሲመሽ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ተመልሶ ፡ ያየውን ፡ በሙሉ ፡ ለናትና ፡ ላባቱ ፡ ነገራቸው ።

ወላጆቹ ፡ በማግስቱ ፡ ከብት ፡ ጠባቂ ፡ ልጃቸውን ፡ ከሶ ፡ ትጠጣ ለሀና ፡ ዛሬ ፡ ከቤት ፡ ዋል ፡ ብለው ፡ በግድ ፡ ሲያለቅስ ፡ አስቀሩት ። በእርሱም ፡ ምትክ ፡ አባቱና ፡ ምሥጢሩን ፡ የተመለከተው ፡ ታናሽ ፡ ወንድሙ ፡ ከብቶቹን ፡ ያዘው ፡ ተሰማሩ ። የምሳ ፡ ጊዜም ፡ ሲደርስ ፡ አባት የው ፡ እንደዚያ ፡ እንደ ፡ ልጁ ፡ ያችን ፡ ወፍ ፡ ለመጥራትና ፡ ስትመጣም ፡ ለመግደል ፡ አስቦ ፤ "ሶረኔ ፡ ሶረኔ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ነይ" ፡ እያለ ፡ ቢጣራ ፡ የማትመጣ ፡ ሆነች ። ወዲያው ፡ ትንሹ ፡ ልጁ ፡ አባባ ፡ እሱ ፡ የሚጠራት ፡ እንዲህ ፡ አይደለም ፡ በለስላሳ ፡ ድምፅና ፡ ባማረ ፡ ዜማ ፡ "የደጋ ፡ ሶረኔ ፡ የቄላ ፡ ሶረኔ ፡ ነይ ፡ እሸክምክም ፡ ከኔ" ፡ እያለ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ድምፅ ፡ ቢያሰማ ፡ ያች ፡ ወፍ ፡ ወዲያው ፡ እንደ ፡ ለመደች ፡ መጥታ ፡ ከጓደኞቿ ፡ ጋራ ፡ ከአገልግሉ ፡ ከንፈር ፡ ላይ ፡ ሲያርፉ ፡ ልጁም ፡ ይህች ፡ ላባዋ ፡ ኸቦጉርጉር ፡ ሆኖ ፡ የምታምረው ፡ ወፍ ፡ ነች ፡ ሲል ፡ ከሳየው ፡ በኋላ ፡ አባትዮው ፡ በያዘው ፡ ጩቤ ፡ አንገቷን ፡ ቀልቶ ፡ ገደላትና ፡ ጩቤውንም ፡ እዚያው ፡ ወረወረው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በማግስቱ ፡ ልጁን ፡ ወደ ፡ አረኝነቱ ፡ ላከው ፤ ልጁም ፡ በምሳ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ተለመደው ፡ "የደጋ ፡ ሶረኔ ፡ የቄላ ፡ ሶረኔ ፡ ነይ ፡ እሸክምክም ፡ ከኔ" ፡ ብሎ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ቢጣራ ፡ የማትመጣ ፡ ሆነች ። በዛ ፉም ፡ አካባቢ ፡ እየዘረና ፡ እየጠራ ፡ ሲፈልግ ፡ ሌላ ፡ ወፍ ፡ "የሶረኔ ፡ አንገት ፡ ወድቋል ፡ ከዳገት ፤ የሶረኔ ፡ ላባ ፡ ወድቋል ፡ ከገለባ" ፡ እያለች ፡ ስትጮኽ ፡ ሰማት ። ልጁም ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ ምን ፡ ማለቷ ፡ ይሆን ፡ እያለ ፡ ሲንቄራጠጥ ፡ ወዲያው ፡ የሶረኔን ፡ ሬሳና ፡ የተቄረጠ ችበትንም ፡ ጩቤ ፡ ጭምር ፡ ከጥሻ ፡ ውስጥ ፡ አገኘው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ተጸጽቶ ፡ ምርር ፡ ብሎ ፡ አለቀሰ ፤ ወዲያው ፡ ያን ፡ የሞተችበትን ፡ ጩቤ ፡ አንሥቶ ፡ እንደ ፡ ሶረኔ ፡ እኔም ፡ እርድ ፡ እርድ ፡ አለና ፡ ራሱን በራሱ ፡ አረዶ ፡ ሞተ ።

ሲመሽም ፡ ቤት ፡ ሰበቹ ፡ መቄየቱን ፡ አይተው ፤ ይህ ፡ ልጅ ፡ ምን ፡ አገኘውና ፡ ቀረ ፡ በማለት ፡ ተጨንቀው ፡ አባቱ ፡ ከብት ፡ ወደሚያበላበት ፡ መስክ ፡ ቢሄድ ፡ ልጁን ፡ ሞቶ ፡ ስላገኘው ፡ እኔም ፡ እንደ ፡ ልጄ ፡ እርድ ፡ እርድ ፡ አለና ፡ ጩቤውን ፡ በባሕር ፡ ሆዱ ፡ ስለ ፡ ከተተው ፡ ወዲያው ፡ ሞተ ። እናቱም ፡ ባሏና ፡ ልጅዋ ፡ ስለ ፡ ቀሩባት ፡ ወርቁ ፡ የተበለውን ፡

ትንሹን ፡ ልጅዋን ፡ ቤት ፡ አስጠብቃ ፡ ለመፈለግ ፡ ሄደች ። አንድ ፡ ጊዜ ፡ የልጅዋን ፡ ስም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ የባሏን ፡ ስም ፡ እየጠራች ፡ ስትፈልግና ፡ ስትቅበዘበዝ ፡ ልጅዋ ፡ የወፏን ፡ ከንፍ ፡ በግራ ፡ እጁ ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ ባሏ ፡ ደግሞ ፡ የልጁን ፡ እንገት ፡ እንደ ፡ ታቀፈ ፡ ሁለቱም ፡ ወርፈው ፡ የሞቱበት ፡ ጩቤ ፡ በባሏ ፡ ሆድ ፡ ላይ ፡ ተሰክቶ ፡ አገኘችው ።

እሷም ፡ አለመጠን ፡ ሐዘን ፡ ልቧን ፡ ስለ ፡ ነካው ፡ ወዲያው ፡ ጩቤውን ፡ ከባሏ ፡ ሆድ ፡ ነቀለችና ፡ እኔም ፡ እንደ ፡ ልጄ ፡ እንደ ፡ ባሌ ፡ ብላ ፡ በጡት ፡ ሥጋ ፡ ስለ ፡ ለቀቀችበት ፡ ሞተች ።



ጩቤውን ፡ ከባሏ ፡ ሆድ ፡ ነቀለችና ፡ እኔም ፡ እንደ ፡ ልጄ ፡ እንደ ፡ ባሌ ፡ ብላ ፡ በጡት ፡ ሥጋ ፡ ስለ ፡ ለቀቀችበት ፡ ሞተች ።

ከቤት ፡ የቀረው ፡ ያ ፡ ትንሽ ፡ ልጅ ፡ ደግሞ ፡ ቢጠብቅ ፡ ቢጠብቅ ፡ ቢወጣ ፡ ቢገባ ፡ ፍለጋቸው ፡ ስለ ፡ ጠፋበት ፡ በደረቅ ፡ ውድቅት ፡ "እማምዬ ፡ አባብዬ" ፡ እያለ ፡ እየወደቀና ፡ እየተነሣ ፡ ቢሄድ ፡ ቤት ፡ ሰበቹ ፡ በሙሉ ፡ አልቀው ፡ ስላገኛቸው ፡ እርሙን ፡ አውጥቶ ፡ ራሱን ፡ በራሱ ፡ አጽናንቶ ፡ ከዚያው ፡ ከዳር ፡ ከብቶቹን ፡ አሀዮቹንና ፡ በጎቹን ፡ ይዘ ፡ እያለቀሰ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሲሄድ ፡ አያ ፡ ኸቦ ፡ በመንገድ ፡ አገኘው ።

ወዲያው ፡ የዛቻ ፡ ድምፅ ፡ እያሰማ ፡ ቢቀርበው ፡ አያ ፡ ኸቦ ፡ አባ ከህ ፡ አትብላኝ ፡ እያለ ፡ በማሳዘን ፡ ለመነው ፤ አያ ፡ ኸቦም ፡ የሞቱትን ፡ በልቶ ፡ ከጨረሰ ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ በማግስቱ ፡ ድምፅ ፡ አሰምቶ ፡ ቢመጣበት ፡ ልጁም ፡ እኔን ፡ ትተህ ፡ አንዷን ፡ አህያ ፡ ውሰድ ፡ ስላለው ፡ ኸቦ ፡ አህያዋን ፡ በላና ፡ ወደ ፡ ጕሬው ፡ ሄደ ።

በሌላም ፡ ቀን ፡ አያ ፡ ኸቦ ፡ ማታ ፡ ማታ ፡ እየመጣ ፡ በማስፈራራት ፡ አንዳንዳቸውን ፡ እየወሰደ ፡ ከብቶቹን ፡ ስለ ፡ ጨረሰ ፡ ልጁ ፡ ነገሩን ፡ አስቦ ፡ ይህ ፡ ኸቦ ፡ የሚበላው ፡ ሲያጣ ፡ እኔን ፡ ይበላኝ ፡ የለምን ፡ ብሎ ፡ እኅቱ ፡ ወደ ፡ ዳር ፡ አገር ፡ ትኖር ፡ ነበርና ፡ ወደሷ ፡ ለመሄድ ፡

ጉዞ ፣ ዝመረ ። አገሩም ፣ በጣም ፣ ሩቅ ፣ ስለ ፣ ነበረ ፣ ብዙ ፣ ቀን ፣ ሲጓዝ ፣ ቄይቶ ፣ ወደ ፣ ተበለው ፣ አገር ፣ ሲቃረብ ፣ የእኅቱን ፣ ባል ፣ ከመንገድ ፣ አገኘው ።

ይሁን ፣ እንጂ ፣ ሁለቱም ፣ አይተዋወቁም ፣ ነበር ፤ በልዮውም ፣ የሚ ሄደው ፣ በሪያ ፣ ለመግዛት ፣ ስለ ፣ ነበር ፤ አንተ ፣ ልጅ ፣ የማነህ ፣ ከየት ስ ፣ ትመጣለህ ፣ ብሎ ፣ ጠየቀው ። ልጁም ፣ እናት ፣ አባቴ ፣ ሞተው ብኝ ፣ መግቢያ ፣ ስላጣሁ ፣ ወደ ፣ ዳር ፣ አገር ፦የምትኖር ፣ ታላቅ ፣ እኅት ፣ ስላ ለችኝ ፤ እሷን ፣ ፍለጋ ፣ መሄዴ ፣ ነው ፣አለው ። ሰውዬውም ፣ ስምህ ፣ ማን ፣ ይበላል ፣ እኅትህስ ፣ ማን ፣ ትበላለች ፣ ብሎ ፣ ስለ ፣ ጠየቀው ፣ የራ ሱንና ፣ የእኅቱን ፣ ስም ፣ ከነገረው ፣ በኋላ ፣ ሌላ ፣ ምንም ፣ ሳይጠይቀው ፣ አፍኖ ፣ ፊቱን ፣ በቀለም ፣ አጥቁሮ ፣ ወደ ፣ ቤቱ ፣ ይዞት ፣ ሄደ ።

በመንገድ ፣ ላይም ፣ ሲጓዙ ፣ ማንም ፣ ሰው ፣ ከየት ፣ እንደ ፣ መጣህ ፣ ቢጠይቅህ ፣ የተሰጠህን ፣ ከመሥራት ፣ በቀር ፣ ምንም ፣ አንዳች ፣ ነገር ፣ እንዳትናገር ፣ ብሎ ፣ አስጠነቀቀውና ፣ እቤቱ ፣ እንደ ፣ ደረሰ ፣ ለሚስቱ ፣ በሪያ ፣ አመጣሁልሽ ፣ ብሎ ፣ ለእኅቱ ፣ አስረከበው ።

እኅቱም ፣ ያልሆነ ፣ ምክንያት ፣ በመፈለግ ፤ ውሃ ፣ በወንፊት ፣ ቅዳ ፣ ከሙቀጫ ፣ ጋራ ፣ ታገል ፣ በጭድ ፣ እሳት ፣ አምጣ ፣ እያለች ፤ ውሃው ፣ ሲፈስ ፣ ትገርፈዋለች ፣ ሙቀጫው ፣ ሲጥለው ፣ ትሥቅበታለች ፤ እሳቱን ፣ በጭድ ፣ በሚያመጣበት ፣ ጊዜ ፣ እያቃጠለ ፣ ሲፈጀው ፣ ትሰድበዋለች ፤ እንደዚህ ፣ እያወጫበረች ፣ ወንድሟ ፣ መሆኑን ፣ ባለማወቅ ፣ ቁም ፣ ስቅ ሉን ፣ አሳየችው ።

ነገር ፣ ግን ፣ የእናቱ ፣ ነፍስ ፣ በርግብ ፣ ተመስላ ፣ እየመጣች ፣ "ልጄ ፣ ወርቁ ፣ እኅትህ ፣ ምን ፣ ትልሃለች" ፣ ትለው ፣ ዝመር ፤ እሱም ፣ የደረሰበ ትን ፣ ግፍ ፣ ሁሉ ፣ ከሙቀጫ ፣ ጋራ ፣ ታገል ፣ ትለኛለች ፣ እያለ ፣ . . . . . በሙሉ ፣ ከነገራት ፣ በኋላ ፣ መቼም ፣ ሁል ፣ ጊዜ ፣ በረኃብ ፣ ከመጠበስ ፣ በቀር ፣ ምግብ ፣ አያገኝም ፣ ነበርና ፣ ከቤታቸው ፣ እጠገብ ፣ ያለውን ፣ የሾላ ፣ ፍሬ ፣ በክንፏ ፣ ርግፍ ፣ ርግፍ ፣ አድርጋለት ፣ ትሄዳለች ።

እኅቱም ፣ ይህች ፣ ርግብ ፣ ሁል ፣ ጊዜ ፣ እዚህ ፣ እዛፍ ፣ ላይ ፣ ምን ፣ ትፈልጋለች ፣ በማለት ፣ ስትጠራጠር ፣ ቄይታ ፣ አንድ ፣ ቀን ፣ ተደብቃ ፣ ስትመለከት ፣ እንደ ፣ ልማዷ ፣ "ልጄ ፣ ወርቁ ፣ እኅትህ ፣ ምን ፣ ትልሃለች" ፣

ስትለው ፣ ሰማች ፤ ወዲያው ፣ ልጁን ፣ ጠርታ ፣ ብትመረምረው ፣ ባሏ ፣ የተ ሰጠኸውን ፣ ሥራ ፣ መሥራት ፣ ብቻ ፣ እንጂ ፣ መናገር ፣ የለብህም ፣ ብሎ ፣ አስጠንቅቆት ፣ ነበርና ፣ ብትለው ፣ ብትሠራው ፣ ቃል ፣ የማይመልስላት ፣ ሆነ ።

በዚህ ፣ ጊዜ ፣ የምታደርገውን ፣ አጥታ ፣ ግራ ፣ ቢገባት ፣ ወደ ፣ አንድ ፣ አስተዋይ ፣ ዘንድ ፣ ሄደችና ፣ ጠየቀች ። ሰውዬውም ፣ በወን ድሟ ፣ ላይ ፣ ያለውን ፣ ምልክት ፣ ታውቂያለሽን ፣ ብሎ ፣ ጠይቆ ፤ በጥ ርሱ ፣ ላይ ፣ ወርቅ ፣ ያለበት ፣ መሆኑን ፣ ከተረዳ ፣ በኋላ ፣ እንዲህ ፣ ሲል ፣ መከራት ። አሁን ፣ እንደ ፣ ገባሽ ፣ ተልባ ፣ በምትቄሊበት ፣ ጊዜ ፣ ልጆቹን ፣ ሁሉ ፣ ሰብስቢና ፣ እሱንም ፣ አጠገብሽ ፣ እንዲቀመጥ ፣ አድር ጊው ። መቼም ፣ ተልባው ፣ መንጣጣቱና ፣ ከፊትሽ ፣ ላይ ፣ ማረፉ ፣ ስለ ማይቀር ፤ በዚያ ፣ ጊዜ ፣ ከት ፣ ብለሽ ፣ ሣቂ ፤ ያን ፣ ጊዜ ፣ ልጆቹ ፣ ሁሉ ፣ ስለሚሥቁ ፣ እሱም ፣ አብሮ ፣ መሣቁ ፣ እይቀርምና ፣ በእንደዚህ ፣ ያለ ፣ ዘዴ ፣ ወንድምሽ ፣ መሆኑን ፣ አለመሆኑን ፣ ምልክቱን ፣ በማየት ፣ ለማወቅ ፣ ትችያለሽ ፣ አሳት ።

ሴቲቱም ፣ እንደ ፣ ተባለችው ፣ አድርጋ ፣ ከት ፣ ብላ ፣ መዝመሪያ ፣ እሷ ፣ ብትሥቅ ፣ እዚያ ፣ ያሉት ፣ ሁሉ ፣ በሙሉ ፣ ሲሥቁ ፣ በዚህ ፣ ጊዜ ፣ መቼም ፣ ምንም ፣ ቢቸገሩ ፣ ጥርስ ፣ አይከደንምና ፣ ፈገግ ፣ ብሎ ፣ ጥር ሱን ፣ ብልጭ ፣ አደረገ ።

ወዲያው ፣ ፊቱን ፣ ብታጥበው ፣ ጠለሸቱ ፣ ስለ ፣ ለቀቀ ፣ የዱሮ ፣ መልኩ ፣ በመታየቱ ፣ በርግጥ ፣ ወንድሟ ፣ መሆኑን ፣ ተረዳች ። ወንድሟ ፣ መሆኑን ፣ ባለማወቅ ፣ በሱ ፣ ላይ ፣ ባደረገችው ፣ ግፍ ፣ ሁሉ ፣ ምርር ፣ ብላ ፣ አልቅሳ ፤ ባሏ ፣ በሠራው ፣ በደል ፣ ተናደደችና ፣ እሱን ፣ ለመግደል ፣ ቀሩጥ ፣ አሳብ ፣ አደረገች ።

ይህም ፣ ሲሆን ፣ ባሏ ፣ አልነበረም ። ከዚያ ፣ በኋላ ፣ በቤቱ ፣ ውስጥ ፣ አራት ፣ ጦር ፣ ስለቱን ፣ ማለት ፣ ሹሉን ፣ ወደ ፣ ላይ ፣ አድርጋ ፣ ተክላ ፣ በጉድጓዱ ፣ አፍ ፣ ላይ ፣ ቀጭበት ፣ አንጥፋ ፣ ባሏ ፣ ከሄደበት ፣ አገር ፣ ሲመጣ ፣ ከዘጋጀችለት ፣ ምንጣፍ ፣ እንዲቀመጥ ፣ ዕቃውን ፣ ተቀብላ ፣ ከቀጭበቱ ፣ ላይ ፣ ዐረፍ ፣ በል ፣ አለችው ። እሱም ፣ ደክሞት ፣ ስለ ፣ ነበር ፣ ቀጭ ፣ ሲል ፣ ወርዶ ፣ ከጦሩ ፣ ላይ ፣ ስለ ፣ ወደቀ ፣ አካላቱ ፣ ተሸረከከተ ። በለ ፣ ቤቱም ፣ ወዲያው ፣ የፈላ ፣ ውሃ ፣ በእናቱ ፣ ላይ ፣ ደጋግማ ፣ ገለበጠችበ ፣ ትና ፣ ሞተ ፣ ይባላል ።

❊ ስለ ፡ ቁም ፡ ነገርና ፡ ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ሳቅር ፡ ማመንታት ፡ በሌለበት ፡ ቁራጥነት ፡ ሕይወትን ፡ ለሞት ፡ አሳልፎ ፡ መስጠት ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ሞያ ፡ ነው ።

አይታወቅብኝም ፡ ብሎ ፡ ግፍ ፡ ወይም ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ መሥራት ፡ ጊዜው ፡ ይዘግይ ፡ እንጂ ፡ በግፍ ፡ ሠሪው ፡ ላይ ፡ የበለጠ ፡ ጉዳት ፡ የሚደርስ ፡ መሆኑን ፡ መዘንጋት ፡ አይገባም ።

"ትንሽ ፡ ሥጋ ፡ እንደ ፡ መርፌ ፡ ትወጋ" ፡ የሚባለውም ፡ ስለዚህ ፡ ነው ።

ማውጫ ፡ ገጽ ፡

መግቢያ ፡ 5
ስንዝሮ ፡ 9
ስለ ፡ አንዲት ፡ የቆቅ ፡ ልጅ ፡ በወጥመድ ፡ መያዝ ፡ 18
ስለ ፡ አንድ ፡ አባት ፡ ኑዛዜ ፡ 19
አንድ ፡ መነኩሴና ፡ ንብር ፡ 25
ስለ ፡ አንዲት ፡ ገበያተኛ ፡ ሴት ፡ 27
የሰው ፡ ገንዘብ ፡ የወሰዱና ፡ ሰው ፡ በግፍ ፡ የገደሉ ፡ ወንበዴዎች ፡ . 30
ያንድ ፡ ሽማግሌ ፡ ምርቃት ፡ 33
ያንድ ፡ ዝሆብ ፡ ሞት ፡ 36
ወታደርና ፡ ተማሪ ፡ 38
ባልና ፡ ሚስትን ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እንዳታለላቸው ፡ 40
ያዝሆብ ፡ ልጅ ፡ ሞት ፡ 43
ሚስቱ ፡ የጐሸ ፡ ወሬት ፡ አምጣ ፡ ስላለችው ፡ ሰው ፡ 45
ሁለት ፡ ሌቦች ፡ 48
አንድ ፡ በሬ ፡ ስለ ፡ ነበራቸው ፡ ቂሎች ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ 50
አንድ ፡ ሚስቱ ፡ የተጫወተችበት ፡ ሰው ፡ 53
የባልና ፡ ሚስት ፡ በተስቦ ፡ መታመም ፡ 56
ያንድ ፡ ድኻ ፡ ሰው ፡ ኑዛዜ ፡ 58
ሦስት ፡ ቂል ፡ ወንድማማቾች ፡ 62
የአሳትና ፡ ውሃ ፡ በሬ ፡ መግዛት ፡ 63
የዝንጀሮ ፡ ገደል ፡ መግባት ፡ 64
ድኻ ፡ ጥጃ ፡ 66
አንበሳና ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ 72
የዶሮ ፡ ዘመቻ ፡ 74

ያውሬ ፡ ሁሉ ፡ ገበያ ፡ 76
የኾቦብና ፡ የነብር ፡ ንስሓ ፡ አባት ፡ መያዝ ፡ 80
አንዲት ፡ ባሏን ፡ የናቀች ፡ ሴት ፡ 86
አንበሳና ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ 88
ደሦስት ፡ ሌቦች ፡ ምክር ፡ 91
ሴቶች ፡ ሹመት ፡ እንደ ፡ ለመኑ ፡ 95
በነውር ፡ የተሰደዱ ፡ ሦስት ፡ ጓደኞች ፡ 96
የኾቦብና ፡ የዝንጀሮ ፡ መጣላት ፡ 102
የአራዊት ፡ ለአንበሳ ፡ ለሴነት ፡ ማደር ፡ 105
ስለ ፡ አንዲት ፡ የጌታ ፡ ልጅ ፡ መፅነስ ፡ 114
ስለ ፡ አንድ ፡ ታማኝ ፡ አሽከር ፡ 117
ሁለት ፡ አታላዮች ፡ 122
ስለ ፡ አንድ ፡ ሽማግሌ ፡ ምርቃት ፡ 128
ስለ ፡ ዘጠኝ ፡ ቂሎች ፡ ወንድማማቾች ፡ 131
ስለ ፡ ሦስት ፡ ሴቶች ፡ 133
አግዜር ፡ ሞትና ፡ ክረምት ፡ ማደሪያ ፡ እንደ ፡ ለመኑ ፡ 138
ስለ ፡ አንድ ፡ መሀይምን ፡ መነኩሴ ፡ ጸሎት ፡ 140
የመልክም ፡ ሥራ ፡ ዋጋ ፡ 142
ስለ ፡ አንድ ፡ መንገድ ፡ የሄደ ፡ ሰው ፡ 145
ስለ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ መተነኳኰል ፡ 146
ስለ ፡ ሁለት ፡ ቂሎች ፡ ልጅ ፡ መውለድ ፡ 151
የሚስት ፡ ወይነቷ ፡ ሦስት ፡ ነው ፡ 156
ወላድ ፡ እንደ ፡ ተመክችና ፡ መክንን ፡ እንደ ፡ ናቀች ፡ 161
ስለ ፡ አንድ ፡ ንጉሥ ፡ የዘመን ፡ ሁናቴ ፡ መጠየቅ ፡ 164
ስለ ፡ አንዲት ፡ ልጃገረድ ፡ መታጨት ፡ 170

